ተስፋዬ ገብረአብ

የጋዜጠኛው ማስታወሻ



SUNNYSIDE PUBLISHERS
PRETORIA, SOUTH AFRICA

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!



©ተስፋዬ ገብረአብ – 2000
የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።
First published — 2008

Author photo: Micktece
© Cover Idea: A. Harboy
©TG Habtezion — 2008
All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, in any form, or by any means without the prior written permission of the publisher.

ስለዚህ መፅሃፍ ያላችሁን አስተያየት በሚከተሉት የኢ - ሜይል አድራሻ ብትልኩ ደራሲው በደስታ ይቀበላል!
ttgebreab@gmail.com
ttgebreab@yahoo.com
መፅሃፉን ለማከፋፈል የምትሹ የሚከተለውን blog ይጎብኙ፣
www.tgindex.blogspot.com

ምስጋና (Acknowledgment)

ይህ መፅሃፍ በተሳካ ሁኔታ ይጠናቀቅ ዘንድ ድጋፍ ላደረጉልኝ ወዳጆቼ ሁሉ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። አበበ እና A(k) እንዲሁም ይመር፣ ያለናንተ ድጋፍ ይህ መፅሃፍ መታተም ባልቻለ ነበር። ወይዘሮ ምስጋናና ሲኖዳ ጊዜያችሁን በከባዱ ለኔ ሰውታችሁዋልና አመሰግናለሁ። በተለይም ደግሞ A. E. ጠቀም ያለ ምስጋና ይገባሃል። Joseph T. ሰላማዊት፤ አማኑኤልና ሰሚር፤ እንዲሁም H.F, Mesfen G. ለሰጣችሁኝ የሃሳብና የሞራል ድጋፍ ባለውለታዎቼ ናችሁ። ቢኒያም ብርሃነ ባለህበት የከበረ ምስጋናዬ ይድረስህ። ለማላዊያዊው Artist Tathokoza khoza እና Trevor nideoo, AJ, Jonathan, በሃይሉ DJ F., Tara G. እንዲሁም መፅሃፉን በማንበብ ጠቃሚ አስተያየት ለሰጣችሁኝ ሁሉ የክብር ምስጋና ይድረሳችሁ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- ማ ው ጫ -

- የጋዜጠኛው ማስታወሻ.....5

ክፍል አንድ

1. ስራ ፍለጋ 9
2. መዝሙረ ዋልዋ..... 18
3. አንድ አገር - ሁለት አለም!..... 33
4. በረከት ስምኦን..... 66
5. በደም የተገኘ ዙፋን..... 88
6. አስቸጋሪ የስራ ቀናት..... 94
7. የማልረሳት ጋዜጠኛ..... 102
8. የልጅነት መምህራን..... 111
9. ወንድሙ ጨበሮ..... 128
10. የአብዱልመጂድ ቁጣ..... 132
11. የዘመናችን አንበሶች..... 136
12. የቁንድዶ ፈረሶች..... 153
13. እነ መለስ! እነተወልደ!..... 165
14. ክንፈ! የፀጥታው ሹም..... 193
15. የመጨረሻው ምሽት..... 209
16. የማይጣላ ህሊና..... 222

ክፍል ሁለት

17. የባከኑ የኛ ሰዎች..... 229
18. የአፍሪቃን ድንበር ስናቋርጥ..... 247
19. ብጫቂ ወረቀቶች..... 269

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

20. የአሰፋ ማሞ ጩቤዎች..... 291
21. የጋዜጠኛው ደብዳቤ..... 295
22. ሲያትል ደህና ሁኝ.....299
23. ኢብሳ አልሞተም!..... 313
24. ደራራ ለምን ተገደለ? 328
25. ኢትዮጵያዊ ወታደር..... 334
26. አንድ ምሽት ከስዬ ጋር..... 339
27. መነኩሴው ቀበሮ..... 342
28. ፅጌረዳን ዳግም አየሁዋት..... 352
29. ሃገር ግን ትኖራለች!..... 370
30. መንገዱ ወዴት ያደርሳል?..... 380
31. ጉዞ ወደ እውቀት..... 387

- ድህረ - ታሪክ..... 397

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የጋዜጠኛው ማስታወሻ

(እንደ መግቢያ)

የቢሾፍቱ ልጅ የሆነ አንድ ዜጋ ይህቺን መፅሃፍ ሊፅፉት ሲጀምር ለራሱ ታማኝ ለመሆን ከህሊናው ጋር ብርቱ ትግል አድርጎአል። በመሆኑም ገልጣችሁ ማንበብ ስትጀምሩ ጥቂትም ቢሆን የሚያስደምሙ ትረካዎችን አታጡበትም። በዚህች መፅሃፍ ውስጥ የሰፈሩት ትረካዎች "ግለ - ታሪክ" አይደሉም። የአንድ ጋዜጠኛ እውነተኛ እለታዊ ገጠመኞች ብቻ ናቸው።

ያ ሰው እኔ ነኝ!

"አንድ በቂ ምክንያት ከሃምሳ ሰበቦች የተሻለ ነው" የሚለውን ብሂል እንደ መርህ ይዤ ሁሉን እንደ ወረደ ተርኬላችኋለሁ። በየትረካው ውስጥ ያልተሟሉ መረጃዎች፣ ሚስጥራቸው ባግባቡ ያልተብራራ ክስተቶች ሊያጋጥሟችሁ ይችላሉ። በጊዜ መርዘም ምክንያትም መርሳት ሊኖር ስለሚችል፣ ቀናት ላይ የተሳሳተ ነገር ቢገጥማችሁ እያስተካከላችሁ ታነቡት ዘንድ ከይቅርታ ጋር እጠይቃለሁ።

በዚህ መፅሃፍ ባልተለመደ ሁኔታ እውነተኛ ስማችሁን ለተጠቀምኩ ሁሉ ባለማስፈቀዴ ይቅርታ እየጠየቅሁ፤ አትቀየሙኝም ብዬ በመገመቴ ደግሞ አመሰግናለሁ። ቀለል አድርጋችሁ ካነበባችሁት በትረካው ይበልጥ እንደምትዝናኑ እምነቴ ነው። በዚህ መፅሃፍ ስማቸው ለተጠቀሰ በህይወት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የሌሉ ሰዎች ታማኝ ለመሆን በእጅጉ ተጠንቅቄያለሁ። ስሜታዊ ሁኔታዎችን ለማስወገድ ስል ደግሞ አንዳንድ ትረካዎች ላይ ስሞችንና ቦታዎችን ለዋውጬ መጠቀሙን መርጫለሁ። ያልተረጋገጡ መረጃዎችን ላለማካተት ብርቱ ጥረት በማድረጌ፣ ከመቶ አምሳ ገፆች በላይ ቆርጬ ጥያለሁ። የአንድ ስህተት መገኘት የሙሉ መፅሃፌን ተአማኒነት እንዳያጓድልብኝ በሚል ስጋት ማጣሪያ የሚያሻቸውን አሳድሬያቸዋለሁ። ምናልባትም ሌላ ሙሉ መፅሃፍ ይወጣቸዋል። በሁለተኛው ክፍል፣ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" ለመገናኘት እንበቃለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ቢሾፍቱ የተወለድሁ ዜጋ እንደመሆኔ፣ የህወሃት አባልና ካድሬ ሆኜ ከአስር አመታት በላይ እንደመስራቴ፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታና የህወሃት - ኢህአዴግ ጉዳይ በቀጥታ ይመለከተኛል። በአናቱ የጋዜጠኝነት የሙያ ግዴታዬ ይፋ አደርግ ዘንድ ያዘዘኝን መረጃዎች በዚህ መፅሃፍ ያካተትኩ በመሆኑ፣ ትረካዎቹን በትእግስት ትመረምሯቸው ዘንድ እጋብዛለሁ። በጋዜጠኝነት ሙያ ከኢህአዴግ ጋር በሰራሁበት ወቅት ያወቅኋቸውን ምስጢሮች ሁሉ ግን እዚህ አላካተትኩም። የሙያውን ስነምግባር ለመጠበቅ ስል ያላተምኳቸው መረጃዎች ከጥቂት በላይ ናቸው። የጠነከረ ሂስ የሰነዘርኩባችሁ የቀድሞ ጓዶቼ ቆዳችሁን አጠንክራችሁ፣ ከቂምና ከጥላቻ በፀዳ መንፈስ ታነቡኝ ዘንድ ምኞቴ ነው።

የእያንዳንዱ ሰው የህይወት መንገድ ላይ ጉዞ አንድ ሙሉ መፅሃፍ እንደሚወጣው ይታመናል። እኔም ገጠመኞቼን ቁራጭ መፅሃፍ ለማድረግ ሞክሬያለሁ። ተሳክቶልኝ ይሆን!?

ተስፋዬ ገብረአብ
ፕሪቶሪያ - 2000

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ክፍል አንድ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 1 -
ሰራ ፍለጋ

ከምድሪቱ በላይ - ሰማዩን አካፍሎ፣
አየሁት ደመናን - ከታች ተንገዋሎ፣
ለጊዜው አየሁት - ባየር ተቀምጬ፣
ተመልሼ እስካየው - ከታች አንጋጥጬ፤

(ግጥም - ትእግስት ሀሩይ)

በክረምቱ ወራት ከደብረዘይት ወደ አዲስ አበባ የተጓዝኩት እንደተለመደው ለስራ ፍለጋ ሲሆን፤ አመቱም 1979 ነበር። አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በሪፖርተርነት ለመቀጠር ማመልከቻ አስገብቼ ስለነበር እነሆ በተስፋ አዲስ አበባ ገብቻለሁ።

የከሰአት በሁዋላው የስራ ሰአት እስኪደርስ አራት ኪሎ ከሚገኘው የኩራዝ አሳታሚ መደብር ገብቼ መፃህፍትን እመለከት ጀመር። ኪሴ ውስጥ ያለው አምስት ብር ብቻ ነውና መፅሃፍ እንደማልገዛ ግልፅ ነው። ዳሩ ግን ማየቱ ብቻ ተስፋ ስለነበር አዲስ ለገቢያ የቀረቡትን መፃህፍት እያገላበጥኩ በመዝናናት ላይ ነበርኩ። አጠገቤ ቆሞ እንደኔው መፅሃፍትን በመነካካት የሚደሰት ሌላ ወጣት በማየቴ እንደዋዛ ወሬ ጀመርኩ፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ገበየሁ አየለ የህፃናት መፅሃፍ ይፅፋል እንዴ ለካ?”

“ይፅፋል!” ሲል አፃነቀ። “...በርግጥ እኔም በቅርቡ ነው ያወቅሁት”

ወጣቱ በሃያዎቹ ማብቂያ ግድም ሊሆን እንደሚችል የገመትኩ ሲሆን፣ ወሬውን እኔ ከከፈትኩ በሁዋላ ወዲያውኑ ጓደኛው አድርጎኝ ስለ ራሱ ይተርክልኝ ጀመር፣

“አዲስ ዘመን ጋዜጣ ታነባለህ?”

“አነባለሁ”

“ተፈሪ አሰፋ - ከጉለሌ የሚል ስም አታውቅም?”

“አውቃለሁ”

“ተፈሪ ማለት እኔ ነኝ!”

ከመደሰቴና ከመደነቄም ወዲያውኑ አከበርኩት። ከመደብሩ ከወጣን በሁዋላ እያወራን ቁልቁል አዘገምን። እኔም ድርሰት መፃፍ እንደምወድ ነገርኩት።

“ከዚህ በፊት ምን ታትሞልሃል?” ሲል ጠየቀኝ።

የአጫጭር ልቦለዶች መድበል ኩራዝ አሳታሚ አስገብቼ ምላሽ እየጠበቅሁ እንደሆነ፤ በሬድዮ መጣጥፍ እንደተነበበልኝ፤ “የስለት ልጅ” በሚል ርእስ አጭር ልቦለድ ድርሰት ፅፌ ጌታቸው ለማ ለተባለ የአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ አቅርቤም እንደነበርና፣ “አብዮት በሚካሄድበት በዚህ ወቅት ስለ ‘ስለት ልጅ‘ መፃፍ ተቀባይነት የለውም” ብሎ እንዳባረረኝ አጫወትኩት።

“ወዴት እየሄድክ ነው አሁን?” ሲል ጠየቀኝ።

“ወደ ፕሬስ መምሪያ”

”እኔም ወደ ፒያሳ ነው የምሄደው” ካለ በሁዋላ ቁልቁል አብረን አዘገምን።

“...በቅርቡ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ አራሚነት ለመቀጠር ተስፋ አግኝቻለሁ” አለኝ።

በአጋጣሚው በመደነቅ እኔም የራሴን ነገርኩት፣

“እኔም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በሪፖርተርነት ለመቀጠር ማመልከቻ አስገብቼያለሁ”

ተፈሪ በአትኩሮት ካጤነኝ በሁዋላ፣

“የሚረዳህ ሰው አለ?” ሲል ጠየቀኝ።

“ማንም የለም” አልኩ በስጋት “...ከብርሃኑ ዘሪሁን ጋር እንተዋወቅ ነበር። እየሞከረልኝ ነበር። ግን ያው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደምታውቀው አረፈ። ሌላ የማውቀው ሰው ስለሌለ ዝም ብዬ በራሴው እየሞከርኩ ነው...”

ተፈሪ ወሽመጥ በሚበጥሱ ቃላት ተስፋ አስቆረጠኝ፣

“...አትልፋ!” አለኝ ቃል በቃል “...ሰው የሌለው ሰው የፕሬስ መምሪያን ደጃፍ አይረግጥም። እኔ እንኳ ይህን ሁሉ ፅሁፍ አዲስ ዘመን ላይ እየፃፍኩ ሊቀጥሩኝ አልቻሉም። ደጅ መጥናት ከጀመርኩ ሁለት አመት ሆነኝ። አልቻልኩም። ሰው ስለሌለኝ እንጂ እኔ ከአዲስ ዘመን ሪፖርተሮች አላንስም። እዚህ መስሪያ ቤት ለመቀጠር ጎጃሜ መሆን አለብህ፤ አለያም ደግሞ ወፍራም ዘመድ ያስፈልግሃል”

“ጎጃሜ ለምን?” አልኩ ማመን እያቃተኝ።

“ሙሉጌታ ሉሌን አታውቀውም?”

“አላውቀውም፤ ማነው?”

“የፕሬስ መምሪያ ሃላፊው ነዋ! እሱም ራሱ የታወቀ የቀድሞ ጋዜጠኛ ነው። ሆኖም የጎጃም ነገር ትጎትተዋለች። ፕሬስ በጎጃም ሰንሰለት የተያያዘ ቤት ነው። ችሎታ የሌላቸውን ሰዎች ጎጃሜ ስለሆኑ ብቻ ቀጥሮአቸዋል። እነ ዋካ ይርሳው፣ እነ አያሌው....” እያለ የማላቃቸውን ስሞች ይደረድርልኝ ጀመር።

ተፈሪ አሰፋ አያያዘና ቀጠለ፣

“አሁን ግን ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የምትሰራ ዘመዴ ሙሉጌታ ሉሌን ቢሮው ገብታ ለመነችው። በዚህ ወር መጨረሻ ልቀጠር ቃል ተገብቶልኛል.”

የነበረኝ ተስፋ ሁሉ ድምጥማጡ ጠፋ። ክፉኛ አዘንኩ። ተፈሪ ተሰናብቶኝ ወደ ፒያሳ አቅጣጫ ሲያመራ፣ እኔ ወደ ብርሃንና ሰላም ህንፃ ገባሁ። ማመልከቻዬን ወዳስገባሁበት ሰባተኛ ፎቅ ያመራሁት ተስፋ ባጣ ስሜት ነበር፤ ማመልከቻዬን ቀደም ሲል ሙሉጌታ ሉሌ ተብሎ እንደሚጠራ ከማላውቀው መምሪያ ሃላፊ ቢሮ ነበርና ያስገባሁት፤ ገብቼ ፀሃፊዋን ጠየቅሁዋት። ሂሩት የተባለችው ፀሃፊ ገፅታዬን ረስታው ኖሮ፣

“ምን ነበር ጉዳይህ?” ስትል በትህትና ጠየቀችኝ።

“ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሪፖርተርነት ለመቀጠር እዚህ ማመልከቻ አስገብቼ ነበር”

“መቼ ነው ያስገባኸው?”

“ወር አለፈው”

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ጥቂት አሰበችና፣

“ለመምሪያ ሃላፊው አስገብቼልህ ነበር መሰለኝ፤ ምላሽ ግን አላገኘሁም”

“መቼ ነው ምላሽ ላገኝ የምችለው?”

“እሱን አላውቅም። እየተመላለስክ ጠይቅ”

“ከደብረዘይት ስለሆነ የምመላለሰው የትራንስፖርት ገንዘብ ችግር አለብኝ። የማይሆን ከሆነ አሁኑኑ ምላሽ ባገኝ ደስ ይለኝ ነበር” አልኩ፤ ስለ ጎጃም ሰንሰለት እያሰላሰልኩ።

“እንግዲህ እኔ ምን ልረዳህ እችላለሁ?”

እንዳዘንችልኝ ከገፅታዋ ተረዳሁ። በተለይ የትራንስፖርት ገንዘብ ችግር ጉዳይ ሳነሳ ትክዝና ጭንቅ አለች። አመስግኜያት የሙሉጌታ ሉሌን ቢሮ ለቅቄ ወጣሁ።

...አሳንሰሩ ወደ ምድር ይዞኝ ወረደ።

ከህንፃው ዋና መግቢያ በር ላይ ያስያዝኩትን የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት ተቀብዬ በአውቶብስ ወደ ለጋህር ሄድኩ። ከለጋህር ወደ ደብረዘይት አቀናሁ። የነበርኩበት የኑሮ መክበድ ተደማምሮ፤ የመረረ ቂም ይዤ ነበር። ከዚህ ቀደም የማላውቀው አይነት ጥላቻ ልቤ ውስጥ እንደደነደነ ይታወቀኛል። ፖለቲካ አላውቅም። ልቤ በጥላቻ አራሙቻ መሞላቱን ግን አውቅ ነበር። በተለይም ተፈሪ አሰፋ ያጫወተኝ የጎጃም ሰንሰለት ጉዳይ የጥላቻ ስሜቴን እንዳባባሰው ይታወቀኛል። በርግጥ ደካማነት ነበር የሚሰማኝ። ብርሃንና ሰላም ሰባተኛ ፎቅ ላይ የገነነው ስልጣን የማይደፈር እንደሆነ ርግጠኛ ነበርኩ። ብርሃኑ ዘርይሁንና ከበደ አኒሳ የተባሉት ጋዜጠኞች በዚያን ወቅት ለኔ ችሎታ ጥሩ አመለካከት ስለነበራቸውና ብርሃኑ ዘርይሁንም ‘አያያዝህ ጥሩ ነው’ ይለኝ ስለነበር፤ ነቀፋዬ በቢሮክራሲው ላይ ነበር።

የሆነው ሆኖ ከዚያን እለት በሁዋላ ወደ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ግቢ አልተመለስኩም። ነቢይ አይደለሁምና በአጭር ጊዜ ውስጥ የሙሉጌታ ሉሌን ስልጣንና ቢሮ እረከባለሁ ብዬ ልተነብይ ግን አልቻልኩም። የሆነው ግን እንዲያ ነበር...

* * *

የተረኩላችሁ ታሪክ በተፈፀመ በአራተኛው አመት፤

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በ1983 የክረምቱ ወራት ማገባደጃ ላይ ከጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ የተፃፈ ደብዳቤ እጄ ላይ ገባ። ደብዳቤው የፕሬስ መምሪያ ሃላፊ ሆኜ መሾሜን የሚገልፅ ነበር።

በአንድ ነጭ ላንድክሩዘር ተጭኜ ወደ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ግቢ ገባሁ። ሾፌሩን ወደመጣበት አሰናብቼ ወደ ሰባተኛ ፎቅ ለመውጣት አሳንሰሩን ያዝኩ። በተስፋ ማጣትና በሃዘን ተውጬ በዚህ አሳንሰር ቁልቁል ከወረድኩ ልክ አራት አመቱ!

ክረምት ነበር ያኔም።

አሳንሰሩ ሰባተኛ ፎቅ ላይ ቆመ። መንገዱን አውቀዋለሁ! በዝግታ አዘገምኩ። የፕሬስ መምሪያ ሃላፊ! ሙሉጌታ ሉሌ! ሂሩት የተባለች ፀሃፊ! ምላሽ ያላገኘ ማመልከቻ...

ጭንቅላቴ ግሎአል! ማመንም ተቸግሬያለሁ።

ከአራት አመታት በፊት እዚህ መስሪያ ቤት ስራ ለመቀጠር ደጅ እየጠናሁ ነበር። ለራሴውም ግራ በሆነብኝ ፍጥነት በሃረር ወታደራዊ ሳይንስና ፖለቲካ ሰልጥኜ፤ የአንድ ወር ደሞዝ ሳልወስድ በጦርነት ተካፍዬና ቆስዬ፤ እጄን ለወያኔ ሰጥቼ፤ ባጭር ጊዜ ውስጥ ከኢህአዴግ የፕሮፓጋንዳ ታጋይ ካድሬዎች አንዱ ሆኜ፤ ደርግ ወድቆ፤ ይሽው ማመልከቻ ካስገባሁበት ቢሮ ተሾምኩ። ሰኞ ተረገዝኩ - ማክሰኞ ተወለድኩ - የሚለውን የስንዝሮ ታሪክ በልቤ እየዘመርኩ ወደ መምሪያ ሃላፊው ቢሮ ገባሁ!

ሂሩት ሻይ እየጠጣች ነበር። እኔ ስገባ ቀና አለች፣

"ጤና ይስጥልኝ ወይዘሮ ሂሩት"

"ጤና ይስጥልኝ"

"በአቶ ሙሉጌታ ሉሌ ቦታ እንድሰራ ታዝዤ ነው የመጣሁት!"

ሂሩት ከመቀመጫዋ ተነስታ በአክብሮት ተቀበለችኝ። እንዳላወቀችኝ ርግጠኛ ነበርኩ። ከወያኔ ጋር ባሳለፍኩት የትግል ወቅት ጢሜ ፊቴን ሞልቶታል። ከሰላሳ በላይ እንጂ እኔን የ 23 አመት ወጣት ነው ብሎ የሚገምት ከቶ የለም። ሹመቴን ያፀደቁት ባለስልጣናት እንኳ ስለ እድሜዬ የተገነዘቡ አይመስለኝም።

"አቶ መዝሙር ደውሎ እንደምትመጣ ነግሮኝ ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንኳን ደህና መጣህ" ስትል በሞቀ ፈገግታ አቀባበል አደረገችልኝ። መዝሙር በወቅቱ የኢህዴን ማእከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረ ሲሆን፤ የዜና አገልግሎት መምሪያን እንዲመራ ተመድቦ ነበር።

ሂሩትን በአንክሮ እያስተዋልኳት ጥቂት ቆየሁ።

ከአራት አመታት በፊት ላስገባሁት ማመልከቻ ገና ምላሽ አላገኘሁም። የጠየቅሁት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሪፖርተር ለመሆን ነበር። አሁንም ፍላጎቴ ሪፖርተር መሆን ነው። ሪፖርተርነቱን ከለከሉኝ። ስለዚህ መምሪያ ሃላፊነቱን በጉልበት ነጥቄ እየወሰድኩ ነው።

ሂሩት አላወቀችኝም።

"ልንገራት ወይስ አልንገራት?" ስል ከራሴ ጋር ተሟገትኩ። "የለም! ሂሩት ባታውቅ ይሻላታል" ስል ወሰንኩ። በርግጥ ከጊዜ በሁዋላ ማወቋ እንደማይቀር አውቃለሁ። ያወቀች ጊዜ በራስዋ ጊዜ ትወቅ። እስከዚያው ግን ባለመተዋወቅ አብረን መሰንበት እንደሚሻለን አመንኩ።

ሂሩት በክብር እየመራች ወደ ሙሉጌታ ሉሌ ቢሮ ይዛኝ ገባች። እጅግ ውብና ድንቅ ቢሮ ተቀበለኝ። ስልክ አደዋወሉን እንኳ አላውቅም ነበርና ሁሉንም ሂሩት አሳይታኝ ስታበቃ፤ ብቻዬን ተወችኝ። ሂሩት በሩን መለስ አድርጋ ከወጣች በሁዋላ ወደ መስኮቱ ተጠግቼ አዲስ አበባን በርቀት ቁልቁል አየሁዋት።

ምኞት አልተሰማኝም!

ስራው እንደሚከብደኝ አውቄያለሁ። ልምድና ችሎታ የለኝም። ታሪክና ስነፅሁፍ ማንበቤን እንደ ብቃት ቆጥሬ ልደላደል አልቻልኩም። ፍላጎቴም ይህ አልነበረም። ይህን ቦታ ተመኝቼው እንደማላውቅ ርግጠኛ ነኝ። ተገቢ ቦታዬን በመከልከሌ ግን ውጤቱ ይህ ሆነ። የሹመቱ ደብዳቤ በታምራት ከመፈረሙ በፊት ስልጣኑ ለኔ መሰጠቱን በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበረው በረከት ስምኦን በቃል ነግሮኝ ነበር። በዚያኑ እለት ቴሌቭዥን ከተመደበው ከአማረ አረጋዊ ጋር ቁጭ ብለን ስንጫወት፤ ስራውን እንደማልችለውና ቢቀርብኝ እንደሚሻል አማክሬው ነበር። አማረ ግን ተቃወመኝ። እኔ ስራውን ባልቀበል ሌላ የተሻለ ሊተካ የሚችል አለመኖሩን በመግለፅ አደፋፈረኝ፣

"ማናችንም ብንሆን ልምድ የለንም። በባለሙያዎች

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እየታገዝን የማረጋጋት ስራ ነው የምንሰራው" ሲል ነገረኝ።

መቸም ሙያና ባለሙያ እድሜ ልክ ያልተገናኙባት አገር ዜጎች ነንና፤ እየቀፈፈኝም ቢሆን እነሆ ከሙሉጌታ ሉሌ ወንበር ላይ ተቀምጫለሁ።

ከአራት አመታት በፊት ያን ህንፃ ለቅቄ ስወጣ በልቤ ቋጥሬው የነበረው ቂምና ጥላቻ አሁን አብሮኝ ስለመኖሩ ግን ርግጠኛ አልነበርኩም። በተቀላቀለ ስሜት ተውጬያለሁ። በሹመት ደስታና የችሎታ ማነስ በሚፈጥረው ፍርሃት ተውጬ አዲስ አበባን ቁልቁል አየሁዋት።

"አንቺ አገር ሆይ! እንደፍላጎታችንና እንደችሎታችን እንኖርና እንሰራ ዘንድ የምትፈቅጂልን መቼ ይሆን?"

መልስ ግን አልነበራትም። ምናልባት ለምንጊዜውም መልስ የሚኖራት አትመስልም! ዛሬም በርቀት ስደት ላይ ሆኜ እንደምታዘባት ከሆነ፤ ስቴሽንዋገን ላይ መፈናጠጥ የሚያሳብዳቸው ጨቅላዎች፤ አለያም የመታዘዝን ልምድ ብቻ ያካበቱ ባለሙያዎች እየተሾሙላት ነው።

* * *

እነሆ! የአዲስ ዘመን ጋዜጠኞችን በሙሉ ቢሮዬ ሰብስቤ የጠፈ ግምገማ እያደረግሁ ነው። ተፈሪ አሰፋን ወዲያውኑ ለየሁት። አልተለወጠም። ጥግ ላይ ተቀምጦ በአንክሮ እያየኝ ነበር።

ተፈሪ አሰፋ - ከጉለሌ!

አዲስ ተሿሚ እንደመሆኔ የጋዜጠኞችን ስም ስተዋወቅ 'ዋካ ይርሳው' የሚል ስም ሰማሁ። 'አያሌው' የሚልም ተከተለ። ሁለቱም ጎን ለጎን ተቀምጠዋል። ተፈሪ አሰፋ እነዚህን ስሞች እንደጠቀሰልኝ በፍፁም አልረሳሁትም። በግምገማ ላይ ታዲያ ዋካ ይርሳውና አያሌው እኔን በመቃወምና ሃይለ ቃል በመናገር ሲረብሹኝ አልተገረምኩም። በትእግስት አዳምጣቸው ነበር። ግምገማችንን በማጠናቀቅ ላይ ሳለን ተፈሪ አሰፋ እጁን አወጣ። በእልህ ይናገርም ያዘ፣

"ባለፈው ስርአት ፍትህ አልነበረም! አሁን ግን ፍትህ እንጠብቃለን! እኔ ለምሳሌ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አራሚ ነኝ። ሪፖርተር የመሆን ብቃት እንዳለኝ ግን ማንም ያውቃል"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተፈሪ የቻለውን ያህል ተናግሮ ሲያበቃ፣

"ተፈሪ... ሁሉንም አውቃለሁ!" አልኩት። አያያዝኩናም ቀጠልኩ "...ሌላው ቀርቶ አንተ እዚህ መስሪያ ቤት እንዴት እንደተቀጠርክ ጭምር አውቃለሁ...ዋካ ይርሳው ዛሬ ለምን እንዲህ እንደሚያስቸግርም መነሻ ምክንያቱን በዝርዝር አውቃለሁ! ያለፈውን ሁሉ በመተው ይህን መስሪያ ቤት እየተጋገዝን ማሳደግ ከቻልን መልካም ነው። ካልሆነ ግን እንቅፋቶችን ሁሉ አስወግዳለሁ!" አልኩ።

በንግግሬ መሃል "ያለፈውን ሁሉ በመተው" የሚለውን ሳስገባ በወቅቱ ከልቤ ነበር። እነ ዋካና ክፍሌ ሙላት ግን በቡድንና በተናጠል ማስቸገራቸውን ሲቀጥሉ፤ አንድ ባንድ እየለቀምኩ አስወገድኳቸው። ዋካ ይርሳውን አይሳኢታ በዝውውር ላኩት። አያሌውን አባረርኩት። የ"አድማስ" አምድ አዘጋጅ የነበረው ክፍሌ ሙላት 'ትግራይ እስክትለማ - ሌላው ሃገር ይድማ' የሚል ግጥም ፅፎ በማተሙ፤ ጋምቤላ በዝውውር ላክሁት። ተፈሪ አሰፋን ደግሞ ወደ ሪፖርተርነት አሳደግሁት። ስብሃት ገብረእግዚብሄር፣ የሺጥላ ኮከብ፣ ደረጀ ደስታና ደምሴ ፅጌ የተባሉትን ደራሲያንና ጋዜጠኞች ደግሞ ከያሉበት እያግባባሁ ወደ ፕሬስ መምሪያ አመጣሁዋቸው። ክፍሌ ሙላትና ዋካ ይርሳውን ጋምቤላና አይሳኢታ ስልካቸው ሄደው ስራቸውን ይሰራሉ ብዬ አስቤ ሳይሆን፤ በፈቃዳቸው ስራቸውን ይለቃሉ ብዬ በመገመቴ ነበር። ክፍሌ ሙላት ጋምቤላ ሄዶ ደሞዙን ከወሰደ በሁዋላ እንደገመትኩት አዲሳባ ተመልሶ የግሉን ጋዜጣ ከፈተ። ስለ ዋካ ይርሳው ግን በውነቱ ረስቼ ነበር።

ከነበርኩበት የፕሬስ መምሪያ ሃላፊነት ወደ ፋና ዴሞክራሲ አሳታሚ ከተዘዋወርኩ ከአራት አመታት በሁዋላ በኢጋማሚ ለስራ ጉዳይ አይሳኢታ ሄጄ ዋካ ይርሳውን እዚያ ሳገኘው ግን በድንጋጤ በድን ነበር የሆንኩት። የምናገረው ቃል ጠፋኝ። እኔ ሁለት ቀናት እንኳ ልቋቋመው ባልቻልኩት በረሃ ውስጥ ዋካ ይርሳው ለአመታት ተረስቶአል። ከዚያም አልፎ ዋካ ይርሳው ጥፋተኝነት እስኪሰማኝ ድረስ በወዳጅነት መንፈስ ነበር ያስተናገደኝ።

ወደ አዲስ አበባ ከተመለስኩ በሁዋላ በዋካ ይርሳው ጉዳይ በጣም ተረበሽኩ። በወቅቱ ዋካን ከአዲስ ዘመን ባልደረባነቱ ያነሳሁትን፤ ተፈሪ በነገረኝ የጎጃም ሰንሰለት ሳቢያ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አልነበረም። የፕሬስን ሃላፊነት ከተረከብኩ በሁዋላ የኢሲፓን ሰንሰለት እንጂ የጎጃም የሚባል ሰንሰለት አለመኖሩን አረጋግጫለሁ። ዋካን ራቅ አድርጌ የወረወርኩት ግን በየስብሰባው ስላስቸገረ ሊሆን ይችላል። ይልቁን አለችሎታ በመሾም እኛው ብሰን ተገኝተን ነበር።

በዚያው ሰሞን *"ዋካ ይርሳው እንዴት እንደ ተረሳ'* የሚል መጣጥፍ ፅፌ የነበረ ቢሆንም፤ ሳላትመው ቀረሁ። ዛሬ ዋካ ይርሳው የት እንዳለ አላውቅም። የዚህ መፅሃፍ ኮፒ እጁ ላይ እንዲገባ ግን ከልብ እመኛለሁ።

የፕሬስ መምሪያ ሃላፊ በነበርኩበት በዚያን ዘመን ብዙ ሾሜያለሁ፤ ብዙ ሽሬያለሁ። የያዝኩት ስልጣን አልፈቀደልኝም እንጂ እኔው ለራሴው የተመኘሁት ቦታ ግን የተፈሪ አሰፋን ቦታ ነበር። የአዲስ ዘመን ሪፖርተር!

የሆነው ሆኖ ለሁለት አመታት ያህል ያንን አስቸጋሪ መስሪያ ቤት እየተንገዳገድኩ ከመራሁ በሁዋላ ደርቤ እሰራው ወደ ነበረ አሳታሚ ድርጅት ተዛወርኩ።

ዛሬ ወያኔን ትቼ ኮብልዬ በስደት ላይ ነኝ። እንደ ማንኛውም ስደተኛ ለእለት ጉርስ፣ ለአመት ልብስ እየሰራሁ ሲሆን፤ እስካሁንም የምወደውን ተገቢ ስራ ገና አላገኘሁም።

ያለ እውቀቴ ቢሾፍቱ ከተወለድኩ ጀምሮ በፍላጎቴ ኖሬና ሰርቼ አላውቅም። 'በዚህች መከረኛ አገር ላይ በርግጥ በፍላጎቱና በችሎታው የሚኖርና የሚሰራ ስንቱ ይሆን?' እያልኩም አስባለሁ...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 2 -

መዝሙረ ዋልዋ

ጥቂቶች ቆራጦች - ያልተንበረከክነው፣
ነገ እልፍ እንሆናለን - ታሪክ ምስክር ነው፣

(ግጥም - ሀላፊ ዮሴፍ)

* * *

በላብህ በደምህ ቦክቶ - ካልተቋቋመ ግድግዳ፣
ቤት የሚሆን አይምሰልህ - የህልም ፕሮፓጋንዳ፤

(ግጥም - ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን)

ደርግ በወደቀ በ18ኛው ወር....

የኢህዴን ካድሬዎች ግምገማ ላይ በአጋጣሚ ተገኝቼ ነበር። አማርኛ ተናጋሪ በመሆኔ ምክንያትና ከስራ ባህርያችን አንፃር የነተፈራ ዋልዋ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ገብቼ ግምገማ እንድካፈል ታዘዝኩ።

ከመቶ በላይ ተሰብሳቢ በተካፈለበት በዚህ ግምገማ አብዛኞቻችን የመንግስት ባለስልጣናት ነበርን። ግምገማውን የሚመሩት ካድሬዎች ፍሬህይወት አያሌውና ሰለሞን ተቀባ የተባሉ ነባር ታጋዮች መሆናቸው ትዝ ይለኛል። እኔን ከመሰሉ ጥቂቶች በቀር ተሰብሳቢው ሁሉ አማራ ነበር። አማራ ያልሆኑ ትዝ የሚሉኝ ከኔ ሌላ ሁለት ነበሩ። የአዲሳባ አስተዳደር አመራር አባል የሆነው ጉራጌው ካሊድ አብዱራህማንና የኢትዮጵያ ሬድዮ የፕሮግራሞች ሃላፊ የነበረው ኦሮሞው ሱሌይማን ደደፎ...

ኢህዴኖች ድንገት የስብሰባውን አጀንዳ ገለበጡት!

ሰብሳቢዎቻችን የሚገቡበት እስኪጠፋቸው ድረስ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተንቀጠቀጡ። እጆች እየተቀሰሩ እንዲህ የሚሉ ብሶቶች ይንተከተኩ ጀመር፣

"ደርግን ለመጣል እኛም ታግለናል! ተሰውተናል! የስልጣን ክፍፍሉን እንደምናየው ግን ዋና ዋና ቦታዎች ሁሉ የተሰጡት ለህወሃት ነው። የመከላከያና የውጭ ጉዳይ ዋና ዋና ቦታዎች በሙሉ በህወሃት ተይዘዋል! ጉምሩክና ኢሚግሬሽን ለማስመሰል እንኳ ከኛ መካከል አንድ ሰው አልገባም! በመላው ሃገሪቱ የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎች ሁሉ ለህወሃት ተሰጡ! እኛ ተጣልን! የበይ ተመልካች ሆንን!"

አዳራሹ በጫጫታ ተናወጠ!

"ተጨማሪ!"

"እዚህ ተጨማሪ!"

"ዝም ስንል የማናውቅ አደረጋችሁን እንዴ!"

"አጥብቆ ዝምታ ለበግም አልበጃት - አስራሁለት ሆና አንድ ነብር ፈጃት! የሚሉት አይነት ሆነናል"

"ተፈራ ዋልዋ ይጠራ!"

"ተፈራ ዛሬውኑ ይጠራ!"

በዚያን ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢህዴን ታጋዮች ያልተለመደ ባህርይ መደነቅ ጀምሬ ነበር። "ለኢህዴኖች ያለኝ አመለካከት የተሳሳተ ነውን?" ስል ራሴን አጥብቄ ጠየቅሁ። አንዳንዶቹ እንባ ሲተናነቃቸው ስመለከት በርግጥም ያበጠው እንደሚፈነዳ ርግጠኛ ወደ መሆን አመራሁ። የአመፁ መጨረሻ የት ሊደርስ እንደሚችል ለማየትም ጓጓሁ። ሞገስ ሃብቱ የተባለው ጋዜጠኛና ገጣሚ ከጎኔ ተቀምጦአል። ሱሌይማንና ካሊድ ስሜቱ ባልታወቀ ሁኔታ አገጫቸውን እጃቸው ላይ አስደግፈው ያዳምጣሉ። እኔ እንደልማዴ የሚንተከተኩትን የካድሬዎችን ቃላት ማስታወሻ ደብተሬ ላይ እመዘግብ ይዣያለሁ።

የመድረኩ ዋና መሪ የነበረችው ፍሬህይወት የተሰብሳቢውን ቁጣ ልትቋቋም አልቻለችም። ሰለሞን ተቀባም የአቅሙን ሞከረ። መነፅሩን ገፋ ገፋ እያደረገ ለማስረዳት ቢሞክርም የሚሰማው ጠፋ። አንድ ታጋይ እንዲናገር እድል ሳይሰጠው ተነስቶ በቁጣ ይደሰኩር ያዘ፣

"ፍሬህይወት ተናገሪ እንጂ!! ሃቁን ታውቂ የለም እንዴ!? ስንት ጓዶቻችንን ቀብረናል? ክበበው ከጎናችን ሲወድቅ እንባችንን ውጠን አልቀበርነውም!? እነ አስራደ፣ እነ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አስማን ለዚህ ነበር የተሰዉት? ወገናችንን ልናስደበድብ ነው የታገልነው? ፍሬህይወት ተናገሪ!?"

የተሰው ጓዶች ስም ሲነሳ አንዲት ሴት እሪታዋን አቀለጠችው። አጠገቤ ከነበሩት ታጋይ ሴቶች አካባቢም የመንሰቅሰቅ ድምፅ ሰማሁ። የኢህዴኖች ቁጣ እንደ መትረየስ እሩምታ መንተክተኩ በመቀጠሉ፣ ሰለሞን ተቀባ ከተቀመጠበት ተነስቶ እጁን ወደ ላይ በማንሳት እንደምንም ፀጥታውን ካስከበረ በሁዋላ የሚከተለውን ተናገረ፣

"አንድ ጊዜ አድምጡኝ!" ሲል በታነቀ ድምፅ መናገር ጀመረ "...እንደማየው ከሆነ ይህ የአብዛኞቻችሁ አቋም ይመስላል! በኔ በኩል ምላሽ ለመስጠት ሞክሬያለሁ። የተሻለው አማራጭ በጥያቄያችሁ መሰረት ነገ ተፈራ ዋልዋ እንዲገኝ እንጋብዘውና እንወያይበት!"

አዳራሹ በጭብጨባ ተናጋ!

ተሰብሳቢው ሁሉ በወኔና በተስፋ ተበታተነ። ወደ መኪኖቻችን በማምራት ላይ ሳለን "ሃቁ መፈንዳት አለበት!" የመሳሰሉ ድምፆች በጨለማው ውስጥ ይሰሙ ነበር። ከሃምሳ በላይ ስቴሽንዋገኖች ግቢውን ለቀን ስንወጣ በዚያን ሌሊት መፈንቅለ መንግስት የሚካሄድ እስኪመስል ድረስ አንድ ንቅናቄ ነበር።

እኔ ወደቤት አልገባሁም። ከጓደኞቼ ጋር ተደዋውዬ እየጠጣን ስለሁኔታው ስናወጋ እኩለ ሌሊት አለፈ።

"የኢህዴኖች የህወሃት ጉዳይ አስፈፃሚነት ሊያበቃ ነው ወይስ አይደለም?" በሚለው ርእሰ ጉዳይ ብንወዛገብም ሳንግባባ ተለያየን።

* * *

በነጋታው እንደተለመደው ስብሰባው በሚጀመርበት ከሰአት በሁዋላ ዘጠኝ ሰአት ላይ አዳራሹ ይበልጥ ተጨናነቀ። በልዩ ልዩ ምክንያት በስብሰባው ያልተገኙ፤ ሆኖም ወሬውን የሰሙ አማራ ታጋዮች ወደ ስብሰባው አዳራሽ እየጎረፉ ነበር። በክራንች ድጋፍ የሚራመድ አንድ ታጋይ በጓደኞቹ እየታገዘ ሲገባ አየሁ። የግራ እግሩ ጣቶች በጀሶ እንደታሸጉ ይታያሉ። የተነሳውን የአመፅ ወሬ ሰምቶ ከሆስፒታል መምጣቱ ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ።

አስር ደቂቃ እንደጠበቅን ተፈራ ዋልዋ መጣ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በዝግታ እየተራመደ ከሰለሞንና ከፍሬህይወት መካከል ቁጭ አለ። ቡኒ አጀንዳ ይዞ ነበር።

ሰላምታ አቀረበልን!

ምላሽ ሰጠነው!

በቀጥታ ወደ አጀንዳው ገባ!

“ትናንት ያነሳችሁትን ጥያቄ ሰለሞንና ፍሬህይወት በዝርዝር አቅርበውልኛል። ስለዚህ ጥያቄውን መድገም አያስፈልግም! ሌሎች አስቸኳይ ስራዎችም ስላሉብኝ ምላሽ ሰጥቼያችሁ እሄዳለሁ። ጥያቄዎች ካላችሁና የግድ መቆየት ካለብኝ ግን መግባባት ላይ እስክንደርስ ልቆይ እችላለሁ!”

ተሰብሳቢው በንቃት እያዳመጠ ነበር፣

ተፈራ ዋልዋ ቀጠለ፣

“...ሃገራቱ በህወሃት ቁጥጥር ስር ገብታለች! እኛ ኢህዴኖች የበይ ተመልካች ሆንን! በእኛ ስም ዜጋችን ተደበደበ፣ ወገናችን ተዘረፈ! የመሳሰለ ቅሬታ አንስታችሁዋል ብለውኛል፣ ይሄ እውነት ነው!?” ሲል ጠንከር ባለ ድምፅ ጠየቀ።

“እውነት ነው!” የሚል ህብረድምፅ አስተጋባ። በርግጥ እንደትናንቱ ጠንካራ ህብረድምፅ ባለመስማቴ፣ ትናንት በቁጣ ሲንተከተኩ የነበሩትን ባይኔ መፈለግ ጀመርኩ።

“ይሄ ነው ጥያቄያችሁ!?” አለ ተፈራ!

“ልክ ነው!!” አሉ ጥቂት ድምፆች!

ተፈራ ፈገግ አለ!

“ይሄማ አዲስ ጥያቄ አይደለም!” ሲል ቀጠለ “...ከትግሉ ጊዜም ጀምሮ የነበረ ጥያቄ ነው። እኛ ኢህዴኖች ውጊያ ላይ ወደ ሁዋላ በማፈግፈግ፤ መሳሪያ ክፍፍል ላይ ደግሞ በመንጫጫት እንታወቃለን! ይሄን የሚክድ አለ!?” ሲል ጠየቀ።

አዳራሹ ፀጥ እንዳለ ቢሆንም ጥቂቶች ግን የሳቅ ድምፅ አሰሙ።

ተፈራ ቀጠለ፣

“በግልፅ እንነጋገር! አብረን ነበርን አይደለም እንዴ!? በውጊያ ወቅት ‘ህወሃት ይዋጋ! እንደ ጠላ በቆንጥርና በተራራ መሮጥ የለመዱት እነሱ ናቸው’ ትሉ አልነበረም!? እንዲህ እያላችሁ ስንት ውጊያ አበላሽታችሁዋል!? ተናገሩ የነበራችሁ! ህወሃት ተሰውቶ የያዘውንና የማረከውን መሳሪያ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ደግሞ ካልተካፈልን እያላችሁ ታጉረመርሙ አልነበረም!? ይሄ ውሸት ነው!? ዛሬም ያንኑ ነው የደገማችሁት! ስለ ስልጣን ከማውራታችሁ በፊት እስኪ ስንቶቻችሁ ናችሁ የተሰጣችሁን ስራ አድምታችሁ የሰራችሁ!?"

አዳራሽዋ በፀጥታ ተዋጠች።

ኮሽታ አልነበረም። ፍፁም ፀጥታ! አንገታቸውን ያቀረቀሩ ይበረክቱ ነበር።

ተፈራ ዋልዋ ሁለት ሰአት ያህል በወቀሳና በሂስ በረዶ ከደበደበን በሁዋላ ንግግሩን አበቃና ፋታ ወሰደ። ማስታወሻ ደብተሩንም አጠፈ። አንገቱን ደፍቶ በዝምታ የተዋጠውን ካድሬ ባይኑ ገረመመ፣

"ጥያቄ ወይም አስተያየት!? "

ፀጥታ! ፍፁም የሆነ ፀጥታ!

"ጥያቄ ወይም አስተያየት የላችሁም?"

ጥግ ላይ አንድ ሰው እጁን መዘዘ።

ተፈራ እድል ሰጠው፣

"አስተያየት አለኝ" ካለ በሁዋላ በሚያስደንቅ ችሎታ ተፈራ የደሰኮረውን አሳጥሮ ደገመልን! በመቀጠል ወኔና ቁጭት ባዘለ መንፈስ የኢህዴንን ድክመቶች ከዘረዘረ በሁዋላ፣ "ቁልፍ ችግራችን ትምክህተኛነት ነው!" ሲል ደመደመ።

"የተለየ አስተያየት ያለው ካለ?" ሲል ጠየቀ ተፈራ።

ምንም አልነበረም!

ጥቂት ጠበቀ! የተለየ አስተያየት በፍፁም አልነበረም! ተፈራ ዋልዋ ቡኒ አጀንዳውን አንስቶ ከመቀመጫው ተነሳ። እናም ተሰናብቶን ሄደ።

መርፌ ብትወድቅ ይሰማ ነበር...

ፍሬህይወት ጉሮሮዋን ሞረደችና ፈገግ አለች፣

"ግምገማችንን እንቀጥላለን!"

ከዚያ በሁዋላ በቀጠለው የአስር ቀናት ግምገማ አንዳችም የረባ ነገር አልተነጋገርንም። እገሌ ቢራ ይጠጣል፤ እንቶኔ ሴት ያማግጣል፤ እገሌ መኪና አጋጭቶአል እየተባባልን ስንሰዳደብ ከረምንና በመጨረሻ "ትምክህተኛነት ቁልፍ ችግራችን ነው!" የሚለውን በሙሉ ድምፅ አፀደቅነው።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

* * *

በነጋታው የተፈራን ንግግር "*መዝሙረ ዋልዋ*' በሚል ርእስ ማስታወሻ ደብተሬ ላይ መዝግቤ ሳበቃ፤ በቀይ አሰመርኩበት።

በነገራችን ላይ የትግል ጓዶቹ ተፈራን በስሙ ጠርተውት አያውቁም። "ዋልዋ" ነው የሚሉት። ተፈራ ቀስቃሽ አንደበት ያለው ካድሬ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ ጀግና ተዋጊም እንደነበር የጦር ሜዳ ገድሉን ሰምቼያለሁ። "ዋልዋ" የሚባል ተራራ ላይ ተፈራ የመራው የመከላከል ውጊያ በጥሩ ውጤት እንደ ተፈፀመም ይነገራል። ለዚህች መከረኛ ሃገር ተፈራ ጊዜውንና ጉልበቱን ብቻ ሳይሆን ውድ አካሉንም ቆርጦ ሰጥቶአታል። በከባዱ የቆሰለና ጉዳት የደረሰበት ታጋይ ነው። ያም ሆኖ ግን ህዝቡ የወደኔን አድሎአዊ አሰራር በመጥላቱ ተፈራ አዲሳባ ላይ ሁለት ጊዜ ለምርጫ ቀርቦ ሁለቱንም ተሸንፎአል።

የተፈራ ዋልዋ ንግግር ብዙ እንዳስብ አድርጎኛል።

"ህወሃት ይዋጋ! እንደጠላ በቆንጥርና በተራራ መሮጥና መዋጋት የለመዱት እነሱ ናቸው፡ ትሉ አልነበረም!? ህወሃት ተሰውቶ የያዘውንና የማረከውን መሳሪያ ደግሞ ካልተካፈልን እያላችሁ ታጉረመርሙ አልነበረም!?"

አመፁ የተከላሸበት ያ ስብሰባ ከተካሄደበት እለት በሁዋላ የባለስልጣናትን ሹመቶች በጥንቃቄ መከታተል፣ መመዝገብ፣ መመርመርና ማገናዘብ ጀመርኩ። በማጠቃለያው የደረስኩበት ድምዳሜም የፓለቲካ የስልጣን ትርጉም ለኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ገና ግልፅ ያለ መሆኑን ነበር።

በኢትዮጵያ የመንግስት መዋቅር የስልጣን ክፍፍሉ ፍትሃዊ ይመስል ዘንድ በፓርላማና በኤምባሲዎች አካባቢ ሚዛናዊ የሚመስል መዛነቅ እንዲታይ የተደረገ ይሁን እንጂ ወሳኞቹ ግን የህወሃት ሰዎች መሆናቸው በተደጋጋሚ ሲገለፅ መቆየቱ ይታወቃል።

ህወሃት እንደ ጠላ በተራራና በቆንጥር እየዘለለ ስለተዋጋ መላ ኢትዮጵያን እንዳሻው ሊቆጣጠር እንደሚገባ ተፈራ ዋልዋ ቃል በቃል ነግሮናል። በዚህም መሰረት የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፅህፈት ቤት፣ ውጭ ጉዳይና መከላከያ የተባሉት መስሪያ ቤቶች ዋና ዋና ቦታዎች ያለ ምንም

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ጥያቄ ለህወሃት ተሰጥተዋል። የደህንነት መስሪያ ቤቱ ስልጣን የህወሃት የግል ጉዋዳ ብቻ ነው። ማሰር፣ መግደል፣ መፍታት፣ ህገወጥ ቢዝነሶችን በህጋዊነት ሽፋን መፈፀም፣ የስለላ ተግባራትን ማከናወን ሁሉ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን የተሰወሩ ናቸው።

በቀድሞ ጊዜ፣

ገበየሁ ቢሞት - ተተካ ባልቻ፣
መድፍ አገላባጭ - ብቻ ለብቻ፣

ይባል ነበር።

ዛሬ እንዲያ አይሰራም።

"ክንፈ ቢሞት - ተተካ ጌታቸው" ነው ዜማው። "ፃድቃን ቢባረር - ተተካ ሳሞራ" ነው ጨዋታው። ሁሉም የህወሃት ካድሬዎች ናቸው። ሚዛናዊ ሆነን እናስብ ካልን፤ ህወሃት ታግሎ ደርግን የጣለ ሃይል እንደመሆኑ ስልጣን ላይ መቀመጡ ግድ ነው' ማለት ይቻላል። ይህንኑም መለስ ዜናዊ ነግሮን ያውቃል።

"ለስልጣን የበቃነው ጀርባችንን በእሳት ሰንሰለት እየገረፍን ነው!" ብሎናል።

የዚህን አባባል ስነአመንክዮአዊ ትርጓሜ መረዳት የማይችል የለም። ኢትዮጵያ ላይ የፖለቲካ ስልጣን በህዝብ ፍላጎትና በምርጫ የሚገኝ ሆኖ አያውቅምና፣ ህወሃት፣ "17 አመታት ተዋግተን ደርግን ስለገለበጥን፤ 27 አመታት ደግሞ ከልዩ መብት ጋር የመንገስ መብት አለን" ቢለን ሊደንቅ አይገባም።

ህወሃት ለስልጣኑ ህልውና መረጋገጥ ወሳኝ የሆኑ መስሪያ ቤቶችን መያዙ የሚጠበቅ ነው። ውጭ ጉዳይ፣ ደህንነት፣ ጠቅላይ ሚኒስትርና መከላከያን ከለቀቀ ህልውና አይኖረውምና ማንም ቢሆን ይህን ይገነዘባል። ህወሃት ህልውናውን ከማስጠበቅ ባሻገር ለሃገሪቱ እድገት ሲል እንኳ ከዚያ በመለስ ያሉ ሙያ ነክ የስልጣን ቦታዎችን ለባለሙያዎች መተው አለመቻሉ ነው ችግሩ። ለሌሎች ብሄር አባላት የይስሙላ ስልጣን ብቻ መስጠቱ ነው አስፀያፊው ባህርይው። ታኮ የማስቀመጥ ልምዱ በሃገሪቱ ህዝብ መካከል አለመተማመንን እያባባሰው ይገኛል። አሳዛኙ ነገር ደግሞ ይህ አሰራሩ እመራዋለሁ ለሚለው ህዝብ የወደፊት ህልውና የማይበጅ መሆኑን አለመገንዘቡ ነው።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ቀዳሚዎቹ የኢትዮጵያ አስተዳዳሪዎች ከወያኔ ጋር ሲነፃፀሩ እጅግ ብልህ ነበሩ። እነ ራስ ጎበና ሙሉ ስልጣን ነበራቸው። ጃንሆይ ለጄኔራል ታደሰ ብሩ የሰጡት ሹመት የይስሙላ አልነበረም። ግፋ ቢል በጋብቻ የማዛመድን ዘዴ ነበር የሚጠቀሙት። ጄኔራል ደምሴ ቡልቶና ረጋሳ ጅማ በችሎታቸው እንጂ በወያኔ የዘር ቀመር የተሾሙ ጄኔራሎች አልነበሩም። ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ኤርትራዊ ነበር። በኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት ውስጥ ግን ባለሙሉ ስልጣን ጄኔራል ሆኖ ማገልገሉ ይታወቃል። ዛሬ ሙሉና ግማሽ የተባሉ ኢትዮጵያዊነቶች በስራ ላይ ውለው እያየን ነው። በዛሬው ዘመን የጄኔራልነት ማእረግ የተሰጣቸው የኦሮሞ መኮንኖች ትግራይ የሆነውን ተራ አስር አለቃ ለመቅጣት አይደፍሩም። በግልባጩ ይፈሩታል።

ሻለቃ ጀማል የተባለ ኦሮሞ መኮንን መቀሌ ላይ በተደረገ አንድ የመኮንኖች ስብሰባ ላይ እንዲህ ሲል መጠየቁን ሰምቻለሁ፣

"ሰአረ መኮንን የወዲ ትኩልን ዘፈን በመኪናው ውስጥ ሲሰማ እኛ ሻእቢያ አንለውም። ኮሎኔል ገመቹ የአሊ ቢራን ዘፈን ትሰማለህ ተብሎ በአነግነት የተፈረጀው በምን ስሌት ይሆን?"

በመከላኪያ መስሪያ ቤት ከ90 በመቶ በላይ የሚካናይዝድ ሻለቃ አዛዦች የህወሃት ሰዎች ናቸው። ወደ ታች እየቀነሱ ይሂዱና የህወሃት አባል የሆነ ተራ ወታደር አይገኝም። በኢትዮ - ኤርትራ ውጊያም ሆነ በሶማሊያ ተራ ወታደር ሆነው መስዋእትነትን በግንባራቸው የተቀበሉት ወይም እየተቀበሉ ያሉት ሌሎች ኢትዮጵያውያን ናቸው። "ሌሎች ኢትዮጵያውያን" የሚለው ቃል ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ቃል ለመሆን በቅቶአል።

ህወሃት እንደጠጣ በቆንጥርና በተራራ ተዋግቼ ያገኘሁት መብቴ ነው የሚለው የፖለቲካ ስልጣን ማብቂያና ገደብ ያለው አይመስልም። የትግራይን ክልል ያለ ጣልቃ ገብነት የመምራት መብቱን በማረጋገጥ ማቆም አልቻለም። ለእያንዳንዱ ክልል ታክ ተቀምጠለታል። "ለምን?" ተብሎ ጥያቄ ሲነሳ "ድርጅታዊ መደጋገፍ" የሚል የፈዝ ምላሽ ይከተላል። የአማራውና የኦሮሞው ክልል የአስተዳደር ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎችን አጥቶ የህወሃት ካድሬዎችን ርዳታ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ጠየቀ መባሉ ምፀት ነው።

የወንጂና የመተሃራ ስኳር ፋብሪካዎች ጄኔራል ሳሞራ የኑስ እንደ አሻንጉሊት ይጫወትባቸው ዘንድ ተመርቀውለታል። የሙገር ሲሚንቶና የአየር መንገድ ቦርድ ደግሞ በስዩም መስፍን እጅ ናቸው። የፌደራል ጉዳዮች በአባይ ፀሃዬ የተያዘ ነው። ማስታወቂያ ሚኒስቴርና ሚዲያ ነክ ስልጣናት የበረከት ስምኦን የግል ንብረቶች ናቸው። *(በረከት የብአዴን አባል ነው ቢባልም አማራ አለመሆኑ ይታወቃል።)* ኢኮኖሚውን የተቆጣጠረውና መለስን የሚያማክረው ንዋይ ገብረአብ ይባላል። እኔ በስደት በተቀመጥኩባት ደቡብ አፍሪቃ ፕሪቶሪያ አምባሳደሩ የደቡብ ሰው ቢሆንም፤ *(ይህን ማስታወሻ በምፅፍበት ወቅት)* የኤምባሲው ዋና አዛዥ ሆና የምትሰራው በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠችው የህወሃት ታጋይ ናት። ይህን መሰል አሰራር በመላ ኤምባሲዎች የሚፈፀም መሆኑም ይታወቃል።

ተፈራ ይህን አያውቅም ማለት አንችልም። ይህን የመጠየቅ መብት የለንም ባይ ነው። የህወሃት መብት ገደብ አልባ መሆን በተለያየ መንገድ ይገለፃል።

በቅርቡ አንድ ኦሮሞ ኮሎኔል ከኮበለለ በሁዋላ ከውጭ ሃገር ሆኖ የሰጠውን ቃለመጠይቅ በሬድዮ ሰምቼው ነበር። ኮሎኔሉ እንደሚገልፀው ተፈሪ መኮንን በተባለው ትምህርት ቤት አጠገብ ሰንሻይን የተባለ ኮንስትራክሽን ድርጅት የገነባው የመኖሪያ ቤት አፓርትመንቶች አሉ። ባለታክሲዎች ፔንታጎን የሚል ቅፅል ስም ሰጥተውታል። ሰባት ፎቅ ያላቸው አራቱ ግዙፍ ህንፃዎች በጠቅላላው 120 ቤተሰቦችን የመያዝ አቅም አላቸው። እነዚህ አፓርታማዎች ለመከላከያ መኮንኖች የተከፋፈሉ ሲሆን፤ 102 አፓርታማዎች ለህወሃት መኮንኖች ተሰጥተዋል። ከሃሜት ለመዳን ተብሎም 18 አፓርታማዎች ለአማራና ለኦሮሞ መኮንኖች ታድለዋል። "እንደ ጠጣ በቆንጥርና በተራራ ተዋግተዋልና ይገባቸዋል" ይልሃል - መዝሙረ ዋልዋ!

ብአዴን ከአማራው ህዝብ ድጋፍ ያጣበትን ምክንያት ቁጭ ብሎ መመርመር ባለመቻሉ ያደረሰው ቀውስ መጠን አልባ ነው። ብአዴን የአማራውን ህዝብ ጥያቄዎች ለማፈን የተዘጋጀ ተቋም ሆኖ ፖሊሳዊ ተግባር እንደሚያከናውን ማመን ሳይችል ቀርቶአል። አንዳንድ ቀላል አብነቶችን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለማንሳት፣ ብአዴን ለአባላቶቹ ያዘጋጀውን የመገምገሚያ ነጥብ ማየት ይቻላል። "ትምክህተኛነት" እና "መስዋእትነት ፍራቻ" የተባሉት ታዋቂ ሆነው ለረጅም ጊዜ ዘልቀዋል። "ሙስና" የመጠባበቂያ መገምገሚያ ነጥብ ሆኖ በሶስተኛ ደረጃ ይከተላል። በህወሃት ግምገማዎች ላይ ግን "መስዋእትነት ፍራቻ" የሚለው መገምገሚያ ስራ ላይ ውሎ አያውቅም።

ይሄ ምን ማለት ነው?

የብአዴን አማራዎች፣ "ህወሃትን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ" የሚለውን መዝሙረ - ዋልዋ ይዘምሩ ዘንድ በትምክህተኛነት መገምገሚያ ይቀጠቀጣሉ። "መስዋእትነት ፍራቻ" የሚለው መገምገሚያ የአማራውን ትምክህት ሊሰብር ይችላል ተብሎ የተዘጋጀ የማሸማቀቂያ ስልት ሲሆን፣ ሙስና ደግሞ ከስራቸው እንደሚባረሩ የምታስጠነቅቅ ማስፈራሪያ ናት። በረከተ - ዋልዋና ደቀመዛሙርቱ አባላቶቻቸውን በዚህ ዘዴ ገርተው እንደ ቢሾፍቱ ፈረሶች ይጋልቧቸዋል። ሚዛናዊ የልማት ጥያቄዎችን እንዳያነሱ በተለያዩ የማሸማቀቂያ ዘዴዎች ያኮላሹዋቸዋል።

"በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎች" የተባለው ቃል ባንድ ወቅት ወቅታዊ ቃል ነበር። ሆኖም በጦርነቱ ወቅት በአስከፊ ሁኔታ ተጠቂ የነበሩት የአማራው ከተሞች የዚህ ቃል ተጠቃሚ ሆነው አያውቁም። ሃሙሲት፣ በለሳ እና አምደወርቅ የተባሉት በአማራው ግዛት የሚገኙ ከተሞች፣ በደርግ የጄት ድብደባ የወደሙ ከተሞች ቢሆኑም፣ እንደ አድዋና ሽሬ "በጦርነት የተጎዱ ከተሞች" ስም ዝርዝር ውስጥ ግን አልነበሩበትም። ዋልዋ ይህን እያወቀ "ለምን?" ብሎ አይጠይቅም። አባባሉን ስንተረጉመው፣ "ካሳ የሚገባው ሃሙሲትና አምደወርቅን ከደርግ *መንጋጋ* ነፃ ላወጡት ነው" የሚል ይሆናል። አምደወርቅ 24 ጊዜ በደርግ የጦር ጄት የተደበደበች ከተማ ናት። አምደወርቅ ትኩረት ታገኝ ዘንድ "ተዋጊ *መሪ* መውለድ አለብሽ" እየተባለች ነው።

በአንድ አገር ሁለት አይነት *ፖ*ሊሲና አመራር ለምን ኖረ? አዲሳባ፣ አምቦ፣ ነቀምት፣ ደብረዘይትና ጎንደር፣ "የጠላት መከማቻ ከተሞች" ተብለው አሸማቃቂ ተፅእኖ ሲደረግባቸው ዋልዋ እያወቀ ዳር ቆሞ ያያል። ቦሌ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አይሮፕላን ማረፊያ ላይ ከተላላፊ የእፅ ነጋዴ መንገደኞች የሚያዙ የኮኬይንና የሄሮይን አደንዛዥ እፆች ተመልሰው አዲስ አበባ ላይ ይቸበቸባሉ። ትውልድን በእጥፍ ድርብ ከሚገድለው ከዚህ ወንጀል በሚገኘው ገቢ የመቆጣጠሪያው የፖሊስ ባለስልጣናት ሁመራ ላይ የሰሊጥ እርሻ ያስፋፉበታል። ተፈራ ዋልዋ "ይህን አላውቅም" የሚል ከሆነ ስልጣኑን በፈቃዱ ቢለቅ ይመረጣል። ትግራይ ላይ ጫት እንዳይሸጥ የከለከለ መንግስት፣ አዲሳባ ላይ ሄሮይን ከነገደ ምን ማለት ነው? የአርሲ ገበሬ በተለየ ሁኔታ በፖሊስና በወታደር የከፋ ግፍ የሚፈፀምበት "አሁንስ በቃ!" ማለት ስለቻለ ብቻ ነው። በጥቅሉ፣ "በመስዋእትነት ፍራቻ" መገምገም ካለባቸው "ህወሃትን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ" በሚለው ራሳቸው በፃፉት መዝሙር ስር የሚሰግዱት እነ በረከት - ዋልዋ፣ እነ ህላዌ - አዲሱ እንጂ ተራው የብአዴን አባልና ካድሬ መሆን ባልነበረበት።

ይህን አጅንዳ ለመቋጨት፣ ከደርግ ውድቀት በሁዋላ እንኳ፤ ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ህወሃት ደርግን ለመጣል ከከፈለው መስዋእትነት በእጥፍ በሃገሩ ስም ተዋግቶ ተሰውቶአል፤ ወይም እንዲጨፈጨፍ ተደርጎአል። መስዋእትነቱ ግን ከቁጥር አልገባለትም። በአጠቃላይ ይህን መሰል ሁኔታዎች ቂም ፈጥረዋል። ቅሬታዎችም በተለያየ መንገድ ሲገለፁ እያየን ነው። የቀድሞ አለቆቹ ቂምና ቁጣው ግንፍሎ ጉልበት ያገኘ ጊዜ፣ ሊከሰት ስለሚችለው አደገኛ ሁኔታ ማሰብ የሚሹ አይመስሉም።

"እኛ ተዋግተን ነፃ ባናወጣህ ኖሮ ደርግ በድጉ ይገዛህ ነበር" እስከማለትም ይደርሳሉ።

የዋልዋ "የጠጣና የቆንጥር" አስተሳሰብ በስራ ላይ መዋሉም እየቀጠለ ሲሆን፤ "እስከመቼ?" ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ግን ነቢይ መሆን ሳያስፈልግ አልቀረም...

* * *

የኢህዴን ካድሬዎች የአዲሳባ አመፅ ከተከላሸ ከአንድ አመት በሁዋላ ማለትም 1985 ላይ የኢህዴን ከፍተኛ አመራር አባል የነበረው ሙሉአለም አበበ ቢሮው ውስጥ በፈንጂ ተገደለ።

አገዳደሉን በተመለከተ ዛሬም ድረስ ሚስጥር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደሆነ ይገኛል። ከመገደሉ ስምንት ወራት በፊት ደሴ ላይ በተደረገ የኢህዴን ኮንፈረንስ ላይ ግን ሙሉአለም በኢህአዴግ አመራር አካሄድ ላይ የሰላ ሂስ ሰንዝሮ እንደነበር የዚያን ሰሞን የኢህዴኖች የመወያያ ርእስ ነበር። ባጭሩ ሙሉአለም፣

"የኢህዴን አባላት ላይ ፍትህ የጎደለው እመቃ እየተደረገ ነው። እንደ ትግሉ ዘመን በእኩልነት የመናገር መብቶች ይጠበቁ፣ የህዝባችንን ቅሬታዎች እናዳምጥ!" የመሳሰሉ ተቃውሞዎችን አቅርቦ ነበር።

ሙሉአለም ቢሮው ውስጥ በሚስጥር በተጠመደ ፈንጂ የተገደለ ሲሆን፣ ከሞተ በሁዋላ የባህርዳሩ ሙዝየም በስሙ ተሰይሞለታል። በወቅቱ የሙሉአለምን ቢሮ ይጠብቁ የነበሩ ዘበኞችና የፅዳት ሰራተኞች ለአጭር ጊዜ ታስረው የነበረ ቢሆንም፣ የሙሉአለም ገዳይ ግን የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቶአል። ሙሉአለም እንደ ገሰሰ አየለ ወይም እንደ ማርሻል ሮሜል ከተገደለ በሁዋላ የተሸመ ሰማእት ነው ብለው የሚያምኑ የኢህአዴግ አባላት ጥቂት አይደሉም። ይህ ግን የታሪክ ፀሃፊዎች ይመራመሩበት ዘንድ በእንጥልጥል የሚቆይ መረጃ ይሆናል...

* * *

ባንድ ወቅት ጎንደር ለስራ በሰነበትኩበት ጊዜ የህዝቡን ብሶት ቀርቤ ለማዳመጥ እድል ማግኘት ችያለሁ። ጎንደር በራሱ ጥንታዊ ዘይቤ ብሶቱን ሁሉ ባዝማሪዎች በኩል ሲተነፍስ አዳምጬያለሁ። የጎንደር አዝማሪዎች የመለስ ዜናዊን፣ የአዲሱ ለገሰን የህላዌን፣ የታደሰ ጥንቅሹን በተለይም ደግሞ የጎንደር ልጅ የሆነውን የበረከትን ስሞች በቅኔዎቻቸው መሃል እየቀላቀሉ በዝገብኝ ቤቶች ደምበኞቻቸውን ሲቀሰቅሱ ያመሻሉ። በጣም የደነቀኝ ነገር ቢኖር ግን ጎንደሬ ብሶቱን በግልፅ ባደባባይ ማስተጋባት መቻሉ ሳይሆን፣ እነ በረከት ይህን የአዝማሪ ቤት ብሶት የሚሰሙበት ዘዴ ያለማበጀታቸው ነበር። ጋባዣቹ እንዳጫወቱኝ ፀጉረ ልውጦች አለያም በጆሮ ጠቢነት የሚታሙ የመንግስት ሰዎች ወደ አዝማሪ ቤቶች ሲገቡ ዜማ ይለውጣሉ። እኔም ለመታመን የበቃሁት በሚታመን የከተማው ነባር ነጋዴ ታጅቤ በመግባቴ ነበር። ብአዴኖች

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ብቅ ሲሉ ዜማው ይቀየርና፣ "እሪ በል ሰቆጣ - እሪ በል ኮረም" ይዜማል። ቅኔ ሞልቶ የተረፈውን የጎንደር ህዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት በዚያ ጉብኝት ሲሆን፣ ያን ህዝብ ከልብ በመነጨ ፍቅር ልወደው በቅቻለሁ። ለጎንደር ህዝብ የቅርብ ሩቅ ለሆኑት ለነዋልዋ ከሶስት አዝማሪ ቤቶች ከቃረምኳቸው ቅኔዎች መካከል ጥቂቱን ላካፍላቸው፣

ይሰሙኝ እንደሆን - መለስ ልምከርዎ፣
ቀንሶ ማጋጨት - ከንግዲህ ይብቃዎ፣
* * *
ሃዘን ይዞአል አሉ - አቶ መለስ ዜና፣
ደህና አይደሉም ወይ - ጌቶች እንደ አምና፣
* * *
ጎንደር ሃገር ጠፍቶ - ሲፈለግ ሌሊት፣
ቀን ካዲሱ ጋራ - ሲሄድ አየሁት፣
* * *
በጎ ምክር መክረው - ክፉን የሚያስጥሉ፣
ያርባራቱ ታቦት - ሊቃውንት እያሉ፣
በረከተ - መርገም - ይቀድሳል አሉ፣
* * *
አዲስ አዲሱ ሰው - በዝቶ እየተባዛ፣
ከባዱ ሜዳ ላይ - ቀረን እንደዋዛ፣
* * *
ሙሉአለም አበበ - አዬ ታላቅ ጌታ፣
ሳይታመም ውሎ - አዳሩን ተፈታ፣
* * *
አዲሱ ህላዌ - ታደሰ ዘመዴ፣
መንገድ አወጡና - ሄዱበት በሆዴ፣
* * *
በረከት ሃገሩ - ስለናፈቀው፣
ዳሸን አናት ሆኖ - አስመራን አየው፣
* * *
ከሁመራ ገብተን - ከመሃሉ ላይ፣
አዲስ ሰው አገኘን - መሬት መሬት ባይ፣
* * *
ዳቦ የመሰለኝ - በሩቁ ሳየው፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አሁን ቀረብ ስል - ለካ ቢራ ነው፣
* * *
በገዛ አገራችን - በገዛ ወንዛችን፣
በቢራ እያጠቡን - ገባን ከጎጆአችን፣
* * *
የደገኛ ነው ወይ - ወይስ የቆለኛ፣
ጠለምት ገዳም ገባች - የሚል አማርኛ፣
* * *
በረከት በሰው ቤት - ሲገባ ሲወጣ፣
እኔም ቤት አልቀረ - መርገም ይዞ መጣ፣
* * *
ጥቂቶች ቆራጦች - በጣም በርትተዋል፣
ያልተንበረከኩት - ጎንደር ላይ ነግሰዋል፣
አልበቀለም እንጂ - ብዙ ዘር ዘርተዋል፣
* * *
ወልቃይት ፀገዴን - አስተውሎ ላያት፣
ወይ ያኔ ወይ ያኔ - ወይን ናት ወይን ናት፣
* * *
መቀሌ ያካፋል - ባድዋ ፀሃይ፣
በጎንደር ጨልሞ - መቅረቱ ነወይ?
* * *
አደባባይ ቆሞ - አበጅሁ ቢላችሁ፣
ይህን ባለ ጊዜ - ምን ትሉታላችሁ?
* * *
ምንም ባንቀበር - ባንገባ መሬት፣
አያሳፍረንም - ሞተናል ማለት!

የብአዴን አመራር አባላት ለራሳቸው ማቅረብ የነበረባቸው አቢይ ጥያቄዎች ነበሩ። የአማራው ህዝብ ለምን እንደጠላቸው መመርመር የመጀመሪያው ነበር። አርሶአደሩ ደጋፊያችን ነው ብሎ መመፃደቅ ወንዝ እንደማያሻግር ከጎንደር ቅኔዎች መገንዘብ ይቻላል። የአማራው አርሶአደሩ ከጥላቻ በላይ ብአዴንን ንቆታል።

"አልበቀለም እንጂ ብዙ ዘር ዘርተዋል!" የሚለው ቅኔ አሰቃቂ ንቀት አዝሎአል። "ዘር የሚበላ" አድርጎ ቆጥሮአቸዋል። ገበሬ ዘር አይበላም። ዘሩን ከመብላቱ በፊት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መሞትን ይመርጣል። ለዘር ልዩ ክብር አለው። ህይወት እንዲቀጥል የዘር እህል ይቀመጣል።

"አልበቀለም እንጂ ብዙ ዘር ዘርተዋል" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ቁጭ ብለው ሊመረምሩት ይገባቸዋል። ምርጫ 97 ስላልበቀለው ዘር የሚያስገነዝብ አስረጅ ነው። በረከት ስምኦን ከጎንደር እስከ ቡግና ወረዳ ዘሩን ዘርቶ መከነ። ህላዌና ተፈራ በአዲስ አበባ የዘሩት ዘር ጫጨ።

"ራእያችን ምን ነበር?" ብለው የብአዴን አመራር አባላት ራሳቸውን መጠየቅና እንደገና ወደሁዋላ መመለስ ይጠበቅባቸዋል።

ህላዌ ዮሴፍ በ1988 እፎይታ መፅሄት ላይ ባሰፈረው ግለ - ገድል ማጠቃለያ ላይ እንዲህ ሲል አስፍሮ ነበር፣

"...አንድ ቀን ኢህዴንን ልንመሰርት ጥቂት ቀናት ሲቀሩን በህይወት ካሉት ታጋዮች መካከል በረከት፣ ታምራት፣ ተፈራ፣ አዲሱ፣ ገነትና ሃይሌ፣ ከተሰውትም መሃል ክበበው፣ አስራደ፣ አስማን፣ ሙሉአለምና አብዲ ዛፍ ስር ተቀምጠናል። አንዳንዶቻችን ሬድዮ እየሰማን ወሬ ይዘናል። ሃይሌና አብዲ ቼዝ ይጫወታሉ..."

ርግጥ ነው፣ የብአዴን ሰዎች ከፍፃሜው ቀን በፊት ወደዚያች ዛፍ ጥላ ስር ተመልሰው፣ የህዝቡን ቅኔ አዳምጠው፣ ሰምና ወርቁን መመርመር ይገባቸው ነበር። ሆኖም የታሪክ ተወቃሽ የሚያደርጋቸውን መንገድ መርጠዋል። መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው።

የኢህዴን የአመራር አባላት አጥብቀው የሚወድዋት አንድ ግጥም አለች። ሁሉም በቃል ያዜሙዋታል። ታዬ የተባለ ታጋይ ለኢህአፓ የቋጠራት ነበረች። ዛሬ ግን ለብአዴን ለራሱ በልኩ የተሰፋች ጥብቆ ሳትሆን አትቀርም፣

ሞኝ ዳቪንቺ ተሳላ - የቀረፀውን አጉል ወዶ፣
ለራሱ ስራ ተንበርክኮ - በፍቅር ትንታግ ተማግዶ፣
የሮም የዋህ ሰው ሊዎናርዶ - አወይ ነዶ አወይ ነዶ፣
ብላሽ መሃንዲስ - ሊዎናርዶ ቃርሽ አናጢ፣
የኪነት ወራዳ - የሰአሊያን መናጢ፣
አዬ ሊዎናርዶ - የሰእል ኪነት ሉጢ....

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 3 -

አንድ አገር - ሁለት አለም

በቀበሮ ጉድጓድ - ቀበሮ መስሏቸው፣
ውሾቹ አጓሩ - በዛ ጩኸታቸው፣
አይ የውሾች ነገር - ማን በነገራቸው፣
አንበሳ እንደሆነ - የሚጠብቃቸው፣

(ግጥም - ደበበ ሰይፉ)

* * *

ድምፆቻችን ከጫካው - ከገደላ ገደሉ፣
ከተራራዎች ከወንዞች - ከበረሃው ይጣራሉ፣
የፋሽቱን የደም ደለል...
እንፈርክሰው! እንናደው! እያሉ፣

(ግጥም - ታምራት ላይኔ)

እነሆ ደብረታቦር እየሱስ ተራራ ላይ እገኛለሁ። በደርግና በወንበዴዎች መካከል የሚደረገውን ጦርነት ለመዘገብና የፕሮፓጋንዳ ፅሁፍ ለማዘጋጀት በ300 ብር የወር ደሞዝ ተቀጥሬያለሁ።

ሻምበል በለጠ የተባለውን መስመራዊ መኮንን የተዋወቅሁት ደብረታቦር እየሱስ ተራራ በደረስንበት እለት ነበር። ደንዳና ሰውነት ያለው የኮሩ የባህል ንኡስ ክፍል ሃላፊ፤

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እየሱስ ተራራ የደረስነውን የፖለቲካ ካድሬዎች በአስቀያሚና በተሰላቸ አነጋገር ነበር የተቀበለን፣

''...ባጭሩ እኛ በጠላት ላይ የበላይነት አለን። በሚዲያ ሰምታችሁት ይሆናል! ከጥቂት ወራት በፊት ሰራዊታችን ታላቅ ድል አፍሷል። ይኸው ነው! በተቀረ በሶስት ቀናት ውስጥ የምድብ ክፍላችሁን ታውቃላችሁ። ለጀግናው የ603ኛ ኮር የፕሮፓጋንዳ ዘርፍ ካድሬ ሆናችሁ በመመደባችሁ ልትኮሩ ይገባችሁዋል! ከናንተ የሚጠበቀው ሰራዊቱን ማንቃት ነው! ሲያዩዋችሁ ግን ፈዛዛና ደንዛዛ ትመስላላችሁ! ሰርግ ተጠርታችሁ አልመጣችሁም ጓዶች! ለራሳችሁ ስትሉ ነቃ ነቃ በሉ! አዋጊና ተዋጊ መሆናችሁንም አትርሱ! ጨርሻለሁ!''

እየሳቅን ወደየድንኳናችን ተበታተንን።

በዚያን እለት ሌሊት የወያኔ ሞርታርና BM ሼል ሲምበለበልና ሲዳፈንብን አደረ። ለቅሶ እንደሚያሰማ ውሻ የእየሱስ ተራራን አቀበት እያላዘነች ወጥታ እኛን ያራገፈችው አውቶብስ ወደመጣችበት ተመልሳለች። አይኖቼ አካባቢውን አጤኑት። በተቃጠሉ ታንኮችና አረንጓዴ ፋቲግ በለበሱ ወታደሮች ተሞልቶአል። የተማረኩ የወያኔ ወታደሮች ሲረሸኑም በአይኔ ተመለከትኩ። ጎምዛዛ ነገር ጉሮሮዬ ላይ መጥቶ አቃረኝ። በተቃራኒው ወገን የተሰለፉት አማፅያን የኤርትራና የትግራይ ወንበዴዎች እየተባሉ እንደሚጠሩ በሬድዮ እየሰማሁ አድጌያለሁ።

ለራሴው ያላመንኩበትን እንዴት ሌላውን ላሳምን እንደምችል ባላውቅም ዋና ዋና የሚባሉ የቅስቀሳ ቃላትን ግን ተጠንቅቄ አጥንቼያቸዋለሁ። እነዚህም 'ገንጣይ' 'አስገንጣይ' 'ወንበዴዎች' 'የባህር በር' 'የኢትዮጵያ አንገት' 'አንድነት' 'የ3000 አመት ታሪክ' 'ጀግንነት ልማዱ የሆነው ህዝብ' 'ከአባቶቻችን የወረስነው ዳር ድንበር' እነዚህን ቃላት በመጠቀም የቅስቀሳ ፅሁፍ ማዘጋጀት ለኔ ገብስ ነበር።

ሻምበል በለጠ እየተነጫነጨ ሲቀበለን ወዲያው ወደድኩት! የሚናገርበትን እንደማያምንበት ለመረዳት አልተቸገርኩም። የተሰላቸና የተበሳጨ ሰው ነበር። 'ፈዛዛና ደንዛዛ' ትመስላላችሁ ያለው እውነቱን ነበር። ሃያችንም ወጣቶች ድህነትና ስራ አጥነት ገፋፍቶን በሃረር የፖለቲካ ትምህርት የተከታተልን፤ ካድሬ የሚለውን ቃል እንኩዋ በቅጡ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ያልተገዘብን፤ ጦርነትን የማናውቅ ጨቅላዎች ስለነበርን እየሱስ ተራራ ላይ ባየነው የተቃጠሉ ታንኮች ምክንያት ተደናግጠን ነበር። አንዳችም ተስፋ የሚያሳድር ነገር አለማየታችን ትንፋሻችንን ቆርጦታል!

* * *

በዚያን እለት ምሽት ጀምበር እንደጠለቀች አንድ መፅሃፍ ይዤ ከአለቶቹ ላይ ተቀመጥኩ። ከፊት ለፊቴ ጉና ተራራ ይታየኛል። የጢስ ክምር እንጂ ተራራ አይመስልም። ሁለት ሄሊኮፕተሮች ከጄኔራል አበበ ሃይለስላሴ ማዘጋ ጣቢያ ደጃፍ ላይ ክንፎቻቸውን አንጨፋረው ቆመዋል። ሻምበል በለጠ እንዳብራራልን ከሆነ የሻእቢያና የወያኔ ወንበዴዎች እዚያ የጢስ ክምር የመሰለው በረዶአማ ተራራ ላይ ሰፍረዋል። ጥቂት ሳይዋጉ ከቆዩ ወደ በረዶነት እንደሚለወጡ እየቀለደ አውግቶናል። ስለዚህ ወደ በረዶነት ከመቀየራቸው በፊት ውጊያ ሊጀምሩ እንደሚችሉ ነበር ሻምበል በለጠ ወታደራዊ ግምቱን የሰጠን። እኛ እዚህ አለን። "በእኛና" "በእነሱ" መሃከል ውጊያ ከተጀመረ ያቺ ምድር በሃበሻ ደም ትጨቀያለች!

መፅሃፍ ይዤ ጥቋቁሮቹ ድንጋዮች ላይ በተቀመጥኩባት በዚያች ደቂቃ ስለ ግል ህይወቴ እያሰብኩ ነበር። ሞት አጠገቤ እንዳለ ተሰምቶኛል! የደራሲነትና የጋዜጠኛነት ህልሞቼ አሁን በንነው ጠፍተዋል። ሞት ወይም ህይወት አማራጭ ብቻ ሆነው በልቤና በአእምሮዬ ውስጥ ድቤያቸውን ይደልቃሉ።

በዚህ ውጊያ መሞት አለብኝ? ለማን ጥቅም? ለማን አላማ? እያልኩ ራሴን በጥያቄ ማሰቃየት ይዤያለሁ!

* * *

በነጋታው ማለዳ ከጓደኞቼ ሁሉ ዘግይቼ ነበር ከእንቅልፌ የነቃሁት። የከባድ መሳሪያ ድምፅ የማረፊያ ድንኳኔን ባይነቀንቃት ኖሮ እንዲያውም የምነሳ አይነት አልነበርኩም። እንዲያም ሆኖ በርግጌ አልተነሳሁም፤ ጆሮዎቼን ከፋፍቼ የሚቀጥለውን የከባድ መሳሪያ ድምፅ ለማዳመጥ ተዘጋጀሁ። ዘግየት ብሎ ተደገመ። የሩቅ ድምፅ መሆኑን ገመትሁ። ሆኖም ሰማዩ የተተረተረ እስኪመስል ድረስ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ይቀረዳደድ ነበር። እየሱስ ተራራን የማንቀጥቀጥ ሃይልም ነበረው።

ብርድልብሴን ወርውሬ ተነሳሁ። የማለዳው ቅዝቃዜ እግርና እጄን አደንዝዞኛል። እጄን ርስበርስ እያፋተግሁ ሙቀት ለመፍጠር ጣርሁ። ካልሲዬ እንደ በረዶ ቀዘቀዘኝ። በተሳሳተ ግምት ወደዚህ የሞት መስሪያ ቤት የተቀጠርኩበትን ቀን እየረገምኩ ጫማዬን አጠለቅሁ። ፊልድ ጃኬቴን ደርቤ ከድንኳኔ ከወጣሁ በሁዋላ ረሃብ ስለሞረሞረኝ ቁርስ ፍለጋ ወደ መመገቢያው ድንኳን ፊጠንሁ። ቀዳሚ መምሪያው የተደራጀ የመመገቢያ ስፍራ አልነበረውም። የኩሩ አዛዥ የጄኔራል አበበ ሃይለስላሴን ማረፊያ ጎጆ የታክሰች አንዲት ኩሽና ብጤ አለች። ኩሽናዋ ደጃፍ ላይ አንድ ወታደር ሻይ እያፈላ ከኩቾሮ ጋር ለውጊያ ሊቃውንቱ ያድላል። ወደዚያው ሄጄ ቁርስ ጠየቅሁ። ወታደሩ ምንም ሳይተነፍስ እርጉዝ ፍየል የመሰለውን ማንቆርቆሪያ አንስቶ እሳት ላይ ጣደው።

የከባድ መሳሪያው ተኩስ ድምፅ እየዘገየ ያምባርቃል! ፊቴን ተጣጥቤ ከኩሽናው ደፍ ላይ አረፍ ከማለቴ ሻምበል በለጠ ከተፍ አለ። ብስል ቀይ ነው። ምክንያቱን ባላውቅም ነገረኛ ጠባዩ ተስማምቶኛል። ገና ከመምጣቱም በነገር ወጋኝ፣

"የታሉ ጓደኞችህ?"

"አላየሁዋቸሁም፤ አሁን ገና ከእንቅልፌ መንቃቴ ነው!"

"አሁን ገና!?" ሻምበል በለጠ አይኑን አፈጠጠብኝ!

በመደነቅም ሰአቱን ተመለከተ፣

"...ዛሬ ከነጋ ሃያ ወታደር ተገድሎብናል! እኛ ደግሞ ሃምሳ ገድለናል...እ....ሶስት መኪኖች ጋይተውብናል...እ...ከነጋ ብቻ ብዙ ታሪክ ተሰርቶአል! እና አንተ ቄንጠኛው ደግሞ ለጥ ብለህ አርፍደሃል!"

"ቅዝቃዜውና ድካሙ ነው መሰለኝ እንቅልፍ አሸነፈኝ!" አልኩ የጥፋተኝነት ስሜት እየተሰማኝ።

ሻምበሉ ተአምር የሰማ ያህል ቃላቶቼን ደገማቸው፣

"እንቅልፍ!? ቅዝቃዜ!? ቀልደኛ ነህ! ይህንን ንግግር ሌላ ቀን እንዳትደግም! ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ታውቃለህ? ትረሸናለህ! ምንድነው አስተምረው የላኩዋችሁ!? የመንግስት ሰራተኛ እንኩዋ እስከ ሶስት ሰአት አይተኛም!"

በቡጢ ደረቴ ላይ ጎሸመኝና ፈገግ አለ። ምክሩን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መቀበሌን ከልቤ አረጋገጥኩለት! ከቁርስ በሁዋላ ጓደኞቼን ፈለግሁዋቸው። ወደ ደብረታቦር ከተማ ሄደው ኖሮ ሳላገኛቸው ቀረሁ። እንደገና ምሳ ላይ በድጋሚ ከሻምበል በለጠ ጋር ተገናኘን። ያንኑ ኮቸሮ እየኮቸርን በቆርቆሮ ወጥ እያጣቀስን በመመገብ ላይ ሳለን ሻምበል በለጠ ስሜን ደግሞ ጠየቀኝና ነገርኩት!

"የስነፅሁፍ ችሎታ ያለህ አንተ ነህ ?"
ጥያቄው ተስፋ ስለጫረብኝ ነቃ ብዬ ምላሽ ሰጠሁ፣
"አዎን! እኔ ነኝ"
ዘግየት ብሎ ያልጠበኩትን ጥያቄ ጣል አደረገ፣
"ትግሬ ነህ እንዴ?"
"አዎን ነኝ" አልኩ።
"ከወዴትኛው?" አለ መልሶ።
"ማለት?" አልኩ ተደናግሮኝ።
"ኤርትራ ነህ ወይስ ትግራይ?"
"...ኤርትራ..."
"ትግርኛ ትችላለህ?"
"መስማት አይቸግረኝም"

ማምሻውን በድንኳኔ ጋደም ብዬ እያነበብኩ ሳለ ከሻምበል በለጠ የተላከ ወታደር በአስቸኳይ እንደምፈለግ ገለፀልኝ። የማነበውን መፅሃፍ አጥፌ ተነሳሁ። ሻምበል በለጠ ከድንኳኑ ደጃፍ ኩርሲው ላይ ተቀምጦ ሬድዮ ሲያዳምጥ ደረስሁ።

"አዳምጥና ትተረጉምልኛለህ!" ሲል አጣደፈኝ።

ሻእቢያ ጄኔራል አሊን ማርከውት ኖሮ እያናዘዙት ነበር። የሻእቢያ ጋዜጠኞች ጄኔራሉን ጥቂት በድምፅ አሰምተው ሲያበቁ፣ ትርጉሙን በትግርኛ የማንበብን አቀራረብ ነበር የሚጠቀሙት። ሃያ ደቂቃ የፈጀው ክፍል አንድ ቃለ - ምልልስ እንዳበቃ ትርጉሙን ጨምቄ ገለፅኩለት።

በምፅዋ ግንባር የተማረከው ጄኔራል የደርግ ሰራዊት በአመራር ብቃት ማነስ ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ መሄዱን፤ የሻእቢያ ሰራዊት በአንፃሩ በውጊያ የአመራር ጥበብ መጠናከሩን፤ የታጋዮቹ የመዋጋት ሞራልም ጠንካራ እንደሆነ አብነቶችን እየጠቀሰ ነበር ያብራራው። ደርግ የሻእቢያን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ማጥቃቶች መቋቋም እንዳቃተው፤ የደርግ ውድቀትና የሻእቢያ ድል ማድረግም አይቀሬ እንደሆነ ምርኮኛው ጀኔራል ተንብዮ ነበር። በሬድዮ የተላለፈውን ባጭሩ ተርጉሜለት ሳበቃ ሻምበል በለጠ ሲጋራውን ክፉኛ እየማገ፣

"መማረኩ ሳያንስ ምን ይሁን ብሎ ነው ታዲያ የሚለፈልፈው!?" ሲል ተነጫነጨ።

አስተያየት አልሰጠሁም። አስተያየት መስጠትም አይጠበቅብኝም ነበር። የተጠራሁበትን ተግባር በመፈፀሜ የሻምበሉን የስንብት ቃል ካንደበቱ ብጠብቅም ሳይሆን ቀረ። እየተነጫነጨ በጦርነቱ ዙሪያ ይደሰኩር ቀጠለ፣

"...ነገሩ ሁሉ የተበላሸው ጀኔራል ታሪኩ አይኔና ደምሴ ቡልቶ የተረሸኑ ጊዜ ነው" አለ ዝቅ ባለ ድምፅ "...ሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊት የፈረሰውና የሻእቢያ ድል የተረጋገጠው ያን ጊዜ ነው። እኔ ሁለቱንም ጀኔራሎች በደንብ አውቃቸዋለሁ። በዚህች ሃገር ላይ የታሪኩንና የደምሴን ያህል ወታደራዊ ሳይንስ የሚያውቅ ጀግና መኮንን አለ ቢሉኝ አላምንም! ለዘመቻ የተፈጠሩ ነበሩ። ግን ተረሸኑ። ሞት ብቻም አልበቃቸውም! በሞት ላይ ውርደት ተመረቀላቸው! ወታደሮች የጀኔራል ደምሴ ቡልቶን አንገት ቆርጠው፣ አንገቱን በገመድ አስረው ሲያበቁ፤ ታላቁ ኢትዮጵያዊ የጦር አርበኛ የታሰረበትን ገመድ እየጎተቱ፣ አስመራ ከተማን እየዞሩ ጨፈሩ። ይሄ ምን ማለት ነው?"

ሻምበሉ ይህን ሲነግረኝ የመናደድ ሳይሆን በስርአቱ ላይ ያለውን ጥላቻና ንቀት በሚያንፀባርቅ መልኩ ነበር። የሻምበሉ ሞራል ምስጥ እንደበላው አገዳ ቀፎውን እንደቀረ ለመገንዘብ አስቸጋሪ አልነበረም። ሻምበሉ አያይዞ በዚያው ንቀት አዘል ድምፁ አሉ የተባሉት የሃገሪቱ የውጊያ ጠቢባን ሁሉ በተለያየ መንገድ ህይወታቸውን እንዳጡ አጫወተኝ። ግዙፉና ተከብሮ የኖረው የኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት በአስመሳይና አቃጣሪ መኮንኖች መዳፍ ላይ መውደቁንም በምሬት አከለበት። ራሴን ላይ ታች እየነቀነቅሁ ከማዳመጥ በቀር አንዳችም ቃል አልተነፈስኩም። በጉዳዩ ላይ ማለት የምችለውም በመሰረቱ አልነበረም። ዝምታዬ ተጭኖት ይሁን በሌላ ባላውቅም ሻምበሉ የጀመረውን ርእሰ ጉዳይ እንደዋዛ ገትቶ፣

"እድሜህ ስንት ነው?" ሲል ጠየቀኝ።

"ሃያ አንድ"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ለምን ወታደር ቤት ገባህ?"

"አማራጭ ስራ ስላጣሁ ነው"

አያያዝኩና ጥቂት አወጋሁት።

ጋዜጠኛ የመሆን ፍላጎትና ዝንባሌ እንደነበረኝ፤ ፕሬስ መምሪያ በሪፖርተርነት ለመስራት አመልክቼ እንዳልተሳካልኝ፤ ለጦር ሃይሎች ሬድዮ ፅሁፍ አቀርብም እንደነበር፤ ምናልባት በዚያ በኩል ፍላጎቴን አገኝ ይሆናል በሚል ስሌት እዚህ ለመገኘት መብቃቴን አጫወትኩት።

ሻምበሉ ትክ ብሎ ካጤነኝ በሁዋላ፣

"ቁጥር አንድ ጅል ነህ!" አለኝ።

ሳቅሁኝ! ሻምበሉ ቀጠለ፣

"እውነቴን ነው፤ ብልህ አይደለህም፤ እንዴት አይነት ሂሳብ አስልተህ ነው በወታደር ቤት በኩል ጋዜጠኛ ለመሆን የሞከርከው?"

ሻምበሉ መልሶ የራሱን አባባል ይቃወም ጀመር፣

"...ለነገሩ ብልህ መሆን የትም አያደርስም! እኔ ብልህ ነኝ ብዬ አስባለሁ። ይሽው ግን እዚህ አብረን ቁጭ ብለናል። እንዲያውም የዋህ በግ መሆን ይሻላል! ፍየል ብልህ ሆና ምንም አላተረፈች!"

ይህን የሻምበሉን አባባል ከዚያ ወዲህ እንደ ህይወት መመሪያ የምጠቀምበት ሲሆን፤ በትክክልም አግዞኛል!

* * *

እየሱስ ተራራ በደረስን በሳምንቱ ሻምበል በለጠ የምደባ ክፍላችንን አሳወቀን። አስራ ስምንቱ ወጣት ካድሬዎች ወደፊት ግንባር ሲላኩ፤ እኔና አምዴ የተባለ ባልደረባዬ ከቀዳሚ መምሪያው ቀረን። ጉዋደኞቻችን በዚያኑ እለት ምሽት ተሰናብተውን እኛ ካለንበት አንፃር ሲታይ ይበልጥ እሳት ወደሚነድበት የውጊያ ቀጠና ተላኩ። በሁሉም ገፅታ ላይ ተስፋ ማጣት ይነበብ ነበር። ከእነርሱ አንዱ የቅርብ ወዳጄ የነበረ ሲሆን፤ ጣሰው ይባል ነበር፣

"አንተ ከኔ የተሻለ ያለመሞት እድል አለህ! መሞቴን ከሰማህ ለቤተሰቦቼ በዚህ አድራሻ ፃፍላቸው" ብሎ አድራሻውን ሰጠኝ።

"መጪውን ማንም አያውቅም" ስል ጣሰውን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አፅናናሁት። አያይዤም "...በልባችን ተስፋ ማሳደር ጠቃሚ ነው" አልኩት።

(... ስለ ጣሰው ከዚያ ወዲያ የሰማሁት ከዘጠኝ አመታት በሁዋላ "የቢሾፍቱ ቆሪጦች" የተባለውን መፅሃፌን ያሳተምኩ ጊዜ ነበር። ጣሰው ከተባለ ሰው በአድራሻዬ ደብዳቤ መጥቶልኝ ከፍቼ ሳነበው፤ ያ የደብረታቦሩ ወዳጄ መሆኑን ተረዳሁ። መፅሃፌን እንዳነበበ፣ አዋሳ መምህር ሆኖ እየሰራ እንደሆነና እንዳልሞተ የሚገልፅ አጭር ደብዳቤ ነበር...)

ከ603ኛ ኮር ቀዳሚ መምሪያ እንድመደብ የተደረገበትን ሚስጥር ምሽት ላይ አምዴ አጫወተኝ። እሱም እንደኔ "መልካም እድል" የገጠመው ነበር፣

"አንተ እዚህ የተመደብከው በስነፅሁፍ ችሎታህ ምክንያት ነው። ሻምበል በለጠ በጣም ወዶሃል" አለኝ።

"ሻምበሉ ስለኔ ችሎታ በምን አወቀ?"

"እዚህ የገባን ምሽት እኔ ተጠርቼ ስለያንዳንዳችን ተጠይቄ አብራርቼ ነበር። ያንተንም ነገርኳቸው"

"አንተስ እንዴት እዚህ መቅረት ቻልክ?"

"እኔ እንኳን ዘመድ ነው የነገረልኝ፤ ሻለቃ ይልማ የዘመዴ ጓደኛ ነው!"

በዚያን ሰሞን በተከታታይ ማምሻው ላይ ሻምበል በለጠ ወደ ድንኳኑ እያስጠራኝ የሻእቢያን ዜናዎች ያስተረጉመኝ ቀጠለ። ይህን ስራ በእጅጉ ነበር የወደድኩት። የሻእቢያ ጋዜጠኞች ድል ቅርብ መሆኑን ነበር የሚዘግቡት። አንድ ቀን ሻምበል በለጠ ስለ ኢሳይያስ አፈወርቂ አንስቶ እንዲህ አለኝ፣

"አደገኛ ሰው ነው!"

"ከምን አንፃር?" ስል ጠየቅሁ።

"ኤርትራውያንን ማስተባበር ችሎአል!"

"ወያኔዎችስ እንዴት ናቸው?"

"አብረው ነው የሚሰሩት። ከሃዲዎች!ምስጠች!"

ዘግየት አለና ደ'ሞ አከለበት፣

"ከሻእቢያ በላይ ወያኔዎችን እጠላለሁ"

"ለምን?"

"የራሳቸው አጀንዳ የላቸውም!"

በዚያው ሰሞን እኩለ ቀን ላይ ሻምበል በለጠ መፅሃፍ ሊዋሰኝ ወደ ድንኳኔ መጣ። ሻንጣዬን ከፍቼ ይመርጥ ዘንድ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ዘረገፍኩለት። ጥቂት ከመራረጠ በሁዋላ፣

"ወደ ግንባር ይህን ሁሉ መፅሃፍ ተሸክሞ መምጣት እስኪ ምን የሚሉት ነው?" ሲል በመገረም ጠየቀኝ።

"ስለምወዳቸው ነው"

"ጠባይህ ለወታደር ቤት አይሆንም"

"እንዴት?"

"ወታደር ቤት ምላሰኛ መሆን አለብህ፣ የኔ ወንድም! አንተ አትናገርም! ዝም ብለህ ታዳምጣለህ! ጭራው ጮሌ መሆን አለብህ እዚህ! በዚህ ጠባይህ ግን በቅርቡ ትሞታለህ!"

ዝም በማለቴ እሱ ቀጠለ፣

"እስኪ ስለ ወላጆችህ ንገረኝ?"

"ገበሬዎች ናቸው"

"ገበሬ? ገበሬ?"

"አዎን! አባቴ ያው ኤርትራ ሳለ ገበሬ ነበር። ኢላበርኢድ ላይ አትክልትና ፍራፍሬ ሲጭን ውሎ ከመኪናዋ ጋር ወደ አዲሳባ መጣ። ከዚያ ወዲያ አልተመለሰም። ደብረዘይት ላይ ለአርመኖች ዘበኛ ሆኖ መስራት ጀመረ። አሁንም ዘበኛ ነው። እናቴም ያው ኤርትራ መንደፈራ አካባቢ የአባቴ ሚስት ነበረች፣ ወደ ደብረዘይት ተከትላው መጣችና እኔና ወንድሞቼ ተወለድን። አሁን እናቴ በህይወት የለችም"

ሻምበል በለጠ ተክዞ ጥቂት ቆየ።

በተከፈተው ሻንጣዬ ውስጥ የተደረደሩትን መፃህፍትም እንደዋዛ እየፈታተሻቸው ከቆየ በሁዋላ፣

"መፅሃፍ ቅዱስ ደ'ሞ ምን ያደርግልሃል?" አለ።

እየሳቅሁ በመገረም አየሁት።

"ለምን ያዝከው?" ሲል መልሶ ጠየቀኝ።

"ለምን የያዝኩት ይመስልሃል?"

"በእግዚአብሄር ታምናለህ?"

"አምናለሁ!! በጣም አምናለሁ!"

ሻምበል በለጠ ራሱን ላይ ታች ሲነቀንቅ ቆየና፣

"የተረጋጋ ሁኔታ የሚታይብህ ለዚህ ነው!" አለ።

"አይደለም!" ስል ፈጥኜ ተቃወምኩ "...ዝም ስለምል ነው እንጂ ውስጤ የተረበሸ ነው! ርጋታና ሰላም በፍፁም የለኝም!"

"አትመስልም ግን!" አለ ዘግየት ብሎ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደገና በዝምታ አጤነው ጀመር።

* * *

ደብረታቦር በገባን በስምንተኛው ቀን፤ የካቲት አስር ምሽት ከሻምበል በለጠ ጋር ወደ ደብረታቦር ከተማ ወርደን ቢራ ጠጣን። የበግ ጥብስም ጋበዘኝ። በአብዛኛው እሱ ነበር የሚናገረው፤ ምንም እንኳን ቢራው ሞቅ ቢያደርገኝም ማዳመጡን መርጬ ነበር። ሻምበሉ በጦርነቱ ዙሪያ ወሬ ጀምሮ ስለ ሃይል የበላይነት ሚዛናዊ አስተያየቱን በግልፅነት ነገረኝ፣

"ምን መሰለህ? ፕሮፓጋንዳውና እውነታው ይለያያል! ነገ ቀኑ የካቲት 11 ነው አይደል? ወያኔዎች በማንኛውም ጊዜ ማጥቃት ሊከፍቱ ይችላሉ። የሻእቢያ ሚካናይዝድ ሃይል ገብቶላቸዋል የሚል መረጃ ሰምቻለሁ። ያሰቡት ነገር አለ ማለት ነው። እኛ የሃይል የበላይነት እንዳለን የመጣችሁ ጊዜ የነገርኳችሁ ውሸት ነው! በዚህ ወር ጦርነት ከከፈቱ ድራሻችንን ነው የሚያጠፉን! ለምን መሰለህ? ነብሮ ክፍለ ጦር ከዚህ ተነስቶ ወደ ምፅዋ መንገድ ተልኳል። ነብሮ ከዚህ መሄድ አልነበረበትም። በርግጥ ቀደም ሲልም ኤርትራ ነው የነበረው። ከሻእቢያ ጋር ሲፋለም ስለኖረ ብዙ ልምድ አለው፤ ገባህ? ወያኔ የእግረኛ ማጥቃትና ቆረጣ ላይ ጥሩ ችሎታ አዳብረዋል። በከባድ መሳሪያ ግን መሃይም ናቸው። ሻእቢያ ብዙ ጊዜ የማጥቃት ውጊያ አይመርጥም። በከባድ መሳሪያ ግን የበላይነት አላቸው። ተኩሰው የምሳ ሳህንህ ላይ ቁጭ ያደርጉልሃል!"

"የት ተማሩ የከባድ መሳሪያ ተኩስ?"

"ሶማሊያ! ዚያድ ባሬ ነው ያሰለጠናቸው"

አያያዘና እንዲህ አለኝ፣

"የሆነው ሆኖ የካቲት በሰላም ካለፈችልን ደብረታቦር ላይ ቢራ እየጠጣን እንሰነብታለን"

"የካቲት ለምን የተለየች ሆነች?" ስል ጠየቅሁት።

"የወያኔ የልደት በአል የካቲት ነው! እና በየካቲት በሚደረግ ጦርነት ድል እንደሚያደርጉ ያምናሉ!! ጠንቋዮች!!"

ሻምበል በለጠ ቢራውን እየገሰመ ቀጠለ፣

"ጠንቋይ ስልህ ጥንቆላ ማለቴ አይደለም። እለቱን ከተዋጊዎቻቸው ስነልቦና ጋር አዋህደው ሞራል ለመፍጠር ይጠቀሙበታል። ከሃዲዎች! ምስጦች!"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ጥቂት በዝምታ እንደቆየን፣

"ሩሲያ ስንት አመት ቆየህ?" ስል ጠየቅሁት፤ ሩሲያ መማሩን ሰምቼ ነበር።

"አምስት አመት" ሲል ፈጥኖ ምላሽ ሰጠኝ "...ጥሩ ጊዜ ነበር ያሳለፍኩት፤ እኔ ሙዚቃ እወዳለሁ። የሙዚቃ መሳሪያዎችንም አውቃለሁ። ልዩ ተሰጥኦ ነው ያለኝ። በተሰጠዬ ዙሪያ ብሰራ ውጤታማ እሆን ነበር። ግን እንዲያ ያለው ቦታ ለመመደብ ዘመድ ያስፈልግሃል! ከንቱ ነው! ኢትዮጵያ የተረገመች አገር! እጆችዋን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች ይላሉ! እጅ የላት፣ እግር የላት! የዶሎዶመች ዱሽ አገር! ከሚፀፅተኝ ታላቁ ነገር አንዱ ኢትዮጵያዊ መሆኔ ነው! ሻእቢያና ወያኔዎች እነማን ናቸው? ከሜዳ የወጡ ምስጦች! እና ከነሱ ጋር እየተዋጋሁ እድሜዬ ማለቅ አለበት!?"

ሲጋራውን እያምበለበለ አንዳች ነገር ሲያሰላስል ቆየና፣

"ለነገሩ እዚህም ቢሆን ከሙዚቃ አልተለየሁም። የመትረየሱ ድምፅ ሙዚቃ ማለት ነው" ብሎ በሳቅ ይንከተከት ቀጠለ። እኔም አጀብኩት።

ፈጥኜ ሰከርኩ።

ቢራው ጭንቅላቴ ላይ ስለወጣ አንድዋን ልጅ እግር የቡና ቤት ሴት ካልሳምኩሽ ብዬ አምባጓሮ ፈጠርኩ። በዚያም አላበቃሁ። 'ወድጄሻለሁ አግቢኝ' ብዬ ለገላጋይ ማስቸገር በመጀመሬ ሻምበል በለጠ ማጅራቴን አንቆ ይዞኝ ወጣ። እንደ ማሰሮ አንጠልጥሎ ከዋዝ ጂፓችን ላይ ከጎለተኝ በሁዋላ ወደ እየሱስ ተራራ መንዳት ጀመረ። በመንገዳችን ላይም እየሳቀ እንዲህ ይለኝ ነበር፣

"ድብቅ ጠባይ ያለህ ሰው ነህ... እንደ ቡና ድንገት ትፈላለህ እንዴ?..."

* * *

ሳምንቱን በአንፃራዊ ሰላም ካሳለፍን በሁዋላ፤ የካቲት 18 ምሽት ከሻምበል በለጠ ድንኳን ብቅ ስል፣

"ውጊያው ነገ ይጀመራል!" አለኝ፤ ከሰላምታ በፊት።

"የተረጋገጠ መረጃ ነው?"

"የተረጋገጠ!" አለኝ፤ በደረቀ ድምፅ "...የሻእቢያ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተዋጊዎች ከትናንት በስቲያ ጉና ገብተው አድረዋል። እኔም እኩለ ሌሊት ላይ ወደ ግንባር እየሄድኩ ነው። ውጊያ ሲጀመር ሃይል ማሚላት የሚባል ነገር ስላለ እዚህ አንድም ሰው አይቀርም። አንተ እዚሁ እንድትቆይ ትእዛዝ ሰጥቻለሁ"

ሃፊርሳኩን እያጠባበቀ ቆይቶ ቀና ሲል፣

"ጅል ነገር ነህ!" ካለኝ በሁዋላ አያይዞ፣ "... ለመሆኑ ሴት ነክተህ ታውቃለህ?" ሲል ጠየቀኝ።

መልስ ሳልሰጠው በፈገግታ ዝም ብዬ አየው ቀጠልሁ። "ጅል" ስላለኝ አልተከፋሁም። ከልጅነቴ ጀምሮ በተለያዩ መንገዶች "ጅል" መሆኔ እየተነገረኝና "ብልጥ" እንድሆን እየተመከርኩ ስላደግሁ ለምጄው ነበር። "ብልጥ" መሆን እችላለሁ ብዬ ማሰብ ባለመቻሌም ጅልነቴን በፀጋ ተቀብዬው ነበር። ብዙውን ጊዜም የብልጥነትና የጅልነት መለያዎችን ለማወቅ እየፈለግሁ ሳይሳካልኝ ቀርቶአል።

ሻምበሉ መናገሩን ቀጠለ፣

"በተቻለህ መጠን ላለመሞት ሞክር"

"ወያኔዎች የሚቀናቸው ይመስልሃል?" ስል ጠየቅሁት።

"ተዘጋጅተውበታል ነው የሚባለው። ነገ ለኛ ከባድ ጊዜ ነው። ካልተገናኘን እንግዲህ ለዘላለሙ ደህና ሁን!"

* * *

በነጋታው ከንጋቱ አስራ አንድ ሰአት ግድም ከእንቅልፍ የቀሰቀሰኝ ጆሮ የሚበጠርቀው የBM ሼል እየሱስ ተራራ ላይ ወድቆ ሲፈነዳ ነበር። ከድንኳኔ ብቅ ስል ምድር ቀውጢ ሆናለች። በደም የተፈተፈተ የሰው ስጋ በየቦታው ወድቆአል። በስቃይ የሚጮሁ ወታደሮች እየሱስ ተራራን አጨናንቀውታል። በፀጥታ ያሸለቡም ይታያሉ።

(የካቲት 19 እና 20 1982 በኢህአዴግና በደርግ መካከል የተደረገው አሰቃቂ ጦርነት በተለያየ መንገድ ብዙ ተብሎለታል። እኔ "ያልተመለሰው ባቡር" በተሰኘው ልቦለድ መፅሃፌ በመጠኑ ገልጬዋለሁ። የ603ኛ ኮር አዛዥ ብርጋዴር ጄኔራል አበበ ሃይለስላሴ ለኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያም ባቀረቡት ሪፖርት ያንን አሰቃቂ፣ አስገራሚና ከ17ሺህ በላይ ሬሳ የወደቀበትን ውጊያ በጥሩ ብእር ገልፀውታል። ሪፖርቱንም

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ" ቅፅ - አንድ ላይ አትሟዋለሁ። በኢህአዴግ ወገን የነበረው የውጊያ ሁኔታ በአቦነህ አሻግሬ ተፅፎ በተጠቀሰው መፅሃፍ ቅፅ - ሶስት ላይ ታትሞ ለንባብ በቅቶአል። በአሜሪካ በአንድ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ፕሮፌሰር የሆነው ገብሩ ታረቀ የደርግና የአማፅያንን የጦርነት ታሪክ ለማጥናት አዲስ አበባ በከተመ ጊዜ፤ ተገናኝተን ጥቂት ያወጋን ሲሆን፤ ጄኔራል አበበ ሃይለስላሴን እስር ቤት ድረስ ሄዶ ሊያነጋግረው እንደሞከረና ሰድቦ እንዳባረረው አጫውቶኛል።)

የካቲት 19 ምሽት ከጄኔራል አበበ ጋር በአንድ ምሽግ ተቀምጠን የነበረ ሲሆን፤ በዚያን እለት ሌሊት ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያምና ጄኔራል አበበ በወታደራዊ ሬድዮ መረጃ ሲለዋወጡ እኔ አጠገባቸው ተቀምጬ አዳምጥ ነበር።

በሁለተኛው ቀን የኢትዮጵያውያን ሬሳ በየመንገዱና በየተራራው እንደ አንሶላ ተነጥፎ በአሰቃቂ ሁኔታ ሽንፈት መከሰቱ ከታመነ በሁዋላ ወደ ባህርዳር እንድናፈገፍግ ጄኔራሉ አዘዙን። አብረውን የነበሩ ሴቶች በሄሊኮፕተር ከተሸኙ በሁዋላ ጄኔራል አበበን አጅበን በመኪና ሽሽት ጀመርን።

ብዙም ሳንጓዝ መንገዱ በተቃጠሉ ታንኮች ተዘጋ። በእግር ሸሸቱን ቀጠልን። በግምት አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ጄኔራሉን ካጀበው ቡድን ጋር አብሬ ሸሸቼ ነበር። በየመንገዱ የተመለከትኩት ሬሳ አእምሮዬን በጠበጠው። ጥቂት የማይባሉ በታንክ የተጨፈለቁ ጭንቅላቶችን እየዘለልን፣ በከባድ መሳሪያ የተገነጣጠሉ እጆችና እግሮች እያደናቀፉን፣ በተለይ ከታንኮች ጋር ያረሩ ሬሳዎች እያሳቀቁን ሸሸት ሆነ። ከተቃጠሉ ታንኮች የሚንበለበለው እሳት ገና አልጠፋም። ጣራቸው ተደርምሶ ከምድር ጋር የተረመጠጠ ጎጆዎችን አየሁ። የጎጆው ዙሪያ በደም ኩሬ ጨቅይቶአል። ጥይቶች ከየት እንደሚተኮሱ ለማወቅ ያዳግታል። የዶሽቃ ጥይት ማቋረጫ የለውም። ወታደሮች ከመሸሻቸው በፊት ያፈነዷቸው የጥይትና የቦምብ መጋዘኖች ደብረታቦርን ቀውጢ አድርገዋታል። የሚትጎለጎል የቢኤም ቁምቡላ ቢጫ ጢስ ደብረታቦርን ትንፋሽ አሳጥሮአታል። ሞት ረክሶአል። በማንኛዋም ደቂቃ አንገትህ ተቀንጥሶ ሊበር ይችላል። ዘባተሎ የለበሱ ገበሬዎች ባገኙት አቅጣጫ ሁሉ ከሞት ለማምለጥ እንደ ሚዳቋ እየዘለሉ ይበራሉ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሽሽቴን መቀጠል አልቻልኩም።

ሁለት ቀን ምግብ ካለማግኘቴም ባሻገር ለመሮጥ ቀርቶ ለመራመድ የሚያበቃ አቅም ፈፅሞ አልነበረኝም። ሽሽቱን አቆምኩና ከአንድ የጎርፍ መሂጃ ድልድይ ስር ተኛሁ።

የሻእቢያና የወያኔ ከባድ መሳሪያዎች እየተከታተሉ ካፈሩና ከምድሩ ይደባልቁናል። በቅርብ ርቀት የAK47 እና የካሊበር ጥይቶቻቸውን ያርከፈክፉብናል። ርቦኛል! ጠምቶኛል! ጃኬቴ እንኳ ስለከበደኝ አውልቄ ጥየዋለሁ። ሃፍረት ይዞኝ እንጂ ሽጉጤንም መጣል ፈልጌ ነበር። ሽጉጡን ለመተኮስ ይቅርና ቀና አድርጎ ለመያዝ የሚያበቃ ጉልበት የለኝም።

ከተኛሁበት ድልድይ ስር በርግጌ የወጣሁት የድልድዩ ግማሽ ጎን በከባድ መሳሪያ ተመትቶ ሲደረመስ ነበር። ከየት እንደመጣ ያልታወቀ ጉልበት በማግኘቴ ተፈትልኬ ወጥቼ ሩጫ ጀመርኩ። የአለምሳጋን ኮረብቶች ሽቅብ ስወጣ አምዴን አገኘሁት፣

"አልሞትክም!" ሲል በደስታ ጮኸ።

"አለሁ፤ አንተስ?"

"እኔም አለሁ"

ከፊልድ ጃኬቱ ኪስ አንድ የቲማቲም ቆርቆሮና ፋሻ አውጥቶ ሰጠኝ። የቲማቲሙን ቆርቆሮ በአምዴ የጠመንጃ ሳንጃ ቀዳድጄ ጥርግርግ አድርጌ በላሁት። ፋሻውን ኪሴ ጨምሬ ጉዞ ቀጠልን።

"ጠመንጃ ለምን አልያዝክም?" ሲል ጠየቀኝ።

"ሽጉጡም ከብዶኛል"

"ለማንኛውም ጠመንጃ ያዝ! ሰርጎ ገብ ነው ብለው ሊመቱህ ይችላሉ"

ሽጉጤን ከወገቤ አውጥቼ ጣልኩና በየመንገዱ ከወደቀው ሬሳ አንድ አጭር AK47 አንስቼ ታጥቄ ጉዞ ቀጠልኩ። የወያኔ BM ሼል ከጆርባችን ይደበድበናል። የካሊበር ጥይቶች የወታደሮችን ጭንቅላት ለሁለት እየሰነጠቁ የአሰቃቂ አሟሟት ትርኢት ያሳዩናል። ቀደም ሲል ቂም የነበራቸው ወታደሮችና መኮንኖች ርስበራስ ሲገዳደሉ አይቼ ትንፋሼ ሊቆም ደርሶ ነበር። የደብረዘይት ሚጎች ደግሞ እየተሳሳቱ እኛው ላይ ቦምባቸውን እያራገፉ ጀብድ እንደሰሩ ሁሉ እያጓሩ ይመለሳሉ። ሰማዩም ምድሩም እሳት ይነድበታል!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“አምዴ!”

“እህ!”

“እኛችንን ለምን ለወያኔ አንሰጥም?”

“አብደሃል!?” በመደነቅ እያየኝም “... የፕሮፓጋንዳ ሰራተኞች ስለሆንን ምላሳችንን ነው የሚቆርጡት!” አለ።

“አይነኩንም ግዴለህም! ይህ መንግስት ፈራሽ ነው! በዚህ ሁኔታ መሞት ደግሞ ቂልነት ነው”

አምዴ ዘግየት ብሎ እንዲህ አለኝ፣

“ዘመዶችህ ስለሆኑ ነው የተማመንክባቸው?”

በዚህ አነጋገሩ በጣም ተከፋሁ።

በዝምታ ጥቂት ተጓዝን።

“አምዴ እመነኝ! እኔ የቢሾፍቱ ልጅ ነኝ። እንደዚያ አስቤ አላውቅም። ሆኖም ለማንመሰገንበት ነገር መሞት ኪሳራ ነው...”

ዘግየት ብሎ፣

“አንተ እጅህን ስጥ! እኔ ግን አላደርገውም” አለኝ።

አምዴ የጎጃም ልጅ ነው – ደብረወርቅ። በጉዞ ወቅት እህቱ ቤት ገብተን ጠጅ በገንቦና ሙሉ በግ ተጋብዘን ነበር። እንግባባ ነበር። አምዴ ያን ከተናገረኝ በሁዋላ ግን እኔ እርምጃዬን ስቀንስ እሱ ፍጥነቱን ጨመረ። በዚያው ተለያየን።

(ከአምዴ ጋር ዳግም የተገናኘነው አዲስ አበባ አራት ኪሎ ላይ ደርግ ከወደቀ ከአራት አመታት በሁዋላ ሲሆን፤ በተገናኘን ጊዜ በወዳጅነት አብረን ሻይ ጠጥተን ተለያየን። ደብረታቦር ስለተለያየንባት ደቂቃ ግን ሁለታችንም የማንሳት ፍላጎት አልነበረንም። ዛሬ ላይ ቆሜ ሁሉንም ስገመግመው በዚያን ወቅት በኔና በአምዴ መካከል ለምን ልዩነት ተፈጠረ ብዬ ሳላስብ አልቀረሁም። በዚያች ደቂቃ የተለያየነው እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ስለወንበዴዎቹ የማውቀውና አምዴ የሚያውቀው የተለያየ ስለነበር ሊሆን ይችላል።)

የሆነው ሆኖ እኔ እርምጃዬን ስቀንስ አምዴ ፍጥነት ጨመረ። እንዲያም ሆኖ ከወያኔ ጋር በሰላም የመቀላቀል እድል አልገጠመኝም። የአለምሳጋን ሁለተኛውን ሰንሰለታማ ተራራ ሽቅቡን ወጥተን ጨርሰን ቁልቁለቱን ስንንደረደር የወያኔ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የደፈጣ ቡድን በተኮሰብን የመትረየስ ጥይት ውርጅብኝ በተራራው ተዳፋት ላይ ተረፈረፍን። አብረውኝ የነበሩት ከአስር ያላነሱ ወታደሮች አናታቸው እየተበረቀሰ፣ ልባቸው እየተነደለ፣ ሲያሸልቡ፣ እኔም ግራ እጄ ላይ ተቀልቤ እንደ ሙቀጫ ከላይ ወደ ታች ተንከባልዬ ከአንድ የግራር ግንድ ጋር ተጋጨሁ።

መሸቶ ነበር...

ከግራ እጄ የሚወጣውን ደም ለማቆም አምዴ የሰጠኝን ፋሻ ተጠቀምኩበት። የተበለቀጠውን ስጋ በፋሻው ከጠቀለልኩ በሁዋላ የተፈጠረውን ሁኔታ ግን ፊፅሞ አላውቀውም።

...ከግራና ከቀኝ የጅቦች ጩኸት ይሰማኛል። ድቅድቅ ያለ ጨለማ ውጦኛል። በፋሻ ጠፍሬ ያሰርኩት የተመታው እጄ ይመዘምዘኛል። ጨርሶ በመድከሜ ማሰብ ወደ ማቆሙ መሆኔ ይሰማኝ ነበር!

* * *

እንደ ሰመመን ካደረገኝ ድንዛዜ ስነቃ፣ ሰማዩ ላይ የተለጠፈች ብረት ምጣድ የምታክል ደማቅ ጨረቃ በቅርብ ርቀት ማየት ቻልኩ። አንድ ግንድ ተደግፌ ተኝቻለሁ። የግራ እጄ ጣቶች ላይ ህመም ተሰማኝ። ማበጣቸውን አስተዋልኩ።

እኔ ማን ነኝ? የት ነው ያለሁት?

ከሰከንዶች በሁዋላ የመጠሪያ ስሜን አስታወስኩ። በመቀጠል ጦርነት ውስጥ እንደ ነበርኩ ትዝ አለኝ። ብርድ እያንቀጠቀጠኝ ነበር። ሸሚዝ ብቻ መልበሴን አወቅሁ። ብርድ ልብስ አስፈልጎኛል። ገልበጥ ስል ከጎኔ አንድ የተኛ ሰው መኖሩን አስተዋልኩ። ትክ ብዬ አየሁት። ጭንቅላቱ ለሁለት ተገምሶአል። ደም ወይም ስጋ ሳይሆን ነጣ ያለ የጎደጎደ የራስ ቅል ነበር የሚታየኝ። የሞተው ወታደር ሬንጀር ጃኬት ለብሶአል። ጃኬቱን ከራሳው ለማላቀቅ ምን ያህል ጊዜ እንደታገልኩ አላውቅም። ሆኖም ተሳካልኝና ከሚቹ ወታደር ላይ አውልቄ ለራሴ ለበስኩት። ትንፋሼ መለስ አለልኝ። በመቀጠል ለዚያ ለተቆረሰ ጭንቅላት ጀርባዬን ሰጠሁና ተኛሁ። ብርዱን ለመቀነስ ሁለት እግሮቼን እስከ አገጬ በማጠፍ ተጠቀለልኩ።

እንደገና የነቃሁት የተኩስ ድምፅ ሰምቼ ሲሆን፤ አይኖቼን ስከፍት ወጣት የወያኔ ተዋጊዎች የሞተና ያልሞተውን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሬሳ እየለዩና እየፈተሹ ከእጆች ላይ ሰአት ሲያወልቁ፣ ከኪሶች ገንዘብ ሲሰበስቡ አየሁ። በጣም የተጎዱትንና በማጣጣር ላይ ያሉ ወታደሮችንም እየተኮሱ ይጨርሱዋቸው ነበር። ጨረቃዋ የለችም። ሰማዩ ወገግ ብሎአል።

'አልሞትኩም!' ለማለት ቀና ስል ግንዲላ የሚያካክሉ ትላልቅ እግሮች ካሉት፤ ጠይም አፍሮ፣ አጭር ቁምጣ ከለበሰ፣ ዝናር ከጠመጠመና መትረየስ ከተሸከመ የወያኔ ተዋጊ ጋር አይን ለአይን ተጋጨን። እንደሌሎቹ እኔንም በአንድ ጥይት ያሰናብተኛል ብዬ ተስፋ በመቁረጥ እመለከተው ጀመር፣

"ተጎድተሃል?" ሲል በትግርኛ ጠየቀኝ።

"ደህና ነኝ" ስል በአማርኛ መለስኩ።

"ተነስ እሞ ምጣ!" አለኝ በተኮላተፈ አማርኛ።

ተነስቼ አጠገቡ እንደደረስኩ ከሃረር ከተማ በ15 ብር የገዛሁዋትን ዲስኮ ሰአቴን ፈታሁና እንዲቀበለኝ ዘረጋሁለት።

አልተቀበለኝም! በትህትና ፈገግ አለ።

እነሆ ተማረክሁ ማለት ነው! የጦር ምርኮኛ ሆንኩ!

በዚያን እለት ረፋዱ ላይ ከኪሴ ብጫቂ ወረቀትና ብእር በማግኘቴ እንደሚከተለው ማስፈር ቻልኩ...

(....አገሩ በሬሳ ተሞልቶአል። የሰው ልጅ ይህን የመሰለ አሰቃቂ ልምድ ባይገጥመው ይመረጣል። በሞት መስመር ላይ በሁለቱም ወገን የተገኘነው የገበሬና የድሃ ልጆች ነን። ለማን ጥቅም እንደምንገዳደል በፍፁም አናውቅም።

....የአለምሳጋ ተራሮች በሰቃይ ድምፆች ተሞልተዋል። የተበተነው ወታደር በደንቢያና በፎገራ፣ በውዶና በደራ፣ በአለፋና በጣቁሳ ሜዳዎች ተረጭቶ ይባዝናል። በአዲስዘመን፣ በእብናት፣ በደንማ፣ በቆላ ሃሙሲት፣ በጃን አሞራ፣ በአምባራስ፣ በደባርቅና በዳባት መንገዶች የእውር ድንብሩን ይዳክራል። በውሃ ጥም የተቃጠሉ እነዚህ የድሃና የገበሬ ልጆች የምንጭ አገር የተባለችውን በጌምድር አራሀዋን፣ ተረተር ጢሻ ሸንተረርዋን፣ እያሰሱ ነው። ጭንጫ ውሃ የት ነህ? እንቁራሪት ምንጭ፣ አለምበጣር ምንጭ፣ ጃንተከል ምንጭ፣ አውዛ ምንጭ የት ናችሁ? ለዛሬ ካልሆናችሁ ለመቼ ልትሆኑ ነው? በመፅሃፍና በካርታ ያነበብናችሁ፣ ገብርዬና ካሳ እግራቸውን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የተለቃለቁባችሁ፣ እነ ጡንጇት ወንዝ፣ ሳሙና በር ምንጭ፣ ድብኮ ወንዝ ሽረ ወዴት ናችሁ? በየዜማው የምንሰማችሁ የጎንደር አርባራቱ ታቦታት ይህ ሁሉ የገበሬ ልጅ በማያውቀው ምክንያት እንዲህ በእሳት ሲቆላ ምነው ደውላችሁ ሳይሰማ ቀረ?)

* * *

የማረኩኝን ታጋዮች ወደ አዛዦቸው እንዲወስዱኝ በተሰባበረ ትግርኛ ጠየቅሁዋቸው። ምግብ ባላገኝም፣ ነፍስን ማቆየት የሚችል ክቡር የእግዜር ውሃ እየጠጡ፣ አንዱ ወደ ሌላው እያቀባበለኝ ጆቤ ወይም አበበ ከተባለ ሰው ዘንድ አደረሱኝ። የዛሬው ጄኔራል አበበ ተክለሃይማኖት በወቅቱ በወያኔ ወገን የግንባሩ አዛዥ ነበር። በደብረታቦር ግንባር የተዋጉት የሁለቱም ወገን አዛዦች ስማቸው አበበ የመሆኑን አጋጣሚ በብጫቂ ወረቀት ላይ በማስፈር የተፈጥሮና የተሰጥኦ ግዴታዬን መፈፀሙን ቀጠልኩ። እነሆ! ከደርግ "አበበ" ወደ ወያኔ "አበበ" ተዘዋወርኩ። ጊዜ እንዳስቀመጡት አይገኝምና ዛሬ ሁለቱም አበበዎች የመለስ ዜናዊ ሰለባ ሆነዋል።

ጆቤ ዘንድ እንደደረስኩ ከኔ መረጃ ለማግኘት ጓጉቶ ነበር ተቀብሎ ያነጋገረኝ። እሱ የሚፈልገው መረጃ ግን እኔ ዘንድ አልነበረም።

"የደርግን ስርአት ለመጣል በሚደረገው ትግል መሳተፍ እፈልጋለሁ" አልኩት።

ጆቤ የኔን ጥያቄ ዘልሎ የራሱን ጥያቄ አስከተለ፣

"ጄኔራል አበበ የት ነው ያለው?"

"እስከ ዋዶሜዳ ድረስ አብረን ሸሽተን ነበር። ከዚያ ወዲያ ግን ስለተለያየን በየት አቅጣጫ እንደሄደ አላውቅም" አልኩ።

ጆቤ ስለማንነቴ፣ ስለ ፍላጎቴ፣ እንዲሁም ያለፉ ታሪኬን ለማወቅ ግማሽ ሰአት ያህል በጥያቄ ካዋከበኝ በሁዋላ ያለመጠራጠርና በእርካታ የመታገል ጥያቄዬን መቀበሉን እዚያው አረጋገጠልኝ። ጆቤ በዚያው ፍጥነት ወደ ትግሉ እንድቀላቀል የወሰነው ከደርግ ጋር ሃያ ቀናት ብቻ መቆየቴን ሲያውቅና የእድሜዬንም ሁኔታ ገምግሞ ይመስለኛል። እያሱ በርሄ የተባለ ሰው ከተጠራ በሁዋላም እንድንተዋወቅ ጋበዘን። እያሱ የህወሃት የባህል ክፍል ሃላፊና ድምፃዊ መሆኑን ተረዳሁ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የመታገል ጥያቄዬ በእያሱ በኩል ተፈፃሚ እንደሚሆን ነግሮ አሰናበተኝ።

ጆቤን ተሰናብቼ ከእያሱ ጋር እንደወጣን እያሱ እንደ ፊኛ የተነረቱ ጣቶቼን እየነካካ ህክምና ላገኝ ወደ ምችልበት ቦታ ሊወስደኝ አሳብ አቀረበ። እኔ ግን ተቃወምኩ። በጣም እንደተራብኩ ነገርኩት። ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ጉሮሮዬ የዘለቀው ምግብ ጥቂት የቆርቆሮ ቲማቲም ብቻ ሲሆን፣ ይህም ከሰላሳ ሰአታት በፊት ነበር። እያሱ በርሄ ወደ ምግብ ቤት ወስዶ የበግ ጥብስ ካዘዘልኝ በሁዋላ በዝምታ ይመለከተኝ ጀመር። አውሬ ሆኜ ነበር። አንዳችም ቃል ሳልተነፍስ ምግቡን በልቼ አንድ ብርጭቆ ውሃ ከጠጣሁ በሁዋላ ነፍሴ መለስ አለች። አይኔም ተከፈተ። ምግብ የማግኘትና ምግብ የማጣትን ልዩነት በዚያች ሰሞን በትክክል ተረዳሁዋቸው።

ከእያሱ በርሄ ጋር ከምግብ ቤቱ ወጥተን ወደ ደብረታቦር መሃል ከተማ ስናመራ ያልተጠበቀ ትርኢት ከአይኖቼ ገፅ ተከሰተ። ከተማዋ AK47 በታጠቁ በሺዎች የሚገመቱ የደርግ ወታደሮች ተጥለቅልቃለች።

ማመን አቃተኝ።

ምርኮኛ ወታደሮች በየመጋዘኑ እስር ላይ ስለነበሩ ለምን እንደተለቀቁ ማሰብ አልቻልኩም። አንዳንዶቹ ወታደሮች ከህወሃት ታጋዮች ጋር በሞቀ ሁኔታ ሲተቃቀፉ፣ ሲስቁና ሲያወሩ በማየቴ የማየውን ማመን ባለመቻሌ ተጣድፌ ስለ ሁኔታው እያሱን ጠየቅሁት፣

"ለሁለተኛ ጊዜ የተማረኩ ወታደሮች ናቸው።" ካለ በሁዋላ ያብራራልኝ ያዘ፣ "...ሽሬ ላይ 604ኛ ኮር ሲደመሰስ የተማረኩት ወታደሮች ትምህርት ተሰጥቶአቸው ወደ የቤተሰቦቻቸው ይሄዱ ዘንድ ተለቀው ነበር። ደርግ ሰብስቦ እንደገና ለውጊያ አሰለፋቸው። በዚህ ውጊያ ግን አንድም ጥይት አልተኩሱብንም። በየት አቅጣጫ እንደሚገኙም ልከውብን ስለነበር እኛም አልተኩስንባቸውም"

አስገራሚው ትርኢት ቀጠለ፣

በእየሱስ ተራራ ቀዳሚ መምሪያ በሾፌርነት ይሰራ የነበረ አንድ ወታደር ከእያሱ ጋር በሞቀ ሁኔታ ተቃቅፈው ተሳሳሙ። ወታደሩ ጠመንጃውን እንዳነገተ ነበር። እያሱ እየሳቀ ይተርበው ገባ፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ይኸው ተመልሰህ መጣህ። ነግረንህ ነበር። መታገል ይሻልሃል!”

ወታደሩ ሲጋራውን እያቦነነ መልስ ሰጠ፣

“መታገሉን መቼ ጠላሁት እያሱ! እንዳልኩህ ግን ሁለት ልጆች አሉኝ። የሚረዳቸው ዘመድ የለኝም። ደርግ መቼ እንደሚወድቅ ደግሞ ማንም ቢሆን ርግጠኛ መሆን አይችልም። መንፈሴ ተረጋግቶ ልታገል አልችልም።”

“አሁንም መሄድ አስበሃል?”

“አማራጭ የለኝም፣ እያሱ”

“በድጋሚ ከያዙህ ግን ሰላይ ነው ብለው ይረሽኑሃል”

“እንደምንም አዲስ አበባ እገባለሁ”

“መቼ ልትሄድ ነው ታዲያ?”

“ዛሬ ማታ አስቤያለሁ”

“ለምን ወደ ሱዳን አትሄድም?’

“ልጆቼን ማየት አለብኝ፣ እያሱ”

...ከአስር ቀናት በሁዋላ በእያሱ ከሚመራው የባህል ቡድን ጋር ተዳብዬ ጉዞ ወደ ትግራይ ሆነ። የጉዞው መድረሻችን አዴት ነው። አክሱም ከተማን አልፎ ከሚገኘው አዴት ከተባለው ገደላማ ወረዳ የአህዴድ ምስረታ እየተካሄደ ስለነበር በምስረታው ማጠቃለያ ላይ የባህል ቡድኑ የሙዚቃ ትርኢት እንዲያቀርብ ሰለታዘዘ ጉዞአችን ወደዚያው መሆኑን እያሱ አጫውቶኛል። በመንገዳችን ላይም በአድዋና በአክሱም ተመሳሳይ የሙዚቃ ትርኢት እንዲያቀርብ የኪነት ቡድኑ ታዞአል። ይህም ጉዞ ለኔ በርካታ ልምድ ያገኘሁበት ልዩ አጋጣሚ ለመሆን በቅቶአል።

ወደ ወያኔ ካምፕ በገባሁበት በዚያን ወቅት ያለምንም ማጋነን ደርግና ወያኔ የሚዋጉበትን ትክክለኛ ምክንያት በቅጡ አላውቀውም ነበር። ደርግ በሬድዮ የሚናገረውን አላምነውም። አማፅያኑ የሚሰብኩትን ደግሞ የመስማት አጋጣሚው አልነበረኝም። በአናቱ ለፖለቲካ አጀንዳዎች ቀዝቃዛ ስለነበርኩ በትንሿ ጭንቅላቴ ውስጥ “ስራ ማግኘት” የሚል ቃል ብቻ ነግሶ ነበር።

በቀላል ቋንቋ ለመግለፅ መጀመሪያ “ወያኔን በቃላት መስደብ” የተባለ ስራ አገኘሁና በወር 300 ብር ሂሳብ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተቀጠርኩ። ወያኔን ለመስደብ ቃላት እያጠራቀምኩ ሳለ ወያኔዎች ተረከቡኝና "ደርግን ከስልጣኑ ማውረድ" የተባለ ሌላ ስራ ሰጡኝ። ይሄኛው ስራ ደሞዝ ባይኖረውም የተሻለ መስሎ ተሰምቶኛል።

በርግጥም "ታጋይ" የተባለው ማእረግ አልተዋሃደኝም ነበር። ቢሆንም ያለፈተናና ያለጥረት የ"ታጋይነት" ካባ ሲደረብልኝ ደስታን በገመቹ አባዝቼ ሃጎስ ሆኛለሁ። ወያኔ ማለት "አብዮት" ማለት መሆኑን ጓዶቼ ነግረውኛል። መመሪያችንና ጋዜጣችን ደግሞ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ሰራዊታችን "አብዮታዊ ሰራዊት" ያልተባለው ደርግ ቃሉን ለጥቂት ስለ ቀደመን ነበር። ስለዚህ "ህዝባዊ ሰራዊት" ተብሎአል።

(ኢህአፓ "እናሸንፋለን" እና "እናቸንፋለን" የሚለውን ልዩነት እንደ መለያው ይወስደው እንደነበረው እዚህም "ወዛደር" በ"ላባደር" ተለውጦ ጠበቀኝ። ደርግ የሰራዊቱን ክፍሎች "ነብሮ" "አንበሳው" እያለ ሲጠራ፣ ወያኔ ደግሞ፣ "አሉላ" "አቃቂ" እያለ ሰይሞአል። "አቃቂ" የሚለው የከተማ ስም የተመረጠው የፋብሪካ መናሸሪያ በሆነችው አቃቂ ብዙ ላባደር አለ በሚል ሲሆን፣ ኢህአዴግ ነፃ ባወጣቸው ከተሞች ገበሬ እንጂ ላባደር ገና ባለማግኘቱ ላባደሮች ይናፍቁት ነበር። ኢህአዴግና ላባደሮች ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙት ባህር ዳር ሲያዝ ነበር። ታጋዮቹ ከአውሰትራሊያ እንደመጣ ልዩ አውሬ ላባደሮችን ለማየት በጣም ጓጉተው እንደነበር ትዝ ይለኛል። ዛሬ ግን ወያኔና ላባደሮች እሳትና ጭድ ሆነዋል። ምን እንደበደሉት ባይታወቅም አዳልጦት እንኳ ሰማቸውን አያነሳም።)

የሆነው ሆኖ አብዮታዊ መስመራችን ለአርሶ አደሩ፣ ለላባደሩና ለጭቁን ህዝቦች ይታገላል። ትርጉሙን ባልረዳውም አብዮታዊ ዴሞክራሲ የተባለውን የድርጅት ርእዮተ አለም እንደ ቀበቶ ታጥቄ ከአብዮታዊ ሰዎች መሃል ለመገኘት በቅቻለሁ። በርግጥ እስከዛሬም አብዮታዊ የሚባለው የዴሞክራሲ አይነት ወይም ርእዮተ አለም ሊገባኝ አልቻለም። ከፊሉ ታጋይም እንዲሁ እንደኔው ርእዮተአለሙ ሳይገባው፣ እግር እየጣለው የታገለ ነበር። ፍየሉን በተኩላ ተነጥቆ አባቱ እንዳይገርፈው ሸሽቶ ለመታገል የበቃው ጥቂት እንዳይደለ ቤተኛ ከሆንኩ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በሁዋላ ተረድቼዋለሁ። ታጋይ ነኝ ማለቱ ግን አልቀረም። ስለዚህ እኔም ታጋይ ነኝ። በአጠቃላይ ግን ጉዞው ወደ ተሻለ ዘመን እንደሚሆን ተስፋ ለማድረግ ፖለቲከኛ መሆን አያሻም ነበር።

* * *

"ታጋይ" ከሆንኩ በሁዋላ መጀመሪያ የተገነዘብኩት እውቀት ቢኖር ጆርጅ ኦርዌል 1984 ላይ የተቸውን ከመሰለው አስተዳደር በቀላሉ እንደማንላቀቅ ነበር። ተግባርና ቲዎሪ እንደማይገናኙ ሁለት መንታ መስመሮች መሳ ለመሳ ይጓዛሉ። መቶ ሰአት ተሰብስበህ ፖለቲካ ትፈተፍታለህ። አንድ አገር ሙሉ ሰበካ ትሰበካለህ። አንድ ጨቅላ ካድሬ አንተ ከምትገነዘበው በታች ጨዋነትና ትህትና በጎደለው ሁኔታ ሲሰብክህና ሲገመግምህ ይውላል። ጉድጓድ ውስጥ ያለች እንቁራሪት የሰማዩ ስፋት ከጉድጓዱ አፍ አይተልቅም ብላ ታስባለች። ያንን አስተሳሰብዋን ለማስለወጥ አንዳችም መንገድ የለም። እንቁራሪት ሆነህ ተወልደህ በእንቁራሪትኛ ብትነግራት እንኳ ተስፋ አይኖርህም። ደርግ ስለ "አንድነት" ስለሚጮህ አንድነት የሚለው ቃል የጠላት ቋንቋ ሆኖአል። ኢህአፓ "መድብለ ፓርቲ" እያለ ስለሚናገር አንድ ካድሬ ይነሳና አፉን ሞልቶ ቃሉ የያዘውን ሃሳብ ሲዘረጥጠው ትሰማለህ። በሬድዮ ጭምር በግጥም! ታጋዩ ሁሉ ገጣሚ ነበር። ግዙፍ ሃሳብ ያዘሉ የፖለቲካ ቃላት እንደ ተበሳ ጣሳ ወድቀው ሲንገላቱ ታያቸዋለህ። "ህዝብ" ማለት አንተን የማይወክል፣ ከሰው በላይ የገዘፈ መቅደስ ሆኖ ቁጭ ብሎአል። "ህዝቡ" እያሉ ሲደሰኩሩ ህዝብ የግለሰቦች ጥርቅም ሳይሆን፣ ሰማይ ላይ ቁጭ ያለ ሃያል አምላክ መስሎ ይሰማሃል። ከገበሬ የተውጣጡት ካድሬዎች መቼም ቢሆን ወደ እርሻ ስራቸው እንደማይመለሱ ግልፅ ሆኖአል። አደገኛው ዝንባሌ ደግሞ የእውቀትን ጫፍ እንደቆነጠጡ እርግጠኛ መሆናቸው ነበር። ይህን ሁኔታ ስገነዘብ ፍርሃት ይወረኝ ነበር። "ጭቁንና ጨቋኝ" የተባሉትን ቃላት ሲጠሩ በቀልና ቂም ቋጥረው መሆኑን አስተውያለሁ። ጭቁኑ ወይም ተጨቋኙ ብሄር ወደ ጨቋኝነት ሊለወጥ እንደሚችል አንዳችም ግንዛቤ የለም። ጭቁንነት እንደ ዘርና ሃይማኖት ባለበት የሚቆይና መቆየትም ያለበት ስለመሆኑ የሚያስተምሩ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ካድሬዎች ድርጅቱን ወረውታል። ኢዲዩ የፖለቲካ ፕሮግራም ነድፎ የሚሰራ ፓርቲ ሳይሆን፣ አጭር፣ ቦርጫም፣ ከዘራ የሚይዝ፣ ክብ የሰሌን ባርኔጣ ያደረገ፣ ሽምገል ያለ ባላባት የሚመስላቸው ይበዙ ነበር።

ከደርግ "አብዮታዊ" ርእዮተአለም ምን እንዳገኘን መቼም አንረሳውም። ንግድ ሚኒስቴር እንጀራና ሽሮ የሚቸረችሩ ሱቆችን ከፈተ። ብሄራዊ ቴአትር ደግሞ "ቴዎድሮስ" የተባለ ቴአትር ለህዝብ አቀረበ። ቴአትሩን ያየን ሰሞን አብዮታዊ መሪያችን፣

"ወጣቶች ሆይ! ኮሌጅ ውስጥ ቦታ ስለሌለ ወታደር ትሆናላችሁ። እንደ ቴዎድሮስ ሽጉጥ ጠጥታችሁም ሙቱ! እኛም ቢሆን አዋጊ እንድንሆን ታሪክ አደራ ጥሎብን ነውንጂ አንድ ጥይትና አንድ ሽጉጥ ስትቀረን እስዋን ጠጥተን መሞታችን አይቀርም። ይህቺ ሃገርስ ያለ እናንተ ማን አላት?" የሚል ጨዋታ አመጡ።

ቁንቁው ተለወጠ እንጂ በኢህአዴግ ወገንም ተመሳሳይ ዜማ እየተዜመ ነበር የጠበቀኝ።

የሆነው ሆኖ ወደ ወያኔ ካምፕ ከተላለፍኩ በሁዋላ ሁለት ምርጫዎች እጄ ላይ ነበሩ። ወደ ሰለጠነው አለም መሰደድ፣ አለያም ለውጥ ለማምጣት መታገል። በኔ በኩል ሁለቱም የሚስማሙኝ አልነበሩም። ለመሰደድም ሆነ ለመታገል ዝግጁ አልነበርኩም። ከተሰደድኩ ደራሲ መሆን አልችልም። የመታገል ወኔው ደግሞ አልነበረኝም። መፍትሄ ሆኖ ያገኘሁት ከሚታገሉት መሃል መሰንበትን ነበር።

ይሁን እንጂ ለደርግ አላማ ህይወቴን መስጠት እንዳልፈለኩት ሁሉ፣ ኢህአዴግ የሚያካሂደው ፖለቲካም ቀልቤን የሚስብ ሆኖ አላገኘሁትም። ህይወት እንደ ጊዜና ገንዘብ አይደለም። ጊዜህንና ገንዘብህን በከፊል ለምታምንበት አላማ ልትሰዋ ትችላለህ። ህይወት ግን መተኪያ የላትም። ልብህ ለተቀበለው አላማ ህይወትህን ትሰጥ እንደሁ እንጂ በእግረ መንገድ ህይወትህን እንደ አረጀ ሽሚዝ የትም ልትወረውራት አይገባም ብዬ አምናለሁ።

ስለ አላማ የምናወጋ ከሆነ በዚያን ወቅት ህይወቴን ልሰጠው የምችለው አላማ በእጄ ላይ አልነበረም። ምኞትና ህልሜ ደራሲና ጋዜጠኛ መሆን እንደመሆኑ፣ ታጋይነትን ወደ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ምኞቴ እንደሚያደርሰኝ መልካም አጋጣሚና ጊዜያዊ ስራ ተቀብዬው ነበር።

* * *

የደብረታቦርን ውጊያ አስመልክቶ የፃፍኩት ሪፖርታዥ በኢህአዴግ ሬድዮ ተደጋግሞ በመነበቡ የባህል ቡድኑ አባላት ባንድ አፍታ ለኔ ያላቸው አመለካከት ተቀየረ። አክብሮታቸውን ጫኑልኝ። ይበልጥ ይንከባከቡኝ ጀመር።

ጠዋት ጠዋት ማሚት ሃኪም ቁስሌን እያጠበች ፋሻ ትቀይርልኛለች። ቤዝ እና ሊድ ጊታር ተጫዋቾቹ ወዲ ሰቦቃና ከድር ይበልጥ ጓደኞቼ ሆነዋል። ስለ አዲስአበባ እየጠየቁኝ ብዙ አጫወትኳቸው። ቁስለኛ እንደመሆኔ በጉዞ ወቅት የማርቸዲሱን የጭነት መኪና ጋቢና ከእያሱ ጋር እንድጋራ ተደርጓል። ጠያይምና ቆንጆ ድምፃውያን ሴት ታጋዮች አጭር AK47 ታጥቀው ከጃዝና ከፒያኖዎች ጋር ከሁዋላ ይጫናሉ። ከእነዚያ ደጋግ፣ ግልፅና ፈገግታ ልዩ መለያቸው ከሆኑት የገበሬ ልጆች ጋር ማውጋት ልዩ ደስታ ያሳድርብኝ ጀመር። የትግርኛ ቋንቋ ችሎታዬን ለማሻሻል ጥረት ማድረጌንም ቀጠልኩ። በተለይም ከማሚት ሃኪም ጋር በጣም ተግባባን። ቁስሌን ስትቀይርልኝ ምንጊዜም ታንጎራጉራለች። ብዙውን ጊዜ "ውፈር ተበገስ" ወይም "ተነስ ዝመት" የተባለውን ዜማ ነበር የምታንጎራጉረው። ዜማውን ዘፈን ከማለት "ዜና ትንታኔ" ቢባል ይቀል ነበር፣ ዘፈኑ ባማርኛ ሲተረጎም እንዲህ የሚሉ ስንኞችን አቅፎአል፣

ባለ ግመሎቹ! ባለ በቅሎዎቹ!
ልጆቻችሁ! እነዚያ ጀግኖቹ!
እየገሰገሱ ካራ ምሽግን ይዘዋል!
የማርቸዲሱ ሾፌር ገሰገሰ!
ሰራዊታችን ቆቦን ረመጠጠ!
ወልዲያን አንቀጠቀጠ!
የደርግ ሰራዊት ተበተነ!
ነፃ ያወጣናቸው ሌሎች ህዝቦች!
በኛ በጣም ኮርተዋል!
ድጋፋቸውን ሰጥተውናል...

አንዳንድ ጊዜም የእያሱ በርሄን "ጎራው ጀግንዬ"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የተባለ፣ በተመሳሳይ ዜና የሚመስል የአማርኛ ዘፈን ታዜማለች። እሱም እንዲህ ይል ነበር፣

አላማጣ ቆቦ፣
በጀግናው ተከቦ፣
ሮቢት ዶሮ ግብር፣
ተቆርጦ ሲያጣጥር፣
መች ሆነልኝ ብሎ፣
ማይጨው ፈረሰ፣
ሄደ ሰራዊቱ እየገሰገሰ፣
ደሴ አዲሳበባም በጭንቀት ታመሰ፣

ከጥቂት ጊዜያት በሁዋላ እኔም ዘፈኑን እንደ ቀልድ ጀምሬው እየወደድኩት ስለመጣሁ ከማሚት ጋር አብረን መዝፈን ጀመርን። ግጥሙን በደንብ ስላልያዝኩት የራሴን እየጨማመርኩ ስዘፍን ማሚት በሳቅ ትዘምራለች፣

አባይን ተሻግሮ - ሸዋ ላይ ተኮሰ፣
በየረር አቋርጦ - ቢሾፍቱ ደረሰ፣
አዋሽና አርሲ - ድሬ ላይ ነገሰ፣
የዱከምን ሰንጋ - እየተቋደሰ፣
ጀግናው ባለበቅሎ - እንጦጦ ቀደሰ፣

"እንጦጦ ምንድነው?"ስትል ጠየቀቺኝ።
"አዲስ አበባ"
"ድሬ ምንድነው?"
"ድሬዳዋ ነዋ! ከተማ ነው"
"የረር ያልከውስ?"
"በጣም ትልቅ ተራራ ነው"
"ቢሾፍቱስ?"
"እሱ እኔ የተወለድኩበት ሃይቅ ነው"
"የት ነው ያሉት እነዚህ ሁሉ"
"ወደ መሃል አገር"
ማሚት ተቃወመቺኝ፣
"ምን ችግር አለው?" ስል ጠየቅሁዋት።
"ከተሞቹ ገና ሳይያዙ እንደዚያ ሊዘፈን አይችልም"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"መያዛቸው አይቀርም! ደሞም ትንቢት ነው"

"የዱከምን ሰንጋ የሚለውም ደስ አይለም" አለቺኝ።

"ለምን?"

"እኛ ስለ ምግብ አንዘፍንም"

"ግጥሙ እንዲያምር ነው ያስገባሁት። ዱከም በሰንጋ ስለሚታወቅና የተወለድኩበት አካባቢ ስለሆነ ነው" ስል አስረዳሁዋት።

ማሚትን በጣም ወደድኳት።

ማሚት ህይወትዋን ልተሰጠው የተዘጋጀችለት አይነት አላማ ይኖረኝ ዘንድ ከልቤ እመኝ ነበር። ማሚት በዚያች ሰአት ለአላማዋ ህይወትዋን ለመስጠት ዝግጁ ነበረች። እኔ ግን ያን የመሰለ ጠብታ ስሜት እንኳ አልነበረኝም። ልዩ ፍቅር የሚያሳድርብኝ ነገር ቢኖር መፃፍ ብቻ ነበር። ውብ ቃላትንና ሃሳቦችን መመዝገብ! ይህ አላማ ሊባል ይችል እንደሁ የማውቀው ነገር አልነበረም። ስለ ማሚት፣ ስለ እያሱ፣ ስለ ተራሮቹና ስለ ሬሳዎች ብዙ ፅፌያለሁ። ቁርጥራጭና ብጣሽ ወረቀቶቹ እየበዙ ሄደዋል። ወረቀትና ቆንጆ ብእር ስመለከት አይኔ ይጎለጎላል። መፃህፍት ሳይ በረሃ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ እንዳገኘ ሰው እስገበገባለሁ።

በደርግ ወገን የተዋወቅሁት ሻምበል በለጠና በወያኔ ወገን ያገኘሁት እያሱ በርሄ የሁለት አለም ሰዎች ቢሆኑም፣ ለኔ ግን አንድ አይነት ሰዎች ነበሩ። እናወራለን፣ እንስቃለን። ሁለቱም ሃገራቱን እንደሚወዱ ይናገራሉ። ሁለቱም የባህል ክፍል ሃላፊዎች ነበሩ። እነሱ ሲናገሩ እኔ አዳምጣለሁ። ይኸው ነው። መቼ እንደምጠቀምባቸው ባላውቅም አዲስ መስለው የሚሰሙኝን አሳቦችና ቃላት በብጣሽ ወረቀቶች ላይ እመዘግባቸዋለሁ። እኔና ማሚትም በተመሳሳይ እድሜ ላይ የምንገኝ፣ የአንድ አገር ዜጎች - የሁለት አለም ሰዎች ነበርን።

የሆነው ሆኖ ወደ ትግራይ እየተጓዝን ነው።

ቀን አንጓዝም። የደርግ ሰላይ አይሮፕላኖች ሰማዩን ሲያስሱ ይውላሉ። የደርግ መውደቂያ ቅርብ መሆኑን ተረድቼው ነበር። የደብረታቦር አሰቃቂና ምስቅልቅል ውጊያ ግንዛቤዬን አዳብሮታል።

የደርግ ጄኔራሎች ያፈጠጠውን ሽንፈታቸውን ማመን እየተቸገሩ፣ "ወይ ታሪክ ዋሽቶአል፣ አለያም ትውልድ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተከላሽቶአል" እያሉ ሲያጉረመርሙ ሰምቼ አባባሉን ለሰአታት ያህል መርምሬው ነበር። ጄኔራሎቹ እኔ እንድሞትላቸው ፈልገው ነበር። "ለማን አላማ?" ብዬ መጠየቅ ስለቻልኩ "ትውልድ ተከላሽቶአል" አሉ። ታሪካቸውንም ተጠራጠሩ። ገበሬው ታዲያ እነዚህ ታሪካቸውን የተጠራጠሩ ጄኔራሎች ላይ በማያልቅ ቅኔው እንዲህ እያለ ያላግጥባቸው ነበር፣

እነ ዶሮ ምሳው - እነ እንቁላል ቁርሱ፣
ሃሙሲት ቢተኩስ - ባሀርዳር ደረሱ፣

* * *

በግር አልሆን ሲለው፣ መጣ በሰማይ፣
መሬት ከለቀቀ፣ መንግስት አለ ወይ?

ውጊያ በተደረገ ቁጥር ይህን ትውልድ የናቁት ጄኔራሎች በሃያ ሺዎች ሬሳ ይታቀፋሉ። በሰራዊቱ ውስጥ "ጀግንነት" "ኢትዮጵያዊነት'' "ባንዲራ" "ዳር ድንበር" የመሳሰሉት መሰረታዊ ቃላት ዋጋ አጥተዋል። ወታደሮች "የቆመ ቀለጠ - የሮጠ አመለጠ" እያሉ በአለቆቻቸው ፊት ይዘፍናሉ። የፖለቲካ ትምህርት የተከታተሉ ወጣት ካድሬዎች የሚሸሸውን ወታደር "በባንዲራው!" "በኢትዮጵያ አምላክ!" እያሉ ሊያቆሙት ሲሞክሩ ወታደሮች፣ "ባንዲራውን ቀደህ ልበሰው!" "ለእናትህ ቀሚስ አሰፋበት!" ከማለት አልፈው አለቆቻቸውን "እናትህን እንዲህ ላድርጋት!" እያሉ መረን በለቀቀ ብልግና ሲሳደቡ በጆሮዬ ሰምቻለሁ። ወታደሩ "በባንዲራው!" እያሉ ከፊቱ የሚደቀኑትን ካድሬዎች ግንባር ግንባራቸውን በጥይት እየበሳ ረግጠአቸው ያልፋል። ስለ አፄ ቴዎድሮስ አሟሟት መስበክ የተበላ እቁብ ሆኖአል።

በርግጥ "እጃችንን ለወያኔ ከምንሰጥ ሞት እንመርጣለን" እያሉ ህይወታቸውን ባንድ ጥይት ያሰናበቱ ጥቂት መስመራዊ መኮንኖች ታይተዋል። ሻምበል በላቸው ካሳ የተባለ ወጣት ራሳቸውን ከገደሉት አንዱ ነው። አብረውት ከነበሩ ወታደሮች ጋር በሽሽት ወቅት ተገናኝተን ሻምበሉ ራሱን እንዴት እንደገደለና በመጨረሻ የተናገራቸውን ቃላት ጭምር አጫውተውኛል። ምሽጋቸው ተሰብሮ በሻምበሉ የሚመሩት ወታደሮች እንደ ሚዳቋ እየዘለሉ ሽሽቱን እንደ ጀመሩ ሻምበሉ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሽጉጡን መዘዘ። እንዲህ ሲልም ጮኸ፣

"...ጓድ መንግስቱ ያስረከቡን አደራ...መይሳው ያስተማሩን ጀግንነት ለዘላለም ይኑር!!"

እናም በኩራት የማካሮቩን ጥይት በራሱ ግንባር ላይ ለቀቀው! ይህን የሚያጫውተኝ ወታደር የሻምበሉ ምስል እየመጣበት ደግሞ ደጋግሞ ስለ ሁኔታው እየዘረዘረ ሲነግረኝ አእምሮው ግራ በተጋባ ስሜትና ግለት ላይ መሆኑን ልረዳ ቻልኩ። በሌባ ጣቱ ደጋግሞ የራሱ ግንባር ላይ እያነጣጠረ ያሳየኛል፣

"...ትንሽ እንኳን አላመነታም! ምላጩን ሲስበው በብርጭቆ ፊቱ ላይ የተቸለሰበት ይመስል ደሙ ፊቱን አለበሰው! እኔ አይኔን ጨፈንኩ። ከዚያ በቃ! መሮጥ ጀመርኩ...."

"ጓድ መንግስቱ ያስተማሩን ፅናት!" እያሉ የራስ ቅላቸውን እየፈረካከሱ የወደቁ እኒያ ወታደሮች የዛሬውን ዘመን የማየት እድል ቢያገኙ ምን ይሰማቸው ነበር? ጓድ መንግስቱ ሚስቱንና ጫጨቶቹን በዘንቢል አንጠልጥሎ "አውጪኝ እግሬ" ማለቱን ቢያውቁስ? ዘመን ተገልብጦ ህይወትን ያህል የከፈሉለት አላማ "የደርግ እንጂ የኢትዮጵያ ወታደሮች" እንኳ ሊያሰኛቸው እንዳልቻለ ቢገነዘቡ ምን ባሉ? የሞተው ወታደር ከመሞቱ በፊት መጠራጠር ቢችል ኖሮ ለግለሰቦች የስልጣን ጥም ሲል በርግጥ ህይወቱን ይከፍል ነበርን?

* * *

መቀሌ ስንገባ ባየሁት ነገር ክፉኛ አዘንኩ።

አቧራማና ደረቅ፣ ህይወትና ውሃ ያለባት የማትመስል ወና ሆና ጠበቀቺኝ። ከተማ ሳትሆን በረሃ ነበረች። በጎዳናዎችዋ ጥቂት ስትጓዝ ፀጉርህ፣ ቅንድብህ፣ ጉሮሮህ ሳይቀር በአቧራ ይሞላል። ይህ ግን ሰው ሰራሽ ችግር እንጂ የትግራይ ተፈጥሮ እንዲያ እንዳልነበር በመጠኑም ቢሆን አንብቤያለሁ።

በ13ኛው ክፍለ ዘመን በዮሃንስ 4ኛ የተቆረቆረችው መቀሌ በዚያን ወቅት በደኖች የተከበበች ነበረች። በዙሪያዋ 12 ምንጮች ነበሩዋት። ማይልሃም፣ አዲወለልና ፈለገዳእሮ ላይ የነበሩት ጥቅጥቅ ደኖች በዱር አውሬ የተሞሉ ነበሩ። አሁን ያገጠጡ ኮረብቶች ብቻ ቀርተዋል። ያቺን ምድር ወደ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ነበረችበት ለመመለስ ብዙ ድካም የሚጠይቅ መሆኑ ግልፅ ነው። በርግጥም ትግራይ ከሚንቋት ወይም ከሚያሾፉባት መሪዎች አበባና ችግኝ ልትጠብቅ ከቶ አትችልም። ስለዚህ ወጣቶቿ ወደፊት ከመገስገስ በቀር ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም።

መቀሌ እንደደረስን እያሱ ወደ እናቱ ቤት ይዞኝ ሄደ። ደርባባና ደግ ወይዘሮ ነበሩ። እንደ ወተት የነጣ የአበሻ ቀሚስ ለብሰው፣ ቁና ተሰርተው ነበር። ውሃ አሞቁልኝና ሰውነቴን ታጠብኩ። እያሱ ወደ ከተማ ሄዶ ሱሪና ሸሚዝ ገዝቶልኝ ተመለሰ። ኮንጎ ጫማ ተሰጠኝ። ጠመንጃ ግን አላስፈለገኝም። የኔ ጠመንጃ ብእሬ ነበር። ብእሬ ይተባ ዘንድ በቅርብ ይረዳኝ የነበረውን ደራሲ ብርሃኑ ዘርይሁንን ለማስታወስ የሱን የብእር ስም በመውሰድ "ዳግማዊ መርቆሬዎስ" በሚል ስም ደርግን የሚያጋልጡ ቀስቃሽ ፅሁፎችን ማንጎድጎድ ጀመርኩ። ለኢህአዴግ ሬድዮ የምልካቸው ፅሁፎች በሬድዮ መነበባቸው በመቀጠሉ ከእያሱ ጋር አያሌ የጋራ የወሬ ርእሶች ይኖሩን ዘንድ አስተዋፆ አደረጉ።

በእያሱ እናት ቤት ቆይታችን መዝሙር ፈንቴ የተባለ ሰው ተዋወቁ ነበር። አለባበሱ እንደ ታጋዮች አልነበረም። ስሙን የማላውቀውን አይነት ረጅም ሽጉጥ ታጥቆአል። ኪሶች የበዙበት ቤዥ ቀለም ሱሪና አንገተ ሙሉ ሹራብ ለብሶአል። ኮንጎ ጫማ ሳይሆን ነጭ አዲዳስ ተጫምቶአል። የኢህዴን አመራር አባል መሆኑንና ሙዚቃም እንደሚጫወት እያሱ ነገረኝ። በተለይም "መልእክት አድርሺልኝ አሞራ'" የተባለች ቀስቃሽ ዘፈኑ ተወዳጅ ነበረች። ያም ብቻም አልነበረም። የመዝሙር ቤተሰቦች በሙሉ ታጋዮች ኖረዋል። እናቱም ጭምር ታጋይ ናቸው።

በቆይታችን የደርግ ጋዜጠኞችን በተመለከተ ወሬ ተነሳና ከመዝሙር ጋር ጥቂት ተከራከርን። አብዛኞቹ ጋዜጠኞች የስርአቱ አገልጋይ የሆኑት ተገደው ሊሆን እንደሚችል ገለፅኩ። መዝሙር ደግሞ ተገደው ሊሆን እንደሚችል ያምንና ቢሆንም ጋዜጠኞች ከህብረተሰቡ በላቀ ሁኔታ መረጃ ሊያገኙ ስለሚችሉ ስርአቱን ለመቃወም የተሻለ እድል ሊኖራቸው ይገባ እንደነበር ይገልፃል።

"የሆነው ሆኖ ደርግ ሊወድቅ ምን ያህል ጊዜ የሚቀረው ይመስልሃል?" ስል መዝሙርን ጠየቅሁት።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ከሁለት አመት በላይ አናቆየውም" አለኝ።

ከሁለት አመታት በሁዋላ ደርግ እንደሚወድቅ ማሰቡ ከፍተኛ ሞራል አሳደረብኝ።

* * *

መቀሌን ተሰናብተን ጉዞ ቀጠልን።

ወደ አድዋ ከማቅናታችን በፊትም ወደ ሃገረሰላም አመራን። አለምሰገድ የተባለውን የእያሱን የቅርብ አለቃ ለማግኘት የህወሃት አመራር አባላት ወደ ነበሩበት ዋሻ በእግር እያዘገምን ሳለም እያሱ ያልጠበቅሁትን አይነት ወሬ አነሳ፣ የትግል ፍላጎቴን እየተጠራጠረው ኖሮአል፣

"ለመታገል ከልብ የወሰንክ አትመስልም" አለኝ።

"ለምን እንደዚያ አልክ?"

"የኢህአዴግን ፕሮግራም ሰጥቼህ ነበር። አነበብከው?"

"ለማንበብ ሞክሬ ነበር። አልገባኝም"

"ምኑ ነው ያልገባህ?"

"የብሄር ብሄረሰቦች ጉዳይ ደስ አላለኝም"

"ለምን?"

"ስለ ዘር መነጋገር ስህተት መስሎ ይታሰበኛል"

እያሱ ጥቂት አሰበበትና፣

"የብሄር ጭቆና መኖሩን አታምንም?" ሲል ጠየቀኝ።

"አስቤው አላውቅም"

"በአማራ ገዢ መደብ ተፅእኖ ስር ስላደግህ ለጊዜው ልታየው አትችልም። አማራ ባትሆንም ባመለካከት ግን የአማራው ገዢ መደብ ሰለባ ሆነሃል" አለኝ።

የአማራው ገዢ መደብ የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ይነሳ የነበረ ሲሆን፣ መጀመሪያ ላይ በፍፁም ልረዳው ተቸግሬ ነበር። በዘራቸው አማራ የሆኑትን የልጅነት ጓደኞቼን በማሰብ፣ በስነፅሁፍ እንድዳብር ከልብ የሚያግዙኝን በዘራቸው አማራ የሆኑ ደራሲዎችን በማስታወስ፣ አሳቡን በአእምሮዬ ቦታ ሰጥቼ ላስተናገደው በጣም ተቸገርኩ። ከኦሮሞዎችና ከአማራዎች ጋር ያደግሁ እንደመሆኔ የዘርን ጉዳይ ልዩነቱን በፍፁም አናውቀውም ነበር። እናቶቻችን እሳትና እንጀራ እየተበዳደሩ አሳድገውናል። ስለ አማራ ገዢ መደብ ማንሳት ያንን የዳበረ የልጅነት ፍቅር፣ ማንነቴ የተገነባበትን መሰረት የሚያፈራርሰው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እየመሰለኝ እጨነቅ ነበር። ሁዋላ ስማቸውን ኦህዴድ ሲሉ የሰየሙት ኦሮሞዎች አዴት ከተባለ ቦታ ላይ የፖለቲካ ድርጅት ለመመስረት የመሰብሰባቸው ወሬም ኮስኩሶኝ ነበር። የቢሾፍቱ ሃይቅ ዳርቻ አስተዳደጌ ይህን የመሰለውን ስር ነቀል የሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማድረግ ችግር ፈጠሮብኝ ነበር።

ከእያሱ ጋር ስናወራም አለመደሱቴን መረዳት ቻለ።

"ፖለቲካ ማንበብና ማወቅ አለብህ! የብሄርን ችግር አቃልለህ እያየኸው ነው። የግለሰቦች መብት መከበር ብቻውን መፍትሄ አይሆንም" እያለ ሊስረዳኝ ይሞክራል።

እኔ ደግሞ "ቋንቋ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ መፍትሄ ችግሩን ከመፍታት ይልቅ የበለጠ ያወሳስበዋል" የሚል ስጋት እንዳለኝ እገልፃለሁ። ሆኖም ሃሳቤን ተንትኜ ለማስረዳት አቅም አጣለሁ። ባጭሩ በቂ እውቀት አልነበረኝም።

ይልቁን የስነፅሁፍ ወሬ ከተጀመረ በግለት እናገራለሁ። በተለይ የራሺያ ጥንታዊ ትረካዎች ላይ ያለኝን እውቀት እያሱ ያምንልኝ ነበር። እሱም ግሩም አንባቢ ነበር። የሚክሻይል ሾሎክሆቭን "And Quiet Flows the Don" የተባለውን መፅሃፍ በጣም ስለሚወደው እንደ መፅሃፍ ቅዱስ ከሻንጣው አይለየውም።

"አንብበኸዋል?" ሲል ጠየቀኝ፡

"የለም"

"በል ያውልህ! አለምህን ቅጭ!" ብሎ ሁለት ጥራዝ አስታቀፈኝ።

እያሱ ሁለገብ ሰው ነበር። የማንበብን ሃይል ደጋግሞ ነግሮኛል። "ጥሩ ፀሃፊ መሆን የምትችለው ጥሩ አንባቢ ከሆንክ ብቻ ነው!" የሚለውን ወርቃማ ምክር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ከእያሱ አንደበት ነበር። በአናቱ ሙዚቃ ይወዳል። የሙዚቃ መሳሪያዎችን እንደጣቶቹ ያውቃቸዋል። ሩባ ለሚን ከተባለ ገደላማ ጫካ ውስጥ ከእያሱ ጋር አንድ የመኝታ ምንጣፍ ተካፍለን ለስድስት ወራት አብረን ኖረናል። ከላስቲክ በተሰራች ጎጆአችን ደጃፍ ላይ ወራጅ ወንዝ ያለማቋረጥ ያልፋል። ጤጣዎችና ዝንጀሮዎች ጣራችን ላይ ይፈነጫሉ። ቁጥር ስፍር የሌላቸው አእዋፍ ከማለዳ እስከ ምሽት ይዘምሩልናል። አንዳንድ ጊዜ እያሱ የአእዋፍን ድምፅ ከሙዚቃ መሳሪያዎች ድምፅ ጋር እያመሳሰለ በስሜት ያጫውተኝ ነበር...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

* * *

እነሆ! ወደ አዴት እየተጓዝን ነው...

አክሱም ከመድረሳችን በፊት እያሱ እንዲህ አለኝ፣

"የኢህአዴግን መሰረታዊ አቋሞች የማትደግፍ ከሆነ ልትታገል አትችልም። ደስ ካላለህ ወደ ሱዳን የመሄድ አማራጭ አለህ"

"ሱዳን ምናደርጋለሁ፣ እያሱ?"

"በስደተኛነት ተመዝግበህ አሜሪካ ልትሄድ ትችላለህ"

የስደት ፍላጎት እንደሌለኝ ነገርኩት።

ከኢህአዴግ ዋነኛ አላማዎች አንዱ ደርግን ከስልጣኑ መገልበጥ ነው ብዬ እንደማምንና በዚህ አጀንዳ ደግሞ ሙሉ በሙሉ እንደምንስማማ ስነግረው እያሱ በሳቅ ፈነዳ።

"ምን አሳቀህ?" አልኩ።

"ደርግን በመጣል አላማማ ከተቃዋሚ ሃይላት ጋር ሁሉ እንስማማለን! የሚያለያየን ደርግ ከወደቀ በሁዋላ ሃገሪቱ የምትመራበት ፖሊሲ ነው" አያያዘና አከለበት እያሱ፣ "...የድርጅት ሰው መሆን የምትችል አትመስልም!"

ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ካሰብኩ በሁዋላ፣

" የኢህአዴግን አላማዎች እየተቃወምኩ አይደለም" ስል ጀመርኩ፣ "...በተፈጥሮ ለፖለቲካ አጀንዳዎች ቀዝቃዛ ነኝ። እንዳልከው ግን ፖለቲካ ማንበብ እጀምራለሁ..."

ለጊዜው በዚሁ ተግባባን!

ከዚያ በሁዋላ ከታሪክና ከስነፅሁፍ ባሻገር የፖለቲካ ንባቤን በሰፊው ተያያዝኩት። ዛሬ ግን በርግጥ የፖለቲካ አጀንዳና ንባብ ሱስ ሆኖብኛል።

* * *

የደርግ ስርአት በወደቀ በአመቱ ላሊበላ ሬስቶራንት ቢራ እየጠጣሁ ቴሌቭዥን ስመለከት አንድ የማውቀው ፊት ወደ ሬስቶራንቱ ገባ።

አይኔን ማመን አቃተኝ። ጮህኩ!!

"ሻምበል በለጠ!"

"ወያኔው ጓደኛዬ!" ሲል እሱም በጩኸት ምላሽ ሰጠኝ!

በሚያስደንቅ የወዳጅነት መንፈስ ተቃቀፍን። ከአምስት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ደቂቃ በሁዋላ ቀዝቃዛ ቢራ ይዘን ወሬ ጀመርን!

"ስላንተ ሁሉንም ሰምቻለሁ!" አለኝ።

"ምን ሰማህ?"

"ተራሮቹ ላይ ቆስለህ፣ ተማርከህ፣ በወያኔ ሬድዮ የሰጠሽውን ቃለ-መጠይቅ ሰማሁ። በመቀጠል በወያኔ ሬድዮ ጋዜጠኛ ሆነህ የምታነበውን ሁሉ እከታተል ነበር። ደርግ ከወደቀ በሁዋላ ግን ድምፅህ ጠፍቶብኝ የት እንዳለህ አላወቅሁም ነበር፤ በቅርቡ ግን የፕሬስ መምሪያ ሃላፊነቱ ስልጣን ላንተ እንደተሰጠ ሰማሁ! ለነገሩ ዛሬ ነገ እያልኩ ዘገየሁ እንጂ ቢሮህ ልመጣ ወስኜ ነበር..."

"በጣም ይገርማል! ለመሆኑ አንተስ እንዴት ነህ? የት ነህ? ምንደረሰብህ?"

ሻምበል በለጠ ፈገግ አለ። ለመናገር ግን ዘገየ፣

"ደብረታቦር ላይ ከተለያየን በሁዋላ ሰራዊቱ ሲበተን አምልጬ ባህርዳር ገባሁ። አዲሳባ እስኪያዝም እየሸሸሁ እዚህ ደረስኩ። በመጨረሻ ግን ያው ወያኔ ሁላችንንም ማረከን..."

ሳቅሁ! እሱም ሳቀ!

"እና አሁን ምን እየሰራህ ነው?"

"ባህል ሚኒስቴር በሙያዬ ቦታዬን ይዤያለሁ!"

"ኸረ ባክህ!? እንዴት በፍጥነት ቀናህ ታዲያ?"

ሻምበል በለጠ ጢሙን ማሻሸት ጀመረ፣

"ያልጠበኩት ነገር ተከሰተ"

"ምን?"

"ከወያኔ መሪዎች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ሆኖ አይገኝ መሰለህ?"

"ማን?" ተጣድፌ ጠየቅሁት።

"ታምራት ላይኔ!"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 4 -
በረከት ስምኦን

መች ይበጠስ ይሆን - ይህ የቂም ሰንሰለት?
ይህ የቂም ጉማሬ - ይሄ የቂም ኡደት፣
መች ይሆን አገሬ - ልጅ የሚወጣላት፣
ቂም አርጅቶ ሞቶ - ሰው የሚኖርባት፣
በቀል ሬሳው ወጥቶ - ሰው የምንሆንባት!

(ግጥም - ነቢይ መኮንን)

በረከት ስምኦን የተባለውን ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅሁት በትግሉ ዘመን ሃገረሰላም በሚገኘው የኢህዴን የአመራር ማዘጋጃ ጣቢያ በአንድ ምሽት ነበር።

በዚያን እለት ለሬድዮ ጣቢያው ቀረፃ ለማካሄድ የኤሌክትሪክ ችግር ስለአጋጠመ፤ ማምሻውን በረከትና ታምራት ወደሚገኙበት የኢህዴን የአመራር ዋሻ ሄደን ስራችንን እንድንሰራ በመታዘዛችን ለመጀመሪያ ጊዜ በረከትን በአካል አየሁት።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከዚያ በፊት ስለበረከት ጥቂት አውቅ ነበር።

የጎንደር ልጅ እንደሆነና ወላጆቹ ኤርትራውያን መሆናቸውን፤ ውጊያ ላይ ጀግናና እብድ እንደነበር የወሬ ወሬ እሰማ ነበር። ከደርግ ጋር በተደረጉ ውጊያዎች ብዙውን ጊዜ እልህ እየያዘው፣ መምራቱን እየተወ፣ ከተራ የተዋጊ መስመር እንደሚገባ አብረውት በውጊያ ላይ የዋሉ ታጋዮች እንዳወጉኝ ትዝ ይለኛል። ይህ የበረከት ጠባይ ታዲያ በሲቪላዊ አመራሩም ወቅት እየተከሰተበት ስመለከት እውነትነቱን አረጋግጫለሁ። የማስታወቂያ ሚኒስትር ሆኖ ሳለ አንዳንድ ጊዜ ርእሰ አንቀፆችን ራሱ ይፅፍ ነበር። ስለ ባህርይውም ጥቂት ሰምቼ ነበር። ስሜታዊ መሆኑ፣ ሰዎችን የሚያስቀይም የንግግር ጠባይ እንዳለው፤ በኢህዴን ህልውናና ነፃነት ዙሪያ በሚነሱ ጉዳዮች ከህወሃት አመራር አባላት ጋር በተደጋጋሚ እንደሚጋጭ፣ ከመለስ ጋር ግን ደህና እንደሚቀራረቡ... እንዲህ ያሉ ወሬዎችን በተለያዩ አጋጣሚዎች እሰማ ነበር።

እነዚህ ሁሉ ገለፃዎች ከግማሽ በላይ ከእውነት ያልራቁ መሆናቸውን ታዲያ ደርግ ከወደቀ በሁዋላ የቅርብ አለቃዬ ስለነበር በተግባር ላያቸው ችያለሁ።

በዚያን እለት ምሽት የግማሽ ሰአት የሬድዮ ፕሮግራም ቀረፃ አካሂደን እንዳበቃን በረከት ወዳለንበት ጊዜያዊ የቀረፃ ስቲድዮ መጥቶ ሲተዋወቀን፤ ስለበረከት በአእምሮዬ ስስለው የነበረውን ስእል በማግኘቴ ሳልደነቅ አልቀረሁም። ግዙፍና ሙሉ ሰውነት ያለው፤ ረጅምና ፀጉሩን ሙልጭ አድርጎ የተቆረጠ፤ እንደ ንስር ጠቋሚ አፍንጫና ተራቢ አይኖቹ ያሉት፤ ያም ሆኖ በቀላሉ የምትቀርበው አይነት ሰው ሆኖ አገኘሁት።

በኢህአዴግ የፕሮፓጋንዳ ክፍል ውስጥ ከበረከት ጋር በቅርብ ሰርተናል። አንዳንድ አይረሴ ገጠመኞቼን ብቻ እያነሳሁ በጨረፍታ አወጋችሁዋለሁ - ስለ በረከት - የስምኦን ልጅ!

* * *

ኢትዮጵያ የኤርትራን ነፃነት ያወቀች ሰሞን በረከት ስምኦን ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሰፊ ቃለ መጠይቅ ሰጠኝ። ቃለ መጠይቁ እንዳበቃ ፍቶግራፍ ላነሳው ካሜራዬን ሳስተካክል፣

"የለም" አለና በረከት አቆመኝ "...ፎቶግራፍ ማንሳት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አያስፈልግህም። ይህ ቃለ መጠይቅ በኔ ስም እንዲወጣ ፍላጎት የለኝም"

የበረከት ምክንያት ወዲያው ገባኝ። አሳማኝም ነበር።

በረከት ምንም እንኳ የአማራው ድርጅት መሪ ቢሆንም፤ በዘሩ ኤርትራዊ ነው። ኤርትራዊ ሆኖ ሳለ ኢትዮጵያን ወክሎ ስለ ኤርትራ ነፃነት ማብራሪያ ቢሰጥ ለአንባቢው ምቾት የሚሰጥ አልነበረምና ችግሩን ፈጥኜ ተረዳሁ።

"ያለ ስም ግን ልናትመው አንችልም" አልኩ።

"የካሳ ደሜን ስም ተጠቀም፤ ፎቶግራፍም እሱን ሄደህ አንሳው" ሲል አዘዘኝ።

ግራ ቢገባኝም አእምሮዬን ለማስተካከል ጥረት አደረግሁ። ካሳ ደሜ የኢህዴን ነባር ታጋይና አማራ ሲሆን፣ አሁን ብርጋዴር ጄኔራል ነው።

"ይስማማል?" ስል ጠየቅሁት።

"ችግር የለውም"

"በል ደውልና ንገረው"

"ራስህ ንገረው" ብሎ አሰናበተኝ።

ቢሮ እንደተመለስኩ የካሳን ስልክ ፈልጌ ደወልኩና አገኘሁት። ካሳ በበረሃው ሬድዮ ጣቢያ አካባቢ ይሰራ ስለነበር እንተዋወቃለን።

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ካሳ ደሜ ከኔ ቢሮ ተገኘ። እንዴት እንደምጀምርለት ግራ ገባኝ። የሙያው ህግ የማይፈቅደውን ተግባር ከመፈፀሜ ባሻገር፣ የካሳ ደሜን ሞራል የሚነካ ድርጊት እንዳይሆን ሰግቼ ነበር። እንደ ምንም ዳር ዳር ማለት ጀመርኩ። ከበረከት ጋር ቃለ መጠይቅ ሳደርግ መዋሌን፤ በረከት ኤርትራዊ ስለሆነ ቃለመጠይቁን በስሙ ማተም እንዳልፈለገ ካብራራሁ በሁዋላ፣

"በአንተ ስምና ፎቶግራፍ ቃለመጠይቁ እንዲታተም በረከት ንገረው ብሎኛል" አልኩት።

ካሳ ደሜ ሊቃወም ይችላል አሊያም 'ቃለ መጠይቁን መጀመሪያ ላንብበው' ብሎ ያዘገይብኛል ብዬ ሰግቼ ነበር። ያገኘሁት ምላሽ ግን የተለየና አስደንጋጭ ነበር።

"ታዲያ ክራቫት አድርጌ እንድመጣ ለምን አልነገርከኝም?" አለኝ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በብርጋዴር ጄኔራል ካሳ ደሜ ስምና ፎቶግራፍ የበረከት ቃለመጠይቅ አዲስ ዘመን ላይ ታትሞ ከወጣ በሁዋላ ካሳ ደሜ ደጋግሞ እየደወለ እንዲህ ይለኝ ነበር፣

"እንዴት ነው? በቃለ መጠይቁ ላይ ሰዎች አስተያየት ይሰጣሉ? ምን ይላሉ? ...እ? አዎን ሰዎች ያነጋግሩኛል ...ግሩም ቃለ መጠይቅ ነው እያሉኝ ነው...አንተስ እንዴት አየኸው? የተለየ ነገር ካለ ደውልልኝ..."

ጄኔራል ካሳ ይህን ሲለኝ በርግጥም ቃለመጠይቁን የሰጠኝ በረከት መሆኑን እሱ ራሱም እንደረሳው ተረዳሁ! በረከት ተከታዮቹን ደህና አድርጎ ያውቃቸው ኖሮአል!

* * *

አንድ ቀን ማለዳ ገና ቢሮ ከመግባቴ በረከት ደወለና እንዲህ አለኝ፣

"መለስ የፃፈው ፅሁፍ ከአንድ ሰነድ ጋር አሁን ይደርስሃል። አንድ የብእር ስም ስጠውና በነገው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ አትመው!"

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ከፕሬዚዳንቱ ቢሮ የመጣ ታጋይ አንዳችም ስም የሌለውን ፖስታ አስረክቦኝ ተመለሰ። በጉጉት ከፍቼ ማንበብ ጀመርኩ። በወቅቱ የፓርላማ አባል ስለነበረ አሰፋ ጫቦ ስለተባለ ሰው የሚተርክ ነበር። በዘመነ ደርግ አሰፋ ጫቦ በጋሞጎፋ ክፍለ ሃገር እንዲረሽኑ ስላደረጋቸው የኢህአፓ ወጣቶች የሚተነትን ፅሁፍ ነበር። ከፁሁፉ ጋር አሰፋ ጫቦ በስሙ የፈረመበት ሰነድ ተያይዞአል። የቀይ ሽብር ርምጃ የተወሰደባቸው ከሃያ የማያንሱ የኢህአፓ አባላት ስም ዝርዝርም ሰነዱ ላይ ሰፍሮአል። አንብቤ ከጨረስኩ በሁዋላ ሰነዱን በድጋሚ ፎቶኮፒ አድርጌ መሳቢያዬ ውስጥ አኖርኩት። ፅሁፉንና ሰነዱን ለአዲስ ዘመን ዋና አዘጋጅ ለማስተላለፍ ስዘጋጅም በረከት ስምኦን የቢሮዬን በር ከፍቶ ገባ፣

"ደረሰህ?" ሲል በችኮላ ጠየቀኝ።

"የሚገርም ታሪክ ነው"

"እስኪ አምጣው ልየው?"

በረከት እንዳላነበበውና ፅሁፉ በቀጥታ ከመለስ ወደኔ መላኩን፤ መለስ ግን ፅሁፉን ወደኔ ከመላኩ በፊት ለበረከት ደውሎ እንደነገረው ተረዳሁ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በረከት አንብቦ ከጨረሰ በሁዋላ የተለመደ አሹዋፊ ሳቁን ሳቀና ተሰናብቶኝ ሄደ። በረከት ከሄደ በሁዋላ ፅሁፉን ወደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላኩት።

ተስያት ዘጠኝ ሰአት ላይ አሰፋ ጫቦ እየተጣደፈ ቢሮዬ ሲገባ ግን ማመን ነበር ያቃተኝ። ከመቀመጫዬ ተነስቼ በአክብሮት እንዲቀመጥ ጋበዝኩት። ቁና ቁና እየተነፈሰ እንዲህ አለኝ፣

"እኔን የተመለከተ ፅሁፍ ደርሶሃል?"

"ደርሶኛል"

"ፅሁፉን ማንበብ እፈልጋለሁ"

"ላስነብብህ አልችልም፣አቶ አሰፋ"

"ለምን?" ሲል ጮኸ "...እኔ የፓርላማ አባል ነኝ! መብት አለኝ!"

"ፅሁፉን ነገ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታነበዋለህ። ከዚያ ምላሽ የመፃፍ መብት አለህ"

ከብዙ ጭቅጭቅ በሁዋላ ግን ለራሴ ለማወቅ ስለፈለግሁ አሰፋ ጫቦ የፈረመበትን የርሸና ሰነድ ፎቶኮፒ አውጥቼ አሳየሁት።

አሰፋ በተረበሸ ሁኔታ ሰነዱን ከተመለከተ በሁዋላ፣

"ውሸት ነው" አለኝ "ተቀነባብሮ የተሰራ ነው። ይህን ማተም ህጋዊ አይሆንም" ሲል ካስጠነቀቀኝ በሁዋላ "... ይህ ሰነድ ፎቶኮፒ የተነሳ ነው። ቢያንስ ዋናውን ኮፒ ማየት አለብህ። ይህ ተቀነባብሮ የተሰራ ነው። እኔ የኢህአፓ ወጣቶች እንዲረሽኑ አልፈረምኩም"

"ሃሰት ከሆነ ነገ ታስተባብላለህ..."

"ይህን የሃሰት ሰነድ ማተም ስም ማጥፋት ነው። አንተንም ያስጠይቅሃል..."

"አቶ አሰፋ ... ሰነዱ ሃሰት ከሆነ አንተ አስተባብልና ክሰሰኝ... ሰነዱን የላኩትን ሰዎችም ስም እሰጥህና ትከሳቸዋለህ" አልኩ።

ይህን ያልኩት አሰፋ ሰነዱና ፅሁፉ ከማን እንደተላከልኝ ማወቅ አለማወቁን ለመፈተሽ ብዬ ነበር። እንዳላወቀ ግን ተረዳሁ፣

"ማነው ይህን ሰነድ የላከልህ?" ሲል አጥብቆ ጠየቀኝ።

"ለጊዜው አልነግርህም!"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሊያግባባኝ ሞከረ። ሊያስፈራራኝም ቃጣው። እንደማይሆን ሲያውቅ ጥሎኝ ወጣና ሄደ። ወደ በረከት ደወልኩና ከአሰፋ ጋር የተነጋገርነውን በዝርዝር ሳጫውተው የተለመደ አሹዋፊ ሳቁን አሰምቶኝ አንዳችም አስተያየት ሳይሰጥ ስልኩን ዘጋ።

በጉዳዩ ላይ ጥቂት ካሰብኩበት በሁዋላ የመለስና የበረከትን ድራማ ለመገመት ሞከርኩ።

አሰፋ ጫቦ አስቸግሮአቸዋል ማለት ነው። ምናልባት ግን በደርግ አስር አመታት የታሰረ በመሆኑ ሊያስሩት አልፈለጉም። ወይም ደግሞ አስረውት ከሚያስቸግራቸው በራሱ ጊዜ እንዲኮበልል ፈልገዋል። ስለዚህ ለመጠባበቂያ አቆይተዋት የነበረችውን ሰነድ መዝዘው አወጧት። አሊያም አሰፋ የሚለው እውነት ከሆነ ሰነዱን አቀነባብረው አዘጋጁት። ሰነዱ ከእነሱ ቢሮ እንደወጣ እንዲረዳ ስለፈለጉም በጎን ወሬው እንዲደርሰው ላኩበት። አለያም ደግሞ ከአዲስ ዘመን ጋዜጠኞች አንዱ ለአሰፋ ደውሎ ነግሮት ሊሆን ይችላል።

በነጋታው አዲስ ዘመን ሰነዱንና የመለስ ዜናዊን መጣጥፍ ይዞ ወጣ። ሰነዱ ይፋ በሆነ በሳምንቱ አሰፋ ጫቦ እንደኮበለለ የግል ጋዜጦች እየተቀባበሉ ዜናውን ነዙት። ከአመት በሁዋላም አሰፋ ጫቦ ከካሊፎርኒያ የተቃውሞ መጣጥፎችን መፃፍ ጀመረ። ምንም ዋጋ አልነበረውም፣ "...በሃገሩ የሌለ - የትም የለም..." ያለው ማን ነበር?

* * *

አንድ ጊዜ አሰፋ ማሞ በሚመራው የፕሮፓጋንዳ ዘርፍ ግምገማ ላይ የዋልታ ኢንፎርሜሽን ሃላፊው ነጋሽ ተክሉ እጁን አውጥቶ፣ በበረከት ስምኦን ላይ ያለኝን አመለካከት እንድናገር ጠየቀኝ።

ባጭሩ መለስኩ፣

"በረከት ስምኦን ብቁ የአመራር ችሎታ አለው ብዬ አላምንም"

ተናግሬ ሳበቃ ተጨማሪ ወይም የተቃውሞ አስተያየት ያቀረበ አልነበረም። አሰፋ ማሞ መድረኩን እንዴት ማስቀጠል እንደነበረበት ግራ ሲጋባ እያስተዋልኩት ነበር። ነጋሽ ጥያቄውን ያነሳው በበረከት ላይ ያለኝን ቅሬታ ስለሚያውቅ ነበር። ከወራት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በፊት ነጋሽ ከመኖሪያ ቤቱ ምሳ ጋብዞኝ ስንጨዋወት በወሬ ወሬ በበረከት ላይ የነበረኝን ቅሬታ እንደዋዛ አጫውቼው ነበር። በግል ያጫወትኩትን መድረክ ላይ ሲያነሳው በውነቱ ሳልደነግጥ አልቀረሁም። ያልጠበቅሁት ነበር። ቢሆንም ወደ ሁዋላ ማፈግፈግ ስላልቻልኩ በግልፅ ተናገርኩ። በርግጥ የበረከት የብቃት ችግር በአብዛኛው ካድሬ ይታወቃል። ስራውን በፕሮግራም መምራት የሚቸገር፣ እየተሳደበ ራሱን ለስድብ የሚያጋልጥ አይነት ሰው ነበር። በስልክ እያወራኸው ሳለ ጆሮህ ላይ ይዘጋብሃል፣ አንተም ታዲያ ጆሮው ላይ ስትዘጋበት ቅር አይለውም። ብዙዎች "የወታደር ጠባይ አለው" ይሉታል። ከተኮሰ በሁዋላ የሚፀፀት፣ ከትእግስት ጋር የማይተዋወቅ ስሜታዊ መሆኑ ይታወቅለታል። በወቅቱ በሃላፊነት ላይ ከነበርነው መምሪያ ሃላፊዎች ካንዱ ጋር በስልክ ሲነታረኩ ቆይተው፣ መምሪያ ሃላፊው በጣም ተናዶ፣ "አትጨማለቅብኝ!" ብሎ ጆሮው ላይ ሲዘጋበት እኔ እዚያው ነበርኩ። ከማእከላዊ ኮሚቴው በታች ያለነው ካድሬዎች በረከት እንዳያጠቃን እንሰጋ እንደሁ እንጂ፣ ክብር የሚሰጠው አልነበረም። ይህ እየታወቀ ነጋሽ ያን ጥያቄ ለኔ ለይቶ ማንሳቱ፣ ከጅርባ የተደገሰልኝ ነገር መኖሩን ቢጠቁምም የነበረኝ ምርጫ የማምንበትን ባደባባይ መድገም ብቻ ነበር።

ከሚናቁት የኢህአዴግ የግምገማ ባህርያት አንዱ በግል የተጨዋወትከውን ያለፈቃድህ ወደ መድረክ የማምጣቱ ልማድ ነበር። አንዱ መጠጥ ላይ ተጠግቶህ የቻለውን ያህል ይሰማህና የተናገርከውን ሁሉ መዝግቦ ግምገማ እስኪመጣ ይጠብቃል። ከዚያም አንተ የረሳኸውን ጭምር ቃል በቃል ያነብልሃል። ሚስት ባልዋን ግምገማ ላይ ታጋልጣለች። ተኝተው ያወሩትን ስብሰባ ላይ ይዘከዝኩታል። የጨውና የበርበሬ ጉዳይ ሳይቀር ይነሳል። ባለስልጣኖች ሊያስወግዱ የፈለጉትን በድርጅታዊ ስራ ድራማ ይሰሩበታል። በአንድ ወቅት ሱሌይማን ደደፎ የተባለውን የኦህዴድ አባል እንዳስወግድ በረከት የቤት ስራ ሰጥቶኝ ነበር። ይኸው ዛሬ ደግሞ የበረከት የእጅ አዙር ጥቃት በነጋሽ በኩል እኔው ላይ ብቅ አለ። በረከት ባደባባይ አክብሮቴን እገልፅለት ዘንድ፣ አለያም ተናግሬ እንዲለይልኝ እንደፈለገ ገምቻለሁ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በዚያን እለት ለምሳ ስንወጣ አሰፋ ማሞ ጠርቶ እንዲህ አለኝ፣

“ስለ በረከት ስትጠየቅ መናገር አልነበረብህም። ጥያቄው አግባብ አለመሆኑን ልገልፅ ስል ቸኩለህ ተናገርክ። ዛሬውኑ ሄደህ በረከትን አናግረው። አለበለዚያ ላንተ ጥሩ አይሆንም።” ሲል መከረኝ።

ምክሩን ግን ሳልቀበል ቀረሁ።

ከወራት በሁዋላ ከአሰፋ ጋር ስንገናኝ፣

“በረከትን አናገርከው?” ሲል ጠየቀኝ።

“ምን ብዬ ነው የማናግረው?”

“በግምገማው ላይ የተናገርከውን በተሳሳተ መንገድ ሊተረጉመው ይችላል”

“የሚተረጎም ነገር የለበትም። ቃላቶቹ ግልፅ ናቸው”

ሲያመነታ ቆየና፣

“በረከት ቂመኛ ነው። ዝም ብሎ አይተውህም። ሄደህ ይቅርታ ጠይቀው...” አለ።

ለሰከንዶች ያህል ተክዤ ሳስብ ቆየሁና፣

“በረከት ቂመኛ መሆኑን አላውቅም። የአመራር ችሎታው ደካማ መሆኑን ግን አንተም ታውቃለህ። ይቅርታ የምጠይቅበት ምክንያት አይታየኝም” አልኩ።

አሰፋ ፈገግ አለና፣

“ብልህ ትመስለኝ ነበር” ሲል ተነፈሰ።

በውነቱ ከኢህአዴግ ጋር መቆየቱ አድክሞኝ ነበር። ተሰላችቼም ነበር። ብዙውን ጊዜ ከድርጅቱ ተለይቼ በነፃነት መኖር የምጀምርበት ቀን በጣም ይናፍቀኝ ነበር። ስደትን አልፈልገውም። ከኢህአዴግ ካምፕ ወጥቼ በሰላም መኖር ደግሞ የሚታሰብ አልነበረም። ለበረከት ጥቃት ያጋልጠኛል። ማጣፊያው እያጠረኝ መንታ መንገድ ላይ መዋገጥ ልማዴ ሆነ።

ከደርግ ውድቀት በሁዋላ በሃገሪቱ የስልጣን ክፍፍል ሲደረግ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት የፕሬስ መምሪያ ሃላፊ የነበረውን የሙሉጌታ ሉሌን ወንበር የተረከብኩት እኔ ብሆንም፣ በተጨባጭ ግን ከሙሉጌታ ጋር ሲነፃፀር የሱ ግማሽ ነፃነት እንኳ እንደሌለኝ በማሰብ እገረም ነበር። ይኸው በተራ ስብሰባ ላይ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በረከትን የተመለከተ የግል አስተያየቴን በመግለፄ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ መግባቴን አሰፋ ማሞ እየነገረኝ ነበር። ይህ ሁኔታ ውስጣዊ አለመረጋጋት ያስከተለብኝ ሲሆን፣ ለዚህ አለመረጋጋት በወቅቱ ስም ፊልጌ አጥቼለት ነበር። ከአያሌ አመታት በሁዋላ ግን አንዳርጋቸው ፅጌ "ነፃ ያልወጡ ነፃ አውጪዎች" የሚል መፅሃፍ ሲያሳትም የመፅሃፉ ርእስ በወቅቱ ለተሰማኝ ስሜት ተገቢ ገላጭ ቃል ሆኖ አገኘሁት። ለጥቂት አምባገነኖች የስልጣን እድሜ መራዘም ስንል ግማሽ እድሜ ላባከንነው ሁሉ ግሩም ስያሜ ነበር..

* * *

ለሁለት አመታት ያህል በፕሬስ መምሪያ ሃላፊነት ካገለገልኩ በሁዋላ የፋና ዴሞክራሲ አሳታሚነት ስራዬን ብቻ በሙሉ ጊዜ ያዝኩት። እፎይታ መፅሄትና ፕሬስ መምሪያን ደርቤ መስራቱም በእጅጉ ከብዶኝ ነበር። በረከት የመፅሄቱን ስራ ብቻ አጠናክሬ እንድሰራ አዘዘኝ።

በዚያው ሰሞን ይመስለኛል፣ በእፎይታ መፅሄት ላይ የሽፋን ዘገባ (Cover Story) ጥላሁን ገሰሰን አትሜ መፅሄቱን በገበያ ላይ ባዋልኩ በነጋታው በረከት እብድ ሆኖ ደወለልኝ። በስልክ የቁጣ ውርጅብኙን ሲያዘንብብኝ በዝምታ አዳመጥኩት። መፅሄቱን ከተመለከተ በሁዋላ ደውሎ እንደሚቆጣ እየጠበቅሁ ስለነበር የበረከትን ስሜታዊ ንግግሮች በትእግስት አስተናገድኩ። በረከት በጥላሁን ገሰሰ ቃለ - መጠይቅ ያን ያህል ሊናደድ የበቃበትን ምክንያት አውቅ ነበር። ከጥቂት ወራት በፊት ጥላሁን ገሰሰ፣ ታማኝ በየነና ንዋይ ደበበ ታምራት ላይኔን የሚያጥላላ ዝግጅት በአዲስ አበባ ስታድየም አቅርበው ስለነበር የመንግስት ሚዲያዎች ሶስቱ አርቲስቶች ላይ የጥቃት ዘመቻ በማካሄድ ላይ ነበሩ። ይህ በሆነበት ሁኔታ "እፎይታ" መፅሄት ጥላሁን ገሰሰን ቃለመጠይቅ አድርጋ፤ የጥበብ ስራዎቹንም በማድነቅ ስታትም በረከት ይህን ሊታገስ አልቻለም። ብዙውን ጊዜ በእፎይታ የሚታተመውን ቢያንስ የሽፋን ዘገባውን አማክረው ስለነበር የጥላሁንን ጉዳይ ግን በሚስጥር ይዤ በማተሜ ሆን ብዬ የፈፀምኩት ድርጊት እንደሆነ ማመኑ ነበር ይበልጥ በረከትን ያበገነው።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነበር። የጥላሁን ገሰሰ ቃለ - መጠይቅ ከመታተሙ ሁለት ሳምንታት በፊት አንድ ቀን የደህንነት ሚንስትሩ ክንፈ ገብረመድህን ደወለልኝና ወደ ቢሮው ባስቸኳይ ጠራኝ። ክንፈ ቢሮ ስደርስ ጥላሁን ገሰሰን ከክንፈ ቢሮ ተቀምጠ አገኘሁት። ክንፈ ባሞሩ የጥላሁን ገሰሰን በጎ ገፅታ የሚያሳይ ጋዜጣዊ ስራ እንድሰራ ጠየቀኝ። ስጋቴን ለክንፈ ነገርኩት።

"የሚዲያው አቅጣጫ ሶስቱን አርቲስቶች ማውገዝ መሆኑን አውቀሃል?"

"አውቃለሁ" አለ ክንፈ "... ስህተት ነው። ያንን ማስተካከል እንፈልጋለን"

"ስህተት ከሆነ ለምን በሃገሪቱ ሚዲያዎች ሁሉ አይታረምም?"

"ስሜታዊ ነገሮች አሉበት"

በእኔ በኩል ደስታዬን አልቻልኩትም። እንደማንኛውም ዜጋ ጥላሁን ገሰሰን እንደ ጥሩ አርቲስት እወደዋለሁ። በዘመነ ደርግ ለሰራዊት የዘፈነውን በማስታወስ ጥላሁንን ማውገዝ በፍፁም የተከበረ ስራ ሊሆን እንደማይችልም አምን ነበርና ክንፈ የጠየቀኝን በደስታ ተቀበልኩት። ይህን ስንነጋገርም ጥላሁን ገሰሰ አብሮን ነበር፤ ይሰማናል! እኔና ጥላሁን ስልክ ተለዋወጥንና በቀጠሮ ተለያየን። በመጨረሻ ግን ክንፈ አንድ ነገር አስጠነቀቀኝ።

"ይህ ግን ምስጢር ነው"

"ገብቶኛል!" አልኩት።

ታምራትና በረከት አርቲስቶቹን በማውገዙ ስራ የተጠመዱበት ጊዜ ስለነበር፤ የምስጢሩ መነሾ ገብቶኛል። እና ቃለመጠይቁ ታተመ።

በረከት የቁጣ ስሜቱን መቆጣጠር አልቻለም። በስልክ ውርጅብኙን ሁሉ አሸከመኝ። በነጋታው ክንፈ ሲደውልልኝ፤ በረከት ስሜታዊ ሆኖ እንደሚናገር በመግለፅ ምሬቴን ስነግረው፤ እሱ ከት ብሎ እየሳቀ፣ "ቻለው እንግዲህ!" ሲል አፅናናኝ። ሆኖም በዚያ ምክንያት ከበረከት ጋር ያለመግባባታችን እያደገ ሄደ። በረከት ሰበብ እየፈለገ ያበሳጨኝ ገባ።

አንድ ቀን ደወለና "መፅሄታችሁ ዜሮ ነው!" አለኝ።

በዚያን ወቅት ግን በርግጥ መፅሄታችን ዜሮ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አልነበረም። ከሰላሳ ሺህ በላይ ኮፒ በየጎዳናው እንሸጥ የነበረ ሲሆን፤ የጥላሁን ገሰሰን ምስል የያዘውንም እትም 45 ሺህ ኮፒ በሁለት ቀናት ሸጠን ጨርሰን ገንዘባችን ባንክ ገብቶ ነበር።

በጥላሁን ገሰሰ ጣጣ በተፈጠረ አለመግባባት የበረከት አለቅነት ወደ አለምሰገድ ገብረአምላክ እንዲዛወር በመደረጉ፤ ከበረከት ጋር የነበረን እለታዊ ግንኙነት እየቀረ መሄድ ጀመረ። ለአመታት ያህልም በግብጥዎች ላይና በተለያዩ ቦታዎች ካልሆነ በቀር የምንገናኝበት አጋጣሚ በእጅጉ ቀነሰ። መደዋወላችንም አስፈላጊነት አልነበረውም።

(ያለምንም ማስተባበል አለምሰገድ ጥሩ አለቃ ነበር። ለማመሰገንም ሆነ ለመውቀስ አይቸኩልም። ሰዎች ከስህተታቸው ሊማሩ ይችላሉ ብሎ ከልብ ያምናል። ስህተቶች ውስጥ ራሱን ለመደባለቅም ፍርሃት የለበትም። ችግር ስታቀርብለት የመፍትሄ አሳብ ታቀርብ ዘንድ በቅድሚያ እድሉን ለራስህ ይሰጥሃል። ወሬ አቀባዮቹ የሚነግሩትን በቀጥታ አይቀበልም። በዘዴ ያነሳልህና አስተያየትህን ይጠይቅሃል። በረከት ስምኦን ከላይ ያሉትን አንዳቸውንም አያውቃቸውም። ትክክል የመሆንን እድል በፍፁም አይሰጥህም። ባለሃይሉ ሁሉ በተቃውሞ ስለሚወድቅብህ እንደሚገነደስ ግንድ ትፈራዋለህ። የመሪነት ተሰጥኦ የሌላቸው ሰዎች የመሪነትን ከዘራ የጨበጡባቸው ጊዜያት ምንጊዜም በጨለማነት ዘመን ሲጠሩ ይኖራሉ። አለቃህ እንድታከብድድለት ካስቸገረህ በአንድ ነገር ርግጠኛ መሆን አለብህ። አለቃህ አምባገነን ብቻ ሳይሆን አጎብዳጅም ጭምር ነው።)

...ጊዜው አሁን ትዝ ባይለኝም ታምራት ላይኔ ከታሰረ በሁዋላ አንድ ቀን ደወልኩለትና፣

"የትግሉ ወቅት ስነግጥሞችን በጋዜጣችን ለማተም ፈልጌ ነበርና ምን ይመስልሃል?" ስል አማከርኩት። የበረከት፣ የህላዌ፣ የመዝሙርና የታምራት ላይኔ ግጥሞች በእጄ ይገኙ ስለነበር እነዚያን ማለቴ መሆኑን በረከት ተገንዝቦ እንዲህ አለኝ፣

"የኔን እንዳታትም! የሌሎቹን ግን እንደፈለግህ"

'የሌሎቹን እንደፈለግህ' ሲለኝ 'አትመው' ማለቱ አለመሆኑ ግልፅ ነው። ታምራት ላይኔ ስለታሰረ ታምራትን ልጠይቀው አልችልም። መጠየቅም አስፈላጊ አልመሰለኝም።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስሙ ባይጠቀስም የታምራት ላይኔን ውብ ስነ -ግጥሞች "ሶረኔ" በተባለ የስነግጥም መድበል ላይ አትሚያቸው ስለነበር የታምራትን ስም በማከል እነዚያን ማተሙ ክፋቱ በፍፁም አልታየኝም ነበርና በእፎይታ ጋዜጣ ላይ የታምራትን ስነ ግጥሞች በተከታታይ ማተም ጀመርኩ። በዚያን ጊዜ በረከት ወደ አሜሪካ ለስራ ተጉዞ ነበር። አራተኛውን የታምራት ስነግጥም እንዳተምን ከአንባብያን አስደናቂ ምላሽ ማግኘት ጀመርን። ሰዎች የታምራትን ግጥሞች ማድነቅ ጀመሩ። ታዋቂው አርቲስት እሸቱ ጥሩነህ ደውሎ ነገረኝ።

"ግጥሞቹን ከጋዜጡቹ ላይ እየቀደድኩ ማጠራቀም ጀምሬያለሁ! ውብ ናቸው! በጣም ውብ!"

አምስተኛው ስነግጥም ታትሞ እንደወጣ ግን ከኢህአዴግ የፕሮፓጋንዳ ክፍል አብርሃ ማንጁስ ደውሎ ስሜታዊ ሆኖ ያነጋግረኝ ጀመር፣

"ግጥሞቹን ለምንድነው የምታትመው?"

"ስነግጥሞች ስለሆኑ ነዋ..."

"ማን ፈቀደልህ እንድታትማቸው?"

"ፈቃድ እንደሚያስፈልግ አላወቅሁም ነበር፣ ሆኖም ለበረከት አንስቼለት ነበር"

"በረከት ነው የፈቀደልህ?"

"በረከት ፈቀደልኝ አላልኩም!"

"ግጥም ከፈለግህ የሌላ ሰው ግጥም ለምን አታትምም? የታምራት ጠበቃዎች ግጥሙን ሆን ብለን ታምራትን ለመጉዳት በማተም ላይ እንዳለን በማንሳት ከሰውናል"

"ታምራት ከተከሰሰበት ጉዳይ ጋር ግጥሞቹን ምን የሚያያይዝ ነገር ይኖረዋል? እንዲያውም ስዎች ግጥሞቹን እየወደዷቸው ነው"

በዚህ አነጋገሬ አብርሃ ማንጁስ እሳት ሆነ፣

"በሙስና የተጨማለቀ ሰው ግጥም ማተም ለምን አስፈለገ? በረከት ነው ያዘዘህ?"

"በረከት አዘዘኝ አላልኩህም"

"'ለበረከት ነግሬዋለሁ' ብለሃል"

"የበረከትንም ግጥም ማተም ፈልጌ ስለነበር ደውዬ አነጋግሬው ስለነበር፣ በእግረ መንገድ ግን የታምራትንና የህላዌ ዮሴፍን ስነ ግጥሞች እንደማትም ነግሬው ነበር። እሱ በወቅቱ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በገጣሚነት መታወቅ እንደማይፈልግ በመግለፅ የሱን ግጥሞች እንዳላትም ከልክሎኛል...”

ከጥቂት መወዛገቦች በሁዋላ የታምራት ግጥሞች መታተም እንዲቋረጥ አዘዘኝ። በቀጣዩ የጋዜጣችን እትም የታምራት ስነግጥሞች ሲቋረጡ ጥቂት የማይባሉ ስልኮች ወደ ቢሮአችን እየተደወለ ተወቀስን። በዚያው ሰሞን መዝሙር ፈንቴን አገኘሁትና ስለዚሁ ጉዳይ ስናወጋ፣ በግጥምቹ መታተም ታምራት አለመደሰቱን እንደሰማ ነገረኝ። ሆኖም ይህን ማመን አቃተኝ። ግጥሞቹ እንዲታተሙ ታምራት ፍላጎት እንደነበረው እኔ በግሌ አውቃለሁ። ከአንደበቱም የሰማሁት ነው። በእጅ ፅሀፈቱ የፃፋቸውን ግጥሞች ረቂቅ ደብተርም ራሱ ነው የሰጠኝ። ዛሬ ታምራት ለምን የግጥሞቹን መታተም ይቃወማል? ከአብርሃ ጋር ባደረግነው ጭቅጭቅ የተረዳሁትም የተገላቢጦሽ ነው። እነ አብርሃ ማንጁስና ተወልደ ወልደማርያም ምን አስበው ነበር ይሆን? የዚህን ሚስጥር ከፊል ምክንያት በጨረፍታም ቢሆን የተረዳሁት በረከት ከአሜሪካ እንደተመለሰ ነበር። ደውሎ እሪታውን አቀለጠው፣

“መቼ ነው የታምራትን ግጥም አትም ያልኩህ?”

ለአብርሃ እንደዚያ እንዳላልኩት ላስረዳው እየሞከርኩ ሳለ ግን ስልኩን ጆሮዬ ላይ ዘጋብኝ። ቆየሁና ግን ተክሌ ተክላይ ከተባለ ታጋይ አንዳንድ ሚስጥሮችን ሰማሁ። በረከት ከነ ተወልደና አለምሰገድ ቡድን ጋር በከረረ አለመግባባት ላይ ኖረዋል። ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይቆራቆሱ ይዘዋል። ሌላው ቀርቶ በረከትና አለምሰገድ የእግዚአብሄር ሰላምታ እንኳን እንደማይለዋወጡ አጫወተኝ። የሚደንቀው ደግሞ በረከትና መለስ በግልባጩ እጅና ጓንት ሆነው ነበር። በኤርትራ አጀንዳ ውስጥ ውስጡን የሚብላላ ሽኩቻ ስለመኖሩም Indian ocean news letter ፅፎ አነበብኩ። የታምራት ግጥሞች የንትርክ ሰበብ እንጂ ዋና ምክንያት ሊሆኑ እንደማይችሉም ተረዳሁ።

በነገራችን ላይ በረከት በገጣሚነት መታወቅ አይፈልግም እንጂ ጥሩ ጥሩ ግጥሞችን ይቋጥራል። ትዳርና ፍቅር ክልክል በነበረበት በትግሉ ወቅት በረከት በሚስጥር አፍቅሮዋት ለነበረችው ለዛሬዋ የልጆቹ እናት የሚከተሉትን ስንኞች ቋጥሮላት እንደነበር “በደጉ ዘመን” አጫውቶኛል። ስነ ግጥሟን ያለ በረከት ፈቃድ ይፋ በማድረጌ ግን በረከት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደማይቀየመኝ ተስፋ አደርጋለሁ፣ "መቸስ ምን እንላለን" ነበር ርእሷ።

እንደተፋቀርን ላንተያይ - ሳንተያይም ልንፋቀር፣
እንደመናን ካ'ለም ነገር - ከሰሙ ተራ ሰንባረር፣
በታጋይ ህግ ተገድበን - በአጉል ስርአት ሰንጠፈር፣
መቸስ ምን እንላለን - በተሰፋ ከመሞት በቀር፤

በረከት መቸም ትግሉን እያማረረ ይህን ስንኝ እንዳልቋጠረ ግልፅ ነው። ስሜትን የማሸነፍ ከባድነትን ለመግለፅ እንጂ። ታዲያ ትዳርና ፍቅር የሚያግደውን ህግ አንስተው ተጋብተው ወልደዋል። በረከት ይህቺን የረሳትን ግጥም ሳስታውሰው ምን ይሰማው ይሆን?

በቅንጅት ተሸንፈን - በባዶ ሜዳ ሰንዘረር፣
መቸስ ምን እንላለን - ስልጣንን ከመልቀቅ በቀር፤

ለማለት አለመቻሉን ያምናል ብዬ እንኳ አልመኝም።

...የሆነው ሆኖ ከበረከት ጋር አለመግባባታችን እየከረረ ሄደ። *'የቡርቃ ዝምታ'* በሚል ርእስ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄዎች ላይ መሰረት አድርጌ የፃፍኩት ታሪክ ቀመስ ልቦለድ መፅሃፍ ከታተመ በሁዋላ በረከት አነበበው። 'ኢህዴን' የተባለው ድርጅት የህወሃት 'የአማራ ክንፍ' መሆኑ ከመገለፁ በቀር የተተረከለት ገድል አለመኖሩን በማንሳት በረከት ወቀሰኝ። ቢሮው ለሌላ ጉዳይ የሄድኩ እለት እንዲህ ሲል ነበር ቅሬታውን የገለፀልኝ፣

"ሻእቢያ አራት ታንክ ይዞ ስለገባ ያን ሁሉ ገድል ጫንክለት! የኢህዴንን የትግል አስተዋፅኦ ግን ሙሉ በሙሉ ዘለልከው"

እኔ ግን ከእውነታው አልራቅኩም። በረከት ስምኦንና ሳሞራ የኑስ በደብረዘይት መንገድ የገባውን የኢህአዴግ ሰራዊት እየመሩ መግባታቸውን ፅፌያለሁ። በረከት፣ አዲሱ፣ ተፈራ፣ ህላዌ ወዘተ በግለሰብ ደረጃ ያላቸውን አስተዋፅኦ እንደ አስፈላጊነቱ በ"*የቡርቃ ዝምታ*" ትረካ ውስጥ አካትቼ ነበር። ኢህዴን እንደ ድርጅት ግን ከጨዋታ ውጭ እንደነበር የሚካድ አልነበረም። በአጠቃላይ ትግሉ የጠየቀው መስዋእትነት ሲገመገምም ታሪካዊ ቦታ እንዳልነበራቸው እነ ገብሩ ታረቀ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የሚፅፉትን ማንበቡ ብቻ በቂ ይሆናል። ዋና ተዋናዮቹ ህወሃትና ሻእቢያ መሆናቸውን በረከት እያወቀ ሊወቅሰኝ መሞከሩ አስገርሞኛል። ኢህዴን በውጊያ በተሳተፈባቸው ጥቂት አውደ ውጊያዎችም ቢሆን የራሱን የካርታ ንድፍ ስሎ አያውቅም። በህወሃት ወይም በሻእቢያ ካርታ ላይ ተለጣፊ ነበር። *"ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ"* የተባለውን መፅሃፍ ስንሰራም ኢህዴንን ማሳተፍ እየፈለግን የረባ ገድል ለማግኘት እንቸገር ነበር። ህላዌ ዮሴፍ የኢህአፓ አባል ሳለ ካጋጠመው ገድል ያለፈ ያገኘነው ቀልብ የሚስብ ታሪክ አልነበረም። የሆነው ሆኖ *"የቡርቃ ዝምታ"* ታሪክ ቀመስ ልቦለድ እንጂ የድርጅት ልሳን አለመሆኑን ለበረከት ያን ቀን አላስታወስኩትም። አዳምጨው ሳበቃ ለአስተያየቱ ምስጋናዬን ገለፅኩለት።

(የኢህዴንን ተለጣፊነት ከሚያሳዩ አብነቶች መካከል የልደት በአሉን የሚያከብርበት እለት አንዱ አስረጅ ነው። ህወሃት የካቲት 11፣ ኢህዴን (ብአዴን) ደግሞ ሀዳር 11 የምስረታ በአሎቻቸውን ያከብራሉ። ህወሃት 11 ቁጥርን የመረጠው ባጋጣሚ ሳይሆን ትግራይ ላይ ከአይን ግራና ቀኝ የሚበጣውን 11 ቁጥር የሚመስል የመለያ ምልክት በማሰብ መሆኑ ይታወቃል። የኢህአዴግ ሬድዮ ሃላፊ የነበረው ገብረመስቀል፣ "አማሮች 11 ቁጥር ስለሚሉን ይለይላቸው በሚል 11 ቁጥርን ለልደት በአላችን መረጥናት እንጂ ህወሃት በትክክል የተመሰረተበት እለት የካቲት 11 አይደለም" ሲል አውግቶኛል። ኢህዴኖች በተመሳሳይ የህወሃት ቅርንጫፍ መሆናቸውን ሊጠቁም የሚችለውን 11 ቁጥር ለልደት በአላቸው እንዲመርጡ ሲጠየቁ 'አይመለከተንም' ማለት አለመቻላቸው ከማስገረም በላይ ያስገርማል።)

* * *

ከበረከት ጋር አለመግባባታችን እያደገ ሄደ።

ጎንደር ሄጄ ስመለስ ኤፎይታ መፅሄት ላይ በፃፍኩት ሪፖርትም በረከት መቆጣቱን ሰማሁ። ሆኖም በወሬ ወሬ እንጂ ለኔ አልደወለልኝም።

በርግጥም ጎንደር ሄጄ ከልብ አዝኜ ነበር የተመለስኩት። የበረከት ፀሃፊ በጉዞው ወቅት አብራኝ ነበረችና አንድ ቀልድ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ነገረችኝ። ጊዜው ህዳር 11 ነበር - የብአዴን ልደት፣

"የጎንደር ህዝብ ምን እያለ እንደሚቀልድ ታውቃለህ?"

"ምን ይላል?"

"ዳሸን ቢራ ለምንድን ነው የማትጠጡት ሲባሉ?"

"እሺ!?"

"አምስት ዳሸን ቢራ ከጠጣህ ትግርኛ መናገር ትጀምራለህ"

አልሳቅሁም!

ቀልዱን ቀደም ብዬ ሰምቼው ነበር። ይህ የጥላቻ ስሜት ሊዳብር የቻለው በወያኔ መሪዎች ይሉኝታ ማጣት ምክንያት ነበር። ዳሸን ቢራ ቀደም ሲል ትግራይ ሊቋቋም ነበር የታሰበው። ትግራይ ከተቋቋመ ግን መሃል ሃገር ገበያ ሊያጣ ይችላል ተብሎ ተሰጋና ፕሮጀክቱ ወደ ጎንደር ዞረ። ጎንደር ላይ ፋብሪካውን የገነባው በህወሃት ንብረትነት የሚታወቀው ሱር ኮንስትራክሽን ነበር። አሳዛኙ ነገር ፋብሪካውን ለመገንባት ወዛደሮች ሳይቀር ከትግራይ ነበር የመጡት!

ጎንደሬ በዝምታ ታዘባቸው።

እየዘፋፈነባቸውም ቆየ።

ቢራው በደረጃው ድንቅና በዋጋው ርካሽ ነበር። ምርቱ ሲጀመር ግን የጎንደር ህዝብ ቢራውን እንደ መርዝ ቆጠረው። ተጨማሪ ከፍሎ ሜታ ቢራ መጠጣቱን ቀጠለ። እንደምንሰማው ዛሬም ዳሸን ቢራ የመጨረሻ ምርጫ እንደሆነ አለ።

ጎንደር ሰነበትኩና የህዝቡን ብሶት ሁሉ መፅሄታችን ላይ አትሜ አወጣሁ። በጣም የገረመኝ ትዝብቴ ቢኖር ትግራይና ጎንደር ላይ የተሰቀሉት መፈክሮች ልዩነት ነበር።

ትግራይ ላይ ስለ ልማት ብቻ ነበር የሚነበበው። የዝናብ ውሃ ስለ ማቀብ፣ ስለ ግድብ ስራ፣ በጥፍርህ ስለ መገንባት። ጎንደር ላይ ግን ትምክህተኞችን የሚያወግዙ መፈክሮች ነበር የተጥለቀለቁት። ጎንደር ላይ ልማትን የተመለከተ ለመድሃኒት እንኳ አንድ መፈክር አጣሁ። ትግራይ ላይ ሎደሮች ሲጭኑና ሲቆፍሩ ተመልክቼ ነበር። ጎንደር ላይም በርግጥ ሎደሮችን አይቻለሁ። መሃል ከተማው ላይ የሎደሩ አካፋ ላይ አንድ ሰአሊ ቆሞ መፈክሮችን ሲፅፍ ነበር ያየሁት። ትምክህተኞችን የሚያወግዝ መፈክር! ብዙ ብር የተከፈለው ሰአሊ "መፀዳዳትን ከድመት ተማሩ" የሚል መፈክር መሃል ጎንደር ላይ ፅፎ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሲያደማምቅ አይቼ በሃዘን አልቅሼያለሁ። በርግጥ አላለቀስኩም። ነገሩ ግን ያስለቅሳል። ከድመት መማር! ጎንደር ላይ ስራ አልነበረም። ጫት በቀን 20ሺ ኪሎ እንደሚሸጥ ነበር ያረጋገጥኩት። የጎንደርን ታሪክ የማያውቅ በዚህ ዜና ላይደነገጥ ይችላል። ጎንደር በብሶት ስትንገበገብ ትውልና ታድር ነበር። አዝማሪ ቤት ስገባ ይህንኑ ተረዳሁ። ብሶቶችና ቁጭቶች በየአዝማሪ ቤቱ እየተንተከተኩ ነበር። ዋነኛው ብሶት የሁመራ ጉዳይ ነበር። የሁመራ ከተማ ከነሰሊጥ ምርትዋ ከህወሃት ለተሰናበቱት ሃያ ሺህ ታጋዮች መሰጠትዋ ጎንደርን እንደ እግር እሳት እያቃጠላት ነበር። የጎንደር አዝማሪም፣

ዴሞክራሲ ማለት - ዳቦ ወይስ ባዶ፣
አለቀለት ጎንደር - ተንዶ ተንዶ፣

እያለ ብሶቱን እንደ አባይ ወንዝ ሲያንፏቀቁው ያመሽ ነበር። ጎንደርና ጎንደሬ መቀለጃ መሆናቸውን የተረዳሁት በተለይ የአዲሱ ለገሰ ሹፌር ለፓርላማ ሲወዳደርና ለጤና ቢሮ ሃላፊ ጎረምሳ የጤና ባለሙያ ሲሾም ነበር። የትግራይ የጤና ቢሮ ሃላፊ በወቅቱ ዶክተር መስፍን የነበሩ ሲሆን፤ በሃገሪቱ ውስጥ ከፕሮፌሰር አስራት ቀጥሎ ታዋቂ ባለሙያ ነበሩ። ለእናታቸው ቀብር እንኳ ጊዜ ያጡ ትጉህ ሰራተኛ ነበሩ። የአማራው ክልል የጤና ቢሮውን ለጎረምሶች የተወላቸው ብቃት ያለው ባለሙያ አጥቶ አለመሆኑ ግልፅ ነው። በረከት ግን ታማኝ ሰው አጣ። እናም ተወለድኩባት የሚላት ጎንደር እንኳ በፍቅር ልቡን መንካት አቃታት!

* * *

ከበረከት ጋር አለመግባባታችን እየጨመረ ሄደ።

የአማራው ልማት ማህበር ቢሮ በእሳት ጋየ። ዜናውን ስናጣራ እሳቱ ከሂሳብ ክፍል መነሳቱን ደረስንበት። ጋዜጣችን ላይ ፃፍነው። "ሂሳብ ክፍል ወጥ ቤት ሆነ እንዴ?" ስንል ጠየቅን። አያያዝንና "ወይስ ቁጥሮች ተጋጭተው እሳት ፈጠሩ?" ይህን ዜና ትንታኔ እንደፃፍን ከአማራው ክልል አንባቢዎቻችን የምስጋና ደብዳቤ ጎረፈልን።

በረከት አልደወለም። ማድፈጡ ገባኝ። ጊዜ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እየጠበቀልኝ እንደሆነም ጠረጠርኩ። በረከት ስሜታዊና ቁጡ ነው። ይህንን አንብቦ መታገሱ አስገርሞኝ ሰነበትኩ። በመቀጠል ህወሃት ለሁለት ተሰነጠቀና የኔ የቅርብ አለቃ የነበረው አለምሰገድ በነፋስ ፍጥነት ተባርሮ፣ በረከት በቦታው ተተካ። ይህ በተከሰተ በሶስተኛው ቀን በረከት ደወለልኝ፣

"የተፈጠረውን ሰምተሃል?" ሲል ጠየቀኝ። 'አገኘሁህ!' አይነት ነበር አነጋገሩ።

"ሰምቻለሁ!"

"ከእንግዲህ ከእኔ ጋር ነው ግንኙነት የምትፈጥረው!"

"ገብቶኛል!"

"እኔ ሳላውቅ አንዳችም ገንዘብ እንዳይንቀሳቀስ። የተለየ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ፅሁፎችን ለማተም ከፈለግህ በቅድሚያ እኔ ማየት አለብኝ! ተግባባን?"

"ገብቶኛል!" አልኩ።

(...ደርግ ሲወድቅ የሃገሪቱን የሚዲያ ተቋማትና የፕሮፓጋንዳውን ስራ የተረከቡት አለምሰገድና በረከት ነበሩ። እኛም ካድሬዎች ከስር ተከለከልን። በፕሮፓጋንዳው ዘርፍ አለምሰገድ ንጉስ ነበር። በረከት ስምኦን ደግሞ የአልጋወራሽነትን ሚና ነበር የሚጫወተው። በየመስሪያ ቤቱ ብአዴኖች የአልጋወራሽነትን ቦታ በብዛት አግኝተዋል። ውጭ ጉዳይ ላይ ዶክተር ተቀዳ አለሙ የሰዩም አልጋወራሽ ሲሆን፣ አዲሱ ለገሰ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ የመለስ አልጋወራሽ ሆኖ ተቀምጦአል። ህላዌ ዮሴፍም ከምርጫ 97 በፊት በአርከበ ኡቅባይ ስር አልጋወራሽ ነበር። ለተመልካች እንዲመች ነውንጂ አልጋውን እንደማይወርሱት ግን ያውቃሉ። በአልጋወራሽነት ከተቀመጡት የብአዴን ሰዎች እስካሁን በለስ ቀንቶት አልጋውን ለመውረስ የበቃው በረከት ብቻ ነው።)

እነሆ አለምሰገድና በረከት ተፎካካሪ ነገስታት ሆነው ለአስር አመታት ከመሩን በሁዋላ አለምሰገድ ከአንጃው ጋር ሲወገድ በረከት ስልጣኑን ጠቀለለ።

በደወለልኝ ሰሞን ለስራ ጉዳይ በረከት ቢሮ ሄጄ በወቅታዊው የህወሃት መከፋፈል ዙሪያ ስንነጋገር በረከት አቋሜን ለመፈተሽ ነው መሰለኝ፣

"አለምሰገድ ብቻውን ቀርቶአል። ሚስቱ ብቻ ናት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የምትደግፈው" አለኝ።

"ልክ ነህ!" ስል አረጋገጥኩለት።

በረከት እውነቱን ነበር።

በአለምሰገድ ስም መማል ይቀራቸው የነበሩ ካድሬዎች አብዛኞቹ ከአንጃው መወገድ በሁዋላ ሌሊቱን ሰልፋቸውን ከበረከት ጋር አስተካክለው ነበር ። በሰልፍ ማስተካከሉ ሂደት መገረም አላደረብኝም። በደንብ እንተዋወቅ ነበር። ባጋጣሚ እኔ እንደ ሌሊት ወፍ የሁለቱም ወገን አልነበርኩም። ወላጆቼ ኤርትራውያን በመሆናቸው ብቻ ከበረከት ጋር የሚያግባባ አጀንዳ እንደሚኖረን የሚያምኑ ነበሩ። በአንፃሩ አለምሰገድ በኔ ጉዳይ በተደጋጋሚ የሚቀርቡለትን ክሶች ችላ ይላቸው ስለነበር አለምሰገድ እኔን በተለየ ሁኔታ እንደሚንከባከብ በማመን ቅሬታቸውን የሚገልፁም ነበሩ። ሁለቱም ግምቶች የተጋነኑ ነበሩ።

የኢትዮ - ኤርትራ ግጭት እንደተከሰተ ከበረከት ጋር በከረረ ሁኔታ ለመጋጨት በቅተን ነበር። የኢትዮጵያና የኤርትራን ግጭት በተመለከተ በበረከት ፀሃፊነት ኢህአዴግ ያወጣውን መግለጫ በተሳሳተ መንገድ ጋዜጣችን ላይ አተምነውና በረከት በቁጣ አበደ። ቢሮው ጠርቶኝ፣

"ይህ ስህተት እንዴት ተፈጠረ?" ሲል ጠየቀኝ።

"የእርማት ስህተት ነው" አልኩ።

"ሻእቢያን የሚጠቅም ስህተት ነው የተሰራው"

"እንዳልኩህ ስህተት ነው። ማረሚያ እናወጣለን።"

በርግጥ ስህተቱ ቀላል አልነበረም።

"የሻእቢያ ርምጃዎች ጦርነቱን ያቃርበዋል" የሚለው አረፍተነገር በስህተት "ጦርነቱ ተቃርቦአል" ተብሎ ነበር የታተመው። ስህተቱን የፈፀመችው ዘውዳለም የተባለች ሪፖርተር ብትሆንም ያንን ለበረከት መንገር አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም ነበር።

በረከት ስሜታዊ ሆኖ ይጮህ ቀጠለ።

"ጦርነቱ ተቃርቦአል የሚለው ቃል ጦርነት ማወጅ ነው። ሻእቢያ ይህን እንደ መረጃ ይዞ ሊጠቀምበት ይችላል!"

"ስህተቱን ልናርመው እንችላለን። ሌላ የሚደረግ ካለ እዘዘኝ!" አልኩ።

"ጋዜጣው ባስቸኳይ ተሰብስቦ ይቃጠል!" አለ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“መልካም!” ብዬ ከመቀመጫዬ ስነሳ፣

“አልጨረስኩም” አለ።

ተመልሼ ቁጭ አልኩ።

“ሃገሪቱ ባስጨናቂ ሁኔታ በተያዘችበት በዚህ ወቅት ስህተቱ ለምን አላማ እንደተፈፀመ ንገረኝ?”

“ምን ለማለት ፈልገህ ነው?” ስል እኔም ስሜታዊ ሆኜ ጠየቅሁት፣ ”...ሆን ብዬ ሻእቢያን ለመጥቀም እንዳደረግሁት እየነገርከኝ ነው?”

“እሱንማ አንተ ንገረኝ!” ሲል ጮኸ!

ጥቂት በዝምታ ቆየሁና፣

“የፈለግኸውን ርምጃ መውሰድ ትችላለህ” ብዬ ቢሮውን ለቅቄ ወጣሁ።

በቀጥታ ወደ አለምሰገድ ቢሮ ነበር የሄድኩት። የሁለቱም ቢሮዎች በአንድ ህንፃ ላይ ነበሩ። በንዴት እየተቃጠልሁ ከአለምሰገድ ቢሮ ገባሁ። ችግሩን አስረዳሁት። ከበረከት ጋር የተነጋገርነውን ነግሬው ሳበቃ፣

“በሻእቢያ ደጋፊነት የምትጠረጥሩኝ ከሆነ ስራውን ባቆም ይሻላል” አልኩ።

አለምሰገድ ግንባሩን እንደቋጠረ፣

“እኛ በሻእቢያ ደጋፊነት አንጠረጥርህም!” አለ።

አያያዘንም አከለበት፣

“በርግጥ ባለፈው ጊዜ የመለስ ቃለመጠይቅ ላይ እንድትገኝ ተነግሮህ ሰበብ ፈጥረህ ቀርተሃል። ይሄ ግልፅ አይደለም”

ፋታ ወሰደ። ምላሽ ሳልሰጠው በመቅረቴም ቀጠለ፣

“...የሆነው ሆኖ በረከትም ኤርትራዊ ነው። የኤርትራዊነት ጉዳይ ሁሌታችሁን ለማጋጨት ምክንያት አይሆንም። ችግራችሁን ራሳችሁ ተነጋገራችሁ ፍቱ!” አለኝ።

ከአለምሰገድ ቢሮ ከወጣሁ በሁዋላ ንግግሩን አብላላሁት። አለምሰገድ የኔንና የበረከትን ፀብ አላመነው ይሆናል ብዬ ጠረጠርኩ። ይህ ጥርጣሬዬ ግን ስህተት መሆኑን ቆይቼ አረጋገጥኩ። ይህም በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ወቅት አለምሰገድ ያለምንም ጥርጣሬ የጦርነት ምስጢሮችን እንዳውቅ ያደርግ የነበረ ሲሆን፣ አንዳንድ የግል ጋዜጦች ከሻእቢያ ጋር በማቆራኘት ስሜን የማጠቋቆር ቅስቀሳ ሲያካሂዱ አለምሰገድ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ፊፅሞ ጆሮውን አያውሳቸውም ነበር።

...የሆነው ሆኖ ከአንጃው መወገድ በሁዋላ ብዙም አልቆየሁ። በመጨረሻው ምእራፍ ላይ በምገልፅላችሁ ምክንያት ሃገሪቱን ጥዬ ኮበለልኩ። እኔና በረከት ሁለታችንም ኢትዮጵያ ውስጥ የተወለድን ኤርትራውያን ነን። ቢሾፍቱና ጎንደር። እንዲህ ከርመን እንዲህ ተለያየን።

* * *

በረከት ብዙ ጊዜ ጤና እንደሚያጣ ሚዲያዎች ይዘግባሉ። እኔ በስደት በምኖርባት ፕሪቶሪያ ከሁለት ጊዜ በላይ ለህክምና እየመጣ ታክሟል። በአጋጣሚ የበረከት አስታማሚ የነበረችውን ጥቁር ደቡብ አፍሪቃዊት ነርስ አውቃታለሁ። ከአበሾች ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበራት። አንድ ቀን ሬስቶራንት ውስጥ ተገናኝተን ስናወጋ እንደዋዛ ርእሰ ወሬውን ጀመርኩ፣

"በረከት ስምኦን የሚባል ኢትዮጵያዊ እናንተ ዘንድ እየታከመ መሆኑን ሰማሁ"

"ኦ! በረከት! በጣም ጥሩ ሰው ነው። በአማርኛ ሰላምታ አቀረብኩለትና በጣም ተገረመ" ስትል ወሬውን በስሜት ቀጠለች።

"አዎን ልክ ነሽ! በጣም ጥሩ ሰው ነው። የሩቅ ዘመዴም ነው" ካልኩ በኋላ አያይዤ፣ "ለመሆኑ ምንድነው በሽታው?" ስል ጠየቅኋት።

እያመነታች ምላሽ ሰጠቺኝ፣

"...Do you know about anxiety neurosis?" ዘግየት ብላ አከለችበት "...It is some kind of mental problem."

በረከት ለአእምሮ ህመም ስለበቃበት ምክንያት ነጮቹ ደቡብ አፍሪቃውያን የበረከት ሃኪሞች ምን እንደሚሉ አላውቅም። በተመሳሳይ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሃኪሞች ካብራሩልኝ በመነሳት ግን፤ በረከት በምርጫ 97 የፕሮፓጋንዳ ዲዛይነር ሆኖ በሰራበት ጊዜ የገጠመው ሽንፈት ለህመም ከዳረጉት ምክንያቶች አንዱ ሊሆን ይችላል። የበረከት የፕሮፓጋንዳ እቅዶችና ንድፎች ለተቃዋሚዎች እድል የሰጠ፣ ተቃዋሚዎች ገንነው እንዲወጡ ያደረገ፣ አቅጣጫውን የሳተ ተብሎ የተገመገመ ሲሆን፤ ግምገማው በረከትን በእጅጉ እንዳዳከመው ሰምቻለሁ። ከዚህ ሌላ በረከትን ለአእምሮ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ጭንቀት ሊዳርጉ የሚችሉ ሶሶት አቢይ ጉዳዮችኝ ማንሳት ይቻል ይሆናል። ኤርትራዊ ሆኖ ሳለ ኤርትራውያንን በሚያባርር ኮሚቴ ውስጥ መስራቱ ሊጠቀስ የሚችል ነው። የአማራ ድርጅት መሪነቱ ተቀባይነት ባጣ ቁጥር ለማንነት ቀውስ መዳረጉ ሌላው ምክንያት ሊሆን ይችላል። በምርጫ 97 ቡግና ወረዳ ላይ መሸነፉና በሚያሰቃይ መንገድ ምርጫውን ለማጭበርበር መገደዱም ለዚህ ህመም ሊዳርግ የሚችል ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ባለሙያዎቹ ይስማሙበታል።

* * *

ለመጨረሻ ጊዜ በረከት ስምኦንን ያየሁት በደቡብ አፍሪካ ዋና ከተማ ፕሪቶሪያ Beatrix Street ላይ ሁለታችንም ቀይ መብራት በያዘን ጊዜ ነበር። የዝሆን ቅርፅ ባለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ማርቸዲስ መኪና ውስጥ፣ መስኮቱን ከፍቶ፣ ከኋላ ዘና ብሎ ተቀምጦ እንደተለመደው አሸፈ ገፅታ ባለው ሁኔታ ከልቡ እየሳቀ ነበር። የስምኦን ልጅ! በረከት!....

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 5 -
በደም የተገኘ ዙፋን

ግማሽ ክቡር - ግማሽ ኑጋዴ፣
ግማሽ ታማኝ - ግማሽ ወንበዴ፣
ግማሽ ሩህሩህ - ግማሽ መደዴ፣
ከሆነ ቡድን ጋር፣
ይቻላል ወይ አብሮ መኖር?

(ግጥም - አሌክሳንደር ፑሽኪን)
- አያልነህ ሙላቱ እንደተረጎመው -

ምርጫ 84 ሊካሄድ አስር ቀናት ብቻ በቀሩት ጊዜ፣ አለምሰገድ ገብረአምላክ የፕሮፓጋንዳው ክፍል ከፍተኛ ካድሬዎችን ሰብስቦ አስደንጋጭ መርዶ ነገረን። አለምሰገድ የተናገረውን ቃል በቃል ስለመዘገብኩት፣ ከማስታወሻ ደብተሬ እንደወረደ ላስነብባችሁ፣

"...በደም የተገኘ ድላችንን በካርድ አናስረክብም። በመላ ኦሮሚያ በቂ ዝግጅት የለንም። ኦህዴድ ተጠናክሮ አልወጣም። ሳምሶናይታቸውን አንጠልጥለው ለመጡት አነጎች በምርጫ ስም አገሪቱን አናስረክብም። ወይ ምርጫው ይሰረዛል፣ አለያም አነግ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከምርጫው መውጣት አለበት!"

በዚያን ቀን ምሽት ጋዜጠኛ ለነበሩ ሁለት ጓደኞቼ ደወልኩና ራት አንድ ላይ ተመገብን። አለምሰገድ የተናገረውን ቃል በቃል ስነግራቸው በመደመም አዳመጡኝ። በጉዳዩ ላይ በርጋታ ከተወያየንበት በሁዋላም አንድ ድምዳሜ ላይ ደረስን። ኢህአዴግ በምንም ተአምር እዚህች ሃገር ላይ ዴሞክራሲን ለመገንባት ፍላጎት እንደሌለው አረጋገጥን። በኢትዮጵያ ላይ የርስበርስ ጦርነቱ ሊቀጥል እንደሚችል ለመተንበይም ነቢይ መሆን አላስፈለገንም።

አለምሰገድ ያንን ከመናገሩ ሶስት ወራት በፊት ተወልደና ሌንጮ በመሩት የኢህአዴግና የኦነግ ካድሬዎች የጋራ ስብሰባ ላይ ተገኝቼ ነበር። በጣም ገንቢ ውይይት ነበር የተካሄደው። በሃገሪቱ ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን በጋራ መስራት እንደሚገባን ተስማምተን ነበር ስብሰባው የተቋጨው። የኦነግና የኢህአዴግ ካድሬዎች በአንድ አዳራሽ ተሰብስበን ስንነጋገርም የመጀመሪያችን ነበርና ተስፋ አድርገን ነበር። ከስብሰባው በሁዋላ አብረን ከሰነበትነው ኦነጎች አንዳንዶቹን እየቀረብን፣ "ይህን የመገንጠል አላማችሁን ብትሰርዙ እኮ አብሮ መስራት ይቻላል" ስንላቸው፣ "በዚህች አገር ላይ መኖር እንደምንችል፣ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንደሚገነባና ህዝባችን በነፃነት የራሱ ጌታ ሆኖ እንደሚኖር፣ አስተማማኝ ዋስትና ካገኘን ምን ፍለጋ ነው የምንገነጠለው?" ይሉን ነበር።

በሻይ ሰአት አብረውኝ የነበሩት ኦሮሞዎች ጥልቅ የሆነ ስሜታቸውን ነግረውኛል።

"...ለመገንጠል የምንመኘው የዚህች አገር መሪዎች ጭንቅላት ተቀይሮ፣ የህዝቦችን መብት የሚያከብሩበት ጊዜ እንደማይመጣ ተስፋ በመቁረጥ ነው'ንጂ አንድ መሆን ታላቅነት መሆኑ ጠፍቶን አይደለም። 'በጉልበት ከተፈጠረ አንድነት ውስጥ በባርነት ከመኖር፣ ተበታትኖ በነፃነት መኖር ይሻላል' ብለን ነው። ብሄራዊ ጭቆና ምን ያህል አሰቃቂ እንደሆነ እናንተ አይገባችሁም። አታውቁትም! አልቀመሳችሁትም! የራስን ባህል ማጣት፣ በራስ ቋንቋ መጠቀምን መከልከል፣ ራስን የመሆን መብት ማጣት፣ በባእዳን ገዢዎች መተዳደር፣ ከሁሉም በላይ ሃገርህን ተነጥቀህ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዜግነት ዝቅ መደረግ፣ እንዴት ፈታኝ እንደሆነ እናንተ አይገባችሁም..."

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንዲህ ያለ ነገር ሲናገሩኝ አባባላቸውና ከገፅታቸው ላይ ያነበብኩት ስሜት ዛሬም ድረስ ትናንት ያየሁት ያህል ይሰማኛል። ምናልባትም የቡርቃ ዝምታ የተባለው መፅሃፌ የተፀነሰው በዚያን እለት ሊሆን ይችላል። በዚያን እለት የቢሾፍቱ ገበሬዎችን በማስታወስ የኦነግ ካድሬዎችን ስሜት በትክክል ልገነዘበው ችያለሁ። ኦነግን የጭራቆች ስብስብ አድርጎ የማየቱን የወቅቱ ዝንባሌ እንደማልጋራው ለራሴ ማረጋገጥ የቻልኩ ሲሆን፣ ኦሮሞዎች የገዛ ሃብታቸው ጠላት እንደሆነባቸውም ማስተዋል ችዬ ነበር።

ይህ በሆነ በሶስተኛው ወር ግን ይኸው አለምሰገድ ከላይ የገለፅኩትን ዱብእዳ መርዶ አርድቶን አረፈው።

አለምሰገድ እቅጩን ከተናገረባት ከዚያች ስብሰባ በሁዋላ በብዙ የኦሮሚያ አካባቢዎች የኦነግ ካድሬዎች ይገደሉ ጀመር። ከተገደሉት መካከል ሁለቱን በጋራ ስብሰባው ወቅት ተዋውቂያቸው ነበር። ይህን ኦነጎችን እያሳደዱ የመግደሉን ዘመቻ በዋነኛነት የመሩት ሳሞራ፣ አባዱላ፣ ኩማና ታደሰ ወረደ ነበሩ። ተወልደ በመራው፣ ለኢህአዴግ ካድሬዎች ብቻ በተዘጋጀ አንድ ስብሰባ ላይ አንዱ የህወሃት ኮማንደር ኦነጎች ላይ እንዴት ጥቃት እንደሚፈፅሙ አብራርቶ ነበር። ምሽት ላይ በየአውራጃው ኦነጎች ስብሰባ ሲቀመጡ፣ የታጠቁ ሲቪል ለባሾች፣ አስቀድሞ የታቀደ ግርግርና ተኩስ ይጀምራሉ። ይሄኔ በግድያ የሰለጠኑ የመከላከያ አባላት በገላጋይነት እየገቡ፣ የተመረጡ ኢላማዎችን ለይተው ይመታሉ። እነማን እንደሚገደሉ ቀደም ብሎ በስብሰባ የሚወሰን ሲሆን፣ የዚህ አይነቱ ኦፕሬሽን ለሁሉም ግልፅ አይደረግም። በወቅቱ "የኦነግ ሰዎች ቢተኩሱባችሁም አትተኩሱባቸው" ሲል ኢህአዴግ ለታጠቁ አባላቱ በይፋ በጥብቅ አዝዞ የነበረ ቢሆንም፣ በጎን ደግሞ ልዩ ኮማንዶዎች ኦነጎችን እያሳደዱ ይፈጁ ቀጥለው ነበር። የኦነግ ፅህፈት ቤቶች እየተዘጉ፣ ሰነዶችን መዝረፍ የእለት ተእለት ዜና ሆነ። በየአካባቢው ስለሚገደሉ የኦነግ ካድሬዎችና አመራር አባላት ዜና ሲመጣ፣ በቀጥታ እንዳይተላለፍ ጥብቅ መመሪያ ተሰጠን። ኦነግ መግለጫ ሲልክ፣ በቅድሚያ በኢህአዴግ አመራር አባላት ይነበብና ምላሽ ይዘጋጅለታል። ከዚያም ሁለቱንም ጎን ለጎን እናቀርባቸዋለን። ኢህአዴግ ለመግለጫዎቹ አፀፋዊ ምላሽ መፃፍ ካልቻለም፣ የተቃዋሚዎቹ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መግለጫዎች ይታገዳሉ።

በወቅቱ ኦነግ የኢህአዴግ ቁጥር አንድ ጠላት ሆኖ ነበር። የኦሮሞ ህዝብ ከገበሬ እስከ ምሁር፣ ተገልብጦ ኦነግን ደግፎታል። ኦህዴድ የእንቅልፍ በሽታ እንዳጠቃው ከብት ፈዞአል።

የኢህአዴግ አመራር መንታ መንገድ ላይ ቆሞ ነበር። ቢቻል ኦህዴድን ማጠናከር፣ ካልተቻለ ኦነግን ማላመድ (Domesticate) ማድረግና ጭንግፍ እየሆነ ያስቸገረውን ኦህዴድን ማስወገድ የሚሉ አማራጮችን ይዞ እንቅልፍ አጥቶ እየሰራ ነበር። ሆኖም ኦህዴድን ማጠናከርም ሆነ፣ ኦነግን ማላመድ የማይቻል እየሆነ በመሄድ ላይ ነበር። 'ኦነግን ማላመድ" የሚለውን አሳብ አጥብቆ የሚገፋበት መለስ ነበር። የአፄ ምኒልክ ቤተመንግስት ስለማይበቃቸው እንጂ፣ መለስና ሌንጮ የሚግባቡ አይነት ነበሩ። ተወልደና አለምሰገድን የሚከተሉ የህወሃት አመራር አባላት ግን፣ "ኦነግ የሚቀየር ተፈጥሮ የለውም" ሲሉ የደመደሙ፣ በግልባጩም፣ "ኦነግ በጥይት ተደብድቦም ቢሆን መጥፋት አለበት" የሚል ፋሺስታዊ አመለካከት የያዙ ነበሩ።

አዲስ አበባ ከመያዙ አንድ ወር አስቀድሞ በተደረገ አንድ ትልቅ የመጨረሻው የበረሃ ስብሰባ ላይ፣ ስለቀጣይ ስራዎቻችን መመሪያ ሲሰጥ፣ "በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የብዙሃን ፓርቲ ስርአት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እንቅፋት ስለሚሆን ተቀባይነት አይኖረውም" የሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሶ እንደነበር አስታውሳለሁ። የብዙሃን ፓርቲ ስርአት የማካሄዱ ጉዳይ ኢህአዴግ ላይ በግድ የተጫነበት በለንደኑ ውይይት ወቅት ነበር።

ደርግ በወደቀ በአመቱ ምርጫው ሲቃረብ፣ ኦነግ ከሚሊዮን በላይ እጩዎችን ሲያቀርብ፣ ኦህዴድ በሺህዎች እንኳ እጩዎችን ማሰባሰብ ተቸግሮ፣ በርካታ አባላት ቤተሰቦቻቸውን እንዲያቀርቡ መመሪያ መሰጠቱን አስታውሳለሁ። በዚህ ጊዜም ኢህአዴግ ወደ ተፈጥሮአዊ ማንነቱ ለመመለስ ተገደደ። ሚዲያዎች ኦነግን በማውገዙ ስራ ተጠመድን። ዜናዎችና ሃተታዎች በበረከት፣ በአለምሰገድና አንዳንድ ጊዜም በመለስ እየተፃፉ ይሰጡናል። የኢህአዴግ ፅህፈትቤትና ቤተመንግስት ከኦነግ ጉዳይ ሌላ አጀንዳ አልነበራቸውም። "ኢትዮጵያ ማለት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ኦሮሚያ ማለት ናት" የሚል አባባል አለ። ኦሮሚያ ደግሞ አነግ ሆና ቁጭ አለች። "በደም የተገኘ ድል - በምርጫ ካርድ አይወሰድም!" መሪ መፈክር ሆነ። አነግ ራሱን ከምርጫ እንዲያገል መካሪ ሽማግሌዎች እንደተላኩበት ጭምር ሰምቻለሁ። አነግ ግን እየተተኮሰበትና እየተገደለ የምርጫ ዝግጅቱን ገፋበት። አነግ ላይ የማስፈራራትና የመምታት ዘመቻ ከታወጀበት ከዚያን እለት ጀምሮም ማታ ማታ እንደሁኔታው እየተፈራረቁ አለምሰገድና በረከት ያገኙን ነበር። አነግ ከምርጫው ራሱን ሊያገል እንደሚችል ግምታቸውን ይነግሩናል። ራሱን ካላገለለ ግን ምርጫውን ለመሰረዝ ተወስኖአል።

ቀናት ቀናትን እየተኩ የመጨረሻዋ እለት ዋዜማ ደረሰች። ምርጫው ነገ ማለዳ ሊካሄድ ነው። ከምሽቱ ሁለት ሰአት ከመሆኑ በፊት፣ የሚዲያው ሃላፊዎች ሁሉ በየቢሮአችን እንደ ወታደር በተጠንቀቅ ላይ ነበርን።

እነሆ! የሚጠበቀው የምስራች ዜና ደረሰ።

በረከት በደስታ ብዛት ራሱን ወደ ተላላኪነት አውርዶ፣ ዜናውን ይዞ ወደያለንበት እየበረረ መጣ! "አስቸኳይ ዜና እየመጣ ነው!" የሚል መልእክት ጆሮአችንን አቃጠለው።

ታላቁ ዜና እጄ ላይ ገባ!

"አነግ ከምርጫ 84 ራሱን አገለለ!!"

ታላቅ ደስታ!

ስሜትን መቆጣጠር አልተቻለም። እፎይታ ሆነ! የኩባና የአሜሪካንን የሚሳይል ግንባታ ውጥረትን የሚያስታውስ እፎይታ። አንዱ ለሌላው ይደውላል፣

"ሰማህ ዜናውን!?"

"ሰማሁ! በጣም ደስ የሚል ነው!"

ተክሉ ተክላይ የተባለ የስራ ባልደረባ ነበረኝ። አስተሳሰቡ እንደ ስሙ የተምታታበት ነው። ተክላይ ተክሉ ወይም ተክሉ ተክላይ። እስከዛሬም ስሙ ከየት እንደሚጀምር አይገባኝም። ቀለል ለማድረግ አታክልቲ ቢባል ይቀል ነበር። ብቻውን የሚያስብ ምስኪን ሰው ነው። መቼም ቢሆን ምንም ነገር አይገባውም። የኦነግን ከምርጫ መውጣት ዜና ሰምቶ ደወለልኝና እንዲህ አለኝ፣

"አነግ ራሱን ከምርጫ ያገለለው ህዝቡ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደማይመርጠው አውቆ ነው! በርግጥም ከሚዋረድ ራሱን ከምርጫ ማግለል ይሻለዋል"

ጨዋታው የገባቸው፣ ነቃ ነቃ ያሉ የህወሃት ካድሬዎች ደግሞ እንዲህ አሉ፣

"ተጨንቀን ነበርኮ! ዜናውን ስንሰማ ተነፈስን!"

የተሻለ አቅም ያላቸው እንዲህ ሲሉ አስጠነቀቁ፣

"መቼም ቢሆን መዘናጋት የለብንም! ኦነግን ማዳከም እንጂ ማጥፋት አይቻልም!"

በርግጥ ኦነግ "ራሱን ከምርጫ አገለለ" ከሚለው ይልቅ፣ "እንዲያገል ተደረገ!" ቢባል ወደ እውነቱ መቃረብ በተቻለ። ታዋቂዋ የትግርኛ አባባል ለኦነግ ራሱን ማግለል ገላጭ ነበረች። ውሻእ አይትበሎ፣ ከምዝወፅእ ግበሮ። ሲተረጎም "ውጣ አትበለው፣ እንደሚወጣ አድርገው" ማለት ነበር። የይስሙላው ምርጫ በተካሄደ ሰሞን ከበረከት ስምኦን ጋር ተገናኝተን ስናወራ ግን ለማስመሰል አልሞከረም። በግልፅ እንዲህ አለኝ፣

"ህዝቡ ተሳስቶ የኦነግን ጠባብ አላማ ተቀብሎ ወደ ገደል ሲሄድ ዝም ብለን ልናይ አንችልም! መደረግ የነበረበት ተደርጎአል!"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 6 -

አስቸጋሪ የስራ ቀናት

አናት ላይ ቁጭ ሲል - ቅቤን ብንጠይቀው፣
"ገፍተውኝ ነው"ይላል - አናት ላይ የወጣው፣
ይህማ ደንብ ነው - ይህማ በጎ ነው፣
ያልተገፋ ወተት - ቅቤ እንደማይወጣው፣
የወተት ልጅ እርጎ - የእርጎ ልጅ ቅቤ ነው፤

(ግጥም - ወሰን ይሄይስ)

በ1984 አንድ ቅዳሜ ማለዳ እንደተለመደው ቢሮ ገብቼ የታተሙትን ጋዜጦች ማገላበጥ ጀመርኩ። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ የመጀመሪያ ገፅ ላይ "ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ወደ ኒውዮርክ ሄዱ" የሚል ዜና ተፅፎ ስመለከት ዜናው የተሳሳተ ይሆናል ብዬ ልገምት ስለማልችል ወደ ውስጥ ገፆቹ ዘለቅሁ።

የባለስልጣኖች መሄድና መምጣት ከአሰልቺ ዜናዎች አንዱ ነበር። ዛሬም ድረስ የአፍሪቃ ሚዲያዎች ይህን በመሰሉ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ዝባዝንኬ ዜናዎች ተጨናንቀው ስመለከት አላነባቸውም። የዜና ርእሱ የሚጓዙበት አጀንዳ ሳይሆን መጓዛቸው መሆኑ ነበር የሚያሰለቸኝ። ብዙውን ጊዜ ለምን እንደሚጓዙ ቢገለፅም የሃሰት ነው። 'ተጋብዘው' 'ለስራ ጉብኝት' 'ለስብሰባ' ይባላል። ሄዱ! መጡ! ተቀበሉ! አነጋገሩ! እና ምን ይጠበስ? በተለይ የኛ ባለስልጣናት ጉዞ ካደረጉ 'ምክንያታቸው ከሁለት ነገር አያልፍም' እያልን እንቀልዳለን። ይህም አንድም ብድር ጥየቃ፣ ካልሆነ ብድር ለማሰረዝ።

ሞገስ ሃብቱ የተባለ ገጣሚ 'የአፍሪቃ መንግስታት' በሚል አጭር ስነግጥሙ ይህንኑ የብድርና የስረዛ ልመና ታሪክ እንዲህ ሲል ጥሩ አድርጎ ተርቦታል፣

የአፍሪቃ መንግስታት - በጣም ይገርማሉ፣
ባሀር ማዶ ሂደው - ብር ይበደራሉ፣
ካጡ ምን ይደረግ - ይበደሩ ደሀና፣
ምንድን ነው በይፋ...
ዱቤ ወሰድን ማለት - እንደ በጎ ዜና!?

በዚያን ቀን ማለዳ ጋዜጦችን እያገላበጥሁ ሳለ የቀጥታው መስመር ስልክ ጮኸና ሳነሳው በረከት ስምኦን ነበር። በጣም ተቆጥቶ ነበር። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ የፊት ገፅ ላይ የታተመው ዜና ነበር ያስቆጣው፣

"ታምራት ወደ ኒውዮርክ አልሄደም። ከኒውዮርክ የመጣ እንግዳ ተቀብሎ ነው ያነጋገረው! ሆን ተብሎ የተደረገ ነው!" አለ።

አስተያየት መስጠት ተቸገርኩ። በርግጥ በረከት እውነት አለው። 'ኒውዮርክ መሄድና ከኒውዮርክ የመጣ እንግዳ መቀበል" የተራራቁ ናቸው። ስህተት አይመስልም። ስህተት አይደለም ካልን ደግሞ፤ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ስሜህ መኮንን ይህን ዜና በመስራት ምን ጉዳት ሊያመጣ ይችላል?

በረከት ስለ ጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ማንነት ጠየቀኝና ጥቂት ማብራሪያ ስነግረው፣

"ሆን ብሎ ያደረገው ነው" አለኝ።

"ላነጋግረውና እንዴት ስህተቱ ሊፈጠር እንደቻለ አጣርቼ ልንገርህ?" አልኩት።

"ማነጋገር አያስፈልግም! አባርረው!" ሲል አዘዘኝ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስልኩን ከማስቀመጤ ፀሃፊዬ በውስጥ መስመር ደውላ ስሜነህ መኮንን ሊያነጋግረኝ እንደሚፈልግ ነገረችኝ።

"አስገቢው" አልኳት።

ስሜነህ እንደተለመደው ሲጋራውን እየማገ በረጋ ሁኔታ ወደ ውስጥ ዘለቀና ተቀመጠ። እንደ በረከት እኔም መናደድ እንዳለብኝ አስታወስኩና ቶሎ ብዬ ግንባሬን ቋጠርኩ። የተናደድኩ መሰልኩ። እውነት ለመናገር ግን ዜናው አላናደደኝም። "ታምራት ላይኔ ወደ ኒውዮርክ ኮበለለ" ቢል ኖሮ በርግጥ በተናደድኩ ነበር።

ስሜነህ መኮሳተሬን ተመለከተና ፈገግ አለ። እንዳልተናደድኩ ያወቀብኝ መሰለኝና ይበልጥ ግንባሬን ቋጠርኩ።

"ስህተቱን አይተኸው ይሆናል" አለ ጋዜጣው ላይ በጣቱ እየጠቆመ "በውነቱ ስህተቱ እንዴት እንደተፈጠረ ለማብራራት አልችልም"

ስሜነህ ተረጋግቶ ሲጋራውን እየማገ ይስቅ ጀመር። ግንባሬን ጨምድጄ መቆየቱ ስለደከመኝ ማስመሰሉን አቆምኩ። ምሽት ላይ ዜና የሚሰሩ ጋዜጠኞች በስራ መሃል ወጣ እያሉ እንደሚቀማምሱ አውቅ ነበርና፣

"ቀማምሰህ ነበር እንዴ?" ስል ጠየቅሁት።

"ብዙም አይደለም! በርግጥ ደክሞኝ ነበር። ራሴ ነኝ ዜናውን የሰራሁት። ጠዋት ሳየው በጣም ነው የገረመኝ"

ስሜነህን አሰናበትኩትና ወደ በረከት ደውዬ ላሳምነው ሞከርኩ። ስሜነህን የማላባርረው ለራሴው ስል ነበር። ከጋዜጠኛነቱ ባሻገር በርካታ የበጀትና ርዳታ ፍለጋ ነክ ስራዎችን የሚሰራልን ስሜነህ ነበር። ከብዙ ልፍለፋ በሁዋላ በረከት የማባረሩን አሳብ ለወጠና "ሙሉ ደሞዙን ቅጣው!" ሲል አዘዘኝ። በኔ ስልጣን ደረጃ ሙሉ ደሞዝ መቅጣት እንደማልችል ሳብራራለት፣

"ምን ያህል መቅጣት ነው ስልጣንህ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ግማሽ ደሞዝ!"

"በል ግማሹን ቅጣው!"

ዘግየት አልኩና ሌላ ሰበብ ፈጠርኩ፣

"እንኳን ግማሹ ተቆርጦ፣ የመስሪያ ቤቱ ሙሉ ደሞዝም ለኑሮ የሚበቃ አይደለም። ደሞዙን ከምንነካበት ብናባርረው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ይሻላል። ደሞዙ ተቆርጦ ስራ ሊሰራ አይችልም።"

በረከት ገና ድሮ ተዳክሞና ቀዝቅዞ ስለነበር፣

"የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ፃፍለት" አለኝ።

ስሜነህን ቢሮዬ ውስጥ ቡና ጋብዤ ቅጣቱን ነገርኩት፣

"የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንደተፃፈልህ ይቆጠር!"

"የቃል ማስጠንቀቂያ ይበዛብኛል!" አለ እየሳቀ፣ ሲጋራውን ማግ ማግ አደረገናም ቀጠለ፣

"እንዲህ ባለ ስህተት መረበሽ የለባችሁም። ወደፊትም ብዙ ሊያጋጥምህ ስለሚችል አለቆችህን ማሳመን አለብህ!" አያያዘናም ቀጠለ፣ "...በደርግ ጊዜ ብዙ ስህተት እንሰራ ነበር። ለምሳሌ 'ጓድ መንግስቱ ሃይለማርያም ከባለቤታቸው ጋር በተገኙበት' የሚለው ዜና በስህተት 'በተኙበት' ተብሎ ታትሞ ያውቃል! ምንም የተፈጠረ ነገር አልነበረም። የጎሹ ወልዴ ፎቶግራፍ ደግሞ 'በቅርቡ ከመሃይምነት ነፃ የወጡ' ተብሎ ታትሞ ያውቃል። እንደ ተራ ስህተት ታልፎአል። ሌላም ብዙ ተከስቶአል! ይህን መቋቋምና ለሚቆጡ አለቆች ማስረዳት ያንተ ድርሻ ነው" ሲል መከረኝ።

...ከሁለት ወራት በሁዋላ ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ ወደ አምቦ ሲጓዙ መኪና ተገልብጦ የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው የሚገልፅ ዜና Ethiopian Herald ጋዜጣ ላይ ከጀርባ የክልሎች አጫጭር ዜና ላይ ታትሞ ወጣ።

ያን ጊዜ ግን ፕሬስ መምሪያ ቀውጢ ሆነች።

በአንድ ታጋይ የደህንነት አባል የሚመሩ አምስት ፖሊሶች ይህን ስህተት የሰራውን ጋዜጠኛ አስረው ለመውሰድ ከኔ ቢሮ ተገኙ። በእውነቱ አሁንም ዜናውን ያላየሁት ሲሆን፤ ፖሊሶቹ ለምን እንደመጡ እንኳ መገመት አልቻልኩም ነበር። እኔን ሊያስሩ የመጡ ነበር የመሰለኝ። የመጡበትን ጉዳይ እንዳወቅሁ ፈጥኜ ጋዜጣውን ገለበጥሁና አየሁት። ከአጫጭር የክልል ዜናዎች አካባቢ አንድ ስህተት ተሰርቶአል።

ዜናው እንዲህ ይል ነበር፣

የመጀመሪያው መስመር ላይ "ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ" የሚለው ይነበባል። ሁለተኛው መስመር ላይ እንዲህ ሲል ዜናው ቀጥሎአል፣ "...ወደ አምቦ ይጓዝ የነበረ አውቶብስ ተገልብጦ ሶስት ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል"

ስህተቱ ግልፅ ነበር። አረፍተ ነገሩ አይገጥምም።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

'ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ' የሚለው ከሌላ ዜና ተቆርጦ በስህተት እዚህ የአምቦ የመኪና አደጋ ዜና ላይ መለጠፉን መረዳት ቀላል ነበር።

ቀና ብዬ አየሁዋቸው!

ወንጀለኛውን ጋዜጠኛ አስረው ለመሄድ ቸኩለዋል። ጋዜጠኛው መለስ ላይ የግድያ ሙከራ ያደረገ ያህል እንደቆጠሩት ቁጣቸው ይመሰክር ነበር። ጋዜጠኛውን አስረው ከማን እንደተላከ፣ ስንት እንደተከፈለው ለመመርመር እንደቸኮሉ አጠያያቂ አልነበረም።

"ስህተቱ እንዴት እንደተፈጠረና ማን እንደፈፀመው አጣርቼ እስክመለስ ምን ይምጣላችሁ? ቡና? ሻይ?" አልኩ።

የፀጥታው መስሪያ ቤት ባልደረባ፣

"ክንፈ ነው የላከን! የታዘዝነው ጋዜጠኛውን አስረን እንድንሄድ ነው"

"ገብቶኛል! ሁለት ደቂቃ ጠብቁኝ ነው ያልኳችሁ!"

ተስማሙ!

ደውዬ በቀላሉ ክፍሎም አድጎይን መጠየቅ በቻልኩ። የምናገረውን ግን እንዲሰሙ አልፈለግሁም። ስለዚህ ቢሮዬ ትቼያቸው ወጣሁ። ከቢሮዬ ስወጣ ፀሃፊዬ፣

"ምንድነው የተፈጠረው?" ስትል በስጋት ጠየቀችኝ።

"ቀላል ነው" ካልኳት በሁዋላ "...ቡና ሻይ ቢያቸው" ብዬ ወደ ክፍሎም አድጎይ ቢሮ በረርኩ።

ክፍሎምም ስህተቱን ገና ማየቱ ነበር።

በአስር ደቂቃ ውስጥ እርማት ሲካሄድባቸው የነበሩትን ወረቀቶች ሰብስበን፣ ስህተቱን የሰራውን ወጣት አራሚ ቁጭ አድርገን ስህተቱ እንዴት እንደተፈጠረ መረመርን።

ምንም ምርመራ የሚያስፈልገው አልነበረም። ዜናው ቃል በቃል ይተርጎም ቢባል እንኳ መለስ ዜናዊ አደጋ እንደደረሰበት አያረጋግጥም። በመሰረቱ ፕሬዚዳንቱ ወደ አምቦ ለመሄድ አውቶብስ አይጠቀምም። የጋዜጣው አንባቢዎች ደግሞ ጥቂት ዲፕሎማቶች ናቸው። እነሱ ከፈለጉ መለስ ዘንድ ደውለው ማጣራት ይችላሉ። መፍትሄው የፕሬስ መምሪያን የለቀማና የሌይ አውት ስራ በኮምፒዩተር ደረጃ ይሰራ ዘንድ ማሳደግ እንጂ አንድ ጀማሪ አራሚን ማሰር አልነበረምና ለክፍሎም ጥብቅ መመሪያ ሰጠሁት፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ስህተቱን የሰራውን ልጅ ስም ማንም ሰው ለፖሊሶች እንዳይገልፅ ለሁሉም ንገር! ስሜታዊ ሆነው ስለመጡ ሊጎዱት ይችላሉ! እኔ ራሴ ጉዳዩን እይዘዋለሁ”

ክፍሎም በጣም ተደሰተ።

ወጣቱ አራሚ ገፅታ ላይ የነበረው ስጋትና ጭንቀት ተገፎ ፊቱ ሲፈካ አስተዋልኩ። ወጣቱ አራሚ ቀይ ረጅም ነው። በማነጋግረው ጊዜ ግን ጠቁሮና አጥሮ ነበር። ችግር እንደማይደርስበት ስነግረው ፊቱ ሲቀላና ቁመቱ ሲረዝም አየሁት።

ወደ ቢሮዬ ተመልሼ የማያወላዳ ምላሽ ሰጠሁዋቸው፣

“በስህተት የተፈፀመ እንጂ ሆን ተብሎ የተደረገ አለመሆኑን ስላጣራሁ፤ ተመልሳችሁ ለክንፈ ይህንኑ ንገሩት!”

የፖሊስ ባልደረባው እንደመደንፋት አለ፣

“የተፈፀመው ወንጀል እንዲጣራ አቶ ክንፈ አዘውናል! ጋዜጠኛውን ሳንይዝ በፍፁም ከዚህ ቢሮ አንወጣም!”

የደህንነት ባልደረባውም አከለ፣

“ጋዜጠኛው ምንም ጉዳት አይደርስበትም! አጣርተን እንለቀዋለን!”

ፖሊሱን ችላ ብዬ ከደህንነቱ ጋር ንግግር ቀጠልኩ፣

“ሆን ተብሎ የተፈፀመ ነው ብዬ ባምን ኖሮ የጋዜጠኛውን ስም እሰጣችሁ ነበር። አዝናለሁ። እኔ እዚህ ሃላፊ ነኝ! ከዚህ በላይ የምንነጋገረው ነገር የለም!”

ከጥቂት ፀጥታና ውጥረት በሁዋላ ታጋዩ ለክንፈ ስልክ መደወል እንደሚፈልግ ገለፀና ስልኩን ሰጠሁት። ደውሎ በትግርኛ ያነጋግረው ጀመር። እኔ ትግርኛ እንደማልችል መገመቱን ተረዳሁ። ምክንያቱም እንዳልተግባባን ሳይሆን ችግር እንደፈጠርኩ ነበር የሚገልፅለት። ላስደነግጠው ስላልፈለግሁ ትኩረት አላደረግሁበትም። ለክንፈ ገልያለት ሲያበቃ ስልኩን ወደኔ አሸጋገረው።

“ምንድነው ችግሩ?” ሲል ጠየቀኝ ክንፈ።

ሆን ተብሎ የተፈፀመ አለመሆኑን ላስረዳው ሞከርኩ።

“ሆን ተብሎ ነው ወይስ በስህተት የሚለውን እኛ መርምረን ማወቅ ፈልገናል” አለኝ በተለመደው ቁጡ የሚመስል አነጋገሩ።

“ገብቶኛል ክንፈ! ጋዜጠኛውን አሳልፌ የምሰጣችሁ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከሆነ ግን እኔ እዚህ ቦታ መስራት አልችልም። የመስሪያ ቤቱ ጋዜጠኞች ሁሉ ቀጥሎ የሚሆነውን እየጠበቁ ነው። ልጁ በፖሊስ ከዚህ ተይዞ የሚሄድ ከሆነ የፖለቲካ ኪሳራ ጭምር ነው"

"አናስረውም! ተጠይቆ ይመለሳል!"

"እሱም ነው ችግሩ ክንፈ! ባለሙያ ሆነህ ስታየው ስህተቱ በጣም ተራ ስህተት ነው። ጋዜጠኛው በፖሊስ ከተወሰደ መናቅን ብቻ ነው የምናተርፈው"

"ሆን ተብሎ የተፈፀመ ሊሆን ይችላል" አለ ክንፈ።

"በፍፁም አይደለም። እንግሊዝኛ አንባቢዎች መለስ በአውቶብስ አምቦ ሊሄድ እንደማይችል ስለሚያውቁ በቀላሉ አንድ ስህተት እንዳለ ይገነዘባሉ!"

ክንፈ ሊጫነኝ ጀመረ፣

"እኛ የራሳችን አሰራር አለን። ለድርጊቱ ተጠያቂ የሆነውን ሰው ማነጋገር እንፈልጋለን!" አለኝ።

አነጋገሩ ጥብቅና ትእዛዝ አዘል ስለሆነብኝ እኔም አንድ እርምጃ ወደፊት በመሄድ የሚከተለውን ምላሽ ሰጠሁት፣

"እንግዲያው ክንፈ...ለዚህ ስህተት ራሴን ተጠያቂ ማድረግ እችላለሁ፤ ከፖሊሶቹ ጋር ልመጣ ዝግጁ ነኝ! ማድረግ የምችለው ይህን ብቻ ነው!"

ለጥቂት ሰከንዶች ዝምታ ከሆነ በሁዋላ፣

"ከአለምሰገድ ጋር እነጋገርበታለሁ!" ሲል ተነፈሰ። አያያዘናም የቡድኑን መሪ እንዳቀርብለት ጠየቀኝ። ስልኩን አስተላለፍኩ።

...የቡድኑ መሪ ይዞአቸው የመጣውን ፖሊሶች አስከትሎ ከቢሮዬ ወጣ። በአንድ ቀጭን ታጋይ እየተመሩ የመጡት ፖሊሶች እንደአመጣጣቸው የፕሬስ መምሪያን ለቀው ሲወጡ እስከ መውጫው በር ሸኘሁዋቸው።

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ የሃገሪቱ የፕሮፖጋንዳ መሃንዲስ አለምሰገድ ገብረአምላክ ደወለና ስለተፈጠረው ችግር ጠየቀኝ። አስረዳሁት። በዝርዝር አስረዳሁት። አዳምጦ ሲያበቃ፣

"እርማት የተካሄደባቸውን ወረቀቶች በሙሉ ይዘህ ና!" ሲል አዘዘኝ።

በሩብ ሰአት ውስጥ ከአለምሰገድ ቢሮ ተገኝቼ ስህተቱ እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ አስረዳሁት። አንዳችም ቃል

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሳይተነፍስ ማስረጃዎቹን ከተመለከተ በሁዋላ፤ ጋዜጠኛውን አሳልፌ መስጠት ያልፈለግሁበትን ዋና ምክንያትም አዳምጦ ሲያበቃ፤ የወሰድኩት ርምጃ ትክክል መሆኑን ግልፆ አሰናበተኝ።

በነጋታው ማለዳ ላይ ስሜነህ መኮንን ስልክ ደወለልኝ። ከአጭር ሰላምታ በሁዋላም፣

"ትናንት የተፈጠረውን ሰማሁ" አለ።

"ትናንት አስቸጋሪ ቀን ነበር"

"እናመሰግናለን!"

ስልኩን ከዘጋሁ በሁዋላ ከመቀመጫዬ ተነስቼ ወደ መስኮቱ ተጠጋሁ። አዲስ አበባ ቁልቁል ወለል ብላ ትታያለች። ጊዜው የግርግር ጊዜ ነው። ኢህአዴግ አዲሳባን ከያዘ ሁለት አመት እንኳን ገና አልሞላውም። ሰዎች ያለፍርድ ታስረው የሚረሱበት ጊዜ ነበር...

ፕሬስ መምሪያ በመቶዎች የሚቆጠሩ በእድሜ የገፉ ምሁራንን ያቀፈ ጥንታዊ መስሪያ ቤት ነው። በዚያ መስሪያ ቤት በእድሜ ትንሹ እኔ ነኝ። የመስሪያ ቤቱ አለቃም ደሞ እኔ ነኝ። እኒያ በእድሜ የገፉ ነባር ሰራተኞች ለህልውናቸው ሲሉ እኔን ወደ ማስተማሩ እየገቡ እንደሆነ ተረዳሁ። ጥሩ ተማሪ መሆኔ ገብቶኛል። ትምህርቱ ግን አይመችም። ከእድገት ህግ ውጭ ነው። ከታች ወደላይ እየተማርኩ ባድግ በተሻለኝ ነበር...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 7 -
የማልረሳት ጋዜጠኛ

ዘልዛላው ህይወቴ....
ጉድ እንዳይዘንብበት - የፈራ ይመስል፣
መብረቅ እንዳይመታኝ - የሰጋሁኝ ያህል፣
ወደሁዋላ ዞሬ - ሰማዩን አየሁት፣
እንደ ክፉ ጠላት - ውበትዋን ሸሸሁት፤

(ግጥም - ሺፈራው ከበደ)

ስለማልረሳት አንዲት ወጣት ጋዜጠኛ ላውጋችሁ።

አንድ ማለዳ ታጋይ ተክሉ ተክላይ እሳት ለብሶ የቢሮዬን በር በርግዶ ገባ። ታጋይ እንደመሆኑ ተክሉ የቢሮክራሲውን ህግ ለማክበር ብዙም አይጨነቅም።

"ችግር አለ እንዴ?" ስል ጠየቅሁት።

እንደ ወቅቱ አስተሳሰብና አነጋገር ፕሬስ መምሪያ ውስጥ ጥቂት የማይባሉ "ጠላቶቻችን" ስለተሰገሰጉ ምናልባት አሻጥር ተሰርቶ ይሆናል ብዬ ነበር ያሰብኩት። ችግሩ ግን እንዲያ አልነበረም። "ጠላቶቻችን" የፈፀሙት አንዳችም አሻጥር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አልነበረም።

"አንድ ያሳሰበኝን ጉዳይ ልጠቁምህ ነው የመጣሁት" አለኝ ፊቱን በመዳፉ እየሻሸ። በጥያቄ መልክ አየሁት፤ ፈጥኖ ቀጠለ ተክሉ ተክላይ፣

"ይህ መስሪያ ቤት ቡና ቤት እየሆነ ነው!" አለ ደሙ እንደተጣደ ማንቆርቆሪያ እየፈላ።

እናም ቀጠለ፣

"አንዲት ጋዜጠኛ ነኝ የምትል ሴት ይህን ድርጅት ወደ ቡና ቤት እየለወጠችው ነው..."

"ምን ገጠመህ ተክሉ? እስኪ ረጋ በልና አጫውተኝ!?" አልኩ።

እኔም እንደ ታጋይ ተክሉ መቆጣት እያማረኝ ነበር። በርግጥም መቆጣት ተገቢ ነበር። በታምራት ላይኔ ፊርማ ተሸሜ ቁጭ ያልኩበት መስሪያ ቤት ወደ ቡና ቤትነት ሲለወጥ እኔ እዚህ እንደ ጉቶ ተጎልቼ ልመለከት አልችልም።

ማብራራቱን ቀጠለ፣

"አንዲት ውጪ ተምራለች የምትባል....ጋዜጠኛ ነኝ የምትል ሴት... መስሪያ ቤቱን እየበጠበጠች ነው... አጭር ቀሚስ ለብሳ ከቢሮ ቢሮ ስትዞር ትውላለች..."

በፀጥታ ከማዳመጥ አልፌ አስተያየት መስጠት አልቻልኩም፣

"ምን መሰለህ..." ሲል ቀጠለ "...ልጅቱ ይሄን ጥፋት ፈፅማለች ልልህ አልችልም። ሆኖም አንዳንድ ሰራተኞችን አነጋግሬ ነበር። የኔን አስተያየት ደግፈውታል! 'ድርጊትዋ ተገቢ አይደለም' ብለውኛል። ከቀድሞው የመምሪያ ሃላፊ ጋር የአንድ አገር ልጅ ስለሆነች ነው የተቀጠረችውም የሚሉ አሉ።"

የማስታወሻ ደብተሬ ላይ "አጭር ቀሚስ" የሚል አሰፈርኩና ባልደረባዬን ቀና ብዬ አየሁት። እንግዲህ ማድረግ የነበረብኝ "አጭር ቀሚስ መልበስ"ን የተመለከተ የሰፈረ የመስሪያ ቤቱ ደንብና ህግ ካለ የአስተዳደር ሃላፊውን መጠየቅ ነበር። ተክሉ ግን አያያዘና ቀጠለ፣

"...በተጨማሪ ደግሞ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ትስቃለች... እንዳልኩህ ነው እንግዲህ... ይሄ ቡና ቤት አይደለም... አጭር ቀሚስ ተለብሶ... ድምፅን ከፍ አድርጎ መሳቅ ምን ማለት ነው? በዚህ ድርጊት ያልተደሰቱ ጥቂት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አይደሉም…"

ተክሉ አብራርቶ ሲጨርስ በጉዳዩ ላይ ጥቂት አሰላሰልኩና እንዲህ አልኩት፣

"እንግዲህ ከገለፅክልኝ ውስጥ ሁለት ነጥቦችን ይገፍያለሁ፤ እነርሱም 'አጭር ቀሚስ መልበስ' እና 'ድምፅን ከፍ አድርጎ መሳቅ' ናቸው። እስኪ ምን እንደምናደርግ እንመካከራለን። ግን ማነው ስምዋ!?" ስል ጠየቅሁት።

"ማን ነበር?" እንደማሰብ ካለ በሁዋላ "ፍፁም ሲሉ ሰምቻለሁ መሰለኝ"

በዚህ ቅፅበት Fitsum A. Kassa የሚለው ስም አእምሮዬ ላይ ደወለ። በርግጥ ገና ደርግ መውደቁ ስለነበርና ሹመታችንም አዲስ በመሆኑ የሰራተኞችን መልክና ስም ገና አላጠናነውም። የዚህችን ልጅ ስም ግን Ethiopian Herald ጋዜጣ ላይ ማየቴን አስታወስኩ። ተክሉ ለመሄድ ከመቀመጫው ሲነሳ በመገረም መልክ ስላለባበስዋ ማብራራቱን እንደቀጠለ ነበር፣

"…በጣም አጭር ቀሚስ… በዚህ ላይ ደግሞ ትስቃለች…"

ፋታ ወስዶ ደሞ ቀጠለ፣

"ራቁትዋን ናት ማለት ይቻላል፤ መሃረብ በለው! ሰውነትዋ ግማሽ በግማሽ ይታያል…እንዲያውም ሙሉ በሙሉ ይታያል…በደንብ ይታያል"

"እስቲ ጉዳዩን ቀስ ብዬ አጣራዋለሁ!" አልኩ።

ተክሉ ከቢሮዬ በመውጣት ላይ ሳለም ማብራራቱን አላቆመም፣

"እና እንዳልኩህ ያንን መሃረብ ለብሳ…ዛሬ ከነጋ እንኳ በኔ ቢሮ በር ሁለት ጊዜ አልፋለች… እየሳቀች!… ስራ መስራት አይቻልም… አንዳንድ ሰራተኞች አልተደሰቱባትም!"

"ቆንጆ ናት?" ስል እንደዋዛ ጠየቅሁት፤ እየሸኘሁት።

ተክሉ በጥያቄዬ አልተደሰተም። በግድ የለሽነት እጁን አወናጨፈ!

"እኔ መልኳን ልብ ብዬ አላየሁትም። ቆንጆ ትሁን አትሁን እሱ አይደለም ጉዳዩ። ይህ ትልቅ መስሪያ ቤት ነው። ስርአት መከበር አለበት። ቡና ቤት አይደለም። እና…ምን ለማለት ፈልጌ ነው?… ልጠቁምህ የመጣሁት ሃላፊነት ስላለብንና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አንተም ደግሞ የመስሪያ ቤቱ ሃላፊ ስለሆንክ ነው።"

ከተክሉ ጋር በዚሁ ተለያየን።

በሶስተኛው ቀን ይመስለኛል ከEthiopian Herald ዋና አዘጋጅ ከክፍሎም አድጎይ ጋር ቁጭ ብለን ስናወጋ ተክሉ ስለጠቆመኝ ሴት ጋዜጠኛ አነሳሁለት፣

"ፍፁም የተባለችው ጋዜጠኛ እንዴት ናት?"

"ፍፁም ...ምስራቅ አውሮፓ ተምራ የመጣች ናት" ክፍሎም በተለመደው ግዴለሽ አነጋገሩ ቀጠለ "...አዲስ ጋዜጠኛ ናት! አያያዟ ግን በጣም ጥሩ ነው! ችግር አለ እንዴ!?"

"ችግር እንኳ የለም!" ካልኩ በሁዋላ "ባህሪዋስ?" ስል ጥያቄዬን አራዘምኩ፣

"ተግባቢ ናት! መጥፎ ነገር አይተንባት አናውቅም!!"

ለክፍሎም አድጎይ ከዚህ ያለፈ ጥያቄ አላቀረብኩለትም። የሆነው ሆኖ በዚያችው ደቂቃ የተክሉን ማመልከቻ ሰርገፎው ነበር።

በዚያው ሰሞን ተክሉ ለሌላ ስራ ጉዳይ ቢሮዬ መጥቶ ሳለ መልሶ ጉዳዩን አነሳልኝ፣

"የልጅቱን ጉዳይ ምን አደረግህ?"

"ክፍሎምን አነጋግሬው ነበር። በባህሪዋም በስራዋም ቅሬታ የለውም"

ተክሉ ባለመስማማት ግንባሩን ሸበሸበ፣

"እንግዲህ እኔ ስለስራዋ የማውቀው ነገር የለም። ስለባህሪዋም በርግጥ አውቃለሁ ማለት አልችልም። በአይኔ ያየሁት፣ በጆሮዬ የሰማሁትን ነው የነገርኩህ። ዋና ችግርዋ አጭር ቀሚስና ሳቋ ነው፤ ሁለቱን ካስተካከለች..."

አቋረጥኩት፣

"አጭር ቀሚስ እንዳታደርግና እንዳትስቅ ልናግዳት አንችልም"

ተክሉ እንደገና ይፈላ ጀመር፣

"እና መስሪያ ቤቱ ቡና ቤት ሆኖ ይቀጥል!?"

በዝምታ አስተዋልኩት።

ገፅታው ላይ የመረረ ቁጣና መጎዳት በትክክል ማየት ችዬ ነበር። 'ጉዳዩን በጥላቻ ያስተናገደው ለምን ይሆን?' ብዬ እያሰላሰልኩ ቆየሁና፣

"ከዚያ ወዲህ አይተሃት ታውቃለህ?" ስል ጠየቅሁት።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"በየቀኑ ነው የማያት...ዛሬም እንደ ነጠላ ስስ የሆነ ቀይ መሃረብ ለብሳ በቢሮዬ በር አልፋለች። የለበሰችው ቀሚስ ለሁለት አመት ህፃን እንኳ ያጥራታል! ትናንት ጥቁር መሃረብ ነበር ያደረገችው... ልብሶችዋ በሙሉ መሃረብ ናቸው...ሰውነቷ በደንብ ይታያል..."

"እንተ ቢሮ ገብታ ታውቃለች?"

"ገብታ አታውቅም! በኮሪደሩ ስታልፍ ነው የማያት!"

ተክሉ የአስተዳደር ሰራተኛ ቢሆንም፣ በክፍሎች እጥረት የሄራልድ ጋዜጠኞች ካሉበት አካባቢ ነበር ቢሮ የሰጠነው። ችግር ውስጥ መግባቱን ተረዳሁ። አሰብኩበትናም ጥያቄ አስከተልኩ፣

"የቢሮህን በር ክፍት ነው የምታደርገው!?"

"አልዘጋውም። ለምን እዘጋዋለሁ?"

"ማለቴ ምናልባት መለስ ብታደርገው ስለማታያት ሳትረበሽ ለመስራት..."

ተክሉ ፈጥኖ አቋረጠኝ፣

"አልተግባባንም ማለት ነው! እኔ እያልኩ ያለሁት በአጠቃላይ በዚህ መስሪያ ቤት ደንብና ስርአት መከበር አለበት ነው'ንጂ ስለኔ አይደለም። በአለባበሷ የማይደሰቱ ሰራተኞች ብዙ ናቸው፤ እኔ ብቻ አይደለሁም..."

"ማንን አነጋገርህ በዚህ ጉዳይ?"

"አቶ ደርቤን አነጋግሬያቸው ነበር። 'አለባበሷ ከባህላችን ውጭ ነው' ብለውኛል፤ አቶ ሃዲስ እንግዳንም አነጋግሬያቸው ነበር፤ በርግጥ እሳቸው 'አስብበታለሁ' ነው ያሉኝ፤ የበሪሳ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ግን 'አለባበሷ ትኩረት ይስባል' ብሎኛል...በጣም የተናደዱና መቀጣት እንዳለባት የነገሩኝም አሉ።"

"ክፍሎም ስለ ፍፁም ጥሩ አመለካከት አለው"

"እውነቱን አልነገረህ ይሆናል!"

"ክፍሎም የመሰለውን የሚናገር ለጣፊ ነው! እንዲያውም በግልባጩ 'ተግባቢ ናት' ነው ያለኝ። ሳቋ እሱን አልረበሸውም"

ከተክሉ ጋር በዚሁ አበቃን።

ባለመደሰት ከቢሮዬ ወጣ።

ከዚህ ቀን በሁዋላ ፍፁምን ጠርቼ ለማየት ፍላጎት አሳደርኩ። የልብስዋም ሆነ የሳቋ ጉዳይ የተዘጋ አጀንዳ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ቢሆንም፤ ተክሉን የረበሸውን አለባበስ ለማየትና ሳቋን ለመስማት ተመኘሁ። ይሁን እንጂ ዛሬ ነገ አስጠራታለሁ እያልኩ ሳስብ ፍፁም ራሷ ቢሮዬ ድረስ መጣች።

አንድ ቀን አርፍጄ ወደ ቢሮዬ ስገባ አጭር ቀሚስ ወይም እንደ ተክሉ አገላለፅ መሃረም የለበሰች፤ የሚስብ ሙሉ ሰውነት ያላት፤ ገፅታዋ ላይ የደስታ ርችት የፈሰሰባት ወጣት ቆንጆ ሴት ከፀሃፊዬ ጋር ስትጫወት ደረስኩ፣

Fitsum A. Kassa እሷ ለመሆንዋ ነጋሪ እንኳ አላስፈለገኝም። በአብዛኛው ልምዴ ለሂሩት አጭር ሰላምታ አቅርቤ ወደቢሮዬ መዝለቅ ነበር። ያን ቀን ግን ሳላደርገው ቀረሁ። ከእንግዳ ማረፊያው ሶፋ ላይ ከፍፁም አጠገብ ቁጭ አልኩ። እናም ተዋወቅኋት። የጠበቅኩትን ስም ነገረችኝ። እንደተለመደው ለአለቃ የመደንገጥ ሁኔታ አልነበረባትም። ለፀሃፊዬ ቡና እንድታዝልኝ ነግሬ፣

"ስራ እንዴት ነው ፍፁም?" ስል ወሬ ጀመርኩ።

"ይሰለቻል" አለች "...ቢሮ ተቀምጠን ነው የምንውለው። የመስክ ስራ እንዲኖር ነበር የምመኘው። ጋዜጠኛ ሆነህ ቢሮ መዋል በጣም የሚሰለችና ያልጠበቅሁት ነው"

"አለባበስሽ ግን ከቢሮ መውጣት የምትመኚ አያስመስልም"

ፍፁም በረጅሙ ሳቀች!!

ሳቋ የሚጥም ዜማ ነበረው። እንደ ልብ የሚወጣ ሳቅ! ተክሉን ያናደደው ሳቅ ይህ ነው ብዬ ማመን ግን ቸገረኝ። በርግጥ ሳቋ አናዶት ይሆን?

...ይህ በሆነ በሶስተኛው ወር ግድም ምስራቅ ኢትዮጵያ በጦርነት ይታመስ ያዘ። አነግና ኢህአዴግ በጠመንጃ ይሞካከሩ ገቡ። የበደኖና የወተር ጭፍጨፋዎች የፕሮፓጋንዳው መሪ አጀንዳዎች ሆኑ። ኢህአዴግ አነግን በበደኖ ጭፍጨፋ ሲከሰው፤ አነግ በበኩሉ የወተሩን ጭፍጨፋ አንስቶ ኢህአዴግን ይወነጅላል። በዚህ መሃል 'አነግን ከህዝብ መነጠል' የሚል የፕሮፓጋንዳ አቅጣጫ በመነደፉ የጋዜጠኛ ቡድን ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ እንድንልክ ታዘዝን። ከኔ መስሪያ ቤትም ከየቋንቋው ጋዜጠኞችና ከፎቶግራፍ ክፍል የተውጣጣ ቡድን አዋቀርኩ። በማዋቀሩ ሂደት ታዲያ ክፍሎም አድጎይ ዘንድ ደወልኩና፣

"ማንን ነው የምትመድበው?" ስል ጠየቅሁት።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“የጋዜጠኛ እጥረት አለብኝ”

“የግድ መመደብ አለብህ”

“እንግዲያው አስቤ ልንገርህ”

“ለምን ፍፁምን አትመድባትም?”

ክፍሎም እያመነታ ሲጋቱን ገለፀ፣

“ቦታው የጦርነት ቦታ ስለሆነ ምናልባት የእግር መንገድም ስለሚኖረው... ነባር ጋዜጠኞች...”

ክፍሎምን አቋረጥኩት፣

“ፍፁምን ላክልኝ ግድየለም!”

በዚያን ቀን ተስያት ላይ ለዚህ ግዳጅ የሚሰማራውን ቡድን ሰብስቤ ስለ ጉዞአቸው ማብራሪያ ሰጠሁ፣

“የምትሄዱት ወደ ጦርነት ቀጠና ነው” ስል በቀጥታ ገለፅኩላቸው። “...ሆኖም በአካባቢው የመንግስት ጦር የበላይነት ስላለ ችግር የመድረሱን እድል ይቀንሰዋል”

መኪና የማይገባበትን ቦታ በእግር ጉዞ የመሸፈን ግዴታ ሊኖርባቸው እንደሚችልም አብራራሁ። የተቀበሩ ፈንጂዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ወዳልታወቁ መሬቶች ላይ መዘዋወር አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ለሾፌሩ አሳሰብኩ። ‘የካቲት” የተባለውን መፅሄት ወክሎ የሚጓዘው ደራሲና ጋዜጠኛ የሺጥላ ኮከብ ለጉዞው መጓጓቱን አስተዋልሁ። የሺጥላ እንደ ደራሲነቱ ጦርነትን አይቶ ስለማያውቅ፤ በዚህ አጋጣሚ ይህን እድል ስላገኘ ፍላጎት ቢያሳድር የሚደንቅ አልነበረም። ፍፁምም ከየሺጥላ ባላነሰ ሁኔታ መደሰቷን ስመለከት ግን ማመን ተቸግሬ ነበር። መግለጫዬን ሰጥቼ እንዳበቃሁ ፍፁም በአካባቢው የሚገኝ የሰራዊት መሪዎችን ስም ጠየቀችኝና የሳሞራ የኑስን ስምና ስልክ ሰጠኋት። ጉዞአቸው በነጋታው ማለዳ ነበርና መልካም ጉዞና እድል ተመኝቼ አሰናበትኳቸው።

በነጋታው ስለጋዜጠኞቹ ጉዞ የገለፀልኝ የአስተዳደር ሃላፊው ሰለሞን ነበር፣

“የፍፁም አለባበስ እንዴት ነበር?” ስል ጠየቅሁት።

ሰሚያዊ ጂንስ ሱሪ፣ ጥቁር ሹራብ እና ቡትስ ቆዳ ጫማ መልበስዋን ገለፀልኝ። ቢሮዬ ገብቼ የተለመደውን ወፍራም ቡና ካዘዝኩ በሁዋላ ለተክሉ ደወልኩለት፣

“ዛሬ ጠዋት አንድ ቡድን ወደ ምስራቅ መላካችንን አውቀሃል?”

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“አውቄያለሁ”
“ልጅቱ ከቡድኑ ጋር መሄዷንስ ሰምተሃል?”
“የታ ልጅ?”
“ፍፁም”
የተክሉ ድምፅ ጠፋ።
ዘግየት ብሎ ግን ምላሽ ሰጠኝ፣
“እሺ ብላ ሄደች?”
“በግልባጩ ደስተኛ ነበረች። ጂንስ ሱሪ ለብሳ ነበር”
እንደገና ዘግየት ብሎ፣
“አደገኛ ቦታ ነውኮ!...ሌላ ጋዜጠኛ ለምን አልላካችሁም?” ሲለኝ በርግጥም ከተክሉ ጋር እያወራሁ መሆኑን ተጠራጠርኩ። ከድምፁ እንደሰጋላት ተረድቼያለሁ።
“ፍፁም ቅሬታ የላትም” አልኩት።

ንግግራችን በዚሁ አበቃ።
በዚያን ሰሞን ተክሉ ወደ ቢሮዬ ለስራ ብቅ ሲል ስለ ልጅቱ ያነሳ እንደሁ ጠብቄ ነበር። አላነሳም። የመጣበትን ጉዳይ ብቻ ፈፅሞ ተመለሰ...
...ፍፁም ወደ ጦርነቱ ቦታ ከተላኩት የጋዜጠኞች ቡድን ጋር ተጉዛ ስትመለስ የተመሰገነ ሚዛናዊ ሪፖርታዥ የፃፈች ሲሆን፤ በስራዋ ትኩረት እየሳበች በመሄድዋ በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቭዥን ተዘዋውራ በሃላፊነት ደረጃ ጭምር ሰራች። የእንግሊዝኛ ሬድዮ ፕሮግራም አድማጮች የፍፁምን ድምፅና ሳቅ እንደሚወዱት ከግብፅ የፕሬስ አታሼ አንደበት ጭምር የሰማሁት ፍፁምም ራሷ በነበረችበት አንድ የግብፅ ኤምባሲ የራት ግብዣ ላይ ነበር። በዚያን ወቅት እኔ የእፎይታ መፅሄት ዋና አዘጋጅ ነበርኩ።
በመጨረሻ ፍፁም አንድ አሜሪካዊ አግብታ ኢትዮጵያን ለቅቃ ሄደች። የሰርግ የጥሪ ካርድ ልትሰጠኝ የደወለችልኝ እለት በቀጠሮ ቻይና ሬስቶራንት ተገናኝተን ለሰአታት ያህል ቁጭ ብለን ብዙ አወራን።
በወሬ ወሬ ታዲያ የአጭር ቀሚሱንና የረጅም ሳቅ ታሪክ፤ እንዲሁም እንዴት ወደ ጦርነት ቦታ ትሄድ ዘንድ እንደተመረጠች ሳወጋት እንደ ርችት የሚፈነዳ ሳቋን ያለገደብ ለቀቀችው። በሬስቶራንቱ ይመገቡ የነበሩት ሁሉ ወደኛ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እስኪመለከቱ ድረስ ትስቅ ነበር።

"ይህን ታሪክ ቀደም ብለህ ልትነግረኝ ይገባ ነበር። ተክሉን ባገኘውና ባነጋግረው ደስ ባለኝ" አለቺኝ። አያያዘችናም "ከመሄዴ በፊትም ቢሆን ላገኘው እፈልጋለሁ..." ስትል አከለችበት።

ፍፁም አግብታ ወደ አሜሪካ ከተጓዘች ከአመት በሁዋላ እኔም ኮበለልሁ። ያቺ ድንቅ ጋዜጠኛ ዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ እንደምትኖር በቅርቡ የሰማሁ ቢሆንም፤ አድራሻዋን ለማግኘት ጥረት አላደረግሁም።

አጭር ቀሚስ የለበሰች ሴት ባየሁ ቁጥር፤ ረጅምና ውብ ሳቅ በሰማሁ ቁጥር ግን Fitsum A. Kassa የሚል ስም ወደ አእምሮዬ ይመጣል...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 8 -
የልጅነት መምህራን

ቢሾፍቱ መሰክ አምና፣
በስታሊን ኦርጋን አፍ - ቦራ ሲኦል ታጥና፥
ያልተብከነከነ - ባከኖ ያልተፅናና፣
ልቤ አልከዳኝም ባይ - ልቦናው የጠና፣
አንደበተ ጅግና፣
አልተናወጥኩም ባይ - ማነው ባለዝና?
"አፍ እምተረፈ ልብ፣ ይነበብ" ነውና፣

(ግጥም - ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን)

ገምታ ጎርፉ ስለተባለች የ11ኛ ክፍል የጂኦግራፊ መምህሬ ላውጋችሁ። የፕሬስ መምሪያ ሃላፊ በነበርኩበት በ1984 ሚያዝያ ወር ... አንድ ማለዳ...

"እንግዳ ይፈልግሃል" አለቺኝ ፀሃፊዬ ሂሩት።

"ማነው?"

"ወይዘሪት ዝምታ ጎርፉ ይባላሉ"

ከዚያች እብድ መምህር ሌላ በዚህ ስም ሊጠራ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የሚችል ሊኖር እንደማይችል እየገመትኩ "አስገቢልኝ" አልኳት።

በሩ ተከፈተና እንግዳዋ ገባች። እራስዋ ነበረች! የማልረሳት መምህር! መቼም ልታውቀኝ አትችልም። እስኪ ታውቀኝ እንደሁ አያታለሁ? ከመቀመጫዬ ተነስቼ ጨበጥኳት። ስሜን ነገርኳት። ስምዋን ነገረቺኝ። እንድትቀመጥ ጋበዝኳትና ተቀመጠች። አተኩራ እያየቺኝ ነበር። ካላስታወሰቺኝ እኔ ስለራሴ እንደማልነግራት ርግጠኛ ነበርኩ። ዝምታ ሃይለኛና ጎበዝ መምህር ነበረች። አተኩራ በጥርጣሬ ስታየኝ ቆየችና፣

"የት ነው የማውቅህ" ስትል ጠየቀቺኝ።

"ታውቂኛለሽ?"

"ተሳስቼ ይሆናል" አለች መልሳ፣ "...ከወያኔዎቹ አንዱ ነህ አይደለም? ላውቅህ አልችልም"

እንደገና እያመነታች "ፊትህ ግን የሆነ ቦታ ትዝ ይለኛል። መምህር ስለሆንኩ ተማሪዎቼ ትዝ እያሉኝ ይሆናል"

ይህን ስትለኝ ማንነቴን ደብቄ ለመቆየት አልቻልኩም። ተናዘዝኩ!

"ዝምታ! ልክ ነሽ፤ ታውቂኛለሽ! ያንቺ ተማሪ ነበርኩ! ቢሾፍቱ! ደብረዘይት! 11ኛ ክፍል ሳለን ድርሰት እየፃፍኩ ታነቢልኝ ዘንድ አስቸግርሽ ነበር"

ፊትዋ ሲፈካ አስተዋልሁ።

"አስታወስኩህ!" ብላ ጮኸች "...ተማሪዎች አዋሽ ፓርክን ልትጎበኙ ስትሄዱ መኪና ተገልብጣችሁ አንተ ግንባርህን በፋሻ ጠቅልለህ ትመጣ ነበር። አስታውስሃለሁ፤ ይኸው ምልክቱ ግንባርህ ላይ አለ"

ከመቀመጫዋ ተነሳችና እንደገና ተቃቅፈን ተሳሳምን። ዝምታ የተለየች ሰው ናት! ባል የላትም። የማግባት ፍላጎት እንደሌላትም ይነገራል። በደብረዘይት ተራራማዎቹ ቀበሌዎች ጫካ ውስጥ ብቻዋን ትኖር ነበር። ቤቷ ውስጥ ሰይጣን አለ የሚል የልጅነት ወሬም እንሰማ ነበር። ክፍል ውስጥ ስታስተምረን ምንጊዜም በፕላስቲክ ጠርሙስ ወተት ይዛ ትመጣና እያስተማረችን የመጎንጨት ልማድ ነበራት። ደብተራችን ላይ ከግራ ጀምረን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንድንፅፍም ታስገድደን ነበር። የማይወዳት ተማሪ አልነበረም! ትልቁ ስድብዋና ዱላዋ "አንተ ሰነፍ!" የሚል ብቻ ነበር። ጎበዝ ነበረች። ማናቸውንም ጉዳይ በቀጥታ የምትናገር ግልፅ ሰው ነበረች። እነሆ ይህቺ ተወዳጅ መምህር ከቢሮዬ ቁጭ ብላለች፣

ዝምታ ወዲያውኑ የጥያቄ ዶፍ ታዘንምብኝ ጀመረች፣

"በ1976 የ11ኛ ክፍል ሰነፍ ተማሪ ነበርክ። እንዴት ነው አሁን እዚህ ቦታ የተቀመጥከው? በምን ተአምር ነው ይህን ስልጣን ያገኘኸው?"

ባጭሩ አስረዳሁዋት።

በጥንቃቄ ካዳመጠቺኝ በሁዋላ፣

"ሊገባኝ አይችልም" አለች "...እዚህ መስሪያ ቤት ሪፖርተር ሆነህ ባገኝህ ባልገረመኝ..."

መሳቅ ጀመርኩ።

ከዚያ በላይ ዝምታን ላስረዳት አልችልም።

"እድሜህ ስንት ሆነ!?" ስትል አፈጠጠችብኝ። መሳቄን በመቀጠሌ ራስዋ ጣትዋን እየቆጠረች አሰላችውና፣

"23 ወይም 24 አመትህ ነው" አለቺኝ።

"ልክ ነሽ ዝምታ!"

"መለስ ዜናዊ ነው የሾመህ?" ስትል ስሜታዊ ሆና ጠየቀቺኝ። መልስ አልሰጠሁዋትም፣

"ምንም ልምድ የሌለውን የ23 አመት ልጅ ይህን የሚያክል መስሪያ ቤት..."

ዝምታ ድንገት መናደድ ጀመረች፣

"...ሊገባኝ አይችልም፤ አንተን እኔ ስላወቅሁህ ነውንጂ በዚህ አይነት አብዛኞቹ ባለስልጣናት እንዳንተ አይነት ሊሆኑ ይችላሉ"

መሳቅ አቆምኩ። ዝምታን አውቃታለሁ። ለጣፊ ናት። ረጋ ብዬ ላስረዳት ሞከርኩ። በማንኛውም መለኪያ የያዝኩት ስልጣን እንደማይገባኝ እንደማውቅ፤ ደስ ብሎኝ እየሰራሁ እንዳልሆነ፣ ሆኖም የታማኝ ሰው እጥረት ስላለ ጊዜያዊ ምደባ እንደሆነ ላሳምናት ጥረት አደረግሁ። በምሰራው ስራም ባለሙያዎችን እንደማማክር በመግለፅ ላረጋጋት ሞከርኩ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አስቂኙ አጋጣሚ ደግሞ ዝምታ ወደኔ ቢሮ የመጣችው በተመሳሳይ በሃገሪቱ ስለሚታየው የአስተዳደር መዘበራረቅ ፅፋ Ethiopian Herald ጋዜጣ ላይ እንዲታተምላት ነበር። እኔ ዘንድ ከመምጣቷ በፊት የፃፈችውን ፅሁፍ ለጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ለክፍሎም አድጎይ አቅርባ እንደ ነበርና ፅሁፉ ይታተም ዘንድ የኔ ፈቃድ በማስፈለጉ ነበር አመጣጧ። ክፍሎም ሊያትመው የሰጋበትን ፅሁፍ ዝምታ አቀበለቺኝና አነበብኩት።

ምንም አላስተረፈችንም። "እስከ ዶቃ ማሰሪያው ነገረው" የሚባለው አይነት ፅሁፍ ነበር። በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚታዩትን አስቂኝና አስገራሚ ክስተቶች ለቅማ ፅፋለች። በደብረዘይት አየር ሃይል በሁለት ሺህ ዶላር የተገዛ አንድ የጦር አይሮፕላን መለዋወጫ እቃ ታጋዮቹ እንደ ወንበር እየተቀመጡበት እንደሆነ ፅፋለች። በመዘጋጃ ቤት ደግሞ ታጋዮቹ ፋይሎችን እያወጡ ለእሳት ማቀጣጠያ ይጠቀሙባቸዋል። የታሪክ ሰነዶች በማይመለከታቸው ሰዎች እጅ እየገቡ ነው። አንብቤ ስጨርስ እንደማይታተም ነገርኳት።

"ለምን?"

"መታተሙ ችግሩን አይፈታውም ዝምታ፤ መለስና ታምራት እንዲያነቡት ግን አደርጋለሁ"

ደስ ባይላትም በዚሁ ተስማማን። ዝምታ ወደ ደብረዘይት ለመመለስ ተነሳች! ሰአቴን አየሁ። 10፡30 ይላል። እለቱ አርብ ነው።

"ደብረዘይት እንዳደርስሽና ራት እንድጋብዝሽ ፍቀጂልኝ ዝምታ። ካንቺ ጋር ጥቂት ማውራት እፈልጋለሁ። በመለማመድ ላይ የነበርኩትን የሃሰት የክብር ካባ ገፈሽ ስለጣልሽልኝ በዛሬው ቀን ያገኘሁትን ትምህርት መቼም አልረሳውም" አልኳት።

... ከዚያ በሁዋላ አፈንጋጯ ዝምታ ጎርፉን ዳግም ያየሁዋት ከአምስት አመታት በሁዋላ አዲስ አበባ ቀይ መብራት ላይ ነበር። መኪና ይዛ ነበር። የመኪናዋን መስታወት ከፍታ የሞቀ ሰላምታ ካቀረበችልኝ በሁዋላ፣

"እስካሁን አላበረሩህም?" ስትል ጮሃ ጠየቀቺኝ።

"አባረውኛል! እንኳን ደስ ያለሽ!"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተከታትለን በመሄድ ፍላሚንጎ ካፌ ገብተን ጥቂት አወጋን። ከዝምታ ጋር በጣም መግባባት እንደሚቻል ገብቶኝ ነበር። ግማሽ ሰአት ያህል ተጫውተን እስከ መኪናዋ ሸኘሁዋት።

ስንለያይ እንዲህ አለቺኝ፣

"አሜሪካን ሃገር የሚኖር ወንድም አለኝ። ይህቺን መኪና እሱ ነው የገዛልኝ። ጎበዝ ገጣሚ ነው። ግጥሞቹ እዚህ እንዲታተሙለት ይፈልጋል። እስኪ ሰሞኑን ቢሮህ እመጣና እንነጋገራለን"

ሆኖም ዝምታ እንዳለችው ቢሮዬ አልመጣችም።

...ከዚያ ወዲያ ስለ ዝምታ በድጋሚ የሰማሁት እንደገና ከሰባት አመታት በሁዋላ ፕሪቶሪያ እያለሁ ሲሆን፤ ፅጌረዳ የተባለች አብሮ አደጌ በፃፈችልኝ የኢ-ሜይል መልእክት ላይ "ተወዳጅዋ መምህራችን ዝምታ ጎርፉ አርፋልች!" የሚል አረፍተ ነገር አስፍራ ነበር። ክፉኛ አመመኝ። የዝምታን የእረፍት ዜና የሰማሁበትን እለትም ከአስቀያሚ ቀናቶች መሃል ደመርኩት። ሃዘን በቀላሉ አይጠጋኝም። ያን እለት ግን ተክዠ ዋልኩ። ራስህን ያለማታለልና ወደ ውስጥህ እንዴት መመልከት እንደሚገባ ያስተማረችኝ መምህር በርግጥም ለዘልአለሙ አርፋለች....

በዚያው ሰሞን "ethiopians.com" ገብቼ የፈላስፋው GE Gorfuን ቃለመጠይቅ ሳነብ ዝምታ እህቱ መሆንዋን አወቅሁ። የዝምታ አባት "ተግሳፅና ምክር" የተባለ መፅሃፍ የደረሱ፣ መፅሃፋቸውም በጃንሆይ ታግዶ እንደነበር ጭምር ተረዳሁ። ያ ብቻም አልነበረም። ፈላስፋው ገብረእየሱስ ጎርፉ የፃፈውን "Gorfu contra Nietzsche" የተባለውን መፅሃፍ አንብቤው ነበርና አፈንጋጭነትን ከአባታቸው ሳይወርሱ እንዳልቀረ ጠረጠርኩ።

* * *

መምህር ዝናቡ ዘነበ የስነፅሁፍ ፍቅር የነበራቸው ደግ መምህር ነበሩ። ሰማያዊ ኮታቸውን ለብሰው ሲንጎራደዱ አሁን ድረስ በአሳብ ይታዩኛል...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“መስፍን ሃብተማርያም ማን እንደሆነ የሚያውቅ አለ?” ሲሉ ጠየቁን አንድ ቀን።

እጄን አወጣሁ። እድሉን ሰጡኝ።

“መስፍን ሃብተማርያም ደራሲ ነው! የቡና ቤት ስእሎች በተባለ መፅሃፉና በእሁድ ማለዳ የሬድዮ ትረካው ይበልጥ ይታወቃል” ስል መለስኩ።

መምህር ዝናቡ “ልክ ነህ!” በሚል ራሳቸውን ላይታች እየነቀነቁ ተጨማሪ አከሉበት።

“መስፍን ደራሲ ነው። ከዚያም በላይ ግን የኔ የልጅነት ጓደኛ ነው። መስፍን የሞጆ ልጅ ቢሆንም፤ እዚሁ ደብረዘይት እኛ ዘንድ ነው የተማረው። ‘ልጅነት’ በሚለው የመስፍን ትረካ ውስጥ ተደባዳቢው ጉልቤ ልጅ እኔ ነበርኩ...”

ጋሽ ዝናቡ ግማሹን ክፍለ ጊዜ ስለራሳቸው ሲተርኩልን ያልቅ ነበር። ሌላ ቀን ደሞ ከኪሳቸው ሁለት እርሳስ አወጡና አሳዩን፣

“እነዚህ እርሳሶች እኔ ድርሰት የምፅፍባቸው ናቸው። አንዱ ከተሰበረ በሌላው እጠቀማለሁ። እኔ ድርሰት የምፅፈው ሌሊት ነው። ፀጥ ባለ ሌሊት፣ ኮሽታ በማይሰማበት፣ ካልጋዬ እወጣና ጠረጴዛዬ ላይ ቁጭ እላላሁ። ድርሰት ከመጣልኝ እፅፋለሁ፣ ካልመጣልኝ እንደ አመጣጤ ሹልክ ብዬ እተኛለሁ። ብዙ ጊዜ ግን አይመጣልኝም። ስነፅሁፍ እንደዚያ ነው። ሲመጣ አይታወቅ፣ ሲሄድ አይታወቅ”

መምህር ዝናቡ ስለ ስነፅሁፍ ሲናገሩ ስነፅሁፍ ፀጉራም፣ ሹል ጥርሶች ያለው፣ ጥቁር አውሬ መስሎ ይሰማኝ ነበር። አንድ ቀን እጄን አወጣሁና ጥያቄ ጠየቅሁዋቸው፣

“ኦሮማይ የተባለው የበአሉ ግርማ መፅሃፍ ለምን ተከለከለ?”

ጋሽ ዝናቡ በዝምታ ሲንጎራደዱ ከቆዩ በሁዋላ፣

“መንግስትን የሚያስቀይም ነገር ስላለበት ተከልክሎአል። በአሉ ግርማ የሃገራችን ድንቅ ደራሲ ነው። መስፍን ሃብተማርያም ስለ በአሉ ብዙ አጫውቶኛል። እንዳልኳችሁ መስፍን የልጅነት ጓደኛዬ ነው። ‘ልጅነት’ በተባለው ትረካ...”

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስለ መስፍን ሃብተማርያም ሳያነሱ የወጡበት ቀን በፍፁም ትዝ አይለኝም። ሌላ ቀን ደግሞ እንዲህ ሲሉ አማረሩ፣

"አማርኛ አስተማሪ መሆን ብቻ ለኔ በቂ አይደለም። እዚህ ትምህርት ቤት ክበቦች እየተቋቋሙ ነው። የስነፅሁፍ ክበብ ሃላፊ እኔ ካልሆንኩ ማን መሆን ይችላል? ምቀኝነት ግን ልማዳችን ነው። እኔን የችግኝ አስተካይ ክበብ ላይ መደቡኝ። የኔን ተሰጥኦ ላለመቀበል ነው። አጋጣሚ ለያየን እንጂ እኔና መስፍን ጓደኛሞች ነበርን፤ ደብረዘይት የጥበብ ከተማ ናት። ከመስፍን ሌላ ለማ ጉያና አሰፋ ጉያ፤ ታዋቂው ሃያሲ ፍቅሩ ደበበ የዚህች ከተማ ፍሬዎች ናቸው። እኔም አለሁ! 'ልጅነት' በተባለው ትረካ...እንደነገርኳችሁ..."

ሌላ ቀን ደግሞ የዘመድ በር አሰራር ስነፅሁፍን እንዴት እንደሚገድል አስተማሩን።

"በየከፍተኛው የአብዮት የዘፈን ግጥም ውድድር ተደርጎ ነበር" ሲሉ ነበር ምሬታቸውን የጀመሩት "... እኔም ጥቂት ስንኞችን ቋጥሬ አቅርቤ ነበር። አዲስ አበባ የከፍተኛ 15 የኪነት ቡድን ባልደረባ አሸነፈ ተባለና ገጣሚው ራሺያ ተላከ። የኔ ግጥም 2ኛ ነው የወጣው። በዘመድ በር ነው የሚሰራው። እልህ ይዞኝ ነበርና አሸነፈ የተባለውን ግጥም ባንድ ዘመዴ በኩል ኮፒውን አጊንቼ አነበብኩት፤ አዝማቹ ምን ይላል መሰላችሁ?..." ንግግራቸውን ገቱና ግጥሙን ሰሌዳው ላይ ፃፉት፤

እኛና ሶማሌ - ኮሶ ጠጥተን፣
ሶማሌን ገደላት - እኛን አሻረን፤

ጋሽ ዝናቡ እየተንጎራደዱ ቀጠሉ፣

"... ይሄ ነው ያሸነፈው። ይሄ ግጥም ነው? ሳይንስም ስነፅሁፍም ይህን ግጥም አይቀበሉትም። ከበደ ሚካኤልና ፀጋዬ ገብረመድህን በበቀሉበት ሃገር ይህን ግጥም ብሎ መሸለም ያሳፍራል። ስለ ጋሽ ፀጋዬ፣ ስለ ከበደ ሚካኤልና መንግስቱ ለማ ወደፊት ብዙ እንማራለን። በተለይ ስለ ጋሽ ፀጋዬ መስፍን ብዙ አጫውቶኛል። ... የዛሬው ትምህርታችን ግን የዘመድ በር ስነፅሁፍን ይገድላል!' የሚል ይሆናል...ፃፉት!"

ይህንኑ ሰሌዳው ላይ አስፍረው ትረካቸውን ቀጠሉ፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"...ካዛንቺስ መናኸሪያ አካባቢ ያለ የከፍተኛ 15 ልጅ በዘመድ በር አሸንፎ ራሺያ ሄደ። እኔ ቀረሁ። ራሺያ ቢቀር ምናለበት ኩባ እንኩዋ ቢልኩኝ? ዘመድ ስለሌለኝ ግን ይኸው እንደ ውሻ በተወለድኩበት ሃገር አረጀሁ። ዘመድ ያላቸው ራሽያ ሄደው ቴሌቭዥን፣ ፍሪጅና ሳሞቫር የተባለ ሻይ ማፍያ ይዘው መጡ። የሚስታቸውንና የራሳቸውን ፎቶግራፍም በእጅ ስራ በቀለም በትልቁ አሰርተው ሳሎናቸው ግድግዳ ላይ ሰቀሉ ... ሲሞቱ ይለቀስበታል!"

አንድ ጊዜ "ይድረስ ለአባቶቻችን!" በሚል ርእስ አጭር ግጥም ፅፌ ያነቡልኝ ዘንድ ሰጠሁዋቸው። ግጥሙ የሚከተለው ነበር፣

ሁለት መቃ-ብሮች - ዳዋ የለበሱ፣
ባረጀ ግራር ስር - ወድቀው የተረሱ፣
ዘር ትተን ዘር ጥለን - አልፈናል ይላሉ፣
ኮትኳች አራሚውን - ሳያስተካክሉ፣

ወደ መኖሪያ ቤታቸው ወስደው ገሰፁኝ።

"ምን ለማለት ነው የፈለግኸው? ምን አደረገህ አባቶች? የአቅማቸውን ሰርተው አልፈዋል!"

ቀዝቀዝ ብለው ጠጉሬን እያሻሹኝ ቀጠሉ፣

"አባቶችን በመውቀስ መጀመር ጥሩ አይደለም። ስለ ፍቅር ፃፍ! የተሰራውን በማድነቅ መጀመር አለብህ። የተጀመረው ላይ መቀጠል...ገብቶሃል የምልህ? በርግጥ ችግር አለ። ያልታደለ ትውልድ ናችሁ። ለማንኛውም ጥሩ ነው። ፃፍ..."

ሲሸኙኝ ሳለ ደጃፋቸው ላይ ከነበረች ሱቅ ፔፕሲኮላ ገዙልኝ። ጠጥቼ እንደጨረስኩ፣ "አይዞህ በርታ" ብለው በድጋሚ ራሴን አሻሽተው አሰናበቱኝ።

ጀምበር ጠልቃ ነበር። ለአይን ያዝ አድርጎአል። "የኛ ተማሪዎች" የምንላቸው የበልግ ወራት አእዋፍ ሰማዩን ሞልተው ደብረዘይትን ቀውጢ አድርገዋታል። ማደሪያቸው ጨለቅላቃ ከተባለው የክረምት ሃይቅ ላይ ነው። ለአይን ያዝ ባደረገው ምሽት እኔም ወደ ማደሪያዬ ገሰገስኩ....

...ጋሽ ዝናቡን ዳግም ያገኘሁዋቸው ደርግ ወድቆ "ኦሮማይ" የተባለው የበአሉ ግርማ መፅሃፍ እንዲታተም ከተደረገ በሁዋላ በምረቃ ስነስርአቱ ላይ ነበር። ለመፅሃፉ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ምረቃ የክብር እንግዳ ሆኖ የተጠራው በረከት ስምኦን ነበር። ስላልተመቸው መዝሙር ፈንቴ ተወከለ። መዝሙርም ያልጠበቀው ስብሰባ ስለገጠመው የክብር እንግድነቱ ስራ ለኔ ተሰጠ።

በምረቃ ስነ ስርአቱ ላይ ከኔ ቀኝ በኩል የበአሉ ግርማ ባለቤት ወይዘሮ አልማዝ አበራ ተቀምጣለች። በግራ በኩል ደግሞ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን አጅበውኛል። አልማዝ እየቆየች እንባዋን ታባብሳለች። ሳፅናናት ከቆየሁ በሁዋላ ወደ ባለቅኔው ዘወር አልኩ።

"ከርሶ ጎን በመቀመጤ እድለኛ ነኝ" ስል ተነፈስኩ። ከበረሃ የገባ ወያኔ መሆኔ ብቻ ስለሚታወቅ ባለቅኔው በአነጋገሬ ግራ ተጋብተው አተኮሩብኝ፣

"ስራዎቼን ታውቃቸዋለህ?" ሲሉ ጠየቁኝ።

"ሁሉንም!" ስል መለስኩ።

ባለቅኔው ነቃ አሉ። አያያዝኩና ቀጠልኩ፣

"ከእሳት ወይ አበባ፡ ግጥሞች ይበልጥ የምወዳት 'ጌራ' የተባለችውን ነው" ካልኩ በሁዋላ የተወሰኑ ስንኞችን በቃሌ ፈጨሁላቸው፣

ጌራ.....
ሽልም ሽፋልሽ ሲያጠላ...
እንደመንፀባረቅ ጥላ... እያልኩ።

ባለቅኔው ወዲያውኑ ወደዱኝ። ከበረሃ የገባ አንድ የወያኔ ባለስልጣን ከግጥሞቻቸው አንዱን በቃሉ ሲያነበንብላቸው የተሰማቸው ደስታ በቃላት የሚገለፅ አልነበረም። ከዚያ ወዲህም ቢሮዬ እየመጡና ዋቢ ሸበሌ ሆቴል የመጨረሻው ፎቅ ላይ ከሚገኘው ባር እየተገናኘን እሳቸው ሲያወጉ እኔ አዳምጥ ነበር። ከባለቅኔው ጋር ባመሸሁ ቁጥር አያሌ ልምድ ዝቄ እመለስ ነበር።

አንድ ቀን እንዲህ ሲሉ አወጉኝ፣

"የተገናኘንን ቀን 'ጌራ'ን እወዳለሁ ስትለኝ ገርሞኝ ነበር። ብዙዎች 'አይ መርካቶ' የተባለውን ነው የሚወዱት። አሁን ደግሞ 'ተይ መርካቶ' የሚል ዕፎያለሁ። እናንተ ከገባችሁ በሁዋላ ሌባ በዝቶአል። እንዲያውም 'ተይ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መርካቶን እሰጥህና መፅሄትህ ላይ ታትማታለህ"

ዘግየት አሉና አከሉበት፣

"ካንተ ሌላ 'ጌራን የምትወድ አንዲት ልጅ ነበረች። እንዳንተ በቃሏ ታውቀው ነበር። መአዛ ብሩ - የኡቴሎ ሚስ ት"

"ርስዎስ ከስነግጥሞችዎ የትኛውን ይወዳሉ?"

"ሁሉም ልጆቼ ናቸው"

"የበለጠ የሚመሰጡበት ማለቴ ነው"

"በልግ የተባለ መፅሃፌን አይተኸዋል?"

ደነገጥሁ።

ሁሉንም ስራዎችዎን አውቃቸዋለሁ ብዬ ስለነበር ነው መደንገጤ። ባለቅኔው "በልግ" የሚል መፅሃፍ ማሳተማቸውን አላውቅም ነበር። አለማንበቤን ተረድተው እሳቸው ቀጠሉ፣

"እዚያ ላይ ይበልጥ የምወዳቸው ስንኞች አሉ"

ከወራት በሁዋላ "በልግ" የተባለውን መፅሃፍ ካሮጌ መፃህፍት መሸጫ መደብር ፈልጌ በማግኘት ባለቅኔው የጠቆሙኝን ስንኞች አነበብኳቸው። ካነበብኳቸው በሁዋላ ግን ሎሬት ፀጋዬ እኒያን ስንኞች የጠቆሙኝ ከሌሎች ስነግጥሞቻቸው በላይ ስለወደዷቸው ሳይሆን፤ ለኔ አንድ መልእክት ለማስተላለፍ ፈልገው ሊሆን ይችላል ብዬ ጠረጠርኩ። በርግጥም እኒያ የባለቅኔው ጥቂት ስንኞች ውስጤን እንድመረምር አግዘውኛል። ላካፍላችሁ፤

ችሎታህን ውሰጥህ ቀብረህ - ህዋሰትክን አታንድደው፣
እምቡጥ እንኳ ሲፈነዳ - አብቧል ነው እሚባለው፣
እውነትን ውስጥህ ቀብረህ - እንደቀበርክም አታስቀር፣
እስዋን ከቀበርካት በታች - ዝቅ ብለህ አትቀበር፣
ብታፍርም ግድ የለም እፈር - በህዝብ ሳቅ ቀልጠህ አታርር፣
ሀሊናህን ካሳፈርካት ይበልጥ - በሰው ዘንድ አታፍር፣
የበታቾችህ ቢደፍሩህ - ትችለዋለህ ተቸገር፣
ይሉኝታህን ከደፈርካት ይልቅ - በነሱ አትደፈር፣
እንዲያውም በዚህ የተነሳ - ያልታለመ ቢፈጠርም፣
እምነትን ከገደልክ ይበልጥ - አንተ የሞት - ሞት አትሞትም፤

....በዚያን እለት "ኦሮማይ"ን መርቄ ከከፈትሁ በሁዋላ በግብጥው ስነስርአት ወቅት መምህር ዝናቡን እዚያ ሳገኛቸው ማመን አቅቶኝ ነበር። በቀጥታ እሳቸው ቆመው ወደ ነበሩበት በመሄድ በሞቀ ሁኔታ ስጨብጣቸው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከመደንገጣቸው የተነሳ ቃላት ሊተነፍሱ አልቻሉም። ጋሽ ዝናቡ መደንገጣቸው የሚጠበቅ ነበር። አንድ የወያኔ ባለስልጣን በዚያ ሁሉ እንግዳ ፊት ስማቸውን ጠርቶ በአክብሮት ሲጨብጣቸው ራሳቸውን አለመሳታቸውም ያስደንቃል። ሁኔታውን ስገነዘብ ታዲያ ማንነቴን ከማስረዳት ይልቅ ሳቄን ማቆም ተቸገርኩ።

"...ጋሽ ዝናቡ...እኔ የርሶ ተማሪ ነበርኩ ... ትዝ ይሎት እንደሆን ስለ መስፍን ሃብተማርያም ይነግሩን ነበር...አንድ ጊዜ ግጥም ፅፌ..."

ጋሽ ዝናቡ ፈገግ አሉ። አስታውሰውኝ ነበር...

* * *

የጥቅምት ብርድ እየቆፈነነን ቢሆንም በፀጥታና በስነ ስርአት ተቀምጠን የ11ኛ ክፍል የፖለቲካ ትምህርቱን ተያይዘነዋል። እንደ ዝቁዋላ ተራራ ግዙፍ የሆነው መምህር አንለይ ሃይሌ ከወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደ ፖለቲካ ማስተማሩን ቀጥሎአል፣

"ቤተክርስትያናት ወደ ቀበሌ ፅህፈት ቤት የሚለወጡበት ጊዜ ቅርብ ነው...አብዮት መራራ ናት... ውጤቷ ግን ጣፋጭ!...ማርክሳዊ ርእዮትን እንደ ቀበቶ ልንታጠቀው ይገባል - እንደ ብረት ቀበቶ!"

ተማሪዎች ሁሉ የፖለቲካ መምህሩን እንጠላዋለን! የጠላነው ፖለቲካ በማስተማሩ ሳይሆን ስለሚደበድበን ነበር። በፖለቲካ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ግማሽ ያህሉ ተማሪ ቡጢና ጥፊ ሳይቀምስ አይወጣም። ወጣት ሴቶችን ጠረጴዛ ላይ ወጥተው እንዲቆሙ በማድረግ እንዲያፍሩና እንዲሳቅባቸው ስለሚያደርግ አንለይ ሃይሌ ገና ሲመጣ የማይንቀጠቀጥ ተማሪ የለም። በዚሁ የ1976 የጥቅምት ወራትም እንደተለመደው ይደሰኩርብን ይዟል...

"አብዮታችን በግብታዊነት ከፊንዳበት እለት ጀምሮ..."

አንለይ ድንገት ዲስኩሩን አቆመና አንድ ባንድ ሲያስተውለን ቆየ።

"ትምህርቱ ሰልችቶአችሁዋል!?" ሲል ጮኾ ጠየቀን።

መልስ የሰጠ የለም። አንለይ እንደገና አምባረቀብን።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ሰልችቶአችሁዋል!?"

"አልሰለቸንም!!" ስንል ጮህን።

"ድገሙት!" አለን።

በጩኽት ደገምነው። አንለይ ፈገግ አለ። በመካከላችን ወዲያ ወዲህ ሲንጎራደድም ቆየ። እኛ ፀጥ ብለናል።

ድንገትም አንድ ያልተጠበቀ ጥያቄ ጠየቀን!

"እስኪ ሃገራችሁን የምትወዱ እጃችሁን አውጡ!"

ተማሪው በሙሉ እጁን አወጣ። ጥያቄውን በትክክል ሰምቻለሁ። ድፍረቱና አሳቡ ከየትና እንዴት እንደመጣልኝ በፍፁም ባላውቅም እጄን ሳላወጣ ቀረሁ። ከጎኔ ተቀምጦ የነበረ ተሻለ ይገዙ የተባለ ጓደኛዬም እንደኔው እጁን አለማውጣቱን አስተዋልኩ። ወዲያው ግን ሲያመነታ ቆየና እጁን ወደላይ መዘዘ። እኔ እጄን ለምን እንዳላወጣሁ በርግጥ አላውቅም ነበር። የማውቀው ነገር ቢኖር የፖለቲካውን ትምህርት እንደማልወደውና መምህሩንም በተደባዳቢነቱ እንደምፈራው ብቻ ነበር።

መምህር አንለይ የገዛ አይኑን ባለማመን እኔ ላይ አፍጥጦ ቀረ። የ11ኛ ክፍል የእርሻ ሙያ ተማሪዎች እጃቸውን እንደቀሰሩ ናቸው። ኤልሳ ዮሴፍ ከመጨረሻው ረድፍ ላይ ተቀምጣለች። አበበ ጉተማ በተለይ ትዝ ይለኛል። ዛሬ የት ይሆን? በበጥባጭነቱ የሚታወቀው አበባው ለገሰ አሜሪካ ነው አሉ። በድሉ ንጋቱ የኢትዮጵያ አየር ሃይል ባልደረባ ሆኖአል። አዜብ በላይ ግብፅ መሆንዋን ሰምቻለሁ። ስለሚያነክስ ኮካ የሚል ቅፅል ስም የሰጠነው የሞጆ ልጅ ማንነበር ስሙ!? እውነት ተሾመ ያቺ ጠይም ቆንጆ፤ ዛሬ የት ትሆን? አልነገርኳትም እንጂ ከዚች ልጅ ጋር ያይን ፍቅር ይዞኝ ነበር። እነዚህ ሁሉ የኛ ክፍል ተማሪዎች በአንለይ ጥያቄ መሰረት እጃቸውን እንደ ጭራሮ ወደ ላይ ዘርግተዋል። ከክፍላችን ውስጥ በብቸኛነት ማትሪክ አልፎ በህክምና ሙያ የተመረቀው ደረጀ አለማየሁ ከኔ ሁዋላ ተቀምጦ እንደነበር በፍፁም አይረሳኝም።

መምህር አንለይ በዝግታ ወደኔ ተራመደና ጠየቀኝ፣

"እጅህን ለምንድን ነው ያላወጣኸው?"

"ሃገሬን አልወዳትም" አልኩ።

"ለምንድነው የማትወዳት?"

"አላውቃትም"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ተነስ" ሲል አዘዘኝ።

ተነሳሁና ቆምኩ። ሰሌዳው አጠገብ እንድቆም ካዘዘኝ በሁዋላ ተማሪዎቹ እጃቸውን እንዲያወርዱ አደርጎ የተለመደ የፖለቲካ ዲስኩሩን ቀጠለ። አስር ደቂቃ ያህል እንደቆምኩ እግሬን ስለደከመኝ የመምህር አንለይን ዲስኩር አቋረጥኩት።

"መቆም ደከመኝ! እንድቀመጥ ፍቀድልኝ..."

ከላይ ያሉትን አረፍተ ነገሮች ተናግሬ ሳልጨርስ የአንለይ ሃይሌ ገበቴ የሚያክል መዳፍ ፊቴ ላይ ሲደረገም መብረቅ የወረደብኝ ያህል መሬትና ጣራው ጨላለመብኝ። በዚያ በተደበላለቀ ዝብርቅርቅ ሁኔታ ውስጥ ግድግዳውን ተደግፌ እንደደነዘዝኩ አንለይ ሲያንባርቅብኝ እየሰማሁት ነበር።

እንዲህ ሲል የወደፊት የህይወት እጣዬን ተነበየልኝ፣

"እንቁላል ነጋዴ ነው የምትሆነው!"

የመጨረሻው ክፍለ ጊዜ ነበር። ደወል እንደተደወለ አንለይ ያረጀ የቆዳ ቦርሳውን አንጠልጥሎ እየወጣ 'ተከተለኝ' ሲል አዘዘኝ። ደብተሬን ለማንሳት ወደ ጠረጴዛዬ ሳመራ ኤልሳ ዮሴፍና ደረጀ አለማየሁ ለሁለት ይዘው በምክር አጣደፉኝ።

"ሃገራችሁን የማትወዱ የተባለ መስሎኝ ነው' ብለህ ይቅርታ ጠይቀው!" ሲሉ ምክራቸውን ሰጡኝ።

በተደረገመብኝ ጥፊ ሳቢያ መጨላለሙ ገና ያልለቀቀኝ ቢሆንም ደብተሮቼን ሰብስቤ አንለይ ሃይሌ ላይ ለመድረስ ሩጫ ጀመርኩ።

ቢሮው ደጃፍ ላይ ደረስኩበት፣

"ማነው ስምህ?" ሲል ጠየቀኝ።

ስሜን ከነአባቴ ነገርኩት።

"ትግሬ ነሃ!?" አለ ዛቻ ባዘለ ድምፅ!

መልስ አልሰጠሁትም። በወቅቱ የቢሾፍቱ ልጅ ከመሆኔ ያለፈ ስለ ዘር መነጋገር አልለመድኩም ነበር። ትግሬ መሆኔ ለአንለይ ለምን የተለየ ትርጉም ሊሰጠው እንደቻለ የተረዳሁትም ከአያሌ አመታት በሁዋላ ከወያኔ ጎን ተሰልፌ መታገል ከጀመርኩ በሁዋላ ነበር።

አንለይ ጥያቄውን በማራዘም ስለ ወላጆቼ ማንነት፣ ስማቸውን፣ የት እንደሚሰሩ በዝርዝር ጠየቀኝ። ከታላቅ እህቴና ከባልዋ ጋር እንደምኖር ነገርኩት። የእህቴ ባል ዮሴፍ አብርሃም እንደሚባል ስነግረው፣ በዚያችው ቅፅበት የአንለይ ቁጣና ንዴት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሲበርድና ሲቀዘቅዝ አስተዋልኩ። የባንክ ኦዲተር ከነበረው የእህቴ ባል ጋር በኢጋማሚ በአንድ መንግስታዊ ኮሚቴ ውስጥ አብረው የሚሰሩና የሚቀራረቡ ኖረዋል።

"በል ሂድ ወደ ቤትህ!?" ሲል ማጅራቴን አንቆ አሽቀነጠረኝ።

ደረጄ አለማየሁና ኤልሳ ዮሴፍ ቆመው ይጠብቁኝ ኖሮ፤ የተፈጠረውን ለማወቅ በጉጉት ጠየቁኝ። ነገርኩአቸው። ሁለቱም በደስታ ከተነፈሱ በሁዋላ "በጣም ጅል" መሆኔን ነገሩኝ። እኔም "ጅል" በመሆኔ ጉዳይ ሳልከራከር ጥፊ የጠገበ ፊቴን እያሻሸሁ ወደቤቴ ሄድኩ። አንለይ "እንቁላል ነጋዴ ትሆናለህ!" ሲል የተነበየልኝን ግን ወዲያው ረስቼው ነበር...

...ከአንለይ ሃይሌ ጋር በድጋሚ የተገናኘነው ከስምንት አመታት በሁዋላ ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ ፕሬስ መምሪያ ሃላፊ የነበርኩ ሲሆን፣ ማለዳ ላይ የእለቱን ጋዜጦች እያገላበጥሁ ሳለ፤ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሊያነጋግረኝ እየጠበቀ መሆኑን ፀሃፊዬ ነገረቺኝ። እንድታስገባው ፈቀድኩ። ዋና አዘጋጁ አንድ የስፖርት ተለማማጅ ጋዜጠኛ ለመቅጠር ፈልጎ ከኔ ፈቃድ ለማግኘት ነበር የመጣው፣

"ለሙከራ ከኛ ጋር ሲሰራ ነው የቆየው። ጎበዝ ነው። ተስፋ አለው" አለኝ።

የስፖርት ዘገባዎችን አንብቤ ስለማላውቅ፣ ዋና አዘጋጁ የሚለኝን ከመስማት በቀር አስተያየት መስጠት እንደልማችል አውቅ ነበር፣

"በፍሪላንሰር ደረጃ እንቅጠረውና ከዚያ አይተን ቋሚ ልናደርገው እንችላለን" አለኝ።

የተቀጣሪውን ጋዜጠኛ ስም እንደዋዛ ጠየቅሁት፣

"አንለይ ሃይሌ ይባላል!" የሚለውን ከዋና አዘጋጁ አንደበት ስሰማ ትንፋሼን ዋጥኩ። የደበደበኝ የፖለቲካ አስተማሪ ይሆናል ብዬ ማመን ግን አልቻልኩም። የስም መመሳሰል ሊሆን ይችላል የሚለውን መቀበል በመፈለጌ፣

"ስለ ሰውየው ዝርዝር ነገር ታውቃለህ?" ስል ማብራሪያ የጠየቅሁት፤ በውስጤ ያደረው የማወቅ ጉጉት እንዳይታወቅብኝ ጥረት እያደረግሁ ነበር፣

በወቅቱ እኛ ወያኔዎች የዘርና የብሄረሰብ ጥያቄ እናበዛ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ነበርና ዋና አዘጋጁ ስለ ተቀጣሪው ሰው ዘር የጠየቅሁ መስሎት፣ ፊቱን ጨፍገግ አድርጎ፣

"አማራ ነው፣ ጎጃም" አለ።

"የጠየቅሁህ የቀድሞ ስራውን ነበር"

"የስፖርት መምህር የነበረ መሆኑን ነግሮናል"

"የት ከተማ?"

"ደብረዘይት"

በረጅሙ ተነፈስኩ። አንለይ ሃይሌ አልዋሸም። የካድሬ ትምህርት ወስዶ የፖለቲካ መምህር ከመሆኑ በፊት የስፖርት መምህር ነበር። ደርግ ሲወድቅ ግን የፖለቲካ መምህራን ቦታ በማጣታቸው አንለይ ስራ አጥ ሆኖ መክረሙን ተረዳሁ። ውሳኔዬን ለዋና አዘጋጁ ገለፅኩ፣

"ለአስተዳደር ሃላፊው ንገረውና ቅጥሩ ይፈፀም!" ስል ትእዛዝ በማስተላለፍ አሰናበትኩት።

ብቻዬን ስሆን ስለ አንለይ ጥቂት አሰላሰልኩ። ሊያውቀኝ እንደማይችል ግልፅ ነበር። ያ ኮስማና ተማሪ የዛሬው የሱ ቀጣሪ መምሪያ ሃላፊ ይሆናል ብሎ ሊገምት ስለማይችል፤ ማንነቴን ሳያውቅ ስራውን በሰላም ይሰራ ዘንድ ወሰንኩ። ካወቀ ሊረበሽ ይችል ይሆናል ብዬ በነፃነት ተውኩት።

ከዚያን እለት ጀምሮ የአዲስ ዘመንን የስፖርት አምድ ማየት ጀመርኩ። አልፎ አልፎም አንለይ የሚፅፋቸውን ዘገባዎች አነብብኩ። ጥሩ ነበሩ። ባጭር ጊዜ ከነባር ጋዜጠኞች ያላነሰ ፅሁፎችን ማስነበብ መጀመሩን ስመለከት፣ ያኔ ተማሪ ሳለን ሲደበድበን የሚውለው ተገቢ ቦታውን ባለማግኘቱ፣ ምናልባትም እሱም የማይወደውን ስራ ታዝዞ በመስራቱ ሊሆን እንደሚችል መገመት ጀምሬ ነበር። በርቀት ሆኜ ስለ አንለይ ባህርያትና የስራ እንቅስቃሴ መከታተሌን ግን ቀጠልኩ። ስብሰባ ላይ የመናገር ፍቅር ያለው ቢሆንም፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ በአዲስ ዘመን ውስጥ ተግባቢና የሁሉም ወዳጅ መሆን መቻሉን ተረዳሁ። አንለይ ስለኔ ማወቅ አለማወቁን ለማጣራት ያህል አንድ ሁለት ጊዜ ያህል ወደ ስፖርት አዘጋጆች ቢሮ ጎራ ብዬ ጥቂት አወጋሁዋቸው። አንለይ በፍፁም አላወቀኝም። ማንነቴን ሳልነግረውም መስሪያ ቤቱን ለቀቅሁ።

አንለይ እዚያው ቀረ...

...ለሶስተኛ ጊዜ ከአንለይ ሃይሌ ጋር የተገናኘንበት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መድረክ ግን ሲያስገርመኝ ይኖራል። ከፕሬስ መምሪያ ከተነሳሁ በሁዋላ በስራ አስኪያጅነት እመራው በነበረው የፋና ዴሞክራሲ አሳታሚ "ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ" የሚል መፅሃፍ አዘጋጅተን ለገበያ አበቃን። ሜጋ የኪነጥበባት ማእከልም በዚሁ መፅሃፍ ላይ አንድ የግምገማ መድረክ ያዘጋጃል። በርካታ እንግዶች በተገኙበት በዚሁ መድረክ ላይ ከመጨረሻው ረድፍ ላይ ተቀምጬ በዝምታ እያዳመጥኩ ነበር። የመፅሃፉን ሃሳብ ከመወጠን አንስቶ፤ ስሙን እስከማውጣት ከዚያም ባሻገር ታሪኮችን በመፃፍና የአርትኦት ስራ ማካሄዱ ባብዛኛው የኔው ስራ ነበርና ተሳታፊዎቹ የሚሰጡትን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ አስተያየቶች በአንክሮ እየተከታተልኩ ነበር። በመካከሉ አንድ ግዙፍ ሰው እጁን ካወጣ በሁዋላ ከመቀመጫው በመነሳት መናገር ጀመረ።

አንለይ ሃይሌ ነበር...

የመፅሃፉንና የዝግጅቱን ድክመቶች እየጠቃቀሰ ብዙ ተናገረ። ጠንካራ የሚላቸውን ነጥቦችም አንድ ባንድ ዘረዘረ። በእግረ መንገዱ ታዲያ የኔን ስም በመጥቀስ ለትረካዎቼ ያለውን አድናቆት ገለፀ። በዝምታ ተቀምጬ አዳመጥኩ።

ከግምገማው ማብቃት በሁዋላ በግብጥው ላይ ሁላችንም በግልፅ ተገናኘን። ረጃጅም የድራፍት ብርጭቆዎችን ይዘን ማውጋት ቀጠልን። ደራሲና ጋዜጠኛ ደምሴ ፅጌ፣ ስለሺ ተሰማና፣ እቁባይ በርሄ እንዲሁም ሌሎች ጋዜጠኞችና የጥበብ ሰዎች ክብ በሰሩበት ቡድን ውስጥ ነበርኩ። በሞቀ ሁኔታ እያወጋን ሳለ አንለይ ሃይሌ ጃምቦ የድራፍት ብርጭቆውን እንደያዘ መጥቶ ተቀላቀለን።

"እነሆ ጊዜው አሁን ነው" አልኩ ለራሴ።

"አንድ ጊዜ አድምጡኝ!" ስል ጮህኩ።

ሁሉም ወደኔ አተኮሩ፤ ዝምታ ሆነ።

"አንድ ታሪክ ላጫውታችሁ፣ ይህ ታሪክ እኔና አንለይ ሃይሌን የሚመለከት ነው!"

እዚያ የነበረው ሁሉ ወደ አንለይ ተመለከተ። አንለይ ግራ በመጋባት አፈጠጠብኝ፣

"የ11ኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ አንለይ መምህሬ ነበር። በዚያን ወቅት በኔና በሱ መካከል ስለተፈጠረ፤ በፍፁም ልረሳው ስለማልችለው አንድ አጋጣሚ ላውጋችሁ..."

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ትረካዬን ገታሁ። የአንለይ ገፅታ በመደነቅ ሲለዋወጥ እያየሁ ነበር። ታሪኩን ተረኩላቸው። በፀጥታ አዳመጡ። ተርኬ እንዳበቃሁ ሁሉም ፊታቸውን ወደ አንለይ ሃይሌ አዞሩ። 'ይህ ታሪክ እውነት ይሆን?' እያሉ በአይኖቻቸው ጠየቁት። አንለይ አላመነታም! እስከዛሬም የሚያስደንቀኝን ምላሽ ሰጠ፣

"የሚገርም ነው!" ሲል ነበር የጀመረው "ያ ጅል ወጣት አንተ ከነበርክ በጣም የሚደንቅ ነው! በዚያን ወቅት ምን አይነት የፖለቲካ ትምህርት ነበር የምትጠብቀው? 'ሃገሬን አልወዳትም' ማለትስ ምን ማለት ነው? ዝም ብዬ ባልፍህ የሚደርስብኝን ታውቅ ነበር? ለመሆኑ በክፍላችሁ ውስጥ አባቶቻቸው የአየር ሃይልና የኢሰፓ የደህንነት አባሎች የነበሩ ስንት እንደነበሩ ታውቅ ነበር? አታውቅም! እና አሁን እንደነገርከን በቡጢ ወይም በጥፊ አነደድኩህ! ከዚያስ? አንተም እኔም ተረፍን!!"

ሁላችንም ሳቅን!

አንለይ ሃይሌ እንደገና የበላይነት ያዘ።

የፖለቲካው መምህር ዛሬ የት ይሆን? ማን ያውቃል? ከእለታት አንድ ቀን ቢሾፍቱ ሃይቅ ዳርቻ ተቀምጠን ቢራ እየጠጣን እናወጋ ይሆናል....

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 9 -
ወንድሙ ጩበሮ

በብርሃን ያየነው - ሲጨልም ከጠፋ፣
ይጨልም ጨርሶ - ጨለማ ምን ከፋ?
ስብሃት ለጨለማ - ይጨልም፣ ይጨልም፣
አይኖቻችን ይጥፉ - እያዩም አይጠቅሙም፤

(ግጥም - ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም)

በጋዜጠኛነት የስራ ዘመኔ ካነጋገርኳቸው መካከል ወንድሙ ጩበሮ የማይረሱ ሰው ሆነው ካይምሮዬ ላይ ተመዝግበዋል። የእኒህን አስገራሚ አዛውንት ዝና ሰምቼ ቃለመጠይቅ ላደርጋቸው ዶርዜ ድረስ ተጉጥለሁ። በጠቋሚ ከቤታቸው ስደርስ፣ ነጭ ጋቢ የተጀቦኑ ግዙፍ ሰው ከቤታቸው በረንዳ ላይ ተቀምጠው ነበር። ተፈጥሮ ከግርማ ሞገሳቸው ጋር የሚስማማ ሃያል ድምፅ ቸራቸዋለች። ተዋወቅሁዋቸው፣

"ከእፎይታ መፅሄት ነው የመጣሁት"

"ምን እፎይታ አለና እፎይታ ሆነ ስማችሁ!?"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከት ብለው ሳቁ!

“ለመፅሄታችሁ ሌላ ስም ፈልጉለት! እናንተ እፎይታ አጊኝታችሁ ከሆነ ደግሞ ’የኛ እፎይታ’ በሉት። ህዝቡ ግን እፎይታ አላገኘም።”

እንደገና በሳቅ ጮሁ!

ሳቃቸው ለጆሮ የሚጥም ዜማ ያለው ደማቅና ግዙፍ ነበር። ዶርዜ ላይ የሚኖሩ አርሶአደር እያነጋገርኩ መሆኑን ልጠራጠር ምንም አልቀረኝ።

“ቀጥል ጥያቄህን?” አሉኝ።

እንደምንም ቀልቤን ተቆጣጥሬ ለአንድ ሰአት ያህል አነጋገርኳቸው። በሰፊው ከገለፁልኝ ሃሳብ ውስጥ እንዲህ የሚል ነበረበት፣

“...ለመለሰ ዜና ‘ሁሉንም እናውቃለን!’ የሚል መልእክት ንገረው! እሱ ሴት ልጁን በእንግሊዝኛ ቋንቋ እያስተማረ መሆኑን ሰምተናል። ምነው ታዲያ በትግርኛ ሳያስተምራት ቀረ? የታገለው በቋንቋችን ስላልተማርን ተበድለናል ብሎ አልነበረም? ምነው ታዲያ ሴት ልጁን ከትግሉ ፍሬ ሳያቀምሳት ቀረ? የማናውቅ አይምሰላችሁ! የባለስልጣናት ልጆች አፋቸውን በእንግሊዝኛ ቋንቋ እየፈቱ አይደለም እንዴ? እኛን ደግሞ ’በዶርዚኛ ቋንቋ በመማር መብታችሁን አስከብሩ!’ ትሉናላችሁ። እኔ ልጆቼ በአማርኛ ቋንቋ እንዲማሩ ነው የምፈልገው። ቢቻል ደግሞ በእንግሊዝኛ! ምክንያቱም ልጄ አማርኛ ከቻለ በመላ ኢትዮጵያ ተዘዋውሮ የመስራት እድል ያገኛል። እንግሊዝኛ ከቻለ ደግሞ በመላ አለም! በዶርዚኛ ተማሩ የምትሉን ልጆቻችን ሸማኔ ሆነው እንዲቀሩ ነው? በል እንግዲህ ጋዜጠኛ ነኝ ካልክ ይህን ሳትቀንስ ፅፈህ መለሰ ዜና እንዲያነባት አድርግ! አትፍራ... ‘ማነው ይህን ያለው?’ ካሉህ ወንድሙ ጨበሮ ነው ብለህ ተናገር! ዶርዜ ከተማ፣ የቤት ቁጥርም ያውልህ፣ ፃፍ! ከፈራህ ደግሞ አሁኑኑ ንገረኝ። ምሳ በልተህ፣ ጠላ ጠጥተህ ትሄዳለህ!”

እንደገና በዚያ ግዙፍ ድምፅ ሳቁ!

ዶርዜን ለቅቄ ስወጣ ሸማግሌው የተናገሩትን ሳልቀንስ እንደማትመው ፎክሬ ነበር። አዲስ አበባ እፎይታ ቢሮ ከገባሁ በሁዋላ ግን ፉከራዬን ፈልጌ አጣሁት።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስለዚህ፣ "...መለሰ ዜና ሴት ልጁን በእንግሊዝኛ ቋንቋ እያስተማረ መሆኑን ሰምተናል። ምነው ታዲያ በትግርኛ ሳያስተምራት ቀረ? የታገለው በቋንቋችን ስላልተማርን ተበድለናል ብሎ አልነበረም?" የሚለውን ቆርጬ ጣልኩት።

"ዋናው አሳባቸውን መግለፃቸው ነው" ብዬም ራሴን ለማሳመን ጣርኩ።

የቆረጥኳቸው አረፍተነገሮች የቃለመጠይቁ ውበትና አስረጅ የነበሩ ቢሆኑም እንደትርፍ ንግግር ወሰድኳቸው።

በርግጥ "ፈርቻለሁ?" ስል ራሴን ጠይቄ ነበር። "አልፈራሁም!" ሆነ መልሴ። ፈርተሃል! አለኝ ህሊናዬ። አልፈራሁም! ብዬ ፎከርኩ። ፈርተሃል! - አልፈራሁም! በመጨረሻ ማታ ላይ እየጠጣሁ ሳለ፣ "ፈርተሃል!" አለኝ እንደገና። አዎ ፈርቻለሁ! ብዬ ተገላገልኩት።

የዶርዜው አዛውንት አመለካከት ትክክልም ይሁን አይሁን አሳባቸውን ገልፀዋል። ልጆች አፋቸውን በፈቱበት ቋንቋ ትምህርት መጀመራቸው በመላው አለም ተቀባይነት ያገኘና የሚሰራበት ነው። ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ግን ወንድሙ ጨበሮ ትክክል ነበሩ። ዶርዜ ኮረብታ ላይ ቆመህ ስታየው ቋንቋ የኢኮኖሚ እንጂ የፖለቲካ አጀንዳ አይደለም እያሉን ነበር። በርግጥም በደከመችው የዶርዜ መንደር ተገኝቶ፣ መፃህፍት በሌለበት ሁኔታ በዶርዜ ቋንቋ እንዲማሩ ስለተቆለፈባቸው ማቲዎች የሚያስብ፣ የወንድሙ ጨበሮን ቁጣ በትክክል መረዳት ይቻለዋል። የመንደሪትዋ ዜጎች ሁሉ ልጆቻቸውን በዶርዜኛ ቋንቋ ማስተማር እንደማይፈልጉ ሽማግሌው ነግረውኛል። ሌላው ቀርቶ የወረዳው አስተዳዳሪ ልጁን አርባምንጭ ልኮ በአማርኛ እያስተማረ ነበር።

ከሁለት ሳምንታት በሁዋላ የመለስን ስሞች በሙሉ ቆራርጬ በመጣል ቀሪውን እፎይታ መፅሄት ላይ አተምኩት። መፅሄቱ ታትሞ እንደወጣ በቅድሚያ የደወለልኝ የጦማር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በፍቃዱ ሞረዳ ነበር፣

"ምንድነው የማነበው?" ሲል ጠየቀኝ።

"እኛም እኮ አንዳንድ ጊዜ እውነት ይርበናል!" አልኩት'

"በዚሁ ከቀጠልክ ከስራ ተባረህ ወደኛ ማህበር መግባትህ አይቀርም" ሲል ቀልዶ ስልኩን ዘጋ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የሽማግሌው ቃለመጠይቅ በኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ ክፍል ማእበል ማስነሳቱ አልቀረም! በተለመደው ወርሃዊ ግምገማ ላይ አጀንዳው ተነስቶ፣ ነጋሽ የተባለው የግምገማው ባልደረባ ስለ ቃለመጠይቁ ማብራሪያ እንድሰጥ ጠየቀኝ፣

"..ልጆች አፋቸውን በፈቱበት ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን መማር እንደሚገባቸው በመርህ ደረጃ የማምንበት ነው። ጋዜጠኛ እንደመሆኔ ግን የወንድሙ ጩበሮን አመለካከት አትሜያለሁ!" ስል መልስ ሰጠሁ።

እንደተለመደው ተወገዝኩ። ስለ አብዮታዊ ጋዜጠኛነት ሚናም ተሰበከሁ። የተለመደ ነበር። እኔም እንደተለመደው ስብሰባውን ለማሳጠር ስህተቴን በነፋስ ፍጥነት ተቀበልኩ።

(...በስብሰባ ፍቅር ከተለከፉ ሰዎች ጋር ከመነታረክ ቶሎ ብዬ፣ "ተቀብዬዋለሁ!" በማለት መገላገልና በሚቀጥለው ቀን የማምንበትን የመሰራቱን ዘዴ እንደ ስልት ይዤው በተደጋጋሚ እጠቀምበት ነበር። አለበለዚያ አንተን ለማሳመን ሲባል ስብሰባው አንድ ሳምንትም ሊወስድ ይችላል። ስለዚህ ባታምንበትም ቶሎ ስህተትን መቀበል ፍቱን ዘዴ ነበረች። ይህቺን ዘዴ ብዙዎች አባላት ለምደዋት፣ አንዳንዶቹ ገና አስተያየት ሳይሰጥ "የምትሉትን ሁሉ እቀበለዋለሁ" ይሉ ነበር።)

የእፎይታ መፅሄት የአርባ ምንጭ ወኪል ሪፖርተር እቱ ገረመው ትባል ነበር። የወንድሙ ጩበሮ ቃለመጠይቅ ከታተመ ከስድስት ወራት በሁዋላ አዲስ አበባ ለስራ መጥታ በወሬ ወሬ ስለ ዶርዜው ሽማግሌ አነሳች፣

"...ወንድሙ ጩበሮ በድፍን አርባምንጭ ታዋቂ ሆነዋል" ስትል በሞቀ ስሜት አወጋቺኝ "...በአንድ የህዝብ ስብሰባ ላይ እሳቸው ሲገቡ ህዝቡ ሁሉ ከመቀመጫው ተነስቶ በከፍተኛ ጭብጨባ ተቀበላቸው። በመንገድ ላይ ሰው አያሳልፋቸውም። እያስቆመ የማይጨብጣቸው የለም..."

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 10 -
የአብዱልመጂድ ቁጣ!

የቆጡን የባጡን - ስቀበጣጥረው፣
የግራ የቀኙን - ስንኮታትለው፣
ልባችሁ ጠርጥሮ - በሌላ ቢያስበኝ፣
አይዞአችሁ እመኑኝ - እኔ ጥሬ ጨው ነኝ፣
መለቀጥ መደለዝ - ገና እሚቀረኝ፣

(ግጥም - ጋንፋሬ ዋቻ)

በ1988 የተፈፀመ አንድ ታሪክ ላጫውታችሁ።

የመገናኛ ሚኒስትር ዶክተር አብዱልመጅድ ቴሌኮሚኒኬሽንን እንደሚጎበኝ ፕሮግራም ይያዝና ለኔ ተደውሎ ይነገረኛል። አብዱልመጅድ ሲናገር መስማት ስለምወድ ሪፖርተር ከመላክ ይልቅ ራሴው ሄድኩ። የልማት ስራ ገለፃ እየተከናወነ ነበር። ምክትል ሚኒስትሩ አየነው ከአብዱልመጅድ ጎን ተገኝቶአል። የቴሌ ሃላፊዎች እነ አቶ ጥበበ አርጋውና አቶ ዘለቀ እንዲሁም ስራ አስኪያጁ አቶ ፍቅሩ...ሁሉም እዚያው ነበሩ።

ከአየነው ጋር በቅርብ እንግባባ ነበር። ከስራ ውጭ ቁጭ ብለን የምናወጋበት ጊዜም ነበር። እኔ ለስራ ወደ ደቡብ አፍሪቃ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ፕሪቶሪያ በሄድኩበት ጊዜ አየነውም በኢጋጣሚ ትግራይ ላይ ባቡር የመዘርጋት ፕሮጀክት ላይ ለመነጋገር ፕሪቶሪያ መጥቶ ጥቂት አብረን ሰነባብተናል።

የሆነው ሆኖ ገለፃው ቀጠለ...

ሁላችንም ደንግጠን ነበር። ከሆላንድ በእርዳታ የተገኘ ARF 101 በሚል የሚታወቀው የማዞሪያ ቴክኖሎጂ አንድ አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በስምንት ከተሞች ላይ መተከሉ እየተብራራ ነበር። ከተሞቹ ግድግዳ ላይ በተሰቀለ ካርታ ላይ በቀይ ቀለማት ምልክት ተደርጎባቸዋል። እነዚህም ከተሞች አዲግራት - አድዋ - ሽሬ - አክሱም - ማይጨው - ተምቤን - ሆሳእናና ወላይታ ነበሩ።

ዶክተር አብዱልመጅድ ድንገት በንዴት እሳት ሆነ፣

"አቶ አየነው!" ሲል ጮኸ "...ምንድነው የምንሰማው ሪፖርት? ከሆላንድ ርዳታ ተገኘ...እና እርዳታው ለስድስት የትግራይ ከተሞችና ለሁለት የደቡብ ከተሞች ተከፋፈለ! ምንድነው ይሄ !? እስቲ እንዴት እንዳሰላችሁት አስረዳኝ - አቶ አየነው!?"

አየነው ቢተውልኝ ይርበተበት ጀመር፤

"ዶክተር አብዱልመጅድ እኔ ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም። አቶ ጥበበና አቶ ፍቅሩ አስፋው ይጠየቁ...እኔ በፍፁም አላውቅም"

አየነው የትግራይ ሰው ነው። በምክትል ሚኒስትርነት ቦታ የተመደበውም ይህን የመሰሉ አድኋዊ ስራዎች እንዲሰራ መሆኑ ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ ያሻውን ያህል አድሎአዊነት ቢያጠቃውም አየነው ይህን የመሰለ ግልፅ ስህተት እንዴት ሊሰራ እንደቻለ ፈፅሞ አልገባኝም ነበር። አቶ ፍቅሩና አቶ ጥበበ ማብራራት ጀመሩ፤

"ትግራይ በጦርነት የተጎዳ ክልል እንደመሆኑ እድሉን ሰጥተናቸዋል!"

አብዱልመጅድ ግራ ተጋብቶ አንዴ አየነውን በመቀጠል አቶ ፍቅሩን ሲመለከት ቆየና፣

"ትግራይ ስድስት ማዞሪያ ሲያገኝ ጅጅጋ አንድ ማዞሪያ የተነፈገው በምን ስሌት እንደሆነ አልገባኝም። ከአድዋና ከጅጅጋስ በንግድ እንቅስቃሴና በህዝብ ብዛት ማን ይበልጣል?" ሲል ጠየቀ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በዚያችው ቅፅበት ድራማ እየሰራ መስሎ ተሰማኝ። የነበርንበት አዳራሽ የተወጠረ መሰለ። አብዱልመጅድ ይህን ውጥረት የተገነዘበ መሰለኝ፤ መልሶ ራሱ አረገበው፣

"በሉ! በአስቸኳይ ለጅጅጋ ከተማ ማዞሪያ እንዲተከል! በጥቂት ወራቶች ውስጥም የዚህን ሪፖርት እፈልጋለሁ"

ከጉብኝቱ ማብቂያ በሁዋላ በልተን ጠጥተን ተለያየን። በግብጦው ሰአት ከአየነው ቢተውልኝ ጎን ነበር የተቀመጥኩት።

"ይህን ሪፖርት እንዳትፅፈው!"ሲል በጆሮዬ ሹክ አለኝ።

"እንዲህ መደረጉን ግን ታውቅ ነበር?" ስል ጠየቅሁት።

አየነው ሳቀ። መልስ አልሰጠኝም። ሞኝነቴ ገባኝና ወደሌላ ጥያቄ ዘለልኩ።

"የአማራው ክልል ጉዳይ ግን አልተነሳም። የኦሮሚያም አልተጠቀሰም። አብዱልመጅድ ሲቆጣ ስለሁሉም ክልሎች ያሰበ መስሎኝ ነበር። የጅጅጋን ብቻ ሲጠይቅ ግን ደነገጥሁ!" ስል ጠየቅሁት፣ አብዱልመጂድ የሶማሌ ክልል ተወላጅ መሆኑን እያሰብኩ።

"የአማራው ክልል ከተሞች በደርግ ጊዜ የተተከለ ማዞሪያ አላቸው" ሲል ገለፃውን ጀመረ አየነው "...ዘለቀና ጥበበ የደብረብርሃን ሰዎች ናቸው። ይህ መስሪያ ቤት በጎጃምና በመንዜዎች የተያዘ ነው። ጎጃሞች GDR ተብለው ይታወቃሉ። (Gojam Democratic Republic) ማለት ነው። መንዜዎችን ደግሞ MDF (Menze Democratic Front) ይሏቸዋል። በደርግ ጊዜ የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም ለአማራው ከተሞች ማዞሪያ ሲተክሉ ነው የኖሩት፤ አሁን ደግሞ የኛ ተራ ነው። እነ ጥበበ ይህን ያውቃሉ። ተቃውሞ የላቸውም። 'ጊዜያችሁ ነው፤ ተራችሁ ነው' ይሉናል"

"የኦሮሚያስ?"

"ደብረዘይት ማዞሪያ አለው፤ ሌላ ምን ትፈልጋለህ?" አለኝ እየሳቀ።

"የምሬን ነው አየነው?"

"በጦርነቱ ለተጎዱ ከተሞች ነው ቅድሚያ የሰጠነው"

ከሁለት አመታት በሁዋላ ይመስለኛል በጉብኝቱ ወቅት ገለፃ ያደርግ ከነበረው ባለሙያ ጋር በአጋጣሚ መጠጥ ቤት እንገናኝ ጀመር። ኢቦኒ ድራፍት ቤት ነበር የተግባባነው። የወያኔ ጋዜጠኛ መሆኔን በፍፁም አላወቀም። የመጀመሪያ ቀን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የመንዝ ተወላጅ ከሆነ ገጣሚና ደራሲ ጋር ስላየኝ በሁለተኛውና በሶስተኛው ቀን ብቻችንን ስንገናኝ አምኖኝ ነፃ ሆኖ ነበር የቀረበኝ። እየተግባባን ስንሄድ በዚያን ቀን አብዱልመጅድ ስለተናገረው ንግግር ከሰዎች መስማቴን ነገርኩት። ሞቅ ብሎትም ስለነበር ከልቡ እየሳቀ ያወጋኝ ያዘ፣

"የአየነው ችግር መስገብገቡ ነው። እርዳታ ተገኘ ሲባል ገና ለገና ትግራይ በጦርነት የተጎዳች...እያለ መስገብገብ ጀመረ። ብቻውን ሊበላው ፈለገ። እኛ ደግሞ ብቻውን እንዲበላ አደረግነው። የሚገርምህ በደርግ ጊዜ እንኳ የማንቀበለው የነበረውን ቴክኖሎጂ ነው ሆላንዶች ለኢትዮጵያና ለኤርትራ በእርዳታ ያቀረቡት። ኤርትራ አልቀበልም ብላ ስትመልሰው የኤርትራን ጨምረው ለኛ ሰጡን። እኛ ደግሞ ለትግራይ አስታቀፍናቸው። ARF-101 ከሚባል ቴክኖሎጂ በሁዋላ ARF 102 የሚባል አለ። ከዚያ በሁዋላ AXE-10 ገብቶ ነበር። እንግዲህ ልብ በል AXE-10 በደርግ ጊዜ ባህርዳር ጎንደርና ደብረብርሃን ተተክሎ ነበር። ARF 101 ኢንተርኔት የማይቀበል ሁዋላ ቀር ቴክኖሎጂ ነው። በደርግ ጊዜ ARF - 102 በእርዳታ ሊሰጠን ተጠይቆ አንቀበልም ብለን መልሰነዋል። አየነው ARF 101 የተባለ በእርዳታ አግኝተናል ብሎ ሲንሰፈሰፍ ምን እናድርግ? አስታቀፍናቸው! ብንነግራቸው ተንኮል ይመስላቸዋል፤ ኢትዮጵያን እየመሩ 'ለትግራይ እርዳታ አግኝተናል' ይሉሃል! 'አግኝታችሁዋል!? ጥሩ ነው!' ገብሩ አስራት ሁለት እጥፍ ውሎ አበል እየከፈለን ትግራይ ከረምን - የሞተ ቴክኖሎጂ ተከልንላቸው!!"

እነ ጥበበ፣ ፍቅሩና ዘለቀ ከስራ መባረራቸውን የሰማሁት ዘግይቼ ነበር። የተባረሩት ግን በቴሌ ስም የአላሙዲንን እቃዎች ማስገባታቸው ተደርሶበት ስለመሆኑ ቢወራም፤ የቴሌው ባለሙያ ያጫወተኝን ታሪክ የፀጥታው መስሪያ ቤት ሳይደርስበት አልቀረም። በሚሊዮናት ወጪ በትግራይ የተተከሉትን ሁዋላ ቀር ማዞሪያዎች እንደገና እየነቀሉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መተካት ጀምረው ነበር። የሚገርመው ግን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሌላውን የኢትዮጵያ ክልል ያስታወሰው አለመኖሩ ነው። አያሌ ባለሙያዎችም ከቴሌና ከየመስሪያ ቤቱ እየተመነጠሩ ተባረሩ።

በስደት ሳለሁ አየነው ራሱን እንደገደለ ሰማሁ። አብዱልመጂድም አረፈ። አምላክ ነፍሳቸውን ይማር!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 11 -
የዘመናችን አንበሶች

ያዜን ዘመን ሽበት - ያጋም ጥጉን ህይወት፣
የሰማዩን ውተት - የንቅርት ላይ ውበት፣
እኔማ ፈጀሁት - ብርቱ ጫማ ሆኜ፣
ሲረግመዱብኝ - ዘለአለም ጨክኜ፣

(ግጥም - አበራ ለማ)

* * *

ለማታምነው ነገር ስትምል፣
የህሊናህ መታፈን ሃይል፣ ሲቀበተት ያንጎልህ ቅል፣
ቅስምህ እኮ ይፈነዳል፣ ደም ስርህ ሌት ተቀን ሲግል፣

(ግጥም - ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን)

ዮንሆይ አንበሶች ነበሯቸው።

አቅማቸው በብረት ግርግም ውስጥ የታገደ እስረኛ አንበሶች። እነሆ! መለስ ዜናዊም ታዲያ የራሱ ዘመናዊ አንበሶች አሉት። ይህን ያስተዋልሁት ከእለታት አንድ ቀን ተስያት ፕሬዚዳንት ነጋሶ ጊዳዳን በቤተመንግስት ተገኝቼ ቃለመጠይቅ ባደረግሁበት ወቅት ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በርግጥ ጥቂት የማይባሉ የመለስ ዜናዊ አንበሶች የብረት አጥራቸውን ሰብረው ወደ ነፃው ጫካ አምልጠዋል። አልማዝ መኮ - ሃሰን አሊ - ተሾመ አስራት እና እኔ ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ነን። የመለስ አንበሶች ከጃንሆይ አንበሶች የሚለዩት ወደ ብረት ግርግሙ ገብተው የሚታሰሩት በፈቃዳቸው በመሆኑ ነው።

ህዳር፣ 1991 ለቃለምልልሱ በተያዘልኝ የቀጠሮ ሰአት ከፕሬዚዳንቱ ቢሮ ተገኘሁ። እናም ሶስት ሰአት ያህል አብሬያቸው ቆየሁ። ዶክተሩ ከሰጡኝ ቃለምልልስ አይነስውሩ ወላጅ አባታቸው ታዋቂ ሚስዮናዊ ከመሆናቸው በፊት በልመና ይተዳደሩ እንደነበርና የስምንተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ወድቀው እንደነበር የገለፁልኝ በእጅጉ መስጠኝ ነበር። ከአንድ ዶክተር ይህን የመሰለ ግልፅ ግለ–ታሪክ መስማት ይመስጣል። የኢህአዴግን ውስጣዊ ችግር በተመለከተ ግን ዶክተሩ በልበሙሉነት መናገር ተሳናቸው። የአራት ጥምር ድርጅቶች ፓርቲ በሆነው ኢህአዴግ ውስጥ የስልጣን ክፍፍሉ ፍትሃዊ መሆኑን ነገሩኝ።

* * *

ቃለ-ምልልሱን በማካሄድ ላይ ሳለሁ የብቸኛ አንበሳ የጩኸት ድምፅ በተደጋጋሚ እሰማ ስለነበር ስራዬን እንዳበቃሁ ስለ አንበሳው አነሳሁላቸው፣

"የጃንሆይ አንበሳ ነው" ሲሉ ነገሩኝ።

"እስካሁን አልሞተም የጃንሆይ አንበሳ?"

"የልጅ ልጅ ሳይሆን አይቀርም"

"ምን ሆኖ ነው ታዲያ የሚጮኸው?"

ዘግየት አሉና ምላሽ ሰጡኝ፣

"እናቱ በቅርቡ ስለሞተችበት ነው"

ፕሬዚዳንት ነጋሶ ከተቀመጡበት በመነሳት መጋረጃውን በመግለጥ የለቅሶ ቃና ባለው ድምፅ የሚያላዝነውን አንበሳ ሊያሳዩኝ ሞከሩ። ከመስኮቱ ባሻገር ያሉት የዛፍ ቅርንጫፎች ስለከለሉኝ ማየት አልቻልኩም። መጋረጃውን እንደነበረ መልሰውት ወደ ወንበራቸው እየተመለሱ፣

"ሌሊትም ቀንም እንዲችው እንዳለቀሰ ነው - ከናቱ ሞት ወዲህ!" ፋታ ወሰዱናም ጢም አልባ አገጫቸውን እያሻሹ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስለ አንበሳው ጥቂት አከሉ፣ "በርግጥ ሚቿ እናቱ ብቻ አልነበረችም። ሚስቱም ነበረች። አንበሳው ሚስቱንና እናቱን በአንድ ቀን አጣ!"

"በምን ሞተች እናቱ?" ስል ጠየቅሁ።

"በወሊድ"

ዘግየት ብዬም፣

"ለመሆኑ ምን ትመግቡታላችሁ ?" ስል ጠየቅሁ።

"በቀን አምስት ኪሎ ስጋ"

ዶክተር ነጋሶ የደመቀ ድምፅ አልባ ሳቅ ካስከተሉ በሁዋላ እንዲህ ሲሉ አከሉበት፣

"ሚስቱና እናቱን ሲያጣ ብቸኛ ሆነ። ብቸኛነቱ ሊያበሳጨው ይችላል። ብረት ቤት ውስጥ ብቻውን ተዘግቶበት ደስተኛ ሊሆን አይችልም..."

ጥቂት በዝምታ ቆየን።

ዶክተር ነጋሶ ምን እየተረኩልኝ እንደነበር በወቅቱ ልብ አላልኩም። ነጋሶ የማስታወቂያ ሚኒስትር ሳሉ የቅርብ አለቃዬ ነበሩ። መኪናቸውን ሱቅ በር ላይ አቁመው ሲጋራ የመግዛት ልምድ እንደነበራቸው አውቃለሁ። በውበት ካጌጠውና በተክሎች ከተሸለመው የጃንሆይ ግቢ በማያረካ የስራ ምደባ ተቀምጠ መዋል በነፃነት የመኖር ልምድ ለነበረው አንድ የታሪክ ምሁር የመታሰር ያህል ፈታኝና ከባድ መሆኑን ያገናዘብኩት ቤተመንግስቱን ለቅቄ ከወጣሁ በሁዋላ ነበር።

ዶክተር ነጋሶ ይህን የእስር ህይወት ለምን መረጡ?

ለነገሩ እኔስ ነፃ ነኝን?

'በአለም ላይ ሶስት አይነት ጋዜጠኞች አሉ' የሚል ነገር አንድ ቦታ አንብቤያለሁ። የመጀመሪያዎቹ "እንዴት ልፃፍ?" ብለው አለቆቻቸውን ይጠይቃሉ። ሁለተኛዎቹ "እንዴት ላስብ?" ብለው ጌቶቻቸውን ያስፈቅዳሉ። የመጨረሻዎቹ ሁለቱንም ጥያቄዎች የሚያቀርቡት ለራሳቸው ነው። እኔ ከሁለተኛው ምድብ አካባቢ እየተንገላታሁ ነበር...

ከፕሬዚዳንቱ ጋር ያደረግሁትን የሶስት ሰአታት ቆይታ እያጠነጠንኩ ወደ ቢሮዬ ገሰገስኩ። ልቦናዬ ሁሉንም ያውቀዋል። የአንበሳው እጣ የገጠማቸው ዶክተር ነጋሶ ብቻ አልነበሩም። ጋዜጠኛውም እንጂ! አባባሌን ለማመን ለዶክተሩ ካቀረብኳቸው ጥያቄዎች ጥቂቱን ማስታወስ ብቻ በቂ ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ከብሄራዊ ተዋፅኦ አንፃር የኢህአዴግ መንግስት የስልጣን ክፍፍሉ ፍትሃዊ አለመሆኑን አያሌ ተቃዋሚዎች ይገልፃሉና ምላሽ ቢሰጡበት?” የሚል ጥያቄ ያቀረብኩላቸው የተቃዋሚዎችን ትችት እንዲያስተባብሉ ፈልጌ እንጂ ሃቁን ቢነግሩኝ ኖሮ አላትመውም ነበር።

ፕሬዚዳንቱን ስጠይቅ እየተመካከርን እንጂ በማፋጠጥ መልክም አልነበረም። ዶክተሩን በጥያቄ የማላፋጥጣቸው “እንዴት ላስብ?” ለሚለው ጥያቄ ገና ድሮ ምላሽ ስላገኘሁ ነበር። ኢህአዴግ አእምሮዬን ገርቶታል። “እንደ ኢህአዴግ ማሰብ” የሚለው መሪ ቃል የድርጅቱን አባላት እየቀጠቀጠ ይሞርዳቸዋል። “እንደ ኢህአዴግ ማሰብ” ማለት ግን “እንደ ኢህአዴግ ፕሮግራም ማሰብ” ማለት አልነበረም።

ከዶክተር ነጋሶ ጋር ባደረግሁት ቆይታ የኢህአዴግን የስልጣን ክፍፍል የተመለከተው ዋና አጀንዳችን ነበር። እኔ ጋዜጠኛ ነኝ። ዶክተሩ ፕሬዚዳንት ናቸው። ቃለ - መጠይቅ እየተካሄደ ነው። ጋዜጠኛውና ፕሬዚዳንቱ ግን “እንደ ኢህአዴግ ማሰብ” በተባለው የብረት ግርግም ውስጥ ተዘግቶባቸዋል። ኢትዮጵያ ላይ የስልጣን ክፍፍሉ ፍትሃዊ አለመሆኑን እኔና ዶክተር ነጋሶ በዝርዝር እናውቃለን። ለምሳሌ የጄኔራል ባጫ ደበሌን ዋና ስራ እንውሰድ፤ ቀዳሚ እመቤት አዜብ መስፍን ወደ ለንደንና ጅቡቲ የምትልከውን የጫት ንግድ ስራ ከማመቻቸት በቀር ሌላ ስራ እንደሌለው እኔና ዶክተር ነጋሶ አሳምረን እናውቃለን። ባጫ ደበሌ ኦሮሞን በመወከል የጄነራልነት ማእረግ እንደተሰጠው ዶክተር ነጋሶ ሲነግሩኝ፤ እኔ ስለ ባጫ ደበሌ ዝርዝር ነገር ባውቅም ያንን ግን አላነሳም። አማራን ወክለው የጄነራልነት ማእረግ ካገኙት መካከል አንዱ ደግሞ ካሳ ደሜ ይባላል። (አማራን ቢወክልም ኦሮሞ ነው) ይህ ሰው በትግሉ ወቅት በኢህአዴግ ሬድዮ ጣቢያ ግምጃ ቤት ውስጥ ይሰራ የነበረ ጥሩ ሰው ብቻ እንደሆነ እኔና ነጋሶ እናውቃለን። መለስ ዜናዊ እንደ ጃንሆይ የራሱን የሰው አንበሶች በብረት ውስጥ ቆልፎ እንደሚያሰራ እያወቅን እንዳላወቅን እንሆናለን። ዶክተር ነጋሶ ‘ፍትሃዊ’ የስልጣን ክፍፍሉን እንዲህ ሲሉ ነበር ያብራሩት፣

“...ኢትዮጵያ ዘጠኝ ጄኔራሎች አሏት። ሶስቱ ከትግራይ፣ ሶስቱ ከአማራ፣ ሶስቱ ከኦሮሞ ናቸው! በሌሎችም

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የመንግስት ስልጣን ዘርፎች የስልጣን ክፍፍሉ በተመሳሳይ ሚዛናዊና ፍትሃዊ ነው"

እኔም ይህንን እፎይታ መፅሄት ላይ አተምኩት። ሃቁ እንዲያ አለመሆኑን ጋዜጠኛውና ፕሬዚዳንቱ በልባቸው ያውቁታል። ህዝቡ ደግሞ ከሁለቱም በላይ ያውቅ ነበር።

ዶክተር ነጋሶ በዚያ የጃንሆይ ግቢ እንደ አንበሳው እስረኛ ስለመሆናቸው ብዙ ጊዜ አስብ ነበር። የራሴን እስረኛነት ግን አከራካሪ እንደሆነ በማሰብ ላለማመን እጣጣራለሁ። እኔ በግሌ 'እስረኛ ከሆንኩ ከእስር ቤት መውጣት ይኖርብኛል' የሚል ሙግት ከራሴ ጋር በመግጠሜ ሙሉ በሙሉ የማምንበትን አሳብ የያዘውን *"የቡርቃ ዝምታ"* የተባለውን መፅሃፍ ፃፍኩ። ያን መፅሃፍ የፃፍኩት በየእለቱ ተስያት ደብረዘይት ሆራ ሃይቅ ዳርቻ እየተመላለስኩ ሲሆን፤ በተወለድኩበትና ባደግሁበት ሃይቅ ዳርቻ በተቀመጥሁ ቁጥር ነፃነት ይሰማኝ ነበር። ወደ እፎይታ መፅሄት ቢሮ ስመለስ ደግሞ አንበሳውን እሆናለሁ። አቅሙን ብረት አግዶት የሚያላዝን ደካማ አንበሳ፤ ጥርሱ የዶለደመ፣ ክንዱ የደከመ፣ ብረት ውስጥ የተቆለፈበት አሻንጉሊት አንበሳ!

* * *

ጋዜጠኛነት በፍቅር የሚታበድለት አስደሳች ሙያ መሆኑ አያጠያይቅም። ከሙያው ስነ ምግባር ያፈነገጠ ስራ ይሰራ ዘንድ ከሚታዘዝ ጋዜጠኛ ግን አንደኛውን ስራ አጥነት ይሻላል። ከኢህአዴግ ጋር በቆየሁባቸው የስራ ዘመናት የተቆለፈበት ዱልዱም አንበሳ ላለመሆን በራሴ በኩል ጥረት መሞካከሬ አልቀረም።

መለስ ዜናዊ "መልስ በኪሱ" እንዳልተባለ ከኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ዋዜማ ጀምሮ ጋዜጠኞችን እንደ ጦር ይፈራ ጀምሮ ነበር። ለመለስ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በፕሮፓጋንዳው መሃንዲሶች ይነደፉና በታይፕ ተፅፈው፣ እንደ ቆሎ ተቆጥረው ይሰጡናል። ተፅፎ ከሚሰጠን ጥያቄ ውጭ መጠየቅ የማይቻል ሲሆን፤ አረፍተ ነገሮችንም ማዛባት እንደሌለብን ያስጠነቅቁን ነበር።

በጦርነቱ አዋጅ ዋዜማ መለስን ቃለመጠይቅ እንዳደርግ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ታዝዤ የነበረ ሲሆን፤ እውነት ለመናገር ግን በቃለ - መጠይቁ ወቅት ተላላኪ ነበር የሆንኩት። ጥያቄዎቹን አለምሰገድ ሰጠኝ፤ ወደ መለስ ቢሮ ሄድኩ፤ እያነበብኩ ጠየቅሁት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ ሰጠ። ያንን ወስጄ እፎይታ መፅሄት ላይ አተምኩት። በአስር አመቱ የጋዜጠኛነት ዘመኔ እንደዚያን ቀን ተሰላችቼና ስራዬን ጠልቼ አላውቅም። ችሎታ አለኝ ብሎ ለሚያምን ጋዜጠኛም ይህን መሰል ስራ መስራት ሞራልን የሚነካ ነበር።

ከጦርነቱ አዋጅ በሁዋላ ይህን መሰል ሁኔታ እየተደጋገመ ሄደ። ቀደም ሲል ይህን አይነት ድርጅታዊ "ጋዜጠኛነት" ስራ የሚሰሩት ሴኮና አታክልቲ የተባሉት ነበሩ። ከጦርነቱ ዋዜማ ጀምሮ ግን ያለምንም እፍረት ለሁላችንም ጥያቄዎች ማደል የተለመደ ሆኖ ነበር። በጦርነቱ አጋማሽ ላይ አንድ ቀን አለምሰገድ ቢሮው ጠራኝ፣

"ከሰአት ዘጠኝ ሰአት ላይ መለስን ቃለ - መጠይቅ ታደርጋላችሁ። ጥያቄዎቹም እነዚህ ናቸው። እጅህን ታወጣለህ፤ እድል ከተሰጠህ ቀጣዩን ጥያቄ ትጠይቃለህ!"

እንደዚህ ሲል ነበር ቃል በቃል ያዘዘኝ።

መለስ ቢሮ ዘጠኝ ተኩል ላይ ደረስኩ።

"ቃለ - መጠይቁ ስለተጀመረ መግባት አትችልም" ተብዬ ተከለከልኩ። ለአለምሰገድ ደወልኩና "እንዳልገባ ከለከሉኝ" ስል ነገርኩት።

"ስንት ሰአት ደረስክ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ዘጠኝ ተኩል"

"ዘጠኝ ሰአት ነው ያልኩህ"

"ዘጠኝ ተኩል ያልከኝ መስሎኝ ነበር"

አለም ሰገድ ጥቂት ፀጥ ብሎ ቆየና፣

"በዚህ ጉዳይ ላይ ሌላ ቀን እንነጋገርበታለን" ብሎ ተቆጥቶ ስልኩን ዘጋ። አለምሰገድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሃይለቃል ተናገረኝ። ከዚያ በሁዋላ አለምሰገድ መለስን በቡድን የመጠየቅ ስራ ላይ አሳትፎኝ አያውቅም። የቴሌቭዥኑ ስራ አስኪያጅ ተሾመ አስራት እንደ ገመድ የረዛዘሙ አረፍተ ነገሮችን የያዙ ጥያቄዎች እየተሰጡት፤ ጥያቄዎቹን በቃሉ ለመያዝ እየተቸገረ እንደ ተለማማጅ ጋዜጠኛ ሲደነቃቀፍ በቲቪ መስኮት እያየነው እናዝን ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከመንግስት ጋር በነበረን የቅርብ ግንኙነት እፎይታ መፅሄት የግል ሚዲያዎች የማያገኙትን ኢንፎርሜሽን የማግኘት እድሎች ነበራት። በአንፃሩ ደግሞ ጉዳቱም ከፍተኛ ነበር። ለአብነት የጄኔራል ሃየሎም ገዳይ የነበረው ሰው ከመረሸኑ በፊት በብቸኝነት ቃለ - መጠይቅ እንዳደርገው ተፈቅዶልኝ ስለነበር፤ የመፅሄታችን ሽያጭ ቁጥር ከፍ ብሎ ነበር። የአዲሳባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሆኑትን ፕሮፌሰር እንድርያስ እሸቴን ቃለ - መጠይቅ እናደርግ ዘንድ በግድ ስንታዘዝና ፎቶአቸውንም ሽፋን ላይ እንድናትም ስንገደድ ደግሞ መፅሄታችንን የሚገዛን አጥተን ለኪሳራ ተዳርገን ነበር።

* * *

የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ይካሄድ በነበረበት ወቅት አንድ ቀን አለምሰገድ የኢህአዴግ የፕሮፓጋንዳ ክፍል ባልደረቦችን ሰብስቦን ስራዎቻችንን ስንገመግም ሳለ አንድ ጥያቄ አነሳ፣

"ህዝቡ የሻእቢያን የአማርኛ የሬድዮ ፕሮግራም ያዳምጣልን?" የሚል ነበር።

ሴኮ የተባለ አንበሳ ካድሬ እጁን አውጥቶ ሰፊ ማብራሪያ ሰጠ። ኒጋሽና አታክልቲ የተባሉትም ተጨማሪ አከሉ። የሶስቱም አስተያየት ተመሳሳይ ነበር። ህዝቡ የሻእቢያን ሬድዮ እንደማያዳምጥ ተነተኑ። እኔ አስተያየት ከመስጠት ተቆጠብኩ። አለምሰገድ ግን አልተወኝም። 'አስተያየት ስጥ እንጂ?' በሚል በአገጩ ምልክት ሰጠኝ።

"የኔ አስተያየት የተለየ ነው" አልኩ።

"ቀጥል ተናገር" አለ።

ያለኝን መረጃ ጨምቄ አቀረብኩ።

"ህዝቡ የሻእቢያን የሬድዮ ፕሮግራም የሚያዳምጥ ይመስለኛል" አልኩ።

ህዝቡ የሻእቢያን ሬድዮ እንደሚያዳምጥ ጢያሳ Tea - Room አካባቢ ማለዳ ላይ ቡና ስንጠጣ ከማገኛቸው ሰዎች መገንዘቤን አብራራሁ። ህዝቡ የሻእቢያን ሬድዮ የሚያዳምጠው ሻእቢያ ስለ ወያኔ ብዙ ምስጢሮችን ያውቃል ብሎ ስለሚገምት መሆኑንም አከልኩ። በተለይ በትግራይ የሚካሄደውን የልማት ስራ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ጋር እያነፃፀሩ ስለሚያቀርቡ፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የሁመራና የጠለምት መሬቶች ከጎንደር ተቀንሶ ለትግራይ የተሰጠበትን ምክንያትም እየተነተኑ በማቅረብ ላይ ስለሆኑ አያያዛቸው አደገኛ መሆኑን ገለፅኩ። "ህዝቡ የሻእቢያን ሬድዮ አያዳምጥም" የሚለው የነ ነጋሽ መረጃ አጠራጣሪ መሆኑንም የግል አስተያየቴን አከልኩ።

ሴኮና ነጋሽ በተቃውሞ እጃቸውን አወጡ፣

አለምሰገድ እድሉን ለሴኮ ሰጠ።

"ተስፋዬ ቲ-ሩም አካባቢ አገኘሁ የሚለው ወሬ ህዝቡን አይወክልም። በመሰረቱ ቲሩም የሚሰበሰቡት ትምክህተኞችና ባለፈው ስርአት ጥቅማቸው የተነካባቸው ኢሰፓዎች ናቸው። በርግጥ ሻእቢያ ስለ ሁመራ መሬት እየቀሰቀሰ ነው። ህዝቡ ግን 'ደግ አደረገ! ምናገባህ! ቀንተህ ነው!' የሚል ምላሽ እየሰጠ ነው። ትላንት ባጋጣሚ በዚሁ ጉዳይ ከአባቴ ጋር እያወራን ነበር። አባቴ..."

አለምሰገድ አቋረጠው።

ነጋሽ 'ተጨማሪ!' ብሎ ቢጮህም እድል አልሰጠውም።

ራሱ ቀጠለ፣

"አስተያየቱ በቲ-ሩም የተገደበ ነው ወይስ ስፋት ያለው የሚለውን እዚህ አንደመድምም። ከደህንነቱ መስሪያ ቤት አካባቢም ተመሳሳይ ጥቆማ ስላለ መረጃውን ይዘነው እናልፋለን" ብሎ ወደ ሌላ አጀንዳ ተሻገረ።

በፕሮፓጋንዳው ዙሪያ የተከማቹት አንበሶች አብዛኞቹ አለቃን የሚያስደስት ነገር እየገመቱ መናገርን የለመዱ ነበሩ። ብዙውን ጊዜ ይሳካላቸዋል። በተለይም የህዝብ አመለካከት ላይ ስንወያይ እሩብ ያህል እንኳ እውነት አንነጋገርም። ሴኮ የተባለው ሰው የህወሃት አባል ቢሆንም አማራ ነው። ወደ ብአዴን እንዲገባ ተጠይቆ ባለመስማማቱ የግል ጋዜጦች "ፎርጅድ ትግሬ" የሚል የፈረስ ስም ሰጥተውታል። የህዝብ አስተያየት ስንጠየቅ ቢያንስ ሴኮ አባቱን እንደ ምንጭ ይጠቅሳል። ብዙውን ጊዜ ግን ምንጭ አይጠቀስም። አንዱ እጁን ያወጣና፣

"ህዝቡ 'ኢህአዴግ አለኝታዬ ነው' የሚል ጠንካራ እምነት አለው" ብሎ አፉን ሞልቶ ይናገራል። አለምሰገድ ይህን የመሰሉ አስተያየቶችን በደስታ ሲያስተናግድ እያስተዋልኩ አዝን ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ህዝቡ 'ኢህአዴግ አለኝታዬ ነው' ብሎ የተናገረው የት ነው? መቼ ነው? ስንት ናቸው? የሚታወቅ ነገር የለም። ሴኮ አባቱ ቤት ራት ተጋብዞ ሄዶ አባቱ የነገሩትን ይዞ "የአማራው ህዝብ" እያለ ያቀርባል። ፐርሰንቶችን እንደፈለግህ መጥራት የተፈቀደ ነበር። "ወይን" የተባለውን ጋዜጣ ያዘጋጅ የነበረው አታክልቲ በተለይ የዚህ አይነት በሽታ ነበረበት። "90% ህዝቡ ይህን ደግፎታል" ይልሃል። "10% ጥቅማቸው የተነካባቸው" ይለሃል መልሶ። በምን ዘዴ ለካኸው? ይህ ጥያቄ አይነሳም። አታክልቲ ተሳስቶ እንኳ 95% ወይም 85% ሲል ሰምቼው አላውቅም። አስር አመት ሙሉ 90 እና 10 በመቶዎችን በንንግሩ መሃል ይገለገልባቸው ነበር። ብዙውን ጊዜ ፐርሰንት እየደረደሩ ረጃጅም ዲስኩር ሲያሰሙ እንቅልፍ ይጫጫነኛል። ከመተኛት ለመዳን ማስታወሻ የምይዝ መስዬ የግል ስራዬን እሰራ ነበር።

አንዳንድ ጊዜ አለምሰገድ ክፉኛ ይናደዳል። ሲዘበራርቁ አንገታቸውን እየያዝ ያፋጥጣቸዋል። አስከፊ ቃላትን ጭምር እየተጠቀመ ያዋርዳቸዋል። በዚህ ወቅት እኔ በጣም እዝናናለሁ። አንድ ቀን ነጋሽን፣

"ቲቪ ላይ መታየት ትወዳለህ! ቲቪ አለ ካሉህ ግንባር ቀደም ነህ!" ሲለው እኔ ሳቄን መያዝ አልቻልኩም።

አለምሰገድ እውነቱን ነበር። ነጋሽ ልክ እንደ ጃንሆይ አንበሳ አለምንም ምክንያት ቲቪ ላይ ብቅ ይላል። በሁለት ተከታታይ ዜናዎች ላይ፣ በአንድ ቀን በተፈፀሙ ድርጊቶች ላይ፣ እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ምስጢሩን ለመረዳት አስቸጋሪ ነበር። በምረቃ፣ በኮንፈረንስ፣ በግብዣዎች ላይ ፈገግ ፈገግ እያለ ከፊት ይታያል...

አብዛኞቹ የፕሮፓጋንዳው አንበሳ ካድሬዎች የችሎታ ማነስ በሚፈጥረው ፍርሃት የሚሰቃዩ ነበሩ። ችሎታ እንደሚያጥራቸው ማመን አለመፈለጋቸው ደግሞ ስቃያቸውን እያባባሰ ቁጡና ክፉ ይሆኑ ዘንድ ይገፋፋቸዋል። ይበልጡናል ብለው በሚያስቧቸው የበታች ሰራተኞቻቸው ላይም በጥላቻ ይዘምቱባቸዋል።

አንበሶቹ ካዳበሩዋቸው አስገራሚ ልማዶች መካከል አለምሰገድ የተጠቀመባቸውን ሃሳብ የያዙ ቃላት መጠቀምና የሱን ንግግሮች አስረዝሞ መድገምን ነበር። አለምሰገድ በየሶስት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ወሩ እንደ ሁኔታው ይሰበስበናል። ነጋሽና አታክልቲ ደግሞ በየወሩ ይጎልቱናል። በዚህ ሂደት የአለምሰገድ ቃላት እንደ ገብስ ይፈተጋሉ። Political Hegemony ያለ እንደሆን ሳምንቱን ያቺ ቃል ትጠናለች። Developmental state የሚል አዲስ ቃል ብቅ ካለ፣ በዚያን ሰሞን ሌላ ወሬ የለም። ግልብ እውቀት ይዘህ እንደ ዶቅዶቂ መንዶቅዶቅ ነው። ቃላት ይለቀማሉ። አስረዝሞ የመድገም ልማድ በተለይ ከየት የተወረሰ እንደሆነ ልደርስበት አልቻልኩም። አሳጥሮ መድገም እንጂ አስረዝሞ የመድገምን ጥቅምና ምክንያቱን ሳልገነዘበው ቀርቻለሁ። የሙሉጌታ ሉሌን፣ "አጥፍቶ መጥፋት" ትረካ ከኔው ገጠመኞች ጋር እያዋሃድኩ፣ አንዳንድ ጊዜ፣ "ለመሆኑ እንደ ኢትዮጵያ የልጆች መጫወቻ የሆነች ሃገር በአለም ላይ ትኖር ይሆን?" እያልኩ አስብ ነበር። ስምንት የአፍሪቃ አገሮችን ከጎበኘሁ በሁዋላ ግን አፍሪቃ ሽበት በወረራቸው ልጆች መዳፍ ላይ የወደቀች አሳዛኝ አህጉር መሆንዋን ልረዳ ቻልኩ። በርግጥ በሌሎች አፍሪቃ አገሮች ባለስልጣናት የገዛ አገራቸውን የማውደም ተግባር ላይ የሚሰማሩት በጥቅም እየተደለሉ እንጂ በእውቀት ማነስ አልነበረም። የእኛ ግን ባለመታደል አብዛኞቹ ባለስልጣኖቻችን የሁለቱም ችግሮች ሰለባ የሆኑ ናቸው።

* * *

አንድ ጊዜ የፕሮፓጋንዳው ካድሬዎች ኢህአዴግ ፅህፈት ቤት ለስብሰባ ተጠርተን ሳለ ሙሉጌታ ሉሌን የተመለከተ አንድ ወግ ተነሳ። ሰብሳቢያችን እስኪመጣ እየተጨዋወትን ነበርና ብርሃኑ አባዲ የተባለው የቴሌቪዥን የትግርኛው ፕሮግራም ሃላፊ፣

"'አጥፍቶ መጥፋት' የተባለውን መፅሃፍ አንብባችሁዋል?" ሲል በስሜት ጠየቀ። የተጠቀሰው መፅሃፍ ከታተመ አንድ አመት አልፎት ነበር። ብርሃኑ አያይዞ ያብራራ ቀጠለ፣ "...ሌሊቱን አንብቤ ጨረስኩት። የደርግን ስርአት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ አስተማሪ መፅሃፍ ነው። ደራሲው ያነበበ ሰው መሆን አለበት። ከጀመርኩት በሁዋላ ቁጭ ላደርገው አልቻልኩም!"

የብርሃኑን ስሜታዊ አድናቆት የሚያቀዘቅዙ አስተያየቶች የጎረፉት ወዲያው ነበር። ነጋሽ ተክሉ፣ ሴኮ፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተክላይና አታክልቲ ያለቅደም ተከተል የማጥላላት የመትረየስ እሩምታ አዘነሙ፣

"ሙሉጌታ ሉሌ ነው የፃፈው..."

"የኢሰፓ አባል ነበር..."

"ለገንዘብ ሲል ነው የፃፈው..."

"የት ነበረ በፊት? ቀንደኛ የደርግ ሹም!"

"ለመንግስቱ ሲሰግድ የነበረ!"

ተክላይ ተክሉ ወደ እኔ እየተመለከተ ተናገረ፣

"ምነው ዝም አልክ? አንተ የበለጠ ታውቀው የለም እንዴ?"

በርግጥም እዚያ ስብሰባ ላይ ከነበርነው ሁሉ ይበልጥ ሙሉጌታን የማውቀው እኔ ነበርኩ። የማውቀው ግን የሚፅፋቸውን ስለምከታተል እንጂ፣ ወንበሩን ስለወረስኩ አልነበረም። የሆነው ሆኖ ለተክላይ ጉንተላ በጥያቄ መልክ አስተያየት ሰጠሁ፣

"...ብርሃኑ አባዲ የጠየቃችሁ ጥያቄ 'አጥፍቶ መጥፋት' የተባለውን መፅሃፍ አንብባችሁዋል ወይ? የሚል ነው። ለዚህ መልስ ስጡንና ከዚያ ስለ ሙሉጌታ አመለካከት መከራከር ይቻላል" አልኩ።

አራቱም መፅሃፉን እንዳላነበቡት ገለፁ።

"ካላነበባችሁት ምንም መነጋገር አይቻልም" ከማለቴ አለቃችን አለምሰገድ ወደ አዳራሹ በመግባቱ ጨዋታችን ተቋረጠ።

በርግጥም የፕሮፓጋንዳው አብዛኞቹ ካድሬዎች የመፅሃፍ ወዳጆች አልነበሩም። የስማ በለው ወሬ ይዘው መፅሃፍን ያክል ነገር ላይ በድፍረት አስተያየት ይሰጣሉ። ዜና ሲፅፉም ሆነ ሲናገሩ ቅፅል ማጅነድነድ ዋና የመለያ ጠባያቸው ነበር። ጨካኙ፣ ፋሺስቱ፣ አረመኔው፣ ሰው በላው ደርግ! ወላዋዩ፣ ፈርጣጩ፣ ተላላኪው፣ ተደራዳሪው ኢህአፓ! ቀንደኛው ፣ኢሰፓው፣ ለደርግ የሰገደው እገሌ! ቅፅሎቹ እንደ እሩምታ ተኩስ የሚንጣጡ አይነት ናቸው። ሰውየውን ባያውቁትም ቅፅል ለመለጠፍ በፍፁም አይሰንፉም። 'አጥፍቶ መጥፋት' የተባለውን መፅሃፍ ለማንበብ ቁራጭ ትእግስት ቢኖራቸው ኖሮ፣ ቢያንስ ያ መፅሃፍ አፍቃሬ ኢሰፓ ወይም ደርግ በሆነ ሰው ሊፃፍ እንደማይችል መገምገም በቻሉ ነበር። መቼም ፖስታ ቤት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ቴምብር የመሸጥ ስራ የሚሰራ ሰው ማንበብ የስራ ግዴታው ላይሆን ይችላል። የማያነብ ሰው የፕሮፓጋንዳው ክፍል ላይ ቁልፍ ቦታ ሲይዝ ምንድነው የሚከተለው? ኢህአዴግ አባላቶቹን ከማንበብ ይልቅ ስብሰባ ላይ ተጎልቶ በትእግስት ማዳመጥን እንዲካኑ አድርጎአቸዋል። በሽምዳጅ ባለሙያዎች በተከበበ ቁጥርም አመራሩ የስልጣን ዋስትናውን ያረጋግጣል። የማያነቡ ሰዎች ግራና ቀኝ ማየት ስለሚሳናቸው ጥያቄ አያነሱም። ይህም የስርአቱ ጭፍን ደጋፊ ሆነው እስከዘልአለሙ እንዲጎለቱ ያደርጋቸዋል።

* * *

"*የቡርቃ ዝምታ*" ታትሞ እንደወጣ ለዶክተር ነጋሶ አንድ ኮፒ ልኬላቸው ነበር። በሳምንት ጊዜ ውስጥ አንብበው ጨረሱት። በዚያው ሰሞን በስልክ ተገናኝተን ስናወጋ ታዲያ "አንብቤዋለሁ! በስልክ ከሚሆን ግን ሲመችህ ደውልና ቢሮ ብቅ በል" አሉኝ። ፕሬዚዳንቱ ስልካቸው ስለሚጠለፍ በስልክ ምንም ምስጢር ነክ ወሬ እንደማያወሩ አውቅ ነበር።

በዚያን ሰሞን ደረጀና ሃብቴ ለህዝብ ያልቀረበ ነጠላ ቀልድ በየድራፍት ቤቱ አሰራጭተው ነበር። በዚያን ሰሞን በቤተመንግስቱ ዙሪያ ፍሎረሰንት መብራቶች ተተክለው ነበር፤ የነጋሶ ግቢ ግድግዳዎች በሙሉ በኤሌክትሪክ ብርሃን ማሸብረቃቸውን መነሻ በማድረግ ደረጀና ሃብቴ እንዲህ ሲሉ ሲያስቁን ሰነበቱ።

"በቤተ መንግስቱ ዙሪያ የተተከለውን መብራት አይታችሁታል?"

"አይተነዋል!"

"ለምን እንደተተከለ አውቃችሁዋል?"

"አላወቅንም፤ ለምንድን ነው?"

"የሃየሎም ገዳይ የጀሚል ያሲንን የሞት ውሳኔ የሚያፀድቀውን ሰነድ እንዲፈርም ለነጋሶ ቀርቦለት 'የፊርማው ቦታ አይታየኝም' ብሎ ስላስቸገረ ቤተመንግስቱ ዙሪያ መብራት ገባለት፤ ከዚያም 'አሁን ታየኝ!' ብሎ ፈረመ!"

ጀሚል የተረሸነበትና መብራቱ የተተከለበት ጊዜ ተመሳሳይ በመሆኑ ኮሜድያኑ እንደተለመደው በውስጥ ለውስጥ ቀልዶቻቸው ሲያዝናኑን ሰነበቱ፤

"ነጋሶ ለምን መፈረም አልፈለገም?" ስል ጠየቅሁ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ጄንጤ ነዋ!"

ነጋሶ ላይ ቀልዶች በርትተው ነበር፤ "ነጋሲ ግደይ" የሚል ቅፅል ስም የተሰጣቸው ሲሆን፤ የቦሌ ቢጫ ታክሲዎች ደግሞ "ነጋሶ" ተብለው ይጠሩ ነበር፤ ነጋሶን "ስራህ እንግዳ መቀበል ብቻ ነው" ለማለት ነበር። ልእልት ዲያና በመኪና አደጋ ስትገደል ነጋሶ ውጭ ሃገር የመሄጃ እድል ስላገኘ "ብራቮ ወንዳታ!" ብሎ ከአልጋ ተስፈንጥሮ ሲነሳና ለቀብር ሲጓዝ የሚያሳዩና የመሳሰሉ ካርቱኖች ሲታተሙ ስመለከት ከልብ ይሰማኝ ነበር። ዶክተር ነጋሶ ሁሉንም የሚገነዘቡ ቅንና ለሃገራቱም በጎ የሚያስቡ የበሰሉ ምሁር ናቸው ብዬ ከልብ አምን ስለነበር በዚህ ሁኔታ ሲቀለድባቸው ሃዘን ይሰማኝ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ 'ዶክተሩ ህሊናቸውን ጭምር እንዲታሰር ያደረጉት በፈቃዳቸው ነው' በሚል አዝንባቸው ነበር። ሌላው ቀርቶ ለቃለመጠይቁ ደውዬ ስጠይቃቸው አለምሰገድን እንዳስፈቅድ ነበር የነገሩኝ። በወቅቱ የፕሮፓጋንዳ ሃላፊ ለነበረው ለአለምሰገድ ገብረአምላክ ደውዬ ነጋሶ የነገሩኝን ስነግረው "ይቻላል!" ሲል ፈቀደ። ከነጋሶ በላይ ያስደነቀኝ ታዲያ አለምሰገድ የነጋሶ ጥያቄ ተገቢ ነው ብሎ አምኖ "ይቻላል" "አይቻልም" እያለ ሲፈቅድ ነበር። የድርጅቱን የስልጣን ተዋረድ ስናይ ነጋሶ የአለምሰገድ የበላይ እንጂ የበታች አልነበረም። ልዩነቱ ግን አለምሰገድ ህወሃት ነበር። ነጋሶ ደግሞ የኛ ዘመን ፈቃደኛ እስረኛ አንበሳ።

የአህዴድ ካድሬዎች ነጋሶ ላይ ተቃውሞ እንዳሰበሩም እንገነዘብ ነበር። ለዚህ ተቃውሞ የበቁትም ነጋሶ በአንድ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ነው። የኦሮሚያ ክልል የተፈጥሮ ሃብቱን በአግባቡ አለመጠቀሙ፤ ከሌሎች ክልሎች የሚመጡ ኢንቨስተሮችንም አላሰራም ስለ ማለቱ በሚወሰበት ግምገማ ላይ ዶክተር ነጋሶ "ታሪካዊ ንግግር" አደረጉ ተብሎላቸው ነበር። ይህም "...አውራ ዶሮ ጭንቅላቱ ላይ ስጋ ተሸክሞአል፤ ወይ አይበላው ወይ አያስበላው!" የሚል ነበር። በዚህ የነጋሶ ንግግር የህወሃት ካድሬዎች በነጋሶ ላይ ከፍተኛ አድናቆት ሲያሳድሩ 'ፈጣን ሎተሪ' የሚል ቅፅል ስም የያዙ በአነግነት የሚጠረጠሩ የአህዴድ አባላት ግን አንጀታቸው ማረሩን ሲገልፁ ሰንብተው እንደነበር ትዝ ይለኛል። በርግጥ ነጋሶ ያን የተናገሩት ከኢትዮጵያዊነት ስሜት ተነስተው ቢሆን ባልከፋ፤ ብዙዎች

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የተገነዘቡት ግን ህወሃት በኦሮሚያ ውስጥ የሚያካሂደውን አድሎአዊ እንቅስቃሴ እንደሚያበረታታ ንግግር ነበር። ትግራይ ውስጥ አንድም የሌላ ብሄር ኢትዮጵያዊ ነጋዴ እንዲሰራ ሳይፈቀድለት፤ የህወሃት ሰዎች በሌሎች ክልሎች በተለይ በኦሮሚያ ክልል ዋና ዋና ነጋዴዎች የመሆናቸውን ኢፍትሃዊ አሰራር የኦህዴድ ካድሬዎች በቁጭት ይቃወሙት ነበር።

* * *

በ1989 የኦህዴድ የማእከላዊ ኮሚቴ የአመራር ግምገማውን ባካሄደበት ጊዜ፣ የተከሰተ አንድ ሁኔታ በተለይ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል የነበረውን የጌታና የሎሌ ግንኙነት የሚያሳይ አስረጅ ነበር።

ግምገማው የተካሄደው ከዶክተር ነጋሶ ቢሮ ብሄራዊ ቤተመንግስት ነበር። የኦህዴድን ግምገማ የመሩት ተወልደ፣ አለምሰገድና በረከት ነበሩ። ኦህዴድ ራሱን ችሎ ችግሮቹን ፈትቶ አያውቅምና ግምገማው በነ አለምሰገድ መካሄዱ የሚደንቅ አልነበረም።

በዚህ የኦህዴድ የአመራር ግምገማ ላይ ከተሳተፉት የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል አለማየሁ ደሳለኝ አንዱ ነበር። አለማየሁ የህወሃትን ጣልቃ ገብነቶች ይቃወም እንደነበር ከግምገማው በፊት ሰምቻለሁ። ለኦሮሞ ህዝብ ጠባባዊ ወገናዊነት ያሳያል፣ የኦነግን አመለካከት ያራምዳል እየተባለ ይታማ ነበር። ረጅም ጊዜ በወሰደው በዚያ ግምገማ ማጠቃለያ እነ አለምሰገድ በጠባብነት ሽፋን አዋራጅ ቃላትን በመጠቀም በሰነዘሩበት ሂስ አለማየሁ ሞራሉ ክፉኛ በመነካቱ እዚያው ቤተመንግስት ግቢ መኪናው ውስጥ ራሱን በሽጉጥ በመግደል ተቃውሞውን ገለፀ።

የአለማየሁን አስከሬን በቅድሚያ የተረከቡት የደህንነቱ ባልደረቦች ነበሩ። ከኮቱ ኪስ ውስጥም ለነ አለምሰገድ የተፃፈ አንድ ገፅ ደብዳቤ መገኘቱን ከአንድ የደህንነት ባልደረባ መረጃውን አጊንቼያለሁ። አለማየሁ ለሶስቱ የግምገማው መሪዎች የፃፈውን ደብዳቤ ስላላነበብኩት ቃል በቃል ለማስፈር እቸገራለሁ። ይዘቱን ግን ሰምቻለሁ።

አለማየሁ በፃፈው ደብዳቤ የግምገማው መሪዎች በግለሰብ ደረጃ እንዳዋረዱትና ክብሩን እንደነኩት ፅፎአል። ከሱ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ውርደት በላይ የኦሮሞ ህዝብ ጭምር እየተዋረደ እንደሆነ መረዳቱን፣ የኦሮሞን ህዝብ በሚያዋርደው በዚያ ግምገማ በመሳተፉ መፀፀቱንም ጠቅሶአል። ውርደቱን ተሸክሞ ከመኖር መሞትን እንደመረጠ፣ መሞቱ ካልቀረ ደግሞ ሶስቱንም የግምገማው መሪዎች ገድሎ ራሱን ማጥፋት ይችል እንደነበር፣ ያን ያላደረገው ከሶስቱ አምባገነኖች የከፉ አለቆቻቸው መኖራቸውን ስለሚያውቅ መሆኑን ጠቅሶአል። "መግደል መፍትሄ በመሆኑ ራሴን ገድያለሁ" ሲልም ቃል በቃል ፅፎአል። እንደ አህያ ሸክምን ለትውልድ ላለማውረስ መወሰኑን፣ የኦህዴድ አባል ለመሆን ወስኖ የነበረው ለውጥ አመጣለሁ በሚል ተስፋ እንደነበር፣ በደብዳቤው ጠቅሶአል። በመደምደሚያው ላይም የኦሮሞ ህዝብ እንደሚያስቡት ሸክምን የሚወርስ አለመሆንኑንና ለማንም የማይበጀው ክፉ የበቀል ቀን ከመወለዱ በፊት ከተኙበት ይነቁ ዘንድ እንደሚመኝ በማስፈር ደብዳቤውን ቋጭቶአል።

ይህን ደብዳቤ መለስ ዜናዊ፣ በረከት፣ አለምሰገድና ተወልደ እንዳነበቡትም ሰምቻለሁ። ዶክተር ነጋሶና ቀሪው የኦህዴድ ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ግን ስለ ደብዳቤው እንዳያውቁ ተደርጎአል። አለማየሁ የተጫነበትን ውርደት መሸከም ስላልቻለና ለልጆቹም ማውረስ ስላልፈለገ ራሱን ገደለ። በእስረኛነት መቀጠል ያልቻሉም አንድ ባንድ ኮብልለዋል። ሸክሙን የቻሉት በግርግሙ መቆየትን መርጠዋል...

* * *

ዶክተር ነጋሶ በመጨረሻ የተዘጋባቸውን የብረት በር ሰብረው መውጣት ችለው ነበር። ከመለስ ጋር ፊትለፊት ለመላተም የሚያበቃ ድፍረት ማግኘታቸው ተነገረ። ነጋሶ መለስን "አሁንስ መንግስቱ ሃይለማርያምን መሰልከኝ" ሲሉ ተናግረው ስብሰባ ረግጠው የመውጣታቸው ዜና ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ከታተመ በሁዋላ ነጋሶ ስማቸውን ማደስ ጀመሩ። የነጋሶ ስም መታደስ መጀመሩን ስሰማ ደስ ብሎኝ ነበር። ደስታዬ ግን ብዙም ሳይቆይ ውሃ ጠጣ። ነጋሶ በምርጫ 97 ደምቢዶሎ ላይ ተወዳድረው በማሸነፍ ፓርላማ ገብተው እንደተለመደው የወያኔ ማዳመቂያ ሆኑ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የኦሮሞ ህዝብ ታጋይ የሆነችው አስሊ ኦሮሞ በ1998 የሞት ፍርድ ሲፈረድባት ነጋሶ ድምፃቸውን አላሰሙም። አስሊ በ1979 ወደ ሃርጌሳ ከተሰደደች ጀምሮ ከደርግና ከወያኔ ጋር ስትፋለም የኖረች ድንቅ ተዋጊ ታጋይ ናት።

የፖለቲካ መሪዎች "አስሊ ኦሮሞ መገደል የለባትም!" "አስሊ ነፃ ልትወጣ ይገባል!" ብለው በመጮህ ህዝብን ካላነቃነቁ የህዝብ ድምፅ ወኪልነታቸው ታዲያ ምኑ ላይ ነው? ወያኔ ፕሮፌሰር አስራትን እንደፈለገው አንገላቶ ገደላቸው። በዚያን ጊዜ ኦሮሞዎች አይመለከተንም ብለው ዳር ቆመው ይመለከቱ ነበር። አስሊ ኦሮሞ ሞት ሲፈረደባት ደግሞ ጉዳዩ ለኦሮሞዎች ተጥሎአል። በዚህ መሃል ተጠቃሚው ወያኔ ብቻ ሆኖአል። አስሊ ኦሮሞ ማናት? ለምንና እንዴት ታሰረች? ወያኔ አስሊ ላይ ሞት ለመፍረድ ለምን ተጣደፈ? ገና ያልተጠየቁ ጥያቄዎች ናቸው።

* * *

ዶክተር ነጋሶና የቀድሞው የኦነግ ምክትል ሊቀመንበር ኦቦ ሌንጮ ለታ ዝምድና አላቸው። በዘመነ ደርግ በወጣትነታቸው አዲስ አበባ ላይ ወጣቱ ነጋሶ ሌንጮን ያገኘውና፤

"የታሪክ ትምህርት ለማጥናት ወደ ጀርመን መሄዴ ነው" ሲል ይነግረዋል።

ሌንጮ እንዲህ ሲል ምላሽ ሰጠ፤

"አንተ ሂድና ታሪክ ተማር! እኛ ደግሞ ታሪክ ሰርተን እንጠብቅሃለን!"

ዛሬ ላይ ቆሜ ስታዘብ የተከበሩት ነጋሶ ታሪክ ቢማሩም የታሪክ ስህተቶችን ደጋግመው ሲሰሩ ስንመለከት የተማሩትን ታሪክ እንጠራጠረዋለን። እንዲያውም የጃንሆይ አንበሳ ተገዶ የታሰረ በመሆኑ ቢያንስ ችግሩን እንገነዘብለታለን...

* * *

ድረገፆችን ስከፍት አልፎ አልፎ ስለተከበሩት ነጋሶ ወሬ እሰማለሁ። በቅርቡ ነጋሶን የተመለከተ አንድ ቆንጆ ቀልድ አንብቤ ነበር፤ ነጋሶ እንደኔ ፈቃደኛ እስረኛ በነበሩበት ወቅት መረራ ጉዲናን ያስጠሩትና፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“የፖለቲካ አቋምህ ምንድነው?” ሲሉ ይጠይቁታል።
መረራ ሳያመነታ ምላሽ ይሰጣቸዋል፣
“እንዳንተው ኦነግ ነኝ!”
ነጋሶ ዛሬም ድረስ ገና ቀልዱን ያጣጣሙት አይመስለኝም። ስለ ዶክተር ነጋሶ ባሰብሁ ቁጥርም የኛ ዘመን አንበሶች ሁሉ ይታወሱኛል። እናም ያወጋነው የመጨረሻ ወግ፣
“ምን ሆኖ ነው አንበሳው የሚጮኸው?”
“ሚስቱንና እናቱን ባንድ ቀን አጣ”
“በምን ሞተችበት ሚስቱ?”
“በወሊድ”
“ለመሆኑ ምን ትመግቡታላችሁ?”
“በቀን አምስት ኪሎ ስጋ!”

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 12 -
የቁንድዶ ፊረሶች

ፍጡር ለመጨፍጨፍ - እድል መልምሎአቸው፣
ሰብአዊ ርህራሄ - ፍፁም የሌላቸው፣
ማስገደጃ ጅራፍ - ጨብጠው በእጃቸው፣
የአርሶአደሩን ጉልበት - ጊዜውን ልፋቱን፣
... አርገው ለግላቸው፤

(ግጥም- አሌክሳንደር ፑሽኪን)
ኢያልነህ ሙላቱ እንደተረጎመው

እንደ ብረት የጠነከረ ክንድ ባለው የኤጀርሳ ጎሮ ገበሬ ድጋፍና በሶስት የሃረሪ ክልል ፖሊሶች አጃቢነት ፈታኙን አቀበት የተያያዝኩት ገና በማለዳው ነበር። የቁን ድዶ ተራራ እንደ ግድግዳ ተገትሮ ሰማዩን ታኮታል። ሳር ሸሽቶት አሸዋማ መሬቱ የተጋለጠ የተራራው ወገብ ሲገጥመኝ ወደ ሁዋላ መንሸራተቴ አልቀረም። የገበሬው ድጋፍ አስተማማኝ ቢሆንም፤ በተንሸራተትሁ ቁጥር እንደናዳ ከመንከባለል ለመዳን የዛፍና የቁጥቋጦ ቅርንጫፎችን በደመ ነፍስ እያነቅሁ ቁና ቁና እተነፍሳለሁ። ሃኪም ጋራ ላይ ሆኜ በርቀት ስመለከተው የጢስ ጉም መስሎ የታየኝ ቁንድዶ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እነሆ በሳርና በቁጥቋጦ የተሸፈነ፣ የዛፍ እጥረትም የሌለበት ሆኖ አገኘሁት።

ላቤ በማጅር ግንዴ ቢንቆረቆርም እንደምንም ትንፋሽ እየመለስሁ ለሃያ ደቂቃ ያህል አቀበቱን እንደወጣን የፖሊስ ቡድኑ ሃላፊ መቶ አለቃ ሃሚድ እረፍት እናደርግ ዘንድ ጠየቀኝ።

ተስማማሁ።

በርግጥም ልቤን ልተፋት ምንም አልቀረኝም ነበር። ጎልማሳው ገበሬ ገና ከእንቅልፉ የተነሳ ያህል ድካም ባጠገቡም ዝር አላለ። ፖሊሶቹ ግን የኔን ያህል ባይሆንም ቁና ቁና ከመተንፈስ አላመለጡም። ያነገቱት ጠመንጃ ክብደትም ለተጨማሪ ድካም ዳርጎአቸው ይሆናል።

"በዚህ አያያዝ ከተራራው አናት የምትደርስ ይመስልሃል?" ሲል ጠየቀኝ የመቶ አለቃው።

"እምቢ ባዮቹን የግድ ማየት አለብኝ" ስል በቁርጠኝነት መለስሁ።

ፈገግ አለ ሃሚድ።

ገበሬው ካነገተው ሻንጣ ውሃ የያዘ የፕላስቲክ ኮዳ አውጥቼ አናቴ ላይ ሳንቆረቁረው ድካሜ በግማሹ ለቀቀኝ። ውሃው ላቦቴን እያጠበ ደረቴን አለበሰው። ስሜቴን ስለወደድኩት ከአናቴ የሚወርደው ውሃ በጆርባዬ ጭምር ያረሰርሰኝ ዘንድ አጥለቀለቅሁት። በዚህ መንገድ ፋታ ወስጄ ሳበቃ የሚቀረንን የአቀበት መንገድ ለመገመት ቀና ብዬ ቁንድዶን አጤንሁት። ገና የተነካም አይመስል።

በሃረርጌ ምድር ጉርሱምና ኤጀርሳ ጎሮን ግራና ቀኝ እንደ ክንፍ ዘርግቶ መሃሉ ላይ ጉብ ያለው የቁንድዶ ተራራ ለአካባቢው የመሬት ንጉስ ነበር። ሁሉን ቁልቁል ያያል። ቁንድዶ ከሌሎች የአፍሪቃ ቀንድ ተራሮች የሚለይበት አፈጣጠሩ አናቱ እንደ ቦሩ ሜዳ ለጥ ያለ፣ "ለፈረስ ግልቢያ የሰጠ" የሚሉት አይነት መሆኑን ሰምቼ ያለሁ። እና እዚያ የሰማይ ጥግ ላይ ፈረሶች አሉ። ከሰው ልጆች ሞገዚትነት ራሳቸውን ያላቀቁ ነፃ ፈረሶች።

የቁንድዶ ፈረሶችን የአመፅ ታሪክ በማስተዋል ያዳመጠ በእጅጉ አስደማሚና ጥልቅ ይዘት ያለው መሆኑን ይገነዘባል።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

* * *

ታሪኩ ከሃምሳ አምስት አመታት በፊት እንደተከሰተ ይነገራል። በቁንድዶ ተራራ አካባቢ የሚኖሩ ገበሬዎች በእርሻና በእንስሳት እርባታ የሚተዳደሩ ናቸው። በእንስሳት እርባታው ፈረሶችን ማርባት ጭምር ይካተታል። ገበሬዎቹ የጋማ ከብቶችን ለብቻ በአንድ በረት፤ የቀንድ ከብቶችንም እንዲሁ በሌላ በረት በመቆለፍ ያሳድሩዋቸው ነበር። በዚህ የአኗኗር ዘዴ ሳቡ በመካከሉ ፈረሶቹ ያልተለመደ ችግር መፍጠር አመጡ። ማለዳ ለግጦሽ ከበረት ሲለቀቁ ጥጆችን የመንከስ አዲስ ልማድ ተጠናወታቸው። ውሃ ሲጠጡና ጨሌ ሲግጡ ተቀላቅለው እንደመሆኑ በየጊዜው በፈረሶች የሚነከሱ ጥጆች ለሞት ይበቁ ጀመር። ይህ ችግር በአንድ የገበሬ ቤተ ሰብ ብቻ ያጋጠመ አልነበረም። የወል ችግር ሆነ። አልፎ ተርፎ ያንዱ ፈረስ የሌላውን ጥጃ እየነከሰ ተከባብረው የኖሩ ጎረቤቶችን ያጋጭ ጀመር። ቀስ በቀስ ችግሩ እየጨመረ በመሄዱ የአካባቢው ሽማግሌች ለምክር ተቀመጡ። ችግሩን አወጡ አወረዱ። መፍትሄም አፈላለጉ። በማብቂያውም ሁነኛ መላ ተገኘ።

የአካባቢው ገበሬዎች ለፈረሶቻቸው የቀን ውሎና የሌሊት አዳር ቁንድዶ ተራራ ይሆን ዘንድ ወሰኑ። ፈረስ በጅብ አይደፈርም። ቁንድዶ ላይ አንበሶች ባለመኖራቸውም ፈረሶቹ ቁንድዶ ማደራቸው አስጊ አልነበረም። ተራራው ላይ ኩሬ በመኖሩ የውሃ ችግር አላሳሰበም። የቁንድዶ ተራራ የግጦሽ መስክ ከሺህ በላይ ፈረስ መቀለብ ይቻለዋልና የመኖ ነገርም አላነጋገረም። ፀሃይ ሲበረታ ማረፊያ ጥላም ሞልቶአቸዋል። ቁንድዶ በዝግባ ዛፎች የተሞላ ነበር። ጥቂት ያወያየው የአካባቢው ፈረሶች በአንድ ላይ ተቀላቅለው ሲኖሩ የባለቤትነት ነገር እንዳያጨቃጭቅ ነበር። ለዚህ መፍትሄ ተበጀለት። እያንዳንዱ ገበሬ በራሱ ፈረስ ላይ ልዩ ምልክት እንዲያደርግ ተደረገ። የሌባ ነገር በአካባቢው አስጊ ባይሆንም ለምናልባቱ በየእለቱ ማቲዎች ወደ ተራራው እየወጡ እንዲያዩዋቸው መከሩ። ከዚህ በሁዋላ ሁሉም ገበሬ የየራሱ ፈረስ ላይ ልዩ ምልክት አበጀ። ምልክት ማድረጉ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አላስቸገረም። ጆሮዎቻቸውን በመብሳት፣ በመተልተል፣ አንገታቸው ላይ ጠፍር በመጎንጎን፣ ጋማና ጭራ በመከርከም፣ በልዩ ቀለማቸው፣ እንዲያ እንዲያ እያሉ እማኝ እያስቆጠሩ፣ ሁሉም ፈረሶቻቸውን ቁንድዶ እያደረሱ ለቀቋቸው። ፈረስ ገዢ ሲመጣ የሚፈለገውን ፈረስ ከቁንድዶ ለይቶ በማምጣት መሸጥ እንደሚቻል ነበር ገበሬዎቹ ያመኑት። በመጀመሪያዎቹ ወራት በርግጥም እንደታሰበው ተፈፅሞአል። ሁለት ሶስት ፈረሶች ከቁንድዶ እንዲወርዱ ተደርገው ለድሬዳዋ ባለጋሪዎች ተሸጠዋል።

ፈረሶቹ የቁንድዶን ግዛት በመኖሪያነት በተረከቡ በስድስተኛው ወር ግን አንድ ያልታሰበ አስደንጋጭ ወሬ ከገበሬዎቹ ዘንድ ደረሰ። እንደተለመደው በአንድ ሰንበት ማለዳ ማቲዎች ፈረሶቹን ለማየት ቁንድዶ ይወጣሉ። ፈረሶቹ እዚያው መዋለዳቸውን ቀጥለው ነበርና ማቲዎቹ ግልገል ፈረሶቹን ለመጋለብ ይመኙና ይሞክራሉ። አንዱ ማቲ ያንዱን ግልገል ጋማ ይዞ ለመፈናጠጥ ሲሞክር እናትየው እየጋለበች ደርሳ ማጅራቱን በጥርስዋ ያዘችው። አልለቀቀችውም። ቀረጠፈችው። ባልገመቱት ሁኔታና ፍጥነት የጓደኛቸው ህይወት ማለፉን የተገነዘቡት እረኞች ኡኡታቸውን እያቀለጡ ከመንደራቸው ደረሱ።

ይህ ዜና ለገበሬዎቹ አሳዛኝና አስደንጋጭ ከመሆን አልፎ፤ የፈረሶቹ የንክሻ ልማድ ከጥጆች ወደ ሰው ልጆች የማደጉ ነገር ያሳሰባቸው አልታጡም ነበር። የሆነው ሆኖ ጉዳዩ እንደ ተራ አጋጣሚ ብቻ ነበር የተቆጠረው። ይህ በሆነ በሳምንቱ ግን ከእረኛው ሞት በላይ የገበሬዎቹን ትኩረት የሳበ ሁኔታ ተከሰተ። አንድ ግሪካዊ ወደ መንደሪቷ ብቅ ይልና ግልገል ፈረስ ለመግዛት እንደሚፈልግ ገለፀ። ግሪካዊው ጠቀም ያለ ገንዘብ ሊከፍል እንደሚችል የተገነዘቡት ግልገል ፈረስ ያላቸው ገበሬዎች፤ የግሪካዊው ምርጫ ያርፍባቸው ዘንድ እየተመኙ ማቲዎቻቸውን በፍጥነት ወደ ተራራው አናት ላኩ። ይሁን እንጂ ከአንድ ሰአት በሁዋላ እረኞቹ ባዶ እጃቸውን ነበር የተመለሱት።

"የታሉ ፈረሶቹ?" የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው። ምላሻቸው ተመሳሳይ ነበር።

"ትልልቆቹ ፈረሶች አናስጠጋም አሉን። ይናከሳሉ"

ግሪካዊው ፈረሱ ለበጎጋታው እንዲዘጋጅለት ነግሮ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ገና ከመመለሱ፤ ድፍን የዚያች መንደር አባወራዎች ገመድ አንጠልጥለው፣ ማቲዎቻቸውን አስከትለው፣ በዳገቱ ሳይሆን በንዴት ቁና ቁና እየተነፈሱ ወደ ቁንድዶ አናት መገስገስ ጀምረው ነበር።

አብዛኞቹ የየራሳቸውን ፈረሶች መርጠው ወደ ቀድሞው በረት ሊመልሱአቸው ወስነው ነበር። ፈረሶቹ ሰው ከመግደል አልፈው ለሞቀ ገበያ እንቅፋት ለመሆን መብቃታቸው ነበር ገበሬዎቹን ያበገናቸው። "ይቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም" አይነት ነበር ስሜታቸው። የቁንድዶን ዳገት በንዴት የወጡትን ያህል ፈረሶቹን በዱላ እየገሰጡ ወደ ቀድሞ ሰፈራቸው በመመለስ እልሃቸውን ሊወጡ ግን አልቻሉም። የቁንድዶ ፈረሶች የሰው ልጅ ንብረት መሆናቸውን ከመርሳታቸው ባሻገር፤ ሰው ሲያዩ በእግራቸው መሬቱን መጫር፣ ማንፋዋረር፣ ገለል የማለት፣ የመሸሽ፣ ጆሮ የመቀሰር የመሳሰለ ያልተለመደ ጠባይ ማምጣታቸውን ገበሬዎቹ ተገነዘቡ። የተገነዘቡት ግን ያን ብቻ አልነበረም። በቁንድዶ ሜዳና ጫካ እየተሯሯጡ ፈረሶችን መያዝ አዳጋች ሆነባቸው። ያን ቀን ገበሬዎቹ ፀሃይ እስክታዘቀዝቅ ድረስ የፈረሶቻቸውን ባለንብረትነት ለማረጋገጥ ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ በመቅረቱ፤ የማታ ማታ ከገመዶቻቸው ጋር እንደመጥረቢያ ጎብጠው ወደየጎጆአቸው ተመለሱ።

በዚያን እለት ሌሊት ገበሬዎቹ እንቅልፍ ሳይወስዳቸው እንዳደረ ይነገራል። ከፊሉ በፈረሶቹ ድፍረት ያረረ ቆሽቱን በአረቄ አረገበ። ሌላው በነጋታው ፈረሶቹን እንዴት በቁጥጥሩ ስር እንደሚያስገባ መላ ሲዘይድ አደረ። ፈረሶቹን ዳግም በእጅ ማስገባት እንደማይቻል ያመነ ግን ከቶ አልነበረም። ሊያምኑ የዳዳቸው የፈረሶቹን ዋጋ በመደመር ሊያጡ የሚችሉትን ገንዘብ ሲረዱ እንደመቃዣት እያደረጋቸው እንደገና ፈረሶቹን ማላመድ የሚቻልበትን መላ ያውጠነጥናሉ።

በነጋታው ገበሬዎቹ ወደ ቁንድዶ ያቀኑት የሰው ሃይላቸውንና የገመድ አይነታቸውን በማጠናከር ነበር። ውጤቱ ግን የከፋ ሆነ። ከጥቂት ሙከራ በሁዋላ የአንዱን ፈረስ አንገት በገመድ መያዝ የቻለ ገበሬ ህይወቱን ከማጣት ለጥቂት ተረፈ። በገመድ የተያዘው ፈረስ ከመከላከል በቀጥታ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ወደ ማጥቃት በመሸጋገር፤ ተቆጥቶ ሁለት የፊት እግሮቹን ወደ ሰማይ በመስቀል እያናፋና እያሸካካ በጥርሶቹ የገበሬውን ትከሻ ነክሶ ጣለው። ገበሬዎቹ ይህን ሲያዩ ያልገመቱት አደጋ መኖሩን ተገነዘቡ። ፈረሶቹን በገመድ መያዝ ብቻውን ፋይዳ አልነበረውም። ቢያዙም ፈረሶቹ በሰላም አይጎተቱም።

ገበሬዎቹ ማድረግ ያለባቸውን መክረው ነበር። ከፈረሶቹ ጋር መታገል ሞት አሊያም ማለዳ ላይ እንደተነከሰው ባልንጀራቸው በወላንሳ መወሰድ፤ ምናልባትም አካለ ስንኩል መሆን እንደሚጠብቃቸው አመኑ። ሆኖም ፈረሶቹ ከቁጥጥራችን ውጪ ሆነዋል ብለው ማመን አልፈለጉም።

"ለጊዜው እንተዋቸውና ቀስ ብለን እናላምዳቸዋለን" በሚል ራሳቸውን አሳምነው ዘመቻውን ትተው ተመለሱ።

በርግጥም ገበሬዎቹ አልፎ አልፎ ፉርሽካ ይዘው በመሄድ ሊያላምዱዋቸው ሞክረው ነበር። አልሆነም። የፈረሶቹ ባለንብረቶች ተስፋ ከቆረጡ በሁዋላም ቢሆን፣ ፈረስ የመግራት ልምድ አለን ያሉ፤ አገር አቋርጠው እየመጡ ፈረሶቹን ለመያዝ ሞክረው ነበር። አልሆነም። ይልቁን ፈረሶቹ በሰው ልጅ ላይ ያላቸው ጥላቻ በከፍተኛ ደረጃ በማደጉ ሰው ሲያዩ በቡድን ሆነው ለፍልሚያ የመዘጋጀትን ልምድ በማዳበራቸው ቀስ በቀስ ፈረሶቹን ለመያዝ የሚደረጉ ሙከራዎች እየቀሩ ሄዱ።

...ቀናት ቀናትን እየተኩ፤ አመታት አለፉ።

አልፎ አልፎ በሽታ እየገባ ቁጥራቸው ቢመናመንም የፈረሶቹ ቁጥር እየጨመረ ሄደ። ከጊዜ ብዛት ታዲያ የአካባቢው ገበሬዎች ፈረሶቹን ለዘልአለሙ ማጣታቸውን አመኑ። እንዲያውም "የኛ ፈረሶች" ማለቱን ትተው "የቁንድዶ ፈረሶች" እያሉ ይጠሩዋቸው ገቡ።

አስደናቂውና አስደማሚው ነገር ግን ሌላ ነው። ገበሬዎቹ ጀግና ሲገጥማቸው፤ አሊያም በራሳቸው የሚተማመኑ፣ የተሰማቸውን ፊት ለፊት የሚገልፁ፣ የዋህ፣ ቅን፣ እውነተኛ የሆኑ አትንኩኝ ባዮች፤ ላመኑበት ህይወታቸውን የሚሰጡ ሰዎችን በቁንድዶ ፈረሶች መመሰል የተለመደ ሆነ። "እገሌ የቁንድዶ ፈረስ ነው" ከተባለ ሙገሳ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ነው። እንደማነፀፀሪያም የጋሪ ፈረሶችን ያነሷቸዋል።

"ለሆዴ አላደርኩም። አላማ ያለኝ፣ ክብር ያለኝ ሰው ነኝ" ማለት ሲሹ "የቁንድዶ እንጂ የጋሪ ፈረስ አይደለሁም" ሲሉ በኩራት ይገልፃሉ።

* * *

እነሆ ኤጀርሳ ጎሮ ላይ በያዝነው ገበሬ ድጋፍ የቁንድዶን አቀበት ተያይዤዋለሁ። ከተራራው ግርጌ ላይ መንደሪቱ ውስጥ የተውናት ላንድ ክሩዘር ጉንዳን አክላ ትታየኛለች። ለነገሩ ለአፍታ ካልሆነ ከተራራው ላይ ቁልቁለቱንና አካባቢውን በሙሉ አይን ማየት አይቻልም። ያጥወለውላል። ሻቦው ያለው ገደላ ገደል አይንን የመጎተትና የመጎልጎል ሃይል ያለው ይመስላል። ቁንድዶ ተራራ ላይ የሚገኙትን እምቢ ባይ የዱር ፈረሶች ለማየት መፈለጌን ለሃረሪ ክልል ፕሬዚዳንት ስገልፅ አጀቤን ጠንከር ያደረጉልኝ አለምክንያት እንዳልሆነ ተረዳሁ። እምቢ ባይ ፈረሶቹ ሊያደርሱ ከሚችሉት አደጋ ባሻገር አቀበቱ በራሱ እንቅፋት ነው።

መቶ አለቃ ሃሚድ ጥያቄ ቢጤ ጣል አደረገ፣

"ፖሊስ ከሆንኩ ጀምሮ አያሌ ባለስልጣናትን፣ ቱሪስቶችንና ጋዜጠኞችን በተለያዩ ጉብኝቶች ላይ አጅቤያለሁ። የቁንድዶ ፈረሶችን ለማየት የጠየቀ ግን ገጥሞኝ አያውቅም"

ሊጠይቀኝ የፈለገውን ያስከተለው ፋታ ወስዶ ነበር፣

"ለምንድነው ፈረሶቹን ለማየት የፈለግከው?"

የአድካሚ ጉዞዬን ምክንያት በቀላሉ ላይገነዘብ ይችላል ብዬ በመስጋት በደፈናው ምላሽ ሰጠሁት።

"አመፀኞች ስለሆኑ ነው ልጎበኛቸው የፈለግሁት"

"ማለት የፈለግሁት ምን መሰለህ?" ሲል ጥያቄውን አራዘመ "ፎቶግራፍ ልታነሳቸው የፈለግህ ነበር የመሰለኝ። ግን ደሞ ካሜራ አልያዝክም"

ቀና ብዬ የተራራውን አናት በአይኔ እየለካሁ፣

"በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ ነፃነትና ባርነት አሉ" አልኩ።

ሆኖም ማለት የፈለግሁትን ሳልቋጭ አቋርጬ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በአጭሩ ምላሽ ሰጠሁት

"…. የሆነው ሆኖ እኔ ደራሲ ነኝ። ከቁንድዶ ፈረሶች ባሻገር ስለ እምቢ ባይና እሺ ባይ ሰዎች የመተረክ ሃሳብ አለኝ። የባለጠመንጃ እሺ ባዮችና የጠመንጃ አልባ እምቢ ባዮችን በአሳበ ህሊናህ መርመር" አልኩት።

ሃሚድ ምላሽ ሳይሰጠኝ በመዘግየቱ፣

"ማለት የፈለግሁት ገብቶሃል?" ስል ጠየቅሁት።

"ይመስለኛል" ሲል ተነፈሰ።

ርግጠኛ እንዳልሆነ ግን ድምፁ ያስገነዝብ ነበር።

ረፋዱ ላይ የቁንድዶን አናት ስንረግጥ ለሰማዩ ቅርብ መሆኔን ከመገንዘቤ ባሻገር፤ በአይኔ መንገድ ላይ የእምቢ ባዮቹ ደሴት ተዘርግቶ ወደ ምናባዊው አለም ይዞኝ ጭልጥ አለ።

"የት ናቸው ታዲያ ፈረሶቹ?" ስል የኤጀርሳው ገበሬ ላይ ጮህኩ።

ገበሬው ፊት ፊት የመምራት ሚናው እንዳይነጠቅ እየተጣደፈ፣ ስለአካባቢው በቂ እውቀት እንዳለው እንድንገ ነዘብለት በሚፈልግ ስሜት ነበር ምላሽ የሰጠኝ።

"በዚህ ሰአት ፈረሶቹ ከኩሬው ጀርባ ነው የሚገኙት። እኒያን ዛፎችና ቁጥቋጦች እልፍ እንዳልን ደሞ ኩሬውን እናየዋለን። ተከተሉኝ"

ማይ ጥግ ላይ ከተዘረጋው የተራራ ሜዳ ላይ ሰርዶውን በእግራችን እያስተኛን ገበሬውን ተከተልነው። እድሜ የጠገቡ የዝግባ ዛፎች በቁንድዶ መስክ ላይ ተጠቅጥቀዋል። ለጥ ያለው መስክ በለምለም ሳርና አልፎ አልፎ በሰርዶና በቁጥቋጦ ተሞልቶአል። ድካሙ ጥሎኝ እልም ብሎአል። ስ ሜቴ ተነሳስቶአል። መንፈሴ ንቁ ሆኖአል። እዚህ ያሉት ፈረሶች ብቸኛዎቹ የአካባቢያችን ነፃ ፈረሶች መሆናቸውን እያሰብኩ ነበር።

ገበሬው ገለፃውን ቀጥሎ ነበር፣

"እንደኔ እንደኔ ቢሆን ግን ፈረሶቹን ከማየታችን በፊት ባህሩን ማየት ይሻላል…"

"የምን ባህር?

"ቀይ ባህር ነዋ!"

የሚቀልድ ነበር የመሰለኝ።

"ቀይ ባህርን ደሞ እዚህ ምናመጣው?"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"እሱ የሚለው ልክ ነው" ሲል መቶ አለቃ ሃሚድ ጣልቃ ገባ "...ማለዳ ላይ ከቁንድዶ አናት ቀይ ባህርን ማየት እንደሚቻል ሰምቼያለሁ"

ገበሬው ገለፃውን ቀጠለ፣

"ቅድሚያ ባህሩን እንይ ያልኩት ለዚህ ነው። ፀሃይ ከዞረች ባህሩን አናየውም። አይናችንን ስለሚጋርደን ባህሩ ይ ሰወርብናል። ፀሃይ ከአናታችን ትይዩ ከሆነች እንኳ አናየውም..."

"ቀጥል እንዳልከው!" አልኩት።

አቅጣጫውን ለውጦ በዛፎች ጥላ ስር ይዞን ገሰገሰ። ከአስር ደቂቃ በላይም አልወሰደብን። ከዛፎቹ ጀርባ ከቁንድዶ ተራራ ምእራባዊ ዳርቻ ብቅ ስንል አይናቹ በቆምኩበት አፍዝዞ ካስቀረኝ ትእይንት ጋር ተዋሃዱ።

ከቁንድዶ አናት ባሻገር፤ የእርሻ መስኮችንና የደንከ ሊያ በረሃዎችን አልፎ እንደ ቆርቆሮ የሚያብረቀርቅ ውሃ የመሰለ ነገር በፀጥታ ተንጣሎአል። ቀይ ባህር ግን አይደለም። ሚራዥ እንጂ ውሃ አልነበረም። በምናብ ቀይ ባህርን ማሰብ ግን ይቻል ይሆናል! ቀይ ባህር የሳኡዲ አረቢያን ሰማይ ተደግፎ፤ የማለዳዋን ፀሃይ ሲሞቅ፤ ከምስራቅ ሰማይ አድማስ ተወልዳ ጀርባችንን እያሞቀች በአናታችን ላይ ተወርውራ ባህሩ ላይ ጨረርዋን ያሳረፈችው የማለዳ ፀሃይ... አእምሮ ከሚያስበው በላይ "የቀይ ባህርን" ደረት ስፋት ገልጣ ሰጠችን።

ለደቂቃዎች ያህል በዝምታ ተደመምን።

"ቀይ ባህር በጣም ቀርቦአል!" ሲል ከፖሊሶቹ አንዱ አግራሞቱን ገለፀ። መቶ አለቃው ወደኔ ተመልክቶ ፈገግ አለ። እሱም የሚታየን ውሃ አለመሆኑን ተረድቶ ነበር።

ከሩብ ሰአት ቆይታ በሁዋላ ጀርባችንን

ለ"ባህሩ" ሰጥተን እንደገና ጢሻዎቹን እየተሹለከለክን፤ የበርሜል ያህል የወፈሩ የዝግባ ዛፎችን እየታከክን፤ ከሰማይ ጠቀስ ዛፎች አናት በሚወረወሩ የዛፍ ፍሬዎች እየተኮረኮምን በቁንድዶ ደቡባዊ ዳርቻ ወደሚገኘው የእምቢ ባዮች መንደር አመራን።

"ስንት ይሆናሉ ፈረሶቹ በጠቅላላው?" ስል ጠየቅሁ።

"የቆጠራቸው የለም እስካሁን" ሲል መለሰ ገበሬው።

"በግምት ማለቴ ነው"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"የገመታችውም የለም"

በተለየ መንገድ ጥያቄዬን አቀረብኩ።

"መቶ ይሆናሉ?"

"መቶ አይሆኑም"

"ምናልባት ሰላሳ"

"ከነግልገሎቹ ከሆነ ከሰላሳ ያልፋሉ"

"ሃምሳ ወይም ስልሳ ይሆናሉ ማለት ነዋ!"

"እንዳልኩት የቆጠራቸው የለም"

ጢሻዎቹን አልፈን ቁጥቋጦና ሳር ውስጥ ስንገባ በግምት በመቶ ሃምሳ ሜትር ርቀት ላይ ኩሬ አየሁ። ከኩሬው ባሻገር ሰማይ ጠቀስ የዝግባ ዛፍ ቆሞአል። ሁለት ዳማ ፈረሶች ከዛፉ ስር በፀጥታ ቆመዋል።

"በዚያ በኩልም እኒያውልህ ፈረሶች!" ሲል በስተቀኝ በኩል አመላከተኝ።

ከአስር የማያንሱ ፈረሶች ሜዳው ላይ በፀጥታ ቆመው የማለዳዋን የፀሃይ በረከት በፀጥታ ይመገቡ ይዘዋል። ሁለት ግልገል ፈረሶች ጋማቻውን እያጋፈሩ በቁም ባንቀላፉት ፈረሶች ዙሪያ ይቡዋርቃሉ።

ወደ ፈረሶቹ በፍጥነት በማምራት ላይ ሳለን ገበሬው የእርምጃ ፍጥነቱን ቀነስ አድርጎ ጥብቅ መመሪያዎችን ይሰጠን ጀመር።

"ብዙም ልናስቆጣቸው አይገባም። ከተቆጡ ሊተናኩሉን ይችላሉ"

ከፖሊሶቹ አንዱ የገበሬውን ስጋት አጣጣለ።

"ጠመንጃ ታጥቀን ፈረስ እንፍራ እንዴ ደሞ?"

ገበሬው ግን እንደገና አምርሮ አስጠነቀቀ።

"ፈረስ መሆናቸው አይካድም። እነኚህ ግን የድሬዳዋ የጋሪ ፈረሶች አይደሉም። የቁንድዶ ፈረሶች ናቸው። ከተቆጡ በህብረት ስለሚያጠቁ ሁሉንም ባንዴ መግደል ሊሳን ይችላል። አንድ ሁለቱ ቢሞቱ ከሶስተኛው ማምለጥ አይቻልም"

ከፈረሶቹ ሃምሳ ሜትር ርቀት ላይ ሁላችንም ቆምን።

"ግልገሎቻቸውን ካልነካንና ገመድ ካልወረወርን ቶሎ አይቆጡም። ትእግስተኞች ናቸው። በቅድሚያ ገለል ማለትን ነው የሚመርጡት"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ፖሊሶቹ ያፍዋጩና በእግራቸው መሬቱን እየተመተሙ ነገር ይፈልጉዋቸው ጀመር።

"ሲቆጡ ነብር ነው የሚመስሉት። በጣም ያስ ፈራሉ" ሲል ማብራሪያውን ቀጠለ ገበሬው ".... ወደ አውሬነት ይለወጣሉ። ሲቆጡ በቅድሚያ በፊት እግራቸው መሬቱን እየጫሩ አፋቸውን መሬት ላይ ተክለው እህህታ ያሰማሉ"

"በጠመንጃ የሚያድናቸው የለም?" ስል ጠየቅሁት።

"በጥይት መግደልማ ይቻላል። ግን ፈረስ ከቆሰለ ምን ይጠቅማል? የፈረስ ጥቅሙ ከነጤናውና ከነጉልበቱ ነው። የቆሰለ ፈረስ ለጋሪ የሚገዛ የለም። ስጋቸው ደሞ አይበላ"

የፖሊሶቹ ፉጨት ሲበረታባቸው ፈረሶቹ በቅድሚያ ጆሮዎቻቸውን ቀሰሩ። ቀጥሎ የተማከሩ ይመስል መንቀሳቀስ ጀመሩ። የመበርገግ ነገር ፈፅሞ አልታየባቸውም። በየከተሞቹ ጋሪ ሲጎትቱ ከማያቸው ፈረሶች ጋር ፈፅሞ አይመሳሰሉም። እነዚህ ኮረብታ ያክላሉ። ታፋቸው እንደ ማእበል ይገላበጣል። ቆዳቸው ወዛም ነው። ያብረቀርቃል። የጠወለገ ገላ ያለው ፈረስ ፈፅሞ አይታይም። ቁስላምና የዝንብ መጫወቻ አይደሉም።

የቁንድዶ ፈረሶች!

ፖሊሶቹ ተንደርድረው እየተጠጓቸው መልሰው ወደ ሁዋላ እያፈገፈጉ ጠብ ያለሽ በዳቦውን ቀጠሉ። እምቢ ባዮቹ የቁንድዶ ፈረሶች በሶምሶማ ግልቢያ እኛ ካለንበት ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ አመሩ።

ተከተልናቸው።

ከአምስት ያልበለጡ ግልገሎቻቸውን አስቀድመው ግልቢያቸውን ጨመሩ። የጩኸት ድምፅ እያሰማን በሩጫ ተከተልናቸው። ፈረሶቹ ጭራቸውን ገተሩ። ተከተልናቸው። ፉጨታችንና መጫጫሃችን ጨመረ። ከፖሊሶቹ አንዱም ድንጋይ አንስቶ ወረወረ።

ለአምስት ደቂቃ ያህል አባሮሹ እንደ ቀጠለ ከእምቢ ባይ ፈረሶቹ አንዱ ድንገት የሁዋሊት ዞሮ በተጠንቀቅ ሲቆም እኛም ባለንበት እንደ ሃውልት ተተክለን ቀረን። ድምፃችን ከመቅፅበት ጠፋ። የታጠቁት ፖሊሶች ጠመንጃዎቻቸውን በፍጥነት አቀባብለው ከእኛ ቀደም አሉ። ፈረሱ ጆሮዎቹን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደጦር ገትሮ ፊት ለፊት እያየን ነበር።

ፖሊሶቹ እንደገና አፋጥጠውበት፤

ፈረሱ ከመቅፅበት ፊቱን አዙሮና ጀርባውን ሰጥቶን በመሸሽ ላይ ወዳሉት የእምቢ ባዮች መንጋ ጋለበ።

"ትእግስታቸውን ገና አልጨረሱም" አለ ገበሬው።

"ይበቃናል" አልኩ።

ፖሊሶቹ ግን ፍልሚያውን ፈለጉት።

"እስከ መጨረሻው እናበሳጫቸው። ጠመንጃ ስለያዝን አያሰጋንም። ሽምጥ እየጋለቡ ቢመጡ በሩምታ ተኩስ ልናስቀራቸው እንችላለን!"

ሆኖም ሳልስማማ ቀረሁ።

"ፍልሚያው ከተጀመረ በሁዋላ ውጤቱ ምናልባት እንደሚገመተው ላይሆን ይችላል" አልኩ "....የቁንድዶ ፈረሶች ወደ ዳግም ባርነት ከመመለሳቸው በፊት ለመሞት ዝግጁ ናቸው"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 13 -

እነ መለስ! እነ ተወልደ!

ኒጋሪት ማስመታት - ነበረ ስራችን፣
እምቢልታ ማስነፋት - ነበረ ስራችን፣
መለከት ማስነፋት - ነበረ ስራችን፣
ሰው መሆን አይቀርም - ደረሰ ተራችን፣

(ግጥም - እቴጌ ጣይቱ ብጡል)

* * *

በቁልቁለት ጉዞ - ሁሉም ተጣመደ፣
ተያይዞ ነጎደ - እየተካካደ፣
ዳገት ላይ ሰው ጠፋ - አቀበት ከበደ፣
ሁሉም በሸርታቴ - ቁልቁለት ወረደ፣

(ግጥም- ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም)

በዚያን ሰሞን የአዲስ አበባ አሽሚጣጭ የእነ መለስ እና የእነ ተወልደን ፍልምያና መከፋፈል ታዝቦ፣ ለኢትዮ - ኤርትራ ግጭት የቋጠረውን መልሶ ዘፈነው።

ጎጃሜ ቡዳ ነው...ብላችሁ ስትሉ፣
ትግሬን ትግሬ በላው... እንግዲህ ምን ትሉ?

አዲሳባ ላይ ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ አይደለምና እኛ ወያኔዎች ይህን ከመስማት አላመለጥንም። በኔው እይታ ስለ ዘመናችን ተራሮች የአንድ ሰሞን ሽኩቻ ከውስጥ ሆኜ ላውጋችሁ...

* * *

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የኤርትራ ጦርነት ካበቃ በሁዋላ በፕሮፓጋንዳው ክፍል ዙሪያ የምንገኝ ጋዜጠኞች ጥቂት የማይባሉ አስደማሚ ወሬዎችን እንሰማ ነበር። በተለይም ተክሉ ተክላይን የመሰሉ የእነ ተወልደ ደጋፊ ካድሬዎች ማብቂያው ላይ ጉድ ሆነዋል። የፕሮፓጋንዳው ክፍል ነባር ባልደረባ ከሆነው ከተክሉ ጋር አልፎ አልፎ እየተገናኘን እናወራ ነበር። ለረጅም ጊዜ አብረን ስለሰራን እንግባባለን። ተክሉ ለህወሃት ታማኝ ሲሆን ፤ ኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ ባንዲራ የመሳሰሉ ቃላት ግን ይከሰክሱታል።

"የኢትዮጵያን ባንዲራ ለምን ትጠላዋለህ?" ስል ጠየቅሁት አንድ ቀን።

"ሳሞራም አይወደውም"

"በምን አወቅህ ሳሞራ እንደማይወደው?"

"3ኛው ጉባኤ ላይ በግልፅ ተናግሮአል"

ሌላ ቀን ደግሞ እንዲህ አለኝ፣

"ህወሃት ከሌለ ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር አትኖርም"

"እንዴት?"

"ስዬ እንደሱ ነው የሚለው?"

"ማለቴ...አብራራው እስኪ?"

"ያለ ህወሃት ኢትዮጵያ እንደ ሃገር ልትቀጥል አትችልም"

ከተክሉ ተክላይ ጋር መነጋገር አይቻልም። ስዬ - አለምሰገድ - ተወልደ - የተባሉትን ስሞች ሳይቀላቅል ሶስት አረፍተነገር ማውራት አይችልም። በባህርይው ግን ልብስ መቀያየርን እንኳ የሚፀየፍ ደግ ሰው ነበር። ልብስ አለመለዋወጥን በአብዮታዊነት እንደመፅናትና ሙስና ውስጥ ያለመግባት ማረጋገጫ አድርጎ ያየዋል፣

"እነ ስዩም እና መለስ አብዮታዊነታቸውን እያጡ ነው" አለኝ ሌላ ቀን በሚስጥር።

"እንዴት?"

"ከአምባሳደሮች ጋር እየዋሉ ተበላሽተዋል! ሱፍና ክራቫት ሲለዋውጡ ነው የሚውሉት። ተወልደን አይተኸዋል? እስካሁን ኮንጎ ጫማ ነው የሚያደርገው"

ስዬ አብርሃ ሁለት ጣቶቹን አገጣጥሞ ክብ በመስራት ቃለ - መጠይቁ "አሰር መፅሄት" ላይ በታተመበት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እለት ምሽት ከተክሉ ጋር አክሱም ሆቴል በተደረገ አንድ ግብዣ ላይ ተገናኝተን ነበር።

"ጦርነቱ ሊጀመር ግፋ ቢል አንድ ሳምንት ቀርቶታል" አለኝ የስዬን ምስል የያዘውን መፅሄት እያሳየኝ።

አያያዘናም ደግሞ ቀጠለ፣

"ዋናውን ሻእቢያ ከመታን በሁዋላ በውስጣችን የተሰገሰጉትን ሻእቢያዎች እንመነጥራቸዋለን!"

አንጃው ከተወገደ በሁዋላ ከስራ ከተባረሩት መካከል ተክሉ የመጀመሪያው ሆነ። የተባረረ ሰሞን ከመደንገጡ ብዛት ከቤቱ አይወጣም ብለው ነገሩኝ። ምድር ጨልማበት ጋቢ ለብሶ ፒያሳ ከሚገኘው የመኖሪያ ቤቱ አፓርታማ በረንዳ ላይ ተቀምጦ እንደሚውል ሰማሁና ላፅናናው ሄድኩ። ፊቱ ገርጥቶ፤ አይኑ በርበሬ የተረጨበት መስሎ ሳገኘው በንዴት ሲቃጠል እንደከረመ ገመትሁ።

"እንኳን ደስ ያለህ!" አለኝ በጥርጣሬ እያየኝ።

"ለምኑ?"

"መለስና በረከት ሁሉንም ተቆጣጠሩት! ሻእቢያ የህዝብ ልጆችን በእጅ አዙር እየመታ ነው"

"እኔ ታዲያ ለምንድነው ደስ የሚለኝ?"

"አንተም የነሱ ወገን ነህ ይባላል"

"ከበረከት ጋር እንደማንግባባ እያወቅህ እንዴት እንደሱ ትላለህ?"

"ሽፋን እንዳይሆን" ብሎ የሽሙጥ ሳቅ ሳቀ።

"እኔ የማንም ወገን አይደለሁም"

ተክሉ ደጅ ደጁን እየተመለከተ ቆየና፣

"ስዬ - ተወልደ - አለምሰገድ - አብርሃ ማንጁስ - አውአሎም - ገብረመስቀል - ገብሩ - አረጋሽ - ማን ቀረ? አሉ የተባሉት ናቸው የተወገዱት... እነዚህ ማለትኮ የሃገሪቱ ጭንቅላት ናቸው። ንገረኝ እስኪ! ማን አለ ሌላ? ማንም የለም!! በዚህ ጦስ ይህቺ አገር በደም ልትታጠብ ትችላለች። ምናለ ተክሉ በለኝ!! ትንሽ ቀን ጠብቅ! ሰራዊቱ ቤተ መንግስቱን ሰብሮ ይገባል። ስዬ ማለትኮ የሰራዊቱ አባት ማለት ነው"

ከዚያም ጣቱን እየቆጠረ እንደገና ይዘረዝርልኝ ጀመር፣ "... ስዬ - ተወልደ..."

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስማቸውን በጠራ ቁጥር ግንባሩ ላይ ያለው የደም ስር ይበልጥ እየተገታተረ ሲወጣጠር በማየቱ ደም ስሩ ተበጥሶ ፀጥ እንዳይል ሰጋሁለት።

ተሰናብቼው ስሄድ አብራው ትኖር የነበረችው እህቱ ተከትላኝ መጣች፣

"ምግብ ሳይቀምስ ሁለት ቀኑ ነው። ማታ ይዘኸው ውጣና አግባብተህ እንዲመገብ አድርገው" ስትል ለመነቺኝና ተስማማሁ። አያያዘችናም እንዴት እንደሰነበተ ጥቂት ነገረቺኝ፣

"ምከረው እባክህ! በጣም ይበሳጫል። ሳናግረው መልስ አይሰጠኝም። 'ህወሃት እንዲህ ተከፋፍሎ ከማየቴ በፊት ምነው እንደጓዶቼ በረሃ በቀረሁ ኖሮ' እያለ ይቆጫል። ስለ ግል ህይወቱ ማሰብ አለበት። ማታ ይዘኸው ውጣና ምከረው። ከተባረረ በሁዋላ ጓደኞቹ ሁሉ ከዱት። አንድ የሚደውልለት እንኳ የለም። ሰው መቼም ከሃዲ ነው..."

የኢፓርታማውን ደረጃዎች ስወርድ የተክሉን ዜማ ለራሴ አዜምኩት፣

"ስዬ .... ተወልደ...አረጋሽ...."

* * *

በእነ ተወልደና በነ መለስ ክፍፍል ዋዜማ ባለስልጣናቱ ቡጢ ገጥመው ነበር። አስደንጋጭ ስድቦች እየተሰዳደቡ ግራ አጋቡን። አንዱ ሌላውን "ጠባብ" ሲለው፤ ሌላው "ሃሜተኛ" ሲል ምላሽ ይሰጣል። ዶክተር ነጋሶ በወቅቱ እነ መለስን አስቸግሮአቸው ነበር። ተወልደ እነ አዲሱ ለገሰን "የፖለቲካ ድሆች!" ሲላቸው፤ በረከት ደግሞ በደም ፍላት "ጋሽ ተወልደ! አናውቅህም እንዴ? ለመሆኑ ከNewsweek ሌላ ምን አንብበህ ታውቃለህ?" ሲል ዘረጠጠው። ተወልደ ይህቺ የበረከት ንግግር ከነከነችውና በነጋሶ መጣጥፍ በኩል፣ "በሃገር ጉዳይ በስራ ተወጥረን Newsweekን እንኳ የማንበብያ ጊዜ አልነበረንም" ሲል ምላሽ ሰጠ።

አባይ ፀሃዬ ስዩም መስፍንን "ከእንግዲህ በስብሰባው አንካፈልም ብለህ ለመለስ ንገረው!" ብሎ ሲነግረው፤ ስዩም ደግሞ እጅግ ተከፍቶ "እኔ የ52 አመት አዛውንት እንጂ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ያንተ ተላላኪ አይደለሁም" ሲል ምላሽ ሰጠው።

እኛም ሽኩቻቸውንና መዘራጠጣቸውን በጎን እየሰማን ጆሮአችን ቆሞ ሰንብተን ነበር። ከዛሬ ነገ "በሽጉጥ ይሞካከሩ ይሆን?" አይነት ስጋትም እየነበንን አሳባችንን በአረቄ አባረነዋል። ስዬ አብርሃ በተለይ የሚታመን አልነበረም። "ሽጉጡን ለመምዘዝ ጥቂት ይበቃዋል" የሚሉ ወሬዎች ስለ ነበሩ፤ ለበረከት ሰግተንለት ነበር። በረከትም ቢሆን ግን የዋዛ አለመሆኑን የሚከራከሩ ነበሩ። "እንደ ሸዋዚንገር ሁለት ጊዜ ተገልብጦ በሶስተኛው መተኮስ አያቅተውም" ሲሉ ነገሩን። እንዲያ ከሆነ ሽኩቻቸው ከመወራረፍ አያልፍም ብለን ሳቅና ስጋታችንን ከአረቄ ጋር ስናወራርድ እናመሽ ነበር።

እነ ተወልደ በረከትን ጠምደውት ነበር። "ብአዴን የኛ አሻንጉሊት ነበር" ብለው የልባቸውን ከመናገር ይልቅ "ብአዴን የራሱ የሆነ ጥናቶች እያደረገ፤ አቂም እየወሰደ የመጣ አመራር አይደለም" ሲሉ በዙሪያ ጥምዝ አድክመውናል። አገር ሰላም በነበረበት ጊዜ "ለዚህ የበቃነው በመለስ ጭንቅላት ነው" ሲሉን እንዳልነበር፤ በተኮራረፉ ማግስት የጆሮአችን ታምቡር በድንጋጤ እስኪቃጠል መለስን የሚዘረጥጡ ወሬዎች ሰማን!

በስብሰባዎቻቸው "አንተ ሰካራም፣ አንተ ወራዳ፣ አንተ አጭበርባሪ፣ አንተ ከሃዲ፣ አውቅሃለው! እንተዋወቃለን!" እስከመባባል ተዳርሰው ነበር። ከዚያም ታልፎ "ወዲ ሸርሙጣ" የተባለችው የሰሜን ታዋቂ ስድብ ሳትቀር አገልግሎት ላይ ውላለች።

እነ ተወልደ ብአዴንን "የኛ አሻንጉሊት ነበር" በማለት ምን ጥቅም ሊያገኙ አቅደው እንደነበር ግን በፍፁም አልገባኝም። ብአዴን አሻንጉሊት ከነበረ ተጠያቂዎቹ እነሱው ናቸው። ብአዴንና አህዴድን እንዴት እንደፈጠሯቸው የዘነጉትም ይመስላሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ የነመለስ የነ ተወልደ ክፍፍል ላይ አስቂኝ ሚና ስለነበራቸው የአህዴድ አመራር አባላት ጥቂት ማለት ሳይገባ አይቀርም።

* * *

አንድ የማውቀው መምህር ተማሪዎቹን ዘወትር፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ኮካኮላ ከመሆን ያድናችሁ” እያለ እንደሚመክራቸው አጫውቶኛል። ሰዎች በቅርፅና በይዘታቸው እንደ ኮካኮላ ፍፁም ተመሳሳይ ከሆኑ ለውጥና እድገት ሊኖር አይችልም። ለዘመናት በኩማ ደመቅሳና በአባዱላ ገመዳ እጅ ሲገላበጥ የኖረው አህዴድ፣ እንደ ኮካኮላ ማስታወቂያ፣ “ዘመን የማይሽረው ምርጫ” የሚል ቅፅል በተሰጣቸው ግለሰቦች የተገነባ ነበር። የህወሃት ካድሬዎች ደግሞ እነዚህን ግለሰቦች፣ “የተከዜ እስስቶች” እያሉ ያላግጡባቸዋል። ከብዙ አመታት በፊት ሟቹ የደህንነት ሹም ክንፈ ገብረመድህን ነበር፣ አህዴዶችን ተከዜ ወንዝ ዳርቻ እንደ ጠላ ቂጣ ጋግሮ የሰራቸው። ከዚያም አዴት የተባለ ቦታ ወስዶአቸው የአህዴድን የመጀመሪያ ጉባኤ እንዲያካሂዱ አደረገ። ከዚህ ቡድን አባላት መካከል ጥቂቶቹ፣ ኩማ ደመቅሳ፣ ኢብራሂም መልካ፣ አባዱላ ገመዳ፣ አበራ ሃይሉ፣ ባጫ ደበሌ፣ ተብለው ይታወቃሉ። የዛሬ ስማቸውን የመረጡትም፣ እዚያው ወንዙ ዳር ነበር። ደርግ ከወደቀ በሁዋላ ኢብራሂም መልካ ተባረረ። “ጎጃምን ነፃ ያወጣነው እኛ ኦሮሞዎች ነን” ብሎ ተናገረ። በዚህ ንግግር የበረከት ባልደረቦች ኮረንቲ ጨበጡ። “ለምን በደፈናው ኢህአዴግ አትልም? ከአማራዎች ልታጣላን ነው ወይ?” ተብሎ ተወቀሰ። በርግጥ ኢብራሂም አልዋሸም። የነ አዲሱ ለገሰ ድርጅት በሰበብ አስባቡ ቀሚሱ ሲያደናቅፈው ኦህዴድ ጎጃም ላይ ገትሮ ተዋግቶአል። ኢብራሂም ወቀሳው ሊሰማው አልቻለም። አያያዘና፣ “ኦሮሞነቴን የማትቀበል ኢትዮጵያ አስር ቦታ ትበጣጠስ” ብሎ ጅራፉን ሲያጮኸው እነ መለስና ተወልደ ቁጭ አሉና መከሩ፣

“ኢብራሂም ኮካኮላ አልነበረም፣ ወደፊትም አይሆንም” ሲሉ ደመደሙ። ሆኖም ኢብራሂም በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ክብር እንዳያገኝ በሙስና ሰበብ እንዲባረር ተጨረሰ። የግል ፋይሉ ሲገለጥ ጥቂት ሰበቦች ተገኙ። በነዚያ ላይ የፈጠራ ቅባት ተቀባ። እኛ ጋዜጠኞችም አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ወሬውን እንዲህ ስንል አባዛነው፣

“ደርግ ወድቆ ገና አመት ሳይሞላ፣ እነ መለስ የካቲት 11ን ሊያከብሩ መቀሌ መሄዳቸውን ጠብቆ፣ ሂልተን ሆቴል ደግሶ ሚስት አገባ”

በዚያን ጊዜ እንኳን ሂልተን መደገስ፣ ሂልተን ገብቶ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሻይ መጠጣት አልተጀመረም ነበርና ወሬው ግቡን መታ። ኢብራሂም ተባረረ! ወሬውን የሰማ ሁሉ፣ "እንኳን ተባረረ! ደግ አረጉት! የታባቱ!" ሲል አሚሚቀ። በአናቱ ምርቃት ወሬዎች ተጫኑለት።

"ከጫት ንግድ በዶላር የሚገኘውን ገቢ ብቻውን በላ! የአነግ ደጋፊ ከሆኑ ቱጃሮች ጋር በጥቅምና በጋብቻ ተሳሰረ"

ከዚያም ማጅራቱ ላይ ካንቻ ተመቶበት፣ "ፎጣ በትከሻ! ፊትህን ወደ መናገሻ!" ተባለ። ከኢብራሂም ሌላ ጥቂቶችም፣ "ስልጣኑ አሳበዳቸው፣ ምኞት አቃወሳቸው፣ ጥጋብ በዛባቸው" ተባሉና ኢብራሂም በሄደበት መንገድ ነጎዱ። ስለዚህ በጎደለ ለመሙላት ኮካኮላዎች ሲፈለጉ፣ ሺፈራው ጃርሶ፣ ሃሰን አሊ፣ ነጋሶ ጊዳዳ፣ ግርማ ብሩ፣ ሶፊያን አህመድ በአቅራቢያው ተገኙና የላይኛው አመራር ውስጥ ተጨመሩ። "አህዴድ በምሁራን ተገነባ" ተባለ። "ግርማ ብሩ የአህዴድ መሪ ቢሆን፣ እንኳን ለኢትዮጵያ ለአፍሪካ በተረፈ" የሚሉ ሙገሳዎች ተደመጡ። እነ መለስ ግን ይህቺን ወግ ሰምተው እንዳልሰሙ በመዝለል አህዴድን ከተከዜ ኮካኮላዎች ጋር በሰንሰለት አቆራኝተው ቆለፉበት። ከውጭ ሃገር የመጣ አንድ የኢህአዴግ ደጋፊ ኦሮሞ ታዲያ ይህንኑ ጉዳይ፣ አንድ የኮክቴል ግብዣ ላይ ለመለስ አንስቶለት ነበር።

"አህዴድ እስከመቼ ነው በአስርአለቆች የሚመራው?"

መለስ ረጋ ብሎ ምላሽ ሰጠ፣

"አስር አለቆቹ አቅም እንደሚያጥራቸው እናውቃለን። ለጊዜው ግን አማራጭ የለንም። ያስፈልጉናል።"

መለስ "ለጊዜው" ሲል "ለአጭር ጊዜ" ለማለት መስሎን ነበር። አስር አለቆቹ "ዘመን የማይሽረው ምርጫ" ይሆናሉ ብሎ የገመተ አልነበረም። ተከዜዎቹ አብዛኞቹ በሻእቢያ ከተማረኩ በሁዋላ ለህወሃት የተሰጡ ወታደሮችና አስር አለቆች መሆናቸው ይታወቃል። መቼም ያሻውን ያህል እብሪተኛ ቢሆን እንኳ፣ መለስ ዜናዊ የኮክቴል ግብዣው ላይ የተናገረውን በይፋ ይደግመዋል ተብሎ የሚታሰብ አልነበረም። ግን አድርጎታል። ፓርላማው ላይ ቀርቦ፣ የሹመት መመዘኛው ችሎታ፣ እውቀት፣ ስነምግባርና ሰብእና ሳይሆን፣ ታማኝነት ብቸኛው መመዘኛ መሆኑን ሲገልፅ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ይሉኝታ እንኳ አላደናቀፈውም። ይህ አባባሉ ይህቺ መከረኛ ሃገር በቤተሙከራነት ደረጃ እንድትቆይ እንደተፈረደባት የሚጠቁም ሆኖ ነበር።

የጋራ አሰራር የለም። አሸናፊ አሳብ አይታወቅም። አንድ ግለሰብ ኮካኮላዎችን ከስሩ ኮልኩሎ "ሳይንሳዊ" ሙከራውን በህዝብ ላይ ያካሂዳል። በህልሙ ያለመው በነጋታው አዋጅ ሆኖ ይፀድቃል። ቅሞ ሲመረቅን ብልጭ ያለለት አሳብ ፖሊሲ ይሆናል። ኮካኮላዎች እስካሉ ድረስ የተናገረውን እያፈረሰ፣ የተቃወመውን መልሶ እየሰበከ መንዝ ይችላል...

ተከዜዎች ህወሃትን እንዳይከዱ በተለያዩ ዘዴዎች ተይዘዋል። በሙስና እንዲዘፈቁ ማድረግ ቀዳሚው ዘዴ ነው። በረቀቀ ዘዴ የገዛ ህዝባቸው ላይ የግድያ ውሳኔ እንዲወስኑ ይደረጋሉ። አንድ ጊዜ በወንጀል የተሳተፈ ወይም የተነካካ የትም አይሄድም ተብሎ ይታመናል። ደም እጃቸው ላይ ካለ ስለሌላው የአይን ጉድፍ አንዲት ቃል ትንፍሽ አይሉም። በትግሉ ወቅት ይህን ለመሰለ የአስፈፃሚነት ስራ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ሁሉ በጊዜ እንዲሰናበቱ መደረጉ ይታወቃል። ያሬድ ጥበቡ ከተሸኙት አንዱ ነበር። አንድ ተሲያት ላይ መለስና ተፈራ ዋልዋ ያሬድ ጥበቡን ለዋና ጋበዙትና ወደ ተከዜ ወንዝ ወረዱ። እናም በግልፅ አማርኛ ነገሩት፣

"አታስፈልገንም! ስለዚህ ወደምትሄድበት ሂድ!"

ያሬድ የታዘዘውን ፈፀመ። ቢቃወም ይገድሉት ነበር። ከኢህዴን አስኳል ውስጥ የኢህአፓ መንፈስ መፅዳቱ ከተረጋገጠ በሁዋላም አህዴድ ተጠፍጥፎ ተጋገረ። ታላቅ መሪ ማለት የራሱን ተተኪ መፍጠር የቻለ መሪ ነው ይባላል። እነ መለስ፣ እነ ተወልደ የሚታወቁት ግን በተገላቢጦሹ ነው። ኢህአዴግ በህወሃት ብቻ እንዲመራ፣ የእህት ድርጅቶች ጭንቅላት በመዶሻ ሲወቀር ዘልቆአል። እነ ተወልደ ከተወገዱ በሁዋላ ደግሞ መለስ ራሱን ወደ አፄነት ማሸጋገር ቻለ።

* * *

በክፍፍሉ ዋዜማ አያሌ ወሬዎችን እንሰማ ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በተለይም ተወልደ እንደ ራስ ሚካኤል ስሁል ሃገራቱን ሊመራ የማቀዱ ነገር ጆሮ የሚያቃጥል ወሬ ሆኖ የፕሮፓጋንዳ ክፍሉን አምሶት ነበር። እነ ተወልደ መለስን አስወግደው አዲሱ ለገሰን በጠቅላይ ሚኒስትርነት ሊያስቀምጡት የማቀዳቸውን ወሬ ከሁለት ምንጮች ነበር የሰማሁት። አዲሱን ጠርተው አነጋግረውት የነበረ ሲሆን "ላስብበት" ብሎ ከተለያቸው በሁዋላ በቀጥታ ወደ መለስ ቢሮ ሄዶ የነተወልደን እቅድ እንደገለፀለት ወሬው ሲከካና ሲቦካ ሰንብቶአል።

(ራስ ሚካኤል ስሁል ጎንደርን በገዛበት ዘመን የመሪነቱን ሚና የተጫወተው ከጀርባ መሆኑን የገድሉ ድርሳናት ይተርካሉ። ራስ ሚካኤል ራሱን እንዲያነግስ የነገስታት ዝርያ አልነበረውም። ስለዚህ የነገስታት ዝርያ ያላቸውን አሻንጉሊቶች እየሾመና እየሻረ እስከ ህይወቱ ፍፃሜ ዘለቀ።)

መለስ የእነ ተወልደን እቅድ ከአዲሱ ካገኘ በሁዋላ፣

"ለሁላችንም የሚበጀን የገጠመንን ሽንፈት ተቀብለን፤ ያገኘነውንም ድል አክብረን በጋራ ብንቀጥል ነው" የሚል መልእክት ለተወልደ ይልክበታል።

በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት የድንበር ግጭት ላይ የቀረበውን ቴክኒካል አሬንጅመንት የመቀበልና ያለመቀበል ጥያቄ ተነስቶ መለስ በድምፅ ከተሸነፈ በሁዋላ የአሸናፊውን ውሳኔ እንደራሱ ውሳኔ ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ ከልቡ መንቀሳቀሱን በመጥቀስም "መለስ ተንበርካኪ ነው" በሚል የጀመሩትን የማስወገድ አሻጥር እንዲያቆሙ ጨምሮ አሳስቦአቸው ነበርም ይባላል።

እነ ተወልደ ግን ያንን ሊቀበሉ ሳይችሉ ቀሩ። "መለስን ማስወገድ እንችላለን" ብለው ተደፋፍረው ወደ ቁማሩ ጨዋታ ሰተት ብለው ገቡ። መለስ - በረከት - ስብሃት - ቴዎድሮስ ሃጎስ ...የመሳሰሉትን የኤርትራ ደም ያላቸውን ጓደኞቻቸውን ሰውተው፤ ከኤርትራ ጋር የተያያዘውን ችግር ሁሉ እነዚሁ ሰዎች ላይ በመደፍደፍ፣ እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ነን በማለት እጃቸውን ታጥበው፤ ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሊታረቁ አልመው እንደነበር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከአንጃው መወገድ በሁዋላ መረጃው ይፋ ሆኖአል።

* * *

ህወሃት ለሁለት የመሰንጠቅ አደጋ የገጠመው ጊዜ አህዴዶች ያልሰለጠኑበትና የማያውቁት ችግር ውስጥ ገብተው ነበር። የአህዴድ አመራር አባላት ነጋሶ ቢሮ እየተሰበሰቡ ስለተፈጠረው ችግር ለመወያየት ሞክረው ነበር። ኩማ የሰለሞን ጢሞ ሎሌ ነበር። ነጋሶ የተወልደ፣ በጎደለ የሞሉት የአህዴድ ምሁራን ደግሞ የመለስ ነበሩ። አህዴድ ግራ ተጋባ። በዚያው ሰሞን ጀኔራል ሳሞራ የኑስ ከመለስ ጎን መቆሙን ወዲያው ግልፅ በማድረጉ ግን አባዱላ ስቃይ ውስጥ ገብቶ ሁለቱም ጋር እጅ መንሳት መጀመሩ ተነግሮለታል። የነመለስም ሆነ የነተወልደ ቡድኖች በየግንኙነት መስመራቸው ቅስቀሳ ያካሂዳሉ። እስስቶቹ ሲሰባሰቡ ማጣፊያው ያጥራቸዋል። የነተወልደ ቡድን ሃይል እያገኘ መሄድ ጀምሮ ነበር። ኩማ በሰለሞን፣ ነጋሶ በተወልደ፣ አባዱላ በፃድቃን ተይዘዋልና ሚዛን ወደነተወልደ እያዘነበለ ነበር። "መለስ ዜናዊ ከስብሃትና ከስዩም ሌላ ደጋፊ የለውም" ብለው ስላመኑ፣ "መለስ ይወድቃል" ወደሚል ግምት ገቡ። ከስብሰባዎቻቸው አጀንዳዎች መረዳት እንደቻልኩት፣ "ህወሃት ሃገሪቱን መምራት ቢያቅተው የኛ ሚና ምን ሊሆን ይገባል?" ብለው በፍፁም አልተወያዩም። ማን ማንን ውጦ፣ ማንስ ተውጦ የጨዋታው ማብቂያ እንደሚሆን፣ ከሂደቱ ለመተንበይ የሚያስችል አቅም አልነበራቸውም። ህወሃቶች በር ዘግተው ይናቆሩ ነበርና ተከዜዎች ለሚካሄደው ሽኩቻ ሁሉ ባእድ ነበሩ። እንደ ተራው ካድሬ ሁሉ እነሱም የእለቱን ውሎ መረጃ የሚያገኙት በወሬ ወሬ እኩለ ሌሊት ግድም ነው። ከዚያ ብጭቅጫቂ መረጃ ተነስተው እንኳ፣ አንደ ወቅቱ አስተሳሰብ ፣ እንደ ተክሉ ተክላይ እንኳ፣ "የህወሃት መፍረስ የሃገሪቱንም መፍረስ እንዳያስከትል ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?" ብለው ሊወያዩ አልቻሉም። "የወከልነውን የኦሮሞ ህዝብ አስተባብረን በመምራት ከጥቃት የምናድንበትን ስትራቴጂ እንንደፍ" ብለው አልተነጋገሩም። በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ላይም ሁሉን እርግፍ አድርገው ትተው፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለአሸናፊው ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ መግለጫ ለማውጣት ብቻ ወደ መጠበቁ ደረሱ።

በሌላ በኩል መለስ ዜናዊ ብአዴንን ጠቅልሎ ቢይዝም፣ ኦህዴድ ወደ እኔ ተወልደ ማዘንበሉና በመወላወል ላይ ስለመሆኑም ይገነዘብ ነበር። በቅርብ አውቅ እንደነበረው ይህ ለመለስ የሚያሳስበው አልነበረም። ቁርጡ ሲለይ ተጠቅልለው ወደእሱ እንደሚገቡ ያውቅ ነበር። በርግጥም መለስ ከኦህዴድ ጋር እልህ ተጋብቶ አያውቅም። በስልጣን ዘመኑ ሁሉ ኦህዴዶችን እየሰበሰበ እንደ ህፃን ልጅ ሲቆጣቸው ነው የኖረው። ነጋሶ ጊዳዳን፣

"እንዲያው የውነት ሌንጮ እና አንተ ሁለታችሁም ከደንቢዶሎ ነው የበቀላችሁት? ከሌንጮ ጋር ቁጭ ማለት እኮ መማር ማለት ነው" ብሎታል። ነጋሶ መለስ ላይ የመረረ ቂም የያዘውም በዚህ ንግግር መሆኑን ብዙዎች ያምናሉ። ሌላ ጊዜ ደግሞ መለስ ኦህዴዶችን ሰብሰቦ፣

"ስራችሁን በትክክል የማትሰሩ ከሆነ፣ እናተን ሜዳ ላይ ጥለን ከኦነግ ጋር እንደራደራለን" ብሎአቸዋል።

መለስ ኦህዴዶችን ችላ ብሎ ከጀርባቸው ያለውን የነተወልደን ቡድን መምታት ላይ ነበር ያተኮረው። ኦህዴዶች ወደ እነ ተወልደ ማዘንበላቸውንም ቢሆን እንደ ጥፋት አልቆጠረባቸውም። ባርጩሜ ሾጥ ሾጥ ተደርገው ወደ መደበኛ ታማኝነታቸው እንደሚገቡ ያውቅ ነበር። ከዚህ ትውልድ ውስጥ እንደ እነርሱ ለጊዜያዊ ጥቅም ሲል ህሊናውን ሸጠ፣ ህዝብን ክዶ ባርነት የሚገባለት ሃይል በቀላሉ ማግኘት እንደማይችል ስለሚገነዘብ ሊያባክናቸው እንደማይፈልግ ግልፅ ነበር።

የህወሃት ክፍፍል ይፋ ከሆነ በሁዋላ መለስ ዜናዊ ፃድቃንን እንዲህ አለው፣ "እየተፈራራን አብረን መስራት ስለማንችል፣ ስራህን ልቀቅ!" ፃድቃን ቢሮውን ለሳሞራ አስረከበ። በዚህ ጊዜ የመለስ ሰዎች እንደ አዲስዘመን ጋዜጣ ረጅምና ባዶ ወደሆነው ጄኔራል በዝግታ ተጠጉ። እንደ ሚዳቋ እንዳይደነብር ተጠግተው ገመድ አንገቱ ላይ አሰሩበት። አባዱላ አልበረገገም። እነ መለስ እንዳልተቀየሙት ሲረዳ ወዲያውኑ የሰለጠነበትን ሙያ መፈፀም ቀጠለ። ኩማን ከፃድቃን ጋር ደርቦ እያወገዘ መከላከያን ለቆ ወደ ኦህዴድ ለመግባት ጠየቀ። የጄኔራልነቱን ማእረግ ድንገት እንደለበሰው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሁሉ፣ ድንገት አውልቆ መሳቢያው ውስጥ ጥሎ ሲቪል ሆነ። ኩማ ግን "ፈጥነህ ግለሂስ አላወረድክም! አመንትተህ ነበር" በሚል ጥቂት ተቀጣ። በመያዣነት ተቀምጠው የነበሩት፣ የገንዘብ ዝርፊያና የስነምግባር ጉድለት ከተሰቀሉበት ወርደው እንደ ሰአት ታሰሩለት። በስደት ሆኜ እንደሰማሁት አባዱላ በምርጫ 97 እንደ በረከት ስምኦን የምርጫ ኮሮጆ ገልብጠ አሸንፌያለሁ ካለ በሁዋላ ኦሮሚያ ላይ ነገሰ።

በርግጥ በረከትና አባዱላን ማመሳሰል ተገቢ አይሆንም። ሁለቱም ምርጫውን በማጭበርበራቸው ሊመሳሰሉ ይችላሉ። ቢያንስ ግን በረከት የፈፀመው ድርጊት እያስጨነቀው ለአእምሮ ህመም ተዳርጎአል። አባዱላ እኮ ከተወለደ ጀምሮ ሆስፒታል ገብቶ አያውቅም። እንደ ድርጊቱ ማበድ ነበረበት። ራስ ምታት የለ! ትኩሳት የለ! ደም ብዛት አያውቅ! ስኳር አያስቸግረው! ሰብሉ እንዳማረለት ገበሬ እጅና እግሩን ዘረጋግቶ ተኝቶ ይውላል። የድምፃዊት አበበች ደራራ ዘመዶች ይበቀሉኛል ብሎ እንኳ አይሰጋም። ኤቢሳ የተባለውን የኦሮሚኛ ቋንቋ ድምፃዊ በነፍሰ ገዳዩ በኮሎኔል ጌትነት ካሰገደለ በሁዋላ እንኳ፣ በሰላም ተኝቶ ያድራል። መለስ ካለ ምን ችግር አለ? በኩባያ ውሃ ውስጥ ያለች እንቁራሪት፣ ከኩባያው ውጭ ሌላ አለም ያለ አይመስላትም። የቢሾፍቱ ኦሮሞዎች፣ "ሃሳብ የለሽ የበላችው ሁሉ ያወፍራታል" ሲሉ እሰማ ነበር። ስለሚኖሩበት ስርአት ምንነት በቂ እውቀት የሌላቸው፣ ማወቅ የሚገባቸው እንደ መድሃኒት እየተመጠነ የሚሰጣቸው፣ በስብሰባ ላይ መናገር ያለባቸውን ሳይቀር እንደ ቴአትር አጥንተው የሚገቡ የጋሪ ፈረሶች። የቁንድዶ ፈረሶች እንኳ አምፀው ነፃ በወጡበት ዘመን፣ ሰው እንደ ጋሪ ፈረስ ሲኖር ማየት ችለናል። ዛሬ ጉልበት አጊኝተህ የምትገድለው ሰው፣ ጊዜ ጠብቆ ደሙን ይመልሳል። ለገሰ አስፋው ከተባለው ድንጋይ የማይማር ሰው ከቶ ምን ስም ይገኝለታል? በዚህ ዘመን እጅህ ላይ ደም ይዘህ መኮብለል እንደማይቻልም ከቀልቤሳ ነገዎ መማር ይቻል ነበር። የኤቢሳና የደራራ ድምፅ ይጮሃል! ያም ሁሉ ሆኖ የእርቅ ጥያቄ ጊዜው አያልፍበትም። የዘመናችን አፄዎች ግን እርቅ ከመፈለግ ይልቅ፣ "ህወሃት አዲስ አበባ ላይ ስልጣን ከእጁ ካመለጠው ትግራይ ትገነጠላለች" የሚል ሁለተኛ አማራጭ እንደማስፈራሪያ ይዘው ይቆምራሉ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተከዜዎች ትግርኛቸውን ላለመርሳት የሚያደርጉትን ጥረትም፣ "ስትራቴጂ" ይሉታል አሉ። ቃላት እንዲህ መቀለጃ ሆነዋል...

* * *

እነ ተወልደና እነ መለስ እየተባሉ የሚታወቁት ጎራዎች ካልተግባቡባቸው አጀንዳዎች መካከል የኤርትራውያን መባረር ጉዳይ አቢዩ ነበር። መለስና በረከት በኤርትራውያን በዚያ መንገድ መባረር ላይ ቅሬታ እንደነበራቸው፤ በተለይም በረከት ስምኦን የተፈፀመውን የማባረር ድርጊት የዘር ማጥራት (Ethnic cleansing) ነው ሲል እንደተናገረ እነ ተወልደ ይተርካሉ። እነ ተወልደ የኤርትራውያንን የማባረር ሂደት ከሚከሩባቸው ድርጊቶቻቸው እንደ አንዱ ይቆጥሩታል። "ኤርትራውያንን ሰብአዊነትን በተላበሰ ሁኔታ ተንከባክበን ነው ያባረርነው" ብለው ሲሟገቱም በተባረሩት ኤርትራውያን ላይ ከፈፀሙት ዝርፊያ በላይ ምን ሊያደርጉ ይችሉ እንደነበር ግልፅ አላደረጉም። በፈፀሙት ድርጊት ከ ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ምስጋና እንደሚያገኙ በመተማመን አጀንዳውን አጨናቁውታል።

ኤርትራውያንን ወደ ሃገራቸው በማሰናበቱ ሂደት የደህንነቱ መስሪያ ቤት ባልደረቦች የፈፀሙት በደል የከፋ የሆነው ኢትዮጵያዊነታቸውን ጠብቀው የቆዩት ላይ፤ ለኢትዮጵያ መስዋእትነት የከፈሉት ላይ ጭምር ህሊና ቢስ ወንጀል መፈፀማቸው ነው።

ይህን መሰል ግፍ ከተፈፀማባቸው አንዱ አሸብር ግርማይ ይባላል። የግራ እግሩንና የቀኝ እጁን ሶስት ጣቶች ያጣው ካራማራ ተራራ ላይ ከሶማሊያ ጋር ሲዋጋ ነበር። ወያኔ የአሸብር ግርማይን ጉዳይ ለማጣራት ጊዜና ትእግስት አልነበረውም። አይኖቻቸውን ከመጨፈናቸውና ከመቻኮላቸው ብዛት የትግራይን ሰው ጭምር ቀላቅለው ወደ ኤርትራ እስከ መላክ ደርሰዋል።

ሰሚ ጆሮ አልነበራቸውም እንጂ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ምክር ፅፈውላቸው ነበር። ፕሮፌሰር መስፍን ኤርትራውያን በህጋዊ መንገድ ጉዳያቸው በግለሰብ ደረጃ እየታየ እንዲሰናበቱ ሲያሳስቡ፤ በአፀፋው ዛቻ ነበር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የተሰነዘረባቸው። ፕሮፌሰሩ በወቅቱ የወያኔን ጅምላ የማባረር ድርጊት የተቃወሙት ለኤርትራውያን የተለየ ወገናዊነት ኖሮአቸው አልነበረም። የሰው ልጆች ሰብአዊ መብት መከበር አለበት ከሚል መሰረታዊ መርህ ተነስተው እንደነበር ግልፅ ነው። የፕሮፌሰሩ መነሻ ያ ብቻ እንዳልነበር ከመጣጥፎቻቸው መረዳት ችዬ ነበር። ህዝብን ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በጅምላ የማፈናቀልና የማባረር ልምድ ለቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብም የማይበጅ ልምድ መሆኑን ፕሮፌሰሩ አሻግረው ማየት ችለው ነበር። ብዙ ብሄሮች ባንድነት የሚኖሩባትን ሃገር የሚመራ፤ የነገውን ማሰብ ካልቻለ ሳያውቀው በራሱ ጥቅም ላይ ሊተኩስ እንደሚችል የሚፃፉ ትንታኔዎችን አለቆቼ እያዩ እንዳላዩ ሆነው የጥላቻ ርምጃቸውን ገፍተውበት ነበር።

(ምርጫ 97 ከተጭበረበረ በሁዋላ በተነሳው የህዝብ ተቃውሞ ወቅትም የፕሮፌሰር መስፍን ሲጋት እውን ሊሆን ተቃርቦ ነበር። አቶ በድሩ አደም "ወያኔዎችን ወደ መጡበት እንመልሳቸዋለን!" ሲሉ ባደባባይ የተናገሩ ሲሆን፤ ህዝቡም "ትግሬ ወደ መቀሌ - ንብረት ወደ ቀበሌ" እያለ ሲዘምር ተሰማ! ፕሮፌሰር መስፍን ታዲያ በዚህ ቀውጢ ጊዜ ከትግራይ ህዝብ ጎን በመቆም እንደገና የማይዘነበል አቋማቸውን አሳይተዋል።)

* * *

በረከትና መለስ የኤርትራውያንን መባረር ተቃውመው ነበር የሚለውን የነ ተወልደ ክስ ለማመን ወይም ላለማመን የሚያስችል በቂ መረጃ የለም። ሆኖም እነ ተወልደ "ሪፖርተር" የተባለው ጋዜጣ ላይ በፃፉት መጣጥፍ በረከት ስለ ኤርትራውያን መባረር "የዘር ማጥራት (Ethnic cleansing)" ነው ሲል መግለፁን ሲፅፉ፤ በረከት በዚያው ጋዜጣ ላይ በሰጠው ምላሽ ይህን ርእሰ ጉዳይ ሳያስተባብል ያለፈ በመሆኑ እነ ተወልደን ለማመን እንገደዳለን።

አንድ ያልተመለሰ ጥያቄ ግን በአእምሮዬ ላይ ቀርቶአል። በረከት የኤርትራውያንን በህገ ወጥ መንገድ መባረር ተቃውሞ ከሆነ ከምን መነሻ ነው የተቃወመው?

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ከመርህ አንፃር ወይስ የኤርትራዊነት ደም ስላለው ለወገኖቹ ተቆርቁሮ? ከመርህ አንፃር ቢሆን ኖሮ ኤርትራውያንን በሚያባርረው ኮሚቴ ውስጥ አብሮ እየሰራ ሳለ አቋሙን ግልፅ ማድረግ ነበረበት። እነ ተወልደ እንደነገሩን ከሆነ በረከት ለሁለት አመታት ያህል የኮሚቴው አባል ሆኖ ሲሰራ ኤርትራውያን ላይ ስለሚፈፀመው በደልና ግፍ ትንፍሽ ባለማለቱ በረከትን መርህ አለው ልንል አንችልም። የኤርትራዊነት ደም ስላለው ለወገኖቹ ተቆርቁሮ ነው ለማለት የሚያበቃ ምልክትም አላየንም። በረከት ስለዚህ ጉዳይ ቢጠየቅ የኤርትራውያንን በህገ ወጥ መንገድ እየተዘረፉ መባረራቸውን የተቃወመው ከ መርህ አንፃር መሆኑን ሊነግረን እንደሚችል ግን መገመት ይቻላል።

ዛሬ ላይ ቆሜ ስታዘብ፤ በረከት በዚህ ወቅት ስለ መርህ ለመናገር የሚያበቃ ሞራል ይኖረዋል ብዬ አልገምትም። ሞቃዲሾ ገብቶ በመቶ ሺህዎች ሶማሊያውያንን የሚጨፈጭፍና የሚያፈናቅልን መንግስት የሚመራ ሰው፤ ስለ ኤርትራውያን በህገ ወጥ መንገድ መፈናቀል ከመርህ አንፃር ስህተት እንደነበር ቢነግረን ከቶ እንዴት ልናምነው እንችላለን?

* * *

በክፍፍሉ ዋዜማ በህወሃት የአመራር አባላት ተዕፈው ከቀረቡት አምስት ፅሁፎች አንዱ በስዬ አብርሃ የተፃፈው ሲሆን፣ ተክሉ ፎቶ ኮፒውን እዚያው ቢሮው ውስጥ ለግማሽ ሰአት አውሶኝ አንብቤዋለሁ። ስዬ እንደተለመደው "እብሪተኛ" ዝንባሌውን በፅሁፉ ውስጥም ቀላቅሎ ነበር። ቀደም ሲል ከአንደበቱ አምልጦት እንደወጣው "ከፈለግን ጦርነትን መስራት እንችላለን!" አይነት አባባል፤ ባቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥም ያካተተ ሲሆን፤ ይህም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችን ህልውና የሚፈታተን ነበር።

ከምርጫው በሁዋላ ሊካሄድ ተታቀደውን ግምገማ አስመልክቶ "ግምገማው በሉአላዊነት ጉዳይ ላይ ያተኩር ወይስ የአስር አመት ግምገማ ሆኖ ሙስናን ቁልፍ ችግር አድርጎ ይካሄድ?" ለሚለው የወቅቱ አወዛጋቢ ጥያቄ ስዬ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የነበረከትን ፕሮፖዛል አጥብቆ ተቃውሞ ነበር የፃፈው። እነ ስዬ መለስን ለማስወገድ ይመቻቸው ዘንድ ግምገማዎች "በሉአላዊነት" ዙሪያ እንዲካሄዱ ግፊት በማድረግ ላይ ነበሩ። ስዬ ባቀረበው ፅሁፍ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችን ሚና ያጥላላ ሲሆን፤ እነ ብአዴንና ኦህዴድ የክልል ጉዳዮቻቸውን ማየት ከቻሉ እንኳ ከበቂ በላይ መሆኑን በገደምዳሜ ሸርድዶአቸዋል። ይህ ለብአዴን ግዙፍ ስድብ ነበር። በረከት ይህን መሰሉን የህወሃት ንቀቶችና ጣልቃ ገብነቶች ከትግሉ ምስረታ ጊዜ ጀምሮ ሲቃወማቸው የነበሩ ሲሆን፤ ለስዬ ፅሁፍም በረከት የመረረ ምላሽ ነበር የሰጠው፣

"እኛ የመንደር ጉዳዮችን እንድንመለከት፤ እናንተ አገራዊ ጉዳዮችን እንድትጨርሱልን የማድረግን ሃሳብ በራሳችን ላይ ተረማምዳችሁ እንድትፈፅሙት እንጂ ሰምምነታችንን አታገኙበትም!!"

በርግጥ የነበረከት የዚያን ሰሞን ድፍረት የመነጨው መለስ ዜናዊን ከጀርባቸው ስለያዙ ነው የሚል አስተያየት የሚሰጡ አሉ። በበኩሌ ይህን አባባል ለማስተባበል የሚያበቃ መነሻ አይቼ አላውቅም። ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ ወዲህ እንደ ድርጅት "ብአዴኖች ነፃ አስተሳሰብ አላቸው" ብለን እናምንላቸው ዘንድ አድርገውን አያውቁም።

* * *

በእነ መለስና በእነ ተወልደ የሽኩቻ ዘመን ስዬ አብርሃ ጆከር ነበርና እነ መለስ የስዬን በሙስና መዘፈቅ እስኪበቃቸው አጨቨውታል። ህዝቡ ግን "ሁላችሁም አንድ ናችሁ" ሲል ችላ ብሎአቸው ነበር። በኔ በኩል ከህዝቡ አስተያየት ጋር እስማማለሁ።

የስዬና የቤተሰቦቹን በሙስና መዘፈቅ በማስረጃ የማረጋገጡ ጉዳይ አከራካሪ ቢሆንም፤ ወሬዎች ግን በስፋት ነበሩ። እነ መለስ ያለጥርጥር ጉዳዩን የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት አውለውታል። የስዬና የቤተሰቡ በሙስና የመዋኘት ወሬ በድፍን ትግራይ ይወራ እንደነበር የሚካድ አይደለም። ከባድ መኪኖች በጎዳና ላይ ሲያልፉ የመቀሌ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ህፃናት ጠጋ ይሉና መኪናውን አሽትተው ሲያበቁ "ስዬ ስዬ ትጨንው" እያሉ ይቀልዱ እንደነበር አውቃለሁ። "ስዬን ትሸታለች" ማለት ነው። የስዬና የቤተሰቡ ጉዳይ ከአጠቃላይ የድርጅቱ አስተሳሰብና የሙስና ሁኔታ ተለይቶ ብቻውን ሊፈረጅ የሚችልበት አንዳችም ልዩ ሁኔታ ግን አልነበረውም።

"ኤፈርት" ተብሎ በሚታወቀው የንግድ ስያሜ ስር የታቀፉት እህትማማች ኩባንያዎች የታወቁ ህጋዊ ዘራፊዎች ስለመሆናቸው ኢትዮጵያ ላይ ነጋሪ የሚያሻው አይደለም። ፍትሃዊ ባልሆነ የውድድር ሜዳ ላይ እየሰሩ ነባር የቢዝነስ ተቋማትን ከስራ ውጭ እያደረጉ ስለመሆናቸው ፀሃይ የሞቀ ወሬ ነው።

ተወልደ - ነጋሶ – በረከት – አለምሰገድ እያልን በግለሰብ ደረጃ ከመረመርን በግላቸው ለዘመዶቻቸው የሰጡት በአይን የሚታይ ልዩ ጥቅም ላይኖር ይችላል። ህገወጥ ተግባራት የሚፈፅሙትን ኩባንያዎች የሚያንቀሳቅሱት ግን እነዚሁ መሪዎች ናቸው። የእነዚህ የህወሃት ኩባንያዎች ገቢ ለትግራይ ህዝብ ነው ቢባልም "ኤፈርት" የተባለውን የኩባንያዎች አስተዳደር አዲተር ጎብኝቶት እንደማያውቅ ሰፊ ትችት አለ። የሆነው ሆኖ ይህን ህጋዊ ሽፋን የለበሰ ዘረፋ ለቀረው የኢትዮጵያ ህዝብስ በምን ቋንቋ ማስረዳትና ማሳመን ይቻላል?

እነ መለስና እነ ተወልደ በስዬ ጉዳይ ላይ ሲሟዋገቱ እህትማማቾቹ ኩባንያዎች የሚፈፅሙትን ወንጀል ሁሉ እንደ ቅዱስ ተግባር ቆጥረው ነበር። ህዝቡም ታዲያ ይህን ሁሉ ያውቃል። "ስዬ በሙስና ተዘፈቀ" የሚለው የነ መለስ ጩኸት የህዝቡን ትኩረት ማግኘት ያልቻለበትም ምክንያት ይህ ነበር። ህዝቡ ባንድ ቃል፣

"ሁላችሁም አንድ ናችሁ!!" ማለት ቻለ።

ህጋዊ ሽፋን በለበሰው በዚህ ዘረፋ የትግራይ ህዝብ ተጠቃሚ አለመሆኑን ለሌላው ዜጋ ማሳመን አስቸጋሪ ቢሆንም፤ እውነታው ግን እንዲያ ነው። በኢትዮጵያዊነቱ ፍፁም ጥርጣሬ እንደሌለው የሚታመነው የትግራይ ህዝብ፤ ከቀሪው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ቂም ቋጥሮ ጥቂት ፋብሪካዎችን በማግኘት ዘላቂ ጥቅም ሊያገኝ እንደማይችል፤

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከቀሪው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ተጋግዞ ማደግን እንደሚመርጥ፤ ይህንንም ፍላጎቱን የኛ ዘመን መሪዎች አሻግረው ሊያዩ አለመቻላቸውን ብዙዎች የትግራይ ምሁራንን የሚያስቆጭ ሆኖአል። የethiomedia.com ባለቤትና ጋዜጠኛ አብርሃ በላይ የትግራይ ህዝብ እንዴት በስሙ እንደሚነገድበት ብዙ ያለለት ቢሆንም፤ ድረ - ገፁ ኢትዮጵያ ላይ እንዳይነበብ በጥብቅ ከታገዱት አንዱ ሆኖአል።

* * *

የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት እነ ተወልደ እንዳልተመኙት ሆኖ ካለቀ በሁዋላ እነ ተወልደ መለስን እንደ አብርሃም በግ መስዋእት ሊያደርጉት ማቀዳቸውን ከተቃወሙት መካከል ዶክተር ካሱ ይላላ አንዱ ነው። "ቴክኒካል አሬንጅመንቱን እንቀበል" ብለው ከተሟገቱት የመለስ ደጋፊዎች አንዱ ካሱ ቢሆንም፤ በሽኩቻው ወቅት ብዙ ስሙ አልተነሳም። ከዶክተር ካሱ ጋር በስራ ብዙ ጊዜ እንገናኝ ስለነበር በእግረ መንገድ ይህንኑ ጉዳይ አንስቼለት ስናወጋ፣ "ከአለማቀፍ ሁኔታዎች ጋር መጓዋዝ ያስፈልጋል። የውጊያ አማራጭ ሁዋላ ቀርነት ነው። ብንዋጋም በመጨረሻ ችግሩ የሚፈታው በጠረጴዛ ዙሪያ ስለሚሆን ብስለት ባለው መንገድ ብንይዘው መልካም በነበረ" ሲል ሃዘኑን አጫውቶኛል። የኢትዮጵያና የኤርትራ ውጊያ ተካሂዶ ከ100ሺ ያላነሱ ዜጎቻችን ህይወታቸውን አጥተው ሲያበቁ፤ አልጀርስ ሄደው በጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ሲሉ በውነቱ ዶክተር ካሱ ነበር ትዝ ያለኝ።

እነተወልደ ከእነመለስ ጋር በቴክኒካል አሬንጅመንቱ ዙሪያ መግባባት ያልቻሉት እነ ተወልደ በጉዳዩ ዙሪያ ድብቅ አጀንዳ ስለነበራቸው መሆኑን ዶክተር ካሱ ይወቅ አይወቅ አላውቅም። የመጨረሻው ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ግን አለምሰገድ የቅርብ አለቃዬ ስለነበርና የፕሮፓጋንዳና የጦርነት ሚስጥሮችን የማወቅ እድል ስለነበረኝ፤ እነ ተወልደ ሉአላዊነትን ከማስከበር ባሻገር ሌላ አጀንዳ እንደነበራቸው ለመረዳት በዙሪያው ለነበርነው ሁሉ አዳጋች አልነበረም። የአንጃው አባላት ሻእቢያን ከሚጠሉት ባላነሰ ሁኔታ በኤርትራ ህዝብ ላይ የመረረ ጥላቻ ነበራቸው።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አለምሰገድ ጥቂት የፕሮፓጋንዳ ሃላፊዎችን ሰብስቦ የነገረንም ሉአላዊነታችንን ስለ ማስከበር ሳይሆን፤ ቂም በቋጠረ ስሜት ክብርን ስለ ማስመለስ ነበር። እንዲህ እያለ፣

"ጦርነቱ ሲጀመር ወደ ኤርትራ ምድር ዘልቀን እንገባለን! ሻእቢያ ለክብሩ ሲል ወደ ኤርትራ ምድር መግባታችንን ይፋ አያደርግም። እኛም ድምፃችንን አጥፍተን አስመራ እንገባለን!"

ኢህአዴግ ኤርትራን ከተቆጣጠረ በሁዋላ የምንሰራውን የፕሮፓጋንዳ ስራ ደግሞ እንዲህ ሲል ነበር የገለፀልን፣

"በመላ ሃገሪቱ ህዝቡ ኢህአዴግን እንዲደግፍና በአፍሪቃ ቀንድ ኢህአዴግ የማይነካና የማይደፈር ህዝባዊ ሃይል መሆኑን እንቀሰቅሳለን! የህዝቡን ትኩስ ድጋፍ በቀጥታ ለድርጅታችን ጥቅም ልናውለው ይገባል። ኢህአዴግ አለኝታችን ነው። ኢህአዴግን ይዘን ማንኛውንም ችግር መፍታት እንችላለን ብሎ እንዲያምን እንቀሰቅሰዋለን"

ከዚህ ስብሰባ በሁዋላ በረከት ስምኦንን የተመለከተ አንዳንድ ወሬዎችን ከተከሉ ሰማሁ። በረከት የነ ስዬን ደም አፋሳሽ የውጊያ ፍላጎት አጥብቆ እየተቃወመ ነበር። በፖለቲካው ቢሮ በተደረገው ስብሰባ በረከት፣

"ደርግና ጃንሆይ ሞክረውት ያልተሳካላቸውን እኛ እንዴት ልንፈፅመው እንችላለን!? ከታሪክ መማር ይገባናል! የኤርትራን ህዝብ አርደንና ገድለን ኤርትራን እንቆጣጠር የምትሉ ከሆነ ደግሞ አሳባችሁን ግልፅ አድርጉ!" ሲል አቋሙን ከነገራቸው በሁዋላ በረከት ከነተወልደ ጋር የእግዚአብሄር ሰላምታ እንኳ ማቆሙን ተከሉ አጫውቶኝ ሲያበቃ፣

"በረከት ያለጥርጥር ሻእቢያ ነው" አለኝ።

"አይመስለኝም"

"አትጠራጠር፤ ሻእቢያ ነው"

"እንዴት ርግጠኛ መሆን ቻልክ?"

"በረከት ሻእቢያ ካልሆነ እንዴት ደፍሮ ተወልደን እንደዚያ ይናገረዋል? ተወልደ እኮ የኢህአዴግ አንጎል ማለት ነው"

ከተከሉ ጋር ማውራት ድካም መሆኑን እያወቅሁ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እኔም አያርመኝም።

* * *

የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት እነ ተወልደ እንዳልተመኙት ሆኖ ካበቃ በሁዋላ እነ ተወልደ ስራዬ ብለው ያስወሩ የነበረው "ከኤርትራ ጋር የተደረገውን ጦርነት የወታደራዊ ሳይንስና ጥበቦች እንዲሁም የወታደራዊ ዶክትሪኖች የነደፈው ፃድቃን ነው" የሚለውን ነበር። በተያያዘም መለስ በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ወቅት ለማስትሬት ዲግሪ የተልእኮ ጥናቱ ላይ አተኩሮ ነበር የሚል ወሬ ያሰራጩበት ነበር። የነመለስ ቡድን በበኩሉ "የውጊያውን እቅድ የነደፈው መለስ ነው" የሚል ፕሮፓጋንዳ አሰራጨ። ከሁለት አቅጣጫ የሚመጣውን ወሬ ስሰማ እኔ በበኩሌ አዝኜ ነበር።

ለመሆኑ የትኛው ወታደራዊ ጥበብ ተሰርቶ ነው ይህ ሁሉ ሙግት? 100 ሺህ ወጣት ወታደር ባንድ አዳር ማስጨፍጨፍ ነው ወታደራዊ ጥበብ? በአንደኛው የአለም ጦርነት የተፈፀመውን ሰራዊትን እንደ ጎርፍ ወደ እሳት የመማገድ ሁዋላቀር ወታደራዊ ስልት በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን ከቶ እንዴት እንደ ጀብድ ሊወሳ ይችላል?

በአጠቃላይ በጦርነቱ ስንት ኢትዮጵያዊ ተሰዋ? ስንት ቆሰለ? ለተሰዉት ቤተሰቦች ምን ተደረገ? የቆሰሉት ዛሬ የት ናቸው? መስዋእትነታቸው እንደ ፍየልና በግ ወዲያው የተረሳውስ የእነማን ልጆች ናቸው? ለመሳሰሉ ጥያቄዎች እነ ተወልደ መልስ ሳይሰጡ ተሰናብተዋል።

* * *

የሆነው ሆኖ መለስ በመጨረሻ እነ ተወልደ ከዘረጉለት ወጥመድ አምልጦ የስልጣን መንበሩን ማስከበር ችሎአል። መለስ ከሚደቀኑበት አደጋዎች እንዴት ሾልኮ ማምለጥ እንዳለበት የሚያውቅ ብልህ መሪ መሆኑ ይታመንለታል። እነ ተወልደ ካዘጋጁለት "ተንበርካኪነት" ከተባለች የአይጥ ወጥመድ ለማምለጥ ጥሩ ጥሩ ዘዴዎችን በመንደፍ ውጤቱን ተገላቢጦሽ ማድረግ የቻለ ሰው ነው።

ጦርነቱ ይካሄድ በነበረበት ጊዜ ሁሉ መለስ የሙስናን ወሬ በመላ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ካድሬዎች ይወራ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ዘንድ አሰራጨው። ብአዴኖች ዋና መሳሪያ ለመሆን ፈቃደኞች ነበሩ። ብአዴኖች በዚህ ጨዋታ በአንድ ልብ የተሳተፉት ግን እነ ተወልደ እንደሚሉት የመለስን የስልጣን እድሜ ለማራዘም አልነበረም። ብአዴኖች በአክራሪ የህወሃት አመራር አባላት ላይ የነበራቸውን የቆየ ቂም በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀሙበት የሚችሉ መስሎአቸው ነበር።

መለስ "የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ሆይ! የትግራ ጭራ መሆን በቃችሁ!" ሲል በስውር የላከላቸውን አምነውት እንደ ጥሩ ወታደር ተነቃነቁለት።

እነ መለስም ሆኑ እነ ተወልደ ግን ከህወሃት ባሻገር ያሉትን አባል ድርጅቶች እንደ ተላላኪዎች ከመቁጠር አንፃር ልዩነት አልነበራቸውም። በክፍፍሉ ወቅት ግን መለስ በተገቢው ሰአት በስሜታቸው ላይ ቂሌ ተጫወተባቸው። በበረከት ፈታውራሪነት የአባል ድርጅቶቹ አመራር አባላት፣ የሰራዊት ወኪሎችና ካድሬዎች እነ ተወልደ ላይ ዘመቱ። በዘመቻው ወቅት መለስ "ቦናፓርቲዝም" የተባለችውን ባንዲራ ለወታደሮቹ አስጨበጠ።

ቦናፓርቲዝም ምንድነው?

ጆሮዎች እንደ ጥንቸል ጆሮ ተቀሰሩ!

አዬ መለስ ዜናዊ! ነፍሱ አይማርም መቸም! "ቦናፓርቲዝም" የተባለውን ቃል እነ ተወልደ መሃል ወስዶ ቁጭ ሲያደርግላቸው አብዛኞቹ ቀደም ሲል ቃሉን ሰምተውት እንኳ አያውቁም ነበር አሉ። "እነ ተወልደ የቦናፓርቲዝምን ፍቺ ለማግኘት መፅሃፍ ፍለጋ ሲሯሯጡ፤ መለስና በረከት ጫት እየቃሙ ይስቁባቸው ነበር" ይልሃል ፒያሳ ቲሩም ላይ ቁጭ ያለ ተራቢ የግል ጋዜጠኛ።

እኔ ደግሞ ቀልድ ነው ብዬ ሳቅሁ፣

"ቀልድ መስሎህ ነው?"

"እና ታዲያ?"

"ይቅማሉ!"

"ውሸት ነው!"

"መለስና በረከት ዳዊት ቤት ይቅማሉ"

(*በርግጥ መለስ ጫት ሲቅም አይተን አናውቅም። የሚወራውን የሚያረጋግጥ መረጃ ግን ከደክተር ነጋሶ አገኝተናል። ነጋሶ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ በፃፉት መጣጥፍ*

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"በህወሃት ክፍፍል ዋዜማ በየጫት መቃሚያው Lobby ይደረግ ነበር" ሲሉ መግለፃቸው የኢህአዴግ አመራር የጫት መቃሚያ ዝንብኝ እንዳለው ጠቁሞናል። መቃሙንስ ይቃሙ፣ መብታቸው ነበር። ሲመረቅኑ ጠባያቸው ምን እንደሚሆን ባለማወቃችን ግን ያሳስበናል። መንግስቱ ሃይለማርያም አወዳይ የተባለውን ጫት ይቅም ነበር። ብዙውን ጊዜ ቅሞ ሲያበቃ ቤተመንግስት ከታሰሩት መካከል ጥቂት እየቆነጠረ ግንብ አስደግፎ በባለ ከዘራ ሽጉጡ ይረሸናቸው እንደበር ከአንጋቾቹ የምስክርነት ቃል አንብበናል። መንጌ ቴክሱ ቅሞ ሲመረቅን በአሉ ግርማ ዘንድ እየደወለ "ና ውሰኪ እንጠጣ" እያለ ያስቸግረው እንደነበርም ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚአብሄር አጫውተውናል። የዘመኖቹስ መርቅነው የወሰኑዋቸው ውሳኔዎች ምን ምን ይሆኑ?)

የሆነው ሆኖ እነ ተወልደ ቦናፓርቲዝምን አጥንተው ሲያበቁ አፀፋውን የቻሉትን ያህል ፃፉ! የፖሊት ቢሮው አባላት ባንድ ሌሊት ራሳቸውን ወደ ደራሲነት ለውጠው ሌሊቱን እየቃሙ ሲፅፉ እንደሚያድሩ ወሬ ስንሰማ ቀልድና እውነቱን መለየት እየተቸገርን ከአረቄ ጋር ልናወራርደው ስንሞክር እናመሻለን!

ያን ሰሞን የቦናፓርቲዝምን የመዝገበ ቃላት ፍቺ እፎይታ ጋዜጣ ላይ አተምነው፣

በረከት ደውሎ ተቆጣ፣

"ምንድነው ችግሩ?" ስል ጠየቅሁት።

"እነ ተወልደና አለምሰገድ ፍቺውን መረዳት ተቸግረው መድረክ ጥለው የወጡበትን ጉዳይ እንደዚህ አቅልላችሁ እንዴት ትፅፉታላችሁ? ጉዳዩን አትነካኩት!"

በጣም እየተገረምኩ ስልኩን ዘጋሁ።

በመሰረቱ የቦናፓርቲዝምን ፅንሰሃሳብ መገንዘብና አለመገንዘብ የልዩነታቸው መሰረት አልነበረም። እነ በረከት ግን የቦናፓርቲዝምን ፅንሰ ሃሳብ ከዚህ ቀደም ታይቶ እንደማይታወቅ ልዩ አውሬ እንደማስፈራሪያ ሊጠቀሙበት ፈልገው ነበር። አባላትም ቦናፓርቲዝም የተባለውን አውሬ ለማየት በጉጉት እየተጠባበቁ ቆዩ። ተገቢ ባሉት ጊዜም አውሬው ተለቀቀ።

"ቦናፓርቲዝም ናፖሊዮናዊ የቤተሰብ ፓርቲና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የቤተሰባዊ ገንዘብ መዝረፊያ ስልት ነው" የሚል ፈጣንና አጭር ትንታኔ ከየት እንደመጣ ሳይታወቅ የኢህአዴግ ካድሬዎችን ጆሮ አቃጠለ!

የቤተሰብ ፓርቲ!?

ያ ሁሉ ታጋይ የተሰዋለት ትግል ወደ ቤተሰብ የጥቅም ማህበር ሊለወጥ!? ያ ሁሉ የዋህ ገበሬ ህይወቱን የከፈለው የስዬ ቤተሰቦች እንዲንደላቀቁ ኖሮአል? እነ ስዬ ኢነትሬውን ሲያገላብጡ፤ የከተማው አልበቃ ብሎአቸው ተንቤን ገጠር ገብተው ቪላ ሲገነቡ፤ እንደ እንግሊዝ ቱጃሮች የገጠርና የከተማ ቤት እየለዩ ሲምነሸነሹ፤ መለስ ዜናዊ ምስኪን! መፅሃፍ ብቻ ንብረቱ! አወይ ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ ታበፅህ ኢደዊሃ ሃበ እግዚአብሄር - እንዲሉ። እንኳን ብቻ መለስ ዜናዊ ተወለደ!

የመለስ ደጋፊዎች እንዲህ ሲሉን ከረሙ።

በዚያው ሰሞን የጆርጅ ኦርዌል "Animal Farm" በፎቶ ኮፒ እየተባዛ በነፃ ታደለ። እንግሊዝኛ ለሚቸግራቸው ደግሞ የአማርኛው ትርጉም "የእንስሳት እድር" ተፈልጎ በየቢሮው ታደላቸው። ስለዚህ ጉዳይ ቀደም ብለው ሰምተው የማያውቁት ግራ ተጋብተው ጥያቄ አቀረቡ፣

"ምንድነው ይሄ?"

"የአሳማዎች፣ የውሾችና የአህዮች ታሪክ"

"ማነው አሳማ? ማነው ውሻ? ማነው አህያ?"

"ባጭሩ አንተ አሳማ ጠባቂ ውሻ ነህ!"

የግል ጋዜጦች አዘጋጆች ቲ-ሩም ላይ ሲያገኙን እኛ የኢህአዴግ ጋዜጠኞች ላይ ይስቁብን ጀመር። ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይስቃሉ። የፕሬስ ድርጅቱ ተክሉ እንደሚለው ድምፅን ከፍ አድርጎ መሳቅ መከልከል ነበረበት። ጋዜጣቸውን እንደ መሃረብ ይዘው፤ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው መሳቅ! እኛ እንድንሰማ አድርገው ደግሞ ያወራሉ፣

"እነማን ናቸው የተወገዱት?"

"ስዬ - ተወልደ - አለምሰገድ..."

የሆነው ሆኖ መለስ ዜናዊ በመጨረሻ የተፈፀመውን ፈፀመና የጨዋታው ማብቂያ ሆነ።

እነ መለስ የተከፋፈሉበት የመጨረሻው ስብሰባ ሂልተን ሆቴል ነበር የተካሄደው ይባላል። ሂልተን ለስብሰባ የተመረጠው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በመካከላቸው ቦምብ መፈንዳቱ እንደማይቀር በመረዳታቸው ነበር። እነ ተወልደ ቤተመንግስቱን አላመኑትም። ዘግይቶ እንደወጣው ምስጢር ከሆነ ደግሞ የስብሰባ አዳራሹ በCIA ስውር የምስልና የድምፅ ቀረፃ ክትትል ስር ነበር። እነ ተወልደ ኮሚንስቶች መሆናቸውን መለስ አሜሪካኖችን በማሳመኑ ስብሰባውን በቅርቡ ይከታተሉ ዘንድ ተስማምተው እንደነበር Paltalk ላይ alama 111 የተባለች ሴት ስትናገር ሰምቼያለሁ።

(*ርግጥ ነው የ Paltalk ወሬ ሁሉ አይታመንም። alama 111 ግን የምትታወቅና የምትታመን የኢህአፓ የቆየች ታጋይ ስትሆን፣ መረጃዎችን ያቀረበችልን ምንጭ ጠቅሳ እንደነበር አስታውሳለሁ።*)

በሂልተኑ ስብሰባ በድምፅ እነተወልደ አሸንፈው ቢሆን ኖሮም ታሪክ ባልተቀየረ ነበር። መለስ በአሜሪካኖች የቅርብ እርዳታ አንጃውን አፍኖም ቢሆን ያስወግደው እንደነበር ሂደቱን በቅርብ የተከታተሉ የፖለቲካ ተንታኞች ፅፈው አንብቤያለሁ።

በህወሃት ክፍፍል ወቅት "መለስ ትግራይ ላይ ድጋፍ ያገኛል" ብሎ የገመተ አልነበረም። "ለእናቱ አገር ለኤርትራ አዘነበለ!" ተብሎ በህቡእ ስለተቀሰቀሰበት የትግራይ ህዝብ ከነተወልደ ጎን ይሰለፋል ተብሎ ተጠብቆ ነበር። ኮሽታ እንኳ ሳይሰማ ገብሩና አረጋሽ፣ "ፎጣ በትከሻ!" ተባሉ። እነ ተወልደ በህቡእ ዘርግተናል ያሉት ድርጅታዊ ስራም አድራሻውን ሳይሰጥ የገባበት ጠፋ። በመጨረሻ መለስ የክፍፍሉን ድራማ የዘጋው የኦህዴድንና የመከላከያን ድጋፍ ለማጠናከር በወሰደው ርምጃ ነው። ይህንኑም ከክንፈ ጋር ቁጭ ብለው እንደተመካከሩበት ዝርዝር መረጃ አለኝ።

ህወሃት ከተዳከመ ብአዴን ወደ እናት ድርጅቱ ወደ ኢህአፓ ጓዳ ሊገባ እንደሚችል ግምታዊ የፖለቲካ ትንተና አስቀመጡ። የብአዴንን ድጋፍ ብቻ ማመን ያለውን አደጋ አሸተቱ። የደቡብ ህዝቦች ገና "ሁኔታው ያልታወቀ" ቢሆንም፣ ለጊዜው "የትም አይሄድም" ተብሎ ፋይሉ ወደ ጎን ተገፍቶአል። ደቡብ ሲባል እነ መለስ ካሱ ይላላ ብቻ ነው ትዝ የሚላቸው። ስለዚህ ሽኩቻውን ለመደምደም የኦህዴድንና የመከላከያን ሁኔታ ማሻሻል ቅድሚያ ተሰጠው።

የመከላከያ ጉዳይ ቀደም ተብሎ ጆሮሮ በሽውራራ ፖሊሲ የተዳከመ ሆኖ ቆይቶአል። መለስ በመከላከያ ላይ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ያለው አመለካከት ከአስገራሚነት በላይ አሳዛኝ ነው። አንድ አብነት አንስቶ ማየቱም መከላከያ ማን መሆኑን እንድንገነዘብ፣ የተከዜዎችን ሚናም እንድንገነዘብ ያደርገናል።

የአፍሪቃ አምባገነን መንግስታት በብዛት በወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት የተገኙና የሚገኙ እንደመሆናቸው፣ መንግስታት ሁሉ ታማኝ ጀኔራሎችን መሾም እንደመፍትሄ የያዙት አሰራር ነው። የመለስ ዜናዊ አስተዳደር ግን ታማኝ ጀኔራሎችን መሾም ብቻውን የመቆጣጠሪያ ዘዴ ሊሆን አይችልም ብሎ ያምናል።

በ1987 በተደረገ መከላከያ ነክ ስብሰባ ላይ የስልጣንና የማእረግ ክፍፍል ከተደረገ በሁዋላ፣ "ምን አይነት ሰራዊት ይኑረን?" የሚል ጥያቄ ተነስቶ ክርክር መደረጉን በቅርብ የማወቅ እድል አጊንቼያለሁ። አብዛኞቹ የመከላከያ ቀደምት ሃላፊዎች ፈራ ተባ እያሉ ያኘጎደጎዱትን ውል አልባ ዲስኩር ወደ ጎን ልተወውና መለስ ዜናዊ ያራመደውን አቋም ላውጋችሁ። አጀንዳውን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ፣ ውይይቱ የተካሄደው ፕሮፌሽናል ቋሚ ሰራዊት የመገንባት አስፈላጊነት ላይ በማተኮር ነበር። "ዘመናዊ ተዋጊ መሪዎችና ሰራዊት ለማፍራት ደረጃውን የጠበቀ የመከላከያ የስልጠና ማእከሎችና የጦር አካዳሚዎች ያስፈልጉናል" የሚል አሳብ በተነሳ ጊዜ መለስ ስሜታዊ ሆነ። መለስ የተናገረውን ቃል በቃል ከማስታወሻ ደብተሬ ላይ ላስነብባችሁ።

"...ኢትዮጵያ Elite ሰራዊት አያስፈልጋትም። ንጉሱ ከአቅሙ በላይ Elite ሰራዊት ገንብቶ ተበላ። ደርግም Elite ሰራዊት ገንብቶ ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግስት እየተካሄደበት፣ እባብ ለእባብ እየሆነ ካብ ለካብ ሲነዳደፍ ኖረ። በጠበበ እድል እያከሸፈው ከመበላት ተረፈ እንጂ የንጉሱ እጣ ይገጥመው ነበር። እኛ ከዚህ መማር አለብን። Elite ሰራዊት አያስፈልገንም። Elite ሰራዊት ጨፍጫፊ ነው የሚሆነው። ብሄራዊ ተዋፆው የተጠበቀ፣ ህዝቡ ያገኘው ድል ላይ የማያምፅ፣ እንዲጠብቀው የፈጠረውን ስርአት መልሶ የማይበላ ሰራዊት ነው መገንባት ያለበት። በተለይም አየር ሃይሉ ሃይል ሆኖ መቀጠል የለበትም። የዚህች ሃገር አቅም አየር ሃይልን ሊሸከም አይችልም። አየር ሃይል የመከላከያ አንድ ክፍል ሆኖ የትራንስፖርት ክፍሉን ብቻ ነው ማጠናከር ያለበት። በአየር ሃይል የተሸነፉ ጠላት አላየንም።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሃይል ማለት ራሱን ችሎ አንድን ግዳጅ የሚወጣ ነው። ጥይት እያቀረበና ቁስለኛ እያገለለ ብቻ ሃይል ነኝ እያለ ሊኖር የሚገባ ሃይል አያስፈልገንም። ሃገሪቱ አደጋ ላይ ከወደቀች ድሮም እንደሚያደርገው ህዝቡ ራሱን ለመከላከል ይችላል"

መለስ ይህን ከተናገረ በሁዋላ ስለ ጦር አካዳሚ፣ ስለ ሰራዊት ጥራት፣ ስለ ምሁር መኮንኖች ሲያወሩ የነበሩት ሁሉ ተገልብጠው ስለ መንግስቱ ንዋይ ክህደት፣ ስለነ መርእድ ንጉሴ እብደት፣ እያስታወሱ የመለስን ትንተና አወድሰው አጀንዳው ተዘጋ። በአባይ ውሃ ጣጣ ማለቂያ በሌለው ስጋት ውስጥ የምትኖረው ኢትዮጵያ፣ በዙሪያዋ ያሉ የቅርብና የሩቅ ባላንጣዎቿ የኒውክሊዬር ላቦራቷሪ አቋቁመው ምርምር በገቡበት በዚህ ጊዜ፣ መለስ አደጋ ከመጣ እንደወትሮው ገበሬ አገሩን ይከላከላል ይለናል። ካርታ ዘርግቶ ያለበትን ቦታ በስሌት ማሳየት የማይችል ጀኔራል፣ የከፍተኛ መኮንንነት ማእረግ ለሾፌርና ከዚያም በታች ላለ ባለሙያ የሚሰጥባት ሃገር ከኢትዮጵያ ሌላ የት ይገኛል?

በህወሃት ክፍፍል ወቅት መለስ የሰራዊቱንና የአህዴድን ሁኔታ በቀላሉ እንደሚሻሻል ያመነው በእነማንና እንዴት አዳክሞ እንዳዋቀረው ስለሚያውቅ ነበር። ስለዚህ ክንፈን ጠርቶ እንዲህ አለው፣

"እኔ መኮንኖቹን እሰበስባለሁ። አህዴድ ያንተ ውልድ ስለሆነ ምን ልታደርግ ትችላለህ?"

ክንፈም እንዲህ ሲል ይመልሳል፣

"አህዴድ አሁን በህይወት የለም። ጥቂት ስትንፋስ ዘርተንበት ግን ልናንቀሳቅሰው እንችላለን። የአመራር አባላቱ ጠንክረው ከጎናችን ባይቆሙም እያሻሻሉ ሊሄዱ ይችላሉ"

በዚህ መሰረት የስራ ክፍፍል አደረጉ። ክንፈ የአህዴድ አመራር አባላትን ሰብስቦ እንዲያነጋግር፣ መለስ ደግሞ የመከላከያ መኮንኖችን እንዲሰበስብ ወሰነው ተለያዩ። በስብሰባው ላይ መገኘት ያለባቸውን የሚመለምሉበትን መስፈርትም ቁጭ ብለው ነደፉ። ስብሰባው በሚጀመርበት እለት ግን እንደታቀደው አልተፈፀመም። ክንፈ ወደ መኮንኖቹ ሄደ። መለስ ደግሞ ወደ አህዴድ አመራር ገባ። ይህ ለውጥ የተደረገው በስብሰባው እለት ማለዳ ሲሆን፣ ባለቀ ሰአት ይህ ለውጥ የመጣበትን ምክንያት፣ ከክንፈና ከመለስ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በቀር ሊያውቅ የሚችል የለም። መለስ ኦህዴዶችን በሰበሰበበት ማለዳ ግን ለውጥ መደረጉን ነግሮአቸዋል። የሁለቱም ወገን ተሰብሳቢዎች በአዳራሹ በተገኙበት ደቂቃ ነበር መድረኩ በማን እንደሚመራ ያወቁት። የሆነው ሆኖ ክንፈ በመኮንኖቹ ስብሰባ ላይ ተገደለ።

ክንፈ በተገደለበት እለት መለስ ዜናዊ የኦህዴድ አመራር አባላትን ሰብስቦ በፕሮግራም በተያዘው መሰረት ስብሰባውን ማካሄዱ ተሰምቶአል። የመለስና የክንፈን የመድረክ መሪነት ቦታ መለዋወጥ እንደ ጠቋሚ መነሻ በመያዝ፣ "በክንፈ መሞት የመለስ እጅ ሊኖርበት ይችላል" ብለው አጥብቀው የሚጠረጥሩ ጥቂት አይደሉም። የዚህ መፅሃፍ ደራሲ ግን ይህን ጥርጣሬ አይጋራውም። በክንፈና በመለስ መካከልም ለመጠፋፋት የሚያበቃ ልዩነት ስለመከሰቱ ሰምተን አናውቅም።

የሆነው ሆኖ መለስ፣ "የደጋፊ ያለህ!" እያለ የእውር ድንብሩን ሲባዝን፣ ቀፎአቸው የፈረሰባቸው የኦህዴድ አመራር አባላትም እናታቸው እንደጠፋችባቸው ጫጩቶች ተበታትነው ሲንጫጩ መንገድ ላይ ተገናኙ። ሁለቱም ከዚያ የተሻለ የሚያስተሳስር አጋጣሚ ሊያገኙ እንደማይችሉ በመረዳት ተቃቀፉ። ኩማና አባዱላ፣ ፃድቃንና ተወልደን እያወዛዙ፣ "ማረን አባሆራ!" እያሉ የመለስ እግር ላይ ተጠመጠሙበት። የኦሮሞን ህዝብ ማፈናቸውን ለመቀጠልም እንደገና መሃላቸውን ፈፀሙ። ምን ቀረ? ምንም! ያ መምህር ምን ነበር ያለው? "ታዳጊዎች ሆይ! ኮካኮላ ከመሆን ያድናችሁ!"

ከአንጃው መወገድ በሁዋላ የእነ ተወልደ ስም ቀስ በቀስ መረሳት ጀመረ።

እነ ተወልደ "አንጃ" ተብለው ከተፈረጁና ከህወሃት ከተወገዱ በሁዋላ ቀሪውን የአመራር አባል፣ "የቤተመንግስት ቡድን" የሚል ስያሜ ሰጥተውት ነበር። የተራውን አባል ተራ ድጋፍ ለማግኘት የመረጡት ቅፅል ስም ይመስላል። በተረፈ ግን መለስ መሪ ስለሆነ የግድ ቤተመንግስት ውስጥ ይኖራል። ከታሪካችንና ከልምዳችን አንፃር ቤተመንግስት ሲባል ምቾት፣ ገንዘነት፣ አምባገንንት አብረው ይታሰባሉና ፍላጎታቸው እነ መለስ በዚያ መነፅር እንዲታዩ ነበር። የያዘላቸው አይመስልም።

የሆነው ሆኖ እነ መለስ እንደገና ማንሰራራት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ችለዋል። ፈተናቸው ግን አላበቃ ኖሮ “ቅንጅት” የተባለ ሌላ ራስ ምታት ህዝበ - ሰራዊቱን ይዞ ተጋፈጣቸው። ያ ዘመን ለነ ተወልደ የጨለማ ዘመን ተብሎ ይታወቃል። ቅንጅት ተገድሎና ታስሮ አረፍ ከማለቱ ደግሞ እነ ተወልደ “አረና” የተባለ ስም አስቀድመው “ተመልሰናል” ሲሉ አውጀዋል። የኤርትራ ስምም ከዘመን ዘመን እንደ ጨውና በርበሬ የፖለቲካ ማጣፈጫ እንደሆነ ቀጥሎአል...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 14 -
ክንፈ! የፀጥታው ሹም

ጠዋት ብትታይም – ፀሃይ ከፍ ብላ፣
የማታ የማታ – እርስዋም አሽቆልቁላ፣
አይቀርም መጥለቋ – አይቀርም መውረዷ፣
ብርሃኗን ሰውራ – ካይን መጋረዷ፣

(ማጥም – ሻምበል አፈወርቅ ዮሃንስ)

ከምላክ ነፍሱን ይማረው...

የፀጥታው መስሪያ ቤት ሹም ክንፈ ገብረመድህን ሲገደል እኔ ናይሮቢ ነበርኩ።

የወሬ ወሬ እንደሰማሁት በክንፈና በገዳዩ በሻለቃ ፀሃዬ መካከል አለመግባባት የተጀመረው ክንፈ የሃይል 22 የመቶ መሪ ሳለ ሲሆን፣ በዚያን ወቅት ደግሞ ፀሃዬ በክንፈ ሃይል ውስጥ ተራ ተዋጊ ነበር። ወደ ትግል አንድ ላይ የገቡ ነበሩም ይባላል። ክንፈ ግን በፍጥነቱም ሆነ በእውቀቱ ፀሃዬን ጣጥሎት ቁንጮው ላይ ደረሰ። በስዬ አብርሃ የሚመካ አይነት ሰው ነበርም አሉ ፀሃዬ። ክንፈን እንደ ማርያም ጠላት ከጠመደው ዘመናት አልነበረውም። ሁዋላ ጊዜና ዘመን ሲለዋወጥ እነስዬን መሬቱም

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ድርጅቱም ከዳቸው። በዚያን ሰሞን እነ ስዬን በቁጥጥር ስር በማዋሉ ረገድ ቁልፍ ሚና የሚጫወተው "የመለስ ክንፍ" ተብሎ የሚታወቀው ክንፈ ነው ተብሎ ሲወራ ሰንብቶአል። በዚያኑ ሰሞንም ክፍፍሉን ለማርገብ ክንፈ የመከላከያ መኮንኖችን እንዲያግባባ ይታዘዛል። ክንፈ በመኮንኖች ክበብ ሲካሄድ የነበረውን ስብሰባ ተቆጣጥሮ ለመሄድ ጥረት በማድረግ ላይ እንደነበር በስብሰባው የተካፈሉ መኮንኖች ይገልፃሉ።

የጄኔራል ጆቤ ሚስት ኮሎኔል ናት።

"እንዴት ርስበራስ ትገዳደላላችሁ?" ስትል እያለቀሰች ባደረገችው ንግግር የትግራይ መኮንኖችን ቀልብ መያዝ ችላ እንደነበር ይነገራል።

ኮሎኔል ጥጋቡ የተባለ መኮንን፣ ህወሃት ፍትህ በጎደለው ሁኔታ ኢኮኖሚውን ተቆጣጥሮ፣ ሃገሪቱን የግል መጠቀሚያ እያደረጋት መሆኑን በመግለፅ እስከመጨረሻው ተከራክሮ በልዩነት መውጣቱን የሰማሁ ሲሆን፣ ጄኔራል አለምሸት ደግሞ እንዲህ ሲል ተናገሮአል፣

"አቅም የላቸውም ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። ሆኖም እዚህ ያለነው ኦሮሞ መኮንኖች አዳራሹን ጥለን ልንወጣ እንችላለን"

ገመቹ የተባለ ኮሎኔል የተናገረውንም ሰምቼዋለሁ፣

"ክንፈ! 22 ሺህ ኦሮሞዎች ባንተ መስሪያ ቤት ትእዛዝ ታስረዋል! ስም ዝርዝራቸውን ይዤያለሁ!" ሲል አፋጠጠው። አያያዘናም ቀጠለ፣ "...ክንፈ! ይሄ ልጅ ማን እንደሆንኩ አያውቅም፣ ሞኝ ነው ብለህ እንዳትስቅ። ይህን የምናገርህ ዛሬ ሌሊት ልታሳፍነኝ እንደምትችል እያወቅሁ ነው። እደግምልሃለሁ! ኦሮሞ በኦሮሞነቱ ብቻ ለምን ይታሰራል?"

ክንፈ ከኦሮሞ መኮንኖች የወረደውን ወቀሳ ያለማመንታት እንደተቀበለውና፣

"ተጠያቂው የኔ መስሪያ ቤት ነው፤ የኦሮሞ ህዝብ ይቅርታ ያደርግልኛል" በማለት ቁጣዎችን ለማብረድ ሞክሮአል።

ነፃ ገበያን አስመልክቶ በተነሳው ውይይት ላይ ግን ክንፈና ፀሃዬ በመረረ ሁኔታ ተጋጩ። የሲሚንቶ እጥረትና የፋብሪካዎቹ ጉዳይ እንደ ምሳሌ በተወሳበት ውይይት ላይ ፀሃዬ፣

"የሲሚንቶ እጥረት ባለበት ሃገር እንዴት ስለ ነፃ ገበያ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እናወራለን? ያንድ ሃገር ኩባንያዎችስ እንዴት ይወዳደራሉ?" ሲል ይጠይቃል።

ክንፉ የፀሃዬን አፍ ለማዘጋት፣

"ለስሙ ቢዝነስ ተምሬያለሁ ትላለህ፤ ይህን እንኳ መረዳት ቸግሮሃል!" ሲል ሃይለ ቃል ተናገረው።

ተሰብሳቢው ሳቀ።

ፀሃዬ ከክንፉ አስፀያፊ ንግግር በሁዋላ እንደተሸማቀቀና ድምፁን እንዳጠፋ ይነገራል። ይህ ንግግር ብቻ ክንፉን ለሞት አብቅቶታል ለማለት ግን አይቻልም። ፀሃዬ ክንፉን ለመግደል ያደፋፈረው ዋናው ምክንያት የክንፉ መመታት ግላዊ ሳይሆን፤ ፖለቲካዊ መልክ ሊይዝለት እንደሚችል የተሳሳተ ስሌት ላይ በመድረሱ ነው የሚሉ አሉ። እነ ስዬና ተወልደ ያሻቸውን ያህል ከመለስና ከክንፉ ጋር በከረረ ፀብ ላይ የሰነበቱ ቢሆንም፤ እስከ መገዳደል የሚያደርስ ሁኔታ ላይ አለመሆናቸውን ማንም ውስጥ አዋቂ ይረዳው ነበር። ቢገዳደሉ የአማራ ተቃዋሚዎች ወይም አነግ ዘለው ቤተመንግስት እንደሚገቡባቸው ስለሚያውቁ፤ ቢሻኩቱም ስልጣኑ ወደነሱ ያለችግር እንደሚተላለፍ ሳያረጋግጡ መለስን ከስልጣኑ ሊነኩት አይሹም ነበር። 'ከመለስ ተወልደ ይሻለናል' ነው ጠባቸው እንጂ ብርቱካን ሚደቅሳን ስልጣን ላይ ማየት ከቶ አይሹም። ፀሃዬ ክንፉን በመግደል አጀንዳውን ፖለቲካዊ ለማድረግ የሞከረበት መንገድ ስህተት የሚሆነው በዚህ መነሻ ነበር።

የሆነው ሆኖ ክንፉ ተገደለ።

በክንፉ ቀብር እለት አበበ ወርቁ የተባሉት የህግ ሰው "ክንፉ ደግ፣ ተግባቢ፣ ቢሮውን ለማንኛውም ዜጋ ክፍት ያደርግ የነበረ፣ ድንቅ ሰው" እንደነበር በጀርመን ሬድዮ ሲናገሩ ሰምቼ ሳልገረም አልቀረሁም። ክንፉ በርግጥም ጥሩ ሰው ነበር። የህወሃትን የሰብአዊ መብት አያያዝ አጥብቆ ያወግዝ ከነበረው ከአበበ ወርቁ ያንን መስማቱ ነበር ያስገረመኝ።

ከክንፉ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅነው አዴት ከተባለ የትግራይ ገደላማ በረሃ ውስጥ በአህዴድ ምስረታ ላይ ነበር። ጋዜጠኛ መሆኔን በመስማቱ ወዳረፈበት ድንኳን አስጠርቶኝ ጥቂት አወጋን፣ "መፅሃፈ ሲራክን ታውቀዋለህ?" ሲል ነበር በቅድሚያ የጠየቀኝ። በዚያው የወሬ መነሻ ነበር የተግባባነው። ይህ ትረካ የአንድ ጋዜጠኛ እለታዊ ማስታወሻ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መሆኑን ላስታውስና ትረካዬን ልቀጥል።

* * *

ከእለታት አንድ ቀን አሰፋ ማሩ ተገደለ።

ፖሊሶች ግንብ አስደግፈው የጥይት እሩምታ አወረዱበት። የግል ጋዜጦች ድርጊቱን በመኮንን እሪታቸው በዛ። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በአደባባይ ተቃውሞአቸውን አሰሙ! ከመምህራን ማህበር አመራር አባላት አንዱ የነበረው አሰፋ ማሩ ለምን ተገደለ? ፖሊስ የገለፀው 'እጅህን ስጥ' ሲባል አሻፈረኝ በማለቱ ነው። አስቂኙን ምክንያት ያመነ አልነበረም። አሰፋ ማሩ ሳምሶናይቱን አንጠልጥሎ ከቤቱ ወደ ስራ በእግሩ ይጉዋዝ ነበር። መሮጫና መደበቂያ በሌለው ግንብ ጥግ ስር ከአምስት ያላነሱ የታጠቁ ፖሊሶች በአረንጉዋዴ የፖሊስ ላንድሮቨር መንገድ ዘግተው 'እጅህን ስጥ' አሉት። አሰፋ ማሩ ከቶ በምን ስሌት ነው እጁን ለመስጠት ፈቃደኛ የማይሆነው?

ዞረም ቀረ አሰፋ ማሩ ተገደለ።

ያን ሰሞን ክንፈን አገኘሁትና መረጃ ጠየቅሁት። ከፖሊስ መግለጫ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ታሪክ ደገመልኝ። ሊነግረኝ አልፈለገም። እንደገና በዚያው ሰሞን ከስዩም መስፍን ጋር ለስራ ጉዳይ ተገናኝተን ስራዬን ካበቃሁ በሁዋላ የአሰፋ ማሩን ጉዳይ አነሳሁለት። እንግሊዝ የአሰፋ ማሩ መገደል አንገብግቧት ነበር። አምባሳደሯን ጭምር ጠርታለች። ጀምራው የነበረውን የፖሊስ ስልጠና አቋርጣለች። ከማንም ሃገር በላይ ተቃውሞዋን እየገለፀች ነበር!

"ምንድንነው ይህ ሁሉ የእንግሊዝ ፉከራ?" ስል ጠየቅሁት።

"አሰፋ ማሩ ሰላያቸው ነበር" አለኝ ስዩም።

ከጥቂት ዝምታ በሁዋላ፣

"ሁኔታው ታዲያ ወዴት እያመራ ነው?" ስል በስጋት ጠየቅሁት።

ስዩም መስፍን ፈገግ አለና፣

"የሚሰጡትን ርዳታ ሁሉ እንደሚያቋርጡ ነግረውኝ ነበር። 'እኛ ድሃ ነን፣ ብትረዱን ደስ ይለናል፤ የለም እጃችንን አስገብተን ካላቦካን እርዳታ አንሰጥም የምትሉ ከሆነ ደግሞ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ርዳታችሁ ይቅርብን እንጂ በውስጥ ጉዳያችን እጃችሁን እንድትከቱ አንፈቅድላችሁም' የሚል መልስ ላኩላቸው። የአፄ ቴዎድሮስ ዘመዶች እንደሆንን አስታወሱ መሰለኝ አሁን ደግሞ ረገብ ማለት ጀምረዋል!"

* * *

ሌላ ቀን ደግሞ ክንፉ በአስቸኩዋይ ወደ ቢሮው አስጠራኝና በደቂቃዎች ጊዜ ውስጥ ቢሮው ተገኘሁ። ከመሳቢያው ሁለት ገፅ ወረቀት አወጣና 'አንብበው!' ሲል ሰጠኝ። አነበብኩት። በእጅ የተፃፈ እንደ ቆሎ ልቅም ያለ የቄስ ፅሀፊት ነበር። ደብዳቤው ከፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ለሃረሪ ክልል የመአህድ ተወካይ የተፃፈ ነበር። ባጭሩ ይዘቱ እንዲህ ይላል "ሃረሪዎች ከወያኔዎች ጋር አብረው አማራውን የማፈናቀል ስራ እየሰሩ መሆናቸውን እየሰማን ስለሆነ፤ ስለዚሁ ጉዳይ አጣርታችሁ መረጃዎችን ላኩልን"

አንብቤ ካበቃሁ በሁዋላ ክንፉ፣

"በፖስታ ቤት ደረሰን ብለህ መፅሄቱ ላይ አትመው!" አለኝ።

"አንተ ግን ከየት አገኘሽው?" ስል ጠየቅሁት።

"በዱርዬ ቦርሳቸውን አስቀማናቸውና እዚያ ውስጥ አገኘነው"

"የደብዳቤው ይፋ መሆን ጥቅምስ ምንድነው?"

"ሃረሪዎች ይህን እንዲያውቁ እንፈልጋለን" አለኝ።

እያዘንኩ የክንፉን ቢሮ ለቅቄ ወጣሁ። የኒኮሎ ማኪያቬሊን ከፋፍሎ የመግዛት ስልት ይበልጥ ተጠግቼ ያየሁት ያን ቀን ነበር። ደብዳቤውን መፅሄታችን ላይ አተምነው። የጠየቀንም የከሰሰንም የለም! ሰማይ አይታረስም....

(ዘግይቼ እንዳረጋገጥኩት አማራዎች ሃረርን ለቀው እንዲሸሹ የተለያዩ ድራማዎች ይሰሩ ነበር። የደህንነቱ መስሪያ ቤት ከሃረሪ ክልል ጋር በመተባበር ከፊፀማቸው አማሮችን የማስበርገግ ወንጀሎች መካከል አቶ ደጀኔ በቀለ በተባሉ የደሴ ሆቴል ባለቤት ላይ የተፈፀመው አሰቃቂ ግፍ ሁነኛ አስረጅ ነበር። ግለሰቡ ያልሞተን ሰው እንደገደሉ ተደርጎ በደረሰባቸው ድብደባ ከነቤተሰባቸው ለአካል ጉዳት የተዳረጉ ሲሆን፣ ከ400

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሺህ ብር በላይ ኪሳራና ቋሚ ንብረታቸውን እንዲያጡ ተደርገዋል። በገንዘብ ተደልሎ ሞተ የተባለው ሰው አለመሞቱ ከተረጋገጠ በሁዋላ፣ ለማስመሰል እንኳ የእርማት ርምጃ አልተወሰደም።)

* * *

አንድ ጊዜ 15 ኮንቴይነሮች ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ከጉምሩክ ስለመውጣታቸው የዜና ጥቆማ ሲደርሰኝ ትልቅ ዜና ያገኘሁ መስሎኝ ነበር። ክንፈ ዘንድ ደወልኩና ስነግረው፣

"መረጃውን የሚያውቀውን ሰው አንተ ዘንድ ይዘኸው ቆይ! ሰው እልክልሃለሁ" አለኝ።

ከደህንነት መስሪያ ቤት ሁለት ሰዎች ወደኔ ቢሮ መጡ። መረጃውን የሚያውቀውን ነጋዴ አግባብቼ ክንፈ ከላካቸው ሰዎች ጋር አገናኝሁት። በነጋታው ባለመረጃውን አግኝቼው ቡና እየጠጣን ወሬውን እንዲነግረኝ ሳጣድፈው እሱ ይስቅ ነበር፤

"ምንድን ነው ጉዳዩ?" ስል በጉጉት ጠየቅኩት።

"የናንተው ሰዎች ንብረት ነው" ሲል ዱብ እዳ አፈነዳብኝ።

"እና!?'

"መረጃ የማግኘት ችሎታህን እናደንቃለን! ለወደፊቱም አብረን እንሰራለን! ይህን ግን ለማንም እንዳታወራ!' አሉኝ"

ይህን ሰው ከስድስት ወራት በሁዋላ በሃብት ላይ ሃብት እየጨመረ ሲሄድ በአይኔ ያየሁት ሲሆን፤ ከእኔም እየራቀ ሄደ። ከደህንነት ሰዎች ጋርም በተደጋጋሚ አየው ጀመር። የነክንፈ ባልደረባ ሆኖ መቀጠሉን ተረዳሁ።

* * *

"ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ" የሚለውን ተከታታይ የትግል ታሪክ ትረካ ማዘጋጀት ጀመርኩ። ይህን ተከታታይ እትም ማተም በመጀመሬ የተፀፀትኩት ሶስተኛው ቅፅ እንደታተመ ነበር። "ለምን?" ቢባል ክንፈና አለምሰገድ የተዛባ ታሪክ እንዳትም ያስገድዱኝ ጀመር። በተለይ የሙሴና የስሁል አሚሚት ሚስጥር አወዛጋቢ ሆኖ ነበር። የዶክተር አታክልቲም አገዳደል እንዲሁ!

ሙሴ በስዬ አብርሃ ይመራ ከነበረ የሃይል 41 ተኳሾች

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከጀርባ ተገድሎ ሳለ፤ በኢዲዩ ጥይት እንደተገደለ ተደርጎ የሚወራበት ምክንያት እስከዛሬ ድረስ ለብዙዎች ምስጢር እንደሆነ አምናለሁ። የሙሴ ገዳይ በርሄ ሃጎስ የሚባል ሲሆን አሁን ካናዳ ይገኛል። በርሄ በስዬ በሚመራው ሃይል 41 ውስጥ ተራ ተዋጊ የነበረ ሲሆን፤ ከሙሴ መገደል በሁዋላ የወሬው ጭምጭምታ መናፈስ በመጀመሩ ወደ ሱዳን እንዲኮበልል ተደረገ። ሙሴ በመላ ሰራዊቱ የተወደደና ያለ ሙሴ መሪ የለም ተብሎ ይታመን ስለነበር በተራ የስልጣን ሽሚያ ሰለባ የሆነ ታጋይ ነው ብለው የሚያምኑ አሉ።

(በህወሃት ምስረታ ሰሞን "ህንፍሽፍሽ" ተብሎ የሚታወቅ ከፍተኛ የስልጣን ሽኩቻ እንደነበር ይታወቃል። ሙሴ የሻእቢያ ታጋይ የነበረ በመሆኑ ራሱን እንደ አመራር አባል ማየት የማይፈልግ የነበረ ቢሆንም፤ ሰራዊቱ ሙሴን መተኪያ እንደሌለው ብቸኛ መሪ ማየት በመጀመሩ ደስተኛ ያልነበሩ የአመራር አባላት ነበሩ።)

ሙሴ የተገደለበትን ምክንያት ከተጋድሎ ሃርነት ትግራይ (TLF) አመራር አባላት መረሸን ጋር የሚያያይዙትም አሉ። ህወሃት ለተጋድሎ ሃርነት ትግራይ "ውህደት እንፈፅም" ሲል ለእርቅና ለድርድር ጥሪ ያቀርብና በአንድ ወንዝ ዳር ይቀጣጠራሉ። ህዳር ወር 1968 ነበር ጊዜው። ሌሊት ስዩም መስፍንና መለስ ዜናዊ በሰጡት ትእዛዝ የተጋድሎ ሃርነት ትግራይ ታጋዮች በተኙበት ተረሸኑ። ይህን ዜና ስብሃት ነጋ ለሙሴ በነገረው ጊዜ ሙሴ ሁለት እጁን ራሱ ላይ አኑሮ መሬት ላይ ቁጭ እንዳለና ክፉኛ እንዳዘነ ከስብሃት ነጋ ተተርኮልኛል። ሙሴ ከጀርባ ተመቶ የተገደለበት ምክንያት በዚህ የተቃውሞ አመለካከቱ መሆኑን የሚገልፁም አሉ።

ሙሴ ከመሞቱ በፊት ሆን ተብሎ ከጀርባ ተመትቶ በገዛ ወገኖቹ እንደተገደለ ተገንዝቦ የነበረ ሲሆን፤ አጠገቡ ለነበሩት ለነአውአሎምና ሃየሎም ይህንኑ እየነገራቸው እንዳፅናናቸው፤ በወቅቱ ለዚህ ታሪክ ቅርብ ከነበሩት ከአውአሎምና ከአሰፋ ማሞ ተነግሮኛል። ከጀኔራል ፃድቃን ጋር ባደረግሁት ቃለ - መጠይቅ ግን ፃድቃን እውነተኛውን ታሪክ ደብቆኝ ነበር። 'ሙሴ በኢዲዩ ነው የተገደለው' ሲል ነበር የነገረኝ። አውአሎምን ደግሞ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሳነጋግረው 'ፃድቃን የሙሴን አሟሟት ነግሮሃል?' ሲል ጠየቀኝ 'አዎን ነገረኝ። አሳዛኝ ነው' አልኩት። አውአሎም ቀጠለ 'በጣም ያሳዝናል፤ የኛው ሰዎች ናቸው የመቱት' አለኝ።

በድንጋጤ አይኔ ፈጠጠ...

ከፃድቃን የሰማሁት የተለየ ታሪክ ነበርና አውአሎምን አውጣጣሁት። ከሃይል 41 በተተኮሰ ጥይት መመታቱንና ጥቂት ዝርዝር ነገሮችን ነገረኝ። በመቀጠል በወቅቱ የሜጋ ማስታወቂያ ስራ አስኪያጅ ወደ ነበረው ወደ አሰፋ ማሞ ዘንድ ሄድኩና ሙሴ ከጆርባ ከሃይል 41 ተተኩሶበት መገደሉን ያውቅ እንደሁ ስጠይቀው እውነታውን ለመዘክዘክ አላመነታም። የገዳዩን ስም ጭምር ነገረኝ። ሙሴ ቆስሎ በነበረበት ጊዜ ከመሞቱ በፊት በገዛ ወገኖቹ ሆን ተብሎ እንደተመታ ማወቁንም ከአሰፋ ማሞ ነበር የሰማሁት።

ይህን የማወጋችሁን ታሪክ ከፊሉን ያህል *"የሙሴ ገድል"* በሚለው *"ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ - ቅፅ ሁለት"* ላይ ካተምኩት በሁዋላ ግን በህወሃት አመራር አካባቢ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆነ። ከያቅጣጫው ጩኸት መጣ። በቅድሚያ ድምፁን ያሰማው በርሄ ሃጎስ ነበር - ከካናዳ፤

'የሙሴ ገዳይ ማነው? ለምን አድበሰበሳችሁት? ማንን ለማለት ፈልጋችሁ ነው? ስም መጠፋፋት ከተጀመረ ሁላችንም የምናውቀውን እንደምናወጣ እነ ስብሃት ነጋ ልብ ሊሉ ይገባል" ሲል ፃፈ።

በጣም ገረመኝ። በርሄ ሃጎስ በመፅሃፉ ስሙ አልተጠቀሰም፤ "የሃይል 41 ተዋጊ የነበረ፣ ሰሜን አሜሪካ ነዋሪ የሆነ" የሚል ነበር የጠቅስኩት። ምን አስለፈለፈው? የማርያምን ብቅል የበላች ፍየል አይነት ሆነ።

በመቀጠል ክንፉ ደወለና እሪታውን አቀለጠው።

"ከየት አመጣህ ይህን ታሪክ?" ሲል በቁጣ ጠየቀኝ።

ታሪኩን ከአምባሳደር አውአሎምና ከአሰፋ ማሞ ማግኘቴን ረጋ ብዬ ስነግረው ንዴቱና ቁጣው ይበልጥ ናረ።

"አውአሎም! እሱ ነው ይህን የሚነግርህ? ከሻእቢያ የሰማውን ታሪክ ነው የነገረህ! እነሱ ዘንድ እየዋለ ያገኘውን!? አሰፋ ማሞስ? ዘባራቂ! አንተስ ብትሆን! እነሱ እንደነገሩህ በቀጥታ መፅሃፉ ላይ ለምን አልፃፍከውም?"

ክንፉ እያበደ ቀጠለ፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“የዶክተር አታኽልቲ ቤተሰቦች ደውለውልኝ ነበር። ‘የአታኽልቲ አሚሚት ይነገረን’ እያሉ ነው። ምንድንነው የምንላቸው? ምን እየሰራህ እንዳለህ ይገባሃል? ምን ብለን ነው ለነሱ የምንነግራቸው?”

በዝምታ አዳመጥኩት። ደጋግሞ ሲጮህብኝ ግን፣

“ሙሴ ህይወቱ ሲያልፍና ሲመታ አውአሎምና አሰፋ አብረውት ነበሩ። ቢያንስ ከሶስት ሰዎች አመሳክሬ ያረጋገጥሁትን ታሪክ ነው የፃፍኩት!” አልኩት።

“ሆን ብለህ ነው!” ሲል ቁጣውን ቀጠለ፤ ለምን ሆን ብዬ ያን እንዳደረግሁ ግን አላብራራልኝም፤ እየጮኽ ቀጠለ፣

“ሳትውል ሳታድር በመፅሄትና በጋዜጣ ይህ ታሪክ ውሸት መሆኑን አስተባብል!”

ክንፉ ባዘዘኝ መሰረት በመፅሄታችን ላይ እንደ ግለሰቦች ደብዳቤ አድርጌ ማስተባበያውን እንደማይነበብ አድርጌ በደቃቅ ፅሁፍ አተምኩት።

ሌላ ቀን ደግሞ የማነ ኪዳነ (ጀማይካ) በቼ ጉዋቬራ ላይ የተፃፈ አዲስ መፅሃፍ አግኝቶ ሊያውሰኝ ቃል ገብቶ ነበርና መፅሃፉን ልቀበል በሄድኩ ጊዜ፤ በሙሴ አሚሚት ጉዳይ ላይ ስንነጋገር እንባ ቀደመውና ፊቱ ሁሉ ታጠበ፣ እንባውን እያባበሰ፣

“የተፃፈውን ታሪክ ፈፅሞ አላውቅም! እውነት ነው ብዬ ለማመን እቸገራለሁ” አለኝ።

“አውአሎም ወልዱ፣ ፃድቃን ገብረትንሳኤና አሰፋ ማሞ ግን ያውቃሉ” አልኩት።

“እንዴት እኔ አላውቅም?” አለ ፊቱ አሁንም እየተለዋወጠ።

ለጀማይካ ስሜታዊ ጥያቄዎች ግን እኔ ምላሽ መስጠት አልቻልኩም። ፃድቃንና ጀማይካ በጣም ይቀራረቡ ነበር። እንዴት ሳይነግረው ቀረ? ጀማይካና ሙሴ ሁለቱም የሻእቢያ ታጋዮች የነበሩ ሲሆን፤ ጓደኝነታቸው ጥብቅ ከመሆኑ የተነሳ ጀማይካ ወንድ ልጁን ሙሴ ሲል ጠርቶታል።

ገብረመስቀል የተባለውን የህወሃት አመራር አባል ኢህአዴግ ፅህፈት ቤት ቁጭ ብሎ አገኘሁትና ከሰላምታ በፊት ይህንኑ አነሳልኝ፣

“ስለ ሙሴ የፃፍከው ምንድነው?”

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“አንተም አታውቅም ይህን ታሪክ?”

“ኢዲዩ እንደገደለችው ነው የማውቀው”

“እኔ ያገኘሁትን ታሪክ ፅፌያለሁ፣ ገብረመስቀል”

“ይህ ታሪክ እውነት ከሆነ፣ እስከ ዛሬ ለምን ተደበቀ? ዛሬስ በምን ምክንያት ነው ሊነገረን የተፈለገው?...”

“ይህን ታሪክ ይፋ እንዳደርግ ያዘዘኝ የለም ገብረመስቀል፣ ታሪኩን ካገኘሁ በሁዋላ አመሳክሬና እውነት መሆኑን አረጋግጬ በራሴው ስልጣን ነው ያተምኩት!”

“ማንም ሳያነበው ራስህ አተምከው?”

“በትክክል!”

ምንም አልተናገረም። ሲጋራ አውጥቶ ማጨስ ጀመረ። በዚያው ተለያየን።

የሙሴ ታናሽ እህት ገና ተክሌ ደወለችልኝና ግዮን ሆቴል ቀጠረችኝ። ምሽት ነበር። ግዮን ሆቴል ቁጭ ብለን ስናወራ ቆየንና እየተንሰቀሰቀች ማልቀስ ጀመረች።

“ታውቂ ነበር ታሪኩን?” ስል ጠየቅሁዋት።

“በመፅሃፍ ሲታተም ሆድ ብሶኝ አለቀስኩ እንጂ ራሳቸው እንደገደሉትማ አውቅ ነበር። እናቴም ታውቃለች” ለረጅም ሰአት እሷ ስታለቅስ እያባበልኳት ቆየሁ።

አለምሰገድ ገብረአምላክን ያገኘሁት ከዚህ ሁሉ በሁዋላ ዘግይቼ ነበር። አለምሰገድ ቀጥተኛ አለቃዬ ነበር። የሙሴን ገድል እንዳነበበው ሰምቼ ነበር፣

“እንዴት አየኸው?” ስል ጠየቅሁት።

“ምኑን?”

“የሙሴን የአሚሚት ታሪክ?”

ከአለምሰገድ ገፅታ ላይ ስሜቱን ማንበብ ከቶ አይቻልም። እንደ አለት ፀጥ ያለ ፊት ያለው ሰው ነው፣

“የሙሴ አሚሚት!” አለ ሲጋራውን እየማገ “.....አከራካሪ ነው። በኢዲዩ ተገደለ የሚሉ አሉ። የለም በእኛ ወገን ነው የተመታው የሚሉም እንደነበሩ አውቃለሁ...” ዘግየት አለና አከለበት፣ “...እንዲህ ያሉ አከራካሪ ታሪኮች ታትመው ባይወጡ ይሻላል” ዘግየት አለና ጨመረበት፣ “...በቀጣይ የምትፅፋቸውን ታሪኮች ከማተምህ በፊት ለእኔና ለክንፉ አንዳንድ ኮፒ ላክልን!”

የስሁል ወይም የገሰሰ አየለ ታሪክ ግማሽ እውነትና የተዛባ ትረካ ሊታተም የበቃውም በዚህ ምክንያት ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በስሁል ወይም በገሰሰ አየለ ትረካ ውስጥም ዋና ዋና እውነታዎችን ቆርጬ እንዳወጣ ወይም እንዳልተርክ ታዝዝ ነበር። ስሁል የእነ መለስን ቡድን ለመግደል በታቀደ ሴራ ውስጥ እጁ እንደነበረበት የሚገልፀው አንቀፅ አንዱ ነበር። የነ መለስ ቡድን የሚባለው አባይ ፀሃዬ፣ ስዬ፣ ግዴይ ዘርአፅዮን፣ አውአሎም፣ ሙሴ፣ ጀማይካ፣ ስዩም መስፍን የመሳሰሉትን በወቅቱ ዩኒቨርሲቲ አካባቢ የነበሩ ተማሪዎችን ያቀፈ ቡድን ሲሆን፣ በአንፃሩ የገበሬዎች ቡድን የሚባል ቡድን ደግሞ ነበር። ይህም የስሁልን ብቸኛ አመራር የሚደግፍ ቡድን ነበር።

አንድ ቀን የገበሬዎቹ ቡድን የነመለስን ቡድን ለመረሸን ይወስንና በአጋጣሚ እቅዱ ይከሽፋል። ከመክሸፉም ጋር ይጋለጣሉ። ከተጋለጡም በሁዋላ ይደመሰሳሉ። ያንን የግድያ እቅድ ስሁል ያውቅ እንደነበር የተረከሁትን ክፍል አለምሰገድ ቆርጦ አወጣው።

"ለምን አወጣኸው?" ስል ጠየቅሁት።

ታሪኩን ያገኘሁት ከስብሃት ነጋ ነበርና ስብሃትና አለምሰገድ በታሪኩ መገለፅ ላይ የተለያየ አቋም እንዳላቸው እየተረዳሁ ነበር። ስብሃት ያንን ሚስጥር የነገረኝ በቀጥታ እንዲታተም ነበር። አለምሰገድ ሲመልስ፣

"ያ ታሪክ የስሁልን ገፅታ ስለሚያበላሽና ስለሚያዛባ ነው" ሲል መለሰልኝ።

እውነታው ግን እንደዚያ አልነበረም። ዘግይቼ እንደተረዳሁት አለምሰገድ ያቺን ትረካ የሰረዛት የዚያ ታሪክ ይፋ መሆን በስሁልና በቀሪዎቹ አመራር አባላት መካከል የነበሩ አለመግባባቶችን ጎልጉሎ ለማውጣት ቀዳዳ ስለሚከፍትና ይህም አከራካሪውን የስሁል አሟሟት ስለሚቀሰቅስ ነበር።

ርግጥ ነው የግድያ እቅዱ ከከሸፈ በሁዋላ ስሁል በአይነ ቁራኛ የሚታይ የቁም እስረኛ ሆኖ ነበር ለአመት ያህል የቆየው። ዲማ ላይ በተደረገው የአመራር ምርጫ ላይም በተለመደው ድርጅታዊ ስራ ስሁል ሳይመረጥ ቀረ። ይሁን እንጂ እነ መለስ በወቅቱ ስሁልን ይፈልጉት ነበር። ስሁል በትግራይ ህዝብ ዘንድ የተከበረ ግዙፍ ስም ስለነበረው በስሙ የገበሬዎችን ድጋፍ ለማግኘት እየተጠቀሙበት ነበርና በቁም እስር ይዘውት ቆዩ። ስሁል እስረኛ መሆኑን ሲገነዘብ ከእለታት አንድ ቀን እንዲህ ሲል ጥያቄ ያቀርብላቸዋል፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"እድሜዬ ገፍቶአል! ሱዳን ልሂድና ገንዘብ በማሰባሰብ እዚያ ሆኜ ላግዛችሁ..."

አዲሶቹ ተመራጮች የስሁልን ጥያቄ ቁጭ ብለው መረመሩት፣ "እውነቱን ሊሆን ይችላል፤ እውነቱን ላይሆንም ይችላል" ተባባሉ። የስሁል ጥያቄ የእውነት ከሆነ ሱዳን ሆኖ ብዙ ሊያግዛቸው እንደሚችል ተገንዝበዋል። ሱዳን ከደረሰ በሁዋላ ከድታቸው ከኢዲዩ ጋር ከተቀላቀለስ? ስሁል የገበሬ ድጋፍ ስለነበረው ድምጥማጣቸውን እንደሚያጠፋቸው ተገነዘቡ። ከብዙ ክርክሮች በሁዋላ ስሁል ወደ ሱዳን ይሂድ ዘንድ ፈቀዱ። 6ሺ ብር እንዲሰጠው ቢጠይቅም 2ሺህ ብቻ ተፈቀደለትና ሱዳን የሚያደርሱት አጃቢዎች ተመድበውለት ስሁል ተሸኘ። በወቅቱ ስሁል ወደ ሱዳን እንደሚጓዝ የሚያውቅ አልነበረም። አለባበሱም እንደተራ ገበሬ ነበር።

ከቀናት በሁዋላ የኢዲዩ ሰዎች አውቶብስ አስቁመው ህዝቡን ሲያነሳሳቅሉ ስሁል ተመልክቶ ያንን በመቃወሙ በኢዲዩ ታጣቂዎች እንደተገደለ ተወራ። በርግጥ ኢዲዩ በወቅቱ ስሁልን አለመግደሉን አስተባብሎ ነበር።

ታሪክ ፀሃፊዎች ይመራመሩበት ዘንድ የሚተው ሌላ አከራካሪ መረጃም አለ። ይህም ስሁል እንደ ማርሻል ሮሜል ከተገደለ በሁዋላ ከፍተኛ ሽልማት የተሸለመ ሰማእት ነው የሚሉ ወገኖች አሉ። ሂትለር ግን ሮሜልን በግልፅ ነበር የነገረው! "ከምንገድልህ ይህችን መርዝ ዋጥና ሙት! በመኪና አደጋ ሞተ ብለን የጀግና ቀብር እናደርግልሃለን!" ነበር ያለው! ሮሜል የታዘዘውን ፈፀመ። የሮሜል ጥፋት ስሙ ከሂትለር በላይ እየገነነ በመሄዱ እንጂ ክህደት አልነበረም። ከሮሜል ጋር ሲነፃፀር ስሁል ታጋይ ተማሪዎቹ ላይ ክህደት ፈፅሞ ነበር።

የዚያን ጊዜው የስሁል እቅድ የተሳካ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የኢትዮጵያ ሁኔታ የተለየ በሆነ ነበር። ምን በሆነ ነበር!? እንደ አንባቢው አመለካከት ይለያያል!

ግራም ነፈሰ ቀኝ አለምሰገድና ክንፉ የቻሉትን ያህል ከጎማመዱለት በሁዋላ የስሁል ታሪክ በተዛባ ሁኔታ ታተመ።

* * *

ክንፉ የሁሉም ወዳጅ የሚሉት አይነት ሰው ነበር።

ፕሮፌሰር አስራትን ወደ ከርቸሌ ከላከ በሁዋላ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ከቀኝአዝማች ነቃጥበብ በቀለ ጋር ወዳጆች ሆነው ነበር። ቀኝአዝማች ሞጆ ላይ ዳቦ ቤት፣ አዲሳባ ላይ መጋዘን ስለነበራቸው ከድርጅቱ ስራ ይልቅ በግል ቢዝነሳቸው የተጠመዱ ሰው ስለነበሩ ክንፈ ወዶአቸው ነበር። እሳቸውም ለክንፈ ጥሩ አመለካከት ነበራቸው። የግል ጋዜጦች የቀኝአዝማችን ድክመት እየመዘዙ ወቀሳ ሲያበዙባቸው ታዲያ ከእለታት አንድ ቀን ክንፈ ዘንድ ደውለው እንዲህ እንዳሉት ክንፈ አጫውቶኛል፤

"ምን እንዳሉኝ ታውቃለህ?"

"ምን አሉህ?"

"ጋዜጦች አስቸገሩኝ! ፕሮፌሰር አስራት ታስረው ሲሰቃዩ እኔ አለመነካቴን እያነሱ ስሜን እያጠፉ ነውና እባክህ ለአንድ ሳምንት አስረህ ጥቂት አንገላታኝ!"

ይህን ብሎ ክንፈ በሳቅ ፈነዳ ! እኔም አጀብኩት!

"እና ምናልካቸው?"

"እድሜዎ ገፍቶአል። እስርቤት ውስጥ ቢሞቱብን ሰበብ ይሆንብናልና አልተባበሮትም' አልኳቸው!"

ቀኛዝማች ብዙ ጊዜ ወደ ክንፈ እየደወሉ "ይህን ይህን አታድርጉ፣ ለስማችሁም በጎ አይደለም" እያሉ እንደ አባት ይመክሩትና ይቆጡት የነበረ ሲሆን፤ ክንፈ ደግሞ መአህድ ተዳክሞ እንዲቆይ ቀኛዝማችን ከስልጣን የሚገለብጥ ሁኔታ እንዳይመጣ በሚስጥር ያስጠብቃቸው ነበር።

* * *

"የቡርቃ ዝምታ" ከታተመ በሁዋላ አስተያየቱን እንዲሰጠኝ ከሚገልፅ ማስታወሻ ጋር ለክንፈ ላክሁለት። በሶስት ቀን ውስጥ አንብቦ ከጨረሰው በሁዋላ ጠርቶ እንዲህ አለኝ፣

"አስተያየት ልሰጥህ ፈቃደኛ አይደለሁም"

"ለምን ክንፈ?"

"ስሜ መፅሃፉ ውስጥ ስላለ፣ በዚህ መፅሃፍ ጉዳይ አልገባበትም"

የፕሮፓጋንዳውና የአህዴድ መሪዎች እነ ኩማና አባዱላ እኔ ላይ ጀምረውት የነበረው የጥቃት ዘመቻ ሳይሳካ የዘገየው ክንፈ በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነበር። እያነጋገሩት አንዳችም አስተያየት ከመስጠት ይቆጠብ እንደነበር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የወሬ ወሬ እየሰማሁ ይገርመኝ ነበር።

ክንፉ ሚዲያዎቹን በቁጥጥሩ ስር ያዋለ ሰውም ነበር። ከግል ጋዜጦች አንዳንድ ለጥቅም ያደሩ ትናንሽ ጋዜጦች ለአንድ ፅሁፍ 150 ብር እየተከፈላቸው የደህንነቱ መስሪያ ቤቱ የሚያዘጋጃቸውን ፅሁፎች ያትሙ ነበር። የግል ጋዜጣ ዋና አዘጋጆችን ለዚህ አይነት ስራ እንዳግባባ ሁለት ጊዜ ታዝዠያለሁ። ክንፉ እንዳጫወተኝ ጋዜጠኞቹ መርፌ የምታክል የድምፅ መቅጃና ማስተላለፊያ መሳሪያ ይዘው ወደ ተቃዋሚዎች ስብሰባዎች ለመግባት 1500 ብር ብቻ ይከፈላቸው ነበር። አበራ የማነአብ የታሰረበትን የግዮን ሆቴል ስብሰባ ክንፉና መለስ ቢሮአቸው ቁጭ ብለው ይከታተሉት ነበር። ክፍሌ ሙላትና በፍቃዱ ሞረዳ የተባሉትን ጋዜጠኞች ግን ክንፉ አጥብቆ ይጠላቸው የነበረ ሲሆን 'አክራሪዎች' ይላቸው ነበር።

የሪፖርተር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አማረ አረጋዊና ክንፉ ገብረመድህን ጉዋደኛሞች ነበሩ። ጉዋደኝነታቸውም የጥንት እንጂ የቅርብ አልነበረም። አማረ አረጋዊ በትግሉ ዘመን በረሃ ውስጥ ሶስት አመታት በታሰረበት ወቅት እንኳ ከክንፉ ጋር ጓደኛነታቸው የተቋረጠ አልነበረም። ለሪፖርተር ጋዜጣ ኢንፎርሜሽን ማግኘት ዋና ምንጭም ክንፉ የነበረ ሲሆን፣ እኛ በድርጅት ስር ታቅፈን እንኳ እየለመንን የማናገኘውን መረጃ አማረ በተኛበት እንደዋዛ ያገኝ ነበር። ለሪፖርተር ጋዜጣ መረጃ ማግኘት ክንፉ አቢይ ሚና ነበረው።

* * *

አንድ እለተ ረቡእ ማለዳ ክንፉ ደወለና፣

"የዛሬውን የኤርትራና የሊቢያ ዜና ከየት አገኘኸው?" ሲል ጠየቀኝ።

በኤርትራና በሊቢያ መካከል አንዳንድ አለመግባባቶች መፈጠራቸውን የሚገልፅ ዜና በሁለተኛው ገፅ ላይ አትመን ነበር።

"መሃመድ ጠሃ ነው የሰጠኝ"

"ከቻልክ አሁኑኑ ቢሮዬ ና" ሲል ክንፉ አዘዘኝ።

እንደደረስኩ እንዲህ አለኝ፣

"ዜናው ስህተት ነው!"

"እንዴት?"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“በኢሳይያስና በጋዳፊ መካከል ችግር የለም”

በእውነቱ ይህ አጀንዳ ለኔ ልዩ ሆኖ የሚታይ አልነበረም። በኢትዮ ኤርትራ ግጭት ወቅት እንደ አቅጣጫ የተሰጠን ስራ ሻእቢያንና ኢሳይያስን ማጥላላት ስለነበር ዜናው ሃሰት ቢሆን’ንኳ ጉዳቱ አልታየኝም ነበር፣

“የሆነው ሆኖ ዜናው ለምን ትኩረትህን ሳበ?” ስል ጠየቅሁት።

“የወጣበትን አላማ ማወቅ ፈልጌ ነበር”

“እንዳልኩህ ጠሃ ነው የሰጠኝ። የተሳሳተ ይሆናል ብዬ ስላልገመትኩ አላረጋገጥኩትም” አልኩት።

በነገራችን ላይ መሃመድ ጠሃ ዙላ አካባቢ የተወለደ ኤርትራዊ ነው። የቀጠር ቴሌቭዥን ወኪል ጋዜጠኛ ሆኖ አዲስ አበባ ተመድቦ የሚሰራ ሲሆን፤ የሃይል ሚዛን እያየ አረማመዱን የሚያስተካክል የጥቅም አይነት ሰው ነው፤ በሙያው ግን የአረብ ሃገራትን መሪዎች በአካል የሚያውቅ ፈጣን ጋዜጠኛ ነበር።

“ስለ ጠሃ ምን አስተያየት አለህ?” ሲል ጠየቀኝ።

“ጠሃ ጎበዝ ጋዜጠኛ ነው” አልኩት።

“ማለቴ ስለአመለካከቱ፤ ታምነዋለህ?”

ሳላመነታ ምላሽ ሰጠሁት።

“ሻእቢያ እንደሚያሳድደው ነግሮኛል”

“ታምነዋለህ? በሻእቢያ ሊጠረጠር ይችላል?”

“ያን ለማለት ማስረጃ የለኝም”

“ሻእቢያ ጠሃን ሊገድል የሚፈልግ ይመስልሃል?”

“አላውቅም፤ መረጃ የለኝም”

“የማስፈራሪያ ደብዳቤ ፅፈውለታል! ይህን ታውቃለህ?”

“ያን ደብዳቤ አሳይቶኛል” አልኩት።

“ከሁለት ሳምንት በፊት የመን - ሰንአ ላይ ካረፈበት ክፍል ድረስ መጥተው ‘ኩርኩር ወያኔ’ (የወያኔ ቡችላ) ሲሉ ሰድበው፤ የሚሰራውን ስራ እንዲያቆምና ከአዲሳባ እንዲወጣ እንዳዘዙትስ ነግሮሃል?”

“ክንፈ! የምትነግረኝን ታሪክ መሃመድ ጠሃ ላገኘው ሰው ሁሉ ነው የሚያወራው!”

ጥቂት ሰከንዶች ፀጥ ብሎ ከቆየ በሁዋላ፣

“በተግባር እንደምናየው ጠሃ ሻእቢያን የሚጎዱ ዘገባዎች እየሰራ ነው። የሚሰራው ስራ ለኛ በጣም ጠቅሞናል! ዛሬ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እናንተ ጋዜጣ ላይ የወጣው ዜና ከጠሃ መምጣቱ አስገርሞኛል" አለኝ።

ክንፈ ከኔ ምን ለማወቅ እንደፈለገ በፍፁም ሳይገባኝ በዚሁ ተለያየን።

ከሁለት ወራት በሁዋላ መሃመድ ጠሃ ሂልተን አካባቢ ይኖርበት ከነበረው አፓርታማ እንደወጣና የተዋበ ሙሉ እቃ ያለው፤ ወላንሳ በወላንሳ የሆነ ድንቅ ቪላ እንደተሰጠው ሰማሁ። በመሃመድ ጠሃ ተወከል ጉዳይ ላይ ከክንፈ ጋር ከተነጋገርን በሁዋላ ክንፈ ከኔ ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነት እያላላ ሄደ። 'ስራ በዝቶበት ይሆናል' ብዬ እኔም ችላ ብዬ ተውኩት።

ወደ ቢሮው ስደውልም ቆይቼ እንድደውል በፀሃፊው በኩል ይነገረኝ ጀመር። በወቅቱ ክንፈ ሊርቀኝ የጀመረው በመሃመድ ጠሃ ምክንያት ይሁን ወይ በሌላ ማወቅ አልቻልኩም ነበር።

* * *

ከዚያ በሁዋላ ክንፈን ያገኘሁት አንድ ጊዜ ሲሆን፣ ይህም ከመኮብለሌ ሁለት ሳምንታት በፊት ቢሮው አስጠርቶኝ ነበር። በዚያን እለት የተነጋገርነውን በመጨረሻዎቹ ምእራፍ ላይ አወጋችሁዋለሁ።

* * *

እነሆ ናይሮቢ ከተማ ዳርቻ ላይ ከሚገኝ የእንግሊዛውያን ባልና ሚስት ንብረት ከሆነ ፀጥተኛና የድሃ ቱሪስቶች ማረፊያ ሆቴል ተቀምጬያለሁ። ከአምስት ደቂቃ በፊት BBC ከተባለው ሬድዮ ጣቢያ የክንፈን የመገደል ወሬ በመስማቴ በተቀመጥኩበት ደንዝዤያለሁ...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 15 -
የመጨረሻው ምሽት

ወደ መጨረሻዬ መጨረሻ - ፊቴን አዞርኩ፣
የሚታየኝን ማየት አቃተኝ፣
ወደ መጀመሪያዬ መጀመሪያ ሃሳቤን መለስኩ፣
ሃሳቤን አላመንኩትም፣
ወደ ውስጠኛ ውስጠኛዬ ገባሁ፣
እዚያው ቀረሁ፤

(ግጥም - ሰንዱ አበበ)

ወደ ግብጣው አዳራሽ እንግዶቼ እየዘለቁ ነው...

ስብሃት ገብረእግዚአብሄር፣ ሄለን መሃመድ፣ ሲሳይ ንጉሱ፣ መአዛ ብሩ፣ ማሞ ውድነህ፣ ትእግስት ሀሩይ፣ ደረጄ ደስታ፣ ታገል ሰይፉ፣ ተፈራ ገዳሙ፣ እንዳለጌታ ከበደ፣ አበበ ባልታ፣ መስፍን ሃብተማርያም፣ አቦነህ አሻግሬ፣ ሰአዳ መሃመድ፣ አብርሃም ረታ አለሙ፣ ኡቅባይ በርሄ፣ ሙሳቱ ገብሩ፣ ፍቅረማርቆስ ደስታ፣ ተፈሪ አለሙ፣ ማንያዘዋል እንዳሻው ...

ሁለት መቶ ሰው እንዴት ልዘርዝር?

ምናለፋችሁ!

እነዚህ ሁሉ ደራስያንና ጋዜጠኞች አሊያም የኢትዮጵያ የስነጥበብ ሰዎች ናቸው። ከዋቢ ሸበሌ ሆቴል

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ቀይ ሳሎን ደጃፍ ላይ ቆሜ ለእንግዶቼ “ቅፅ አምስት - እፍታ” መፅሃፍን እያደልኩ እቀበላቸው ይገፍያለሁ። ተጋባዦቼ ለመፅሃፍ ምረቃ መጠራታቸውን ነው የሚያውቁት። እኔ ግን ስለመጨረሻው ምሽት እያንጎራጎርኩ ነበር። ስውር የስንብት ምሽት።

ሁሉም ነገር የተፈፀመው እንደ ሰመመን ባለ ቅዠት ውስጥ ሆኖ ይሰማኛል። ጀርባዬን ለትውልድ ሃገሬ ሰጥቼ ለመኮብለል ተገድጄ፣ የኢትዮጵያን እውቅ የስነጥበብ ሰዎች የመፅሃፍ ምረቃና የስንብት ግብዣ ጠርቼ በማስተናግድባት በዚያች ደቂቃ የሚካሄደውን ሁሉ የፀጥታው መስሪያ ቤት ሹም ክንፈ ሁሉን ያውቅ ነበር። የግብዣው ገንዘብም በበረከት ስምኦን ተፈቅዶ ወጪ የተደረገ ነበር።

ማሞ ውድነህ ሙሉ ጥቁር ሱፍ ልብስ ለብሰዋል። ቁመናቸውና በረዶ የመሰለ ጠጉራቸው ለግርማ ሞገሳቸው ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ነበር። “ማሞ ማናቸው?” ብሎ የሚጠይቅ መቸም የለም። ወራሪው የኢጣሊያ ሰራዊት ኢትዮጵያን በያዘበት ዘመን በአንድ የጣሊያን የጭነት መኪና ተሳፍሮ አዲስ አበባ የገባው የዚያን ዘመኑ እረኛ፤ የዛሬው 40 መፅሃፍ ያሳተሙት ማሞ ናቸው።

ጋሽ ስብሃት ከአዳራሹ ግድግዳ አጠገብ ከልጁ ከዜና ጋር ተቀምጠአል። በዛሬው የመፅሃፍ ምረቃ ላይ የንግግር ሰአት ከተያዘላቸው መካከል አንዱ ነው። ይህን ተወዳጅ ደራሲ ምናልባትም ለመጨረሻ ጊዜ ነው የማየው። ማለዳ ላይ ቡና ስንጠጣ የሚያወጋኝ ውብ ወጎች ለዘልአለሙ ሊቀሩብኝ ነው። ስብሃትን የማያከብርና የማይወድ መቸም የለም፡፡ እኔ በታሪክ አጋጣሚ አለቃው ብሆንም፤ ግንኙነታችን ግን የተማሪና የአስተማሪ ነበር፡፡ በስነፅሁፍ እንድዳብር ካደረጉኝ ዋና ዋና ሰዎች አንዱ ስብሃት መሆኑን በኩራት ስናገር እኖራለሁ፡፡ ከዚያም በላይ ግን ስብሃት የሁሉም ጓደኛ ነው፡፡ ለስብሃት አለቃው ሆኜ ለአመታት አብረን ብንሰራም፤ አንዳንድ ጉዳዮች ላይ እሱ ነበር የሚያዘኝ፣

አንድ ቀን እንዲህ ሲል ጠይቆኛል፣

“ላማክርህ ነበር የመጣሁት...”

“እሺ ጋሽ ስብሃት... ምን ነበር?”

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ገንዘብ ችግሮኛል..."

ዝም አልኩ፡፡ ምክንያቱም የመጨዎቼን ሁለት ወራት ደሞዙን ከወዲሁ ወስዶአቸው ነበርና ምን እንደማደርግ ግራ ሊገባኝ ጀምሮ ነበር፡፡ እሱም ይህን ተገንዝቦ ኖሮ ፈጥኖ ንግግሩን ቀጠለ፣

"ደሞዜን ቀድመህ ስጠኝ ልልህ አልችልም፡፡ ወስጄዋለሁ፡፡ አሁን ግን ሳስብበት ቆየሁና አንድ ሌላ ዘዴ መጣልኝ።"

"ምን ዘዴ አገኘህ ጋሽ ስብሃት?"

"ታታሪ ሰራተኛ በሚል ለምን ቦነስ አትሰጠኝም?"

በሳቅ ነበር የፈነዳሁት!!

ለነገሩ ስብሃት ታታሪ ሰራተኛ ነበር፡፡ 'እነሆ በረከት' የተሰኘች አምዱን አንድም ቀን አንድሎ አያውቅም። ስብሃት በራሱ ሰአት ጊዜውን በትክክል መጠቀም የሚችል ደራሲና ጋዜጠኛ ስለመሆኑ ዘነበ ወላ "ማስታወሻ" በተባለ መፅሃፉ ብዙ ብሎለታል። እኔም ወደፊት እድሜና ጊዜ ካገኘሁ ስለ ደራሲ ስብሃት መፃፌ አይቀርም፡፡

በረከትና ክንፉ ምን እየቀረብኝ እንደሆነ ባለመገንዘብ ከሃገሬና ከወዳጆቼ እየነጠሉኝ ይገኛሉ። ይህ በኔ ላይ የሚፈፀም ወደር የሌለው ግፍና ወንጀል መሆኑን ግን ሊረዱ አይችሉም።

* * *

የስራ ባልደረባዬ መኩሪያ መካሻ ጥግ ላይ ከሶስት ከማላውቃቸው ሰዎች ጋር ተቀምጠ ቢራውን ይቀመቅማል። ስለ ራሺያ ደራሲያን እየተረከላቸው እንደሚሆን ግልፅ ነው። ቼኮቭና ቶልስቶይ የመኩሪያ ቅደመ አያቶች እስኪመስሉኝ በነሱ ፍቅር የተለከፈ ነው። በሃገራችን ደራስያን መካከል የሚታየው መመቀኛኘት መኩሪያን ከልብ ያሳዝነዋል፣

"ምቀኝነት በየትም አለም ላይ ያለ ነው። የኛ ግን ይበዛል። ምቀኝነት ከማለትም መገዳደል ቢባል ይቀላል" አለኝ አንድ ቀን፤ አያያዘናም ቀጠለ "...እስኪ አሁን የታገል ሰይፉን ስራዎች ተመልከት። ከፑሽኪን በምን ያንሳሉ? ታገልን በቅርብ የምናውቀው እንወደዋለን እንጂ ሃገሪቱ አንዳችም እድል አልሰጠችውም"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሌላ ቀን ደግሞ እንዲሁ ስለምቀኝነት ስናወራ የሩስያ ደራሲያንን ጠቀሰልኝ፣

"ጎጎል ታዋቂ የሆነበትን The great inspector የተባለውን ድርሰት ሃሳቡን ያገኘው ከፑሽኪን ነው። ፑሽኪን አንድ ቀን ጎጎልን እንዲህ አለው፣ 'ጎጎል ይህን አንተ ብትፅፈው ከኔ የተሻለ ይዋጣለታል' እና ሰጠው። የኛ ሰው'ኮ የፃፍከውን ትቶ ስለግል ጉዳይህ ገብቶ ነው የሚፈተፍተው!"

መኩሪያ በጣም ቀጭን ሲሆን አምስት አመት አብረን ስንሰራ፣ እኩል እየበላንና እየጠጣን ምንም ክብደት ባለመጨመሩ እቀናበት ነበር። "የማትወፍረው ስለ ምቀኝነት እያሰብክ ስለምትንጨረጨር ነው" እያልኩ እቀልድበት ነበር።

እንግዶቼ እየዘለቁ ነው፣

ደረጀ ሃይሌ ገብረመድህን - ጋዜጠኛው ሳምሶን ማሞና ባለቤቱ ዜድ - ይሁን እንዳሻው - ኤፍሬም እንዳለ - ግርማይ ወልደጊዮርጊስ - ሺፈራው ከበደ - ቶማስ አርጋው -ሰለሞን አበበ - ዘነበ ወላ - ወሰን ይሄይስ - ተክሌ ተስፋልደት እን ደ አመጣጣቸው በመዝለቅ ላይ ናቸው። ....

* * *

"እፍታ" የተባለችውን መድበል ለመመስረት የወጠን ኩት በኛ ዘመን ወርቃማ ዘመን መፍጠር ይቻላል የሚል ህልም ይዤ ነበር። "እፍታ" የተለያዩ አጫጭር የስነፅሁፍ ስራዎችን እያሰባሰበች የምትታተም መፅሃፍ ናት። ዛሬ ቅፅ አምስትን ለማተም ስንበቃ በመቶዎች የሚቆጠሩ ፀሃፊዎችን ማሳተፍ ችለን ነበር። ይህን ቅዱስ ፕሮጀክት እኔ ልቀጥለው ባልችልም፤ ሌሎች በተሻለ መንገድ ሊያስቡበት እንደሚችሉ ተስፋ አድርጌያለሁ።

* * *

የዜና አገልግሎት አንድ ጋዜጠኛ ሲመጣ በትኩረት አጤንኩት። እንዳልተጠራ አውቃለሁ። አስተያየቴ ገባው መሰለኝ፣

"አቶ ስሜነህ መኮንን ናቸው ወክለው የላኩኝ" ሲል ተሽቀዳድሞ ነገረኝ።

"ስሜነህ ለምን አልመጣም?" ስል ጠየቅሁት።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"አልቻለም! ይቅርታ በልልኝ ብሎኛል"

ይቅርታውን ተቀብዬ ወደውስጥ አስገባሁት። ስሜነህ እንዲመጣ ተመኝቼ ነበር። በጋዜጠኛነትና በስነጥበብ ህይወት መንገድ ላይ እንደ መምህር ከማያቸው ከነ አረፈአይኔ ሃነስ፣ አበራ ለማ፣ ሃይለ መለኮት መዋእል፣ ከነ መንግስቱ ወልደማርያም፣ ብርሃኑ ዘርይሁን እና ስብሃት ቀጥሎ ስሜነህ መኮንንም በኔ ህይወት ውስጥ የክብር ቦታ አለው።

* * *

ስላልመጡት ማሰብ ጀመርኩ።

ዶክተር ፈቃደ አዘዘ ተጠርተው ነበር። ምነው አልመጡም? አንጋፋው ደራሲና ሃያሲ አስፋው ዳምጤም እንዲሁ፣ ተስፋዬ ገሰሰ፣ አታክልት ሃገገ፣ ገበየሁ ዋለልኝ፣ ተሾመ ብርሃኑ፣ ቴዎድሮስ ሙላቱ፣ መዝሙር ፈንቴ፣ መኮንን ቶላ፣ ነቢይ መኮንን፣ አሰፋ ማሞ ገና አልመጡም። ለፕሬስ ድርጅት ፀሃፊ ለሂሩት የጥሪ ወረቀት ልኬላት ነበር። ከመጣች ምላሽ ያላገኘውን ማመልከቻ ያስገባሁት እኔ እንደነበርኩ እነግራታለሁ።

በር በሩን አሻግሬ እያየሁ ነው። ፊርማዬ አለሙ በህይወት የለችም እንጂ ዋና እንግዳዬ በሆነች ነበር።

"*ክራር*" የተሰኘችው የፊርማዬ ግጥም ትዝ አላችሁ?

በጣትዋ ፈላልጋ - ባወጣችው መንገድ፣
ታሳዝነኛለች - ተቀምጣ ስትነጉድ፣
ባምስቱ ጣቶችዋ - ደርድራ ደርድራ፣
አጠገቤ እያለች - ወጣች ተንደርድራ፣

አበራ ለማ ኖርዌይ ተሰዶአል። ለአማረ አረጋዊም የጥሪ ካርድ ልኬለት ነበር። ሳህለስላሴ ብርሃነማርያም ሲዘገዩብኝ በአቶ ማሞ ውድነህ ሞባይል ስልክ ደወልኩላቸውና እንዳልቻሉ ከይቅርታ ጋር ነገሩኝ። በስውር ተሰናበትኳቸው። ሴኮ ባይመጣም ጆሮ ጠቢ ልኳል። እስከ ዛሬ ምስጢሩ ባልተገለጠልኝ ምክንያት ጠምዶ ይዞኛል።

መስፍን ሃብተማርያም ሽክ ብሎ ብቅ አለ። እንደዚህ ለብሶ አይቼው ስለማላውቅ ሳልገረም አልቀረሁም።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ሽክ ብለሃል!" አልኩት "እፍታ"ን እያስያዝኩት።

"ወንድሜ ነው ከውጭ ያመጣልኝ" አለ ልብሱን እየ ነካካ፣ "....ዛሬ ከቤቴ ስወጣ የሰፈራችን ሰዎች ሊያውቁኝ አልቻሉም። የኛ ሰፈር እንደምታውቀው ጭቃና ኮረኮንች ስለሆነ እየተጠነቀቅሁ ስራመድ፣ 'ከየት የመጣ ሃብታም ነው?' እያሉ በመገረም ያዩኝ ነበር። አሮጊቶች ቡዳ እንዳይበላኝ ቱፍ ቱፍ አሉብኝ። ጠጉራቸውን ይቆረጡ የነበሩ ሳይቀር እያቋረጡ ወጥተው አዩኝ። አንዳንዶቹ ፊቴን ትክ ብለው ያዩና 'መስፍንን ይመስላል እያሉ ሲነጋገሩ 'መስፍን ነኝ አልኳቸው። ልብስ ሰውን እንዲህ ይለውጣል ለካ ብዬ ተገረምኩ..."

ልብሱን እየነካካ ሳቀ። መስፍን ሲናገር እንዲሁ ነው። ምፀቱ አንጀት ያርሳል። ከሚፅፈው በላይም ወጉ ይጣፍጣል። መስፍንን ሳይ የደብረዘይቱ የአማርኛ መምህራችን ጋሽ ዝናቡ ዘነበ ትዝ ይሉኛል።

* * *

ታገል ሰይፉ ብቻውን መጣ። ትህትናውን እንደ ግጥሞቹ እወድለታለሁ። ታገል ጥሩ ጓደኛዬ ነው። ገና ሲመጣ በራሱ ግጥም ተቀበልኩት። ከታገል ተወዳጅ ግጥሞች የአንድዋን የመጀመሪያ መስመር ስንኞች፣

"ፍየሊቱ ገደ ቢስ ናት..." ብዬ ስጮህ፣
ይህን ሳታይ የሞተችው!... " እሱ ቀጠለ።

ተሳስቀን ተቃቀፍን። ታገል ወደ ውስጥ ከገባ በሁዋላ ቀሪዎቹን ስንኞች እኔው ለራሴው አዜምኳቸው።

ፍየሊቱ ገደቢስ ናት - ይህን ሳታይ የሞተችው፣
ቆዳዋ ሰሙን ቀይሮ - እሳት ሲያነድ መች አየችው፣
ኽረ ወናፍ ክብሩ ይስፋ - አየር መሳቡ በሱ ያምራል፣
ያመዱን ጭጋግ ገላልጦ - የእሳቱን አይን ያበራል፣
ከንቱ ሰው ግን እንደ ወናፍ - አየሩን ስቦ ቢተፋው፣
በተለከፈ ትንፋሹ - የጊዜን ብርሃን አጠፋው፤

ከበደ ደበሌ ሮቢና ሞገስ ሃብቱ ተከታትለው ገቡ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሁለቱም ተፈጥሮ ጥበብን ያለስስት የቸረቻቸው የዘመናችን ጥበቦች ናቸው። ሞገስ ሃብቱ ታጋይ ቢሆንም "እንደ ኢህአዴግ ማሰብ" ከተባለው እስር ቤት ህሊናውን ነፃ ያወጣ ጀግና ነው። የመከላከያ ጋዜጠኛ እንደመሆኑ በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ወቅት ግንባር ሄዶ አዛዦች በሺ፵ዝ ዊስኪ ሲራጩ ተመልክቶ ደስ አላለውም። እንደነገረኝ ለሱም ተቀድቶለት ጠጥቶአል፤ እየጠጣ ታዲያ ጥቂት ስንኞችን ቋጠረ፤ ከፊሉን ላስነብባችሁ፣

መቶ ሺህ ብር ይውጣ፣
ሰው ጠግቦ እንዲወጣ፣
ውስኪም ብዙ ግዙ፣
ቢራም ብዙ ብዙ፣
ምግብም ብዙ ግዙ፣
ሁሉም በገፍ ይምጣ፣
ሰው ጠግቦ እንዲወጣ፣
እየበላህ ብላ፣ እየጠጣህ ጠጣ፣
ከሠዘብ ነው እንጂ ካንተ ኪስ አይወጣ!፤

ሞገስ ነጭናጫና አፈንጋጭ ነው። ለአለባበሱ ግድ የለውም። በትግሉ ጊዜ ጀምሮ በሬድዮ ጣቢያው አብረን እንሰራ ነበር። እንግባባለን። እድገት ታዲያ ወደ ሞገስ አጠገብ ደርሳ አታውቅም። ሞገስም ለስልጣንና ለገንዘብ በፍፁም ግድ የለውም። የሚያረካው ቢኖር በነፃ ህሊና የተሰማውን ወረቀት ላይ ማስፈር ነበር። እነዚያን በነፃ ህሊና የሚያሰፍራቸውን ስነ ግጥሞች ታዲያ ወደኔ ነበር ይዞ የሚመጣው።

"እነዚህ ግጥሞች... ያውልህ!" ይለኛል። በደስታ ነበር የምቀበለው።

* * *

እንግዶቼ ወደ ግብጣ አዳራሹ እየዘለቁ ነው...

አብዛኞቹ መጥተዋል። እሩብ ያህል ይቀራሉ። ለሪፖርተር ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ለእሸቴ አሰፋም የጥሪ ወረቀት ልኬለት ነበር። የሚመጣ ግን አይመስለኝም። እንደተቀየመኝ ወሬ ሰምቻለሁ። እንደ ማርያም ጠላት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደጠላኝ ነግረውኛል። በግል የበደልሁት ነገር የለም። "የቡርቃ ዝምታ" በተባለው መፅሃፍ ላይ አፄ ሚኒሊክን "አንቱ" ማለት ሲገባህ "አንተ!" ብለህ ዘረጠጥካቸው በሚል ነበር ቂም የያዘብኝ።

* * *

ትእግስት ህሩይ ዘግይታ መጣች። ሰላምታም ሳንለዋወጥ እንዲህ አለችኝ፣

"The Brothers Karamazovን አንብበሃል?"

"አንብቤዋለሁ ትእግስት፤ በጣም ድንቅ ነው"

"ሞስኮ ሳለሁ ወልጄ አልጋ ላይ ሆኜ ነው ያነበብኩት"

"ደግሚ ማንበብ እፈልጋለሁ፣ እሱን መፅሃፍ"

"አውስሃለሁ!"

ወደ ግብጦው አዳራሽ መራሁዋት። ከትእግስት ጋር በእጅጉ እንግባባለን።

* * *

አርቲስት አበበ ባልቻና ጋዜጠኛ መአዛ ብሩ አንድ ላይ መጡ። አዲስ አበባ የገባን ሰሞን እሁድ እሁድ እነ መአዛ ቤት እየተሰባሰብን ግጥም እናዳምጥ ነበር። አማረ የዊንጌት ተማሪ ሳለ ከመአዛ ጋር ይተዋወቁ ነበርና ኦቴሎና ባለቤቱን በሱ በኩል ነበር ያወቅሁዋቸው። አንድ የስነጥበብ ማህበር ልንመሰርት ጀምረን ሳንገፋበት ቀረን። ከስብስቡ ውስጥ እኔና አማረ አረጋዊ ብቻ ነበርን ወያኔዎች። የፕሮፌሰር መስፍንን "መሰላል" የተሰኘች ግጥም ከአርቲስት እሸቱ ጥሩነህ አንደበት የሰማሁት እነ መአዛ ብሩ ቤት ነበር። "በመሰላል ወደ ላይ ስትወጣ የጨበጥከውን ትረግጣለህ፤ ወደ ታች ስትወርድ ደግሞ የረገጥከውን ትጨብጣለህ" የሚለውን የግጥሙን ይዘት በጣም ወድጄው የነበረ ሲሆን፣ የፕሬስ መምሪያው ስልጣን እንዳይጣፍጠኝ ከመከሩኝ መካከል "መሰላል" አንዱ ነው። አንዳርጋቸው ፅጌም አብሮን ነበር። ሁዋላ ግን ደበርነውና መምጣት አቆመ። እኛም ብዙም ሳንቆይ ተበታተንን...

ሃይለመለኮት መዋእል የታለ?

ይምጣ አይምጣ ርግጠኛ አይደለሁም። ግማሽ መንዜ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- ግማሽ ኤርትራዊ ነው። ከሁለቱም ወገን አክስቶቹ እሱ ቤት ሲገናኙ እሱ አስተርጓሚ ሆኖ ያዋያቸዋል። ማርያም ሰላም ታመጣ ዘንድ የሚለምኑ ደጋግ አክስቶች ነበሩት። የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት እየተካሄደ እነሱ ቡና እየጠጡ አምላክን ይለማመኑ ነበር። አዬ የዘመናችን ፖለቲካ!

* * *

ከሃገር እየኮበለልኩ ነውና የቢሾፍቱን ልጆች በሃሳብ ተሰናበትኩዋቸው! እንደማንኛውም ሰፈር ልጆች እኛም ብዙ ትዝታዎች ነበሩን። ገንዘብ እያስያዝን ኪስ ተጫውተናል። በርግጥ እኔ ኪስ አልወድም። እናቴ ግን "ልጆች ሁሉ ኪስ ሲጫወቱ አንተ ፈዛዛ ሆንክ" አለችና ጆሮዬን እየመዠለገች ወደ ኪስ ሜዳው ይዛኝ ሄደች። የኪስ ሜዳው ንጉስ ሲራክ ተሾመ ይባል ነበር። በዚያች በቢሾፍቱ ቀበሌ ፍትህ በሌለው ሁኔታ የሲራክን ካልቾና ቡጢ ያልቀመሰ የለም። ዛሬ ታዲያ ሲራክ ከፍተኛው ፍርድ ቤት አካባቢ የፍትህ አካሉ ባልደረባ ነው። እናቴ ጆሮዬን እየመዠለገች ወስዳ ለሲራክ አስረከበች፣

"ልጆች ሁሉ ሲጫወቱ እሱ ፈዛዛ ሆነ። ከናንተ ጋር ይጫወት" አለችው።

"መዋጮ አለው፤ ሃምሳ ሳንቲም ያስከፍላል!" አላት።

እናቴ ሳታመነታ ነጭ ክብ ሃምሳ ሳንቲም ለሲራክ ሰጥታው ተመለሰች። ሲራክ ወዲያውኑ የራሱ ቡድን በረኛ አደረገኝ። የጎሉን ግንድ ተደግፌ በሃሳብ ተውጬ ሳለ ጎል ገባብኝ። ሲራክ እንደ ግስላ እየዘለለ መጥቶ ከጥሩ ጥፊ ጋር ሃምሳ ሳንቲሙን መልሶልኝ አባረረኝ። እያለቀስኩ ወደ ቤት! በህይወቴ ሙሉም አዲስ አበባ ስታድየም የገባሁት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፤ እሱም ለድርቅ እርዳታ ለመሰብሰብ በተዘጋጀ በአል ላይ ታምራት ላይኔን አጅቤ እንድገኝ ግዴታ ሆኖብኝ ነበር።

ወግን ወግ ያነሳዋል እንዲሉ፣ የዚያን እለቱ የስታድየም ቆይታችን አሰቃቂ ነበር። ካታንጋዎች ታምራትን "ሌባ! ሌባ!" እያሉ ሲጮሁበት የምንገባበት እስኪጠፋን ተጨነቅን። ለታምራት አዝኜለት ነበር። ታምራት 17 አመታት ድንጋይ ላይ እየተኛ የታገለው ለመሰደብ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አልነበረም። በወቅቱ እነ መለስ ካታንጋዎችን እንደ ወመኔ የፈረጁዋቸው ታምራትን ለማፅናናት እንጂ የካታናጋ ድምፅ የህዝብ ነፀብራቅ መሆኑን አጥተውት አልነበረም። በዚያን እለት ከታምራት በቅርብ ርቀት ላይ ተቀምጬ የነበረ ሲሆን፤ በወቅቱ በታምራት ገፅታ ላይ ጠብቄው የነበረውን ድንጋጤ ወይም ንዴት አላየሁም። ትክዝ ብሎ የሚያወግዘውን ህዝብ እያስተዋለ ነበር። ታምራት እራሱን መሸንገሉን ለማቆምና ከተቆለፈበት የብረት ግቢ ለመውጣት ይችል ዘንድ ካታንጋዎች አስተዋፆ ሳያደርጉለት እንዳልቀሩ የራሴ ጥርጣሬ አለኝ።

(ታምራት ላይኔ የታሰረበት ወይም ከህወሃት ጋር የተጋጨበት ምክንያት ሙስና እንዳልሆነ ብዙዎች የኢህአዴግ አባላት በርግጠኛነት ይናገራሉ። ውስጥ ውስጡን የሚነገረው ታምራት አውሮፓ ለጉብኝት በሄደበት ወቅት ከኢህአፓ ጋር ምስጢራዊ ግንኙነት አድርጎአል የሚል ነበር። በሙስና ምክንያት የታሰረ የኢህአዴግ አባልም እስከ ዛሬ የለም። ህወሃት የአባል ድርጅት አመራር አባላትን "ብላ! ጠጣ! ደስ ይበልህ፣ የፖለቲካ ተቃውሞ ግን አታንሳ" በሚል መርህ እንደሚያሰተዳድራቸው የሚታወቅ ነው።)

* * *

አብርሃም ረታ አለሙ አብረውት ካሉት ጋር የሞቀ ጨዋታ እንደያዘ አሻግሬ አየሁት። "አልን፣ ተባልን፣ ይባላል" የተባለ መጣጥፉ በተወዳጅነት ከመዘገብኳቸው መካከ ል አንዱ ነው። አብርሃም በዚህ መጣጥፉ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ መለስ ዜናዊ ያለውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት በአስቂኝና በገላጭ መንገድ ማቅረብ የቻለ የብእር ጀግና ነው። ለአብነት የኤርትራውን የቀይ ኮከብ ዘመቻ እንዴት እንደገለፀው ልቀንጭብላችሁ፣

"የሰሜኑን ክፍለ ሃገራችንን ችግር ለመፍታት "ቀይ - ኮከብ" ዘመቻ ብቸኛው አማራጭ ሆነና ጉድ ጉድ ተያዘ። እና አስመራና ምፅዋ በቀይ አጊጠው "ቀይ" ተመከረባቸው። ህዝቡም "ቀይ" አሰበ። ውጤቱም "ቀይ" ሆኖ ቀረ። ወዲያው ኢህድሪና ህገ መንግስት ተባለና ህዝቡ "ቀይ" ሙታንቲ በሰማያዊ ኮትና ሱሪ ለብሶ..." እያለ ይቀጥላል። ፈልጉና አንብቡት።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

* * *

ሞገስ ሃብቱ ብቻውን ቆሞ በርቀት አየሁት። ገፅታው ላይ የተለመደው አለመደሰት ረብቦአል። መቸ ይሆን የሚስቀው? ቢስቅም ለነገሩ የንዴት ሳቅ ነው የሚስቅ። እና አንድ ቀን "ጥርስና ሳቅ" የሚል ግጥም አምጥቶ ሰጥቶኝ ነበር። ሙሉው ትዝ አይለኝም፣ ጥቂት ስንኞችን ግን በፍፁም አልረሳቸውም፣ እንደ አባቴ ስም በአይምሮዬ ላይ ተቀርፀዋል፣

ካንገት በላይ ስንሰቅበት - የዘመኑ ጥርስ አረጀ፣
ሳቅ ራሱ ጥርስ ናፈቀ - ጥርስም ፈገግታን ጎመጀ፣
ምነው ሰው ሁሉ ሳቅ ራበው ፣
ምነው ሰው ሁሉ ጥርስ አጣ፣
ቁም ነገር ዳዋ ለበሰ - ህይወት ሆነ የለበጣ፣
ጥርስ መሳቂያ ጊዜ አጣ - ማንክ ብቻ ሆነ ሰራው፣
ክልክ በላይ መብላት ለምዶ - ሆዳችን እያስፈራራው፣
የትውልድ ጥርስ ሻገተ - አጓጉል ሰራ በዛበት፣
ያልሰራንበትን ጎርሰን - የሰው ላብ ሰናኝክበት፤

ሞገስ የኢህአዴግ ታጋይ መሆኑን አትርሱ። በረከት ስምኦንም ሆነ ሌሎች አለቆቹ ሞገስን እንደ ፍቅር እስከ መቃብሩ ጉዱ ካሳ እንደ ንክ የሚያዩት ይመስለኛል።

* * *

እነሆ እንግዶቼ ሁሉ ገብተዋል! ያልመጡት ባይመጡም የመጡት መጥተዋል፤ በደንቡ መሰረት ንግግር ለማድረግ ወደ መድረኩ ወጣሁ። የሃገሪቱ ድንቅ የስነጥበብ ሰዎች በአብዛኞቹ እዚህ አሉ። ሁሉም ወዳጆቼ ናቸው። ይህም የስንብት ግብዣ ነው።

አጭር የንባብ ንግግር አደረግሁ።

ወጣቶቻችን ለፅሁፎቻቸው መድረክ ያገኙ ዘንድ ሁሉም ጥረት እንዲያደርግ ከመማፀን ያለፈ ልናገረው የምችለው አልነበረኝም። አማረ ማሞ ለጥቀው ተናገሩ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ማሞ ውድነህና ደረጀ ደስታ ቀጠሉ። ደረጀ ደስታ ድንቅ ብእረኛ ነው። በተለይ ወደ አያቶቹ የገጠር ቀበሌ ወደ ጎጃም ሄዶ "አፈርና ሰው" ሲል የፃፈውን መጣጥፍ መቼም ቢሆን እንዳደነቅሁ እኖራለሁ። እኔ የገበሬ ልጅ ነኝ፤ የደረጀን ያህል ስለ ገበሬው መግለፅ ባለመቻሌ ግን እቀናበታለሁ።

ስብሃት ገብረእግዚአብሄር ተራቸው ደረሰና ወደ መድረኩ ወጡ።

ህንዶች ችግር በገጠማቸው ጊዜ ወይም ዋስትና ባጡ ጊዜ እንዲህ እንደሚሰባሰቡ በመግለፅ ያቺን ምሽት አወዳደስዋት። "ተሰባስበን ስንነጋገር ደህንነት ይሰማናል" ሲሉም አከሉበት። ስለኔም ጥቂት ተናገሩ። የሃላፊነቱን ስራዎች ሁሉ ትቼ ወደ ፅሁፍ ስራ ብቻ አተኩር ዘንድ መከሩኝ።

"ስራ አስኪያጅነቱን ተወውና ዝም ብለህ ፃፍ!" በማለት እንግዶቼ ፊት ሲነግሩኝ ለመኮብለል ሁለት ቀናት ብቻ እንደቀረኝ የጥበብ አማልክት ሹክ ብለዋቸው ይሆን? ስል ለራሴ አንጎራጎርኩ። አጠገቤ ቆሞ የነበረው ደረጀ ደስታ፣

"እንደ ስብሃት የማምንበትን እንደ ልቤ የምናገርበት ቀን ይናፍቀኛል" አለኝ።

ከስብሃት በመቀጠል አቦነህ አሻግሬ መድረኩን ያዘ። በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ክፍል መምህር አቦነህ ያልተጠበቀ ንግግር በማድረግ የእንግዶቼን ትኩረት መሳብ ቻለ፣

"ተጋባዦች! ዛሬ ሲታደለን የዋለውን መፅሀፍ የመጨረሻ ገፅ አንብባችሁዋል?" ሲል በጋለ ድምፅ ከጠየቀ በሁዋላ ቀጠለ፣ "...ተስፋዬ ገብረአብ በፈረመበት ማስታወሻ ይህ "እፍታ" የመጨረሻው ቅፅ መሆኑን አስፍሮአል። ምክንያቱንም "ከአቅም በላይ" ሲል ነው የገለፀው። እኛ የማንፈታው ከአቅም በላይ የሆነበት ችግር ምንድነው? "እፍታ" የኛ መድረክ ናት! መዘጋት የለባትም..."

ተጋባዦች ድንገት መነጋገር ጀመሩ። በመጠኑ ሰጋሁ። በመፅሀፉ መጨረሻ የሰፈረውን ማስታወሻ ባለቀ ሰአት ነበር ያስገባሁት። በግብዣው ላይ የሚያነበው ይኖራል ብዬ ግን አልገመትኩም ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ደምሴ ፅጌ ወደኔ መጣና ጠየቀኝ፣
“ለምንድነው ልትዘጋው የወሰንከው?”
“ችግር አለ” አልኩ በደፈናው።
“ሊፈታ የማይችል ችግር ነው?”
“ይመስለኛል”
አቦነህ አሻግሬም እንዲሁ አፋጥጦ ያዘኝ፣
“ምን ሆነሃል?”
“ምንም አልሆንኩም”
“የደረሰብህ ችግር አለ?”
“ብዙም አይደለም፣ አቦነህ”
ደረጄ ደስታ በጥርጣሬ ሲያጤነኝ አየሁትና አይኑን ሸሸሁት። ኡቅባይ በርሂም ስጋት ተሰምቶት ነበር። የትግራይ አምቼ ነው። ወደ ደጅ ይዞኝ ወጣ።
“አዲስ ነገር አለ እንዴ?” ሲል ጠየቀኝ።
“ሌላ ቀን እነግርሃለሁ” አልኩት።
ከኡቅባይ ስለያይ መአዛ ብሩ ያዘቺኝ። አስጨንቃ ጠየቀቺኝ። ከመአዛ ጋር ያለን ግንኙነት የቤተሰብ ያህል ስለ ነበር ጥቂት ነገርኳት፣
“በረከትና ክንፉ አልፈለጉኝም፤ መአዛ”
መአዛ ሳታመነታ አስተያየት አቀረበች።
“ስራውን ለምን አትተወውም ታዲያ? እኛ ዘንድ ና! ብዙ የምትሰራው ስራ አለ! ለምን ራስህን ታሰቃያለህ!?”
መአዛ “አደይ ፕሮሞሽን” የተባለ ድርጅት ባለቤት ናት። ሆኖም ቀረውን ዋና እውነት ለመአዛ ለመንገር ሳልደፍር ቀረሁ። ጊዜው አልነበረም። የክንፉና የበረከት ሰዎች በግብግቡ ላይ መኖራቸውን አውቃለሁ። በአስር ሺህዎች የተከፈለበት ግብግብ በክንፉና በበረከት ፈቃድ የተደረገ እንደመሆኑ እዚያ የተወራችው ሁሉ ማምሻውን እንደምትደርሳቸው አውቅ ነበርና ዋናውን ምክንያት ለመአዛ ለመንገር ሳልደፍር ቀረሁ።
የወዳጅቼ መጨነቅ ግን ክፉኛ አሰቃየኝ። ወደ መፀዳጃ ቤት ገባሁና ልቤ ላይ አፍኖ ያሰቃየኝ የነበረውን እንባ ያለገደብ ለቀቅሁት። የጎርኪይን አባባል ልዋሰውና ከልቤ ገንፍሎ የወጣው እንባ ውስጤ ተከማችቶ የከረመውን ጥላቻ አጥቦ ይዞት ወጣ...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 16 -
የማይጣላ ህሊና

አይንን ተከዋክብት - ያስተካክልና፣
ጥርስን ከከናፍር - ያሸሞነሙንና፣
የሚጨለፍ ፀዳል - ያጎናፅፍና፣
ከራስ እስከ ጥፍር - ውበት ይቀባና፣
ያን ተክለሰውነት - ያንን ውብ ቁመና፣
አድርጎት ይቀራል...
የማስተዋል ምስኪን፣ የመገንዘብ ወና፣

(ግጥም - አረጋሽ ሰይፉ)

ኢትዮጵያን ለቅቄ ከመኮበለሌ ሃያ ቀናት በፊት በረከት ስምኦን ቢሮው ካስጠራኝ በሁዋላ የሚከተለውን ነገረኝ፣

"በገዛ ገንዘባችን በሚታተም መፅሄት እየተሰደብን ልንቀጥል አንችልም። ጎንደር ሄደህ በሰራኸው ስራ ብዙ ጓዶችን አቁስለሃል። ስለዚህ የምትመራው ድርጅት የሚዘጋም ከሆነ ወይም ሌላ የሚደረግ ካለ በቅርቡ ውሳኔያችንን እንነግርሃለን!"

በረከትን ተሰናብቼ ወጣሁ።

እንደገና በሶስተኛው ቀን የፀጥታው መስሪያ ቤት ሹም ክንፈ ከጠራኝ በሁዋላ ለሻእቢያ መረጃዎችን የማቀበል ስራ እንደምሰራ ከተለያዩ ምንጮች ጥቆማዎች እንደደረሳቸው ነገረኝ። አያያዘናም ጥቆማውን የሚያረጋግጥ በቂ መረጃ አለማግኘታቸውን በማከል የኔን ምላሽ ጠየቀኝ፣

አልደነገጥሁም!

የክንፈ ንግግር አስደንጋጭ ቢሆንም ያልደነገጥሁበት ምክንያት ነበረኝ። የከረመ ወሬ ነበር። በዚያው ሰሞን አንዳንድ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የግል ጋዜጦች ይህን የመሰለ ስም ማጥፋት በኔ ላይ እየፃፉ ነበር። የአብዮታዊ ዴሞክራሲና የወይን ጋዜጦች ዋና አዘጋጆችም ይህን የመሰለ ወሬ ማስወራት ከጀማመሩ ሰነባብተዋል። ከፋና ሬድዮ ስራ አስኪያጅ ከሙሉጌታ ገሰሰ ጋር ባቡር ጣቢያው አጠገብ ከሚገኘው ከረንቦላ ቤት ተገናኝተን ስለዚሁ ጉዳይ አንስተን ስናወራ፣ "የሻእቢያ ሰላይ ነህ ብለው ካመኑ ምን ወሬ ያስፈልጋል? መፍትሄው አንተን በድብቅ መከታተል ብቻ ነበር" ሲል የግል አስተያየቱን ነግሮኝ ነበር። ዞሮ ዞሮ በተለያዩ መነሻዎችና ፍላጎቶች፤ ታዘውም ሆነ በግላቸው በሚዲያው አካባቢ ስሜን የማጥቆር ዘመቻዎች በማካሄድ ላይ መሆናቸው ግልፅ ነበር። በመጨረሻ ይኸው ክንፉ ቢሮው ጠርቶ መልሶ ለኔ ይነግረኛል፤

(ከኮበለልኩ በሁዋላ ጣቢያ ጋዜጣ በግንቦት 2, 1993 እትሙ፤ የሻእቢያ ሰላይ ሆኜ ቆይቼ ስራዬን አብቅቼ እንደወጣሁ ፅፎአል። አያይዞም በፕሮፓጋንዳው ዙሪያ ያሉ ካድሬዎች 'የሚሰማን አጣን እንጂ ተናግረን ነበር' ብለው መቆጨታቸውን ዘግቦ አንብቤያለሁ። Indian ocean news letter በቁጥር 949 እትሙ እኔን በተመለከተ በአብዛኛው ሃሰት የሆነ ዘገባ አትሞአል። የኢህአዴግ መሪዎች ጥሎአቸው የሚሄድ አባላቸውን ቀድመው ስም የማጥቆርን ዘዴ እንደሚጠቀሙ አውቃለሁ።)

የሆነው ሆኖ ወሬው ሃሰት መሆኑና ሚዲያዎችም እየፃፉት እንደከረሙ ባጭሩ ላስረዳው ሞከርኩ።

ክንፉ አዳምጦኝ ሲያበቃ፣

"ወሬው ሃሰት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ወደፊት እናየዋለን" ሲል ጀመረና "...አንተ ላይ ብዙ ግፊት አለብን!" ሲል አከለበት። እናም አሰናበተኝ።

ክንፉ ሰበብ ፈጥሮ እኔን ከሃገር እንዲያባርር መታዘዙን ጠረጠርኩ። የቡርቃ ዝምታ አልተመቻቸውም። በጋዜጦች ላይ በፃፍኳቸው ደግሞ በረከት ቂም ይዞአል። ይኸው ነው። ያ ባይሆን ኖሮ ክንፉ ቢሮው ጠርቶ፤ አይኔን ማየት እየሸሸ፤ በተለሳለሰ ሁኔታ አያናግረኝም ነበር። በርግጥ የሻእቢያ ሰላይ ነው ብለው ጠርጥረው ቢሆን ኖሮ እንደ አሰፋ ማሩ ግንብ አስደግፈው ይረሽኑኝ ነበር...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

.....ብፁእ አቡነ መርቆርዮስ በኬንያ በኩል ሲሸሹ ክንፉ ያውቅ የነበር ሲሆን፣ መንገድ ላይ ችግር እንዳይገጥማቸውም ጥበቃ ተደርጎላቸዋል። እሳቸው ግን ያን አያውቁም ነበር። አሰፋ ጫቦ ላይ በተሰራው ድራማ እኔም ተካፋይ ነበርኩ። የደራሲና የገጣሚ አበራ ለማን ጉዳይም ወሬ ሰምቻለሁ። በተለመደው ድራማ እንዲኮበልል ነበር የተደረገው። እውቁ ዲፕሎማትና ጋዜጠኛ ማእረጉ በዛብህም ለመኮብለል ፈቃደኛ ባለመሆኑ፤ ያለ ስሙ ስም ተለጥፎለት እስር ቤት እንዲሰነብት ተደርጎአል። የቴሌቭዝን ድርጅት ስራ አስኪያጅ ተሾመ አስራት በተመሳሳይ 'ውጣ አትበለው እንዲወጣ አድርገው' እንደሚባለው ተገፍቶ መኮብለሉን እያወቅን እንዳላወቅን ከራርመናል። ፕሮፌሰር ታዬ ወልደሰማያት ከአሜሪካ እንዳይመለስ ተነግሮት ነበር። ፈቃደኛ ባለመሆኑ አምስት አመት ተቆለፈበት። አሰፋ ማሩ በጥይት ተደብድቦ የተገደለው በእንግሊዝ ሰላይነት ተጠርጥሮ እንጂ የደህንነቱ መስሪያ ቤት የተጨበጠ ማስረጃ አልነበረውም። ታምራት ላይኔ "ተመክሬ፣ ተመክሬ አልሰማ ብያለሁ" የተሰኘውን ታሪካዊ ንግግር ያደረገው "ይህን ካልተናገርክ ብሌን የተባለውን ልጅህን አይንህ እያየ እንገድለዋለን" ብለው ስላስፈራሩት መሆኑን ታምራት ራሱ ተናግሮአል።

...አለቆቼ ያልፈለጓቸውን ሰዎች ለማስወገድ ከጃንሆይና ከደርግ የተለዩ ስልቶችን ይጠቀማሉ። ጃንሆይ የተቀነባበሩ አደጋዎችንና የመጠጥ ቤት ግጭቶችን ይጠቀሙ የነበረ ሲሆን፤ ደርግ ሰበብ አይፈልግም፤ ገድሎህ በሬድዮ የፍየል ወጠጤን ያስዘፍናል። የኔዎቹ ሰዎች የማስወገጃ ስልት ካለፉት ስርአቶች ሁሉ የተለየ ነው። በቅድሚያ ከቀይ ሽብር ጋር እንደምንም ሊያያይዙህ ይሞክራሉ። አልያያዝ ካላቸው ሙስና የሚመስል ነገር ለማግኘት ደፋ ቀና ይላሉ፤ ወይም አንብበውት የማያውቁትን የፈረደበትን ህገመንግስት ይጠቅሳሉ። ህጋዊ ይመስል ዘንድ ደግሞ ፍርድ ቤት እያመለሉ፣ በቲቪ እያሳዩ ያሸማቅቁሃል።

ለመታሰር የሚያበቃ ሰበብ ፈልገው ካጡ እንድትከበልል ያስፈራሩሃል፤ የድርጅት አባል ከሆንክ ደግሞ በጎን ያስመክሩሃል። እንድትታሰር የታዘዘበትን ወረቀት እንድታይ ይደረጋል። አንተ ሚስጥር ያገኘህ ይመስልህና እንደ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ገበሬ ለብሰህ፤ እንደ ተዋናይ ድራማ እየሰራህ በሞያሌ በኩል ስትገሰግስ እነሱ እየሳቁ ኬላ ላይ እንዳትያዝና እንቅፋት እንዳይገጥምህ መንገዱን ያመቻቹልሃል። አንድ ሰሞን በሬድዮ የጉዞ ጀብድህን ከለፈለፍክ በሁዋላ ለዘልአለሙ ትረሳለህ። አለቀቹ "ሰላይነት" የተባለችውንም እንደ አንድ ፍቱን ዘዴ ይጠቀሙባታል! ከአሜሪካ ከመጣህ CIA የሚል ወሬ ሲያስወሩብህ 'ከነገሩ ዖም ይደሩ' የተባለውን ያልተዘፈነ ዘፈን እየዘፈንክ ትኬትህን ታድሳለህ። የምር ለCIA እንደሚሰራ የሚታማ ሰው ሲሾምና ሲሸለም ትመለከትናም የአገርህ ነገር ግራ ፈትል ይሆንብሃል።

እንግዲህ ልዩ ልዩ ታርጋ እየተለጠፈላቸው የተገደሉ፣ የታሰሩና ከሃገር የተባረሩ ዜጎችን ቤቱ ይቁጠራቸው።

እኔም ታዲያ ከስርአቱ ጋር እጅና ጓንት ሆኜ ቢያንስ በሚዲያ በሚደረጉ የስም ማጥፋት ዘመቻዎች ላይ ሰርቼያለሁ። በአንድ ወቅት "ማኔ ተቂል - መስፍን" በሚል ርእስ እፎይታ መፅሄት ላይ ስለፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የሰፈረው ባብዛኛው ነጭ ውሸት ነበር። የኛ ዘመን አንበሶች ቃላትና አሳብ እያዋጡ የሚፅፉዋቸውን የማተም ግዴታ ነበረብኝ።

እነሆ እኔም ተራዬ ደረሰ!

ለኔ የተዘጋጀችልኝ የማስወገጃ ታርጋ ደግሞ "የሻእቢያ ሰላይነት" ሆነች። ያን ቀን ከክንፉ ቢሮ ከወጣሁ በሁዋላ የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን ጥቂት ስንኞች ለማስታወስ እየሞከርኩ ወደ ቢሾፍቱ ነዳሁ። እዚያ ለማደር ወስኜ ነበር፣

የማይጣላ ህሊና ያለው!
እንዴት የታደለ ነው?
ህሊናውን የገደለ ሰው!
ማን ሊቀረው? ምን ሊያቅተው?
የጉልበቱ መሳሪያ ነው!
ጊዜ ጉልበቱን እስቲሰብረው!

* * *

በወርሃ ሚያዝያ 1993 አንድ ቀን ማለዳ ቀላል ሻንጣ አንጠልጥዬ ከቦሌ አየር ማረፊያ ተገኘሁ። የቤት እቃዬንና መፃህፍቶቼን እንዳሉ ትቼያቸዋለሁ። ሆኖም ድንገት መንገዴ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተደናቀፈ። ከመጨረሻው ፍተሻ ላይ ካሉት ፓስፖርት መርማሪዎች አንድዋ ዱብ እዳ አፈነዳችብኝ።

"ተስፋዬ ገብረአብ... ከሃገር እንዳትወጣ የሚል መመሪያ ከፀጥታው መስሪያ ቤት ደርሶናል" አለችኝ።

ክንፈ ከርቸሌ ሊልከኝ ማሰቡን ጠረጠርኩ፣

"ለምን?" ስል ጠየቅሁዋት።

"እሱን አላውቅም" አያያዘችና "....ለማንኛውም ተከተለኝ"

እየመራች ወስዳ ለአንዲት በእድሜ የገፋች ሴት አስረከበችኝ። የተረከበችኝ ሴት አንድ ወንበር ላይ ጎልታኝ ወደ ውስጥ ገብታ ስልክ ደወለች። በሩን ስላልዘጋችው ስትነጋገር ይሰማኛል። ጆሮዬን ጣል አደረግሁ፣

"መጥቶአል፤ አለ...አዎ..." የሚሉ ቃላትን ሰማሁ። ቆየችና ደግሞ ምላሽ ቀጠለች፣ ድምፅዋን ለመቀነስ አልሞከረችም፣

" . . . አ ለ ... እ ዚ ሁ ነ ው . . . ም ን ም አላልነውም...አዎን...አዎ...አይ...እሺ...እሺ...ገብቶኛል!"

ስልኩን ዘግታ ወደኔ መጣች። በፈገግታ ተውጣ ፓስፖርቴን እየመለሰችልኝ እንዲህ አለችኝ፣

"በስመ ሞክሼ ስለሆነ ያቆየንህ ከይቅርታ ጋር መንገድህን መቀጠል ትችላለህ!"

በዚያችው ቅፅበት አንድ ሃሳብ ብልጭ አለልኝ፣

"ክንፈ ዘንድ ነበር የደወልሽው?" ስል ጠየቅሁዋት።

"እ! አይ! አይደለም! አቶ ክንፈ አይደሉም!"

በድንገት ስለጠየቅሁዋት ገፅታዋ ላይ ከሚነበበው ድንጋጤ ሁሉንም ተረዳሁ። የደወለችው ለክንፈ ነበር።

"ክንፈ ካልሆነ እኔን ሊያስቆመኝ የሚችል የለም ብዬ ነው!" አልኳት

"አይ! እሱን አናውቅም! አሁን መሄድ ትችላለህ!"

ከአንድ ሰአት ተኩል በሁዋላ አይሮፕላኑ ናይሮቢ አረፈ። በእድሜ የገፋችው ሴት በሩን ሳትዘጋ ክንፈን ያነጋገረችው እንደዚያ እንድታደርግ ታዛ ሊሆን እንደሚችል እያውጠነጠንኩ ናይሮቢ ገባሁ። ክንፈ ከያዘኝ በሁዋላ መልሶ ለምን ሊለቀኝ እንደወሰነ ሳልጠይቀውም ተገደለ!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ክ ፍ ል ሁ ለ ት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 17 -
የባከኑ የኛ ሰዎች

ማነህ የተኛኸው?
እንቅልፍ የደበተህ - ሲጋህን ጥለኸው፣
ምን ኖረሃል አንተ? ኖረሃል ወይ አንተ?
አጥንትህ ወላልቆ - እንዲህ የሻገተ፣
ከሙታን ማህበር - በመዝገብ ገብተሃል፣
ማንኛውም አጥንት - አስከሬን ሆነሃል፤

(ግጥም - ገብረክርስቶስ ደስታ)

እነሆ! ዳግም ስደተኛ ሆንኩ...

በአንድ ጠባብ ማድቤት ውስጥ ከሃያ የማናንስ የአፍሪቃ ቀንድ ስደተኞች ተጠቅጥቀናል። በዚያች ጠባብ መጠጥ ቤት በአግዳሚ ወንበሮች ላይ የተኮለኮለው ሁሉ ጫቱን ወይም ቢራውን እያሻመደ ይቆዝማል።

የሚሊማኒ ቀበሌ አካል የሆነው ሴጎር ከናይሮቢ መሃል ከተማ ላይ የሚገኝ ቢሆንም፣ ቁጭራ ሰፈር ነው። ቤቶቹ በዛገ ቆርቆሮ የተሰሩ፣ መፀዳጃ ቤታቸው ቱቦው ሞልቶ የተደፈነ፣ ስጋውም ዳቦውም ተደራርቦና ተከማችቶ ባልፀዳ ሁኔታ የሚሸጥበት አስቀያሚ መንደር ነው። ማደሪያዬ በዚያ መንደር ባይሆንም በራሴው ፍላጎት ከእኒያ አጋጣሚ ካሰባሰባቸው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስደተኞች መካከል መዋል መርጫለሁ።

የሚያውቀኝ የለም። ስሜንም ቀይሬያለሁ። IS እና WAS የማይገባበት እንግሊዝኛ በዚያች ማድቤት በጭንቅላቱ ቆሞ ዳንኪራውን ያስነካዋል። ኤርትራውያን ትግርኛ ይናገራሉ። አማርኛና ኦሮምኛም በዚያች ማድቤት ዋና ቋንቋዎች ናቸው። ከስደተኞቹ ሁሉ እኔ የተለየ እድል ነበረኝ። ይህም ለሶስቱም ቋንቋዎችና ባህል ቅርብ በመሆኔ የሁሉም ወዳጅ ለመሆን መቻሌ ነበር።

ዛሬም ከምሳ በሁዋላ በዚያች ጠባብ ማድ ቤት ተገኝቻለሁ። እንደምንጊዜውም ዱባለ በመዋጮ የተሰጠውን ጫት እየቀረጣጠፈ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሃሜቱን ያስነካዋል።

"የሰው ምክር አትስሙ!" እያለ ነበር ዛሬ ደግሞ "... የሰው መጥፊያው የሰው ምክር ነው! እኔ እንዲህ ሆኜ የቀረሁት በሰው ምክር ነው!"

"ምን ሆንክ?" ስል ጠየቅሁት።

"ፍቅር የሚባል ነገር አላውቅም። የዋህ ብሆንም ጨካኝ ነኝ! ፈልፈላ ሳይ በተለይ ደሜ ይፈላል። ህፃናትን አልወድም። መላኩ የሚባል የትምህርት ቤት ጓደኛዬን ምክር በመስማት ነው ለዚህ የበቃሁት። ልንገራችሁ ታሪኩን?" ሲል ዙሪያ ገባውን ጠየቀ።

ምላሽ የሰጠው አልነበረም።

እሱ ግን ቀጠለ

"...አንዲት ፍየል የምትመስል ቀይ ልጅ ወድጄ ነበር። የላይኛው ከንፈሯ ላይ እንደ ወንድ ጢም ያበቀለች እስስት ነገር ናት። 'ፍቅርሽ ነጋ ጠባ እንደ ፀሃይ ብልጭ ይልብኛል' የሚል ደብዳቤ ፃፍኩላት። መላኩ ያልኳችሁ ጓደኛዬ ነው የፃፈላት። እኔ መለማመጥ አልወድም። እኔ በላኩላት ደብዳቤ ጀርባ ላይ ምላሽ ፃፈችልኝ። ምን አለችኝ መሰላችሁ? 'ብልጭ እንዳለብህ ድርግም ይበልብህ! አንተ አባጨጓሬ ፊት!!"

ከፍተኛ የአጀብ ሳቅ ያችን ማድቤት ነቀነቃት።

በርግጥም ዱባለ ፊቱ እንደ አባጨጓሬ ማስፈራሪያ አይነት ስለነበር ሳቃቸውን ማቆም ያልቻሉም ነበሩ።

ወርቁ ግን አልሳቀም።

ከዱባለ ጋር አይዋደዱም። ወርቁ ቀይና አጭር ሲሆን እድሜው 56 መድረሱን ይናገራል። የአፄ ሃይለስላሴን ልጆች

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንግሊዝኛ ማስተማሩን ደጋግሞ የደሰኮረልን ቢሆንም ያመነው የለም። በዚያች የደከመች መንደር ከሚኖሩት ስደተኛ ሃበሾች የተሻለ እንግሊዝኛ እንደሚናገር ግን ማሳመን ችሎአል።

ሳቁ ጋብ ሲል ጠበቀና ዱባለ ቀጠለ...

"ያን ደብዳቤ ካነበብኩ በሁዋላ የፍቅር ዘር ከልቤ ውስጥ ጠፋ! በቃ! ጨካኝ ሆንኩ። ትምህርቴንም አቋርጬ ወደዚህ ወደ ናይሮቢ ተሰደድኩ። አሳቤ አሜሪካ ለመሄድ ነበር። እንደምታዩኝ ግን ይኸው 19 አመት ሞላኝ እዚህ። ጫት እየለመንኩ እቅማለሁ..."

"ስራ ለምን አትሰራም?" ስል ጠየቅሁት።

ዱባለ ፈገግ አለ።

"ባንድ ወቅት የታወቅሁ ሃብታም ነበርኩ። ሂና እነግድ ነበር..." ካለኝ በሁዋላ አያያዘና ጠየቀኝ "...ሂና ታውቃለህ?"

"ህንዶች የሚቀቡት አረንጓዴ ነገር..."

"ልክ ነህ!" አለና ቀጠለ "...ሂና በጣሳ እያሸግሁ ለአከፋፋዮች አቀርብ ነበር። ጥሩ ስራ ነበር። ቅጠል ሰብስቤ አደርቅና አብኩቼ በጣሳ እሞላዋለሁ። ከዚያም እውነተኛውን ሂና የያዘ ገረወይና እገዛና ከዚያ ላይ እየቆነጠርኩ የኔን ጣሳዎች ከላይ አመሳስላቸዋለሁ። ነጋዴዎችም ጎሸዎችም እውነተኛ ሂና መሆኑን ለማረጋገጥ ከላይ ያለውን ነው የሚመረምሩት። እስኪነቃብኝ ድረስ ቸበቸብኩት። የኔ ወንድም! ቸበቸብኩት ነው የሚባለው። በመጨረሻ ግን ተያዝኩ። ሶስት ቀን ታስሬ ተፈታሁ። ኬንያ ነው አገሩ። ምን ችግር አለ? ለፖሊስ ካነረስከው ይለቅሃል..."

ወርቁ ጢሙን በዝምታ እየጎተተ ጫቱን ይቀረጣጥፋል! መድረኩ በዱባለ ስለተያዘበት አኩርፎአል። ያንኑ የአፄ ሃይለስላሴን ልጆች እንግሊዝኛ ማስተማሩን ሊደግምልን ካልሆነ ግን ሌላ ወሬ አይኖረውም። ግፋ ቢል ግን ስለ እናቱ ፍቅር ሊተርክ ይችላል። ስለ እናቱ መናገር ከጀመረ ካላለቀሰ አያቆምም።

አንድ ቀን እንዲህ አልኩት፣

"56 አመቴ ነው እያልክ እንዴት ስለ እናትህ እያነሳህ ታለቅሳለህ?"

በዚህ ጥያቄዬ ወርቁ በጣም ተበሳጨ።

"የእናት ፍቅር በእድሜ ይለካል ያለህ ማነው? ደግሞም

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እናት ሲባል የሁሉም ሰው እናት አንድ አይነት ናት? የኔ እናት ዝም ብሎ 'እናት' አልነበረችም። ቃል ያንሳታል! ባጭሩ ግን 'እናት' ነበረች። ከመነሻው ልዩ ነገሯ ወልዳ አሳድጋኛለች! ልጅ እያለሁ በየደቂቃው ትስመኝ ነበር። ፋፋ እየገዛች መግባኛለች። ሌላው ሁሉ ቀርቶ 'ወርቁ' የሚለውን ስም ያወጣችልኝ እናቴ ናት"

እንባ ያቀረሩ አይኖቹን ካበሰ በሁዋላ ዱባለ በአካባቢው አለመኖሩን ባይኑ አረጋገጠ ዲስኩሩን ቀጠለ "... ለምሳሌ ስለ ዱባለ እናት ልንገራችሁ? የስድስት አመት ልጅ ሳለ እንጀራ ሰረቅህ ብላ አናቱን በፍልጥ ተርትራዋለች። ራሱ ነው የነገረኝ። ጠባሳውን ጭምር አሳይቶኛል"

አንዱ ስለሌላው የሚያነሱት ከሁለት አንዳቸው ከሌሉ ብቻ ነው። አለበለዚያ ለጠብ ይገባበዛሉ። እኔ ባለሁበት እንኳ ሶስት ጊዜ ያህል ለጠብ ተያይዘው ገላግለናቸዋል። ዛሬ ግን ዱባለ መድረኩን ብቻውን ይዞታል፣

"ተስፋ መቁረጥ የለብህም! ጫት መንገድም ቢሆን ስራ ልትጀምር ትችላለህ" አልኩት ዱባለን።

ዱባለ ግን ምክሬን አጣጣለው፣

"ጫት ነግደህ የትም አትደርስም፣ የኔ ወንድም። ደግሞ አዲስ ምክር የሰጠሽኝ አይምሰልህ። ሞክሬዋለሁ። ያልሞከርኩት ስራ የለም። ሌላው ቀርቶ ከሁለት አመት በፊት ሞምባሳ ሂጄ ነጭ አሜሪካዊት ለማግባት ሞክሬ ነበር። ነጮች ራስታ ስለሚወዱ ሹሩባ ተሰርተህ ሞምባሳ ሂድና እድልህን ሞክር ብላ ያታለለቺኝ አንዲት ወፈፌ ኡጋንዳዊት ናት። ያኔ ጅል ስለነበርኩ የሰው ምክር ሰማሁና ተነሳሁ። ለነገሩ እሷ ሰው ልትባል አትችልም። ጭንቅላትዋ ላይ ፀጉር የሚባል የላትም። ዊግ መቀጠል ስላልቻለች የፀጉር ኮፍያ ነው የምታደርገው። የሆነው ሆኖ ራስታ ለመሆን ቆርጬ ተነሳሁ። ሆኖም ፀጉሬን ለማሳደግ መቼም አስር አመትም አይበቃ! እዩት ፀጉሬን ... እንደ በረሃ ግራር ክችች ያለ ነው። ዊግ ተሰራሁና ባቋራጭ ራስታ ሆንኩ! ከዚያም በባቡር ሞምባሳ ገባሁ።

ናይት ክለብ!

ሸሌ አበሾች ብዛታቸው! ገና ሲያዩኝ ሴቶቹ ደማቸው ፈላ! ወንድ የምሻማቸው ይመስል በቅናት አበዱ! የአበሻን ቅናት በእግሩ ቆሞ ሲሄድ በአይኔ ያየሁት ያን ቀን ነው። እስቲ ከልብ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ንገሩኝ? ሰው እንዴት በኔ ይቀናል? ...ገና በገና ነጭ አግብቶ አሜሪካ ይገባል ብለው መቅናት!

አቤት አበሻ! አይ አበሻ!

ወደ ክለቡ ገና ስገባ አንዷ መጥታ ለከፈችኝ፣ 'ምነው ቋንጣ ራስ መሰልክ?' እንዲህ አለቺኝ! አሁን እንዲህ ይባላል? የአገሯ የወንዝዋ ልጅ ነኝ! እውነቴን ነው የምላችሁ፣ ሙዴን ሰረቀችው!

ሌላዋ ደግሞ መጣች፣

'ጠጉርህ አይጥ የበላው ዳንቴል መስሏል!' እንደዚህ አሉኝ እየተፈራረቁ። እንዲህ ይባላል? የስደቱ ስቃይ አይበቃኝም? ቋንጣ ራስ፣ አይጥ... ዳንቴል...ምናምን። እኔ ወንድ ነኝ! የሁለቱንም መንጋጋ መስበር እችል ነበር። ግን ለምን ብዬ? እኔ አላማ ያለኝ ሰው ነኝ። ለአላማዬ ስል አለሌዎቹን ችላ ብዬ፤ ወደ ዳንስ መድረኩ ወጥቼ ነጭ ሴት ቱሪስቶች እንዲያዩኝ ሆኜ መደነስ ጀመርኩ።

እንደዚያን ቀን ተዋርጄ አላውቅም።

በደነስኩ ቁጥር ፀጉሬ እየተነቀለ ይወድቅ ጀመር። ግማሹ ያህል ተነቅሎ እየበረረ ከኔ ተለየ። ሰዎች ይስቁ ጀመር። ምን ታደርገዋለህ? የወዳደቁትን ሹሩባዎቼን ለቃቅሜ ወጣሁ..."

በዚህ መሃል ወደ ታጨቅንባት ማድቤት አንድ ሰው አንገቱን ብቅ አደረገና " ቹቹ ቀበሮን አይታችሁታል?" ሲል ጠየቀን።

እንዳላየነው ስንነግረው ተመልሶ ሄደ። በዚህ ሁኔታ በጣም የተናደደው ዱባለ ነበር። የራሱን ታሪክ መተረክ ትቶ ወደ እንግዳው ሰው ዞረ፣

"ኢያችሁት!? ቹቹ ቀበሮን ፈልጎ የመጣ መሰላችሁ? ጫት ሊለምን ነበር አመጣጡ ወይንም ማን ከማን ጋር እንደሚቅም አይቶ ሊያወራ! ቹቹ ይላል! አበሻ ሲባል መቸም ሆዱ የማይገኝ ገበሎ! ና ቃም ቢባልኮ ሰተት ብሎ ይገባ ነበር! ቦርጩን ኢያችሁት ደሞ?" ሲል ቀጠለ ዱባለ "...ያገኘውን ሁሉ ስለሚውጥ እዩት ምን እንዳከለ!? ደሞኮ ሲያወሩ ሰምቶ ጂም ጀምሬያለሁ እያለ ያወራል። ስድስት ወር ሙሉ ሲያወራ ቦርጩ ግን እንኳን ሊቀንስ እየጨመረ ሄዶአል። ዘጠኝ ወር ሲሞላው አንደኛውን ቢወልድ ይሻለዋል። ሰሞኑን ደግሞ አግብቼያለሁ ሆኖአል ወሬው። ያገባትን ሴት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አይቻታለሁ - እንደዘንቢል አንጠልጥሏት ይዞራል። ድንቢጥ የምታክል ዶሮ ናት። ጣቱ ላይ ቀለበት ስላደረገ ሴት ሊተው? ልንገራችሁ? ትልቅ ቀለበት ተሰርቶ ሁለቱም እግሩ ላይ ካልገባለት ይሄ በፍፁም አይታመንም። ባለፈው ታሞ ሆስፒታል ሲሄድ አብሬው ሄጄ ነበር። ነርስዋ 'ኮትህን አውልቅ' ስትለው የፈለገችው መስሎት ይገለፍጣል። ምን ያስገለፍጠዋል? ኩቱን ዝም ብሎ አያወልቅም? ከፍሎ እየታከመ ቢሆን እኮ ደህና! የነፃ ህክምና ወረቀት ከ UN ይዞ ሄዶ የተፈለገ ይመስለዋል። ፊቱን ደሞ አይታችሁታል? ምን ይመስላል? አባጣ ጎባጣ! ገብጋባ ወፍ የበላው ማንጎ! ሰዎች ውሻና ድመት ሲያሳድጉ አይቶ እሱ ኤሊ ያሳድጋል። የኤሊ እድሜ 300 አመት ነው። የልጅ ልጆቹ እንኳ ትልቅ ሆና ሊያዩዋት አይችሉም። ደሞ ጭካኔው! ከቤት ሲወጣ ግድግዳ ላይ ካለ ሚስማር ላይ ያንጠለጥላታል። 'የእግዚአብሄር ፍጡር ናት፣ ለምን እንደዚያ ታደርጋለህ?' ብዬ ስጠይቀው ምን አለኝ መሰላችሁ? 'መሬት ላይ ከተውኳት ወጥ ትደፋብኛለች' እና እንደ ጃንጥላ ግድግዳ ላይ ያንጠለጥላታል። አሰዳቢ አረመኔ! ሞባይሉን ደሞ አይታችሁታል? እንደ ክላሽ የሚወለወል ከዘራ የሚያክል ሞባይል ይዞ...አያፍርም ሰው ፊት እየመዘዘ ያወጣዋል። ማፊሪያ!"

ያን ቀን ለዱባለ አንድ ቢራ ጋበዝኩት።

ስጋብዘው እሱም አፀፋውን ለመመለስ ነው መሰለኝ ኬንያ ላይ ነባር እንደመሆኑ እንዲህ ሲል መከረኝ።

"ፓስፖርትህን እንዳትጥል! ፓስፖርትህ ከሚጠፋ አንድ እጅህ ቢቆረጥ ይሻልሃል!"

ዱባለ ፖለቲካ የሚያወራበት ጊዜም አለው። የዱባለ ፖለቲካ ግን የመለስ ዜናዊን ራሰ በራነት አንስቶ ከመተቸች አያልፍም።

"ይሄ መላጣ!" ሲል ይጀምራል "ፖለቲካ" ማውራት ያማረው ቀን "... ሰው እንዴት 40 አመት ሳይሞላው ይመለጣል? ጃንሆይ እኮ በ80 አመታቸው እንኳ አልተመለጡም ነበር። መንጊስ ቢሆን? ቡሩሽ ራስ ሆነ እንጂ አልተመለጠም። ይሄ ፀጉሩ በልጅነቱ የከዳው ከሃዲ!"

በሄድኩበት ሃገር ሁሉ መለስን ስለሰደቡ ብቻ ተቃዋሚ ፖለቲከኛ የሆኑ የሚመስላቸው፣ የማይማሩና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መፅሃፍትን የማያውቁ፣ ብኩን አሉባልተኞች በየምግብ ቤቱና በየሻይ ቤቱ ያጋጥሙኝ ነበር። ፀጋዬ ገብረመድህን ለጥራዝ ነጠቅ የዲያስፖራ ፖለቲከኞች ጥሩ ቋጥሮላቸዋል፣

ይሽ ነው የናንተ ኑሮ? - ይሽ ነው የናንተ ዋጋ?
የእውቀትህን ሸርፍራፊ - አንድህ ከአንድህ ሰታላጋ፣
አንጎልህን ከሌላው አንጎል - በመጠዋ ቤት ሰታዋጋ፣
ከፓርቲ ቤት እቁማር ቤት - በሽቅድምድም ሰትንጋጋ፣
ዘመንህ እኮ ጨለመች - የምፅአት ቀንህ ነጋ፣
መፅሃፍ ጋዜጣ ብታነብ - ትምህርት ቤት ብትጋገር፣
የዚህን ሃገር ጨርሰህ - ባህርማዶ ብትሻገር፣
የሃሳብ አበባው ሳይሆን - ፍሬው ነው ትልቁ ነገር፣

ሌላ ቀን ደግሞ ዱባለ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ።

"ይሄ ኩባያ ራስ መላጣ ባንዲራችንን ጨርቅ ብሎ ሰድቦአል እንዴ?"

መለስ ይህን ከተናገረ አስር አመት እንዳለፈው እያሰብኩ በአወንታ ራሴን ነቀነቅሁ።

"ትናንት ነውኮ የሰማሁት" አለኝ በቁጭት ጉልበቱን እየደበደበ። ዱባለ እንድችው እንደለፈለፈ ረጅሙ የከሰት በሁዋላው ጊዜ ሳይታወቀን ያልፋል።

የዚያች ማድቤት ባልደረባ ከነበሩት መካከል ሙሉአለምና ፊሊሞንን አልረሳቸውም። ፊሊሞን ኤርትራዊ ነው። ቀይና ረጅም ሲሆን ሳቂታ ፊት አለው። በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ከተካፈለ በሁዋላ ውጊያው ሲቆም ወደ ኬንያ መጣ። እኛ ዘንድ የደረሰ ሰሞን ስለ ውጊያ ብቻ እየተረከ አስቸግሮ ነበር። ቃላቶቹ ሁሉ መትረየስና ቦምብ ነበሩ። ማድቤታችንን በጦር መሳሪያ አጨናነቃት። እንደምን ም ተረባርበን አረሳሳነው። እየቆየ ሲሄድ እንደኛው ስለ ሴት ማውራትና ሃሜት ለመደ። ብዙ ሲጠጣ ግን መትረየሱን እያነሳ ያዘንበዋል።

ሙሉአለም ዝምተኛ ነው። አንድ ቀን ብዙ ጠጣና ከጎኔ መጥቶ ተቀመጠ።

"እኔ ጥሩ እጅ ያለኝ መካኒክ ነኝ" ሲል ጀመረና ስለ ዝንባሌው ያወጋኝ ጀመር "... ፍላጎቴ ግን አርቲስት መሆን ነበር። ኮሜዲያን መሆን የምችል ሰው ነበርኩ። እዚህ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ወርቁና ዱባለ እድል አልሰጥ አሉኝ እንጂ ጠጪውን ሁሉ በሳቅ ማንፈርፈር በቻልኩ"

"ምንም አይደል" ስል አፅናናሁት፣ "እንዳልተመኙት መኖር የአፍሪቃዊ እጣ ፈንታ ነው"

በዚህ አነጋገሬ በጣም ከመደሰቱ የተነሳ ባገኘኝ ቁጥር፣

"... ያ ያልከኝ አባባል እስካሁን ባይምሮዬ ላይ አለ" እያለ ያስቸግረኝ ጀመር። ይባስ ብሎ አባባሉን በታይፕ አስፅፎ ግድግዳው ላይ መስቀሉን ነገረኝ። ኬንያን እስክለቅ ድረስም ስለ "ጥቅሱ" ታላቅነት እያነሳ ይነዘንዘኝ ነበር።

* * *

ከታጨቅንባት ማድቤት ፊትለፊት ከምትገኝ የቆርቆሮ ሱቅ wa ku peda — wa ku peda" (እወድሻለሁ) የተሰኘ ዘፈን በኪስዋሂሊ ሲዘፈን ይሰማል። የሱቋ ባለቤት ጄራልድ የሚባል ሲሆን፤ እሱም ጫቱን ያኘምዳል። የጄራልድ Wa Ku Peda የተባለ ዘፈን ቀዝቀዝ ሲል ዋናው ጎዳና ላይ የቆሙ ታክሲዎች ተሳፋሪ ፍለጋ ሲጮሁ ይሰማናል። የተሳፋሪ ጥሪ ቃላቸው በፍፁም አትለወጥም። "Bado mutu mojo" ሲሉ ይውላሉ። በኪስዋሂሊ "አንድ ሰው የቀረ" ማለት ነው።

ኤዱ የሚባል የአምስት አመት ህፃን ምንጊዜም ወደ ማድቤታችን ብቅ እያለ ዱባለን "Embuwfu " እያለ እየሰደበው ይሮጣል። "ምን ማለት ነው Embuwfu!?" ስል ዱባለን ጠየቅሁት።

"Useless ማለት ነው" ሲለኝ ከልቤ ሳቅሁ።

የዚህን ትረካ ርእስ ያገኘሁትም ኤዱ ወይም ኤድዋርድ ተብሎ ከሚጠራው የዚያች ቀበሌ ማቲ ሲሆን፤ ምናልባትም ያ ህፃን ይህን ቃል ያገኘው ወላጆቹ ስለኛ የሚያወሩትን ሰምቶ ሊሆን እንደሚችል ገምቻለሁ!

በኛው ማድቤት ዙሪያ የተለያዩ ከቆርቆሮ የተሰሩ የንግድ ሱቆች ተኮልኩለዋል። መጠጥ ቤት፣ ሱቅ፣ ስጋ ቤት፣ የፀጉር ቤት... የሌለ የለም። የመጠጥ ቤቱ ባለቤት ማቱምቦ ኩቦ ፑል እየተጫወተ ቁማር ሲቆምር የሚውል ስራ ፈት አዛውንት ነው። መጠጥ ሸጦ ያተረፈውን እዚያው በቁማር ያስረክባል!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ዱባለ ማቱምቦ ኩቦን በቀን ቢያንስ መቶ ሽልንግ ይበላዋል። የመንደሪትዋ ባለ ስጋ ቤት ካማዎ ይባላል። ማካዎ የሚባል ታክሲ ነጂ ደግሞ አለ። ማርጋሬት የማቱምቦ ኩቦ መጠጥ አስተናጋጅ ናት። አንድም ቀን መልስ በትክክል ሰጥታ ስለማታውቅ ከጠጪዎች ቡጢ ጭምር ትቀምሳለች።

* * *

እነሆ በዚያች ማድቤት ተቀምጠናል!

በዚያን እለት ዱባለ የሞምባሳውን ታሪክ ሲተርክ ከኔ በቀር የሳቀ አልነበረም። የዚህን ምክንያት አጠገቤ የነበረ ስደተኛ ሹክ አለኝ። ዱባለ ያንን ታሪክ እዚያች ማድቤት ውስጥ ብቻ ከሃያ ጊዜ በላይ ስለተረከው ሰዎች ተሰላችተው ኖሮአል። ሊተባበረው ብሎንኳ የሚስቅለት አልነበረም። ለነገሩ ዱባለ ዝም ካለ ማድቤቷ ጭር ስለምትል ዱባለን የሚቃወም አልነበረም። ወርቁ ግን በዱባለ ላይ ባለው ጥላቻ ተጨምሮበት ነው መሰል የዱባለን ትረካ ላለመስማት ጫቱን ብብቱ ስር ወሽቆ ማድቤቷን ለቆ ወደ ማቱምቦ ኩቦ መጠጥ ቤት አቅጣጫ ሄደ።

ይህን ጊዜ ግን ዱባለ ተመቸው። ገና የወርቁ እግር ከመውጣቱ የእርግማን ዶፍ ያወርድበት ጀመር፣

"ቀይ እባብ! ሲያዩት ደህና ሰው ይመስላል! ከዚህ ሾካካ መቶ በመቶ እኔ እሻላለሁ። እኔ የዋህ ነኝ! ካለኝ ተካፍዬ መብላት እወዳለሁ። ከሶስት አመት በፊት እዚህ የነበሩ አበሾችን ጠይቁ! ግማሽ ኪሎ ስጋ ከካማዎ ቤት አስቆርጬ፤ ካቹንባሪ አሰርቼ፣ ኡጋሊና እንጀራ አዝዤ ተካፍዬ እበላ ነበር። ማቱምቦ ኩቦን እንኳ ጋብዤው አውቃለሁ! ይሄ ዳቦ ገዝቶ ብቻውን የሚበላ ቡራቡሬ ዘንዶ! ደሞ ወርቁ ይሉታል! እሱ ወርቅ ከተባለ እኛ ምን ልንባል ነው? ቆርቆሮው ቢሉት ይሻል ነበር። ደሞ አያፍርም ወሬ አገኘሁ ብሎ 'እናቴ ናት ወርቁ የሚል ስም የሰጠቺኝ!' ወርቁ ሳይሆን ጆሮ ጠቢ ቢሉት ይሻል ነበር። ሰላይ ነገር ነው። ኢህአፓ ነበርኩ ምናምን ይላል። እዚህ ሰውን ሁሉ ሲሰልል ነው የሚውለው። ማታ ማታ ሲሰልል አድሮ ጠዋት የሰማውንና ያየውን በዝርዝር ይነግረናል። ጨለማ ውስጥ ተደብቆ እያንዳንዱ ሰው የሚያወራውን በሚስጥር ያዳምጣል! ያልተቀጠረ ሰላይ! ሳይቀጠር እንደዚህ የሰራ ቢቀጥሩት ምን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሊሰራ ነው? ፖሊስ ሲፈራ ደግሞ! እኔ አሁን ፖሊስ አልፈራም፣ ጓደኞቼ ናቸው። ፖሊስ ለምን እንደሚፈራ ታውቃለህ?" ሲል ጠየቀኝ።

አያይዞም ቀጠለ "... ፎርጅድ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ይሰራ ነበር። አንድ ቀን ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ተደወለለትና 'ከኢትዮጵያ ፖስታ መጥቶልሃልና መጥተህ ውሰድ' አሉት። እናቱ ሽሮና በርበሬ የላከችለት መስሎት በርሮ ሲሄድ ፖሊሶች ተረከቡና አንድ ወር አበሰበሱት! ከዚያ ወዲህ ፖሊስ ሲያይ ይደነብራል። ደሞ አንድ ቦታ አርፎ አይቀመጥም። ጠላት ሞልቶታል። አንድ ሊገድለው የሚፈልግ ሱማሌ አለ። ጩቤ ይዞ ወርቁን ሲፈልግ ነው የሚውለው። ያገኘው ቀን መቸም ወርቁ አለቀላት!" ብሎ በሳቅ ይንፈራፈር ጀመር።

"ከሶማሌው ጋር በምን ተጋጨ?" ስል ጠየቅሁት።

"ጓደኞሞች ነበሩ" ሲል ዱባለ ቀጠለ "... አብረው ይቅሙ ነበር። ሱማሌው ፕሮሰሱን ጨርሶ ካናዳ ሊሄድ የጤና ምርመራ ሲያደርግ ኤድስ አለብህ ብለው አስቀሩት። በዚህ ነው ወርቁን ሊገድል የሚፈልገው። ኤድስ የተላለፈብኝ ከወርቁ ነው ብሎ ያምናል!"

"እንዴት?" አልኩ ገርሞኝ።

"አብረው ይቅሙ ነበር። በአንድ የኮካ ጠርሙስ ይጠቀሙ ስለነበር በዚያ የተላለፈበት መሰለው። ሶማሌ ምን ያውቃል? ብትነግረውም አይገባውም። ያኔ ወርቁ ሽርኬ ስለነበር ሽማግሌ ሆኜ ሶማሌውን ለማግባባት ሄጄ ነበር። 'የተኛሃት ሴት ካለች ሄደህ እስዋን ውጋ! ኤድስ ግን በኮካ ጠርሙስ አይተላለፍም! ወርቁም ኤድስ የለበትም' አልነው እሱ ከሴት ጋር ተኝቼ አላውቅም ነው የሚለው..."

ወርቁ ተመልሶ በመምጣቱ ዱባለ ወሬ ቀየረ።

ለነገሩ ወርቁም ቢሆን ከዱባለ የሚያንስ አልነበረም። ዱባለ ከሌለ እሱም በተራው ውርጅብኙን ይለቅበታል። ከትናንት በስቲያ ዱባለ አልመጣም ነበርና ጠጋ ብሎ እንዲህ አለኝ፣

"እንደማይህ ከሆነ አንተ የተከበረ ትልቅ ሰው ትመስላለህ! ከዚህ ማጅራት መቺ ጎን መቀመጥ ለክብርህ ጥሩ አይደለም። ካንተ ባላውቅም እዚህ አካባቢ ባትመጣም ጥሩ ነው..."

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ለጨዋታ ብዬ ነው” አልኩት።

“ቢቀርብህ ይሻላል!” ሲል አስጠነቀቀኝ “...ዱባለ አጥንቶህ ሲያበቃ አንድ ቀን በጨቤ ገድሎ ይዘርፍሃል!”

“እንደዚያ ያደርጋል ብለህ ነው?"

“ሲወለድ ጀምሮ ሌባ የነበረ ነው” ሲል ቀጠለ “... መርካቶ ነው የተወለደው። መንገድ ላይ ነው ከእናቱ ማህፀን ሾልኮ የወጣው። 'ዱብ - አለ' ያለችው ለዚህ ነው። ከማህፀንዋ ዱብ ብሎ ሲሮጥባት ምን ትበለው ታዲያ? 'ዱባለ' አለችው። እዚህ እያጭበረበረ የሚዘርፍ ሌባ፣ የሌባ ልጅ! ልንገርህ? 'ወደ ኢትዮጵያ ልመለስ ነው' ብሎ ሶስት ጊዜ መዋጮ በልቶአል። ግን አልተመለሰም። ቆርቆሮ ቤት ውስጥ አንዲት ሴትኛ አዳሪ አስጠግታው ነው የሚኖረው! የሰከረች ቀን ቦርሳዋን ይበረብርና ይሰርቃታል። የራስዋን ገንዘብ መልሶ ለቤት ኪራይ ይከፍላታል። ስደት አስተካከለን እንጂ እኔ ባንድ ወቅት የጃንሆይን ልጆች እንግሊዝኛ አስተምር የነበርኩ ሰው ነኝ። አንተ መቼም የተማርክ ነህ! እስቲ አዲሳባ ጉርድ ሾላ ሂድና ወርቁ ማን ነው?' ብለህ ጠይቅ። ጥርሴን በጨቤ የምፍቅ፣ ጀርባዬን በጎራዴ የማክ ሰው ነበርኩ። ዛሬ የዱባለ መቀለጃ ሆንኩ! ዱባለ ብሎ ስም 'ዱባ' ቢሉት ይሻል ነበር - ዱባ ራስ!”

በነጋታው ደግሞ ዱባለ እንዳይቀድመው ተሽቀዳድሞ ካጠገቤ ከተቀመጠ በሁዋላ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

“አንድ ታሪካዊ ነገር ላሳይህ?”

“ምንድንነው?”

“ደጅ እንውጣና ላሳይህ”

“እዚሁ አሳየኝ?”

ከኪሱ የምታምር ቀይ ላይተር አውጥቶ አሳየኝ፣

“እና ምንድነው?”

“ከእንግሊዝ ሃገር የመጣች ሴት ናት ስጦታ የሰጠቺኝ”

“እና!?”

ማለት የፈለገውን ለማወቅ ጉዋጉቼ ነበር። እሱ ግን በጥያቄዬ በጣም ተናደደ፣

“ሰጠቺኛ!! እንዴት እና? ብለህ ትጠይቀኛለህ? ሰጠቺኝ! በቃ!!”

በቁጣ ካጠገቤ ተነስቶ ሄደ።

ወርቁ ሲሄድለት ዱባለ ፈጥኖ ወደኔ መጣ፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"....ላይተር በስጦታ ተሰጠኝ ነው የሚልህ?" አለ እየሳቀ፣ "... ከትናንት ጀምሮ ሌላ ወሬ የለውም። ለሁሉም በሚስጥር ደጅ እየወሰደ ያሳያል። እኔን ለማናደድ እኮ ነው። ይሄኔ ልለኩስበት ብሎ ሰርቆአት ነው። ለዚህ እድሜ በቂጡ ምን ብላ ነው ከእንግሊዝ የመጣች ሴት ላይተር የምትሰጠው? ከኔ ጋር መፎካከሩ ነውኮ"

"በምንድነው ካንተ ጋር የሚፎካከረው?"

"አንዲት ሃብታም ኬንያዊት ወዳኛለች እያልኩ ለፉገራ ሳወራ ሰምቶ፤ እሱ ደግሞ ላይተር ይዞ መጣ"

ዱባለ እየሳቀ ቆየና፣

"እጁን በፋሻ የጠቀለለውን አይተሃል?"

"ልብ አላልኩም፤ ምን ሆኖ ነው?"

"ኬንያውያን በጩቤ ወጉኝ ነው የሚለው። ውሸቱን ነው። ሰክሮ የተሰበረ ጠርሙስ ላይ ወድቆ ነው። ይሄ ምኑ ይወጋል? አፅም!!"

በመካከላችን አንድ የትግራይ ልጅ ነበር። ዘርአይ የሚባል። የመጣ ሰሞን 'የአድዋ ልጅ ነኝ፣ መለስ ጎረቤቴ ነው' እያለ በማስቸገሩ ዱባለ ደብድቦ አባረረው። ከሳምንት በሁዋላ ግን አማላጅ ልኮ የመለስን ጎረቤት መሆን ላለማንሳት ቃል ገብቶ፤ ሁሉም በዚህ ተስማምተው መለሱት። ብዙም ሳይቆይ ከዱባለ ጋር ጉዋደኛሞች ሆኑ።

"ያ! መላጣ ነውን'ጂ ያለያየን እኛ ወንድማማቾች ነን" ብሎ በመናገር ከሁሉም ጋር አስታረቀው።

ሲጠጡም ሆነ ሲቀመጡ በፍፁም የማይለያዩ ሶስት ኤርትራውያንም በመካከላችን አሉ። የሚያወሩትም በትግርኛ ነው። በራሳቸው ወሬ ተጠምደው ዘወትር እንደሳቁ ነበር። አንድ ቀን ጆሮዬን ጣል አድርጌ ሰማሁዋቸው። እንደ አለቃነት የሚቃጣው በእድሜውም ገፋ ያለ ጉዋደኛቸው እንዲህ ሲል ሰማሁት፣

"....አባቴ አንድ ጊዜ ሊመታኝ እጁን ሲሰነዝር ፈጥኜ እጁን ያዝኩትና 'በማርያም ይገርሃለሁ እንዳትመታኝ' ስለው ቀጥ አለ። አባቴ ማርያምን በጣም ነው የሚያመልካት..."

በዚህ ንግግር ያጀቡት በከፍተኛ ሁኔታ ሲስቁ በመስማቴ ግራ ተጋባሁ። በትክክል ሰምቼያለሁ። እንደዚያ ያሳቃቸው ምን እንደሆነ ፈፅሞ ሊገባኝ አልቻለም ነበር። በዚያው ሰሞን ግን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ምስጢሩን ደረስኩበት።

አንድ ቀን እንደተለመደው እየጠጡ እየሳቁ በሰላም ቆይተው ሳለ ያልተጠበቀ ፀብ ተፈጠረና ጠርሙስ እስከመወራወር ደረሱ። በመከራ ገላገለናቸውና ለያይተን አስቀመጥናቸው። አንደኛው እኔ አጠገብ ነበር የተቀመጠውና፣

"ምን አጣላችሁ?" ስል ጠየቅሁት።

አጫወተኝ፣

አለቃ መሳዩ ሰው ለካስ ምንጊዜም ጋባዣቸው ኖሮዋል። እሱ ሲያወራ ካልሳቁ ያኮርፋል። በዚያን ቀን በደርግ ጊዜ የውስጥ ሰላይ ሆኖ የፈፀመውን ጀብድ ሲተርክ የማይመስል ነገር ያመልጠውና፣ አንደኛው ይከራከረዋል። ጋባዡም በጣም ተናዶ፣

"የምነግርህን የማታምን ከሆነ ከፍለህ ጠጣ! በኔ ገንዘብ እየጠጣህ አትከራከር፤ ወይ ከፍለህ ጠጣ ወይ ደግሞ ዝም ብለህ አዳምጥ!" ይላቸዋል።

ይሽው ነበር የፀቡ መነሻ። ላፅናናው በማሰብ በዚያን ቀን እሱ እያወራ እኔ ጋበዝኩት። በጣም ተደስቶ እንዲህ አለኝ፣

"አሰቃየን እኮ! በውሸት ሳቅ አፈ ተሰነጠቀ! ዛሬ ግን አልቻልኩም! ባይጋብዘኝ ይቅር...."

በተመሳሳይ ለብቻቸው ቁጭ የሚሉ ኦሮሞዎችም አሉ። ከኔ ጋር እንግባባለን። አንደኛው አንድ ቀን እንዲህ አለኝ፣

"ብዙ ጊዜ ስታዳምጥ ነው የማይህ፤ ለምን አታወራም?" ሲል በኦሮምኛ ጠየቀኝ።

"ዝምታ መጥፎ ነው እንዴ?" ስል መልሼ ጠየቅሁት።

ሳቀና በወረቀት ላይ አንድ የኦሮምኛ ጥቅስ ፅፎ ሰጠኝ፣ ጥቅስ የመሰብሰብ ፍላጎትና ልማድ የለኝም። ያቺን ጥቅስ ግን ከማስታወሻ ደብተሬ ላይ ፃፍኩዋት። እንዲህ የምትል ነበረች፣

"Yoomiyyuu Kan hin maraanne hoolaadha, maraachuu irraa kanhinoolle ammoo sareedha" ትርጉሙም "ምንጊዜም የማያብድ በግ ነው፤ ማበዱ የማይቀር ደግሞ ውሻ ነው" ማለት ነበር።

ይህቺን ጥቅስ የሰጠኝ ኦሮሞ ኬንያን ልለቅ አካባቢ "የቡርቃ ዝምታ"ን ይዞ አየሁት።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አንድ ቀን ወርቁ ሰክሮ ይጮህ ጀመር። መድረኩን በጉልበት ከዱባለ ላይ ነጥቆ ተቆጣጠረው። ያን ቀን ወርቁ የተለየ ሰው ሆኖ ዋለ። ምርር ብሎት እንዲህ ይለን ያዘ፣

"ኬንያ ሰለቸኝ ወንድሞቼ! ብታምኑም ባታምኑም በዚህ አመት ናይሮቢን ለቅቄ አገሬ እገባለሁ። ይህ አገር ይባላል እንዴ? 'ሃኩና ማታታ' ይሉሃል! 'ችግር የለም' ማለት ነው። 'ማታታ' ማለት 'ችግር' ማለት ነው ። 'ማቲቲ' ደግሞ ጡት። 'ሙቶቶ' ህፃን። 'ማታቱ' ታክሲ። እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል? 'ማፉታ' ይላሉ 'ቤንዚን' ለማለት። የወጥ ዘይት ልትገዛ ስትሄድም 'ማፉታ' ቅቤ 'ማፉታ' ጋዝ 'ማፉታ' ምንድነው ይሄ? ርግብ ለማለት 'ኢንዳጎ' ይላሉ። ቁራ፣ ሄሊኮፕተር፣ አይሮፕላን ሁሉንም 'ኢንዳጎ' ይሏቸዋል። የሚበረውን ነገር ሁሉ ባንድ ቃል የሚጠሩ ቀልደኞች። እዚህ ቀልድ መሃል መኖር ሰለቸኝ...ዳን ሳቸውን አይታችሁዋል? እንደ ጠጣ ወደ ላይ ይዘላሉ። አን ገታቸውን እያነቃነቁ የሚደንሱትን ደግሞ ከወፍ ነው የወሰዱት። ዋነስ ከተባለች ወፍ። ስለ ማሳይ ጎሳ ሰምታችሁዋል? ቢራ ለመጠጣት ብለው ከብት ይሸጣሉ! ከብቶች ሁሉ ደግሞ የነሱ ይመስሏቸዋል። ከቁራና ከፈረስ ሳይቀር ዳንስ ኮርጀዋል። የደነገጠ ቁራና የደነበረ ፈረስ የሚመስል ዳንስ አላቸው። ሴት ሲያፈቅሩ 'Wa ku peda kama niama choma' ይላሉ። I love u like a roasted meat ማለት ነው። እንግሊዝኛ ለማይችሉ ለነዱባለ ለመተርጎም ደግሞ 'እንደተጠበሰ ስጋ እወድሻለሁ' ማለት ነው..."

በዚህ ቀንም ዱባለና ወርቁ ቦክስ በመግጠማቸው በመከራ ገላገልናቸው። በዚያው ሰሞን ወርቁና ዱባለን ወደ ፍሎሪዳና ማዘርላንድ ወደተባሉ ምግብ ቤቶችና ክለቦች ይገፎያቸው በመሄድ ላስታርቃቸው ብሞክርም እንደማይሆን ገባኝ። በመረረ ሁኔታ ቂም ይዘው ኖሮአል። በምን ሰበብ እንዲያ እንደተጣሙ ግን ሁለቱም አይናገሩም።

ሌላ ቀን ደግሞ ዱባለ ስለ አባቱ ጥቂት አጫወተኝ፣

"ነፍሱን ይማረውና አባቴ የሚገርም ሰው ነበር" ሲል ጀመረ፣ "...አባቴ አልተማረም። ኬንያ ምን አይነት ሃገር እንደሆነ አያውቅም። እኔ የኮበለልኩ ሰሞን 'ልጄ ውጭ ሃገር ገባ' እያለ ሲያወራ ከረመ። ያዲሳባ ሰው ደግሞ ክፉ ነው።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

‘ልጅህ ዶላር አልላከም እንዴ? ላክ በለው እንጂ? ጋብዘን እንጂ?’ እንዲህ እያሉ አሳበዱት። ጉዋደኛዬ ደግሞ ይፅፍልኛል። ‘ለእኛስ ግዴለም፣ አባትህ ግን የመንደር መሳቂያ ከሚሆኑ 100 ዶላር እንኳ በጥስላቸው!’ እኔ ምን ልሁን!? ከየት አመጣለሁ!? የሰፈር ሽሙጥ ሲበዛበት አባቴ ምን እንዳደረገ ታውቃለህ? ጊዮርጊስ ቤተክርስትያን ሄዶ የሰፈር ሰው ሁሉ እየሰማው፣ ባንድ እግሩ ቆሞ ረገመኝ! ጓደኛዬ ይህን ሲፅፍልኝ ተረበሽኩ። ገንዘብ ከየት ልውለድ? የውሸት ሽጉጥ ገዛሁና አንድ ሱቅ ገብቼ አስፈራርቼ 200 ዶላር ያህል ዘረፍኩ። መቶውን ለአባቴ ልኬ፣ ቀሪውን ሊይዙኝ ከመጡት ፖሊሶች ጋር ጠጣሁበት። መቶ ዶላር ሲደርሰው አባቴ ምን እንዳደረገ ታውቃለህ? ጊዮርጊስ ሄዶ መቶ ዶላርዋን ለሁሉም እያሳየ፣ በአንድ እግሩ ቆሞ መረቀኝ። የአዲሳባ ሰው መቼም ክፉ ነው። ምን ብለው አሸሙዋጠጡት መሰለህ? ’ጎርጊስ የዱባለን ፋይል ሲፅፍና ሲሰርዝ መከራውን አየ...”

* * *

እነሆ ደጁ መምሸት ጀምሮአል።

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ያቺን መንደር ለቀን ወደ ሌሊት ክለቦች እንጉዋዛለን። ፍሎሪዳ የተባለው የሌሊት የዳንስ ክለብ አፉን ከፍቶ ይጠብቀናል። ክለብ ሃውስ ገብተን ፑል እንጫወታለን። ከአስር በላይ ሃገራትን የማውቅ ሲሆን፣ እንደ ናይሮቢው ፍሎሪዳ 2000 የመሰለ ተወዳዳሪ የሌለው ክለብ ግን በፍፁም አይቼ አላውቅም። በዋሽንግተን ዲሲ፣ በሲያትል፣ በዱባይ፣ በአዲስ አበባ፣ በኬፕታውን፣ በጆሃንስበርግና በፕሪቶሪያ ያየሁዋቸው ክለቦች የፍሎሪዳ ጭራ ላይ ኩቶ አይደርሱበትም። ናይሮቢ ላይ ህይወት አለ። ውበት አለ። አፍሪቃዊ ሙዚቃ አለ። በርግጥ ወንጀልና ድህነትም አለ። የዚያኑ ያህል በዚያ አለማቀፋዊ ደረጃውን በጠበቀ ግዙፍ ክለብ ውስጥ የአስቴር አወቀንና የሃመልማልን ዜማ መስማትና በዚያ ዜማም አውሮፓውያንንና አፍሪቃውያን ሲደንሱበት ማየትም ሌላው ልዩ ውበቱ ነበር።

አሁን ሚሊማኒ ጨላልማለች።

ደጁ ላይ ማካዎ ታክሲ ነጂው እየጠበቀን ነው። በሲጃራ ጪስ የታመቀችውን ማድቤት እየለቀቅን መውጣት ጀመርን።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

* * *

እነሆ በዚህ አይነት እለታዊ የህይወት ድግግሞሽ በዚያች መንደር ጥቂት ወራት ከቆየሁ በሁዋላ ናይሮቢን ለመልቀቅ የሚያስገድድ አንዳንድ ሁኔታዎች ይገጥሙኝ ጀመር፣

በዚያች መንደር ዘወትር ምሽት ላይ ሊጠጣ የሚመጣ አንድ ባለስልጣን አለ። ጁማ ይባላል። የኬንያ የፀጥታው መስሪያ ቤት ባልደረባ መሆኑን ሰምቻለሁ። አንድ ቀን ፑል ስንጫወት እንዲህ አለኝ፣

"እዚህ ካሉት ስደተኞች የተለየህ ነህ"

"በምን እለያለሁ?"

"ቦርሳ ትይዛለህ! ቦርሳህ ውስጥ ምንድነው ያለው?"

"ሬድዮና ማስታወሻ ደብተር" ስል ነገርኩት።

"ጋዜጠኛ ነህ እንዴ?"

"ነበርኩ"

ሲጋራውን እየማገ ደስ በማይል ሁኔታ እየተመለከተኝ እንደሆነ በመረዳቴ ወደዚያ ቁጭራ ሰፈር መመላለሴን ማቆም እንዳለብኝ መረዳት ጀምሬ ነበር። ብዙም ሳይቆይ ግን ኬንያን መተው እንዳለብኝ ተረዳሁ፣

አንድ ቀን ከሙሉአለም ጋር ስናወራ፣

"ስላንተ ሲወራ ሰማሁ" ሲል በምስጢር ነገረኝ።

"ምን ሰማህ?"

"አማራና ኦሮሞን የሚያጣላ መፅሃፍ ፅፎአል - ምናምን ይላሉ። እኔ ደግሞ ተከራከርኩ። እሱ እንኳን ሰውና ሰው ሊያጣላ ወርቁንና ዱባለን ሊያስታርቅ ሲሞክር ነው ያየሁት ብዬ ተከራከርኩ"

ይህን የመሰለ ነገር በተደጋጋሚ ስለምሰማ ተከዝኩኝ፣

"መፅሃፉን ቢያነቡ ኖሮ እንደዚያ አይሉም ነበር" አልኩት።

ሙሉአለም ዘግየት አለና አከለበት፣

"ብዙ ነው ስላንተ የሚያወሩት"

"ሌላ ምን ይላሉ?"

"የወያኔ ባለስልጣን ነበር፣ ጋዜጠኛ ነበር፣ የማይሉት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የለምኝ ሰላይ ነው እያሉም ያወራሉ”

“ሰላይ!? የማን ሰላይ!?” አልኩ።

“የወያኔ”

ዘግየት ብዬም፣

“ለመሆኑ ማንን ነው የምሰልለው?” ስል ጠየቅሁት።

“እዚህ እንግዲህ ያው ፖለቲካ የሚያወራው ዱባለ ስለሆነ እሱ የሚናገረውን እየፃፍክ ለኤምባሲ እንደምትሰጥ ነው የሚያወሩት። ዱባለንም አስጠንቅቀውት ነበር...”

ከሁለት ሳምንት በሁዋላ ኬንያን ለቅቄ ወደ ደቡብ ተጓዝኩ። የናይሮቢውን ህይወት በፍፁም ልረሳው ባለመቻሌም ሚሊማኒ ለተባለችው መንደር፣ ለነዋሪዎቿና ለስደተኞቿ ጥቂት ስንኞች ቋጠርኩላቸው፣

ትዝ አለኝ ናይሮቢ - ሚሊማኒ ደብረ አለሌ፣
የባከኑ ሃበሾች ሰፈር - ሚሊማኒ የሳቅ ቀበሌ፣
ትዝ አለኝ የመደበሪያው ጨለማ፣
Wa ku peda ሲባል - kama niama choma
ትዝ አለኝ ኪሰዋሂሊ - የቃላት ቋንቋ ጨዋታ፣
ከሃኩና ማቲቲ እስከ ሃኩና ማታታ፣
Wa ku peda ናፈቀኝ Wa ku peda
በሲፐርስ፣ በባቫሪያን፣ በክለብሃውስ፣ በፍሎሪዳ፣
አ! ናይሮቢ! አ! ኬንያ - የተጠላም ይናፍቃል ለካ፣
ጫካው ትዝ አለኝ - የኪኩዩ ትራንፔትም ሲያስካካ፣
ትዝ አለኝ ሚሊማኒ፣
ሚራ ሲመረር - ታስካር ሲሰክር – ፖሊስ እስኪያስደነብር፣
አ! ፖሊስ! የዲያቢሎስ ታላቅ አሽከር፣
ጊዜ ፈቅዶልህ አበሻ ላይ ጉራ እምትቸረችር፣
አዎን አሁን ሁሉም ቀረ - ብቻ ብቸኝነት ብቻ ቀረ፣
የዱባለ ፖለቲካ፣ የወርቁ እንጉርጉሮም ቀረ፣
አዎን! ርቄያለሁ - ለኔ ትዝታ ብቻ ሆኖ ቀረ።

እንደራቅሁ አልቀረሁም።

1999 አጋማሽ ላይ ከጉልበት ስራ ያልተናነሰ ስራ አጊንቼ፤ ወደ ሲሸልስ ደሴት ስጉዋዝ፤ በናይሮቢ በኩል የማለፍ እድል ገጠመኝ። ያለኝ ጊዜ አንድ ሌሊት ብቻ ስለነበር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሻንጣዬን ወርውሬ በቀጥታ ወደ ሚሊማኒ ታክሲ ይገዩ በረርኩ። ከዱባለ በቀር ግን ማንንም ላገኝ አልቻልኩም። ባክኖ የቀረው የኛ ሰው ዱባለ ከዚያችው ካስጠጋችው ሴትኛ አዳሪ የቆርቆሮ ዛኒጋባ ውስጥ በጠራራ ፀሃይ ብርድ ልብስ ተከናንቦ ተኝቶ አገኘሁት።

ሲያየኝ በጣም ካለማመኑ የተነሳ ለደቂቃዎች ያህል ተንሰቅስቆ አለቀሰ። ብቸኝነትና መረሳት እንደጎዳው መገንዘብ አላዳገተኝም። ካረጋጋሁት በሁዋላ ሁሉንም አጫወተኝ።

በዚያች መንደር ይቀመጡ የነበሩት ስደተኛ ሃበሾች ጥቂቶቹ ተሳክቶላቸው ወደ አውስትራሊያና ካናዳ መሄዳቸውን፤ ወርቁ ግን መዋጮ ተሰብስቦለት ወደ ኢትዮጵያ መመለሱን አወጋኝ። እያወጋኝ ሳለ ከቆርቆሮ ዛኒጋባው ግድግዳ ላይ የብርሃኑ ነጋን ምስል ተለጥፎ በማየቴ በመገረም እንደዋዛ አነሳሁለት፣

"ማነው ይሄ ሰው ዱባለ?"

በፍጥነት ምላሽ ሰጠኝ፣

"ዶክተር ብርሃኑ ነዋ! የጋሽ ነጋ ልጅ!" አያያዘናም

"...እንዴት አታውቀውም?" ሲል ጠየቀኝ።

"አሃ! እሱ ነውን'ዴ? በስም እንጂ በፎቶው አላውቀውም ነበር" ስል አምታታሁ።

"የአንድ ሰፊር ልጆች ነን!" ሲል ቀጠለ ዱባለ "... አባቴ ከመሞቱ በፊት የዳማ ሆቴል ዘበኛ ነበር። ጋሽ ነጋ ለኔ አባቴ ማለት ናቸው። የነብርሃኑና የኛ ቤት እዚህና እዚያ ማለት ነው። እነሱ ቤት እንደ ቤቴ እገባና እወጣ ነበር። አመት ባል ሲሆን ገብቼ እበላለሁ እጠጣለሁ። ምን ዋጋ አለሁ ብለህ ነው? መለስ ዜናዊ የሚባለው መላጣ አክሮባት ሰርቶ ሁሉንም እንዳይሆን አደረገው። ይሄኔ ዛሬ እኔ እዚህ አልገኝም ነበር..."

ከጥቂት ዝምታ በሁዋላ፣

"በል ልብስህን ልበስና እንውጣ! ራት ልጋብዝህ?" አልኩት።

ዱባለ ጥቁር ብርድ ልብሱን ከላዩ ላይ ወርውሮ በፍጥነት ተነሳ። እሱ ልብሱን እየለበሰ ሳለ አይኖቼ ግድግዳው ላይ ነበሩ። ከመፅሄት ላይ ተቀዶ ግድግዳው ላይ የተለጠፈውን ፎቶግራፍ አጤንሁት። የብርሃኑ መላጣ ለዱባለ አልታየው ኖሮአል....

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 18 -

የአፍሪቃን ድንበር ሰናቋርጥ

በሃዘን ጭጋግ ተጋርዶ - ህሊናው ሲጨልምበት፣
እንዳልፀና ሊጋ ችግኝ - አብራኩ ፅናት ሲያጣበት፣
ከመከራው አውታር አልፎ - ከጭንቀት ክልል ባሻገር፣
መልካሙን ፀጋ ለማጤን - ተስፋ ብቻ ነው እሚሻገር፣

(ግጥም - ከበደች ተክለአብ)

እነሆ ሉሳካ የተባለችውን ደባሪ ከተማ በመተው ወደ ምስራቅ ጉዞ ቀጠልኩ። ያረጀ መጋዣ የመሰለው አውቶብስ ከጠበቅሁት በላይ ፈጣን ሲሆን፤ የዛምቢያን ጫካዎች እየሰነጠቀ ወደ ሞዛምቢክ ድንበር እየገሰገሰ ነው። የወያኔ ዲፕሎማቶች ፓስፖርቴን ናይሮቢ ላይ መንጠቅ የቻሉ ቢሆንም፤ ኢትዮጵያዊነቴን መንካት እንደማይችሉ ግን አልተረዱትም። ማንም ቢሆን ይህን ማድረግ አይቻለውም። እንኳን ኢትዮጵያ አፍሪቃ ራስዋም የኔው ናት። ወደ ባሌ ጎባ መጉዋዝና ወደ ሞዛምቢክ መጉዋዝ አንዳችም ልዩነት እንደሌለው ይኸው ባይኔ እያየሁ ነው። ዶሮና አገዳ በዘንቢል የታቀፉ ገበሬዎች ከጎኔ ተቀምጠዋል።

ጫካው አፍሪቃዊ ነው። ዶሮዎቹ የአፍሪቃ ዶሮዎች

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ናቸው። ጥረው ግረው የእለት ጉርስ የሚያገኙ፣ ጫጩቶቻቸውን መግበው የሚያሳድጉ የአፍሪቃ ዶሮዎች።

ናይሮቢ ላይ የተሾመው ዲፕሎማት፣

"አዝናለሁ፤ ፓስፖርትህን ላድስልህ አልችልም! ዜግነትህ ታግዶአል!" ብሎ ባዶ እጄን ባሰናበተኝ ደቂቃ ድርጊቱ ህገ ወጥ መሆኑን በመገንዘቡ አይኔን እንኳ ደፍሮ የማየት ወኔ አልነበረውም።

የኢትዮጵያን ኤምባሲ ለቅቄ ስወጣ ከምንጊዜውም በላይ አገር አልባነትና ባዶነት ተሰምቶኝ የነበረ ቢሆንም፤ ይኸው አሁን ሁሉን ለምጄዋለሁ። የሃሰት የጉዞ ሰነዶችን በመግዛት የአፍሪቃን ጫካዎች የማቋረጥን ህገወጥ ተግባር ተምሬያለሁ።

ቤሳቤስቲን የሌላቸው የዚህች የጥቁር አህጉር ዜጎች ጦርነትና ድህነትን እየሸሹ፤ ከአምባገነን መሪዎች ማጎሪያ እያመለጡ፤ እንደመሸጋገሪያ ወደምትታየው የተስፋ ምድር ለመድረስ የአፍሪቃን ጫካዎች በከርካሳ አውቶብሶችና በእግር ያቋርጡታል። የተስፋይቱ ሃገር ደቡብ አፍሪቃ ናት። ያቺ የነጮችና የጥቁሮች ምድር፤ ያቺ የኔልሰን ማንዴላ ሃገር፤ ከድሃ ቤተሰብ የተወለዱና ረዳት አልባ ስደተኞችን ሁለት እጆችዋን ዘርግታ እንደምትቀበል የሰማሁ በመሆኑ የኔም ጉዞ ወደዚያው ነው።

ባልጠበቅሁት ሁኔታ ከሃገሬ ከተባረርኩ በሁዋላ፤ የደራሲነቱ መንፈሴ ጥሎኝ ጠፍቶአል። ብእርና ወረቀት ባይለየኝም፤ በጥቂት ወራት አንድ መፅሃፍ መውለድ የሚችለው ጉልበቴ አሁን ተዳክሞአል። በእቅድ ተመርቶ የማያውቀው የህይወቴ መድረሻ የት ሊሆን እንደሚችል ከቶ አላውቅም።

ገብረክርስቶስ ደስታ "በባእድ አገር" ሲል የቋጠራት ስንኝ የየእለት መዝሙር ሆናልኛለች።

የት እንደምትቀሪ...
ምን እንደምትሰሪ...
እንቆቅልሽ ነፍሴ - ንገሪኝ በእርጋታ፣
ጨንቆኛል ጠቦኛል - ያለሽበት ቦታ፣

ለመሆኑ ለምን ቢሾፍቱ ተወለድኩ? የወጣትነት እጣ ፈንታዬ ጦርነት ለመሆን የበቃው ከቶ በማን ስህተት ነበር?

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ቢሾፍቱን ረስቼ የሌላ ሃገርን ልማድና ባህል መውረስ ለምን አልቻልኩም? አሁንስ እዚህ የአፍሪቃ ዱር መሃል ምን እሰራለሁ? ወዴት ነው የምገሰግሰው? መጪው ህይወቴስ ምን ይሆናል? ከእንግዲህ የመፃፍ ነገር አበቃ ማለት ይሆን?

ምላሽ የሌላቸው ጥያቄዎች የአእምሮዬን ጓዳ ሲደበድቡት ውለው ያድራሉ!

* * *

ሉሳካ ላይ አንዳችም የተውኩት አሊያ የቀረኝ ነገር ያለ አይመስለኝም። ያቺ እንቅልፋም አፍሪቃዊት ከተማ በኔ ህይወት ውስጥ ያልነበረች ያህል ጭልም፣ ድፍን አድርጌ ልረሳት ቸኩያለሁ። በሉሳካ የቆየሁባቸው ሁለት ወራት እጅግ አድካሚና አሰልቺ ነበሩ። አልጋና ወንበሮች ያሉት ቤት ተከራይቼ እኖር የነበረ ሲሆን፤ ምሽት ላይ ገበሎዎች በግድግዳው ላይ ሲመላለሱ እየተመለከትሁ በስጋት እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር አድር ነበር። ቀን ቀን ደግሞ Manda hill ተብሎ ወደ ሚጠራው የገበያ አዳራሽ እሄዳለሁ። እዚያው አካባቢ ሳውደለድል እውልናም ምሳ ሰአት ላይ ያገኘሁትን ቀማምሼ ሳበቃ፤ O'Hagan ተብሎ ወደሚጠራው የአይሪሾች Pub ገብቼ በጊዜ እሰየማለሁ። የከሰረ ሰው ስሜት ይሰማኝ ነበር።

O'Hagan ተስያት ላይ ጭር ይላል። ብዙውን ጊዜ ሙሲ የተባለውን ርካሽ ድራፍት እየገለበጥሁ ብቻዬን ስቆዝም እውል ነበር። ሉሳካ ላይ አንዳችም ትዝታ አልተውኩም ብዬ እንዳልምል ግን ካሮል በርገር በህይወቴ ውስጥ ገብታ ኖሮአል። ክልስ ዛምቢያዊት ናት። እንደኔው መሄጃ በማጣት ተስያት ላይ O'Hagan ስትመጣ ቀስ በቀስ ተግባባንና ወሬ ጀመርን። በጣም ቆንጆ ስትሆን፤ ያለማቋዋረጥ የምታጨስ፣ የቀለጠች የሉሳካ "ቃጠሎ" ነበረች።

"ስራ የለህም እንዴ? " ብላ ጠየቀችኝ።

"ስደተኛ ነኝ። አንቺስ?"

"እኔ ስራ የለኝም። የምን ሃገር ዜጋ ነህ?"

"ኢትዮጵያ! አንቺስ?"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ዛምቢያዊት ነኝ። አባቴ ግን ነጭ ነው። ግን አላውቀውም” አያያዘችና“ ኢትዮጵያ ማለት የት ነው? ” ስትል ጠየቀችኝ።

“ምስራቅ አፍሪቃ!”

ጥቂት ካሰበች በሁዋላ፡

“ሞዛምቢክ ነው ወይስ ደርባን?” ስትል ጠየቀቺኝ።

ስቄ ዝም አልኩ። ይህን ባለማወቅዋ አልተደነቅሁም። እስዋ ልክ ናት። እኛ ሃበሾች ገና ስንወለድ ጀምሮ የአለምን ካርታ ለማወቅ የተገደድንበት በቂ ምክንያት ነበረን። በሃገራችን ተስፋ ስለምናጣ ልባችንና ቀልባችን በባህር ማዶ ስልጣኔና ንዋይ ተማርኮ መንፈሳችን ቀድሞ ይኮበልላል። ይህቺ የደቡብ ቆንጆ ግን ከአካባቢዋ ርቃ ለመሄድ ፍላጎት እንደሌላት ግልፅ ነው። ስለዚህ “አፍሪቃ” ሲባል “ደቡባዊው አፍሪቃ” ብቻ ቢመስላት ምን ያስደንቃል?

ከካሮል ጋር እየተግባባን ስንሄድ በሶስተኛው ቀን ግድም ወደ ቤቷ ይዛኝ ሄደች። ከእናትዋና ከታናሽ ወንድሟ ጋር በአንድ የደከመች ዛኒጋባ ውስጥ ትኖር ነበር። ቡና አይነት ቀለምና ጠንካራ አፍሪቃዊ ሰውነት ያለው ወንድሟ ታላቅ እህቱን በጣም ሲያከብራትና ሲሳሳላት ተመለከትሁ። ወንበሮች አውጥቶ ከጃካራንዳ ዛፍ ስር አመቻቸልን።

ተሸክመን የገባነውን ሁለት ደርዘን ቢራ ተቀብሎ ተሸቆጥቁጦ አስተናገደን። እንደ ወተት የነጡ ጥርሶችና ሳቂታ ጥቁር ዓይኖች ያሉት ወጣት ነበር። ካሮል ከወንድሟ ጋር በአባት እንደማይገናኙ አጫወተቺኝ። እናትየዋ በእድሜ መግፋታቸው በቆዳቸው መሸብሸብ ቢታወቅም፤ ዘመናዊነት ይታይባቸው ነበር። እንደ ካሮል ጠጪና አጫሽ ነበሩ። ተግባቢና ደግ ሴት ሆነው አገኘሁዋቸው። ይዘን ከመጣነው ቢራ ለሶስታችንም ከበፊቱ በሁዋላ ሲጋራቸውን ለኩሰው በጥያቄ ያጣድፉኝ ያዙ፣

“...ሃገርህ የት ነው? ...ኢትዮጵያ? ...ህንድ ማለትህ ይሆን? ...ጠጉርህ የህንዶችን ይመስላል ብዬ ነው... ለምን ተሰደድክ ታዲያ? ...ባለስልጣኖች? ...ለምን አትከሳቸውም? ...መቼ ትመለሳለህ ወደ ሃገርህ? ...አታውቀውም? ...ከዘመዶችህ ተለይተህ እንዴት ትኖራለህ? ...አስቸጋሪ ነው። ...እኔ ከልጆቼ አንድ ሳምንት መለየት አልችልም፤ አሜሪካ ለትምህርት የሄዱ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ዛምቢያውያን የጉልበት ስራ መስራት ስላልቻሉ በረሃብ ሊሞቱ መድረሳቸውን ሰምተናል፤ የሰው ልጅ ከሃገሩ መውጣት የለበትም"

ካሮል ስሜን በትክክል አልያዘችውም። "ደስፋዜ" እያለች ትጠራኝ የነበረ ሲሆን፤ አስፈላጊነቱ ስለልታየኝ ሳላስ ተካክልላት ተውኩት። እንዲያውም "ደስፋዜ" የሚለው ይበልጥ ተስማምቶኝ ነበር። በመጀመሪያ "ካሮል ዱርዬ ናት" የሚል ግምት ይዤ ነበር። እየቀረብኳት ስሄድ ግን ያለማቋረጥ ማጨስዋና መጠጣትዋ እንዲያ እንዳስብ እንዳደረገኝ ተረዳሁ። በተረፈ ግን በጣም ጥሩ ሰው ነበረች። ካፌ ውስጥ ዌይተር ሆና እየሰራች ቤተሰብዋን ታግዝ እንደ ነበር አጫወተቺኝ። አሁንም ስራ እየፈለገች ሲሆን፤ እንደርስዋው ክልስ የሆነ ዛምቢያዊ ጓደኛ አላት። ከስድስት ወራት በሁዋላ የኮሌጅ ትምህርቱን ሲጨርስ እንደሚጋቡ ጭምር አጫወተቺኝ።

ካሮል የኔ ሁኔታ በጣም ያሳስባት ጀምሮ ነበር። ስደተኛ መሆኔ፣ አፍሪቃዊ መሆኔ፣ ወዴት እንደምሄድ አለማወቄ አጥብቆ እያስጨነቃት "ምን ልንረዳህ እንችላለን!?" እያለች ደጋግማ ትጠይቀኝ ነበር። ከሃገሬ የተባረርኩት በገዛ ወገኖቼ መሆኑ በተለይ በፍፁም ሊገባት አልቻለም። ያባረሩኝ "ነጮች" ይሆኑ እንደሆን ደጋግማ ብትጠይቀኝም በአገራችን "ነጭ ጠላት" አለመኖሩንና ርስበራስ እንደምንበላላ በሚገባት መንገድ አወጋሁዋት። ስለ ሩዋንዳ፣ ኮንጎ፣ የሶማሊያን የርስበርስ ግጭት አጫወትኳት። ስለዚሁ ጉዳይ በቴሌቪዥን የሰማች ቢሆንም፤ ብዙም ግልፅ አልሆነላትም ነበር። የኮንጎ እልቂት ማእድን በሚያድኑ ምእራባውያን የተፈጠረ ሰው ሰራሽ ግጭት መሆኑን ግን ግንዛቤ ነበራት። ስለ ኢትዮጵያ አንዳችም እውቀት ያልነበራት ሲሆን፤ ስማችን ተደጋግሞ በድርቅና በረሃብ እንደሚነሳ፤ ኢትዮጵያ ግን በአፍሪቃ ካሉት ሃገራት የበለጠ ውሃ ያላት፤ ለምለምና ሃብታም አገር መሆኗን፤ ራእይ ያለው መሪ በማጣትዋ ምክንያት ግን ህዝባችን በችጋር እንደተዋረደ አጫወትኳት። ከልብ እያዘነች አዳመጠቺኝ። አይኖችዋ እንባ ሲያቀሩም አስተዋልኩና ርእሰ ወሬያችንን ለወጥኩት።

...ሉሳካን የሁዋሊት በመተው መጋዣ በመሰለው አውቶብስ ተጭኜ ወደ ሞዛምቢክ ጉዞ ስጀምር በርግጥ ካሮል

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ውስጤ ቀርታ ነበር። እነዚያ የሚያባብሉና ፈጥነው የሚያዝኑ አይኖችዋ ገና አብረውኝ አሉ። እውቂያችን ያጭር ጊዜ ቢሆንም፣ በጣም ተላምደንና ተግባብተን ስለነበር ስሰናበታት ገፅታዋ ባንድ አፍታ አመድ መስሎ ነበር። እንባዋም ባይንዋ ሞላ፣

"ወዴት ነው የምትሂደው?" አለች በስሜት ተወጣ።

"ሞዛምቢክ። ከዚያም ድንበሩን አቋርጬ ደቡብ አፍሪቃ እገባለሁ"

"ለምን እዚህ ዛምቢያ አትኖርም?"

"እዚህ ስራ የለም ካሮል፤ እጄ ላይ ያለው ገንዘብ ከማለቁ በፊት ስራ ማግኘት አለብኝ"

ጥቂት ቆዘመችና፣

"በአይሮፕላን ለምን አትሂድም ታዲያ?" አለች።

"ቪዛ አይሰጡኝም"

"ለምን?"

"ፓስፖርትም የለኝም ካሮል"

"እንዴት ዛምቢያ ገባህ ታዲያ?"

"የሃሰት የማላዊ ፓስፖርት ይዤያለሁ። ድንበር ላይ ለፖሊሶች ጉቦ እየሰጠሁ ነው የማልፈው። በአይሮፕላን ከሆነ ግን ፍተሻው ይከብዳል"

የካሮል ገፅታ እጅግ አዝኖና ከብዶ አየሁት። አቅም አጥታ እንጂ በአለም ላይ ያላትን ነገር ሁሉ ልትሰጠኝ ፈቃደኛ እንደነበረች ምዬ መናገር እችላለሁ። ስደት ምን ማለት እንደሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ የገባት ይመስለኛል። ብዙ የሚያስቁ ታሪኮችን አውርቼላታለሁ። እንባዋ እስኪፈስ ስቃለች። እስዋም ስለ ወንድ ጓደኞችዋና ዛምቢያን የተመለከቱ ገጠመኞችዋን እያነሳች ስታወራኝ ከልብ ተመስጬ አዳምጬያታለሁ። አብረን ባሳለፍናቸው ጥቂት ሳምንታት ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ ችለን ነበር። አቦካዶ፣ ቲማቲምና ቃሪያ ባንድ ላይ ተቀላቅሎ በመክተፍ፣ የሚዘጋጀውን የኬንያ ካቹንባሪ የተባለ ምግብ ሰርቼ፤ አቅምሼያት በደስታ ልታብድ ደርሳ ነበር። በተለይም ፎጣ መስሎአት አልበላውም ብላ የሸሸችውን እንጀራ ከቀመሰችው በሁዋላ ሱስ ይዞአት ነበር።

በመጨረሻ ግን ለካሮልና ለሱሳካ ጀርባዬን ሰጥቼ መሄድ ግዴታዬ ሆነ። ማድረግ የምችለው የለም። ከአፍሪቃ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ጋር ካለኝ ፅኑ ቁርኝት መለየት ባልችልም፤ ይቺ ሃብታም አህጉር ዜጎችዋን ላም እንዳንከችው ጨርቅ አጨማዳቸዋለች። ያም ሆኖ እኔ አፍሪቃዊ ነኝ። ከነጮች መሃል መኖር አይቻለኝም። በቋንቋ ከማልግባባቸው አፍሪቃውያን ጋር ፍፁም የሆነ ሰላም አለኝ። ያሻውን ያህል ስጋት ቢወረኝም የአፍሪቃ ልጆች በየትም ቦታ ሁሉ ምቾት ይሰጡኛል። በአፍሮ ዛፎች ጥላ ስር ተቀምጬ መቆየት እንዳለብኝ ይሰማኛል። በሲያትል የደረሰብኝን ጉዳት ልረሳው አልችልም። እንደ ካሮልና እንደ ኬንያውያን ደግና እውነተኛ ገፅታ፣ ከልብ የሚፈልቅ ፈገግታ ያለው የሰው ፊት በሲያትል በፍፁም አላየሁም። ከወላይታ ወደ አርባምንጭ ጉዞ ባደረግሁበት በአንድ ወቅት የተሰማኝን ስሜት ማጣት ከቶ አልሻም። መልከአ ምድሩ፣ የኮባ ዛፎች፣ የለመለመ ሳር፣ እንሰት፣ ጠያይምና ውብ ገፅታዎች ሁሉ የኔ ናቸው። የኔው የራሴው ሆነውም ይኖራሉ።

ራሴን ማታለል እንደማልችል አውቃለሁ። የጋሪ ፈረስ አለመሆኔንም አውቃለሁ። የነፃነት መንፈስ አለኝ። አእምሮዬ እንደ ዱር ፈረሶች በነፃነት እንዲጋልብ እሻለሁ። በነፃ ሀሊና የማሰብ ችሎታዬ እንዲነካ አልፈልግም። ከወያኔ ጋር በቆየሁባቸው ጊዜያት ሳላውቀውም ይሁን ባለመብሰል፤ ስፈጠር ጀምሮ ይዤው የተወለድኩትን ነፃነት እያጣሁ፤ ወደ ባርነት አዘቅት ማሽቆልቆል ጀምሬ እንደነበር መገንዘብ ችያለሁ። ሆኖም የ"ቡርቃ ዝምታ"ን በመፃፍ በራሴ አስተሳሰብ መጓዝ እንደምችል ራሴን ለማሳመን ሞክሬ ነበር። በራስህ መንገድ ማሰብ ከጀመርክ ግን ለገዢው መደብ ጠላት መሆንህ አይቀርም። እናም አሁን ለስደት ተዳርጌያለሁ።

* * *

መጋጣው አውቶቡስ ወደ ሞዛምቢክ ድንበር እየገሰገሰ ነው። በአውቶብሱ ውስጥ በዘንቢል የተያዙ ዶሮዎች አልፎ አልፎ ይንጫጫሉ። በማይመች ሁኔታ በአንቀልባ የታዘሉ አፍሪቃውያን ህፃናት ሙቀቱና አስተዛዘላቸው አስጨንቋቸው ያለቅሳሉ። አይኖቼ በውበቱ ተወዳዳሪ የሌለውን የአፍሪቃ ጫካና ድንቅ መልከአ ምድር ይቃኛሉ። በየመንገዱ ዳር በተኮለኮሉ ጎጆዎች ደጃፍ ውሾች፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ዶሮዎች፣ በጎችና ፍየሎችን እያየሁ በመንገዝ ላይ ነኝ። አልፎ አልፎ ከወዲያ ወዲህ የሚሯሯጡ ጥቂቁር አሳማዎችን አያለሁ። ከዚህ ቀደም ጥቁር አሳማ አይቼ አላውቅም ነበር።

ምድሩ ከዳር እስከ ዳር አረንጓዴ ለብሶአል። ሜዳው ሲያልቅ ጫካ ውስጥ ገባን። በጫካው ውስጥ የዝሆን መንጋ ሲነጋጋ አየሁ። አንዲት ቀጭኔ ቆማ ቅጠል ስትቀነጥስ በፈጣን መንገድ ላይ አለፍናት። "ቂንዲ አንገትዋን አስግጋ" የሚለው የዳኛችው ወርቁ የአደፍርስ ትረካ አእምሮዬ ውስጥ መጥቶ ጥልቅ አለ። ቂንዲ ግን የአማራው አገር የተራራ አንገት እንጂ ቀጭኔ አልነበረም።

የዝሆኖቹ መንጋ ትርኢት ተደጋገመ። National Geography ላይ ብቻ የማውቃቸውን የዝሆን ግልግሎች ይኸው በአይኔ አየሁዋቸው። ትልቁ ዝሆን አምሳሉን ተክቶአል። የዝሆን ልጅ ዝሆን ነው። የአፍሪቃ ልጅ አፍሪቃዊ መሆን ሲገባው፤ እኛ ግን ርስበራስ እንበላላለን። ያለህርራሄ እንመቀኛኛለን! ባእድ አክብረን የራሳችንን እንን ቃለን! ወያኔ ከኢትዮጵያ አባረረኝ! ዛምቢያዊትዋ ካሮል ደግሞ አገር ስለሌለኝ አዝና እንባዋ ባይንዋ ሞላ! ስልጣን አልነበራትም እንጂ ዛምቢያዊነትን ትሰጠኝ እንደነበር ርግጠኛ ነኝ።

ማስታወሻ ደብተሬን አወጣሁና ለካሮል ጥቂት ስንኞችን ቋጠርኩላት። በመጋዣው አውቶቡስ መስኮት ወዲያ ማዶ የምመለከተው ውብ መልከአ ምድር የስነጥበብ ቆሌዬን ቀሰቀሰው፣

"ካሮል!" ስል ጮህኩ!

ካሮል የነጭና የጥቁር ቅልቅል፣
የሉሳካ እምብርት ቅምጥል፣
የድህነትና የቅንነት ምስቅልቅል፣
ጓደኛዬ ነህ አትብይኝ - ሲቃ ብቻ ነበር ሲቃ!
እንደ ሃምሌ ፀሃይ - ብልጭ ያለ ደቂቃ፣
የአንድ አህጉር ብሶት - ያባት አገር ያፍሪቃ፣
የማግኘትና ማጣት ተረት - የጥቁር ህዝብ ሰቆቃ፣
እና ካሮል ቻው! - ቻው፣ ቻው በቃ፣
ድርግም አድርገሽ እርሺኝ - እልም ይበል አዚሙ፣
ደስፋሂ አልነበረም - የለምም ለዘልአለሙ፤

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ይህን ግጥም ስቋጥር በአእምሮዬና በልቤ የነበረው ስሜት ከዚያች ደግና ውብ ዛምቢያዊት ወጣት ሴት ርቄ የመሄዴ አስጨናቂ ስሜት ነበር። ዳግምም የማላያት መስሎኝ ነበር። ዳሩ ግን በአስገራሚ ሁኔታ ተሳስቼ ኖሮአል። ርቄ የሄድኩ ይምሰለኝ እንጂ ለካስ ካሮል ጎረቤቴ ነበረች።

(ከሶስት አመታት በሁዋላ ጆሃንስበርግ ላይ የአዲሱን አመት በአል ስናከብር፤ ሳንተን ከተባለ ቀበሌ አንድ ናይት ክለብ ውስጥ ካሮልን አገኘሁዋት። እኔ ጫካ ለጫካ እየተሸሎከለኩሁ ከደረስኩበት አገር እስዋ ለሶስት ቀናት እረፍት ነበር የመጣችው። "ደስፋሂ" ብላ ጮኻ እጆቼን ይዛ እንደ ሀፃን ልጅ ትዘል ጀመር። የጠጣነው ተደምሮበት ደስታችን ሰማይ ነካ። እንደ ርስዋው ክልስ የሆነ ጎልማሳ ሰው አብሮአት የነበረ ሲሆን፤ ባልዋ እንደሆነ ነግራ አስተዋወቀችኝ። የፈረንጆች 2005 አዲስ አመት እኩለ ሌሊት ላይ ጆሃንስበርግ ሲገባም አብረን ተቀበልነው። የደቡብ አፍሪቃን መታወቂያና ፓስፖርት ማግኘቴን ስነግራት በተለይ ካሮል ደስታው እጥፍ ሆነላት። ስሜትዋን ሳትደብቅ ሁለት እጆችዋን ዘርግታ አቀፈቺኝ።)

* * *

መጋጣው አውቶብስ ከሞዛምቢክ ድንበር ላይ ሲያራግፈን ሊመሽ ምንም አልቀረውም። ያቺ የዛምቢያ የድንበር ከተማ ጨርሳ የሞተችና የህይወት እንቅስቃሴ የሌለባት የገጠር መንደር ነበረች።

ስፍር ቁጥር የሌለው ቂጠሮ የተሸከሙ፣ ደማቅ ጨርቅ የለበሱ አሮጊቶች የሚታዩባት፣ ከዘመናዊነትና ከስልጣኔ የራቀች ቀበሌ ነበረች።

አገሩን የሚያውቁ ሃበሾች ሉሳካ ላይ በጠቆሙኝ መሰረት ፊጥኜ በአካባቢው ወደ ነበሩ ሚኒባሶች በማምራት ወደ ድንበሩ ኬላ መሄድ እንደምፈልግ ገለፅኩ። ከኔ ሌላ በዚያ ሰአት ወደ ኬላው የሚሄድ ሊገኝ ባለመቻሉ ከመደበኛ ክፍያው ሶስት እጥፍ ከፍዬ ብቻዬን ይዘውኝ ለመሄድ ተስማሙ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በግማሽ ሰአት ውስጥ ከኬላው ደርሼ እንደነገሩ ፎቶዬ የተለጠፈበትን የማላዊ ፓስፖርት ለተቆጣጣሪው አቀረብኩለት። 20 ዶላር ፓስፖርቱ ውስጥ አስቀምጬ ነበርና ሃላፊው ዶላሩን ሲመለከት ፊቱ ፈካ። የይለፉን ማህተምም ያለማወላወል ደረገመልኝ! በዚህም አላበቃም። ቢሮውን ዘግቶ፣ ሻንጣዬን እራሱ አንጠልጥሎ ወደሞዛምቢክ ድንበር ይሸኘኝ ጀመር።

"የምን አገር ዜጋ ነህ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ኢትዮጵያ"

"ብዙ ኢትዮጵያውያን በዚህ በኩል ይመጣሉ። እናግዛቸዋለን!"

ፋታ ወስዶ ደግሞ እንዲህ ሲል አከለበት፣

"... አይዞአችሁ! ሰላም ሲሆን አንድ ቀን ወደ ሃገራችሁ መመለሳችሁ አይቀርም! ታሪክ ስናነብማ በናንተ የማይቀና አልነበረም! ጊዜ ነው ያዋረዳችሁ፤ እንኳን ለራሳችሁ ለሌላውም የምትተርፉ ነበራችሁ! "

ዛምቢያዊው የተናገራቸው እነዚህ ቃላት በህይወት መንገድ ላይ ከሰማሁዋቸው የተስፋ ቃላት ሁሉ ይበልጥ ጠቃሚና የማይዘነጉ ሆነው አጊንቼያቸዋለሁ። መጨለም በጀመረበት ገጠር፣ በሞዛምቢክና በዛምቢያ ድንበር ላይ፣ ህገወጥ ሰነድ የያዘ ስደተኛ ይህን የመሰለ ቃል ሲሰማ ምን ሊሰማው የሚችል ይመስላችሁዋል!? መቆጣጠር ያልቻልኩት እንባ የቀላቀለ ሲቃ ተናነቀኝ። ይህ ዛምቢያዊ ይህን የመሰሉ ደግ ቃላት የተናገረው በ20 ዶላር ተደልሎ እንዳልነበር በርግጠኛነት መናገር እችላለሁ። ጉቦ በመስጠት ወንጅሎ ቢያስረኝ ያለኝን ሁሉ አስረክበው ነበር። ሊዘርፈኝና ሊያስገድለኝ በቻለ። ጨምርልኝ ማለትም ይችላል። ማላዊያዊ አለመሆኔን ያውቃል። የዚያ ኬላ ተቆጣጣሪ ደግነት የሚለካው እኔ ካለሁበት ችግር አንፃር ነበር። ምሽት ነው፣ ገጠር ነው፣ ህገወጥ ነኝ፣ አገሩን አላውቀውም። ይቺው ግን ኢትዮጵያ ስለተባለችው ሃገር በጎ በጎውን እያወጋኝ፤ ሻንጣዬን ተሸክሞልኝ የዛምቢያን ድንበር አሻገረኝ። እናም እንዲህ ሲል አሰናበተኝ፣

"ደህና ሁን! ይቅናህ! በወዲያኛው የሞዛምቢክ ድንበር ላይ ያለው ሰው አንጀሎ ይባላል። በግልፅ ንገረው! ይረዳሃል!"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በዚህች አለም ላይ በንብረትነት የቀረቺኝንና በቁርጥራጭ ወረቀት የተሞላች ሻንጣዬን አንጠልጥዬ ብቻዬን ወደ ሞዛምቢክ የኬላ ጣቢያ ተጠጋሁ። የሞዛምቢኩ የኢሚግሬሽን ተቆጣጣሪ ብቻውን በመደዳ ከተሰሩ ከባለ ሶስት ክፍል ቢሮው ደጃፍ ላይ ተቀምጦ በኩባያ ሻይ ሲጠጣ ነበር ያገኘሁት። ፓስፖርቴን ተቀበለኝና የይለፍ ማህተም ከደረገመበት በሁዋላ፣

"አሁን መሽቶአል! እዚህ ማደርህ ነው" አለኝ።

"ሆቴል አለ?"

"አምስት ዶላር ያስከፍሉሃል"

"ችግር የለም"

"ትንሽ ጠብቀኝና አብረን እንሂዳለን"

ከአስር ደቂቃ በሁዋላ ተያይዘን ጉዞ ጀመርን። ከሩብ ሰአት በሁዋላ ከአገዳና ከጭቃ ከተሰሩ ዛኒጋባዎች ደጃፍ ላይ ተገኘን። ሆቴል ሊባል የሚችል አልነበረም። መደዳውን የተሰሩት አምስት ክፍሎች በር አልነበራቸውም። አልጋ የሚመስል የተጋደመ ነገር ጥግ ላይ ይታያል። ቆሻሻ ብርድ ልብስ ላዩ ላይ ጣል ተደርጎበታል።

"በር ያለው ክፍል የላችሁም?" ስል ጠየቅሁ።

"የለንም!" ባለሆቴሉ ፈገግ አለ። "...እዚህ ምንም በር ያለው ክፍል አያስፈልግህም። ከፈለግህ ደጅ ማደር ትችላለህ። እነዚህን ክፍሎች የሰራናቸው ኒጋዴዎች በዚህ ሲያልፉ እንዳይቸገሩ በማሰብ ነው። አይዞህ! አትፍራ! ወንድሞችህ ነን! "

የኢሚግሬሽኑ ተቆጣጣሪም ፈገግ አለና፣

"ሻንጣህን እዚሁ ተወው! አሁን እኔ ቤት እንሂድና ራት እንብላ! ከፈለግህ ደግሞ ቢራ የሚሸጥበት ቤት ስላለ እዚያ እናመሻለን!"

መንደሪትዋ ኤሌክትሪክ ስላልነበራት ባለ ሆቴሉ ላምባዲና ሰጠኝ። የኬላው ተቆጣጣሪ ቤቱ ወስዶኝ ራት በላን። የአሳማ ሽኮና በገንፎ ነበር የቀረበልን። ምንተእፍረት ይዞኝ እየተናነቀኝ በላሁት። ሊያስመልሰኝ ቂቅ እያለኝ የአሳማ ኩቴ መረቁን በገንፎ እያጣቀስኩ ከበላሁ በሁዋላ ከተቆጣጣሪው ጋር ተያይዘን ወደ ቢራ ቤት ሄድን።

(ከወራት በሁዋላ የአሳማ ሽኮና ከነመረቁ በመላ የደቡብ አፍሪቃ ከተሞች ምርጡ ምግብ መሆኑን የተረዳሁ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሲሆን፣ በርግጥም ከዚያ ወዲህ ለምጄውና ወድጄው ፕሪቶሪያ ላይ የአሳማ ሽኮና መረቅ የሚሸጥባቸውን ቤቶች እስክ ማፈላለግ ደርሼ ነበር።)

ደጄ ጨልሞአል።

በላምባዲናችን እየተመራን ስንዝዝ ትግራይ - ሃገረ ሰላም ትዝ እያለኝ ነበር። ከወያኔ ጋር በትግል በቆየሁባቸው ዘመናት በላምባዲና እየተመሩ፤ ቀጫጭን የእግር መንገዶችን እየተጠማዘዙ መጓዝን ተላምጄው ነበር።

ከኬላ ተቆጣጣሪው ጋር ዶዢም የተባለውን የሞዛምቢክ ቢራ እየጠጣን ብዙ አወጋን። የኬላው ሃላፊ በፍፁም የፖለቲካ ወሬ የሚያውቅ አልነበረም። ያጫወተኝ ስለ ቢዝነስ ነበር። በኬላው ከሚያልፉ ስደተኞች የሚያገኘውን ጥቂት ጉርሻ እያጠራቀመ አንድ ሚኒባስ መግዛቱን በኩራት ነገረኝ። ሁለት ልጆች የወለደ ሲሆን፤ በዝውውር ወደ ማፑቱ ከጠሩት እንደ ሞት ፍርድ እንደሚቆጥረው አጫወተኝ። ራሴን ላይ ታች እየነቀነቅሁ አዳምጬ ሳበቃ፣

"ብዙ ተባብረሽኛል። ለቢራ መጠጫ ይሆንሃል" በማለት ቀደም ብዬ ያዘጋጀሁዋትን ሃያ ዶላር አስጨበጥኩት። በደስታ አመስግኖኝ እስከ ሆቴሌ ሸኘኝ።

ሌሊቱን ሊዘርፉኝ የሚመጡ ወሮበሎች ይኖራሉ ብዬ በመስጋቴ ክፍሌን ለቅቄ ደጁ ላይ ካለ አንድ ዛፍ ስር ብርድ ልብሴን አንጥፌ፣ ሻንጣዬን ተንተርሼ ተኛሁ። እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር ወደኔ ክፍል የሚገባውን ዘራፊ ለማየት ብጠብቅም ያሰብኩትን ሳላይ ሌሊቱ ነጋ። ባለ ሆቴሉና ቤተሰቡ ከእንቅልፋቸው የነቁት ከረፈደ በሁዋላ ነበር።

ከምሳ በፊት ግድም ወደ ማፑቶ የሚያደርስ አውቶብስ ላይ ተሳፍሬ ጉዞ ጀመርኩ። ከሁለት ቀናት አሰልቺ ጉዞ በሁዋላም ማፑቶ ገባን።

በመንገዳችን ላይ ታዲያ ሳሞራ ማሼል የተዋጋባቸውን ደኖችና ዱሮች ሁሉ እያለፍን ተጉዘናል። ታዋቂውን የዛምቤዚ ወንዝ ስናቋርጥ በደስታ ብዛት ጩኸቴን አሰምቻለሁ። የዝሆን መንጋ የዛምቤዚን ወንዝ በዋና ሲያቋርጥ በአይኔ በብረቱ ተመልክቼያለሁ። የሞዛምቢክን ማለቂያ የሌለው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ እየሰነጠቅን ስንዝዝ ልብን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ቀጥ የሚያደርግ ውበት ያላቸው ኮረዶች ከጫካው ውስጥ የማንጎ ፍሬ ሲለቅሙ ተመልክቼያለሁ። ይህ ጉዞ ያለምንም ልዩነት ከአርባ ምንጭ ወደ ዶርዜ ያደረግሁትን ጉዞ አስታውሰኛል። የመልከአ ምድሩ፣ የዛፎቹ፣ የወንዞቹ፣ የሰዎቹ አይነት ፍፁም ተመሳሳይ ነበር።

ማፑቶ ላይ ሁለት ወራት ከቆየሁ በሁዋላ ወደ ተስፋይቱ ሃገር ለመሻገር ወሰንኩ። ማፑቶ ላይ ሁለት ወራት ለመቆየት የቻልኩት እጅግ ድንቅ የሚባሉ ጥቂት አበሾችን ስላገኘሁና እዚያ ቀላል ንግድ ቢጤ ጀምሬ ኑሮ ልመሰርት እችል ይሆናል በሚል ግምት ነበር። እንዳሰብኩት ግን አልሆነም። ፖርቲጊዝ የተባለውን ቋንቋ ልለምደው አልቻልኩም። ህዝቡን ወድጄው ነበር። ሌባና ወንጀል የለም ማለት ይቻላል። መኪናህን ደጅ ብታሳድር የሚነካብህ የለም። ደግና መዝናናትን የሚወድ፣ ሙዚቃ የሚያፈቅር ህዝብ መሃል መቆየት መንፈስን ያድሳል። በየእለቱ ምሽት ላይ ህንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ሞዛምቢካውያን አለማቸውን ይቀጫሉ። የአሳና የዶሮ ጥብስ ውቅያኖሱ ዳርቻ በርካሽ ይቸበቸባል። ሞዛምቢካውያን ፍቅር ያውቃሉ ከማለት ይልቅ እንዲያው በደፈናው ፍቅር ናቸው ማለቱ ይቀላል። ባዶ ኪስ ህን ውቅያኖሱ ዳር ተጋድመህ ደስታን በጆንያ ዝቀህ ወደ ቤትህ ትመለሳለህ። "አብሪጋዶ - አመሰግናለሁ" የሚለውን ቃል በየሰከንዱ ትሰማዋለህ። አብዛኞቹ ጆሮአቸውን ቢቆርጡዋቸው እንኳ እንግሊዝኛ አይሰሙም። ብዙውን ጊዜ ግን ለመግባባት ቋንቋ አያስፈልግህም። ውቅያኖሱ ሲሸሽ ወደ ባህሩ ዘልቀን እንገባለን። ተሰያት ላይ የውቅያኖሱ ማእበል እየደነፋ ሲመጣ እየሸሸን ወደ ዳርቻው እንመጣለን። ለአይን ያዝ ሲያደርግ ህንድ ውቅያኖስ እንደ ጎፈራም አንበሳ እየተቆጣ ዳርቻውን ቀውጢ ያደርገዋል። የማፑቶ ወጣቶች፣ ባልና ሚስቶች አጫጭር ቁምጣ አድርገው የውቅያኖሱን ዳርቻ ያጨናንቁታል። እዚያው ተዋውቀው፣ እዚያው በፍቅር አብደው፣ የጋብቻ ቀነ ቀጠሮውን እዚያው የሚጨርሱ ፍቅረኞችን ማየት የተለመደ ነው። ይህም የባህሩ ፀጋ ነው። በውቅያኖሱ ዳርቻ ጥንቆላ የሚያካሂዱ፣ እንደ ቢሾፍቱ ሃይቅ ዳርቻ ገበሬዎች እርጥብ ቅጠል ይዘው ባህሩን የሚለማመኑም ይታያሉ። ይህ አፍሪቃ ነው። መሬቱና ባህሩ አፍሪቃ ነው። ማፑቶ በቆየሁባቸው ሁለት ወራት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አእምሮዬ ፀጥተኛና የተረጋጋ ሆኖ ነበር።

* * *

ከሁለት ወራት ቆይታ በሁዋላ ግን ሞዛምቢክን ለቅቄ ወደ ስዋዚላንድ ገባሁ። ስዋዚላንድ ላይ አበሾችን ወደ ደቡብ አፍሪቃ የሚያሻግር "ሰለሞን ማጂላን" በሚል ስም የሚታወቅ አበሻ አለ። የኔ መምጣት ከአደራ ጋር በማጥቶ ወዳጆቼ ተነግሮት ነበርና ስዋዚላንድ ዋና ከተማ ምባባኔ ደርሼ ስደውልለት አክብሮት አክሎ አነጋገረኝ።

"አሁኑኑ እመጣለሁ! አምስት ደቂቃ ብቻ ስጠኝ!"

ከሃያ ደቂቃ በሁዋላ መጣ።

በነጋታው ማለዳ የማላዊ ፓስፖርቴን ቀዳድጄ ከምድረ ገፅ ካጠፋሁት በሁዋላ ማጂላንን አምኜ ለጉዞ ዝግጁ ሆንኩ። በርግጥ አስጊ ሁኔታ አልነበረውም። ከኔ በፊት በሺህዎች የሚቆጠሩ አፍሪቃውያን ስደተኞች በዚህ መንገድ አልፈዋል። ሴቶችና ህፃናትን ጭምር ይዘው ኬላውን ተሻግረዋል። ነፍሰ ጡር ሴቶች ሳይቀር ይህን መንገድ ተመላልሰውበታል። ማንዴላ ስልጣን ከያዘ በሁዋላ ደቡብ አፍሪቃ ሆደ ሰፊ እናት ሆናለች። ያም ሆኖ ግን አያሌ አደጋዎች ተከስተዋል። በጫካ ወንበዴዎች ተዘርፈው የተገደሉ፣ የተደፈሩ ሴቶች፣ በአውሬ የተበሉ ዜጎች ጥቂት አይደሉም። ወደ አውሮፓና አሜሪካ ለመሻገር አቅሙ የሌላቸው ሁሉ በመንገድ ላይ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ችግር እየተጋፈጡ ወደ ተስፋይቱ ሃገር ይጓዛሉ። በሰላም መግባት የቻሉ ጥረው ግረው ጥቂት ጥሪት ከቋጠሩ በሁዋላ ወደ አውሮፓ ወይም አሜሪካ ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ። የተሰማማቸው ደግሞ እዚያው አግብተው፣ ወልደው፣ ህይወትን ቀጥለዋል። ርግጥ ነው በዚያች ምድር ወንጀል አለ። አፍሪቃውያን ስደተኞች በተደጋጋሚ በጨቤ ታርደው ሞተዋል። በዘራፊዎች ተተኩሶባቸው ህይወታቸውን አጥተዋል። ይህ ሚስጥር አይደለም። የአፍሪቃ ስደተኞች ወደዚያች የተስፋ ሃገር የሚጓዙት ይህን ሁሉ እያወቁ ነው።

እኔም ማጂላንን ተከትዬ የደቡብ አፍሪቃን ዱርና ጫካ አቋርጬ ስጓዝ የእድል ጉዳይ ሆኖ መንገዱ ቀና ሳይሆንልኝ ቀርቶአል። የድንበሩን አጥር ሾልከን ገብተን፣ ጫካውን በእግር አቋርጠን ወደ ዋናው የአስፋልት መንገድ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከወጣን በሁዋላ በአካባቢ ፖሊሶች ተያዝን።

* * *

ስምንት ቀናት ታሰርን!

የእስር ቤት ቆይታችን ግን ከባድ አልነበረም። የደቡብ አፍሪቃ እስር ቤቶች ለክፉ አይሰጡም። በሊጋጣሚ ብርድም ሙቀትም አልነበረም። እስር ቤቶቹ ንፁህ ናቸው። ሙቅና ቀዝቃዛ ውሃ ሻወር አለው። አስራ አምስት ሆነን በታሰርንበት ክፍል ውስጥ አራት የመታጠቢያ ሻወርና ሁለት መፀዳጃዎች ነበሩት። ሌሊት ይዘጋብናል። ቀን ቀን ግቢያችን ውስጥ ፀሃይ እንሞቃለን። ልብሶቻችንንም እናጥባለን። ምግቡ ጥሩ ባይሆንም አይርበንም። ፓፕ የተባለውን ገንፎና ስጋ ያነሰው መረቅ ከሻይ ጋር ያቀርቡልናል።

በእስር ቤቱ ቆይታ ከማጂላን ጋር ጥቂት ለማውራት እድል አገኘን። አውሮፓና ላቲን አሜሪካን በደንብ እንደሚያውቃቸው ተረዳሁ። ኩባና ቡልጋሪያ ተምሮአል። ስደተኞችን ወደ ደቡብ አፍሪቃ የማሻገሩን ስራ ከጀመረው ዘጠኝ አመት አልፎታል።

እኔም የመንግስት ጋዜጠኛ እንደነበርኩ ነገርኩት።

"ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሰርተሃል?" ሲል ጠየቀኝ።

"ሰርቻለሁ"

"ቴሌቪዥን የምትሰራ ትእግስት የምትባል ልጅ ታውቃለህ?"

"አላውቃትም። እኔ ፕሬስ ነበርኩ"

"ፕሬስ! ፍፁምን ታውቃታለሃ!"

"ፍፁም!" አልኩ በደመቀ ድምፅ፣ "...አውቃታለሁ! በደንብ አውቃታለሁ"

"አብረን ነው የተማርነው" አለ።

"ምስራቅ አውሮፓ መማርዋን አውቃለሁ" አልኩ።

"በጣም ጥሩ ልጅ ናት"

"ልክ ነህ"

ወሬውን የመቀጠል ፍላጎት በማጣቴ ወደ ሌላ ርእስ አሻገርኩት።

"ለምን ወደ አውሮፓ አትሂድም?"

"ምናደርጋለሁ?" አለ ፈጥኖ፣ "...የአውሮፓን ቆሻሻ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለማፅዳት?"

"እዚህ ከመኖር አይሻልህም?"

"አይሻለኝም!" ሲል አረጋገጠልኝ። "...ሰዎች ወደ አውሮፓ የሚጎርፉት በተሳሳተ ግምት ነው። በሃገራችን መኖር ላልቻልን ሃበሾች አፍሪቃ የተሻለ ቦታ ነው ብዬ አስባለሁ። በተለይ ጭንቅላትህን መጠቀም ከፈለግህ እዚህ ይሻላል። ይሄ ገነት ነው፣ የኔ ወንድም"

አባባሉ እውነት ሊሆን ይችላል። ሆኖም የማጂላን የራሱን ኑሮ ካየን ግን ገነታዊ ሊባል የሚችል አልነበረም። ስደተኞችን አስከትሎ አንበሳና ሌሎች አውሬዎች የሚመላለሱበትን ዱር ማቋረጥ አስጊና የቆቅ ህይወት መስሎ ተሰማኝ። ማጂላን ጥሩ ገንዘብ እንደሚሰራ አያጠያይቅም። አውሮፓን የሚያውቅና መሄድ ከፈለገም እንደሚችል ስለተረዳሁ ሳልገረም አልቀረሁም። እንደ አፍሪቃ ዱር አራዊት ጎጆ በበዛባቸው የገጠር ቀበሌዎች መኖርን ያለጥርጥር ወዶ ያደረገው ነበር። የአካባቢውን ቋንቋዎች እንደ አማርኛ ያቀላጥፈዋል። በመንገዳችን ላይ የስዋዚላንድ ገበሬዎች ስሙን እየጠሩ ሰላምታ ሲያቀርቡለት ሰምቻለሁ። ውሃ ለመጠጣት አረፍ ባልንበት አንድ ቤትም እንደ ቤተኛ ተስተናግደናል። "ምግብ ብሉ" ብለው አስቸግረውን ነበር። ብጥስጣሽ ቁምጣ የለበሱ ማቲዎች ማጂላንን እንደ አጎታቸው በሞቀ ሁኔታ ነበር የሚቀበሉት።

በሶስተኛው የእስር ቀን ከእስረኞቹ ጋር ይበልጥ ተግባባን። ከኮንጎ፣ ከታንዛንያ፣ ከሶማሌያ፣ ከኢትዮጵያ፣ ከአልጄሪያ፣ ከናይጄሪያ፣ ከዚምቡዋቤ፣ የተሰባሰብን ነበርን። ኢትዮጵያዊው እስረኛ አንዳንድ አስቂኝ ገጠመኞቹን እያነሳ ሲያወጋን ጥሩ ጊዜ ገደልን። ከበደ ይባላል፣

"የደርግ አስር አለቃ ነበርኩ" ሲል ጀመረ፣ "...ሞያሌ ላይ ተመድቤ እየሰራሁ ሳለ ቢዝነስ ተሳካልኝ። ደረጃውን ያልጠበቀ ቆርቆሮ ወደ ኢትዮጵያ እያሰገባን የጉቦ ገንዘብ ጠገብኩ። እብድ የሚያክል ቪላ ቤት ሰራሁ፣ እዚያው ሞያሌ። ቆንጆ ሚስት መርጬ አገባሁ። ወለድኩ። ምን ቀረኝ? የቀረኝ ነገር ቢኖር ከወታደር ቤት በቦርድ መሰናበት ብቻ ነበር። በሰው በሰው፣ በጉቦ ተረማምጄ አበድኩ አልኩና ጦር ሃይሎች ሆስፒታል ገባሁ። ቦርድ ለመውጣት አምስት ዶክተሮች እንደሚመረምሩኝ ሲነገረኝ በድንጋጤ ውሃ ሆንኩ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እስኪ ይታያችሁ! ጤነኛ ነኝ! ያበደ ሰው እንዴት እንደሚሆን አላውቅም።

በአንዲት ነርስ መሪነት ዶክተሮቹ ወደ ተቀመጡበት ክፍል ሰገባ ማበዴ እንዲታወቅልኝ ስለፈለግሁ፣ አንድ ፍሬ የምታክለዋን ነርስ በጥፊ ይገር ድርግም! የኔ ወንድም ተሸከርካሪ እግሬ ስር ጥቅልል! በዚህ ገበቴ እጅ! እግዜር ያሳያችሁ! ወዲያው ተረባረቡና ይዘው መርፌ ወጉኝ።

በስንተኛው ቀን እንደሆነ አላውቅም፣ ከደነዘዝኩበት ስነቃ ከእብዶች መሃል አማኑኤል ሆስፒታል ቁጭ ብያለሁ። ወይኔ ከበደ! ከቢሾ! ከቤ! ጉድ ሆንኩኝ። አእምሮዬ ምንም አያስታውስ። እንደምንም ብዬ ሞያሌ የሰራሁት ቤት ታወሰኝ። በመቀጠል ሚስት ማግባቴ፣ መልኳ ቀስ እያለ መጣልኝ... በመቀጠል ልጆቼ...ከዚያ ወታደር መሆኔ...እያለ እያለ ነርሷን በጥፊ መምታቴ ትዝ ሲለኝ ከተኛሁበት ተስፈንጥሬ ስነሳ ለካስ ተደባዳቢ ነው ተብሎ ተወርቶ ኖሮአል እንደገና ተረባረቡና መርፌ! ወይኔ ከቤ!...እኔ እኮ ተሽሎኛል ልል ነበር አሳቤ።

በስንተኛው ቀን እንደሆነ አላውቅም እንደገና ስነቃ ተረባርበው ይዘው መርፌ! ገና ስነቃ፣ ወሬ የለም። ግርግር! ያዘው! ያዘው! መርፌ! ስንት ጊዜ እንደ ወጉኝ አምላክ ይወቅ...በመጨረሻው ላይ ስነቃ ግን ሰው የሚባል የለም። ጥቂት እብዶች አሉ። ተነስቼ ወደ ደጅ ስወጣ ዘበኛ ነው መሰለኝ በተረበሸ ሁኔታ ገባ ወጣ ይላል፣

'ምንድነው ጉዳዩ?' ስል ጠየቅሁት።

'ደርግ ወደቀ፣ ወያኔዎች አዲሳባ ገቡ!'

አይ ከበደ ከርታታው!

ደርግ እንዲህ መውደቂያው ቀርቦ እያለ ነው መርፌ ስወጋ የሰነበትኩት። ልብሴን ለብሼ ወደ ሞያሌ...”

አልጄሪያዊው ደግሞ አብዱልመጂድ ይባል ነበር። ለምን እንደተሰደደ አጫወተን።

አንድ ምሽት ሙባረክ የተባለ የከተማዋ ሃብታም፣ ምሽት ላይ ሰው ሲገድል ይመለከታል። ሄዶ ያየውን ለፖሊስ በማመልከቱ ስድስት ወር ታሰረ። በስድስተኛው ወር አንዱ ፖሊስ እንዲህ ሲል መክሮ ለቀቀው፣

“ሙባረክ ሰው ሲገድል ማየት አልነበረብህም። ተሳስተሃል። ብታይም እንዳላየህ መሆን ነበረብህ። ምስጢሩን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንዳታወጣበት ሲል አንተንም ሊገድልህ ይችላል። አሁን የምንመክርህ አገር ለቀህ እንድትጠፋ ነው። ወሬም አታውራ"

መሰደድ የቻለው ወደ ደቡብ አፍሪቃ ብቻ ሆነ።

ናይጄሪያዊው ደግሞ ጁነዲን ይባላል። ጠጉሩን ሹሩባ የተሰራ፣ ባለግዙፍ ሰውነት፣ ጨካኝ ገፅታ ያለው ወጣት ነበር። የአደንዛዥ እፅ ነጋዴ መሆኑን አልደበቀንም።

ሶማሌው ወሬ ከጀመረ አራት ነጥብ የሚባል የማያውቅ ሲሆን፣ ሃሳቡ ሁሉ ሲጨመቅ አሜሪካንን ማውገዝ ብቻ ነበር። የወደፊት ህልሙም አሜሪካ መግባት ነው።

"አሁንስ ምን እየሰራህ ነው?" ስል ለሞያሌው ከበደ ጥያቄ አቀረብኩ።

"ነዋሪነቴ ሞያሌ ነው። የኤድስ ህይወት ማራዘሚያ መድሃኒት ከደቡብ አፍሪቃ ወደ ኢትዮጵያ እያመላለስኩ እነግዳለሁ። የሃዲያ ወጣቶችንም በሞያሌ በኩል እስከ ናይሮቢ አጓጉዛለሁ። የማልሰራው የስራ አይነት የለም። ቪዛ ስለማላገኝ ግን ያው ድንበር እየጣስኩ ነው የምጓዘው"

የኮንጎ ስደተኞች በከርሰ ምድር መአድን ሃብት ስለገነነችው ሃገራቸው ሲያጫውቱኝ የጨለመ መንፈስ ወረረኝ። ለሃብት የሚስገበገቡ ነጮች በሚፈጥሩት የርስበርስ ጦርነት የዚህች አህጉር ዜጎች ከመሬታቸው እየተነቀሉ ይሰደዳሉ። ኮንጎ በአለም ላይ ካሉ ሃብታም ሃገራት በመጀመሪያው ጠርዝ ላይ መገኘት ሲገባት ወጣቶችዋ ይኸው እዚህ እስር ቤት ይገኛሉ።

ከእኛ የእስር ክፍል ፊትለፊት ሶስት ወጣት ነጮች ታስረዋል። ነጮቹም ሆነ ጥቁሮቹ ቀኑን ሙሉ ሲስቁና ሲተራረቡ ይውላሉ። መጨነቅ የለባቸውም። የሚፈልጉት ሁሉ ይገባላቸዋል። ማሪዋና ያጨሳሉ። ወደ ጓደኞቻቸውና ቤተሰቦቻቸው በፖሊሶች ስልክ ይደውላሉ። ፖሊሶቹ በወዳጅነት መንፈስና በክብር ያነጋግሩናል።

በአራተኛው ቀን የፖሊስ አዛዡን ለማነጋገር እንደምፈልግ ገለፅኩና ወደ ቢሮው ተወሰድኩ፣ ባጭሩ መቼ ውሳኔ ልናገኝ እንደምንችል ጠየቅሁ፣

"ወደ ፍርድ ቤት ሳትቀርቡ እዚህ በመቆየታችሁ የኔ ጥፋት አይደለም። እናንተ የአደራ እስረኞች ናችሁ" አለኝ።

"መቼ ነው ውሳኔ የምናገኘው?" ደግሜ ጠየቅሁ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"እዚህ የታሰራችሁት ከህግ ውጭ ነው። በሶስት ቀናት ውስጥ መጥተው ካልወሰዱዋችሁ ፈትቼ እለቃችሁዋለሁ"

አመስግኜ ከመቀመጫዬ ስነሳ፣

"ምናልባት ወደ ከተማ ወጣ ማለት ከፈለግህ ግን መታመምህን ግለፅልን" አለኝ።

በነጋታው እኔና ማጂላን በአንድ ፖሊስ አጃቢነት ወደ ሆስፒታልና ከተማ ወጣን። ጋዜጦችን በብዛት ገዝቼ ተመለስኩ። ከኔልሰን ማንዴላ መምጣት ወዲህ የደቡብ አፍሪቃ እስር ቤቶች የተመቹ ይሆኑ ዘንድ አንዳንድ ርምጃዎች መወሰዳቸውን ተረድቼያለሁ። በታሰርንበት ክፍል ግድግዳ ላይ ቀደምት እስረኞች የፃፉት ፅሁፍም እንዲህ ይል ነበር፣

"እዚህ ስትታሰር ማንዴላን አስታውስ! እሱ የእስር ቤት ስቃዮችን ሁሉ ተሰቃይቶልሃል"

በመጨረሻው የእስር ቤቱ ሌሊት እንቅልፍ እንቢ አለኝ። የእስር ባልደረቦቼ በሰላም ተኝተው ያንቀላፋሉ። ምንም እንኳ አስጨናቂ ሁኔታ ባይገጥመኝም ካንድ ቀን በላይ ስታሰር ይህ የመጀመሪያዬ በመሆኑ ከእስር ቤቱ የምወጣበት እለት በእጅጉ ናፍቆኝና ርቆብኝ ነበር።

ሌሊት አይኖቼን ጣራው ላይ ተክዬ ለረጅም ሰአት ብዙ አሰብኩ። ሊያረካኝ ስለሚችለው ህይወት አጥብቄ መረመርኩ። ምንድነው የምፈልገው? አንዳችም የተጨበጠ ፍላጎት አጣሁ። ርካታ አጠገቤ ደርሶ እንደማያውቅ ይሰማኛል። ቀደም ሲል መፅሃፍቶቼ መታተም ሲጀምሩ በመጨረሻው የእርካታ ደረጃ ላይ የደረስኩ ይመስለኝ ነበር። ገበያ ላይ ከዋሉ በሁዋላ ደግሞ ባንድ አፍታ ውስጤ ባዶውን ይቀርና መንፈሴን የጭለማ ጉድጓድ ውስጥ ወድቆ አገኘዋለሁ። የተጫነኝን ከባድ ስሜት ለማባረር ምንጊዜም እንደማደርገው የምወዳቸውን ግጥሞች እያስታወስኩ መዘመር ጀመርኩ፣

ዋይ ትላለች ሶረኔ፣
ወገንዋ አልቆባት እንደ እኔ፣
* * *
ያ ዶሮዬ ጮኸ - መንጋቱን ነገረኝ፣
በዛሬው ቀን ላርደው - ቀጠሮ ነበረኝ፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

* * *

አይ ጅቦ ቢጮህ – ትላንትና ማታ፣
እንኮዬ ደማሚ – አለመጠን ፈርታ፣
እሳት ዳር ነበረ – የተቀመጠችው፣
ሳታስብ በድንገት – ፍሙን ጨበጠችው፤

የሻምበል አፈወርቅ ዮሃንስና የታገል ግጥሞች ነበሩ። የፑሽኪን፣ የፀጋዬ፣ የነቢይ መኮንን፣ የመንግስቱ ለማ እያልኩ የቻልኩትን ያህል ዘመርኩ፣

አንድ የነቢይ ግጥም በተለይ፣

በገዛ ግልምጫው፣
በገዛ ምላሱ፣
በገዛ ጅራፉ - ሰው በገረፈበት፣
አይ ሰው ባለተራው - ሲገረፍ አየሁት...

በመጨረሻም ደከመኝ።

አይኖቼን ከደንኳቸው። ምን ያህል እንደተኛሁም አላስታውስ፣ የክፍላችን በር ሲከፈት ነቃሁ። "ተነሱ!" የሚል የደቡብ አፍሪቃ ፖሊስ ድምፅም ተከተለ።

እነሆ! ስምንት ቀናት ነልስፕሪት ከተባለች ከተማ ከአፍሪቃውያን ስደተኞች ጋር ከታሰርን በሁዋላ በፖሊስ ፒካፕ ተጭነን ወደ ዋና ከተማይቱ ፕሪቶሪያ ተወሰድን።

በጉዞ ላይ ሳለን በከባድ ዝምታ ተውጬ ነበር። የጫነችን የፖሊስ መኪና ወደ ደቡብ አፍሪቃ ዋና ከተማ በመቃረብ ላይ ሳለች ማጂላን ሊያነቃቃኝ ሞከረ፣

"የተከፋህ ትመስላለህ"

"ደህና ነኝ" አልኩ።

"ፕሪቶሪያ እንደደረስን ይለቁናል"

"እሱ አላሳሰበኝም"

"ምንድነው ያሳሰበህ?"

"ምን ልልህ እንደምችል አላውቅም። ብቻ ስደት ከባህር እንደ ወጣ አሳ ማለት ይሆንብኛል...የሆነው ሆኖ ወደድኩም ጠላሁም እለምደዋለሁ..."

* * *

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ፕሪቶሪያ ኢሚግሬሽን እንደደረስን ለመማርና ለመስራት የሚያስችል ጊዜያዊ የፈቃድ ወረቀት ከሰጡን በሁዋላ፣ አንዱ የመስሪያ ቤቱ ባልደረባ እንዲህ ሲል አሰናበተን፣

"ይህ የኔልሰን ማንዴላ ሃገር ነው። ነፃ ናችሁ!"

ማጂላን በዚህ መንገድ ሲታሰርና ሲፈታ ይህ አምስተኛው መሆኑን እያጫወተኝ እስከ ባቡር ጣቢያው ሸኘሁት። እሱ በባቡር ወደ ስዋዚላንድ ሲመለስ እኔ ፕሪቶሪያ ቀረሁ።

በዚያች ሃገር የመኖር ጊዜያዊ ፈቃድ እንዳለኝ የሚገልፅ ወረቀት እጄ ላይ አለ። በርግጥም ነፃ ነኝ። ይህ ሃገሬ ባይሆንም አፍሪቃ ነው። በወይን ጠጅ ጃካራንዳ ዛፎችዋ ለምትታወቀው ፕሪቶሪያ አዲስ አልነበርኩም። የወያኔ ሹም በነበርኩበት ጊዜ አውቃታለሁ። ያኔ ግን ፕሪቶሪያን የተዘዋወርኩባት በኢትዮጵያ ኤምባሲ የክብር አጀብ ነበር። በርግጥ ያን ጊዜ ውስጣዊ ነፃነት አልነበረኝም። ዛሬ በእግር ጫካ ለጫካ ተጉዤ እንደገና መጣሁባት። ሳነፃፅረው አሁን የተሻለ ነፃነት ይሰማኝ ነበር...

ፕሪቶሪያን አውቃታለሁና አልተቸገርኩም። ተስያት ላይ ታክሲ ይዤ ወደማውቃቸው ሆቴሎች ሄድኩና አልጋ ያዝኩ። ሻንጣዬን ካስቀመጥኩ በሁዋላም በስም አውቀው ወደ ነበረው ትርሲት ምግብ ቤት አጠያይቄ ሄድኩ። ተፈጥሮ ቅን ገፅታን ያለስስት የቸራት ባለ ምግብ ቤት በኢትዮጵያዊ ወግና ባህል ተቀብላ አስተናገደቺኝ።

* * *

ይህ በሆነ በሶስተኛው ወር ፕሪቶሪያ ከሚገኘው UNISA ከተባለው ዩኒቨርሲቲ ታሪክና የፖለቲካ ሳይንስ ለማጥናት ተመዘገብኩ። በዚያው ሰሞንም በሶስት ኮምፕዩተሮች የተዋቀረች ሚጢጢ ኢንተርኔት ካፌ ከፈትኩ። እንደገና ተረጋግቼ ለመፃፍም በቃሁ። ከእለታት አንድ ቀን ምሽትም በብጫቂ ወረቀቶች የተሞላ ሻንጣዬን ጠረጴዛዬ ላይ ዘረገፍኩት። "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" የሚል ቃልም ወደ አእምሮዬ መጣ።

* * *

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ፕሪቶሪያ በከተምሁ በሁለተኛው አመት የደቡብ አፍሪቃ የአገር ውስጥ ጉዳይ መስሪያ ቤት ባልደረባ የሆነች፣ ሴት ጠርታኝ አንድ ወረቀት ላይ አስፈረመችኝ። ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ አገኘሁ ማለት ነው። ከጥቂት ሳምንታት በሁዋላ ደግሞ የመታወቂያ ወረቀትና ፓስፖርት ተሰጠኝ።

ደቡብ አፍሪቃን እወዳታለሁ።

ርግጥ ነው፣ ስራ አጥነቱ እየጨመረ በመሄዱ፣ ደቡብ አፍሪቃ ለስደተኞች የስጋት ምድር በመሆን ላይ ናት። በመሆኑም የተረጋጋሁና ደስተኛ አይደለሁም።

ሌሊት በህልም ምንጊዜም ቢሾፍቱ ነኝ። አንድም ቀን ደቡብ አፍሪቃ ላይ የተሰራ ህልም አይቼ አላውቅም። ሌሊቱን ቢሾፍቱ እያደርኩ ጠዋት ፕሪቶሪያ መመላለሱን ተያይዤዋለሁ...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 19 -
ብጫቂ ወረቀቶች

ሰዎች ሆይ እነሆ!
ገነት ውስጥ ለመግባት - የሚሰጥ ፈተና፣
ከዛሬ ጀምሮ - ተደምስሶአልና፣
እብደት እንጨምር - እንሁን እንዳሻን፣
ምንግዜም ክፍት ነው - ገሃነም እንደሆን፣

(ግጥም - ምገስ ሃብቱ)

በዚህ ምእራፍ በብጫቂ ወረቀቶች ላይ ያሰፈርኳቸውን ገጠመኞቼን ለቃቅሜ አወጋችሁዋለሁ። አንዳንዶቹ አስቂኝ ናቸውና "አብዮታዊ ቀልዶች" ብንላቸው ያስኬዳል። አብዮታዊ ቀልዶች ግን ላያስቁ ይችላሉ። የሚያናድድና የሚያስለቅስ ቀልድ መኖሩም አይዘንጋ። ጥቅማቸው የተነካባቸውና በምርጫ የተሸነፉ፤ ገጠርን ማእከል ባደረጉት አብዮታዊ ቀልዶች ባይስቁ አይገርመኝም። ይስቃሉ ብዬም አልጠብቅም። "አንስቅም" ብለው እልህ ውስጥ ከገቡ፤ ግማሽ መንገድ ድረስ ሄደን እናሳስቃቸዋለን። አሻፈረኝ የሚሉ ከሆነ ደግሞ መንገዱን ሳቅ ያድርግላቸው። በርግጥ መንገዱ ሳቅ በሳቅ ይሆናል ብለው ባይጠብቁ ጥሩ ነው። አራት ነጥብ!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

* * *

አንድ ጊዜ ዶክተር ገብረአብ ባርናባስ ስብሰባ ላይ እጁን አወጣና እንዲህ ሲል ጠየቀ፣

"ክልል የሚለው ቃል State ለሚለው ቃል ተኪ አይደለም። መለወጥ አለበት"

"ምን እንበለው ዶክተር ገብረአብ?" መለስ ዜናዊ ጠየቀው።

"በርግጥ ለጊዜው ተኪ ቃል አላዘጋጀሁም..."

"ተኪ ቃል ስታገኝ ይዘህልን ተመለስና እንወያይበታለን"

* * *

ሌላ ጊዜ ደግሞ መቀሌ ላይ ነፃነት አስፋው፣

"በደቡብ ክልል ከእበት ባዮጋዝ የማውጣት ስራ እየተሳካላቸው ነው። ሴቶችን ከማገዶ ለቀማ የሚያድን ጠቃሚ ፕሮጀክት ነው። ሄጄ ጎብኝቼዋለሁ። በትግራይ ክልልም ከእበት ባዮጋዝ የማውጣት ፕሮጀክት ቢነደፍ ጥሩ ይመስለኛል"

መለስ ዜናዊ ፈጥኖ ምላሽ ሰጣት፣

"አንድ አህያና ሁለት ፍየሎች ይዘን ስለ ባዮ ጋዝ ልናወራ አንችልም!"

* * *

የህወሃት 4ኛ ጉባኤ መቀሌ ላይ ሲካሄድ እኔም በተሳታፊነት ተመርጬ ጉባኤው ላይ ተገኝቼ ነበር። መለስ ይመራው በነበረው በዚህ ጉባኤ ወዲ መምሬ ተብሎ ስለ ሚታወቅ አንድ ታጋይ ሙስናን የተመለከተ መረጃ ቀርቦ ነበር። ይህ ታጋይ ጃንሜዳ አካባቢ የሚገኘው የመከላከያ የነዳጅ እደላ ጣቢያ ሃላፊ ነበር።

አዲተሮች ሲላኩበት ወዲ መምሬ ሰባት ሚሊዮን ብር ማጉደሉ ታወቀ። ከወዲ መምሬ መሳቢያ ውስጥ የተወላገደ ፊርማ ያረፈባቸው ጥቂት ደረሰኞች ተገኝተዋል።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ወዲ መምሬ የስንት ብር ነዳጅ እንደተቀበለና የስንት ብር ነዳጅ ለማን እንደሰጠ ለመመዝገብ አቅም አልነበረውም። ሰባት ሚሊዮን አጎደልክ ሲባልም በመደንገጥ ፈንታ ይስቅ ነበር። የሆነው ሆኖ በጉባኤው የተነሳውን የወዲ መምሬ ጉዳይ መለስ ትኩረት ሳይሰጠው ተዘለለ። ወዲ መምሬ አቅም እንደሌለው እየታወቀ ለምን ያን ያህል ሃላፊነት ተሰጠው? በወዲ መምሬ ስም ማን ምን ያህል ዘረፈ? የሚታወቅ ነገር አልነበረም። ወዲ መምሬ ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ እንዳላዋለው ግን እኔም አንዱ ምስክር ነኝ። ከጎደለው ሰባት ሚሊዮን፤ 200 ብር ወስጃለሁ።

ታሪኩ እንዲህ ነበር።

ወደ ላንጋኖ ለመዝናናት ለመሄድ ፕሮግራም ያዝኩና ስለ ነዳጅ ስናወራ፣

"ወዲ መምሬን ሄደህ ለምነው፣ ይተባበርሃል" ብለው መከሩኝ።

ቅዳሜ ጠዋት ጃንሜዳ ተገኘሁ። ወዲ መምሬ የጣቢያው ሃላፊ ቢሆንም "ትጉህ" በመሆኑ ራሱ ነበር ነዳጅ የሚሞላው። ላግባባውና ላሳምነው ቃላት ሳማርጥ፣

"ከየት ክፍል ነህ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ከፕሮፓጋንዳ"

ነዳጁን ግጥም አድርጎ እየሞላልኝ ያዋራኝ ያዘ፣

"አለምሰገድ ደህና ነው?"

"ደህና ነው"

"ኢብራሂም እናንተ ዘንድ ነው?"

"አይደለም፤ እኔ ሌላ ቦታ ነኝ"

"ኢብራሂም ዜና ሲያነብ ደስ ይለኛል"

በዚሁ ተሰነባበትን።

ከወዲ መምሬ ጋር ከዚህ ቀደም ተዋውቀን ባናውቅም፤ አለምሰገድና ኢብራሂምን ማወቁ ለሱ በቂ ደረሰኝ ነበር። በውጭ ምንዛሪ የሚገባውን ነዳጅ ወዲ መምሬ በዚህ መንገድ በትኖ፤ ሰባት ሚሊዮን ብር አጎደልክ ሲሉት እንደተኮረኮረ ሰው ይስቃል...

* * *

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ኀሀአዴግ የባህርዳር ከተማን በተቆጣጠረ ባምስተኛው ቀን ግድም ሶስት የባህርዳር ወጣቶች ወደ አንዱ የኢህዴን ታጋይ ቀረብ ብለው ሊያነጋግሩት እንደሚፈልጉ ይነግሩታል። ታጋዩ ባልሳሳት የህላዌ ዮሴፍ አጃቢ ነበር። እና ያን ቀን የህላዌን ላንድ ክሩዘር በመጠበቅ ላይ ነበር፣

"ምን ፈለጋችሁ?" ታጋዩ ኮስተር ብሎ ይጠይቃል።

"ጥያቄ ነበረን"

"የምን ጥያቄ?"

"የኤርትራ ጥያቄ አልገባንም። ኤርትራን ለማስገንጠል ነው የምትታገሉት ይባላል። ይሄ ወሬ እውነት ነው ወይስ ውሸት?"

ታጋዩ ያልተማረ ወጣት ገበሬ ቢሆንም እንደሚታወቀው የወቅቱ ታጋዮች በዋና ዋና የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ የሽምደዳ እውቀት ነበራቸው። ታጋዩ በእድሜ እኩዮቹ ለሆኑት ከተሜ ወጣቶች ማብራሪያ ለመስጠት መሬቱ ላይ ቁጢጥ አለ። ወጣቶቹም እሱን መሰሉ፣

"የኤርትራ ህዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን ዴሞክራሲያዊ መብቱ...."

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ወጣቶቹ ማብራሪያው በደንብ እንደገባቸው በመግለፅ አመስግነው ተሰናበቱት።

ታጋዩም ጥበቃውን ቀጠለ።

ህላዌ ዮሴፍ ስብሰባውን ጨርሶ ሲወጣ የገዛ አይኑን ማመን አልቻለም። በቀኝ በኩል የላንድ ክሩዘርዋ ሁለት ጎማዎች አልነበሩም። መኪናዋ ድንጋይ ተደግፋ ቆማለች። ወጣቱ ታጋይም በወዲያኛው የመኪናዋ ጎን ቆሞ በንቃት ይጠብቃል...

* * *

ቋሚ እመቤት አዜብ መስፍን (የመለስ ዜናዊ ባለቤት) ያጫወተችንን ደግሞ ላውጋችሁ።

በ1988 ለቤተመንግስት ጥበቃ የተመለመሉ የህወሃት ታጋዮች ቤተመንግስት እንደደረሱ፤ በጥበቃ ሃላፊው ሰፊ መመሪያና ገለፃዎች ተሰጣቸው። ከተገለፀላቸው ጥብቅ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መመሪያዎች አንዱ "ማንኛውም እንግዳ የመግቢያ ወረቀት ካልተላከለት መግባት አይችልም" የሚል ነበር።

በዚያን እለት ምሳ ሰአት ላይ ያልተጠበቀና ያልተገመተ ሁኔታ ተፈጠረ። አዜብ ሜጋ ማተሚያ ቤት ስራዋ ላይ ውላ ለምሳ ወደ ቤት ተመለሰች። ጥበቃዎቹ ስራቸውን የጀመሩበት እለት ነበር። ታጋዩ በእጁ ላይ ያሉትን የመግቢያ ወረቀቶች መመልከት ሲጀምር፣ አዜብ ሳቅ ብላ፣

"አታውቀኝም እንዴ?" ትለዋለች በትግርኛ።

"አውቅሻለሁ" ብሎ ወረቀቱን ማገለባጡን ሲቀጥል፣

"ካወቅሽኝ ክፈት በሩን፣ አታቁመኝ" ትለዋለች።

ታጋዩ ግን በሩን አልከፈተም።

"አዜብ የሚል ስም አልተሰጠኝም። የመግቢያ ወረቀት እስኪላክልሽ ትቆያለሽ" ይላታል።

ቀዳሚ እመቤት ቦግ አለች።

"ሰምተኸኛል!?" ተቆጣች "...የመለስ ሚስት ነኝ!"

"አውቃለሁ!" ሲል ቀዳሚ ዋርዲያውም ቆጣ ብሎ መለሰ "...መመሪያ ተሰጥቶናል። ማንም ቢሆን የመግቢያ ወረቀት ሳይላክለት አይገባም"

አዜብ መኪናዋን አዙራ ወደ ቢሮዋ ተመለሰች። ኮምፕዩተር የሆነ ጭንቅላት ያላቸው ሰዎች ጥቂት አይደሉም። መሪዎች ለጥበቃ ስራ እነሱን ይመርጣሉ።

* * *

በአንድ ወቅት ኢህአፓ የህወሃት የአመራር ዋሻ ላይ ጥቃት ሊከፍት የማቀዱ መረጃ ይደርስና ስብሃት ነጋ ለተረኛ ጥበቃው መመሪያ ይሰጣል፣

"በጥንቃቄ ጠብቅ! የኢህአፓ ኮማንዶዎች ሌሊት ጥቃት ሊፈፅሙ ይችላሉ የሚል መረጃ ደርሶናል። ስለዚህ 'ኮሽ' ካለ 'ማነህ!?' ማለት አለብህ...."

ስብሃት ነጋ መመሪያውን ሰጥቶ ሲያበቃ እዚያው እልፍ ብሎ ሽንቱን መሸናት ጀመረ፤ በዚያችው ቅፅበት ጥበቃው ድምፁን ከፍ አድርጎ ስብሃት ራሱ ላይ ጮኸበት፤

"ማነህ!?"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

* * *

በትግሉ ዘመን ትዳርና ፍቅር ክልክል ነበር። ሁዋላ ግን ተፈቀደ። በተፈቀደ ሰሞን ታዲያ ታጋዮቹ ልምዱ ስላልነበራቸው ግራ ተጋብተው ነበር። ስለዚህ በየክፍሉ ስለ ትዳርና ፍቅር የልምድ ልውውጥ ኮንፈረንሶች እንዲካሄዱ ስብሃት ነጋ መመሪያ ያስተላልፋል።

የህወሃት የባህል ቡድን ያካሄደውን የፍቅር የልምድ ልውውጥ ኮንፈረንስ የመራው ድምፃዊ እያሱ በርሄ ነበር። እያሱ ከተማ እንደመሆኑ ስለ ፍቅር በቂ ልምድ ነበረው። እድሉን ግን ለሌሎች ሰጠ። ገዳሙ የተባለው ድምፃዊ በወኔ እጁን አወጣ። ቀድመው ትዳር ከመሰረቱት አንዱ ነበር፣ እያሱ ፈቀደለት። ገዳሙ ልምዱን ማካፈል ጀመረ፣

"ሚስቴን በቅድሚያ የወደድኳት በአላማ ፅናትዋ ነው። ለጋብቻ ካሰብኳት በሁዋላ፣ በቁልፍ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ...ማለትም በመሬት ጥያቄ ላይ ያላትን አቋም መረመርኩ። መሬት አይሸጥም አይለወጥም በሚለው መርሃችን ላይ የማያወላውል አቋም እንዳላት ስገነዘብ ፍቅሬ ጨመረ። በመቀጠል በወላዋዮችና በአድህሮት ሃይላት ላይ ያላትን አቋም ስገነዘብ....በአከራካሪው የኤርትራ ጉዳይም ሆነ በማሌሊት..."

* * *

ጓፎይታ መፅሄትን ማተም የጀመርን ሰሞን አመንዝራነትን የተመለከተ አንድ መጣጥፍ ፃፍንና ካርቱን ስእል ማስገባት ፈለግን። በቅርብ ከማውቃቸው ታጋይ የኢህዴን ሰአሊዎች አንዱን የሴትኛ አዳሪ ካርቱን እንዲሰራልኝ ነገርኩት። ታጋዩ ሰአሊ በነጋታው ካርቱኑን ጨርሶ ይዞልኝ መጣ።

በመገረም ፀጥ ብዬ ቀረሁ።

ምናለፋችሁ!

ጠመንጃ አልያዘችም እንጂ ታጋይ ሴት ስሎ ነበር ያመጣልኝ።

* * *

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የኤርትራ ሪፈረንደም በተካሄደበት እለት ምሽት የኢትዮጵያ ማስታወቂያ ሚኒስቴር መምሪያ ሃላፊዎች ስብሰባ ላይ ነበርን። አማረ አረጋዊ ወደ ስብሰባው ዘግይቶ መጣ። የስብሰባ ሰአት በማክበር ረገድ የተመሰገነ ነበርና፣ "ምን ገጥሞት ይሆን?" በሚል ይነግረን ዘንድ ጠበቅነው።

"አደገኛ ዜና ሊተላለፍ ሲል ለጥቂት ያዝኩት!" አለን።

"ምንድነው?" አይናችን ፈጥጦ ጠየቅን።

"የመለስ እናት ሪፈረንደም መምረጣቸውን፣ 'ነፃነት መርጨያለሁ' ሲሉ በድምፅ የሚናገሩበት ዜና በቴሌቪዥንና በሬድዮ ሊተላለፍ ሲል ደርሼበት ሁለቱንም አስቆምኩት"

ለሰከንዶች ፀጥ ብለን ቀረን።

"ጠላቶቻችን መሃላችን ተሰግስገው እያጠቁን" መሆኑን ተነጋግረን ስናበቃ ስብሰባችን ቀጠለ። ማታ ወደ ቤቴ ስሄድ መኪናዬ ውስጥ ሬድዮ ስከፍት በአራት ሰአቱ የሬድዮ ዜና የመለስ ዜናዊ እናት የኤርትራ ሪፈረንደም ላይ መሳተፋቸውንና ነፃነት መምረጣቸውን የሚገልፅ ዜና እየተነበበ ነበር። ማመን እያቃተኝ መኪናዬን አቁሜ ስልክ መደማገኝበት ሱቅ በረርኩ። እና ደወልኩ። የኢትዮጵያ ሬድዮ የፕሮግራሞች ሃላፊ ሱሌይማን ደደፎን አገኘሁት። በችኮላ ስለ ዜናው ጠየቅሁት፣

"ይተላለፍ ስለተባለ ለቀነዋል" አለኝ።

"ማነው ይተላለፍ ያለው?"

"ከላይ የመጣ ትእዛዝ ነው"

ስልኩን ዘግቼ መንገዴን ቀጠልሁ። ለምን ነበር ግን የተደናገጥኩት? አማረ አረጋዊን በነጋታው ለምን ደንግጠ እንዳስደነገጠን ልጠይቀው አስቤ ነበር። ሆኖም ሳልጠይቀው ረሳሁት...

* * *

በማእከላዊ ኮሚቴ ምርጫ ወቅት መለስ ዜናዊ ሊያስመርጥ የፈለገውን ያስመርጣል። እንዳይመረጥ የፈለገውንም በተመሳሳይ በረቀቀ ዘዴ ያስወግዳል። ተስፋማርያምና ጀማይካ ላይ ይህንኑ ሲፈፅም እያዳመጥሁና እየሳቅሁ ንግግሩን በብጫቂ ወረቀት ላይ እመዘግበው ነበር።

ተስፋማርያም ለማእከላዊ ኮሚቴነት ተጠቆመ፤

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሰው ሲጠቆም ታዲያ ተቃውሞና ድጋፍ ይጠየቃል። መለስ እጁን አወጣ፣

"ተስፋማርያም ሙስና ውስጥ ያልገባ ጠንካራ ታጋይ ነው። ህወሃት ውስጥ ካሉት ታጋዮች እንደ ተስፋማርያም ንፁህ ታጋይ የለም። አንድ ሳንቲም እንኳ ከድርጅታችን አላግባብ አባክኖ አያውቅም። ወደ አመራር ብቃቱ ስንመጣ ግን ድክመቶች አሉበት..."

ተስፋማርያም ሳይመረጥ ቀረ።

ጀማይካ ተጠቆመ።

ስዬ አብርሃና ስዩም መስፍን በየተራ እጃቸውን እያወጡ የጀማይካን ድክመት እየዘረዘሩ እንዳይመረጥ ቀሰቀሱ። መለስ ሶስተኛ ሆኖ እጁን አወጣ፣

"ጀማይካ እንደምታወቁት እኛ ትግሉን ሳንጀምር ትግል የጀመረ መስራች አባል ነው። ዛሬ እዚህ ያለነው ሁሉ በጀማይካ ስልጠና የተሰጠን ነን!....."

ጀማይካ ተመረጠ።

ጅማ ከተማ በተካሄደው የኢህአዴግ ጉባኤ ላይ ደግሞ ለኢህአዴግ ምክር ቤት አባል የሚሆኑ፤ ከኦህዴድ አመራር አባላት ጥቆማ ሲደረግ ነጋሶ፣ ኩማና ሃሰን አሊን የሚጠቁማቸው ጠፍቶ ነበር። ሁላችንም ደንግጠን ነበር። "ዋናዋናዎቹ ጉድ ሊሆኑ ነው" እያልን መጨረሻውን ለማየት ስንጠብቅ መለስ እንደተለመደው አክሮባቱን ሰራ!

"...እንዴት ነው ነገሩ!? ዋናዋናዎቹ ተረሱ'ኮ። እስኪ ጥቆማ...እሺ... አንተ..." አለና እድሉን ለሃሰን አሊ ሰጠ። ሃሰን አሊ ኩማን ጠቆመ " ሌላ...ቀጥል...ማነህ? አንተ..." እድሉን ለኩማ ሰጠ። ኩማ ነጋሶን ጠቆመ።

ያቺ የጉባኤ አዳራሽ ተንፈስ አለች። ከዚያ በሁዋላ ያለው ድምፅ የመቁጠር ሂደት ችግር አልነበረውም። ኢህአዴግ ልምድ ስላለው ሊያስተካክለው ይችላል።

(...የኢህአዴግ የምርጫ ውጤትን የማምታታት ችሎታ በቅንጅት ላይ እንደታየው በአገር አቀፍ ምርጫዎች ላይ ብቻ የሚፈፀም አይደለም። በውስጣዊ ምርጫው የተለማመደውን ነው በአደባባይም የሚደግመው። ኦህዴዶች በአገራዊ ምርጫው ዋዜማ ማምሻውን ጫት እየቃሙ ካርድ ሲሞሉ የሚያሳይ ቪዲዮ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለምርጫ ቦርድ ሊቀመንበር ለአሰፋ ብሩ ተልኮለት አፍኖአት ፀጥ ማለቱን አውቃለሁ። ቀረፃውን በምስጢር ያካሄዱት ሃረሪዎችም ከስልጣናቸው ተባረዋል።)

* * *

ዝውቂን ተዋናይ ደበበ እሸቱን የማያውቅ አለ? አይኖርም ብዬ እገምታለሁ። የሆነው ሆኖ ደበበ እሸቱ ቴአትር መስራቱን በመተው በምርጫ 97 ቅንጅት የተባለውን ፓርቲ ወክሎ ተወዳድሮ ነበር፣

ጋዜጠኛ፡

"ምርጫ 97 ላይ ኢህአዴግ ድራማ ሰርቶአል ይላል ህዝቡ። ይህን አባባል እንዴት ያዩታል?"

መለስ ዜናዊ፡

"የተሰራ ድራማ የለም። ምናልባት በምርጫው ደበበ እሸቱ ስለተሳተፈ ድራማ የመሰላቸው ካሉ ተሳስተዋል" *(ይህች ግን የድረገፆች ፈጠራ ናት)*

* * *

በአንድ ወቅት አለምሰገድ በአያቱ የኦሮሞ ዘር እንዳለበት ወሬ ሰምቼ አምኜ ነበር። መረጃው ስህተት መሆኑን ግን ቆይቼ ተረዳሁ። ቦቴ ጫላ የተባለ ወንድም ነው የነበረው። ክንፈና አለምሰገድ ቦቴ ጫላን ፍለጋ አምቦ ገጠር ድረስ ተጉዘው ተሳክቶላቸዋል።

የአለምሰገድ አባት ግራዝማች ገብረአምላክ በዘመነ ጃንሆይ በአምቦ አካባቢ የአንድ ወረዳ አስተዳዳሪ በነበሩበት ወቅት ከአንዲት የአካባቢው ኦሮሞ ወንድ ልጅ ይወልዳሉ። ወደ አድዋ ከተመለሱ በሁዋላም በጎን ስለተወለደው ልጅ ለልጆቻቸው አጫውተዋቸው ሲያበቁ፣

"በተመቻችሁ ጊዜ ወንድማችሁን ፈልጉና አግኙት" ሲሉ አደራ ያስረክቡአቸዋል።

አለምሰገድ ከጓደኞቹ ጋር ተጋግዞ ደርግን ከስልጣኑ ካባረረ በሁዋላ ስለ ወንድሙ አስታወሰ። እና በፍለጋ ያግዘው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ዘንድ ክንፈን ያማክረዋል። ክንፈም በደህንነቱ መስሪያ ቤት መዋቅር በኩል ማፈላለጉን ይጀምርና በጥቂት ወራት ውስጥ የቦቴ ጫላ አድራሻ ተገኘ። ቦቴ ጫላ ግን ስለ ወንድሞቹና እህቶቹ የሚያውቀው ነገር አልነበረም። አባቱ አንድ የትግራይ ባላባት ስለ መሆናቸውም መረጃ አልነበረውም።

የደራሲ ብእሬን ተጠቅሜ ልተርክላችሁ...

...ከእለታት አንድ ቀን እኩለ ቀን ላይ ሁለት ውሃ ያልነካቸው ኒሳን ፓትሮል መኪኖች ከጭቃና ከሳር ከተሰራች አንዲት ጎጆ ደጃፍ ላይ ተከሰቱ።

ቦቴ ጫላ ደነገጠ!

እንጨት ለመስበር ወደ ዱር ሊወርድ መጥረቢያውን በእጁ፣ የቃጫ ገመዱን በትከሻው እንደያዘ ነው እነዚያ ያልተጠበቁ መኪኖች ከደጁ የተከሰቱት። ስለ ክስተቱ ለማሰብ ፋታ እንኳ ሳያገኝ የመኪኖቹ በሮች ተከፋፍተው በመልካቸው ቁርጥ እሱን የሚመስሉ ሴቶችና ወንዶች ሲወርዱ፣ እህቶቹና ወንድሞቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ አልገመተም። የአለምሰገድ እህት አባትዋን የሚመስል ገበሬ መጥረቢያ ይዞ ጎጆው ደጃፍ ላይ ቆሞ ስትመለከት እንባዋን መቆጣጠር አቅቶአት እዬዬዋን አቀለጠችው...

የጊዜ እጥረት ባይኖርብኝ ኖሮ "ቦቴ ጫላ" በሚል ርእስ አንድ ታሪክ - ቀመስ ልቦለድ እፅፍ ነበር። ከፃፍኩት ግን በዚህ ልቦለድ አፅመ - ታሪክ ውስጥ አንድ አቢይ ግጭት ይኖራል...

በምናብ አብረን ጥቂት እንጓዝ...

....በዚያን እለት ቦቴ ጫላና አለምሰገድ ከኮረብታዎቹ አናት ላይ ተቀመጡ፣

"ምን ይቸግራችሁዋል፣ ቦቴ ጫላ?"

"ችግር የለብንም አለምሰገድ። እንደምታየው መሬቱ ሃብታም ነው።"

ዘግየት አለና ግን አከለበት፣

"...አህዴድ የተባሉ የወያኔ ሰዎች ግን አስቸግረውናል። ወንድምህ አነግ ሆነ ብለው አስረው ደበደቡኝ። ይሄ የኔ ጠፋት ነው እንዴ አለምሰገድ? ወንድሜን አነግ ከመሆን እንዴት እንደማስቀረው ዘዴውን አላውቅም"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"እነግ አሁንም እዚህ አካባቢ ይንቀሳቀሳል?"

ቦቴ ጫላ ፈገግ አለ፣

"አገሩ ሁሉ እነግ ነው፣ አለምሰገድ! ህዝቡ አህዴዶችን የትግሬ አሽከር እያለ ነው የሚጠራቸው!"

ይሁን እንጂ አለምሰገድ በወቅቱ በቦቴ ጫላ ጉብኝት ሳይባንን ቀረ። ህወሃት የብሄር ድርጅቶችን በአምሳሉ እየፈለፈለ መጠቀሚያ እንደሚያደርጋቸው ያመነው ከአንጃው መወገድ በሁዋላ ነበር።

* * *

አቶ ፍሬው ለምለም ደግ አዛውንት ነበሩ። የብሄራዊ ሎተሪ ተጠባባቂ ስራ አስኪያጅ ሆነው የተመደቡ ሰሞን እንደ አንበጣ ወረርናቸው። የመንግስትና የኢህአዴግ ሚዲያዎች ሁሉ ማስታወቂያ ይሰጡአቸው ዘንድ የሽያጭ ወኪሎቻቸውን ላኩባቸው። ተጠባባቂ ስራ አስኪያጆች ሹመቱ እስኪፀድቅላቸው ብዙ ጊዜ ፈሪ ይሆናሉ። አቶ ፍሬው ለምለም አዲሱን ቢሮ የተረከቡ ሰሞን ከባድ ፈተናዎች ገጥሞአቸው ነበር። ከቴሌቭዥን፣ ከሬዲዮ፣ ከአዲስዘመን ከበሪሳ ጋዜጣ ለመጡት ሁሉ ይሉኝታ ይዞአቸው ቼክ ፈረሙ። በመቀጠል "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ጋዜጣ መጣ። እምቢ ማለት አልቻሉም። የሾማቸው ኢህአዴግ ነውና ፈረሙ። ከ"ማህቶት" ጋዜጣ ለመጣው ግን ገንዘብ ላለመስጠት አንገራግረው ነበር። "በአማራው ክልል ዋና የሎተሪ ደምበኞች ዘንድ እንደርሳለን" እያለ ሲለፈልፍባቸው ለመገላገል ብለው ቼክ ፈረሙለት። በነጋታው የኦሮሚያ ጋዜጣ ወኪል መጣ። "ለአማራው ፈርመህ ለኦሮሞ ያልፈረምከው ነፍጠኛ ስለሆንክ ነው" እንዳይባሉ በመስጋት ፈረሙ። ከደቡብና ከትግራይ መጡባቸው። ከነገር ለመሸሽና ላለመነካካት ሲሉ ፈረሙ። በመጨረሻ እኛ ሄድን - ከእፎይታ መፅሄት። አርብ ጠዋት የሽያጭ ሰራተኛውን አስከትዬ ከአቶ ፍሬው ለምለም ቢሮ ስገባ ግስላ ሆነው ጠበቁኝ፣

"ምንፈለጋችሁ እናንተ ደሞ!?" ሲሉ ጮኹ፣"...አታፍሩም እንዴ!? ምንጣፉንም ጠቅልሉና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ውሰዱታ! ጠረጴዛውንም ጫኑ! እሱ ነው የቀራችሁ! ነውር አይደለም እንዴ?"

ካረጋጋናቸው በሁዋላ ሳምንቱን ሙሉ የደረሰባቸውን በምሬት አጫውተውን ሲያበቁ እንዲህ አሉን፣

"እስኪ ይሁን እንግዲህ...ዳግመኛ አትምጡብኝ እንጂ ዛሬ መቸም ባዶ እጃችሁን አልመልሳችሁም..."

* * *

"የመለስ ዜናዊ የእስራት ዘመን" በሚል ርእስ አንድ መጣጥፍ ልፅፍ አስቤ ነበር። መረጃዎች ሲያጥሩኝ "ብጫቂ" ላይ ልወሽቃት ተገደድኩ። የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ይካሄድ በነበረበት ወቅት መለስ የሚሰጣቸው ቃለመጠይቆች ገብሩ አስራት ዘንድ ወደ መቀሌ እየተላኩ ይታዩ ነበር። ይህም ከመለስ እውቅና ውጭ ይካሄድ እንደነበር እኔም ሆንኩ የ"አሰር" መፅሄት ዋና አዘጋጅ አታክልቲ እምባዬ ምስክሮች ነን። ይህ ድርጊት መቼም ከክንፈ ጆሮ ያመልጣል የሚባል አይሆንም። መለስ ግን አውቆም ይሁን ሳያውቅ የታሰረ መስሎ ጊዜ ይጠብቅ እንደነበር ይታመናል። በመጨረሻም የተፈፀመውን ፈፀመና የጨዋታው ማብቂያ ሆነ። ከእለታት አንድ ቀን ምሽት መለስ ዜናዊ በቴሌቭዥን ቀረበና የድራማውን ማብቂያ አወጀልን፣

"ለምሳ ሲያስቡን ለቁርስ አደረግናቸው! በታንክ ሳይሆን፣ በብእር!"

* * *

ፓልቶክ እየሰማሁ ነበር።

ብቻዬን በሳቅ ፈነዳሁ። ብቻውን የሚስቅ እብድ ነው ይባላል። ምን ይደረግ? አንዳንዱ ተናጋሪ ምላሱ ጨቤ ነው። ሃጎስ 24 የተባለ የማታ ፓልቶክ ደምበኛ በጎንደር አማርኛ እንዲህ ሲል ሰማሁት፣

"እዚህ አሜሪካ እየኖራችሁ እንግሊዝኛ መናገር የማትችሉ ብዙ ናችሁ። IS ሲባል "እዚ ነው" ትላላችሁ። WAS ሲባል ደግሞ "ወደዚያ ነው" የተባለ ይመስላችሁዋል። is እና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

was እንኳ ሳታውቁ ፖለቲካ ታወራላችሁ። ኢ-ሜይል ምን እንደሆነ የማታውቁም አላችሁ። ወያኔ ወድቆ ስልጣን ስትይዙ በጡሩንባ ልትነጋገሩ ነው? ስለዚህ ተማሩ። ኢ-ሜይል መላክ መማር አለባችሁ። አትፍሩ! እንግሊዝኛም ቢሆን ቀላል ነው። ሞክሩት። የመለስ ሚስት እንኳ እንግሊዝኛ በሞከረችበት ዘመን እናንተ...”

* * *

በ1985 ማብቂያ ግድም በታጠቅ ጦር ሰፈር ይካሄድ በነበረው የፖለቲካ ውይይት ላይ ተሳትፌ ነበር። በረከት ነበር የኛ ቡድን የውይይት መሪ። አብዛኞቹ የውይይቱ ተሳታፊዎች ከጎንደርና ከጎጃም የመጡ ነበሩ። በጦፈ ውይይት መሃል በረከት እንዲህ ሲል ጠየቀ፣

“መአህድ በምርጫ ቢያሸንፍ ህዝባዊ እንለዋለን ወይስ አንለውም?”

እጆች እየተቀሰሩ ምላሽ ይሰጡ ጀመር፣

“በህዝብ ከተመረጠማ ህዝባዊ ነው!”

“ህዝባዊ እንለዋለን! ህዝብ ከመረጠው ሌላ ምን ሊባል ይችላል?”

በረከት በፀጥታ ሲያዳምጥ ከቆየ በሁዋላ፣ ልክ እንደ አራተኛ ክፍል ተማሪዎች ይቆጣን ጀመር። ከውይይቱ መንፈስ ባፈነገጠ ሁኔታ አስተያየት መቀበሉን በማቋረጥ፣

“ይህን የምትደግፉ እጃችሁን አውጡ!” አለ።

ሁላችንም እጃችንን አወጣን።

በረከት በጣም አዘነብን። ብዙ ወቀሰን። እንዲህ ሲልም ፖለቲካ ያስተምረን ያዘ፣

“መአህድ በምርጫ ተወዳድሮ ቢያሸንፍም ቢሸነፍም ፀረ ህዝብነቱ አይለወጥም። ህዝቦች ተታለው ወይም ተሳስተው ፀረ ህዝብ ድርጅት ሊመርጡ ይችላሉ”

(ይህቺ የበረከት አባባል በምርጫ 97 ተግባራዊ ስትሆን አየሁዋት። የአዲሳባ ህዝብ ተታልሎ ወይም ተሳስቶ ፀረ ህዝቡን ቅንጅት መረጠ። የቡግና ወረዳ ህዝብም በረከትን መምረጥ ሲገባው፣ በስህተት ሌላ ግለሰብ መረጠ። በረከትም “የሚወደንና የምንወደው ህዝባችን አይናችን እያየ ሲሳሳት ዝም አንልም” በሚል ምርጫው እንዲደገም ተደርጎ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ህዝቡ ስህተቱን አረመ።)

በታጠቅ ጦር ሰፈር ውይይት ላይ ታዲያ በረከት አምርሮ ከወቀሰን በሁዋላ፣

"መአህድ በምርጫ ቢሸነፍም ቢያሸንፍም ምንጊዜም ፀረ ህዝብ ነው የምትሉ እጃችሁን አውጡ" ብሎን ነበር።

በሽሙጥ እየተሳሳቅን ሁላችንም እጆቻችንን ቀሰርን። በዚያ ውይይት ላይ 150 ካድሬዎች የተካፈልን ሲሆን፣ ሁሉም አማራዎች ነበሩ - ከእኔና ከበረከት በቀር።

በዚያን እለት ታዋቂው የሩስያ ደራሲ ኢቫን ቱርጌኔቭ ለጓደኞቹ ከፃፋቸው ደብዳቤዎች መካከል ጥቂት መስመሮችን አስታወስኩ፣

"እባካችሁ! በህዝቡ ላይ መቀለድ ይቻላል ብላችሁ አታስቡ። ...እናንተ እንደምትሉት አንድ አገር ሙሉ ውሸት? ማታለል? ...ሁዋላም ጥሩ እንደሰሩ ለማሳየት መሞከር። ታውቃላችሁ!? ህዝቡን ቅንጣት ታህል ማታለል አይቻልም። ህዝብ ከእኛ ከእያንዳንዳችን የበለጠ ብልህ ነው። እንደዚሁም ለህዝቡ ሁሉንም ነገር ራሳችሁን ረስታችሁ፣ ደማችሁንና ላባችሁን አፍሳችሁ ለሰራችሁት ስራ፣ ህዝቡ ስራችሁ ከገባውና ድካማችሁንም ዋጋ ከሰጠው፣ እናንተንም ማስተዋል ከጀመረ የበለጠ ለህዝቡ ባለውለታ መሆን አለባችሁ። ይህም ግልፅ ነው። የበለጠ ልናገር። ይህ ሃቅ ነው። ህዝቡ እንጂ የሚያስፈልጋችሁ፣ ለህዝቡ እናንተ አታስፈልጉትም።"

* * *

የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ይካሄድ በነበረበት ወቅት አንድ ቀን ወደ ስብሃት ነጋ ቢሮ ለስራ ሄጄ ነበር። ቢሮው ቁጭ ባልኩባት ደቂቃ ስብሃት ረጅም ስልክ ይዞ ነበርና አይኖቼ ሲንከራተቱ ጠረጴዛው ላይ በአፍጢሙ የተደፋ መፅሃፍ አየሁ። "አጥፍቶ መጥፋት" የተባለው የዮሃንስ ሙሉጌታ መፅሃፍ ነበር። እንደዋዛ ብድግ አደረግሁት። ገፅ 202 ላይ ነበር የታጠፈው። የተወሰኑ አረፍተነገሮች ላይ በእስክርቢቶ ተሰምሮበታል። እንዲህ ይነበባሉ፣

"...በአንድ ወቅት (መንግስቱ ሃይለማርያ) ማስታወቂያ ሚኒስትርን ሲነበኝ ከምንም የበለጠ ትኩረት የሰጠው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለጃሚንግ ስራ ነበር። እንደ ፕሬዚዳንቱ ፍላጎት ቢሆን የአሜሪካ ሬድዮ የአማርኛ ፕሮግራም መታፈን ነበረበት። ቮይስ ኦፍ አሜሪካ ከ80 ትራንስሚተሮች በላይ ስላሉት ያንን ማፈን እንደማይቻል ተገለጠለት። እንደ እውነቱ ግን የሻእቢያንና የህወሃትን ራድዮ ጣቢያዎች እንኳ ለማፈን የማስታወቂያ ሚኒስቴር አቅም አልነበረውም። የሚገርመው ግን ባንድ በኩል የራድዮ ጣቢያዎች ጃም ይደረጉ እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ ጃም በተደረጉት ጣቢያዎች የቀረበው ዜናና ፕሮግራም እየተቀረፀ ጠዋት ጠዋት ይቅረብልን ይባል የነበረው ቀጭን ትእዛዝ ነው...” ይላል።

መፅሃፉን ወደ ነበረበት መለስኩት።

ዛሬ ላይ ቆሜ ስገመግመው በጃሚንግ ስራ ኢህአዴግ ውጤት ተኮር የሆነ እድገት አሳይቶአል። የሻእቢያን ብቻ ሳይሆን ቮይስ ኦፍ አሜሪካንና የጀርመንን የአማርኛ ፕሮግራሞች ጭምር ጃም ማድረግ እየቻለ ይመስላል።

* * *

ከባዱላ ገመዳ የ700 ሺህ ብር መኖሪያ ቤት ገንብቶ በዶላር ካከራየ በሁዋላ ጉዳዩ በአህዴድ ግምገማ ላይ ተነስቶ ነበር፣

“ቪላውን ከየት አምጥተህ ገነባህ?” ተብሎ ተጠየቀ።

“ጓደኞቼ አበደሩኝና ሰራሁት። አሁን አከራይቼዋለሁ። ከኪራዩ በሚገኘው ገቢ ደግሞ ብድሬን እየከፈልኩ ነው።”

ጉዳዩ ለውሳኔ የሚያስቸግር ነው ተባለና ከአህዴድ ወደ ኢህአዴግ መድረክ ተላለፈ። መለስ ዝርዝሩ ከቀረበለት በሁዋላ የሰጠው ምላሽ አጭር ነበር፣

“አባዱላን የሚተካ ታማኝ ሰው የለንም!”

* * *

የአዲስ አበባ ህዝብ ወደ መስቀል አደባባይ እየተመመ ነው። ህዝቡ ይጨፍራል...ከበሮ ይደልቃል... ሆታው ማቋረጫ የለውም።

ሴቶች ነጭ ለብሰዋል። ወንዶችም ነጭ በነጭ ሆነዋል።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የባንዲሮች ቀለማት ያጥበረብራል። ቢጫና ቀይ ይበረክታል። የህዋሃት ባንዲራ - የኢህዴን - የኦህዴድ - የኢህአዴግ - የማሌሊት - የኢማሌሃ - ባንዲራዎች። ቀይና ቢጫ። ቀዩ ደም ነው። ቢጫው ተስፋ። ትርጉሙ "በደማችን ባለተስፋ ሆነናል" ማለት ነው።

ይህ ሁሉ እውነት ነበር።

የኢትዮጵያ ህዝብ ወደ መስቀል አደባባይ እየጎረፉ ነበር። በአይኔ አይቻለሁ። ከቀበና - ከቦሌ - ከኮተቤ - ከጉርድሾላ...

ስራዬን መቀጠል ነበረብኝ። ጋዜጠኛ ነኝ! ወደ ጩኸት ባህሩ ገባሁ። አንድ ፈረሰኛ አይኔን ሳቡት። ፈረሳቸው ተንቆጥቁጧል። እርሳቸውም ፈረሳቸውን መስለዋል። እኒህ ሽማግሌ ያቅራራሉ፣ ጃሎታውን ያስነኩታል! ጡሩንባም ይነፋሉ! ደስታቸው ገፅታቸው ላይ ይነበባል። በሃይለስላሴና በደርግ ዘመናት ክፉ በደል የደረሰባቸው ይሆኑ? ወይስ መሬትና ቤት የተወረሰባቸው?

ለማንኛውም የግንቦት ሃያ አንደኛ አመት በአል የፈጠረባቸውን የደስታ ስሜት መሸከም አለመቻላቸው ግልፅ ነበር። ቀረብ ብዬ ለቃለ - ምልልስ ጋበዝኳቸው፣

"አባት በቅድሚያ ሙሉ ስሞትን ቢገልፁልኝ?"

"ባህሩ እባላለሁ። ባህሩ ከበደ!"

ሃይለኛ ድምፅ!

"አቶ ባህሩ! በዛሬው እለት እንዲህ አምረውና ተውበው ፈረስዎንም አንቆጥቁጠው ወደ መስቀል አደባባይ የመጡበትን ምክንያት ቢያብራሩልኝ?

ሽማግሌው ሳያመነቱ ነበር ለምላሽ የፈጠኑት፣

"እኔ!" ሲሉ ጀመሩ "...ከአፄ ሃይሌስላሴ ስርአት ጀምሮ፤ በደርግም ጭምር፣ አሁንም ወያኔ ከመጣ በሁዋላ የድጋፍ ሰልፍ የሚባል አምልጠኝ አያውቅም። ሰልፍ አለ ከተባለ የክት ልብሴን ለብሼ፤ ፈረሴን ጭኜ ብቅ ነው!"

* * *

ደርባን የተባለች ከተማ ላይ የተዋወቅሁት አንድ የሻእቢያ ጋዜጠኛ ያጫወተኝን ላውጋችሁ!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

...ግንቦት 24 የተባለውን የኤርትራ የነፃነት በአል ለማክበር የአስመራ ህዝብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶአል። ከጎዳይፍ - ከሰታንታኡቶ – ከፎሮቢያ – ከእምባጋሊያኖ– ከገዛታኒካ – ከሃዝሃዝ – ከቲራቮሎ - ከካምፖቮሎ - ከፀፀራት - ኪፓራዲዞ - ከቁሸት – ከአባሻውል - ከገዛባንዳ.... ህዝቡ ከበሮውን እየደለቀ...ፈንዲሻውን እየበተነ...ወደ ጎዳና ሃርነት...ወደ ባህቲ መስከረም...

ጋዜጠኛው አንዲት ሴት ወይዘሮ ካይኑ ገቡለት። ከበሮ ይዘዋል። ዘፈን አውራጅ ናቸው። ሹሩባቸው ከማማሩ የተነሳ አንበሳ መስለዋል...ነጭ በነጭ ለብሰው...በደስታ አብደዋል... ጋዜጠኛው እኒህን ወይዘሮ ለማነጋገር ያጀቡዋቸውን ሰንጥቆ መሃል ገባ፣

"እናቴ ... አንድ ጊዜ ያድምጡኝ! አንድ ጊዜ..."

ወይዘሮዋ ከበሮ መደለቃቸውን ገቱ፣

"እንኳን ለኤርትራ የነፃነት በአል አደረስዎት?"

"እንኳን አብሮ አደረሰን! ደስ ብሎኛል። ኤሪትሪያ ሃገራችን ከኢትዮጵያ አገዛዝ ነፃ በመውጣቷ ደስ ብሎኛል! የዛሬዋ እለት የልደት በአላችን ናት!"

"መልካም። ስምዎትን ቢገልፁልን?"

"ወይዘሮ ኢትዮጵያ እባላለሁ!"

* * *

የቡርቃ ዝምታ ታትሞ እንደተሰራጨ ጠላቶችንም ወዳጆችንም በብዛት አፈራሁ። የመጀመሪያውን አስተያየት የሰጡኝ ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚብሄር ነበሩ። ማኪያቶ ጋብዘውኝ እንዲህ አሉኝ፣

"አሪፍ መፅሃፍ ፅፈሃል። አሪፍ መፅሃፍ ፅፌያለሁ ብለህ ካበጥክ ግን አለቀልህ። ገና አልፃፍኩም ብለህ አስብና ከዜሮ ጀምር። ሰዎች ሲያደንቁህ አትኩራራ! ሲያጥላሉህ ደግሞ አትደንግጥ። የሚረግሙህም የሚያደንቁህም ሰዎች በብዛት ይፈጠራሉ። መልስ እንዳትሰጥ። ይህን እርሳውና ሌላ መፅሃፍ ጀምር። ይህቺ ደግሞ የፀጋዬ ገብረመድህን ዘዴ ናት..."

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በዚያው ሰሞን ጦቢያ ጋዜጣ እንዲህ ሲል ፃፈ፣

"የቡርቃ ዝምታ ሻእቢያና ወያኔ በግለሰቦች ስም የፃፉት መፅሃፍ ነው። አላማውም አማራውንና ኦሮሞውን በማናከስ ይህቺን ሃገር ማፈራረስ ነው። ደራሲው ከነመፅሃፉ ተቃጥሎ ከምድራችን የሚወገድበት እለት ሩቅ አይሆንም።"

ሴኮ የተባለ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጠኛ ደብዳቤ ፃፈልኝ። ባጭሩ ሲጨመቅ እንዲህ ይላል፣

"የፃፍከውን መፅሃፍ አነበብኩት። ድራዳዋ የሚገኝ አባላችን (ኮሎኔል) መፅሃፍህን ካነበበ በሁዋላ 'ጠላታችንን በጉያችሁ አቅፋችሁ ተቀምጣችሁዋል' ካለኝ በሁዋላ ነበር ያነበብኩት። የኢህአዴግ ጠላት መሆንህን ባደባባይ አውጀሃል! እንኳን ደስ ያለህ!" የሚል ሽሙጥ ነበር።

በዚያው ሰሞን ደግሞ ስብሃት ነጋ ልጁን ይዞ ወደ ግዮን ሆቴል መዋኛ ቦታ ሲገባ ደጃፉ ላይ ተገናኘን፣

"አነበብኩት።" አለኝ፣ ከሰላምታ በፊት፣ "... በጣም ጥሩ መፅሃፍ ፅፈሃል። ቢሮ ብቅ በልና እናወራለን"

ከሀላቄ ዮሴፍ ጋር በስልክ ስናወራ፣

"ወድጄዋለሁ። ከጀመርኩት በሁዋላ ማቆም አቃተኝ። በረከትም አንብቦታል። አስተያየቱን ጠየቅሁትና 'ፍራንክ ነው' አለኝ። በረከትን አግኘው። በደንብ አስተያየት ይሰጥሃል..."

በረከትን ሳገኘው ግን ተገላቢጦሹን ነገረኝ፣

"ሻእቢያ አራት ታንክ ይዞ ስለገባ ያን ሁሉ ገድል ጫንክለት። የኢህዴንን አስተዋፆ ግን ሙሉ በሙሉ ዘለልከው።"

በረከት ደስ እንዳይለኝ ብሎ መፅሃፉን ማድነቁን ሊነግረኝ እንዳልፈለገ ገምቼና ታዝቤ ዝም አልኩ።

ጄኔራል አለምሸት ደግፌን ቃለመጠይቅ ላደርገው ቢሮው ሄጄ ሳለሁ ደግሞ እንዲህ አለኝ፣

"አላነበብኩትም። አባዱላ ግን አንብቦታል። ደስ አላለውም። ምንድነው የፃፍከው? ላነበው እፈልጋለሁ..."

በፈረንሳይ የስለላ ድርጅት እንደሚዘጋጅ የሚነገርለት Indian Ocean Newsletter በቁጥር 949 እትሙ እንዲህ ሲል ፃፈ፣

"Yeburka Zimta (The Silence of Burka), a fictional account a bit too close to reality since it led to accusations of his having wanted to stir up passions

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

between the Oromo and the Amhara communities."

ከአበበ ባልቻ ጋር በስልክ፣

"በጣም ወድጀዋለሁ። በተለይ ሃወኒ ዋቆ እስር ቤት ያገኘቻቸው ወጣቶች...በጣም ሳቅሁ...መአዛ (ባለቤቱ) ግን አልወደደችልህም። በተለይ አስናቀ የተባለውን ገፀ ባህርይ በትክክል አልቀረፅከውም ብላ አስባለች። ደውልላት። ብዙ አስተያየት አላት..."

ከበደ ህንፃ አሳንሰሩ ደጃፍ ላይ፣ የ"ከቡስካ በስተጀርባ" ደራሲ ፍቅረማርቆስ ደስታን አገኘሁትና እንዲህ አለኝ፣

"...መፃፍ ከሆነ እንደዚህ ነው። የቡርቃ ዝምታን በጣም የወደዱት የመኖራቸውን ያህል የጠሉትም ብዙ ናቸው። እኔ በመፅሃፎቼ ላይ በሺህዎች ደብዳቤዎች ተቀብያለሁ። አምርሮ የጠላኝ ወይም በስሜት ያደነቀኝ ግን አላገኘሁም..."

ታዋቂው ጋዜጠኛና ደራሲ ሙሉጌታ ጉደታ በበኩሉ የቡርቃ ዝምታን መፅሃፍ ብሎ ከመጥራት፣ 461 ገፅ ጋዜጣ ቢባል እንደሚቀል በመግለፅ አጥላላው።

ሲሳይ ንጉሱ፣

"...የፖለቲካ ጉዳይ አንስተህ ተነባቢ መፅሃፍ መፃፍህ የሚደነቅ ነው" አለኝ።

አስፋው ዳምጤ ቢሮዬ መጥተው ሳለ፣

"አከራካሪ መፅሃፍ ነው" ከማለት ሌላ የጨመሩት ቃል አልነበረም።

አንድ አንባቢ ከአጭር ማስታወሻ ጋር መፅሃፉን መልሶ በፖስታ የላከልኝ ሲሆን፣

"ይህን ችሎታህን ለቅዱስ ተግባር ብትጠቀምበት ምናለበት? እግዚአብሄር የእጅህን ይስጥህ። ጠቢያ መፅሄት ለመፅሃፍህ 'በመርዝ የተቦካ ቂጣ' ሲል ስም መስጠቱ እውነት አለው። ለማንኛውም የመርዙ ቂጣ ቤቴ እንዲቀመጥ ስላልፈለግሁ መልሼ ልኬልሃለሁ" ሲል አስፍሮ ነበር። ይህ ግን በመጠኑም ቢሆን ሳያስደነግጠኝ አልቀረም።

ከሌንጮ ለታ ወንድም ከአባጫላ ለታ ጋር ዱባይ ተርሚናል ትራንዚት ላይ ተገናኘንና አብረን ምሳ በላን፣ እኔ ወደ ሲሸልስ ደሴት፣ እሱ ወደ አስመራ ጉዞ ላይ ነበርን። እየሳቀ እንዲህ አለኝ፣

"...ካነበብኩት በሁዋላ በጣም ተናደድኩ። ይህን መፅሃፍ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ኦሮሞ የሆነ ሰው ቢፅፈው ተመኝቼ ነበር።"
ዶክተር ሰለሞን እንቋይ የትግራይ ክልል ባለስልጣን ናቸው። አንብበውት ወደውት ነበር። የእፎይታ ጋዜጣን ሪፖርተር ጠርተውም አድናቆታቸውን ገለጡለት። ሪፖርተሩ ዶክተሩን ቃለመጠይቅ አደረጋቸውና ላከልን። ስብሃት ገብረእግዚአብሄርም በመፅሃፉ ላይ ሂስ ፅፈው ስለነበር አንድ ላይ አተምነው።

የወይን ጋዜጠኛ አታክልቲ ለዶክተሩ ደውሎ፣

"ደራሲው ኤርትራዊና በሻእቢያ የሚጠረጠር ነው። እንዴት ያን የመሰለ የአድናቆት አስተያየት ትሰጣለህ?" ይላቸዋል።

የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት እየተካሄደ ነበርና ዶክተሩ ደንግጠው፣ "ማረሚያ ይውጣልኝ" ይላሉ። ሪፖርተራችን ሲያነጋግራቸው፣ "ደራሲው ኤርትራዊ መሆኑን ለምን አልነገርከኝም? አሳሳትከኝ" ብለው ይቆጡታል። ነገሩን ለማሳጠር የዶክተሩን የማስተባበያ ደብዳቤ አተምነው። ደብዳቤውን ያረቀቀው አታክልቲ ነበር። ሁሉን በጎን ብንሰማም አተምነው። ማስተባበያው ታትሞ እንደወጣ አለምሰገድ አስጠራኝና፣

"ምንድነው ይሄ?" ሲል ጠየቀኝ።

አስረዳሁት፣

"...ዶክተሩ አስተያየት ሰጥተው ነበር። ማስረጃው እጃችን ላይ አለ። ለማጋነን ስላልፈለግሁ ግን በፍላጎታቸው መሰረት አስተባብዬላቸዋለሁ። ዶክተሩ መጀመሪያ ያደነቁኝ የትግራይ ሰው መስዬአቸው ነበር። አለመሆኔን ሲሰሙ አሳባቸውን ለወጡ..."

አለምሰገድ በጣም አዝኖ አሰናበተኝ።

አማረ አረጋዊ የቡርቃ ዝምታን አንብቦ መጨረሱን ሰማሁና ደወልኩለት። ሌላ ሌላውን አወራን። አላነሳልኝም። እንደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝም አለ። ዝም ዝም፣ ዝም ዝም። በዚህ ጊዜ አንድ ግጥም ትዝ አለኝ፣

እነ ማቱሳላ - እነ አብርሃም፣
ጠጡ ሃቲሃላ - እድሜ የሚያረዝም፣
ምስጢሩን ለማንም - አልተናገሩም፣
ጠጥተው ዝም ዝም - እንዲያው ዝም ዝም፣

ዶክተር ሰለሞን፣ "ደራሲው ኤርትራዊ ነው" ሲባሉ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ደንግጠው ነበር። ሰለሞን ሙሉ ታፈሰ የተባለ የግሉ ሚዲያ ባልደረባ ግን እንዲህ ሲል ፃፈ፣

"ኤርትራዊ ቢሆን ታዲያ ምንድነው? አፍጋኒስታናዊም ይሁን! የማደንቀውን አደንቃለሁ..."

ጩኸቱ በበዛ ቁጥር የመፅሃፉ ፈላጊዎች ስለበረከቱ የመጀመሪያው እትም ወዲያው ተሸጠ አለቀ። ሁለተኛው እትም ታተመ። ሁለተኛውን እትም መኪና ላይ ስንጭን ሳለ ተክላይ ተክሉ መጣ፣

"ነጋዴ ሆነሃል" አለኝ። ነገር ፍለጋ መሆኑ ነው።

"ሌቦች እንጂ ነጋዴዎች ሃገሪቱን አላስቸገሩዋትም" አልኩት።

"ምን ለማለት ፈልገህ ነው?" አለ።

"የመንግስትን ገንዘብ የሚሰርቁ ታጋዮች በዝተዋል ማለቴ ነው"

ዘግየት አለና እንዲህ አለ፣

"መፅሃፍህን የሚገዛህ የለም ሲባል ነው የሰማሁት። እንዴት ድጋሚ አሳተምክ?"

"አንተ ከየት አምጥተህ አነበብክ?" ስል ጠየቅሁት።

"ተውሼ ነው ያነበብኩት"

"በዶላር እየተከፈለህ እንዴት ተውሰህ ታነባለህ?"

"የምን ዶላር?" አለ ቱግ ብሎ።

"የሚወራውን ነው የነገርኩህ" አልኩ።

"ምንድነው የሚወራው?"

"አሁን ቸኩያለሁ። ቻው። ቢራ ከጋበዝከኝ ግን ሌላ ቀን ሰው የሚያወራብህን እነግርሃለሁ።" ብዬ ትቼው ልሄድ ስል ክንዴ ላይ ይዞ አቆመኝ። እጁ ይንቀጠቀጥ ነበር። እውነት ለመናገር ግን ስለ ዶላር ክፍያ ምንም የሰማሁት ወሬ አልነበረም። አሜሪካ ላይ የሚሸጡት የትግርኛ ጋዜጣና መፅሄት ክፍያ ያለደረሰኝ በዶላር እንድሚላክላቸው ስለማውቅ ላስደነግጠው ብዬ ነበር ያን ማለቴ። በዚያውም ነገር ፍለጋውን ገለበጥኩበት። እጁን ካስለቀቅሁት በሁዋላም፣ "ቸኩያለሁ ቻው" ብዬው ሄድኩ።

ከኮበለልኩ በሁዋላ ደረገዎች ላይና በኢሜይል አንዳንድ አስተያየቶችን አጊንቼ ነበር። አንዳንድ ትኩረት የሚስቡ አባባሎች ነበሩባቸው...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

.... እውነትን መፍራት የለብንም። በአማርኛ ስነፅሁፍ ውስጥ ጫላና ጫልቱ ዋና ገፀባህርይ ሆነው አይታዩም።

....ጫላ ጩቤ ጨበጠ...የቡልቻ ልብ...ብልሁ አየለ... ...የመሳሰሉት የልጅነት ተረቶች ትዝ ይሉአችሁዋል? አየለ ለምን ጩቤ አልጨበጠም? ቡልቻ ለምን ብልህ ሳይሆን ቀረ?

....በአሉ ግርማ እናቱ ኦሮሞ ናት። ካድማስ ባሻገር ላይ የቀረፃት ሉሊት ታደሰ እናቱ ናት። ጠይም ጣኦት ይላታል። የሉሊት የመጀመሪያ ስም ጫልቱ ነበር። አሁን ዘመኑ መለወጡን ማስታወስ ይገባል። "ብፁእ አቡነ ቡልቻ" የሚለውን ስያሜ እንቀበል ዘንድ ዘመኑ ጠይቆናል...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 20 -
የአሰፋ ማሞ ጨቤዎች

ሃሩሩ ያቃጥለን - በረዶ ይውረድብን፣
ዋሻ ውስጥ እንኑር - ውሃ ጥም ያንድደን፣
በሌት በቀን ጉዞ - እንራብ እንድከም፣
የማንወጣው ተራራ - የማንሻገረው ወንዝ የለም፣
አላማችን ነው ሃይላችን - ከቶ አንበገርም፣

(ግጥም - የህወሃት መዝሙር)

ከማልረሳቸው የህወሃት ታጋዮች አንዱ አሰፋ ማሞ ይባላል። በጣም ጥሩ ሰው ነበር። መፅሃፍ የመፃፍና የማሳተም ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው። ነፍሱን ይማረውና አሁን በህይወት የለም...

የአሰፋ ማሞ የመፃፍ ሞራል በእጅጉ ጠንካራ ነበር። ሻይ ስንጠጣ አንዳንድ ጊዜ ሊፅፈው ስላቀደው መፅሃፍ ያነሳልኝ ነበር።

"ጀምረኸዋል?" ስል ጠየቅሁት አንድ ቀን።

"አንዳንድ ነጥቦችን እየያዝኩ ነው። እንደምታየው ስራ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ይበዛል...”

“ስለምንድነው መፃፍ የፈለግኸው?’

“የራሴን የትግል ታሪክ”

“መቼ ትጀምረዋለህ?”

“መፅሃፉኮ አልቆአል ማለት ይቻላል። አንጎሌ ውስጥ አለ። የቀረኝ ነገር ቢኖር ብእርና ወረቀት ማገናኘት ብቻ ነው። ከጀመርኩት ያልቃል። ግን ርግጠኛ አይደለሁም። ጥሩ የመፃፍ ችሎታ አለኝ ልልህ አልችልም።”

“እስኪ ልትፅፈው ካሰብከው ታሪክ ጥቂት አጫውተኝ?” ስል ጠየቅሁት።

አጫወተኝ።

“አንድ ጊዜ ከኢዲዩ ጋር እየተዋጋን ነበር” ሲል ነበር ትረካውን የጀመረው “.... እኔ አዋጊ ኮማንደር ነበርኩ። መለስ ደግሞ ኮሚሳር ነበር። ኢዲዩ ጠነከረችብን። ከበበችን። አልቻልናትም። የመገናኛ ሬድዮ ይገር እያዋጋሁ ነበር። የያዝኳት ሬድዮ ብልጭ ብልጭ የሚል ብርሃን ነበራት። የኢዲዩ ተኳሾች በዚያች ብርሃን አነጣጥረው ተኩሰው የታችኛው ከንፈሬን ገነጠሉት፣ ጥርሶቼም እንዳሉ ረገፉ...”

ትረካውን አቋርጦ፣

“...ይሄ የምታየው በሙሉ አርተፊሻል ጥርስና ከንፈር ነው” ካለ በሁዋላ ትረካውን ካቆመበት ቀጠለ፣

“...ከንፈሬን ገነጠሉት፣ ጥርሶቼም እንዳሉ ረገፉ...እናም ወደቅሁ። መለስ እኔን ተክቶ ማዋጋቱን ቀጠለ። በዚህ መሃል ለሳሙኤል ደውለን ርዳታ ጠይቀነው ነበር...” ካለ በሁዋላ እንደገና ትረካውን አቋርጦ፣ “...ሳሙኤልን አወቅኸው?” ሲል ጠየቀኝ።

“ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ የፀጥታ ሃላፊ ሆኖ የሚሰራው ነው?” አልኩ ርግጠኛ ባለመሆን።

“ልክ ነህ” ብሎ ትረካውን ቀጠለ፣ “...ሳሙኤል አንድ ጋንታ ሃይል ይዞ ሌሊቱን ሙሉ ሲገሰግስ አድሮ ሊነጋጋ ሲል ደረሰልን። ኢዲዩን ከሁዋላ ሲያርበደብዳት ጥላ ሸሸች። ሳሙኤል ያን ጊዜ ባይደርስልን ኖሮ ዛሬ እኔና መለስ በህይወት ባልተገኘን ነበር...”

አሰፋ ያሰበውን መፅሃፍ እንደማይፅፈው ርግጠኛ ነበርኩ። ጥሩ ተናጋሪ እንጂ ፀሃፊ አለመሆኑን አውቅ ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የራስህን የህይወት ታሪክ መፃፍ ባናቱ ቀላል አይደለም። በርግጥ አሰፋ ብዙ ገጠመኞች ስላሉት ያን እኔ እንድፅፈው መፈለጉን ሳልገነዘብ አልቀረሁም። ልረዳው ግን አልቻልኩም። ጊዜ አልነበረኝምና ቃል ሳልገባለት ቀረሁ።

ደቡብ አፍሪቃ በስደት በከተምኩ በአራተኛው አመት አካባቢ፣ አሰፋ ማሞ ታሞ ለህክምና ፕሪቶሪያ ሲመጣ ሂጄ ጠየቅሁት። ቁጭ ብለን ጥቂት አወጋን። በጣም ታሞ ነበር።

እንደማይድንም አጫወተኝ።

በመጨረሻም እንዲህ አለኝ፣

"...ብዙ ማስታወሻዎች ይዤ ነበር...ሳልፅፈው ጊዜዬ አለቀ...ሌላ ምን ቀሪ ነገር ይኖራል ብለህ ነው? ያሳለፍነውን ወረቀት ላይ ብናሰፍረው ቢያንስ መጪው ትውልድ ይጠቀምበት ነበር...ምን ታደርገዋለህ?....አንተ እንድትፅፈው ሃሳብ ነበረኝ..."

ዘግየት አለና ያልጠበቅሁትን ጥያቄ ጠየቀኝ፣

"...ግን ምን ሆነህ ነው የኮበለልከው? እስኪ እውነቱን ተናገር...ምንም በቂ ምክንያት አልነበረህም...በል ንገረኝ...እስኪ ምን ተበደልክ?"

አሰፋ በመጨረሻው የህይወት መስመር ላይ ስለነበር ሁሉንም አጫወትኩት። ዘርዝሬ በግልፅ አወጋሁት። በዝምታ አዳመጠ ሲያበቃ፣

"አዝናለሁ!" ብሎ ትክዝ ካለ በሁዋላ፣ "...ብዙ ችግሮች አሉ በርግጥ። እጃችንን በእጃችን እየበላን እየተጓዝን ነው" ሲል ተነፈሰ።

ከጥቂት ሳምንታት በሁዋላ አሰፋ ማሞ መሞቱን ድረገፆች ላይ ተፅፎ አነበብኩ።

አሰፋ ማሞ በአሜሪካ የኢህአዴግ ወኪል ሆኖ አያሌ አመታት ሰርቶአል። ኢህአዴግ አዲስ አበባን የያዘ ሰሞን በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ሰብስቦ ሲያነጋግር ከፍተኛ ተቃውሞ አዘል ጥያቄዎች ይቀርቡለት የነበረ ሲሆን፤ የአሰፋ ማሞን ምላሾች ምንጊዜም ሳደንቅ እኖራለሁ።

አንድ ሁለቱን ልቀንጭብላችሁ፣

"አቶ አሰፋ በግልፅ እንነጋገር! ወያኔ ውስጥ እንግሊዝኛ መናገር የሚችሉ ታጋዮች አንተን ጨምሮ አምስት ብቻ ናችሁ ይባላል። እንዴት ነው ሃገር ልትመሩ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የምትችሉት?"

አሰፋ ፈጣን ምላሽ ሰጠ፣

"እኛ እኮ የእንግሊዝ ነፃ አውጪ አይደለንም! የኢትዮጵያን ገበሬ ነው ነፃ ያወጣነው!"

ከፍተኛ ሳቅ አዳራሹን ነቀነቀው።

"ጩቤ ቀረቀረለት!! ሰካበት! ኸረ ንቀልለት!!" ከሚል ተረብ ጋር ሳቆች ቀጠሉ።

ሌላ ጥያቄ፣

"አቶ አሰፋ...ተዋጊዎቻችሁን በቴሌቭዥን እንደምናያቸው ኮተታሞች ናቸው። እጅጌው የረዘመ ልብስ ለብሰው እየተንጎለጎሉ በዋና ከተማችን ይታያሉ! አዋረዳችሁን!"

አሰፋ ማሞ!

"ልክ ነው! ግን ምን እናድርግ!? አዲሳባ ስንገባ ያገኘነው የወታደር ልብስ ለቦርጫም ጀኔራሎች የተሰፋውን ነው። በልካችን እስክናሰፋ እባካችሁ ታገሱን!"

ከፍተኛ ሳቅ!

ሌላ ጥያቄ፣ ጎሹ ወልዴ እጁን አወጣ፣

"አቶ አሰፋ...እኔ ወደ አዲሳባ ብመለስ ምን ይገጥመኛል?"

አሰፋ ማሞ!

"ምንም አይገጥምህም። ከኤርፖርት በቀጥታ ወደ እስር ቤት ትላካለህ"

ሌላ ጥያቄ፣

"አቶ አሰፋ...አልሰለጠናችሁም! ገበሬዎች ናችሁ! ይህን ትክዳለህ?"

አሰፋ ሳቀ፣

"አልክድም! አልሰለጠንንም! ገበሬዎች ነን! የታገልንበት ጉዳይኮ ይኸው ነው! አለመሰልጠናችን ግን የኛ ጠፋት አይደለም። ማን እየመራን እንሰልጥን?"

አሰፋ ማሞ እጅግ ተናጋሪ ነበር - ነፍሱን ይማረውና!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 21 -
የጋዜጠኛው ደብዳቤ

መቅደስ ነው ሃገሬ – አድባር ነው ሃገሬ፣
ሰንብ እሄዳለሁ – ቢሰበርም እግሬ፣
አለብኝ ቀጠሮ – ከትውልድ ሃገሬ፣
አለብኝ ቀጠሮ፣
ከትውልድ ሃገሬ፣ ካሳደገኝ ጓሮ፣

(ግጥም - ገብረክርስቶስ ደስታ)

የአዲስአበባ ነዋሪ የሆነ አንድ አንጋፋ ጋዜጠኛ ወዳጅ አለኝ። በምርጫ 97 ወቅት CUD የተባለውን የተቃዋሚዎች ፓርቲ ደግፈሃል በሚል ከፕሬስ ድርጅት እንዳባረሩት ዜና ላይ አይቼ፤ ደብዳቤ ልኬለት ነበር። የሚከተለውን ምላሽ ላከልኝ። አንዲትም ቃል ያልጨመርኩና ያልቀነስኩ ሲሆን እንደወረደ አንብቡት።

* * *

ስማ እንጂ! ደህና ነህ ወይ?
የመጀመሪያው ታሪካዊ ደብዳቤህ ደረሰኝ። ሰላምና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ጤንነትህን እየተመኘሁ አመሰግንሃለሁ። መቼም ሁሉ ነገራችን ታሪካዊ ነው። ባህል ሆኖብን ደብዳቤአችን ታሪካዊ፣ ሃላፊነታችን ታሪካዊ፣ ንግግራችን ታሪካዊ፣ ሳቅና ለቅሶአችን ታሪካዊ፣ አሟሟትና አገዳደላችን ሳይቀር ገድላዊና ታሪካዊ ነው። ታሪካችንም ራሱ ታሪካዊ ነው።

ታሪካዊ ደብዳቤህ ደረሰኝ።

እንዴት ደስ አለኝ መሰለህ? ግን በጣም ዘግይቶአል። ግንቦት 13 የተፃፈ ደብዳቤ ሰኔ 21 ቀን ደረሰኝ። ታሪካዊ ጉዞ ነው ያደረገው። ለመሆኑ መቼ ይሆን ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ... ሃላፊነት የምንወጣው? በታሪክ ስለ ታሪክ፣ እንደ ታሪክ ኖረን ለታሪክ የምንሞት ጉዶች ሆነን ቀረንኮ!

አይገርምህም?

አንድም የኔ የሚለው ነገር የሌለው ሙጃ ትውልድ! አያሳዝንም? ከተረት አቅም እንኳን የራሱ ተረት የሌለው ትውልድ! ባባቶቹ ተረት የሚተርት ትውልድ፣ እንደ ተስቦ ሁዋላቀርነትን እየተቀባበለ በውርስ ኖሮ ወራሽ የሚፈለፍል ትውልድ!

የናቴ ልጅ ወፈፍ አደረገኝና ወዴት ወዴት ሄድኩ?

የኔ ነገር እንዲሁ ነኝ። እንደ ተምታታብኝ ህይወቴን አንጋደድኩ። እግዜር ደግሞ አንዳንዴ ካልመሰለው ክፉ ነው። አንጋደድኩ ስል ቆሞ ቀር አድርጎኝ 90 አመት እድሜ ይሰጠኝና ጉዴ እንዳይፈላ ነው ስጋቴ። ይታይህ ሃምሳው ሲያቅለሸልሸኝ ዘጠና ስታቀፍ?

ወዳጄ ሆይ! እወድህ ነበር...

እኔኮ ሰው በቀላሉ አልወድም። ሰብአዊነት አንሶኝ እንዳልሆነ ታውቃለህ። እኔ አላውቅም። ነፍሴ ራስዋ ምን እንደምትፈልግ ሳይገባኝ እየኖርኩ ነው። አንተ ደግሞ ከስራ የመባረሬን ዜና ሰምተህ የማፅናኛ ደብዳቤ ፃፍክልኝ። ሞኝ ነህ ልበል? ማንስ ምን ስራ አለው? "ስራ" የሚለውን ቃል በደንብ እንተርጉመው ካልን እኮ 'የነፍስ ጥሪ፣ አላማ፣ ምኞት፣ ፍላጎት... ይኖረን እንደሆነ እንጂ ስራ ሰርተን የምናውቅ አይመስለኝም። ሰራን ካልንማ የሰራ ሰው እንደ እኛ ኖሮ አያውቅም። አንድ ደግ እምነቴን ልንገርህ? ድሮም ቢሆን እንደ ተፈቀደልኝ እንጂ እንደፈለኩት ኖሬ አላውቅም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ኖርኩ ማለት ራሱ የሚገለማ ምፀት ነው።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በተረፈ በአዲሳባችን አዲስ ነገር ካለ የጠየከኝ መሰለኝ? ምን አዲስ ነገር ይኖራል? አዲስ ነገር ለመቅበር እንጂ አዲስ ነገር ለመፍጠር መቼ ታደልንና? ለአንድ ሰአት ተኩል እድሜ አትጨነቅ። ክፋቱ ደግሞ ይህችው አንድ ሰአት ተኩል እድሜ ፍዳ ሳታሳይህ አለማለቋ ነው።

አሁን ይልቅ ቀልዱን ተውና ከስነ ፅሁፍ በምትተርፍህ ጊዜ ድንጋይ ፈልጠህም ይሁን ካርቶን ተሸክመህ ለቤት ኪራይ ገንዘብ ላክ። ይህንንም የምታደርገው ለራስህ ስትል ነው። እውነቴን ነው! ታዲያ የት ኖሬ በምን አድራሻ ልፅፍልህ ነው?

ስለ ፍልስፍናዬ የጠቀስከው ነገር አለ! እኔ አንድ የገጠር ልጅ መሆኔን አውቃለሁ። አዲስ አበባ መኖር መሰልጠን ነው ማለቴ አይደለም። ግን አንድ ነገር አውቃለሁ። ያ ነገር ነው ከማንኛውም የአገሬ ዜጎች የሚለየኝ፤ ሁሌም እምነቴ "ሰው" በሚል ቃል ላይ የተመሰረተ ነው። ለኔ ደግሞ ሰው ማለት ጎሳ ወይም ኢትዮጵያዊነት ሳይሆን አምላክ ወሰን በሌላት ምድር ላይ በአምሳሉ የፈጠረው ሰው ሁሉ ለኔ ሰው ነው።

እንደዚህ እንዳላስብ የሚያደርገኝ ነገር ደግሞ የለም። እግዜር ብቻዬን ፈጠረኝ፤ ብቻዬን እየኖርኩ ነው። እና ለማን ነው ወገናዊ ልሁን ብልስ ወገናዊ መሆን የምችለው? በዚያም ላይ ምኞቴ ባይሳካም የደራሲ መንፈስ እንዳለኝ አትርሳ። ለዚህም ነው ፍጥረታት ሁሉ ለኔ የጋራ ስሜት የሚፈጥሩት።

ወዳጄ ሆይ! ደግና ቅን መሆን ስላለመሆንህ እራስህን ጠይቅ እንጂ ስለሰዎች ክፋት ስታምሰለስል ጊዜህን አታሳልፍ። በሃጢያት፣ በቅጥፈትና በጭካኔ በቦካች ምድር ላይ 'ስራህ ያውጣህ' ተብለን የተበተንን ጉዶች መሆናችንን እኔ ላንተ መንገር አለብኝ?

ከተቻለህ አንድ ነገር አድርግ። እድሜና ጨርቅ እንደዋዛ ያልቃልና ያ ከመሆኑ በፊት ሰይጣንም ይሁን መልአክ ሹክ የሚልህንና መንፈስህ ውስጥ የሚያቃጭል ነገር ሲኖር ፃፍ! ይህ የህይወት ጥሪህ ነው! ይህንን ተሰጥኦ ሲሰጥ ደግሞ ለቀልድ አይምሰልህ። ተሰጥኦ ራሱ እድሜህን እንዴት እንደምትጨርስ ተፈጥሮ የሰጠችህ ማዘናጊያ ነው። አናፂም ግንበኛም ሰራሁ እያለ ነው የሚኖረው። ሰራሁ እያልክ፣ ኖርኩ እያልክ ሳታስበው ኮንትራትህን የማገባደጃ ስልቶች ናቸው። በቃ! የህይወት ትልቁ ብልጠትዋ ይኸው ነው።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስለዚህ የምታደንቀውንም አጣሁ ብለህ የምትቆጭበት ነገር መኖር የለበትም። በቃ! ስትኖር ኑር! ስትሞት ትሞታለህ! በኔ በኩል እስከዚያች ደቂቃ ድረስ ለሰው ያለኝ ፍቅር አይነጥፍም። በጥላቻ ያተረፈ ሰው ታውቃለህ? በፍቅር እንጂ።

በተረፈ የላክህልኝ ደብዳቤ ድንቅ ነበር። በተለይም የዛምቢያና የሞዛምቢክ ጫካዎች ገጠመኞችህ ልቤን ነክቶታል። በሰው ልጅ ላይ ያለኝን እምነት እንዳጠነክርም አግዘውኛል። የኛው ዘመን ፖለቲከኛ ዱባለ የማይረሳ ሰው ነው። ትረካህ በጣም ያስቃል። እኔ ግን አልሳቅሁም። የእንባ ከረጢቴ ደርቆአል እንጂ ባለቅስ እመርጥ ነበር።

ቢሾፍቱ! ቢሾፍቱ! እያልክ ማለቃቀስህን ግን አልወደድኩልህም። የኔ ወንድም... የያዘ ይዞት እንጂ ይህ ህዝብ መሪ በማጣቱ በሃገሩ ተስፋ አጥቶ ልቡና ቀልቡ ከኮበለለ ዘመን የለውም። እንደ ገብረክርስቶስ ደስታ በወጣህበት እቀራለሁ ብለህ መስጋትህም ቢሆን ተገቢ ስጋት አይደለም። በዚያው ብትቀርስ ምን ለውጥ አለው? በቃ! ባለህበት ትሞታለህ። በርግጥ መሰደድህ ላይቀር ወደ አሜሪካ ብታቀና በተሻለ። ቀድሞውንም ከሲያትል መመለስ አልነበረብህም።

የሆነው ሆኖ እንዳልኩህ ካንተ የሚጠበቀው መፃፍ ብቻ ነው። ይልቁን "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" በሚል ርእስ ጀመርኩ ያልከው መፅሃፍ አልቆ እስካነበው ጓጉቻለሁ። ከቻልክ እንዲያውም ከስር ከስሩ ብትልክልኝ ጥሩ ነው። እንደሰጋኸው በዚያው ቀልጠህ የምትቀር ከሆነ እኛው እንደሚሆን እናደርገዋለን።

ደህና ሁን!

ገና ፅፍልሃለሁ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 22 -
ሲያትል ደህና ሁኝ!

ጉድባይ ደህና ሁኝ፣
ጥፋቱስ አይደለም - ካንቺ ወይም ከኔ፣
ፍቅር የመሆኑ - ፅድቅና ኩነኔ፣
አንቺ አንቺ መሆንሽ - እኔ እኔ መሆኔ፤

(ግጥም- መንግስቱ ለማ)

ከስር አመታት ወደ ሁዋላ ተመልሼ ላውጋችሁ...

...ወደ ፋብሪካው በሚያስገባው የውቅያኖሱ ዳርቻ ከሁለት ሺህ በላይ ወዛደሮች የሩጫ ያህል እንደ ጎርፍ እየገሰገሰን ነው። ገና አልነጋም። የውቅያኖሱ ነፍሳትና አእዋፍ ድምፅ ግን በጨለማማው ንጋት ውስጥ ጫጫታው ይሰማል። የሲያትል ዋሽንግተን ምስራቃዊ ሰማይ ወገግ ማለት ቢጀምርም በመንገዱ ዳርቻ በተተከሉት መብራቶች እርዳታ እንገሰግሳለን። የፋብሪካው ሰራተኞች የችካላ የርምጃ ጉዞአችንን ወታደራዊ ጉዞ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አስመስሎታል።

አፍሪቃዊ ነኝና ያለፍላጎቴ የምሰራቸውን ስራዎች ተላምጄያቸዋለሁ። ከአመታት በፊት የተከበረ የፕሬስ መምሪያ ሃላፊ ነበርኩ። ከወራት በፊት ደግሞ የአንድ ታዋቂ መፅሄት ዋና አዘጋጅ ነበርኩ። እነሆ አሁን አሳ በሚያሽግ ፋብሪካ ውስጥ ከሚሰሩ በሺዎች ከሚቆጠሩ ወዛደሮች አንዱ ነኝ።

ገና ሳይነጋ 305 የመስመር ቁጥር አውቶብስን ይዤ Downtown እገባለሁ። ከዚያም ሃያ ደቂቃ የሚፈጀው የእግር ቀሪ መንገድ ይጠብቀኛል!

ሁለት በእድሜ የገፉ እናቶች ከኔ በፊጠነ ርምጃ አልፈውኝ ሸመጠጡ። አበሾች ናቸው። እንዲህ ሲባባሉ ሰማሁ፣

"ይህ ስራ ለልጆቻችን እንጂ ለኛ መሆን አልነበረበትም"

"ምን ይደረግ! እንጀራ ነው"

"የማረፊያችን ጊዜ ነበር አሁን!"

አልፈውኝ ገሰገሱ። የተነጋገሩት በትግርኛ ሲሆን፣ ኤርትራውያን ናቸው። ያቺ ከተማ አድካሚ የጉልበት ስራ በሚሰሩ ኤርትራውያን እናቶች የተወረረች መሆኑን መታዘብ ችያለሁ። "ሲያትል ታይምስ" በተባለው ታዋቂው ጋዜጣ ማተሚያ ቤት በሌሊት ሽፍት የሚሰሩ ኤርትራውያን እናቶች ከመብዛታቸው የተነሳ፣ "ሃርሊ" የተባለውን ስራአስኪያጅ "ሃይሌ" ብለው የሚጠሩት ሲሆን እሱም ትግርኛ መናገር ጀምሮአል።

ከደቂቃዎች በሁዋላ እኔ ከምሰራበት አዳራሽ ደርሼ ጠጉሬን፣ ጢሜንና እጆቼን በፕላስቲክ ጓንቶች ሸፍኜ አሳ ለማሸግ ተዘጋጀሁ። ወደ ስራ መግባታችንን የሚያረጋግጠውን በስማችን ትይዩ "ማህተም" እያደረግን ተደረደርን።

እነሆ! ተገፎ የደረቀ አሳ የተሸከመ ጋሪ መሽከርከር ጀመረ። ስራችን አሳውን ካርቶን ውስጥ መጨመር ነው። አሳ የሞላቸውን ካርቶኖች በፕላስቲክ የሚያሽግ ሌላ ቡድን አለ። የታሸገውን ትንሽ ካርቶን ከፍ ወዳለ ካርቶን እየሞላ ፎርክሊፍት ላይ የሚጭን ደግሞ ሌላ ቡድን አለ። ስራው አዙሪት ነው። ማሸኑ ከማለዳ እስከ ሌሊት ይሽከረከራል። ጋሪው በዞረ ቁጥር ጭንቅላታችንም አብሮ ይዞራል። ለነገሩ እዚህ ለመስራት ጭንቅላት አያስፈልግም። ስለማይነቀል ነውንጂ እንደ ኮፍያ ጭንቅላታችንንም ቤት ትተነው መምጣት በቻልን ነበር። እዚህ ለመስራት እጆች ብቻ በቂ ናቸው።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስምንት ሰአት ከሰራን በሁዋላ እንደገና የምንወጣበትን ሰአት "ማህተም" አድርገን ወደየመንደሮቻችን የሚያደርሱንን አውቶብሶች እንጠብቃለን! ህይወት እንዲሁ ትሽከረከራለች። ዝንተ አለም! አሜሪካ ! የሚሽከረከር የህይወት ጋሪ!!

ይህን ስራ ከጀመርኩ 19 ቀናት ሞላኝ። ለኔ ግን በእውነቱ 19 አመት ሆኖብኛል። ከዚህ ስራ በፊት ከተማ ውስጥ ሌሊት በአንድ መስሪያ ቤት ውስጥ የፅዳት ስራ እሰራ ነበር። ለአንድ ሳምንት ያህል የሌሊት ቆሻሻዎችን ካፀዳሁ በሁዋላ ጭንቅላቴ ውስጥ ቆሻሻ የሞላ ስለመሰለኝ ስራውን ትቼ ሸሸሁ።

በመቀጠል ዳቦ መሸከም ተቀጠርኩ። ከሁለት ቀናት በላይ አልሰራሁም። ዳቦ የሞሉ ካርቶኖች እየጫንኩ ከራሴ ጋር እንዲህ እያልኩ አወጋ ነበር፣

"እሺ! ጋዜጠኛው! ካርቶን ትጭናለህ! ካርቶን ራስ ነህ! ወኔህም ካርቶን ነው። ጓደኞችህና ዘመዶችህ 'አሜሪካ ነው' እያሉ ይኮሩብሃል! 'እማራለሁ' ስትል አልነበር? የታለ የምትማረው? የሚከፈልህ ደሞዝ በዶላር ነው! ጎሽ የኔ ካርቶን! ነዋሪነትህም በአሜሪካ! አብሮህ የሚሰራው ማን ነው ስሙ? እንኳን ስሙን የመጣበትን ሃገር አታውቅም! ትንፋሽ እስኪያጥርህ ትፈጋለህ! ገብተህ ትጋደማለህ! የኛ ካርቶን !"

ራሴን የማዋረዱ ሂደት ስለከበደኝ እነዚያን ዳቦ የሞሉ ካርቶኖች ጥዬ ይሽው አሳ እያሸሁ ነው። አሳዎቹ አያልቁም። ሰአቱ ቆሞአል። አንድ ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከሺዎች በላይ አሳዎችን አሽገናል። ምሳ ሰአት ግን እንደናፈቀን ነው። ከፊት ለፊቴ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ግዙፍ ሰአት ቀና ብሎ ለማየት አስቸጋሪ ነው። በዚያች ቅፅበት የጋሪው ላይ አሳዎች እየተፈነጣጠሩ ሊወድቁ ይችላሉ። ጋሪው ይዞራል! ማቆሚያ የለውም። ካልተበላሸ በቀር ይዞራል...

ተመስገን አምላኬ!

ድንገት ጋሪው ቆመ። አንድ የቴክኒክ ችግር ገጠመው ማለት ነው። እፎይ! ፋታ በማግኘቴ ደስታ ዋጠኝ።

ትንፋሼን ሰብስቤ ከጎኔ ወዳለው ሰው ዘወር አልኩ። ከፊቱ ጋር ያልተመጣጠነ እንደ ጎራዴ ጠማማ አፍንጫ ያለው ሲሆን፤ አይኖቹ ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ሰጥመዋል፣

"ሰላም" አልኩት።

"ሰላም"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ከየት መጣህ?” ስል ጠየቅሁት።

“ከኢራቅ”

“ለምን ተሰደድክ?”

“አስተማሪ ነበርኩ። የሳዳም ሁሴንን በደል መቻል አቅቶኝ እዚህ መጣሁ። ይኸው አሳ አሽጋለሁ። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የኬሚስትሪ መምህር ነበርኩ። አንተስ ከየት መጣህ?”

“ከኢትዮጵያ፤ ጋዜጠኛ ነበርኩ”

“ዴሞክራሲ የለም እናንተም ዘንድ?”

“የውሸት ዴሞክራሲ አለን። የሆነው ሆኖ እኔ እንኳ በደል ሳይደርስብኝ ነው የመጣሁት”

“ለምን መጣህ?”

“ሰዎች ሁሉ ወደዚህ ይመጣሉ!”

ጋሪው ተሰርቶ ኖሮ አሳዎቹን ማምጣት በመጀመሩ ወሬያችን ተቋረጠ።

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ግን ራሴን ያዞረኝ ጀመር። ጋሪው ቆሞ እኔ በጋሪው ፍጥነት የምሽከረከር ይመስለኝ ጀመር። አሳዎቹን ከጋሪው ላይ በትክክል ማንሳት አልቻልኩም። ከእጄ ላይ ይወድቁብኝ ጀመር። አይኔን ጨፈንኩ። መልሼ ገለጥሁ። አሁን ተስተካከለ፤ እኔ ቆሜያለሁ፤ ጋሪው ይሽከረከር ጀመር።

አሳዎቹ ጋሪው ላይ ሞልተው እየተፈናጠሩ መውደቅ በመጀመራቸው ስፓኒሽ መናገር የሚቀናው ድቡልቡል ላቲናዊ በአፍንጫው እየጮኸ ወደኔ መጣ። ምን እንደሚናገር ባላውቅም እየሰደበኝ ስለመሆኑ አልተጠራጠርኩም። ያቺ ደቂቃ ወደ ሃገሬ ለመመለስ የመጨረሻ የውሳኔ ደቂቃ ለመሆን በቃች! በዚያች ደቂቃ ሲያትልን ለመሰናበት ወሰንኩ። አሜሪካ ላይ መኖር እንደማልችል ገመትኩ።

አሳዎቹን ተውኳቸውና በደረጃው ቁልቁል ወረድኩ። ከጭንቅላቴ፣ ከጢሜ ላይና ከእጄ ላይ የፕላስቲክ ጓንቲዎችን እያወለቅሁ ወደ መውጪያው አመራሁ። ድቡልቡሉ ላቲናዊ በማይገባኝ ቋንቋ እየጮኸ ይከተለኛል። ምላሽ ሳልሰጠው ማህተሙን በስሜ ትይዩ መትቼ ወጣሁ!

እኩለ ቀን አልሆነም።

በጋ እንደመሆኑ ሞቃታማው የሲያትል አየር ተስማምቶኛል። ሲያትል ውብ ናት። ሽማግሌዎችና አሮጊቶች

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የሚበዙባት፤ ከሌሎች የአሜሪካ ግዛቶች ጋር ስትወዳደር ለስላሳ አየር ያላትና ግርግር ያልበዛባት በሃበሾች ዘንድም የተወደደች ከተማ ናት። ከብዙ ሺህ ወዛደሮች ጋር በጨለማ እየተንጋጋሁ ከገባሁበት ግቢ በ19ኛው ቀን በዚህ መልክ ስራዬን አቁሜ ሳልሰናበት ወጣሁ። ሆኖም ያጎፈረ ጠጉሬን የተቆረጥሁ ያህል ቀለል አለኝ። በመንገዱ ላይ ሰው የለም። መኪኖች ብቻ አልፎ አልፎ ያልፋሉ!

ወደ አሜሪካ የመጣሁበት ዋና ምክንያት ለእረፍት ቢሆንም፣ በእግረመንገድ አንዳንድ ስራዎች ተሰጥተውኝ ነበር። ከወያኔ ጋር የመቀጠሉ ፍላጎት ግን ስላልነበረኝ ላለመመለስ ሃሳብ ነበረኝ። እንደማይሆን ግን አወቅሁ። አሜሪካን ሃገር መኖር እንደማልችል ተገነዘብኩት።

ብቻዬን ጮህኩ!

"አሜሪካ! ጂንስሽን ውሰጂ! ክብሬን መልሽልኝ!"

አውቶብስ ይዤ Downtown ገባሁ። የተጠበሰ አሳ የሚሸጡ አየሁና ደሜ ፈላ። እኔ ሳሽጋቸው የከረምኩት አሳዎች እዚህ እየተጠበሱ ይቸበቸባሉ። የሲያትል Downtown ሳምንቱን ሙሉ እንደሞቀ ይውላል። በዝግታ እየተዘዋወርኩ በውቅያኖሱ ዳርቻ ተጓዝኩ። ርቄ እንደመምጣቴ በርግጥም ባእድነት ተሰምቶኛል። ርግጥ ነው ብቻዬን አይደለሁም። ከእጮኛዬ ጋር እንደመምጣቴ አንድ ክፍል ቤት ተከራይተን እየኖርን ነበር። ህይወት ትባላለች። ውብ ልጅ ነበረች። ወደ ሲያትል ተከታትለን የመጣን በመሆኑ ሁሉታችንም ለአሜሪካ እንግዶች ነበርን። ሆኖም መጨቃጨቅ ጀምረናል። "ወደ ኢትዮጵያ እንመለስ" የሚል ጥያቄ ማንሳት በመጀመሬ በእኔም ሆነ በእስዋ ዘመዶች፤ እንደ እብድ ተቆጥሬ ነበር። እስዋም በኔ ተስፋ መቁረጥ መጀመርዋን ሳላስተውል አልቀረሁም።

ህይወት ሌሊትና ቀን ትሰራለች። በትርፍ ሰአት ደ'ሞ ማተሚያ ቤት ውስጥ ቅዳሜ ሌሊቱን ሙሉ ጋዜጣ ስታዛንቅ አድራ ሊነጋጋ ሲል ትመጣና ጀርባዋን እንዳሻት ትጠይቀኛለች። ጀርባዋን እያሸሁዋት ሳለ ገና ድሮ እንቅልፍ ይዞአት ሄዶአል። እንደዚያ ነፍስና ስጋዋ እስኪላቀቅ ሰርታ 80 ዶላር ይዛ መጥታለች። አዬ አሜሪካ!

ስራ ካቆምኩ በሁዋላ ራሴን እንደ ቱሪስት ቆጠርኩት። ወደ አዲስ አበባ ወደ ቅርብ አለቃዬ ወደ አለምሰገድ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ገብረአምላክ በመደወል፤ ስለዘገየሁ ይቅርታ ጠይቄ "እየመጣሁ ነው!" ስል ነገርኩት። አከታትዬ ወደ እፎይታ መፅሄት ቢሮ ደወልኩ። በወቅቱ የስራ ባልደረባዬ የነበረው ደረጄ ደስታ ነበር ስልኩን ያነሳው፣

"እንዴት ነው አሜሪካ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ከአስር ቀን በሁዋላ እመለሳለሁ"

"ጠብቄ ነበር"

"እውነት?"

"አሜሪካ ላንተ አይሆንም!"

ብሮድዌይ በተባለው ቀበሌ የሚገኘው ቤተክርስትያን ከእለተ ሰንበት የጊዜ ማሳለፊያዎች አንዱ ነው። ለኔ ባይመቸኝም ምርጫ ስለሌለኝ እዚያው ሄጄ አብሬያቸው እውላለሁ። በፀሎት ወቅት ከመሬት ተነስተው እንባቸው የሚወርድ፣ እዬዬ እያሉ የሚጮሁ ይበዛሉ።

አንድ ቀን ከጎኔ ተቀምጣ የነበረች ሴት ሰው እንደሞተባት እየተንሰቀሰቀች እያለቀሰች ነበርና እየነካካሁ አፅናናሁዋት። መዳፍዋን ሳሻሻት ወዲያው አተኮሳት። እንባዋም ድራሹ ጠፋ፣

"ይቅርታ! ረበሽኩህ! ወድጄ አይደለም"

"ምን ደረሰብሽ?"

ጥቂት ካመነታች በሁዋላ፣

"እንግዳ ነህ አይደለም? አይቼህ አላውቅም"

"አዎ እንግዳ ነኝ"

"እውነቱን ልንገርህ?"

"ንገሪኝ! ይወጣልሻል..."

እንደመተከዝ አለችና እንዲያ እያንገበገበ የሚያስለቅሳትን ታሪኳን አጫወተችኝ፣

"ምን መሰለህ!? ይልማ የሚባል ባል ነበረኝ። እኔ Citezen ነኝ ገባህ? እሱ ወረቀት አልነበረውም። በሰርግ ተጋባን። የምንዋደድ ይመስለኝ ነበር። ከሁለት አመታት በሁዋላ ከትናንት ወዲያ አርብ ወረቀቱን አገኘ...ገባህ? በኔ ነው ያገኘው! ገባህ? ምን እንዳደረገ ታውቃለህ? ወረቀቱን አርብ አግኝቶ...ቅዳሜ ጠዋት ሻንጣውን ይዞ ወጣ..." እንደገና ትንሰቀሰቅ ጀመር "...እንደዚህ ይደረጋል? ለወረቀት ብሎ ነበር ያገባኝ ማለት ነው? እሺ ይሁን! ምናለበት ቢያስመስል? ትንሽ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ቀን ቢቆይ? ሰበብ ፈጥሮ ተጣልቶኝ በሽማግሌ ብንፋታ እንኳ ምናለበት? ሰው አይደለሁም? እህቱ አይደለሁም? ሞራሌን መስበር ለሱ ምን ይጠቅመዋል?"

እጅዋን ያዝኳት። ይሞቃሉ፣ ረጥበዋል፤

"ማነው ስምሽ?"

ስምዋን ነገረችኝ። የኔንም ነገርኳት። መዳፎቿን አጥብቄ ይዤ አፅናናሁዋት። 'ወጣት ነሽ፤ ጥሩ ሰው ነሽ፤ አዲስ ኑሮ መጀመር ትችያለሽ' እያልኩ አፅናናሁዋት። ማለት ያለብኝ እንዲያ ስለሆነ እንጂ በርግጥ የተሰበረ ሞራሏን እንደገና ለመጠገን ምን ያህል ጉልበት እንደሚያሻት ሳልረዳላት ቀርቼ አልነበረም። ይህች ሴት በርግጥ ጠንካራ ሰውነት ያላት ብርቱ ሰራተኛ መሆንዋን መገንዘብ ይቻል ነበር። እንዳጫወተችኝ አእምሮን ወደሚያደነዝዘው አላስካ ተጉዛ ለሁለት ወራት ያህል አሳ የመግፈፍ ስራ ሰርታ የተመለሰች ጀግና ናት። በአካላዊ ቅርፅዋ ግን 'ውብ' የምትባል አልነበረችምና የጮሌ ጎረምሳ መጠቀሚያ መሆኗን ተረድቼ ከልብ አዘንኩ። ስሜታዊ ሆና እንዳጫወተችኝ አላስካ ሄዳ ያመጣችውን ገንዘብ ያ ጎረምሳ ቅርጥፍ አድርጎ በልቶታል።

ሌላ ቀንም እዚያው ቤተክርስትያን ውስጥ ከሌላ ፀፀትና ብሶት ካቃጠላት ሴት ጋር ተዋውቄ ነበር። ይህች ግን ይህ ቀረሽ የማትባል ውብ ነበረች። ባሏ አዲሳባ አይሮፕላን አብራሪ ነበር። ሁለት ወልዳለች። አሜሪካ ለእረፍት ሲልካት በዚያው ቀረች። ከአንድ አመት በሁዋላ 'ተፀፅቻለሁ ልመለስ' ስትል ለባሏ ሽማግሌ ላከች። ሳይስማማ ቀረ። አሁን ፀፀትና የልጆችዋ ናፍቆት ሊገድላት ደርሶአል። ዘክዝካ አጫወተችኝ። ከአንደበትዋ የሚወጡት አረፍተ ነገሮች በሙሉ በጥያቄ የተሞሉ ነበሩ፣

"ምን ፈልጌ ቀረሁ? እኔ ማነኝ አሁን? ከባሌና ከልጆቼ ጋር ምን ጎድሎብኝ ነበር? ቅብጠት እንጂ ሌላ ምን ሊባል ይችላል? ዛሬ ማነኝ? ነርሲንግ ሆም እሰራለሁ። አሮጊቶችን ... እ....ሃቁን ልንገርህ? ... ልዋሽህ አልችልም! ... ይሄ ሃቅ ነው! ለምን እዋሻለሁ? 'ማር ቆራጭ' ነው ቅፅል ስሜ! ልጆቼ ናፈቁኝ። እነዚያ ውብ እንቦቃቅላዎች...ወይኔ ትዳሬ! ወይኔ ቤቴ? ወይኔ መኝታ ቤቴ?"

በቅርቡ እንደምታብድ አሊያ ከፎቅ ላይ ዘልላ ራሷን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደምትገድል አልተጠራጠርኩም።

* * *

ስራ ካቆምኩ በሁዋላ አእምሮዬ ወደ ደራሲነቱ እንደተመለሰ መረዳት ቻልኩ። ትኩረቴን የሚስቡ ድርጊቶች ሲገጥመኝ እንደ ቀድሞው ልማዴ ብጫቂ ወረቀቶች ላይ ማስፈር ጀመርኩ።

የፖለቲካ ሰዎችንና ከአሜሪካ አሰቃቂ የአዙሪት ህይወት ራሳቸውን ማዳን የቻሉ ሃበሾችንም ተዋወቅሁ። ከእነዚህ አንዱ ሰለሞን የሚባል ነባር የሲያትል ነዋሪ ነበር። ቤቱ ጋብዞኝ ጥቂት አወጋን። መውጫ ከሌለው የአሜሪካ አዘቅት ራሱንና ልጆቹን እንዴት ማዳን እንደቻለ ሲያጫውተኝ እኔ በጊዜ ለመመለስ መወሰኔ ትክክል መሆኑን አረጋገጠልኝ። በአሜሪካ የተከሰተ የአንድ ሃበሻ አስገራሚ ታሪክም አንስቶ አጫወተኝ። በራሴው መንገድ ልተርክላችሁ።

...ሰውየው አሜሪካ ላይ ሁለት ልጆች ወልዶአል። በመኖሪያ ቤቱ ምንጊዜም እንጀራና ወጥ እንዲኖር የሚፈልግ አይነት ሰው ነበር። እንጀራ ካልበላ አይኑ አይገለጥለትም። እዚያው ሲያትል የወለዳቸው ሁለት ልጆቹ ደግሞ ትምህርት ቤት ስለሚውሉ እንጀራን አያውቁትም። ራት ላይ ፀብ ተጀመረ። ልጆች ሌላ ምግብ ፈለጉ። አባት ደግሞ እንደ ራሱ አስተዳደግ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር በአንድ ገበታ እንጀራ መመገብ ፈለገ። ልጆች ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አባት፣

"ወደዳችሁም ጠላችሁም ትበላላችሁ - ልጆቼ ናችሁና!" ሲል ሊያስገድዳቸው ይሞክራል።

ታላቅየው ወንድ ልጅ በአባቱ ትእዛዝና ቁጣ አልተደናገጠም። በቀጥታ ወደ ስልኩ ሄደና 911 ደወለ።

ፖሊስ መጣ። "ያልታወቀ ምግብ እንድበላ አባቴ አስገደደኝ" ሲል ልጅ ችግሩን አስረዳ። ፖሊሶቹ ነጮች ነበሩ። ምግቡን ማየት ፈለጉ። የረጅም ዘመን ታሪክ ያለው ክቡሩ እንጀራችን ለፖሊሶቹ ቀረበ። ፖሊሶቹ አይተውት አያውቁም። ለናሙና በመቀስ ቆረጡና ይዘው ሄዱ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መርምረውትም ተመለሱ። እንጀራው ጉዳት የማያመጣ ምግብ መሆኑ ተረጋገጠ። ሆኖም እንዲህ ሲሉ አባትየውን አዘዙ፣

"ባህላዊ ምግብህን ለራስህ መብላት መብትህ ነው። ልጆቹን ግን አታስገድዳቸው፤ ልጆቹ የሚፈልጉትን የመመገብ አቅም ከሌለህ ንገረንና እኛ እንመግባቸዋለን - ምክንያቱም አሜሪካዊ ናቸውና!"

አባት በዚህ አንጀቱ እርር ድብን አለና ልጆቹን ፒዛና በርገር መመገብ ጀመረ። ቂም ግን ያዘ። ታላቅየውን ወንድ ልጁንም ቀስ በቀስ አረሳሳውና ትምህርት ቤት ሲዘጋ ጠብቆ ለስለስ ብሎ ቀረበው።

"ቤቢሾ! ለአንድ ሳምንት አያቶችህ ጋር እንሄዳለን!"

ልጅ እውነት መሰለው።

አባት ልጁን በአይሮፕላን ጭኖ አዲስ አበባ ገባ። እናቱ ቤት። እንዲህ አላት ለእናቱ፣

"በይ! እኔን ቀጥተኛ እንዳሳደግሺኝ ይህንንም ውሪ ልክ አግቢልኝ!"

እና ልጁን አዲስ አበባ ትቶ ወደ አሜሪካ ተመለሰ! አሜሪካ ሲመለስ ትንሽዋ ሴት ልጅ ስለ ወንድሟ ጠየቀችው። "አያቶቹ ጋር ሆኖ ይማራል" ይላታል። ልጅቱ ደስ አላላትም። አባትዋ ስራ ሲሄድ ጠብቃ ወደ ፖሊስ ደወለች። ፖሊስ መጣና ልጁ የት እንዳለ ጠየቀ። አባት ያልጠበቀው ነበርና መሬት ብትውጠው መረጠ። "አያቶቹ ዘንድ ነው" ሲል ሊያሳምን ሞከረ። ልጁ አያቶቹ ዘንድ ኢትዮጵያ የተቀመጠው በፈቃዱ መሆን አለመሆኑን ፖሊስ ማጣራት ፈለገና የአዲስ አበባውን ስልክ ጠየቀ። አባት እየሰቀጠጠው ተገዶ ስልክ ሰጠ። ፖሊሶቹ ህፃኑ ዘንድ ደወሉና አነጋገሩት። እያለቀሰ የደረሰበትን "ግፍ" ተናዘዘ። አባት በፖሊስ ተያዘ። ልጁን ወደ አሜሪካ መልሶ እን ዲያመጣ የ48 ሰአት ጊዜ ሰጡት። ልጁ ተመልሶ መጣ...

ሰለሞን ይህን ተርኮልኝ ሲያበቃ ፈገግ አለ።

"አሜሪካ ላይ ልጅህን በዘዴ ማሳደግ ካልቻልክ ያንተ አይሆንም"

ዘዴ ማለት ምንድነው?

ልዩ ምስጢር አልነበረውም። ከልጆችህ ጋር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የምትውልበት ጊዜ ሊኖርህ ይገባል። በቀን ከአስር ሰአት በላይ አድካሚ ስራ እየሰራህ ግን እንዴት ከልጅህ ጋር የምታሳልፈው ጊዜ ሊኖርህ ይችላል? ስለዚህ ልጅህ ያንተ አይሆንም - ባብዛኛው!

"ባብዛኛው" እያልን ስለምናወጋ እንጂ አሜሪካ ላይ ህይወት የተሳካለት ቤተሰብ ጥቂት አለመሆኑ መቸም ግልፅ ነው። ባብዛኛው ግን ህይወት ከዚያው አዙሪት ላይ ስትሽከረከር እንደምትውል ስራ ካቆምኩ በሁዋላ መታዘብ ቻልኩ። ተሳፍሬበት ከነበረው ፈጣን ጋሪ ላይ ዘልዬ ከወረድኩ በሁዋላ ተጋርዶብኝ የነበረው ሁሉ ተገላልጦ ይታየኝ ጀመር።

አንድ ቀን አዲሳባ አውቀው ከነበረ ከአንድ ኢንጂንየር ጋር ተገናኝተን ስንጫወት፣

"ቦይንግ አይሮፕላን ፋብሪካ ተቀጥሬ እየሰራሁ ነው" ሲል አጫወተኝ።

"እድለኛ ነህ!" አልኩት።

"አዎ እድለኛ ነኝ!" ብሎ ተስማማ።

ወደ ከተማ ወረድንና ቢራ መጠጣት ጀመርን። ሶስት እንደጠጣ ታዲያ ማለቃቀስ ጀመረ።

"ቦይንግ ፋብሪካ እሰራለሁ ስልህ ለምንድነው ምን እንደምሰራ ያልጠየቅሽኝ? .... እ ....ምን እንደምሰራ ልን ገርህ? የታሸጉ ሳጥኖች ይመጣሉ። ሚስማሩን እነቅላለሁ። በቃ! እና ይሄ ስራ ነው? ሚስማር መንቀል! እስከዛሬ ስንት ሚስማር የነቀልኩ ይመስልሃል? አንድ ሚሊዮን ይሆናሉ። ኢንጂንየር የነበርኩ ሰው ነኝ። እና አሁን ሚስማር መንቀል...."

"ዋናው ጉዳይ አላማ ነው! አላማ ካለህና ገንዘብ አጠራቅመህ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰህ የራስህን ድርጅት ለመክፈት ከቻልክ የዛሬው ጉዳት ለነገ ጥቅም ከዋለ..."

እጁን አንስቶ አስቆመኝ! ከዚያም ጣቱን አፉ ላይ በማኖር "ዝም በል" አለኝ። ዝም አልኩ።

"እንጠጣ" አለኝ።

ዝም ብለን መጠጣት ቀጠልን!

በአንድ የቻይናውያን አነስተኛ አምፖል ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ መምህር የነበረ ሰውም አጋጥሞኛል።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አምፖሎቹ እንደሚበሩና እንደማይበሩ መሞከር ነው ስራው። በቀን ስፍር ቁጥር የሌላቸው አምፖሎችን የሚሞክር ሲሆን የስራው ጠባይ ሊያሳብደው እንደደረሰ አጫውቶኛል።

"አንተ እንዲያውም እድለኛ ነህ" አልኩት "ቁጭ ብለህ አምፖል መሞከር ጥሩ ስራ ነው፤ አይደክምህም!"

ከት ብሎ ከመሳቅ ባሻገር ምንም አስተያየት አልሰጠኝም። አሁን ሳስበው ግን ከባድ ሊሆን እንደሚችል ገምቻለሁ። መሞከሪያው ላይ ስትሰካቸው ይበራሉ። ካርቶን ውስጥ ትከትና ሌላ አምፖል ታነሳለህ። አምፖሎቹ አያልቁም። ዝንተ አለም! መቸም ይህን የመሰሉ ስራዎች በሃገርህና በወገንህ መሃል ብትሰራው ባልከፋ። በባእድ አገር መሆኑ ግን ህይወትን አሰልቺ ያደርጋታል። አንጎልህን ባልተጠቀምክበት ቁጥር ደግሞ በየደቂቃው ብዙ ሺህ ሴሎች ከስራ ውጭ እየሆኑ ይሄዳሉ።

በመጨረሻስ? ደግነቱ ከመጨረሻው በፊት ህይወት እንደ አምፖል ትቃጠላለች።

* * *

የኔ የመመለስ ዜና ይፋ እንደሆነ በኔና በእጮኛዬ መካከል ጣልቃ ለመግባት ፊራ ተባ ይሉ የነበሩ የሲያትል ጎረምሳ አበሾች ሳይቀደሙ ለመቅደም ሽሚያ መጀመራቸውን አስተዋልኩ።

መጀመሪያ ድንጋጤ አደንዝዞኝ ነበር። ትዳር ያላቸው ሳይቀሩ ይንከባከቧት መጀመራቸውን ሳይ ቅናት ያነፍረኝ ጀምሮ ነበር። እጮኛዬ ወደ ኢትዮጵያ እንደማትመለስ እንቅጩን ስለነገረችኝ፣ ፍቅራችን ያለቀለት መሆኑን ተገንዝቤው ነበር። ግን ገና ሳልመለስ ሽሚያው መጀመሩ ነበር ያሳበደኝ። ሆኖም ክስተቱን ቀለል አድርጌ ለማየት ወሰንኩና ወዳጅ መስለው ቤታችን የሚያንጎራብቡትን ጎረምሶች ችላ አልኳቸው። ከሁሉም አስቂኙ ነገር ግን ወደ ቤታችን የሚመጡበት ምክንያት 'ለኔ አንዳንድ ስጦታ ለመስጠት' በሚል መሆኑ ነበር። ለህይወት ይህንኑ ነገርኳት፣

"አንቺን ፈልገው ነው የሚመጡት" ስላት ተቆጣችኝ።

''ወዳጆቻችን ናቸው፣ እንደዚያ ማሰብ ተገቢ አይደለም''

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እሷም ሽሚያውን ወዳው ሊሆን ይችላል ብዬ ጠረጠርኩ። የመሄጃዬ ጊዜም እየተቃረበ መጣ።

አንድ ቀን ህይወት ከምትሰራበት ሬስቶራንት ሄጄ ከስራ እስክምትወጣ እየጠበቅሁዋት ሳለ፤ አንድ ትዳር ያለው ጎረቤታችንም መጥቶ በሌላ ወገን መኪናውን አቆመ። የስራ መውጫዋን ሰአት ተረድቶ እንደመጣ ተገንዝቤ፤ ንዴቴን ዋጥ አድርጌ የሚሆነውን ለማየት እጠብቅ ጀመር።

አስራ አንድ ሰአት ላይ ወጣች!

ከኔ ጋር ቀጠሮ ስለነበረን በቀጥታ ወደኔ በመምጣት ላይ ሳለች፤ የኔን መኖር ያልተረዳው ጎረቤታችን፣ የመኪናውን ጥሩምባ ነፋ።

አየችው! አየችኝ! ግራ ገባት። እሱ አላየኝም። ከመኪናው ወረደና ወደሷ አመራ። እኔም ተነሳሁና ወደሷ ሄድኩ። ልክ ሲያየኝ እንደ አላስካ በረዶ ደርቆ ቀረ። እኔ ሳቅሁኝ። ሳቅሁ ከማለት እንኳ አገጠጥሁ ብል ይሻላል። ተቃጥዬ ነበር። እሱ ለማስመሰል እየሞከረ መጥቶ ሰላምታ አቀረበልኝ፣

"ምን ልታደርግ መጣህ!" አልኩት በቀጥታ።

"እግረመንገዴን ልሸኛት ብዬ ነው ... በዚህ ሳልፍ..."

"ቤታችን ቅርብ ነው፤ ምን መሸኘት ያስፈልጋል?"

"ማለቴ..." እያለ ተንተባተበ።

ክልስ ነገር ሲሆን፤ ሽቶ መታጠብ የሚወድ ዋልጌ አይነት ሰው ነው። ምንም ጥፋት እንዳልሰራ ተሰናብቶን ወደመኪናው እየሄደ ሳለ፣

"ሚስትህ ቆንጆ ናት" ስል ጮህኩ።

ሚስቱን አውቃታለሁ። ሃይማኖተኛና የማደንቃት አይነት ሴት ነበረች። ክልሱ ቆመ። ዘወር አለና አየኝ። አላመነታም! ተመልሶ ወደኛ መጣ፣

"ይህ አሜሪካ ነው" አለኝ።

"እና!?"

"ነገሮችን ቀለል አድርገህ ለማየት ሞክር!"

ምክሩን አልተቀበልኩትም። ይህን የመሰለውን ባህርይ ከመለማመድ በተወለድኩበት የገበሬዎች መንደር ተመልሼ መኖርን የምመርጥ አይነት ሰው ነበርኩ። እጮኛዬ በኔና በክልሱ መካከል በተፈጠረው መፋጠጥ ደንግጣ ትንፋሽ አጥሮአታል፣

"ጨርሰናል!" አልኩት "...ሚስትህ ትበቃሃለች!"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ፊቱ ከክልስነት ወደ አመድነት ተለውጦ አንዳችም ቃል ሳይተነፍስ ጀርባውን ሰጥቶኝ ጥቁር ስትሽንዋገኑን አስነስቶ ሄደ።

ከህይወት ጋር በዝምታ ማዝገም ጀመርን። ደንግጣለች። የተምታታ ስሜት ውስጥ ገብታለች፣

"እሱ የፈለገውን ቢያደርግ እኔ ካለፈለግሁ ምንም ሊያደርግ አይችልም። ለምን እንደዚያ ትናገረዋለህ?" አለችኝ።

"ምን እንዳደርግ ትጠብቂ ነበር?"

መልስ አልሰጠችኝም። ዘግይታ ግን ፊትዋ ሲለዋወጥ አየሁ፣

"እኔ በጣም እወድሃለሁ" አለችና እንባዋ ተዘረጋገፈ።

እቅፍ አደረግሁዋት!

"እኔም አፈቅርሻለሁ!" ስል ተነፈስኩ።

ከልቤ ግን አልነበረም። የሚያጅቧትን የማስተናገድ ዝንባሌ ስላየሁባት ልቤ ሻክሮ ነበር። ሌላ ቃላት ሳንጨምር ቤታችን ገባን። ጥሩ ራት ሰራችና በላን። በፍቅር አወራን። በፍቅር፤ በሞቀ ፍቅር አደርን። ለዘላለሙ እየተለያየን እንደሆነ ሁለታችንም ስላወቅነው ቀሪዋን ጊዜ በጥሩ ሁኔታ አሳለፍናት።

በነጋታው ከስራ ቀረችና ፌየሪ በተባለችው ድልድይ መርከብ ተሳፍረን አንድ ሰአት ያህል ሰላማዊ ውቅያኖስ ላይ ተንሳፈፍን። የጀርመን ትላልቅ መርከቦች ወደ ሲያትል ወደቦች ሲጠጉ ፀሃይቱን ከለሏት። በትርኢቱ እኔ በደስታ ጮህኩ። ማምሻውን ደግሞ Lake city በተባለው ቀበሌ የሚገኘውን ሰው ሰራሽ ሃይቅ በዝግታ ርምጃ ዞርነው። በዚያች ደቂቃ በርግጥ በእጮኛዬ ልብ ምን እንደነበር ሙሉ በሙሉ ባላውቅም ስሜቷን ያለስስት ሰጥታኝ እንደነበር ግን አምናለሁ።

በአካባቢያችን የነበሩት ጎረምሶች እሷን መከታ-ተልና ማጀባቸውን ያጠናከሩ መሆናቸውን እያየሁ እንዳላየሁ ሰነበትኩ።

በመጨረሻ ጊዜው ደረሰ።

ሻንጣዎቼን በመፃህፍት ሞልቼ ከአይሮፕላን ጣቢያው ለመገኘት በቃሁ። ከህይወት ጋር ለአስር ደቂቃ ያህል ተቃቅፈን ተላቀስንና ለዘልአለሙ ተሰነባበትን። ለዘልአለሙ!

* * *

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አዲሳባ እንደተመለስኩ ማህበራዊ ህይወቴን ጥርቅም አድርጌ ዘግቼ፣ ሙሉ ጊዜዬን በማንበብና በመፃፍ ስራ ላይ አደረግሁ። ከወራት በሁዋላ አንድ ሌሊት፣ "*የቡርቃ ዝምታ*" የሚል ቃል አንድ ብጫቂ ወረቀት ላይ አሰፈርኩ። ርግጥ ነው የቡርቃ ዝምታን ለመፃፍ ካቀድኩ አመታት አልፈው ነበር። ከአሜሪካ ከተመለስኩ በሁዋላ ግን እንዴት እንደምፅፈው በትክክል ለማወቅ ቻልኩ።

* * *

ከዚያ ወዲያ አሜሪካ ላይ ስለተውኳት ስለዚያች ቆንጆ ወሬ የሰማሁት ግን ዳግም ለዳግም ስደት ተዳርጌ ፕሪቶሪያ ከከተምኩ በሁዋላ ነበር። ግዮን ሆቴል ሰርግ ደግሳ ጋብቻ መፈፀሟን የወሬ ወሬ ሰማሁ። አምላክ ትዳሯን ይባርክላት! እኔ የማፈቅራትን ያህል ባልዋ ያፈቅራት ዘንድም እመኝላታለሁ...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 23 -
ኢብሳ አልሞተም!

ገፈርሳ ሂዶ - እንጨት መስበር ቀረ፣
ሁሩፊ ቦምቢ ላይ - ጥጆች ማገድ ቀረ፣
እንጦጦ ላይ ሆኖ - መስኩን ማየት ቀረ፣
ከብቶችን ፊንፊኔ ወስዶ - ሆራ ማጠጣቱ ቀረ፣
ዳለቲ ላይ - የጉለሌዎች ሽንጎ ቀረ፣
ሰዎቹ ከመጡ ወዲህ - የኛ ነፃነት ቀረ፣

(የኦሮሞ ህዝብ እንጉርጉሮ)

የፋሲካን በአል ደርባን ከተማ ላይ ለማክበር እየተጓዝኩ ነው። ቢንያም መስፍን የተባለው ጓደኛዬና ቤተ ሰቡ ደርባን ይጠብቁኛል። በጊዜ ለመድረስ ወደዚያው እየከነፍኩ ነበር።

* * *

ሌዲስሚዝ ከተባለችው መንደር ከመግባቴ በፊት አበሾች የሚመስሉ ሁለት ወጣቶች ከመንገዱ ዳር ቆመው እጃቸውን እያወዛወዙ አልፈዉያቸው ሄድኩ። በፕላስቲክ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከረጢት የታሸጉ የቻይና አልጋ ልብሶችን እንደ ተራራ የጫነች ፒካፕ ከአስፓልቱ ዳር ቆማለች። ተበላሽታባቸው ሳይሆን እንዳልቀረ በመጠርጠሬ ወደ ሁዋላ ተመለስኩ!

የገብርኤል ያለህ! ኢብሳ ገዳ!

የመኪናዬን በር ከፍቼ ወርጄ ጮህኩ!

"ኢብሳ ገዳ አይደለህም'ንዴ!?"

"አዎን ነኝ!" አለ ግራ እየተጋባ።

"አታውቀኝም እኔን!?" ስል በስሜት ጮህኩ!

"ይቅርታ! አላወቅሁህም!" አለ ግራ ተጋብቶ!

"Dheekamsa Burqaa hirraanfattaa?" አልኩት።

"የቡርቃን ቁጣ ትረሳዋለህ!?" ማለቱ ነበር።

ኢብሳ ከኔ በላይ ጨኸቱን ለቀቀው።

እኔ በበኩሌ የሞተ ወንድሜ ከመቃብር ወጥቶ ያየሁት ያህል ተሰምቶኝ ነበር። የኢብሳ ገዳ ስሜት ግን ከኔ በላይ ሆኖ ነበር። የሚናገረው ቃል ጠፋው። ተቃቅፈን ካበቃን በሁዋላ፤ ፊቱን በሁለት እጆቹ ሸፍኖ መሬት ላይ ተቀመጠ። አብሮት የነበረው ሌላኛው ወጣት የሚናገረው ጠፍቶት ፈዝዞአል። ኢብሳ ካቀረቀረበት ቀና እንዲል ብዙ ጥረት አደረግሁ።

"እንኳን በህይወት አየሁህ! እኔስ ሞተሃል ብዬ ነበር!"

ኢብሳ መልስ አልሰጠኝም!

አጠገቡ እኔም መሬቱ ላይ ቁጭ ብያለሁ። ከፊት ለፊታችን የበቆሎ እርሻ ተዘርግቶአል። ኮረብታ የመሰለ ግዙፍ ነጭ ደቡብ አፍሪቃዊ ገበሬ በማሳው መሃል የቆመች ጥቁር ቼቭሮሌት ተደግፎ ሲጋራ ያጨሳል። መኪኖች በነፋስ ፍጥነት ወደ ደርባን አቅጣጫ ይከንፋሉ። ነፋሻ ነው አየሩ...

በመጨረሻ ኢብሳ ቀና አለ፣

"ይቅርታ!" ሲል ተነፈሰ።

"ምንም አይደለም። ስሜትህ ይገባኛል" አልኩ።

* * *

ከኢብሳ ገዳ ጋር እንዴት እንደተዋወቅን ላውጋችሁ፣

በ1992 የክረምቱ ወራት ማብቂያ ላይ አንድ ማለዳ የፀጥታው መስሪያ ቤት ባለስልጣን ክንፈ ገብረመድህን ወደ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ቢሮው አስጠርቶ እንዲህ አለኝ፣

"አንድ ከበድ ያለ ስራ ልሰጥህ እፈልጋለሁ!"

"መልካም!" አልኩ ልሰማው እየተዘጋጀሁ። ክንፈ ቀደም ሲል አያሌ ምስጢራዊ ስራዎችን ያሰራኝ በመሆኑ ለምጄዋለሁ። የዛሬው አነጋገሩ ግን በመጠኑ ስጋት አሳደረብኝ። ልቤ ቆሞ አይን አይኑን እመለከተው ጀመር።

ክንፈ ቀጠለ፣

"አንድ የኦነግ ሰው እስር ቤት አለ። የሚያውቃቸው ሚስጥሮች መኖራቸውን ጠርጥረናል። ትንፍሽ ሊል ግን አልቻለም። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነው። የባሌ ጫካዎች ሲቃጠሉ እሳቱን ለማጥፋት የዘመቱትን ወጣቶች ካስተባበሩት አንዱ ነው። አደገኛ ልጅ ነው። እንዳልኩህ ከኦነግ ጋር ግንኙነት አለው ብለን ጠርጥረናል። መስመሩን ልናገኝ ግን አልቻልንም። ከኦህዴድ ባለስልጣናት መካከል ከዚህ ልጅ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችል ስሞችን አግኝተናል። የተረጋገጠ መረጃ ባለመሆኑ ግን ርምጃ ለመውሰድ አልቻልንም። ብንገለብጠውም ትንፍሽ አላለም። ብዙ ሙከራ አድርገን ነበር። እስቲ አንተ ደሞ ሞክረው?" አለኝ ትክ ብሎ እያየኝ።

በጣም ደነገጥሁ።

"እኔ ጋዜጠኛ ነኝ ክንፈ። እንዴት ልመረምረው እችላለሁ? ምን ላደርግ እችላለሁ?"

ክንፈ ባልተለመደ ጠባዩ ረጋ ብሎ ሲያስብ አስተዋልኩት።

"ምን መሰለህ?" ሲል ቀጠለ "...ይህ ልጅ የቡርቃ ዝምታን አንብቦታል። ከጥቂት የዩኒቨርሲቲ ኦሮሞ ተማሪዎች ጋር ተሰባስቦው በመፅሃፉ ላይ ግምገማ ማድረጋቸውንም መረጃ አግኝተናል። በምርመራ ወቅት ስለዚሁ ጉዳይም ጠይቀነው ነበር። 'የቡርቃ ዝምታን የፃፈው የናንተው ካድሬ ነው። ሂዳችሁ እሱን ጠይቁ እንጂ እኔን ለምን ትጠይቁኛላችሁ!' ሲል ምላሽ ሰጠ። የሆነው ሆኖ ምናልባት አንተን ሊያምንህ ይችላል። ገብተህ አነጋግረው። እኛን እያጥላላህ ቅረበው። 'ለታሪክ የሚቀር ስለሚሆን የምታውቀውን ንገረኝ' ብለህ አግባባው። ይገድሉኛል ብሎ ተስፋ የቆረጠበት ሁኔታ ላይ ስላለ አንዳንድ ነገሮች ሊነግርህ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ይችላል። 'የቡርቃ ዝምታን የፃፍከው አንተ መሆንህን ካወቀ ሊጠራጠርህ አይችልም"

ዝግ ብዬ አሰብኩ።

የተለያዩ አሳቦች ወደ አይምሮዬ እየዘለሉ ገቡ። በህይወቴ ሙሉ እንደዚያች ደቂቃ ፈታኝ ሁኔታ ገጥሞኝ አያውቅም።

ገና ከመነሻው የቡርቃ ዝምታን ለምን እንደፃፍኩት ክንፈ ራሱ እንዳልገባው ተረዳሁ። እኔ ኦሮሞ ባልሆንም በኦሮሞ ህብረተሰብ መሃል ያደግሁ ሰው ነኝ። ደጋጎቹና ድንቅ አእምሮ ያላቸው፣ ቅንነት መለያቸው የሆኑት ኦሮሞዎች ጎረቤቶቼ ነበሩ። ከወደዱህ የራሳቸው የሚያደርጉህ፣ ከጠሉህ ደግሞ ሰሜታቸውን መደበቅ የማይቻላቸው የኦሮሞ ገበሬዎችን በቅርብ አውቃቸዋለሁ። ከቢሾፍቱ የገጠር መንደሮች ወደ ቅዳሜ ገበያ ሸቀጣቻቸውን ጭነው የሚያልፉት በኛ በራፍ በኩል ነበር። ሸለሸል የተባለ ኩበት፣ ዶሮ፣ እንቁላል፣ ቁርጥራጭ የማገዶ እንጨት፣ በቅጠል የተጠቀለለ ቅቤ፣ በግና ፍየል፣ ጭድ፣ የገብስ ገለባ፣ እህል፣ ጥራጥሬ፣ የአተርና የሽምብራ እሸት፣ ወደ ገበያ ይዘው በቤታችን ደጃፍ ያልፋሉ። እናቴ ኦሮምኛ ትናገራለች። ከአካባቢው ኦሮሞዎችና ምንጃሬዎች ጋር ጥሩ ዝምድና ነበራት። ኦሮምኛ ለመናገር በመሞከርዋ ደግሞ ኦሮሞዎቹ የበለጠ ይወዱዋት ነበር። ነጭ ጤፍ ተከራክራ ትገዛቸዋለች። "ሽቃባ መስፈሪያ" "ቂጡ የጎደጎደ" "አያዋጣም" "ኪሳራ ነው" እያሉ ሲከራከሩ እስካሁን ትዝ ይለኛል። እናቴ አንድ ዶሮ በሶስት ብር ከሃምሳ ስትገዛቸው፣ አምስት እንቁላል ይመርቁላታል። እናቴ ደግሞ ከገበያ ሲመለሱ ጠብቃ፣ "ግቡና ቡና ጠጡ" ትላቸዋለች። ይህ ሁሉ የልጅነት ትዝታ ዛሬም ድረስ ወለል ብሎ አእምሮዬ ላይ ታትሞአል።

በዚያን ዘመን የእናቴን ቀሚስ አንቄ ይዤ ሁሉን አዳምጥ፣ ሁሉም ደግሞ በደመነፍስ አእምሮዬ ላይ እየተሳለ ነበር። አንዳንድ ጊዜ የጋራበሩ ገበሬዎች በኛ ደጃፍ ሲያልፉ በራችንን ያንኳኩና፣

"ሸለሸል ይዘናል። ገበያ ከሄድን አምስት ብር ያወጣል! ላንቺ ግን በአራት ብር ውሰጂው!" ይሉዋታል። እናቴ ደግሞ ካልተከራከረች መግዛት አትወድም።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ርግጥ ነው ይሄ ሽለሸል አምስት ብር ያወጣል። ያለኝ ግን ሶስት ከሃምሳ ብቻ ነው” ትላለች።

ወዲያው ይስማሙና “ሽለሸሉ እስኪራገፍ... ቡና ጠጥታችሁ ትሄዳላችሁ” ትላቸዋለች።

ቡና ሲጠጡ፣ የቡና ቁርስ ሃምባሻ ይቀርባል። በብዛት የሚያወሩት ስለ ኑሮ ውድነትና ስለ ልጆቻቸው ነበር። አምስት እንቁላል እንደምርቃት እየተቆጠረ፤ ስለ ኑሮ ውድነት ረጃጅም ወጎች ኣሏቸው። ስለታመሙ ሰዎችና ስለ ህመሞቻቸውም ያወጋሉ። እናቴ የመድሃኒት ማስቀመጫ ሳጥንዋን በኩራት ከፍታ ምንነታቸው ያልታወቁ የከረሙ ኪኒኖችን ቆንጥራ ትሰጣቸዋለች። ማንኛውንም መድሃኒት ማጠራቀም የምትወድ ሲሆን፣ ራስዋን እንደ ዶክተር ለማሰብም ይቃጣታል። ያለማመንታት ለማንኛውም በሽታ መድሃኒት የምትሰጥ ሴት ነበረች።

“...ሆድ ቁርጠት ነው ያመመዎት? ምን ችግር አለ? ይቺን ይዋጡ። እኔ ይቺን ውጬ ተሽሎኛል። ጨጓራዎትን ያቃጥሎታል? በርበሬ እንዳይቀምሱ...ፊልቶ የቀዘቀዘ ወተት ይጠጡበት። ሽሮፕ አለኝ ቆይ...” ሃኪም ለራስዋ ከሰጣት ሽሮፕ በብልቃጥ ቀንሳ ትሰጣቸዋለች “...ይቺን ማታ ይጠጡና ጥቅልል ብለው ይተኙ። ልጆች እንዳይንጫጩ ያድርጉ። ዋናው የጨጓራ በሽታን የሚያባብስ የልጅ ጫጫታ ነው” እናቴ ወደኔ መልከት ታደርግና ታክልበታልች፣ “... ይሄ እንኳ ፈዛዛ ቢጤ ነው። አፉን ከፍቶ አጠገቤ ተጎልቶ ይውላል” ጠጉሬን እያሻሸች ትቀጥላለች፣ “...የዚህ ታናሽ ግን ግልገል ሰይጣን ነው። እሱ ሲረብሽ ጨጓራዬ ይብስብኛል...”

ገበሬዎቹ እናቴን ያምኑዋታል። የሶስት ብር ከሃምሳ ሽለሸል ሸጠው፣ ቡና ጠጥተው፣ ሃምባሻ በልተው፣ ለህመማቸው መድሃኒት ተቀብለው ይመለሳሉ። ገበሬዎቹ በሚቀጥለው የገበያ ቀን ሽቀጣቸውን ይዘው በበራችን ሲያልፉ እንደገና በራችንን ይደበድባሉ። በፍፁም ውለታ አይረሱም።

አንድ ቀን በሩን እኔ ስከፍት ሁለት አህዮችና አንድ በእድሜ የገፉ ኦሮሞ ሴት ቆመው ነበር፣

“እናትህ አለች?”

“የለችም”

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“የት ሂደች?”

“ገበያ”

“በል ይህንን ስጣት! እንዳትጥለው፤ በደንብ ያዘው! ለጋ ቅቤ ነው። ለጠጉርሽ ነው ብለህ ንገራት! ባለፈው የሰጠሽኝ መድሃኒት በሽታዬን ሁሉ ድራሹን አጥፍቶታል ብለህ ንገራት። ከገበያ ስመለስ በዚህ አልፋለሁ፤ እንዳትረሳ”

የቡርቃ ዝምታን ስፅፍ እነዚህ ኦሮሞ ገበሬዎች አእምሮዬና ልቤ ውስጥ ነበሩ።

ይሸው አሁን ክንፈ አንድ የኦሮሞ ተማሪ ገልብጠ ሲደበድብ መክረሙን ይነግረኛል። እናም ያን በዱላ የተሰባበረ ወጣት እንድሰልል ያማክረኛል። ክንፈ የህወሃት ፖሊት ቢሮ አባልና የፀጥታው መስሪያ ቤት ሹም በመሆኑ ለኔ የአለቃዬም አለቃ ነው። በልቤና በአእምሮዬ ውስጥ ፅኑ የፍቅር መሰረት እየገነባ ያሳደግኝን ህብረተሰብ እንድሰልልለት ሲጠይቀኝ ግን በእውነቱ አዝኜ ነበር። የሆነው ሆኖ ፈጣን ምላሽ ሰጠሁት።

“መልካም፤ እሞክራለሁ!”

በእጅጉ ተጎድቼ ነበር። ድርጊቱን እንደማልፈፅመው ባውቅም ስለተጠየቅሁ ብቻ ቆጨኝ።

እስረኛውን የማነጋግርበት ቀጠሮ ተያዘና ከክንፈ ጋር ተለያየን።

ኢብሳ ገዳ ከኢሲኤ ጀርባ ከሚገኘው የደህንነቱ ምስጢራዊ እስርቤት አንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ ወንበር ላይ ተቀምጦ ነበር የጠበቀኝ። ገፅታው ተዳክሞአል። ፊቱ ላይ ቁስል ባይታይበትም አቀማመጡ መጣመሙን አስተዋልኩ። ያደፈና የተጨማደደ ነጭ ሸሚዝ ለብሶአል። በተገጣጠበ ሁኔታ ፀጉሩ ተላጭቶአል። የግራ አይኑ እንደ እሳት ቀልቶ የጥላቻ ረመጥ ይተፋል። የቆሰለ አውሬ መስሎ ተሰማኝ።

ሙሉ ስሜን በመንገር ተዋወቅሁት። አንዳችም ድምፅ ሳያሰማ በዝምታ ያስተውለኛል። ከአይኖቹ የሚወረወሩት የጥላቻ ቀስቶች ውጋት ለቀቁብኝ። ስሜን በአግባቡ አልሰማውም ብዬ በማሰብ መታወቂያ ወረቀቴን አውጥቼ ፊቱ አስቀመጥኩለት። መታወቂያዬን እንደዋዛ ተመለከተ። ግንባሩን ሲቋጥርና ሲፈታ ተመለከትሁ። ገፅታው ላይ ለውጥ አየሁ። “አውቆኛል” ብዬ ገመትኩ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደተጠራጠረ ግን መገመት ቻልኩ።

"ቃለመጠይቅ እንዳደርግህ የፀጥታው መስሪያ ቤት ፈቅዶልኛል። ከኔ ጋር ነፃ ሆነህ እንድንነጋገር እፈልጋለሁ" አልኩ ድምፄን ከፍ አድርጌ።

ቀደም ብዬ ተዘጋጅቼበት ስለነበር ከማስታወሻ ደብተሬ ውስጥ አንድ ወረቀትና ብእር አውጥቼ ወደፊቱ ገፋሁለት። ወረቀቱ ላይ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ፅፌ ነበር።

"እኔ ራሴ ነፃ አይደለሁም። እዚህ ክፍል ውስጥ የድምፅ መቅጃ መሳሪያ ሊኖር ይችላል። ቃለመጠይቅ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆንህን ገልፀህ አሰናብተኝ" የሚል ፅሁፍ አስፍሬ ነበር።

ኢብሳ ገዳ ፈገግ ሲል አየሁት። በአይን ተግባባን። በደንብ ተግባባን። ከዚያ በሁዋላ ለማማሸ ሰአት ያህል ድራማ ሰራን። ላግባባው ሙከራዬን ቀጠልኩ። ኢብሳም ድምፁን ከፍ አድርጎ ይሟገተኛል።

"የቡርቃ ዝምታን የፃፍኩት እኔ ነኝ። እኔን ልታም ነኝ ይገባል። ወያኔ ሊገልህ ይችላል። ስለዚህ ለታሪክ የሚቀሩ ምስጢሮችህን ንገረኝ። በኦሮሞ ህዝብ ስም እምልልሃለሁ! ምስጢሩን ጠብቄ እቆያለሁ" እያልኩ ዘላበድኩ።

እሱም በተመሳሳይ፣

"እኔ ኦነግ አይደለሁም። የኦሮሚያ ጫካ ሲቃጠል እሳቱን ለማጥፋት ለዘመቻ አስተባብሬያለሁ። ይሄን መፈፀም እንዴት ኦነግነት ይሆናል? 'ከኦህዴድ ባለስልጣናት መካከል ማነው ካንተ ጋር የሚገናኘው?' እያሉ ይደበድቡኛል። ማንንም አላውቅም። የሃሰት ስም እንድጠራላችሁ የምትፈልጉ ከሆነ አባዱላ እላችሁዋለሁ። የማንን ስም እንድናገር ነው የምትፈልጉት?"

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ክንፈ ዘንድ ቀረብኩ፣

"ፈቃደኛ አይደለም" አልኩት "...እንደሚመስለኝ ግን ስሜታዊ ሆኖ እንቅስቃሴዎችን ያደርግ ይሆናል እንጂ የተደራጀ መስመር ይኖረዋል ብዬ አልገምትም"

እኔና ኢብሳ ስናወራ የነበረውን ክንፈ ቢሮው ተቀምጦ ሰምቶን ይሆናል ብዬ ገምቻለሁ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ክንፈ እንደተለመደው ጥቂት ቀላልዶ አሰናበተኝ። ወደ ቢሮዬ በመመለስ ላይ ሳለሁ አንድ ጥርጣሬ አእምሮዬ ላይ ብልጭ አለ። ክንፈ እኔን ይሆን የሰለለኝ? ኢብሳ በድብደባ ብዛት ያልተናገረ፤ የቡርቃ ዝምታን ስለፃፍኩ ብቻ እንዴት ለኔ ምስጢር ይነግረኛል? ክንፈ ሚስጥር የፈለገው ከኢብሳ ሳይሆን ከእኔ ሊሆን እንደሚችል ጠረጠርኩ። ርግጠኛ ለመሆን ግን አልቻልኩም። ክንፈ በዚያች ክፍል ውስጥ የድምፅ መቅጃ ማኖር አለማኖሩንም ቢሆን ርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም። እንደዚያ እንደሚያደርጉ ግን ቀደም ሲል ክንፈ ራሱ አጫውቶኛል። የእሳት ቃጠሎውን የማጥፋት ዘመቻ ከተከናወነ አስራስምንት ወራት ያለፈው በመሆኑ ኢብሳን ያሰሩት በቀጥታ ከዚያ ዘመቻ ጋር የተያያዘ ሊሆን እንደማይችል ገምቻለሁ። ክንፈ እንደነገረኝ አነግ አህዴድ ውስጥ የዘረጋውን መረብ ከኢብሳ ለማግኘት እየጣሩ ይሆን? በዚህ ጉዳይ ላይስ ክንፈ እኔን ማሳተፍ ለምን ፈለገ?

ዝብርቅርቅ ባለና በተምታታ ሃሳብ ተዘፍቄ ሰነበትኩ። በራሱ በክንፈ ትእዛዝ ለእስረኛው የተናገርኩትን ፀረ - ወያኔ ቃላት እንደማስረጃ ይዞ መልሶ ቢወነጅለኝስ?

እየቆየሁ ግን በአእምሮዬ ያደረውን ውዥንብርም ሆነ ኢብሳ ገዳን እየረሳሁ ሄድኩ። ኢብሳ ከእስር ይፈታል ብዬ ግን አልጠበቅሁም ነበር። ሞቶአል ብዬ ደምድሜ ነበር። ይኸው አሁን የደቡብ አፍሪቃ ምድር ላይ አገኘሁት።

* * *

አብሮት የነበረ ባልደረባውን ከተበላሸችው መኪና ጋር በመተው እኔና ኢብሳ መካኒክ ፍለጋ ወደ Ladysmith ጉዞ ጀመርን። ብቻችንን እንደሆንን ፋታ አጥቼ የደረሰበትን ይነግረኝ ዘንድ ወተወትኩት።

"አንተ ካነጋገርከኝ በሁዋላ በሁለተኛው ሳምንት ለቀቂኝ" ሲል አጫወተኝ። "...በቀጣይ ማንኛውም አመፅ ውስጥ አልሳተፍም' የሚል ወረቀት አቀረቡልኝና ፈረምኩ። ከዚያም አሰናበቱኝ"

ኢብሳ አያያዘና ከእስር ከተፈታ በሁዋላ ወደ ቦረና ገብቶ ከአነግ ሰራዊት ጋር መቀላቀሉን አጫወተኝ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በደህንነቱ መስሪያ ቤት በደረሰበት ድብደባ ምክንያት የግራ እግሩ ላይ የጡንቻ መሸማቀቅ እንደገጠመውና ከሁለት ወራት በፊት ለህክምና ደቡብ አፍሪቃ መምጣቱን፣ እዚህም ከጓደኞቹ ዘንድ ማረፉን፣ ህክምናውን ሲጨርስ ግን ወደ ባሌ ጫካ እንደሚመለስ አወጋኝ።

በመካከሉ የከነከነኝን አንድ ጉዳይ አነሳሁበት፣

"ከአህዴድ ባለስልጣናት ጋር ግን ግንኙነት ነበረህ?"

ኢብሳ ፈገግ አለ።

"አዎን ነበረኝ! ሆኖም ለመሞት ዝግጁ ነበርኩ። ከኔ አንዳችም ምስጢር እንደማያገኙ ርግጠኛ ነበርኩ"

"ብዙ ደበደቡህ?" ስል ጠየቅሁት።

"ከባድ ነበር" አለ ፊቱን አጨፍግጎ "ደርግ ይጠቀምበት ነበር የሚባለውን የምርመራ ዘዴ ሁሉ ይጠቀማሉ። ገልብጠው የውስጥ እግሬን ገርፈውኛል! ቆሻሻ ውሃ የሞላ በርሜል ውስጥ እየደፈቁ ምስጢር ለማግኘት ሞክረዋል። የመግረፊያ ጉማሬም አላቸው"

ኢብሳ ሸምቅቅ እያለ አጫወተኝ። የደረሰበት ግፍና ሰቆቃ ገና ጥሎት እንዳልጠፋ ከድምፁ ይታወቅ ነበር።

"መቋቋም መቻልህ የሚደንቅ ነው። ጠንካራ ሰው ነህ!" አልኩት።

ኢብሳ ተክዞ ጥቂት ቆየና፣

"ሲደበድቡኝ ያለ ማቋረጥ ዳውድ ኢብሳን አስታው ሰው ነበር። በደርግ ጊዜ እሱም ልክ በዚህ መንገድ ማለፉን አውቅ ስለነበር፣ ያለማቋረጥ እሱን እያሰብኩ ለራሴ ውስጣዊ ሃይል እፈጥር ነበር..."

* * *

ይህ ወጣት ስለ ዳውድ ሲያነሳ በትዝታ ወደ ሁዋላ መለሰኝ፣

"ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ" የተባለውን መፅሃፍ በማዘጋጀት ላይ በነበርኩበት ጊዜ፤ በኔ በኩል ቅፅ ሶስት ላይ ለማተም ያዘጋጀሁት ሁለት ታሪኮችን ነበር። የህወሃት መሪ የነበረውን የስሁልን ታሪክና በወቅቱ የአነግ አመራር አባል የነበረውን የዳውድ ኢብሳን ገጠመኞች።

ክንፈና አለምሰገድ የስሁልን ታሪክ ቆራርጠው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንዲታተም ሲፈቅዱ፤ የዳውድ ኢብሳን ግን ውድቅ አደረጉብኝ። ክንፈ በተለመደው አነጋገሩ፣

"አነግ ሽብርተኛ ድርጅት መሆኑን እያወቅህ እንዴት የዳውድን ገድል ትዕፋለህ!?" ብሎ ተበሳጭቶ ጭምር ነበር።

ላግባባው ሞከርኩ፣

"እንዳልከው አነግ ሽብርተኛ መሆኑን አጥቼው አይደለም። ሆኖም መፅሃፉ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል እንዲነበብ፤ ባናምንበትም የዳውድ ታሪክ ቢገባ መልካም ነው" አልኩት።

አልተዋጠለትም! ከለከለኝ!

የዳውድን አስገራሚ የትግል ሜዳ ገጠመኞች ያገኘሁት ከዚያው ከክንፈ ቢሮ ሲሆን፤ በዚያን ወቅት የደህንነቱም ሆነ አባዱላ ገመዳ የሚመራው የወታደራዊ ደህን ነት ሰነዶች ለኔ በራቸው ክፍት ነበር። የፈለግሁትን ሰነድ የመመርመርና ወደቤቴ ተውሼ የመውሰድ ልዩ ፈቃድ ተሰጥቶኛል። ጀኔራል አባዱላ እንዳጫወተኝ ከኔ በቀር የታሪክ ሰነዶችን ለማየት የጠየቃቸው አንድም ሰው አል ነበረም።

እነ ክንፈ ዳውድን የተመለከተውን ትረካ እንዳይታተም ለማገድ የሚያበቃ በቂ ምክንያት አልነበራቸውም። እኛ አተምነውም አገድነውም በተለይ ወጣቱ ኦሮሞ የዚህን ሰው ገድል በኩራት እንደሚያውቁት አስተውያለሁ።

...ዳውድ ሆሮጉድሩ ነው የተወለደው። እንደ መለስ ዜናዊ የዊንጌት ተማሪ ነበር። መለስን በሁለት አመት ይቀድመዋል። አራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ስታትስቲክስ አጥንቶአል። ወላጆቹ የሰጡት ስም ፍሬው ይባል እንደነበር በወሊጋ አስተዳዳሪ በንጉሴ ፋንታ ስር የነበረው የደህንነቱ ቅርንጫፍ ለተስፋዬ ወልደስላሴ የፃፈው ሪፖርት ይጠቁማል።

በተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት ደርግ ለሁለት አመታት አስሮ ፈትቶታል። ከእስር ሲለቀቅ ወደ አነግ የትጥቅ ትግል ገባ። አነግ በ1968 ሃያ ስምንት የማእከላዊ ኮሚቴ አባላትን ሲመርጥ ዳውድ አንዱ ሆኖ ተመረጠ። በ1971 አነግ ትግሉን በምእራብ ኢትዮጵያ ለማስፋፋት ይወስናል። ዳውድ ኢብሳና የሌንጮ ለታ ወንድም አባጫላ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለታ ዋናና ምክትል ሆነው የምእራቡን ትግል እንዲመሩ ይመደቡና በጥቅሉ 17 ሆነው በሱዳን በኩል አቋርጠው ወለጋ በመግባት ቤጊ እና ጊዳሚ አካባቢ እንቅስቃሴ ይጀምራሉ።

ደርግ ይህን የኦነግን የምእራብ እንቅስቃሴ ለማፈን ትኩረት ሰጥቶ ማጥናት ይጀምራል። የጊዳሚ ወረዳ አስተዳዳሪ ሂካ መሳዲ እና የወለጋ ክፍለሃገር አስተዳዳሪ የነበረው ንጉሴ ፈንታ የትግሉን ጅማሮ ለማጨናገፍ አንድ መላ ይዘይዳሉ። በዳውድ ይመሩ ከነበሩት 16 ታጋዮች የአንዱ ወንድም ዘካርያስ ሾሮ ይባላል። ሂካ መሳዲ ዘካርያስን ጠርቶ ግዳጅ ይሰጠዋል።

"ወንድምህንና ጓደኞቹን ቤትህ ራት ጋብዛቸው። የምንሰጥህን መርዝ ምግቡ ውስጥ ትጨምርና ታበላቸዋለህ። ይህን የማትፈፅም ከሆነ ከነ ቤተሰብህ ትገደላለህ! ከብትህ ይዘረፋል! መሬትህን ታጣለህ! ዘርህ ከምድረ ገፅ ይጠፋል!"

ዘካርያስ ግዴታ ሆኖበት እንደተስማማ የደህንነቱ ሪፖርት ላይ ተጠቅሶአል።

"ወንድሜን እንዴት በመርዝ እገድላለሁ!" ብሎ አቅማምቶ ነበር።

"ከቻልክ ወንድምህን ለይተህ እንዳይበላ አድርገው። ካልተቻለ ግን አብሮ ይሙት! ወንድምህ ሃገር ሊያጠፋ የተቀጠረ ከሃዲ ነው" ሲሉ ፊት ለፊት ይነግሩታል።

የገበሬ ልብስ የለበሱ ወታደሮች በአካባቢው አድፍጠው ዘካርያስ ሾሮ እንዳያመልጥ ይጠብቁት ነበር። ምግብ ውስጥ የሚጨመረው መርዝ ከአዲስ አበባ ተልኮ በንጉሴ ፋንታ በኩል ለሂካ መሳዲ ተሰጠ። ሂካ መሳዲ ለዘካርያስ አስረከበው።

ዘካርያስ ለወንድሙና ለጓደኞቹ የራት ግብዣ ጥሪ ከላከባቸው በሁዋላ በግ አርዶ ጥሩ ምግብ አዘጋጀ። በዚያን ሰሞን 17ቱ የኦነግ ታጋዮች ለሁለት ተከፍለው ይንቀሳቀሱ ነበር። አባጫላ ለታ ዘጠኝ ራሱን ሆኖ በሌላ አቅጣጫ ይንቀሳቀስ ነበር። ዳውድና ቀሪዎቹ ታጋዮች የዘካርያስን የራት ግብዣ ተቀብለው ማምሻው ላይ በገበታው ዙሪያ ተገኙ።

ዘካርያስ ወንድሙን ለይቶ ማስቀረት ሳይቻለው ቀረ። "አንተ ቆይ ሁዋላ ትበላለህ" ቢለውም አሻፈረኝ ብሎ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለገበታው ቀረበ። ወንድሙና ጓደኞቹ በመርዝ የተለወሰውን ምግብ ሲበሉ ዘካርያስ የጎጆውን ምሰሶ ተደግፎ በትካዜ ይመለከታቸው ነበር። የዛሬው የአነግ ሊቀመንበር ዳውድ ኢብሳ ከምግቡ ጥቂት ቀማምሶ ሲያበቃ፣ ደጅ ጥበቃ ላይ የነበረውን ጓደኛቸውን ለመተካት ገበታውን ትቶ ወደ ደጅ ወጣ። ሌሎቹ መርዙን መብላት ቀጠሉ። ብዙም አልቆዩ፤ ታጋዮቹ ሰውነታቸው እንደ እሳት እየተቃጠለ እየጮሁ ይወድቁ ጀመር። ዘካርያስ የወንድሙን ራሳ እጁ ላይ ታቀፈ። ዳውድ ኢብሳ ብዙ የተመገበ ባይሆንም ከመመረዝ አላመለጠም። በጥበቃው ላይ እንዳለ ሰውነቱ ሲቃጠልበት፤ ቅጠላ ቅጠልና አፈር እየቃመ፣ ውሃ በብዛት ጠጣበት። ደግሞ ደጋግሞም አስታወከ። ሆኖም ከመውደቅ አልዳነም። ራሱን ስቶ እንደ ጓደኞቹ ከዘካርያስ ጓሮ ወደቀ።

የገበሬ ልብስ ለብሰው በአካባቢው አድፍጠው ውጤቱን ይጠብቁ የነበሩ ወታደሮች፤ በተያዘላቸው ቀጠሮ ዘካርያስ ቤት ሲደርሱ ሰባቱ ታጋዮች ሞተው፤ ዳውድ ኢብሳ ግን ነፍሱን እንደሳተ አገኙዋቸው። ዳውድን ይዘውት ወደ ደምቢዶሎ ከነፉ። የአነግን ምስጢሮች ከዳውድ ለማግኘት ፍላጎት ስለነበራቸው ፈጣን ህክምና ሰጥተው ህይወቱን አተረፉዋት። ከደምቢዶሎ ወደ ነቀምት አዘዋውረውትም ተጨማሪ ህክምና ሰጡት። ነቀምት ላይ እንዳገገመ፣ ወደ እስር ቤት ወስደው ገልብጠው ይገርፉት ጀመር። የወሊጋው የደህንነት ፅህፈት ቤት ሪፖርት እንደሚገልፀው ከዳውድ አንደበት አንዳችም ምስጢር ሊያገኙ አልቻሉም። ሲያቅታቸው ወደ አዲስ አበባ ማእከላዊ ላኩት። በቤንዚንና በቆሻሻ ውሃ የሞላ በርሜል ውስጥ እየደፈቁ መረመሩት። ለመሞት ዝግጁ ስለነበር አንዳችም የተነፈሰው አልነበረም። ደግመው ደጋግመው ማእከላዊና አለም በቃኝ እያመላለሱ በተለያዩ የማሰቃያ ስልቶች እንደመረመሩት የደህንነቱ መስሪያ ቤት ሰነድ በዝርዝር ያብራራል።

ዳውድ በአለም በቃኝ አምስት አመታት ታሰረ። ከመላመድ ብዛትም ዳውድ ጠባቂው የነበረውን ፖሊስ ማግባባት ቻለ። ለህክምና ሲወጡም ከሁለት ባልደረቦቹ ጋር ከሆስፒታል አምልጦ ወለጋ ገባ። የቤኒሻንጉልን ጫካዎች

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አቋርጠው ኦነግ ካለበት ለመድረስ የሁለት ሳምንታት የሌሊት ጉዞ አድርገዋል። ዳውድ መርዝ በልቶ ሲማረክ ምእራብ ወለጋ ጫካ ውስጥ የቀሩት አባጫላ ለታ እና ዘጠኝ ጓደኞቹ ከአንድ ብርጌድ በላይ ሰራዊት ሆነው ጠበቁት። የመሪያቸውን በህይወት መመለስ ማመን ያልቻሉት ታጋዮችም ዳውድን በታላቅ ደስታ ተቀበሉት....

"ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ" ላይ ይታተም ዘንድ በ46 ገፆች ያቀረብኩት የዳውድ የትግል ገጠመኝ ባጭሩ ይኸው ነበር። እነ ክንፈ ይህ ታሪክ አልተመቻቸውም።

ተከታታዩ መድበል ከእውነተኛ የትግል ታሪክነት ሙሉ በሙሉ ወደ ወገናዊ ልሳንነት እየተለወጠ በመሄድ ላይ መሆኑን ስገነዘብም በዚያ መፅሃፍ ላይ የነበረኝን ተሳትፎ አቋረጥሁ።

* * *

ከኢብሳ ገዳ ጋር እስከ ሌዲስሚዝ እያወጋን ተጓዝን።

ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታዎችን አንስተን ስንጨዋወት ብዙዎች ኢትዮጵያውያን የሚጠይቁትንና በበቂ ሁኔታ ያልተብራራውን አንጋፋ ጥያቄ ሳላነሳለት አልቀረሁም።

"ለመሆኑ ኦነግ አሁንም የመገንጠልን ጥያቄ ያራምዳል?"

ኢብሳ ቀጥተኛ ምላሽ ሊሰጠኝ ሞከረ፣

"ህዝቡ ይወስን ነው የምንለው!...OLF በ1983 የመሸጋገሪያ መንግስት ውስጥ ሲሳተፍ የምንፈልገው ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ይመጣል ብለን ተስፋ አድርገን ነበር። ሆኖም ወያኔ ምን እንደፈፀመብን ላንተ አልነግርህም። የህዝቦች እኩልነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ስርአት....."

አቋረጥኩት!

"የግልህን ፍላጎት ንገረኝ" አልኩት ጫን ብዬ።

ኢብሳ በጥያቄዬ አለመደሰቱን አስተዋልኩ፣

"እኔ የ OLF አባል ነኝ። ከድርጅቱ አላማዎች የተለየ ፍላጎት ሊኖረኝ አይችልም" ብሎ ቅጭም አለ።

"አውቃለሁ ኢብሳ" አልኩ "...የኦነግን ፕሮግራም

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አውቀዋለሁ። እስቲ አንጎልህን ሳትጠቀም የልብህን አጫውተኝ?"

ኢብሳ በመደነቅ ሲያጤነኝ ቆየ፣

"ኦሮሞ ያልሆኑ ወገኖቻችን ኦነግን እንደሚጠራጠሩት አውቃለሁ። አዝናለሁ። እኔ ባሌ ጫካ ህዝቡ ውስጥ ነው ያለሁት..."

ትክዝ ብሎ ቆየና መናገሩን ቀጠለ፣

"...የመገንጠልን ጥያቄ ያነሳው ጭቆና ነው" ሲል ንግግሩን ቀጠለ "... እንደ ሁለተኛ ዜጋ በመቆጠራችን የመጣ ጥያቄ ነው። ጭቆናው ከተወገደ የኦሮሞ ህዝብ ከመገንጠል ጋር ጉዳይ አይኖረውም። በመሰረቱ ኦሮሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ግንድ እንጂ ቅርንጫፍ አይደለም። ስለሆነም ግንድ አይገነጠልም።

"... ኢትዮጵያዊነት ላይም ቢሆን እኔ በግሌ ጥላቻ የለኝም። ኢትዮጵያዊነት ወንጀል አይደለም። ገዢዎች በዜጎች መሃል 'የበለጠ ኢትዮጵያዊ' የሚባል ልዩነት ስለፈጠሩ የመጣ ችግር ነው። በመሰረቱ ኢትዮጵያ ማለት የተቃጠለ ፊት ወይም ጥቁር ማለት ከሆነ እኛ የበለጠ ኢትዮጵያዊ ነን።

"...እንዳልኩህ ነው። የፖለቲካ ቁማር የትም አያደርስም። አብላጫ ድምፅ ያለው ሃገሪቱን ሊመራት ይገባል። ዴሞክራሲን እንደ ማጭበረበሪያ ስለተጠቀሙበት ግን የትጥቅ ትግሉን ቀጥለናል። ፍላጎቱ ካለ መፍትሄውም አለ። የኦሮሞ ህዝብ ለዴሞክራሲ አዲስ አይደለም። የገዳ፣ የሞጋሳ፣ የጉዲፈቻ ባህል ያለን ህዝብ ነን። መግባባት ከተቻለ በኢትዮጵያ አንድነት የበለጠ ተጠቃሚ የምንሆነው እኛ ኦሮሞዎች ነን።

"...ወያኔ ሽብርተኞች ይለናል። ቅስቀሳው እንዳልተሳካለት አረጋግጥልሃለሁ። ኦሮሞውና አማራው መነጋገር ጀምሮአል። ህዝብ እንደ ህዝብ ችግር አለበት ብዬም አላምንም። የትግራይ ህዝብ የኦሮሞ ህዝብ ጠላት ሆኖ አያውቅም። መሪዎች የሚፈጥሩት ችግር ነው። ወያኔ ኦነግ ሞቶ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መቀበሩን ደጋግሞ የሚያውጀው እንደማይሞት ስለሚያውቅና ስለሚፈራ ነው።

"...ህብረት ያስፈልገናል...መቻቻል....ይህቺ ሃገር እኩል እንድምትደርሰን ካልተማመንን...ሁላችንም ለሃገሪቱ እኩል ሃላፊነት እንዳለብን ካልተግባባን ግን ሰላም ሊኖር አይችልም...ይህ እስካልሆነ ድረስም እኔ ቦረና ጫካ ውስጥ እገኛለሁ...የባሌ ተራሮች ላይ ከነጠመንጃዬ እቆያለሁ...ይህም ወደማይፈለግ ውጤት ሊመራን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል... "

ሌዲስሚዝ ላይ ከኢብሳ ጋር ተለያየን።

ርግጥ ነው በዚያች አጭር መንገድ ላይ ላነሳሁት ጥያቄ ኢብሳ ገና በቂ ምላሽ አልሰጠኝም። ከፋሲካ በአል በሁዋላ ፕሪቶሪያ ላይ ልንገናኝ ቀጠሮ ይዘናል።

ጉዞዬን ወደ ደርባን ቀጠልኩ።

የፋሲካን በአል ደርባን ከተማ ላይ ለማክበር የወሰኑ ደቡብ አፍሪቃውያን መንገዱን ሞልተው እንደ ነፋስ ይከንፋሉ...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 24 -

ደራራ ለምን ተገደለ?

አይሆንም አትበሉ - ሆኖ እንደሆነሳ፣
ተቀብሮ ተቀብሮ - የተኛው ሬሳ፣
ድንጋዩን ፈንቅሎ - ማን ያውቃል ቢነሳ?
"ድንጋይ ተቆልሎ - አፈር ተለውሶ፣
በፀጥታ እሚኖር - ሳር ቅጠሉን ለብሶ፣
በድን ነው ተራራ - አፍ የለውም ጆሮ፣
አይሰማም አይለማም - ግኡዝ ነው ደንቆሮ፣"
ብላችሁ ሰትንቁ - የውስጡን ሳታውቁ፣
ለናንተ እኔ ፈራሁ - ፈንድቶ እንዳታልቁ፣

(ግጥም - ፑሽኪ ሃኒት)

በሳንጣዬ ከያዝኳቸው ቁርጥራጭ ወረቀቶች አንዱ የደራራ ከፊኔን አሟሟት ይተርካል። ትረካው ለአመታት አብሮኝ የተቀመጠ ሲሆን፣ መረጃውን ለማመን ግን ተቸግሬ ቆይቼያለሁ። መስከረም ወር 2000 ላይ ግን አሳዛኙን የደራራ አሟሟት ታሪክ የሚያረጋግጥ ተጨማሪ ፍንጭ በማግኘቴና መረጃውን የሰጠኝ ሰውም መሞቱን ስለሰማሁ፣ ታሪኩን በዚህ መድበል ለማካተት ወሰንኩ።

* * *

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አነግ ከመሸጋገሪያው መንግስት ከወጣበት ከ1984 በሁዋላ የኦሮሚያ ሁኔታ ውስብስብና አስቸጋሪ እየሆነ መሄዱ ይታመናል። በተለይም በኦሮሚያ ገጠሮች አመፅና እምቢተኛነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ ሄዶአል። የኦሮሚያን ክልል በቁጥጥር ስር ለማዋል የደህንነት መስሪያ ቤቱ ከዘየዳቸው መላዎች አንዱ ታዲያ፣ የአነግ ደጋፊ የሚባሉ ታዋቂ ሰዎችን፣ ህዝቡን ያሳምፃሉ ተብለው የሚጠረጠሩ አንጋፋ አድባሮችን፣ በየከተማው በመምታት የህዝቡን ሞራል መስበርና አቀርቅሮ እንዲገዛ ማድረግን ነበር። የዚህ እቅድ አፈፃፀምም በረቀቀ ዘዴ ተነድፎ ስራ ላይ ውሎአል። የኦሮሞ ህዝብ እንደ አድባር የሚመለከታቸው አንጋፋ ሰዎች በኦሮሚያ ዋና ዋና ከተሞች ሁሉ ግንባር ግንባራቸውን እየተመቱ ተገድለዋል። በዚህ ትረካ የአምቦን ህዝብ አንገት ለማስደፋት ማን እንደተገደለና ግድያው እንዴት እንደተፈፀመ አወጋችሁዋለሁ።

"አምቦ ላይ ማን ይገደል?" የሚለው ጥያቄ የተወሰነው በኮሚቴ ነበር። የኮሚቴው ሰብሳቢ በወቅቱ የመከላከያ የመረጃ ሃላፊ የነበረው ጄኔራል አባዱላ ገመዳ ሲሆን፣ በኮሚቴው አባልነት አምስት ሰዎች ተሳትፈዋል። እነርሱም፣ በወቅቱ የማእከላዊ እዝ የፖለቲካ ሃላፊ የነበረው ጄኔራል ሃይሌ ጥላሁን፣ በወቅቱ የማእከላዊ እዝ ዘመቻ ሃላፊ የነበረው ተክላይ አሸብር (ወዲ አሸብር)፣ አንድ ስሙ ያልታወቀ የፀጥታው መስሪያ ቤት ተወካይ፣ በወቅቱ አምቦ አካባቢ የተመደበ የኦዳ ሻለቃ ምክትል አዛዥ ኮሎኔል ድሪባ መኮንን፣ በወቅቱ የኦዳ ሻለቃ ፖለቲካ ሃላፊ የነበረው ሻለቃ ጀማል ዩሱፍ ነበሩ። በወቅቱ የኦዳ ሻለቃ አዛዥ የነበረው ኡመር ዩሱፍ የፖለቲካ አቋሙ አጠራጣሪ ነው በሚል በስብሰባው ላይ እንዳይገኝ ተወስኖ፣ ለፀጥታ ስራ ጉዳይ በሚል ሰበብ በስብሰባው እለት ወደ ፊንጫሃ እንዲሄድ ተደርጎአል።

የኮሚቴው አባላት አምቦ ቤተ መንግስት ተሰብስበው "አምቦ ላይ ማን ይገደል?" ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሰጡ። በእጩነት ሶስት የአምቦ ከተማ አንጋፋ ኦሮሞዎች ቀርበው ነበር። እነርሱም፣ የድምፃዊት አበበች ደራራ አባት፣ ደራራ ከፈኔ፣ ደቃ ሙለታ እና ደንደና የተባሉ ነበሩ። በህዝብ ተቀባይነቱና በአነግ ተጠርጣሪነቱ በድምፅ ብልጫ ደራራ ከፈኔ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አሸነፈ። ዝርዝር እቅድ ከተነደፈ በሁዋላም ደራራ የሚገደልበት እለት፣ ሰአትና ቦታ ተወስኖ ስብሰባው አበቃ።

ግድያው በታቀደው መሰረት ተፈፀመ።

በዚያን እለት ምሽት ደራራ ከፊኔ መኖሪያ ቤቱ ደጅ ላይ ከላንድክሩዘር ውስጥ በተተኮሰበት ጥይት ጭንቅላቱ ላይ በሁለት ጥይት ተመትቶ ህይወቱ አለፈ። የተኩስ ድምፅ እንደተሰማ በእቅዱ መሰረት ኮሎኔል ድሪባና ሻለቃ ጀማል ወደ አዳ ሻለቃ አዛዥ በመሄድ ደራራ ከፊኔ መገደሉን ገልፀውለት፣ ሰራዊቱ ባስቸኳይ የአምቦን ከተማ ከብቦ ፍተሻ እንዲያካሂድ በተረበሸ ሁኔታ አጣደፉት። ኮሎኔል ኡመር ዩሱፍ ለቴአትሩ ባዳ እንደመሆኑ የበታቾቹ ያቀረቡለትን የማስመሰያ አሳብ በቅንነት ተቀብሎ ሰራዊቱን አዘዘ። ደራራን የገደሉትን ሰዎች የያዝችው ላንድክሩዘር ቀኝሁዋላ በመዞር የፈታሾቹ አስተባባሪ ሆነች። በዚያን እለት በተደረገ ጥብቅ ፍተሻ ጠመንጃ ይዘው የተገኙ ፖሊሶች ጭምር በቁጥጥር ስር ዋሉ። አምቦ ቀውጢ ሆና በፍተሻ ስትታመስ አደረች። በአባዱላ ኮሚቴ ስር የነበሩት ኮሎኔል ድሪባና ሻለቃ ጀማል ድራማውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቁ።

ደራራ ሞተ!!!

ለመሞት በድምፅ በማሸነፉ ተገደለ!

ውጤቱ ግን የተገላቢጦሽ ሆነ። በነጋታው ማለዳ ህዝቡ የሌሊቱን ድራማ ሁሉ መገንዘቡን በገሃድና ባደባባይ አሳወቀ። በደራራ ቀብር ላይ ህዝቡ ግልብጥ ብሎ ወጣ። በቁጭት የሚፎክሩ እንጂ የሚያለቅሱ አልታዩም። በአምቦ ከተማ ታሪክ ያን የመሰለ ህዝብ የተገኘበት የቀብር ስነስርአት ተፈፅሞ የማያውቅ ሲሆን፣ ህዝቡ፣ "ደራራ ሆይ! አንድ ቀን እንደሚበሉህ እናውቅ ነበር። አምላክ ነፍስህን ይቀበላት! በዛሬዋ እለት በሺህዎች ደራራዎች ተወልደው እንደሚያድሩ ጠላቶቻችን አለማወቃቸው እንዴት የዋህ ቢሆኑ ነው!?" ሲል ተሰማ። የቀብር ስነስርአቱም በሆታ የተመላ ነበር።

* * *

ኢህአዴግን ትቼ ከመኮብለሌ አንድ አመት በፊት ባንድ ምሽት ሞባይል ስልኬ ላይ ተደወለልኝ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ማን ልበል?" አልኩ።

"ሻለቃ ጀማል እባላለሁ። አንተ አታውቀኝም፣ እኔ ግን አውቅሃለሁ።"

"እሺ! ምን ልርዳህ?"

"ላንድ ጉዳይ ስለምፈልግህ፣ የሚመችህ ከሆነ ከምሽቱ ሁለት ሰአት ራስ ሆቴል ላገኝህ እፈልጋለሁ።"

"በምን ጉዳይ ነው የፈለግሽኝ?"

"በስልክ አይሆንም። ስንገናኝ እነግርሃለሁ።"

"መልካም! በምን አውቅሃለሁ?"

"እኔ ስለማውቅህ መጥቼ አናግርሃለሁ"

ጋዜጠኛ እንደመሆኔ ይህን የመሰሉ አያሌ ሁኔታዎች ይገጥሙኛልና የጀማል የስልክ ጥሪ ትኩረቴን አልሳበውም ነበር። በቀጠሮው ሰአት ጠልቀው የሚያዩ አይኖችና የሃዘን ድባብ የተጫነው ጠጉሩ ገባ ያለ፣ ቀጭን ረጅም ሰው መጥቶ ከጨበጠኝ በሁዋላ፣ "ሻለቃ ጀማል ዩሱፍ" እንደሚባል ነገረኝ።

ሁለት ሰአታት ያህል ቆይታ አደረግን።

ከላይ ያወጋሁዋችሁን ሁሉ ካጫወተኝ በሁዋላም ሁለት ቅጠል ወረቀቶችን አውጥቶ እየሰጠኝ እንዲህ አለኝ፣

"ስሞችን እንዳትረሳ ዋና ዋና ነጥቦቹን ወረቀቱ ላይ አስፍሬልሃለሁ። እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ እስካለሁ ድረስም ይህን ታሪክ ልትፅፈው አትችልም። ይህን ታሪክ የምናውቀው በጣም ጥቂት ሰዎች ስለሆንን ታሪኩ ይፋ ከሆነ በቀላሉ ይይዙኛል። ስለዚህ ታሪኩን ይዘኸው ቆይና በተገቢው ጊዜ ተመካክረን ይፋ እናደርገዋለን። ደራራ ከፈኔን፣ የአበበችን አባት እንዴት እንደገደልነው የኢትዮጵያ ህዝብ ማወቅ አለበት። ይኸው ኑዛዜዬ፣ ወንድሜ!"

ሻለቃ ጀማል ይህን ብሎኝ ሲያበቃ፣ ያስቀዳውን ውስኪ ባንድ ትንፋሽ ዝርው አደረገው። ፊቱ የተቃጠለ ላስቲክ መስሎአል። ፀፀት ውስጥ ልቡን እያቃጠለ እንደሚያሰቃየው እያስተዋልኩ ቢሆንም፣ የክንፈን ጓዳ አውቀዋለሁና ሻለቃው ድራማ እየተወነ ሊሆን ይችላል፣ ድምፅ መቅጃም ብብቱ ስር ደብቆ ሊሆን ይችላል ብዬ መጠራጠሬ አልቀረም። ይህንኑ ለማጣራት ቢረዳኝ በሚል አንዳንድ ጥያቄዎችን ጣል አደረግሁ።

"እኔ የህወሃት ካድሬ መሆኔን እያወቅህ እንዴት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ይህን ሁሉ ምስጢር አምነህ ልትነግረኝ ቻልክ?" ስል ጠየቅሁት።

"አንተን አለማመን አይቻልም" አለ ፍርጥም ብሎ፣ "የቡርቃ ዝምታን በመፃፍህ አባዱላና ኩማ እንደ ጠላት እንደሚያዩህ አውቃለሁ። ወዲ እምበይተይም የኦነግ ሰርጎ ገብ ነው ይልሃል...ስብሃት ነጋ እየተከላከለለት ነውንጂ መወገድ ያለበት ሰው ነው ይሉሃል። ለምን እንደጠሉህ ስለማውቅ አንተን መጠራጠር አይቻልም...በቅርቡ ደግሞ ኤርትራዊ መሆንህን ሰማሁ..."

ላምነው ተቃረብኩ። ወዲ እምበይተይ የተባለው የህወሃት ጄኔራል ኮሎኔል ገመቹ ከተባለ ከፍተኛ መኮንን ጋር በዚሁ መፅሃፍ ጉዳይ እንደተጋጨ ቀደም ብዬ ሰምቼ ስለነበር ጀግልን ወደ ማመኑ አዘነበልኩ። ቢሆንም ከገፅታዬ ላይ አንዳችም ስሜታዊ ምልክት እንዳይታይ እየተጠነቀቅሁ ጥያቄዬን አራዘምኩ፣

"በሰራኸው ድርጊት የተፀፀትከው መቼ ነው?"

"በቀብሩ እለት!" አለ ፈጥኖ፣ እና በስሜት ቀጠለ፣ "...በነጋታው በደራራ ቀብር ላይ የአምቦ ህዝብ እንደ ማእበል ተገልብጦ ሲወጣ ፍርሃት እንደ ወባ አንቀጠቀጠኝ። እኔ ኦሮሞ ነኝ። በህወሃት ትእዛዝ የገዛ ወገኔን ገደልኩት። የአባቶቼ ባህል ይሄ አልነበረም። ጠላትህን በጉዲፈቻ ቤተሰብህ ታደርጋለህ እንጂ ወንድምህን አትገድልም። ከየት አመጣሁት ይህን ክህደት? በነጋታው የአምቦ ህዝብ በቁጣ እየጮኸ ወደ ቀብሩ ሲጎርፍ... ምን ብዬ ልንገርህ?... ቃላት የለኝም... ንፍሴን ናቅሁዋት... በዚያን ቀን ደራራ ከፊኔ አልሞተም። የሞትኩት እኔ ነበርኩ። አየህ እኔ ውሻ እንጂ ሰው አልነበርኩም። ልክ ጄኔራል ታደሰ ብሩ በአንድ ክስተት ድንገት እንደተለወጡት እኔም በዚያን እለት የኦሮሞን ህዝብ ዳግም ላለመክዳት ከራሴ ጋር ቃል ገባሁ..."

ለደቂቃዎች ያህል በዝምታ ከቆየን በሁዋላ፣

"አሁን ከኦነግ ጋር እየሰራህ ነው?" ስል ጠየቅሁት።

"አንተን አልደብቅህም። ግንኙነት አለኝ!"

"የደራራን አሟሟት ነግረሃቸዋል?"

"በፅሁፍ ልኬላቸዋለሁ። ለኔ ደህንነት ሲባል ግን በሚዲያ አያስተላልፉትም። ከዚህ የከፋ ብዙ ታሪክ በየእለቱ ሊሰሙ ስለሚችሉም በደራራ አሟሟት ላይደነቁ ይችላሉ። ላንተ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ልነግርህ የወሰንኩት ደራሲ ስለሆንክ፣ ልዩ ትኩረት ልታደርግበት ትችላለህ ብዬ ነው። እንዳልኩህ ግን እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ እስካለሁ ድረስ ምስጢሩ የግድ መጠበቅ አለበት...”

በዚሁ ተለያየን። ከመለያየታችን በፊት ግን የሰጠኝን ወረቀት መለስኩለት።

“ምነው?” አለኝ።

“ሁሉንም በአእምሮዬ መዝግቤዋለሁ” አልኩት።

እውነቴን አልነበረም። ከጀማል ጋር ከተለያየን በሁዋላ፣ የሚከተሉኝ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ ብዬ በመስጋቴ ነበር ወረቀቱን የመለስኩለት። ከጀማል እንደተለያየን ወዲያው ገለል ብዬ፣ ወረቀቱ ላይ የተፃፉትን ነጥቦች ሳልረሳቸው፣ በራሴው መንገድ ብጫቂ ወረቀት ላይ አሰፈርኳቸው። ሻለቃው ከደህንነት ሹሙ ከክንፉ የተላከ ሰላይ ከሆነም ከኔ ምንም ያገኘው ፍንጭ ባለመኖሩ ስጋት አላደረብኝም ነበር።

* * *

እነሆ ከአምስት አመታት በሁዋላ አንድ ወዳጄ በላከልኝ የኢ - ሜይል መልእክት ላይ ሻለቃ ጀማል ዩሱፍ መሞቱን ጠቀሰልኝ። በጥቅሉ ታሞ መሞቱ ተነገረኝ እንጂ፣ ዝርዝር ነገር ላገኝ አልቻልኩም። እንግዲህ አሳዛኙ ታሪክ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ ደረሰ ማለት ነው። የሙያ ግዴታዬን ለመወጣትና የደራራን “የአሸናፊነት” ታሪክ ለመተረክ ቁርጥራጭ ወረቀቶቼን መበርበር ጀመርኩ...

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 25 -

ኢትዮጵያዊ ወታደር

የሞተው ወታደር - ሰላም የሚነሳው - የረሳው ምንድን ነው?
ከመቃብር ጀርባ - አንዳች ትዝታ አለው?
ሲንጉሩ ውለው - ሲንጉሩ እሚያድሩ - የሚያገሱ መድፎች፣
ለሞተው ወታደር እርስቶቹ ናቸው?
ሰባራ ጠመንጃስ - ቀሪ ትዝታው ነው?

(ግጥም - ሹንታሮ ታኒካዋ)
- ከበደ ደበሌ ሮቢ እንደተረጎመው

በደርግ ውድቀት ዋዜማ አረና ከተባለች የትግራይ የገጠር ቀበሌ ከአማረ አረጋዊ ጋር ተለማማጅ ጋዜጠኞችን የማሰልጠን ስራ ተሰጥቶን ነበር። በእኔ በኩል የተሰጠኝን የማስተማር ክፍለ ጊዜ እንዳበቃሁ አማረንና ተማሪዎቼን ተሰናብቼ ወደ ሬድዮ ጣቢያው ለመመለስ ተዘጋጀሁ።

ይሁን እንጂ እንዳሰብኩት ሳይሆን ቀረ።

እኔ ለምመራው የሶስት ቀናት የሬድዮ ፕሮግራም የሚያገለግል ስራ እሰራ ዘንድ ወደ ግንባር እንድሄድ ታዘዝኩ። በወሎ ግንባር ውጊያ እየተካሄደ ነበርና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለፕሮፓጋንዳችን የሚያገለግል ብዙ መረጃዎች እንደሚገኝ በማመን በዚያኑ እለት ሌሊት ከአረና ወደ ደሴ ግንባር አቀናሁ።

እዚያ ስደርስ ውጊያው ገና በመካሄድ ላይ እንዳለ የመድፈኛው ክፍል አዛዥ አለምሸት ደግፌ አጫወተኝ። የደርግ ወታደሮች ሬሳ ተቀብሮ ከማለቁ በፊት ደብዳቤዎቻቸውን ከየኪሶቻቸው ለመልቀም ወደ አውደ ውጊያው ትጓዝ ከነበረች ፒካፕ ላይ ተጭኜ ወደ ተራሮቹ ገሰገስኩ።

ሌሊት ነው።

ድቅድቅ ያለ ጭለማ ውጦናል። ይዛን በምትጓዘው ፒካፕ ላይ ስድስት ያህል ሰዎች ተጭነናል። ማን እንደሆኑ አላውቃቸውም። ሁላችንም ወደ ጉጉፍቱ ተራሮች ለተለያየ ስራ እንደምንጓዝ ግን ግልፅ ነው። ካሜራ የያዘ፣ አንገቱ ላይ ሰማያዊ ክሹክ የጠመጠመ፣ ለስላሳ ፀጉር ያለው ወፍራም ሳቂታ ታጋይ ከፊት ለፊቴ ተቀምጦአል። ፎቶግራፍ አንሺ ሊሆን እንደሚችል ብገምትም አልተነጋገርንም።

በፒስታው መንገድ ላይ እየተንገጫገጨች የምትከንፈው ፒካፕ፣ በቻለችው አቅም ሁሉ ታጎሳቁለን ይዛለች። ጦርነቱ በሚካሄድበት የጉጉፍቱ ግንባር እንደተቃረብን ድንገት ከፍተኛ የጩኸት ድምፅ ሰማን፣

"እርዱኝ! እርዱኝ! ወገኖቼ እርዱኝ!" የሚለው ጩኸት ድቅድቅ ጨለማውን ሰንጥቆ ጆሮአችንን በጠረቀው።

ታጋዩ ሾፌር በዚያው ፍጥነት የመኪናውን ፍሬን በመያዙ፤ ከሁዋላ ተጭነን የነበርነው እርስበርስ ተላተምን። መኪናችን በሁዋላ ማርሽ ጥቂት ከተጓዘች በሁዋላ ድምፁን ከሰማንበት አካባቢ ቆመች።

ጩኸቱ ቀጥሎ ነበር።

"እዚህ ነኝ! ቀብረውኛል! እርዱኝ ወገኖቼ! አልሞትኩም!"

ከመኪናችን እየዘለልን ወረድን።

የመኪናዋ ሾፌር ጩኸቱ ወደሚሰማበት አቅጣጫ የመኪናዋን ፊት በማዞር ረጅሙን መብራት ለቀቀው! እንደ ቀትር ወለል ብሎ በሚታየው የመኪናው መብራት እየተመራን ጩኸቱ ወደተሰማበት ጢሻማ ተዳፋት ስንጠጋ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ማመን የማንችለው ትርኢት ከገፅታችን ተከሰተ።

የተቀበረ የደርግ ወታደር!

ወታደሩ አንድ እጁንና አንገቱን ብቻ ከተቀበረበት ፈንቅሎ ማውጣት ችሎአል።

ይጮሃል! አይኑ ፈጠአል!

ሁለት ታጋዮች ተረዳድተው ጎትተው ሲያወጡት እንደገና አሰቃቂ ትርኢት ለማየት በቃን! ሁለቱም እግሮቹ ዱቄት ሆነዋል። ታንክ የረገጣቸው እስኪመስሉ ተጨፈላልቀዋል። ወታደሩ ከተቀበረበት ተጎትቶ ከወጣ በሁዋላ ጩኸቱን ቀጠለ፣

"ተፈሪ ዘመድኩን እባላለሁ! የአዲስ አበባ ልጅ ነኝ! ጎላ ሰፈር ነው ቤቴ! ሳልሞት ነው ቀብረውኝ የሄዱት፤ ሳልሞት ቀብረውኝ ሄዱ!!"

ድንጋጤና ደስታ በተቀላቀለበት ሲቃ እየለፈለፈ በተስፋ ፈገግ ለማለት ሲሞክር በማየቴ የተደበላለቀና የሚያቅለሸልሽ ስሜት ተፈጠረብኝ።

"መቼ ነው የቀበሩህ?" ሲል ሾፌሩ ጠየቀው።

"አላውቅም"

"ሲቀብሩህስ ታውቅ ነበር?

"አላውቅም"

"እንዴት ፈንቅለህ ወጣህ?

"አላውቅም"

በደምና በጭቃ የራሰው ወታደር ይንቀጠቀጣል። ሌላው እጁም መሰበሩን አስተዋልኩ። የማይነቃነቅ ሲሆን፤ እንደ ገመድ ተዝለፍልፎአል። በድንጋጤ የፈጠጡት አይኖቹና የግራ እጁ ብቻ ባላቸው ሃይል ሁሉ ህያው መሆኑን ለማሳመን ይጥራሉ። ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ እርስ በርስ እንተያይ ጀመር።

የመኪናችን ሾፌር ሽጉጡን በእጁ ይዞ ነበር!

"ማነው ስምህ?" ሲል ጠየቀው።

"ተፈሪ ዘመድኩን! አዲሳባ... የጎላ ሰፈር ልጅ ነኝ...አባቴ በጎላ ሰፈር የታወቀ መምህር ነበር...አሁን ጡረታ ላይ ነው...ዘመድኩን ዋሴ ...የ7ኛ ክፍል ሳይንስ አስተማሪ ነበር..."

"ልንረዳህ አንችልም፣ በጣም ተጎድተሃል!"

ወታደሩ እንደመቅለስለስ እያለ መለማመጥ ጀመረ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“አልሞትኩም! እየተናገርኩ አይደል እንዴ? ሳልሞት ነው'ኮ የቀበሩኝ...ጤነኛ ነኝ...ከረዳችሁኝ እራመዳለሁ!”

ሁለት እግሮቹን ለማንቀሳቀስ ፈለገና አቃተው። አመድ መሆናቸውን ተረዳ። ገፅታው ላይ ግን ፊፅሞ የህመም ስሜት አልነበረበትም።

“ልንረዳህ አንችልም። በጣም ተጎድተሃል”

ወታደሩ በመለማመጥ መልኩ ሲያየን ቆየና፣

“እናንተ ወያኔዎች ናችሁ እንዴ?” ሲል ጠየቀን።

“አዎን። ወያኔዎች ነን!”

ወታደሩ ተስፋ በመቁረጥ አይኖቹን ጨፈናቸው። መልሶ ገለጣቸው። እንደገና ጨፈናቸው።

ፊቴን አዙሬ ሄድኩ። የወታደሩ የሲቃ ድምፅ ከሁዋላ ይሰማኝ ነበር፣ ወዲያው ግን ተቋረጠ፣

“...አባቴ አለመሞቴን ካወቀ...የጎረቤት የስልክ ቁጥር...”

ከደቂቃዎች በሁዋላ ጉዞአችንን ቀጠልን! ቀሪው ጉዞአችን የበለጠ ከባድና በዝምታ የተሞላ ነበር። ፎቶግራፍ አንሺው ግን ሊያናግረኝ መሞከሩ አልቀረም።

“አማራጭ አልነበረንም”

“ልክ ነህ!”

“መሞቱ አይቀርም ነበር”

“ልክ ነህ!”

ከአመት በሁዋላ ደርግ ወደቀ።

እኛ ጋዜጠኞችም “የደርግ ወታደሮች” እያልን በሚዲያ ስንለፈልፍ ብዙውን ጊዜ ተፈሪ ዘመድኩን ትዝ ይለኝ ነበር። ያ ወጣት ሌላው ሁሉ ቢቀርበት “የኢትዮጵያ ወታደር” የሚል ስም እንኳ ማግኘት አለመቻሉን እያሰብኩ ሃዘን ይሰማኝ ነበር።

...እነሆ ጊዜ ጊዜን እየወለደ ጊዜ ይሄዳል።

ይህን ማስታወሻ የምፅፍላችሁ ፕሪቶሪያ ከተባለው የደቡብ አፍሪቃ ዋና ከተማ በስደት ላይ ሆኜ ነው። ከመኖሪያ ቤቴ በፀጥታ ተቀምጬ ድረገፆችን መፈተሽ ይገፍያለሁ። ኢትዮጵያ ነክ ድረገፆች የሞቃዲሾን ጦርነት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በስፋት እየዘገቡ ይገኛሉ። አንድ "የወያኔ" ወታደር ሬሳ በሞቃዲሾ ከተማ በገመድ ታስሮ ሬሳው ሲጎተት ተመለከትኩ። የወታደሩ የራስ ቅል ተገነጣጥሎ ስመለከት ስቃይ ልቤን አፈነው። "የወያኔ ወታደር" የሚሉ አገላለፆች በየድረገፁ ስመለከት ድርብ ሃዘን መላ ሰውነቴን ይንጠው ያዘ።

አዝኜያለሁ!

የመለስ አስተዳደር በሶማሊያ ውጊያ የተሰውትን 3000 ያህል የኢትዮጵያ ወታደሮች እያመላለሰ ደሎ መና ጫካ ውስጥ እንደቀበራቸውና ለቤተሰብ መርዶ አለመንገሩንም አንብቤ ሃዘኔ ጨምሮአል። ወያኔ ሶማሊያ ላይ ለፈፀመው "ጀብዱ" የአሜሪካ መንግስት 92 ሚሊዮን ዶላር መክፈሉን ገልፆአል። ይህ ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና አለመግባቱም የሚሊኒየሙ የድረገፆች የሹክሹክታ ወሬ ሆኖ እንደዋዛ አልፎአል። በሶማሊያ የተሰውት ወታደሮች ለህይወታቸው ካሳ ማግኘቱ ይቅርባቸውና "የኢትዮጵያ ወታደር" ለመባል እንኳ ገና አልበቁም።

የሆነው ሆኖ አንድ ወታደር "ኢትዮጵያዊ ወታደር" የሚል የክብር ስም አግኝቶ፤ ሃገሩን በስራ የሚያገለግልበትና መስዋእትነቱ የሚያበቃበት እለት መቼ ይመጣ ይሆን?

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 26 -
አንድ ምሽት ከስዬ ጋር

ጀንበር ወጥታ እስክትጠልቅ - ቀኑ ተለውጦ፣
ሻጩ ገዢን ገዝቶ - ገዢም ሻጭን ሸጦ፣
አዬ ሰው ሸንኮራው - ይጣላል ተመጦ፣
ያም ተሻሪ ሽሮ፣ ቦታ ተቀያይሮ፣ ጅራፉን ቀይሮ፣
ተመቺው መቺ ነው
መቺውም ተመቺ ደሞ ለነግ እሮሮ፣

(ግጥም - ነቢይ መኮንን)

ደርግ በወደቀበት ምሽት አራት የበረሃው ሬድዮ ጣቢያ ባልደረቦች ስዬ አብርሃ ወደሚገኝበት ዋሻ ስንደርስ እኩለ ሌሊት ሁኖ ነበር፡፡ የህወሃት መሪዎች የስራና የመኖሪያ ዋሻዎችን ሹሉክሉክ እየተጠማዘዝን፣ እያንዳንዳችን በያዝነው ባትሪ መሪነት እየታገዝን፣ ስዬ ከነ አጃቢዎቹና ከነረዳቶቹ ከተቀመጠበት ዋሻ ስንገባ የደስታ የሚመስል አንዳች የሆታ ድምፅ ሰማን፡፡

ካልተሳሳትኩ እለቱ ግንቦት 21 ወይም 22 ሳይሆን አይቀርም። ስዬና አጃቢዎቹ በከፍተኛ የደስታ ስሜት ተውጠው ጠበቁን፡፡ ጠረጴዛው ላይ ግማሹ የጎደለለት የዊስኪ ጠርሙስ የሚታይ ሲሆን፤ ታጋዮቹ በአጭር ኩባያ እየቀዱ በፈሽታ መደሰት ይዘው ነበር፡፡ ይህ የደስታ ግብግ በደርግ ስርአት መውደቅ ሊሆን እንደማይችል ግን ርግጠኛ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ነበርኩ፡፡ በርግጥም መንግስቱ ሃይለማርያም ከሳምንት በፊት ሲኮበልል ደርግ ያለቀለት መሆኑ መላው አለም የተረዳው ነበርና የነስዬ ፌሽታ ምክንያት ሌላ እንደሚሆን ግልፅ ነበር። መዝሙር ፈንቴና ሙሉጌታ ገሰሰ ቀድመው ለስዬ ሰላምታ እያቀረቡለት ምን አዲስ ዜና እንደተገኘ ጠየቁት፡፡

ስዬ በባህርይው ረጋ ያለና በዝግታ የሚናገር ሰው ሲሆን፤ ያን ቀን ግን ፍፁም የራሱ ባልሆነ የደስታ ስሜት ተውጦ የሚከተለውን የብስራት ዜና ነገረን፣

"ደርግ አስሮት የነበረው ታናሽ ወንድሜ በህይወት የመገኘቱን ዜና አሁን ገና መስማታችን ነው! በጣም ደስ ብሎናል!"

በእውነቱ ሁላችንም በደስታ ጮህን፡፡ ስለ ስዬ ወንድም ብዙዎቻችን እናውቅ ነበር፡፡ ደርግ በመጨረሻዋ ደቂቃ በእልህ ተገፋፍቶ የወያኔ መሪዎችን ዘመድ አዝማዶች ሁሉ ይረሽን ይሆናል የሚል ስጋትም ነበረ፡፡ በተለይ እንደ አሰፋ አብርሃ ያሉትን ለይቶ ቢረሽን ደግሞ የሚደንቅ ላይሆን በቻለ፡፡

የሆነው ሆኖ ከውስኪው ለኛም ተቀዳልንና የአሰፋ አብርሃን በህይወት የመገኘት ብስራት ከስዬ ጋር ሆነን አከበርነው፡፡ በዚያን እለት ወደ ስዬ የተጓዝነው ከሬድዮ ጣቢያው ባልደረቦች ግማሻችን ያህል ወደ አዲሳባ እንድንጓዝ በመታዘዙ፤ የጉዞውን ሁኔታ ከስዬ ጋር ለመነጋገር ነበር፡፡ ጉዳያችንን አብቅተን ወደ ቦታችን ተመለስን፡፡

...ይህ ታሪክ ከተፈፀመ አያሌ አመታት አልፈዋል፡፡ ዛሬ ባለበት ያለ የለም። እኔ ወያኔን ትቼ ኮብልያለሁ፡፡ ስዬ አብርሃ ስድስት አመታት፣ አሰፋ አብርሃ ደግሞ ሰባት አመታት ታስረው ተፈትተዋል፡፡ ሙሉጌታ ከስራው እንደተሰናበተ ሰምቻለሁ። ስለ መዝሙር ወሬ የለኝም።

ይህን ማስታወሻ በምፅፍባት ደቂቃ ስለ አሰፋ አብርሃ ጥቂት አሰላሰልኩ፡፡ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የመፅሃፉን ማስ ታወሻ ካበረከተላቸው ሰዎች አንዱ የሆነው የአሰፋ አብርሃ የህይወት እጣ የሚያስተክዝ ሆኖ አገኘሁት።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ደርግ የስዬ ወንድም ስለሆነ ብቻ ከስምንት አመታት በላይ አሰረው፡፡ ወያኔ ደግሞ የስዬ ወንድም ስለሆነ ታላቅ ሹመት ሰጠው፡፡ መለስና ስዬ በመጨረሻው ስብሰባ ሃይለ ቃል ስለተለዋወጡና ስዬ አብርሃ፣ "እንደገና ደደቢት ገብተን ም ቢሆን ትግሉን እንጀምራለን" በማለቱ አሰፋ በስዬ ምክንያት ዘጠኝ የእስር አመታት ተፈርዶበት፣ ሰባት አመታት ታሰረ፡፡

መቸም አሰፋ አብርሃ የታሰረው በሙስና ምክንያት እንዳልሆነ ፍርዱን የሰጡት ዳኞች ልቦናቸው ያውቀዋል፡፡ ህወሃት "የትግራይ ሃብታሞችና ምሁራንን ማፍራት" በሚለው የቆየ ፕሮግራሙ መሰረት እነ አሰፋ አያሌ ሃብታሞችን መፍጠራቸው የአዋጁን በጆሮ ማለት ነው፡፡ ስርአቱ እንደ ስርአት ህገወጥ ንግድ እንደሚያካሂድ ያደባባይ ሚስጥር ነውና አሰፋ ተለይቶ ሙሰኛ ሊባል አይችልም።

አሳዛኙ ታሪክ አሰፋ አብርሃ ከወጣትነት ወርቃማ ጊዜው፣ አለ በቂ ምክንያት፣ የራሱ ባልሆነ አጀንዳ ከአስራ አምስት ያላነሱ አመታት በእስር ቤት ማባከኑ ነው፡፡

የሆነው ሆኖ ይህቺን ማስታወሻ ስጫጭር ያቺ የግንቦት ሃያ ማግስት ሌሊት ትውስ ትለኛለች፡፡ ስዬ የውስኪ ብርጭቆውን ጨብጦ፣

"ደርግ አስሮት የነበረው ወንድሜ በህይወት ተገኘ! ደስ ብሎኛል! ደስ ይበላችሁ!!"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 27 -
መነኩሴው ቀበሮ

ሰናይ ግርማ ምገስ - አበባ ቃላቱን፣
ርቱእ አንደበቱን - ሰንቆ ክህሎቱን፣
"ሃቅን ሊመሰክር - ክፉትን ሊረታው"
መነኩሴው ቀበሮ፣
የበግ ለምድ ለብሶ - ገባ ከበግ ተርታ፣
የተንኮል ፈላስፋው - ሾተላዩ አደባ፣
በግምገማ ተገን....
ባተሌውን ታጋይ - ሊወጋው ከጅርባ፣

(ግጥም - ሺፈራው ከበደ)

እሳ! ትኩረቴን ሊስብ የቻለ አንድ ዜና ድረ-ገፅ ላይ ተፅፎ አነበብኩ። ሱሌይማን ደደፎ የተባለ የኢትዮጵያ አምባሳደር ከቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ከጂሚ ካርተር ጋር ፣ አቡጃ ናይጄሪያ ላይ ቆይታ ማድረጉ እየተዘገበ ነው። ወዲያው ጎግል ገባሁና "ስለ አምባሳደር ሱሌይማን ጎልጉልልኝ" አልኩት። ጎልጉሎ ዘረገፈልኝ። ጥር 5፣ 1998 ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደጊዮርስ 19 አምባሳደሮችን ሾመው ኖሮአል። ከነዚህ አንዱ እኔ የማውቀው ሰው ነው።

ለደቂቃዎች ያህል ተክዤ ቆየሁ።

ሱሌይማን የአርሲ ገጠር ልጅ ነው። በመሾሙ የተሰማኝን ስሜት ፈተሽኩ። በችሎታው ላይ ጥርጣሬ አልነበረኝም። ካንድም ሁለት ዲግሪ መያዙን አውቃለሁ። ከዚህ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሰው ጋር ለዘመናት በህይወትና ሞት ፀብ ተፈላልገን ነበር። "ድንገት ሞቼ ብታገኙኝ፣ የኔ ገዳይ ሱሌይማን ነው" እያልኩ እስከ መቀለድ ደርሼ ነበር። ይሽው አሁን የወደኔ አምባሳደር ሆኖአል።

ከሱሌይማን ጋር የተዋወቅነው በትግሉ ወቅት ሃገረሰላም በሚገኘው የኢህአዴግ ሬድዮ ጣቢያ ገጠር ውስጥ ነበር። ጥሩ ብእር ነበረው። ይፅፋል። በጣም ይፅፋል። በሳምንት ሶስት ጊዜ በሚተላለፍ የሬድዮ ፕሮግራም የደርግ ወታደሮች እንዳይዋጉ እንቀሰቅስ ነበር። በወቅቱ ጥሩ ወዳጆች መሆን ችለን ነበር። አዲስ አበባ ከገባን በሁዋላ እድሜ ለበረከት በፀብ የምንፈላለግ ጠላቶች ሆነን አረፍነው። ዛሬም ድረስ ሁሉም ነገር ወለል ብሎ ይታየኛል።

አይኖቼን ከመስኮቱ ወዲያ ማዶ ወረወርኩ..

ቁጭ ካልኩበት ሳሎን ፊት ለፊት ከመስኮቱ ባሻገር ከፕሪዶሪያ ቀበሌዎች አንዱ የሆነው ሊንውድ ልክ እንደ አርሲ ገጠር ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ተሞልቶ ከፊት ለፊቴ ተዘርግቶአል....

* * *

ጊዜው 1985 አጋማሽ ነበር።

በወቅቱ የፕሬስ መምሪያ ሃላፊ ነበርኩ። በረከት ስምኦን ወደ ቢሮዬ ደውሎ አንድ ጁብእዳ አፈነዳብኝ። የኢትዮጵያ ሬድዮ የፕሮግራሞች ሃላፊ ከነበረው ከሱሌይማን ደደፎ ጋር ለአንድ የጋራ ግምገማ የተዘጋጀንበት ጊዜ ነበር። በረከት ደወለና አንድ እምነትን የሚፈታተን ተልእኮ ሰጠኝ። ሱሌይማን ከስራ ሃላፊነቱና ከድርጅት አባልነቱ እንዲወገድ እንዳስተባብር አዘዘኝ። ስልኩን ከዘጋሁ በሁዋላ በቆንጥር እሾክ እንደተያዘ ሰው አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ገብቼ እንደነበር አስታውሳለሁ። አንዳችም ጥፋት ያላየሁበትን ሰው ከመሬት ተነስቼ ወንጅዬ እንዲባረር ማድረግ እምነትን የሚፈትን እንደመሆኑ ማድረግ ያለብኝን ቁጭ ብዬ አስቤበት ነበር።

ራሴን በሱሌይማን ቦታ ሳስቀምጠው ዘግናኝ ነበር። በረከት የበላይ አለቃዬ ነው። ጥብቅ መመሪያውን መጣስ ስለመቻል አለመቻሌ በርግጠኛነት አላውቅም። "ትግል ማለት ይሄ ኖሮአል?" እያልኩ ራሴን መጠየቄ አልቀረም። ትግል ማለት አንድን ጨቋኝ ስርአት አስወግዶ፣ ራስንና ህዝቡን ነፃ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ማውጣት ብቻ አይደለም ለካ!? አይነ ውሃው ያላማረህን ከጀርባ መውጋትም ትግል ኖሮአል። የትግል መጋዝ ሲሄድም ሲመለስም ይቆርጣል። ትግል ነፃ መውጫ ብቻ ሳይሆን ነፃነት ማፈኛና መግፈፊያም ኖሮአል። የሁሉም ትግሎች ይዘትና ባህርይ ተመሳሳይ ነውን? ወይስ ትግል እንደመሪዎቹ ባህርይና ፍላጎት የሚቃኝ ነው? ይህን የመሰለ አሳብ እያነሳሁና እየጣልሁ፣ ካንዱ ጫፍ ወደ ሌላው ተላጋሁ። በወቅቱ መውጫ የሌለው ብሽቦታ ውስጥ የገባሁ ቢሆንም፣ በአንድ ነገር ላይ ግን ርግጠኛ መሆን ችዬ ነበር። የጊዜ ጉዳይና የኬላው ልዩነት ካልሆነ በቀር፣ እኔም ከእንዲህ አይነቱ አደጋ የምድንበት መከላከያ፣ (Immunity) እንደሌለኝ ለመገንዘብ ቻልኩ። ገና ከመነሻው እያሱ በርሄ "የድርጅት ሰው መሆን አትችልም" ያለኝንም ሳላስታውስ አልቀረሁም። እናም ትግልን የሚገዛ ህግ የለም። ታጋዮች በመካከላቸው በፈጠሩት የመተዳደሪያ ህግም የሚጠቀምና የሚጎዳ አለ ማለት ነው። የማስፈፀም ስልጣን ያለው ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናል። ህጉ የሚፈፀመውም "ምራኝ" ብሎ ከመብቱ ላይ ቀንሶ በሰጠው ሰፊው ታጋይ ላይ ነው።

አሁን አንድ ነገር እየተሰማኝ ነው።

ፈረንጆች፣ "Law of the jungle" የሚሉት ነገር። የስልጣን ሰይፍ በእጁ የያዘ ሁሉ፣ ሰይፉን እየመዘዘ ያልተመቸውን አንገት ይቀላል። እንደልብ የሚተጣጠፉ አንገቶች ብቻ ይኖራሉ። ተፈጥሮ እንዳደለችህ መኖር በፍፁም አይፈቀድልህም። ሰይፉን ለጨበጡት ጨካኞች ራስህን ማመቻቸት አለብህ። በየደቂቃው ራስህን እየሞረድክ ተሳቅቀህ ብቻ የመኖር እድል ነው ያለህ። ሱሌይማን የማይመች ፀባይ እንዳለው አውቃለሁ። በዘዴ እየያዝኩት እንጂ በስራ ከጥቂት ጊዜ በላይ ተጋጭተናል። ሆኖም በርትቶ የሚሰራ ሰው መሆኑን እያወቅሁ እንዴት ልዘምትበት እችላለሁ? አንድ ጋዜጣ ላይ ያነበብኩት ጥቅስ ታወሰኝ፣ "If you are one and have no one, leave the way for twos"

ቲፎዞ!

መተጋገል ቀርቶ መተዛዘል።

በሱሌይማንና በበረከት መካከል በግል ምን የተፈጠረ ችግር እንዳለ አላውቅም። ደርግ ወድቆ የሽመት ድልድል ሲደረግ፣ በረከት ለሬድዮ ጣቢያው መምሪያ ሃላፊ ይሆን ዘንድ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሱሌይማንን መርጦ እንደነበር ግን አስታውሳለሁ። ሙሉጌታ ገሰሰ አጥብቆ ስለተቃወመ ግን ስዩም መለሰ የተባለው ልጅ እንዲይዘውና፣ ሱሌይማን ከስር ሆኖ ስራዎችን እንዲሰራ ተወስኖ ነበር። ዛሬ ደግሞ ባልታወቀ ምክንያት በረከት ሱሌይማን ላይ ሰይፉን መዘበታል። እነሆ! የበረከት የስሜት ነፋስ የሚነፍስበትን አቅጣጫ እያሸተትን ስራችንን እናቅዳለን...

ማምሻውን በጣም ተረበሽኩ። ግምገማው ሊጀመር ሁለት ቀናት ቀርተውታል። የበረከትን ትእዛዝ ፊት ለፊት ባለ መቃወሜ የህሊና ወቀሳው ቢበዛብኝ፣ ማታ ላይ ወደ አለምሰገድ መኖሪያ ቤት ደወልኩና አነጋገርኩት፣

"አንድ ነገር ላማክርህ ነበር"

"ችግር አለ እንዴ?"

"በረከት ዛሬ ደውሎ ሱሌይማን ከስራውና ከድርጅት አባልነቱ እንዲባረር እንዳስተባብር አዘዘኝ" አልኩ።

"ምንድነው ምክንያቱ?" አለምሰገድ ጠየቀ።

"አላወቅሁም።"

"እና አንተ ምን አሰብክ?" ሲል መልሶ ጠየቀኝ።

"ሱሌይማንን ማስወገድ አላመንኩበትም"

"ካላመንክበት፣ ያመንክበትን ፈፅም!"

ከአለምሰገድ ጋር በዚሁ አበቃን። አለምሰገድ እዚህ ጉዳይ ላይ እጁን ማስገባት እንዳልፈለገ ጠረጠርኩ። ምክር ነበር የጠየቅሁት። ሚዛናዊ መስሎ ሜዳ ላይ ተወኝ። በነጋታው በረከት ወደ ቢሮዬ ደወለልኝና፣

"ተዘጋጅተሃል?" ሲል ጠየቀኝ።

"ሱሌይማን ላይ መረጃ አፈላልጌ ነበር። ግን ምንም አላገኘሁም። ያዘዝከኝን እንዴት ልፈፅም እችላለሁ?" አልኩ።

"ሱሌይማን ሙስና ውስጥ ገብቶአል" ሲል ተንደረደረ፣ "...ጉቦ እንደሚቀበል መረጃዎች አጊኝተናል። ጉቦ ወስዶ የዜናህ መኮንንን ልቦለድ መፅሃፍ በሬድዮ እንዲተረክ አድርጎአል። ጠባብና የኦነግ አመለካከት ተሸካሚ እንደሆነ ፍንጮች አሉ። ሬድዮ ጣቢያውን ለኦነግ አሳልፈን ልንሰጥ አንችልም። የኢህዴን አባላትን ይንቃል። እብሪተኛ ነው። እነዚህ ሁሉ የሚታወቁ ናቸው። አንተም ታውቃቸዋለህ። ከዚህ በላይ ምንድነው የፈለግኸው?" ሲል ጫን ብሎ ጠየቀኝ።

"እሞክራለሁ!" ስል ተነፈስኩ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስልኩን ከዘጋሁ በሁዋላ ውሃቦንብር ውስጥ ገባሁ። ያን ቀን ምሽትም ቮድካ ስገለብጥ አደርኩ። ሱሌይማን ሙስና ውስጥ እንዳልገባ ገምቼያለሁ። የተጠቀሱትን ክሶች በርግጥም ሰምቼያቸው ነበር። ዜናነህ መኮንን ዜና አንባቢ እንደመሆኑ፣ ለሱሌይማን ጉቦ ሊሰጥ አይችልም። ለጉቦ የሚያበቃ ገቢ የለውም። መፅሃፉ እንዲተረክለት አግባብቶት ሊሆን ይችላል። ያን ለማለትም ቢሆን ማስረጃ የለም። ሱሌይማን አነግ ሆኖአል ለማለት የሚያበቃም መረጃ የለም። በደፈናው ጥርጣሬ ነበር። የህወሃትና የብአዴን አመራር አባላት ጠንከር ያሉባቸውን አባላት አነግ ወይም መአህድ የሚል ታርጋ እየለጠፉ ማባረሩን ተላምደውታል። "ሱሌይማን የኢህዴን አባላትን ይንቃል" የሚለውም የተጋነነ ነበር። በኢትዮጵያ ሬድዮ መምሪያ ሃላፊ ሆኖ የተመደበው የኢህዴን ታጋይ ምስኪን የእግዚአብሄር ሰው ነበር። የተሰጠው ሃላፊነት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ እንኳ አልተረዳውም። የሬድዮ ጣቢያውን የሃላፊነት ስራ በሙሉ ሱሌይማን ላይ ጥሎ፣ እሱ ከቢሮ ቢሮ እየዞረ ያለማቋረጥ ሲሰቅ፣ ሲጫወት የሚውል፣ ልክ የስራ ሰአት መውጫ ላይ ደግሞ ወደ ድራፍት ቤት የሚሮጥ፣ በቀን ሁለት ጊዜ መኪና የሚያጋጭ ደግ ልጅ ነበር። ሌላው ኢትዮጵያ ሬድዮ የተመደበው የኢህዴን አባል ሞገስ ሃብቱ የተባለ ገጣሚ ነበር። በጣም ጎበዝ ገጣሚ ነበር። በሬድዮ ጣቢያው አመራር ግን ሱሌይማንን ሊያግዝ የሚችል አልነበረም። በተቀረ ሱሌይማን እንዲባረር የተፈለገበት ምክንያት ብዙም ግልፅ አልነበረም። ለረጅም ጊዜ የሃገሪቱን ርእሰ አንቀፆች ይፅፍ የነበረው ሱሌይማን ነው። በርግጥ ግትርነት፣ የእልኸኛነትና የቂመኛነት ባህሪ እንዳለው የሚካድ አልነበረም። ሃሳበ ግትሮችና ቂመኞች ሁሉ ይባረሩ ከተባለ ደግሞ ጠረጋው ከላይ መጀመር ይኖርበታል። ድርጅቱ በግትሮችና በቂመኞች የተሞላ መሆኑ ምን ያጠያይቃል?

ይህን ሁሉ እውነት እያወቅሁ ሱሌይማንን እንዳባርር ስታዘዝ በረከትን ፊት ለፊት ልላተመው ሳልችል ቀረሁ። ግን ለምን? ለስልጣን ፍርፋሪ ብዬ ይሆን? በፍፁም አይመስለኝም። የስልጣን ጥምና ፍላጎት እንደሌለኝ አይኔን ሳላሽ መናገር እችላለሁ። እንግዲያው ፈሪ ነኝ! የለም! እኔ ፈሪ ሰው አይደለሁም። በርግጥ ጠመንጃና አምባጓሮ አልወድም። እውነትን ግን አልፈራትም። ስለዚህ ሱሌይማንን እንዳባርር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የተሰጠኝን ትእዛዝ ፊት ለፊት ተጋፍጬ ያልመለስኩት ባለመብሰል ሊሆን ይችላል። በዚያን ወቅት በረከትና ሱሌይማን ወደ 40ዎቹ የተጠጉ ጎልማሶች ሲሆኑ፣ እኔ ገና የ20ዎቹ አጋማሽ ላይ ነበርኩ። ልምድ አልነበረኝም። የፖለቲካና የጠልፎ መጣል ተንኮሎችን አላውቅም። የሆነው ሆኖ በግምገማው እለት በረከት ያስታጠቀኝን ቦምቦች ይዤ ስብሰባው ላይ በመግባት፣ በግማሽ ልብ ሱሌይማንን በኦነግነትና በሙስና ልወነጅለው ሞከርኩ። ሆኖም ሱሌይማን እንደዋዛ እጁን አልሰጠም። አፋጠጠኝ። አዋከበኝ። ከመነሻውም በሙሉ እምነት የገባሁበት አልነበረምና ሳልገፋበት አፈገፈግሁ። በመሰረቱ 'ሱሌይማን ከዜናነህ መኮንን ላይ ጉቦ በልቶል' ብዬ ላሳምን አልችልም ነበር። ስንት ብር? ማን ነገረህ? በምን አረጋገጥክ? መልስ አልነበረኝም። 'ሱሌይማን ኦነግ ነው' የታለ ማስረጃው? የበረከት እቅድ ወዲያው ከሸፈ። "አሳ ጎርጓሪ - ዘንዶ ያወጣል" የሚለው ተረት እዚያው እኔው ላይ ተፈፀመ። በግልባጩ ሱሌይማን እኔ ላይ ዘመተብኝ። ተሰብሳቢዎቹ ከጀርባዬ አንድ የሚገፋኝ ሃይል እንዳለ ተረድተው አድማ መቱብኝና ከሃላፊነት እንድነሳ ወሰኑብኝ። ግምገማው እንዳበቃ ወደ አለምሰገድ ሄድኩ።

"እንዴት ነው ግምገማው?" አለኝ።

"አባረሩኝ" አልኩት።

አለምሰገድ ከት ብሎ ሳቀ። እኔ አልሳቅሁም።

"ምነው?" አለ።

"ሱሌይማን ተሰብሳቢዎቹን አሳደመብኝ። ያው እንደነገርኩህ በረከት ተፅእኖ አድርጎብኝ ነበር" አልኩ።

በዚያች ደቂቃ በረከትን እንደ ሰይጣን ጠልቼው ነበር። ትእዛዙን ለመፈፀም በመሞከሬ ፀፀት ይበላኝ ይዞአል። ይህን የመሰለ ወራዳ ተግባር ዳግም እንደማልፈፅምም ለራሴ ቃል እየገባሁ ነበር። አለምሰገድም በደንብ ገብቶት ነበር። ወደ አባይ ፀሃዬ ደወለና አጫወተው። የተጀመረው ግምገማ ተቋረጠና እንደ አዲስ በአባይ ፀሃዬ እንዲካሄድ ተደረገ። "በአድማ ተባርሬያለሁ" ብዬ ከሰስኩና ራሴን ለማዳን የግድ ሱሌይማንን ወደ ማጥቃት ገባሁ። አሁን ግን የኔና የሱሌይማን ጦርነት የምር ሆነ። ከልቤ ፍልሚያ ውስጥ ገባሁ። አባይ ፀሃዬ ያን ግምገማ ሲመራ ለኔ ወገናዊ ነበር ማለት አልችልም። በአድማ መባረሬን ግን ማሳመን ችዬ ነበር። ማስረጃ ሳይኖረኝ ሱሌይማንን በሙስና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እና በኦነግነት መወንጀሌም ቢሆን የሚያስወቅስ አልነበረም። በሂስና ግለሂስ ወቅት አባላት ያሻቸውን መናገር ይችላሉ። በዚህ ሽፋን ሱሌይማን ላይ የተሞከረው የማባረር ርምጃ ግን አልተነሳም። በግምገማው ማጠቃለያም የኔ ጠንካራ ጎኖች በደንብ ተነግረው በነበርኩበት የስልጣን ደረጃ እንድቀጥል፣ ሱሌይማን ከሃላፊነቱ እንዲነሳ አፀደቅን። በረከት እኔና ሱሌይማንን እንደ ቦክሰኛ ዶሮዎች አጋጭቶ አላማውን በከፊል ተፈፃሚ አደረገ። እኔ ከዚያች ግምገማ በሁዋላ የበግ ለምዱን አውልቄ ጣልኩ። በረከት ግን የበግ ለምዱን በተለያየ ዲዛይን እያሰፋ ይለብሰው ቀጥሎአል። ግምገማው አብቅቶ ከኢህአዴግ ፅህፈት ቤት ስንወጣ፣ ሱሌይማን መኪና አልነበረውምና፣ እንድሸኘው ጠየቀኝ፣ በርግጥ ከሌሎች ጋር ተዳብሎ መሄድ በቻለ። ሊያናግረኝ ስለፈለገ እንድሸኘው ጠየቀኝ። በኔ ላይ ያሳደረው ጥላቻ ገፅታው ላይ በግልፅ ይነበብ ነበር፣

"ወዴት ነህ?" አልኩት።

"ሬድዮ ጣቢያ ጣለኝ" አለ።

ወደ ሬድዮ ጣቢያ እየነዳሁ ሳለ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

"ማነው ከጀርባህ ያለው?"

"ምን እያልከኝ ነው?"

"ተገፍተህ ነው የዘመትክብኝ"

"አልዘመትኩብህም። ሂስና ግለሂስ ነው ያካሄድነው"

በበረከት የተሰራውን ድራማ ልነግረው እንደማልችል ግልፅ ነበር። ያን ቀን ሱሌይማንን ሬድዮ ጣቢያ አድርሼው ሳበቃ ወደ መጠጥ ቤት ነዳሁ። ሊነጋጋ ሲልም ጨርቅ ሆኜ ቤቴ ገባሁ። ሱሌይማን ችሎታ ያለው ሰው ብቻ ሳይሆን፣ ሃይማኖቱን የሚያከብር፣ የሚፆም፣ የሚሰግድ ብዙ ልጆች ያሉት የቤተሰብ ሰው መሆኑን አውቃለሁ።

ከዚያ ግምገማ በሁዋላ ስራ እንዲያቆም በመደረጉ ቤት እንደሚውል ሰማሁ። መኪታተሌን ቀጠልኩ። በኑሮውና በቤተሰቡ ላይ ችግር እየደረሰበት መሆኑን ስረዳ እረፍት ማጣት ያስጨንቀኝ ጀመር። በዚያው ሰሞንም አለምሰገድ ቢሮው ጠርቶ እንዳነጋገረው ሰማሁና በመጠኑ እፎይታ ተሰማኝ። በመቀጠል በፋና ሬድዮ ስር የኦሮሚኛ ፕሮግራም ሃላፊ ሆኖ ተመደበ። ወደ ተረጋጋ ሁኔታም ተመለሰ። እኔን ግን የእግዚአብሄር ሰላምታ እንኳ ነፈገኝ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አንድ ቀን ሽራተን ሆቴል በአንድ ግብጣ ላይ ድንገት ተገናኝተን ሰላምታ ሳቀርብለት ፊቱን አዞረ።

ይህ ከተፈፀመ ከአምስት አመታት በሁዋላ ከሱሌይማን ጋር የሚቀራረብ አንድ ሰው ፈለግሁና የይቅርታ ቃል ላክሁበት። የላክሁት ሰው በሶስተኛው እለት መጥቶ እንዲህ አለኝ፣

"በጣም ይጠላሃል።"

"ይቅርታውን አልተቀበለም?"

"አልተቀበለም! ተፀፅተሃል ብሎ አላመነም። የሆነ ሰው እንደላከህ ይጠረጥራል።"

"በማንም እንዳልተላክሁ ነግሬው ነበር" አልኩ።

"አላመነህም" ካለ በሁዋላ ለመናገር እያመነታ፣ "...እስከ ግምገማው እለት ጥሩ ወዳጆች እንደነበራችሁ፣ ሚዛናዊ ሰው ነው ብሎም ያምን እንደነበር ነግሮኛል፣ በዚያን እለት ግን የሃሰት ወሬዎችን ይዘህ ለምን እንደዘመትክበት እውነተኛውን ምክንያት ማወቅ ይፈልግ ነበር። በጥቅሉ ግን ሊያገኝህ ፍላጎት የለውም።"

"የጠረጠረው ነገር ይኖራል?" ስል አጥብቄ ጠየቅሁት።

"እሱማ ይኖራል።"

"ንገረኝ" አልኩት።

"የሆነ ሰው ካልላከህ፣ ኦሮሞዎች ላይ ጥላቻ ሊኖርህ እንደሚችል ያስባል።"

ጥቂት ተክዤ ቆየሁ።

ያን ድርጊት የፈፀምኩት በበረከት ታዝዤ መሆኑን ልነግረው ግን አልፈለግሁም። ዞሮ ዞሮ በረከት አሁንም የሁለታችንም አለቃ ነበር። በኦሮሞዎች ላይ የተለየ ጥላቻ እንዳለኝ የገመተውን ማስተባበል አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም። *"የቡርቃ ዝምታ"* የተባለው መፅሃፌ ማተሚያ ቤት ገብቶ እየተባዛ ነበር።

የቡርቃ ዝምታ ገበያ ላይ በዋለ በሁለተኛው ወር ግድም ፣ ነጋሽና አታክልቲ የተባሉ የህወሃት ካድሬዎች በሚመሩት ግምገማ ላይ የመፅሃፉ ጉዳይ ለግምገማ ቀረበ። ነጋሽ የሚገርም አስተያየት ሰጠ፣

'*የቡርቃ ዝምታ*' የሚባለው መፅሃፍ በአነግ፣ በሻእቢያ፣ በኢሰፓና በኢህአፓ ብቻ ሊወደድ የሚችል መፅሃፍ መሆኑን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንዳመጣለት ተነተነ። አታክልቲና ሴኮም የአቅማቸውን ተናገሩ። ታደሰ የተባለ የኦሮሚያ ጋዜጣ አዘጋጅም አፍንጫና አይን በሌላቸው ቃላት አወገዘኝ። ሱሌይማን ከስብስባው ተካፋዮች አንዱ ነበር። በጠጉሬ ልክ ጠላቶች ባፈራሁበት በዚህ ወቅት እኔ ላይ የበቀል ርምጃ ለመውሰድ ምቹ ጊዜ እንደሚሆንለት ገምቼ የሚናገረውን ለመስማት ስጠባበቅ፣ ዘግይቶ እጁን አወጣ። እድል ተሰጠው፣

"የቡርቃ ዝምታን የፃፍክበት አላማ ምንድነው?" ሲል ጠየቀኝ።

ምንም የተለየ አላማ እንደሌለኝ ገለፅኩ። አያይዤም የኛ ዘመን ሰው እንዴት ይኖርና እንዴት ያስብ እንደነበር የሚያሳይ ትረካ መሆኑን በአጭሩ አስረዳሁ።

ሱሌይማን ጥያቄውን በዚያው ገታ።

አታክልቲ ግልፅ ያልሆነ መረጃዎችን እያቀረበ፣ እኔ ከሻእቢያ ጋር ልዩ ግንኙነት ሊኖረኝ እንደሚችል ለማሳመን ሞከረ። ግምገማው አድካሚና የሚያሰለች ሆነብኝ። ሰአቴን ደጋግሜ እያየሁ አዛጋሁ። እነ አታክልቲን "የእግዜር ፍየሎች" የሚል ቅፅል ስም ሰጥቼያቸው ነበር። በግ እንዳትላቸው እንደ በግ የዋህ አይደሉም። ብልህ እንዳትላቸው የሚናገሩትን አያውቁም። ከተዋወቅሁዋቸው ጊዜ ጀምሮ እንደ ጄኔሬተር እንደተንደቀደቁ ናቸው። ብዙውን ጊዜ ማለት የሚፈልጉት አይገባኝም። የቡርቃ ዝምታ በሻእቢያ፣ በኢሰፓ፣ በኢህአፓ፣ በኦነግ ሊወደድ የሚችል መፅሃፍ መሆኑን ነጋሽ ተናገረ። ይሄ ምን ማለት ነው? ነጋሽ የሚናገረውን ስለማያውቅ እንጂ፣ የተጠቀሱት የፖለቲካ ድርጅቶች እንኳን በቡርቃ ዝምታ በፋሲካ በአል እንኳ ሊግባቡ አይችሉም። አንዳንድ ጊዜ ካድሬዎቹ ንግግር በማብዛት ጉሮሮአቸው ቃናውን ይቀይራል። ነጋሽ በተለይ በፕሮፓጋንዳው ክፍል በረጃጅም ዲስኩሮቹ ይታወቅ ነበር። ስብሰባ ላይ ንግግር ከጀመረ ስለማያቋርጥ እሱ እጁን ሲያወጣ ተስፋ እቆርጣለሁ። ነጋሽ መናገር ሲጀምር ምንጊዜም አንድ የሎሬት ፀጋዬ ግጥም ትዝ ትለኛለች፣

ባክህ ጃል አትንኳኳብኝ -እደጅ ውጣና አጓራ፣
ይህን የሃሳብ ነጎድጓድክን -እላዬ ላይ አታባራ፣

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በመሰረቱ የቡርቃ ዝምታን በመድረክ ላይ እየተቃወሙ እኔን ለማውገዝ ምንም መብት አልነበራቸውም። የመፃፍ ነፃነት ተፈቅዶአል። አሳብ ካላቸው አስተያየታቸውን ጋዜጣ ላይ መፃፍ ነው መብታቸው።

በዚያን ቀን ለምሳ እንደተበተንን ጥቂት አሰብኩ። ከሰአት ወደ ስብሰባው ላለመሄድ ወሰንኩ። ደብረዘይት ሂጄ ሆራ ሃይቅ ዳርቻ ቀዝቃዛ ቢራ መጠጣት እንደሚሻለኝ አመንኩ። ሽው አልኩ ወደ ቢሾፍቱ። ሁዋላ እንደሰማሁት እኔ በሌለሁበትም ሲያወግዙኝ አምሽተው ነበር።

ሱሌይማን በዚያን ቀን እስኪደንቀኝ ድረስ በዝምታ ማዳመጡ ገርሞኝ አመሸ። ምን እንደሚያስብ ግን ሳላውቅ ቀረሁ። ያቀረበው ጥያቄም ትሁት ጥያቄ ነበር። አንዳንድ የጋራ ወዳጆቻችን ስለኔ ጉዳይ ሲያነሱለት አንዳችም አስተያየት እንደማይሰጥ ነገሩኝ። እኔን ለማጥቃት ምቹ ጊዜ አግኝቶ ሳለ፣ ለምን እንዳልተጠቀመበት አጥብቄ አስብም ነበር። ማመን ግን አልቻልኩም። ከቂመኛነት ባህርይው ስነሳ፣ ከጀርባ አንድ ድራማ አልሰራብኝም ብዬ ለማመን እቸገራለሁ። የሆነው ሆኖ በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለን እኔ ሃገር ጥዬ ኮበለልኩ። ሱሌይማን ደግሞ አምባሳደር ሆኖ መሾሙን ይኸው ድረገፅ ላይ እያነበብኩ ነው። ይህ መፅሃፍ ታትሞ ሲወጣ የዚያን ስብሰባ ምስጢር እንደሚያገኝ አምናለሁ። የበግ ለምድ ከለበሰ ተኩላ ጋር ባንድ ጎጆ ውስጥ እንደሚኖር ለመገንዘብ እድል ያገኛል። በርግጥ ጠላቶች በበዙብኝ በዚያ አስከፊ ወቅት እኔን ለማጥቃት ያልሞከረ ከሆነ ግን አመሰግነዋለሁ። አምባሳደርነት በመሾሙ በርግጥ፣ "ሹመት ያዳብር" ልለው አልችልም። እሱን የሾመው ስርአት፣ እሱ የሚያገለግለው አገዛዝ እድሜ እንዲራዘም ልፀልይ አልችልም። "ሹመትህን ያዳብርልህ" ብሎ መመረቅ ባህላችን ነው ከተባለ ግን መቼስ ምን ይደረግ፣ ደራሲና ገጣሚ ታገል ሰይፉ በቋጠራት አንድ ግጥም "እንኳን ደስ ያለህ!" ልለው እችላለሁ፣

ከፍ በል ወደ ላይ.....
ከሰልጣኑ ሰማይ፣ ከሰም አደባባይ፣
በሃብት ከፍ ከፍ፣ ከፍ ከፍ - ከፍ ከፍ፣
ከዚያ የወደቅክለት - አጥንትህ እንዳይተርፍ፤

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 28 -

ፅጌረዳን ዳግም አየሁዋት

ፊትህን እይና - በመስታወት ፊት፣
እንዲህ በል ንገረው - "አንተ የኔው ፊት፣
አሁን ነው መተግበር - ሌላ ፊት መስራት፣
እድሜህም እንዲሁ - ያንተ መስታወት፣
አይንህን በአይንህ - የምታይበት፣
ልረሳ ካልክ ግን - ልሁን አልባሌ፣
ስትኖርም ባተሌ - ስትሞት ባተሌ፣

(ግጥም - ተስፋዬ ገሰሰ)

* * *

ሲወዱኝ ጠልቼ - ሲጠጉኝ ሸሽቼ፣
ሰፈራን ወለላ - እሬት ቀባብቼ፣
ላቤን ጠብ አደርጌ - ሌት ከቀን ለፍቼ፣
ፍቅርን ገደልኩት - ሞቼ ተሙዋሙቼ፤

(ግጥም - ቶማስ አርጋው)

ፅጌረዳ የሃንስ ዛሬ እህቴ ሆናለች። በጣም እወዳታለሁ። መወለድ ምን ያደርጋል? ጎረቤት ነበርን። በቤቶቻችን መካከል ያለው ርቀት ከአንድ ኪሎሜትር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አይበልጥም ነበር። ፅጌረዳ ቆንጆ ልጅ ናት! የመጀመሪያ ፍቅረኛዬ ነበረች። የፍቅር አይኔን የከፈትኩት በዚህች ውብ የቢሾፍቱ ቀጤማ ነበር። ከዛሬ ነገ ሊጋብቻ እጠይቃታለሁ እያልኩ መንታ መንገድ ላይ ቆሜ ሳመነታ፣ አግብታ አራት ከወለደች አስር አመት አለፈው። ፅሁፌን ስጀምር 'እህቴ' የሚለውን ያስቀደምሁት የሷ ነገር ያለቀለት ስለሆነ ነው። እሷ አንድ በወለደች ቁጥር እኔ አንድ መፅሃፍ እያሳተምኩ ይኸው በወዳጅነታችን ፀንተናል። ፅጌረዳ ዛሬ በስዊድን አገር በስደት ትኖራለች። ጥራ ግራ ቤተሰብዋን ትመራለች!

በ1998 በገና በአል ዋዜማ ፅጌረዳ እኔን ለመጠየቅ ፕሪቶሪያ መጥታ ነበር። ለአንድ ሳምንት እረፍት ወደ ኬፕታውን ወስጄ ማንዴላ የታሰረበትን የሮቢን ደሴት አስጎበኘሁዋት። ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ዳርቻ ከአስደናቂው Water Front ላይ ተቀምጠን የአሳ ጥብስ አዝዘን ቢራችንን ማጣጣም ጀመርን።

ፅጌረዳ የደብረ ዘይት ወሬዎችን እያመጣች ስታወጋ ወሬ ከማብዛቷ ብዛት ጆሮዬ ውስጥ ልትገባ ምንም አይቀራት፣

"ገዙ አባ ነፍሶ እኮ ሞተ"

"ኸረ ባክሽ?" አልኩ አዝኜ "...ምን ሆኖ ሞተ?"

"ምን ሆኖ እንደሞተ የሚያውቅ የለም። የሆነው ሆኖ ሞቶአል። እህትማማቾቹ የአለምወርቅና ቀለመወርቅም ሞተዋል። በአንድ ቀን በመኪና አደጋ ነው የሞቱት። አባትዬው የሁለቱንም ስም በየተራ ከመጥራት ብሎ ለለቅሶ እንዲያመቸው ባጭሩ 'ወርቆቼ፣ ወርቆቼ' እያለ ሲጮህ ነበር አሉ። የቢሾፍቱ ተራቢዎች ደግሞ 'ወርቅ የተሰረቀበት ነበር የሚመስለው' እያሉ ሲያሽሟጥጡ ዋሉ..."

"ወይኔ ገዙ አባነፍሶ?" አልኩኝ በትዝታ ወደሁዋላ ተመልሼ። ገዙን በአንድ ነገር በፍፁም አልረሳውም።

* * *

....አንድ እሁድ ቀን በደብረዘይት መንገድ የትሩማንትሪው ጥላ ስር በመኪና ውስጥ ተቀምጬ "እፍታ" ለተባለው መፅሃፍ የቀረቡ ፅሁፎችን እያነበብኩ ሳለ፣ ገዙ ከተፍ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አለና የሞቀ ሰላምታ አቀረበልኝ። ጫት በአፉ ግጥም ብሎአል። ጠጉሩ አልተበጠረም።

"መኖር አቃተኝ ባክህ፤ ራሴን ልገድል እያሰብኩ ነው"

"አብደሃል?" ስል ጮህኩበት "ምን ችግር ገጠመህ?"

"ባዶ ሆዴን ነው የምቅመው"

ድንጋጤዬ መለስ አለልኝ። ራሱን ስለ መግደል የሚያወራው ያው አስር ብር ፈልጎ ነው፤ ግን ያልተረዳሁ መሰልኩ፣

"ምን መሰለሽ ተስፈሽ..." ሲል ቀጠለ "...ስራ አቋረጥኩ። ሆራ ላይ Life saver ነበርኩ። አሁን ሆራን አላመዱ ገዛውና ስራ ቆመ። ችግር መጣ..."

አስር ብር ሰጠሁት።

"ልጅ እንደወለድኩ አውቀሃል?" ሲል ጠየቀኝ፤ የሰጠሁትን አስር ብር ፈጥኖ ወደኪሱ እየጨመረ፣

"ኸረ አላወቅሁም፤ መቼ ወለድክ?"

"እስር ቤት እያለሁ ነው የተወለደችው"

"ታስረህ ነበር እንዴ?"

"አልሰማህም?"

"በጭራሽ!" አልኩ " ለምን ታሰርክ?"

"አንድ የጠገበ ሃብታም ነበር። ታውቀዋለህ! ሃይሌ ቅቤ! 'ገንዘቤን የምጥልበት አጣሁ' እያለ ሲያስቸግር ሌሊት ሄድኩና ተቀበልኩት። በዚያ ጦስ ሁለት አመት ታሰርኩ..."

"ተቀበልኩት ስትል..."

"ሌሊት ቤቱ ገብቼ የሳሎኑን ዋና ዋና እቃዎች ይዤ ወጣሁና ሸጥኳቸው። ፖሊስ እንደምታውቀው ስራ ፈት ነው። ይህን እንደ ጥፋት ቆጥረው ሁለት አመት..."

"ታዲያ እንዴት ወለድክ?"

"ከመታሰሬ በፊት አንዷን አስታቅፈያት ነበር። እንዋደዳለን። ጥሩ ልጅ ነበረች"

"አሁን ታዲያ ልጅህን እያሳደግህ ነው?"

"እኔማ ምን ገንዘብ አለኝ? ሆኖም ስፖንሰር ተገኝላት። ግን ምን ያረጉኛል መሰለህ? 50 ዶላር ከተላከ 20ውን ቀንሰው ለራሳቸው ያደርጋሉ ይባላል። ወልጄ ለሌላ ሲሳይ ሆንኩ!"

"አይ! ዋናው ልጅህ ከተማረች ጥሩ ነው"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"እሱማ አዎ! ግን የልጄን ብር ሌላ ከሚበላው እኔ ብቅምበት አይሻልም?"

"ማነው ስፖንሰር ያገኘላት?"

"እሱማ ራሳቸው ናቸው! በኔ ልጅ እነሱ መክበራቸው ነው ያናደደኝ!"

"ስራ ስታገኝ ልጅህን ራስህ ታሳድጋለህ! እስከዚያው ግን መታገስ ይሻላል" ስል አፅናናሁት።

"ልክ ነህ። ያንተ ምክር ሁልጊዜ ያስደስተኛል"

ዘግየት ብዬ ጠየቅሁት፣

"ስራ ከሌለህ ታዲያ ጊዜህን በምን ታሳልፋለህ?"

"ድርሰት እፅፋለሁ"

"ኸረ ባክህ?" አልኩ ገርሞኝ።

"ላንተ አክብሮት ያለኝ'ኮ ተመሳሳይ ሙያ ስላለን ነው"

"አላውቅም ነበር"

"ቆይ ላሳይህ" አለና ከጆርባው ሱሪ ኪስ ውስጥ የወሸቀውን ደብተር አውጥቶ ሰጠኝ።

በችኮላ ገለጥኩት።

ልቅም ያለ ጥሩ የእጅ ፅህፈት ነበር። እንደዋዛ ማንበብ ጀመርኩ። ፍልስፍና ቢጤ ነው። ስለ ህይወት የሚተነትን። ቃላቶቹንና ሃረጎቹን ከዚህ ቀደም እንዳነበብኳቸው ታወሰኝ። ግን የት ነበር? ...አዎን! የበአሉ ግርማ 'ደራሲው' ላይ... ሲራክ አርአያ የተባለው ገፀ - ባህርይ ብቻውን የሚያወራቸው ነበሩ።

"ይህማ ከበአሉ ግርማ ድርሰት የተገለበጠ ነው" አልኩ።

ገዙ አባነፍሶ አልተከራከረኝም፤

"ተስፍሽ... እኔ የበአሉ ይሁን የማን አላውቅም... የእጅ ፅህፈቱ ግን የኔ ነው። እስኪርቢቶ ካለህ ስጠኝና እዚሁ ላሳይህና ልታመሳስለው ትችላለህ..."

ለጥቂት ሰከንዶች በዝምታ ቆየን፣

"የእጅ ፅህፈትህ ግን ቆሎ ነው" ከማለት ሌላ የምለው አልነበረኝም።

ገዙ በተረጋጋ ሁኔታ ምላሽ ሰጠኝ፣

"ቤተሰባችን በሙሉ ፅህፈታችን እንደዚሁ ነው። ግን ምን ዋጋ አለው...ችሎታ ቢኖረኝም በባዶ ሆዴ እየቃምኩ ነው..." ሲል አማረረ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አሁን ፅጌረዳ ገዙ አባነፍሶ፤ ያ የቢሾፍቱ ዜጋ! እንደሞተ እየነገረችኝ ነው። ምን ሆኖ ይሆን የሞተው?

* * *

ፅጌረዳ ጆሮዬ ውስጥ እንዳትገባ እየተከላከልኩ አዳምጣታለሁ፣

"ጓደኛህ ነቢዩ አበበ አሜሪካ መሄዱንና በጣም ቆንጆ ሚስት ማግባቱን ሰምተሃል?"

"ሰምቻለሁ"

"የደሞዙን መጠንስ?"

"አልሰማሁም"

"በየወሩ እቁብ ይበላል ነው የሚባለው። ሆስተሷ ጓደኛህንስ ታገኛታለህ?"

"በፍፁም። ሁለት ልጆች መውለዷን ግን ሰምቻለሁ።"

"ሙሊታንስ ታስታውሰዋለህ?"

"ማነው እሱ ደግሞ?"

"ዘጠኝ አህዮች ያሉት፣ ጥቁቁር ድንጋዮች እየጫነ በኛ ሰፈር የሚመላለሰው ሙሊታ ባለ አህያው? የጭቃ ለጣፊው የሳለቤቱ ጎረቤት..."

የምትጠራቸውን ስሞች ሁሉ የረሳሁዋቸው ሲሆን፤ ጥቋቁር ድንጋዮችን እየጫኑ በበራችን የሚያልፉት አህዮች ግን ትዝ ይሉኛል። ለማንኛውም ግን ለፅጌረዳ ወሬውን ቀጠልኩላት...

"እሺ ባለ አህያው ምን ሆነ?"

"አይኑን ታወረ! ሄጄ ጠይቄው ነበር፤ መቶ ብር ለቡና ብዬ ስሰጠው ፊቴን እየደባበሰ መረቀኝ። 'የረገጥሽው ለምለም፤ የተናገርሽው ቀለም ይሁን' ብሎ መረቀኝ። ደብረዘይት የሄድኩ ጊዜ በሻንጣ ሙሉ ምርቃት አፍሼ ነው የተመለስኩት። ከነሚልክያስ ጋር ሆናችሁ ሆራ ላይ የሰረቃችሁት አገልግል ሙሉ የዶሮ ፍርፍር ትዝ ይልሃል?"

"እሱ መቸም አይረሳኝም!" አልኩ ትዝታው ፊቴ ድቅን እያለ።

"ዶሮውን ከበላችሁ በሁዋላ አገልግሉን ለባለቤቶቹ አራት ብር እንደሸጣችሁላቸውስ?"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ትዝ አይለኝም"

"እኔ ለምን እንዳልረሳሁት ልንገርህ? 'ምግባቸውን መብላታችሁ ሳይበቃ አገልግሉን እንዴት ትሸጡላቸዋላችሁ?' ብዬ ሚልኪያስን ስጠይቀው ምን እንዳለኝ ልንገርህ?"

"ምን አለሽ?"

"ወላጆቻቸው በአገልግሉ መጥፋት እንዳይቆጧቸው ብለን ነው' ነበር ያለኝ!"

"ውሸትሽን ነው" ስል ተቃወምኩ "...ያን ያህል ግፈኞች አልነበርንም"

"ማርያምን!" እያለች ትስቅ ቀጠለች "...አንተ ግን በጣም ትረሳለህ" አለችኝ።

"አንቺ የማያስፈልግሽን ሁሉ እያስታወስሽ እንዳይሆን!"

"እሺ ሌላውን ተወው! እኔና አንተ እንዴት ነበር የተዋወቅነው?"

"ትምህርት ቤት ነዋ"

"አይደለም! ከነቹቹ ቤት ወተት ይዤ ስመለስ 'ለምንድንነው ሰላም የማትይኝ?' ብለህ ስትታገለኝ ወተቱ ተደፋ። ከዚያ እናቴ ለእህትህ ነግራ ተገረፍክ..."

"እሱማ በሁዋላ ነው ...እኔ ከዚያ በፊት ትምህርት ቤት አይቼሽ ውድጄሽ ነበር። ያኔ አንቺን ባልወድ ኖሮ ዛሬ እንዲህ አይምታታብኝም ነበር። ፍቅር አንድ ጊዜ ነው የሚባለው ግን እውነት ነው። አሁን ይኸው ሁለታችንም ሽበት ወርሮናል፤ ላንቺ ያለኝ ፍቅር ግን እስካሁን..."

"ዝም በል! ወሬኛ! አንተማ መቼም ፍቅር ይዞህ አያውቅም። እኔን ወድጄሻለሁ እያልክ ለርብቃ ደግሞ አስር ገፅ የፍቅር ደብዳቤ ትፅፍላት ነበር። አሳይታኛለች! እንዲያውም ማንበብ ደክሞአት አልጨረሰችውም"

ይህን ብላ ተንከትክታ ትስቅብኛለች!

"ርብቃ! አፈንጋጭ ባህርይዋ ደስ ይለኝ ነበር፤ እውነት ለመናገር ያንቺኮ ሁሉ ነገርሽ ነበር..."

ፅጌረዳ በመደነቅ ታየኝ ጀመር፣

"አሁንም ደ'ሞ ልታምታታ ትሞክራለህ? መሰረትንም ትወዳት ነበር"

"እሷንማ ማን የማይወድ ነበር? የሰፈሩ ተማሪ ሁሉ ነበር በፍቅር ያበደላት። ለመሆኑ ስለ እሷ ወሬ አለሽ? "

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“አንድ ኢንጅነር አግብታ ሁለት ወልዳለች። አንድ የውጭ ድርጅት ውስጥ ፀሃፊ ሆና እየሰራች ነው። እንዳማረባት አለች...”

አያያዘችና ቀጠለች፣

“ሄለን ከምትባል ልጅ ጋር ደግሞ ፍቅር ጀምረህ ነበር ሲባል ሰማሁ።”

“መጀመር አይባልም” ብዬ ተቃወምኩ፣ “...አንድ ቀን ቤቷ ጋበዘቺኝ! በዚያው አበቃ!”

“ለምን አበቃ?”

“አትሆንኝም።”

“እኮ ለምን?”

ዘርዝሬ አጫወትኳትና አሳመንኳት። እንዴት ተጀምሮ እንዴት እንዳለቀ ላውጋችሁ....

* * *

ሄለን ውብ የሃረር ልጅ ናት።

ውበትዋ አይንዋ ላይ ነው። ምን አለፋችሁ? እንጋባ ብዬ ልጠይቃት ምንም አልቀረኝም ነበር። በጨዋ ደንብ አርፌ በተቀመጥኩበት ራሷ ቆስቁሳ ነበር የተዋወቀቺኝ። ከዚያም ቤትዋ ጋበዘችኝ። ማንም ቢሆን ያንን ግብዣ ሊዘለው አይችልም ነበር።

ቤቷ ስደርስ ሉባን ዘከር እጣን ቀጥ ብሎ እየወጣ ከጣራው ይጋጫል። ረከቦቱ - ቁጤማው - ፍራሹ ተፈርሾ - በአናቱ ደግሞ ደብረዘይት ላይ መሆኑ ተጨምሮበት - አለም መዳፌ ላይ ቁጭ አለች።

“ከጎንህ ልቀመጥ?” ስትል ጠየቀችኝ

“በደስታ!”

ከጎኔ ተቀመጠች።

ሰብለ የምትባል ልጅ ቡና እያፈላችልን ነው። ሄለንን ያስተዋወቀችኝ ሰብለ ናት።

...በእለተ ቅዳሜ በደብረዘይት መንገድ ላይ በትራማንትሪው ጥላ ስር እንደተለመደው መኪናዬ ውስጥ ተቀምጬ *“የቡርቃ ዝምታ”* የተባለውን መፅሃፍ እየፃፍኩ ነበር።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሰብለ በዚያ በትሩማንትሪ ጥላ ስር ለሚዝናኑ ባለመኪኖች ሻይ በመሸጥ ትተዳደር ኖሮአል።

ያን ቀን ሰብለ ሻይ አቀረበችልኝ።

"እድሜሽ ስንት ነው ሰብለ?"
ሳቀች።
"እስኪ ገምት?"
"18 ይሆንሻል?"
"ተሳስተሃል 19'
"እየተማርሽ ነው?"
"አቋርጫለሁ"
"ለምን?"
"ታናናሾቼ እንደማሩ ብዬ። እናቴን አግዛታለሁ"
"አባትና እናትሽ ምን ይሰራሉ?"
"አባቴ የለም፤ ሞቷል። እናቴ እንጀራ ጋጋሪ ናት"

ገፅታዋ ላይ የሃዘን ድባብ ስላጠላ ወሬ ቀየርኩ፣

"ቆንጆ እንደሆንሽ ታውቂያለሽ?"
"አውቃለሁ"
"በምን አወቅሽ?"
"በመስታወት አየሁት"

ይህን ብላ አይኖችዋን በልጥጣ ሳቀች። ከዚያም ግራና ቀኝ ገልመጥመጥ አለች። ሻይ የመሸጫ ጊዜዋን እየተሻማሁባት መሆኔን ተረዳሁ።

"በወሬ ጠመድኩሽ አይደል?"
"አዎን"
"መሄድ ፈልገሻል?"
"አዎን"
"በይ ሂጅ እንግዲህ! ጊዜሽን አልግደልብሽ። ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ግን ቡና አምጭልኝ..."
"እሺ!"

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ቡና ይዛልኝ ስትመጣ በተገላቢጦሹ እሷ ጠያቂ እኔ ምላሽ ሰጪ ሆንን፣

"የደብረዘይት ልጅ ነህ እንዴ ለካ?"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"አምን!?"
"የኛ መሆንህን ሳውቅ ደስ አለኝ" ብላ ሳቀች።
"ማን ነገረሽ የደብረዘይት ልጅ መሆኔን?"
"የሚያውቁህ አሉ"
"ማን?"
"አታውቃትም!"
"ማናት?"

ሰብለ ፊትዋን እኔ ካለሁበት ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ መልከት አደረገች። ሁለት ሴቶችና አንድ ወንድ በትሩማንትሪው ጥላ ስር ምንጣፍ ዘርግተው ጫት ይቅማሉ።
"ጥቁር የለበሰችው ልጅ ያንተን መፅሃፍ አንብባለች። እሷ ነው የነገረችኝ"

መላ ሰውነቴን አተኮሰኝ።
ጥቁር የለበሰችውን ልጅ ገና መኪናዬን ሳቆም ነው ያየሁዋት። ሆኖም አንድ ወንድ መሃላቸው ስላለ ደግሜ አላተኮርኩባትም እንጂ አስደንጋጭ ውበት እንዳላት ታዝቤ ነበር።
"እና ምን አለችሽ?"
"ምንም አላለችኝም። ግን ብቻህን ከምትሆን ለምን ከነሱ ጋር ቁጭ አትልም?"
"ያንቺ ሃሳብ ነው የሷ?"
"ምኑ?"
"ምን አለችሽ ስለኔ?"

ሳቀች! ስትስቅ ያምርባታል!

"እንዳትነግራት እንጂ 'ና' በይው ብላኛለች!"
ወዲያው በደስታ ብዛት እንባ ተናነቀኝ።
"አብሮአቸው ያለው ወንድ ማነው?"
"ዘመዳቸው ነው፤ ችግር የለውም!"
"እና ሄጄ አብራያቸው ቁጭ ልበል?"
"ምን ችግር አለው? የቢሾፍቱ ልጅ አይደለህ እንዴ?"

ሰብለ በዚህ መንገድ ነበር ከሄለን ጋር ያስተዋወቀችኝ። ከዚያም ሄለን ቤታ ጋበዘችኝ። እናታ ቁልቢ ሄደው ነበር። ሰብለ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ቡና እያፈላች ነው። ተደስተናል።

'ይህ ውበትና ፍቅር ምናለ ለዘላለሙ ቢቀጥል?' እያልኩ በማሰላሰል ላይ ሳለሁ ሄለን ከተቀመጠችበት ተነሳች፣

"ወዴት ነሽ ታዲያ?" አልኩ መነሳቷን እየጠላሁ።

"አልበም ላሳይህ ብዬ ነው"

"እ! በጣም ጥሩ ነው! አልበም ማየት እወዳለሁ" አልኩ።

እውነት ለመናገር ግን አልበም ማየት አልወድም ነበር። ወፍራም አልበም ይዛ መጣች። ተጠጋግተን ተቀምጠናል። በአፍዝ አደንግዝ አይኖችዋ ባየችኝ ቁጥር መላ ሰውነቴን ደስታ ይነዝረኝ ጀምሮአል። ሄለን አልበሟን ይዛ ተጠግታኝ ተቀመጠች።

የሄለን አልበም!!

የመጀመሪያው ፎቶግራፍ ያልጠበቅሁት ነበር። ሄለን ጋውን ለብሳ የተነሳችው ፎቶግራፍ። ኮስተር ብላ ትታያለች። በፍፁም ኮሌጅ ቀመስ ናት ብዬ አልገመትኩም ነበር። ቀና ብዬ አየሁዋት፤ በሚያምሩ አይኖችዋ እያየቺኝ ፈገግ አለች፣

"የኔ መስሎህ ነው?" ስትል ጠየቀችኝ።

"ማለት?"

"አንድ ዘመዴ ከዩኒቨርሲቲ ሲመረቅ አጋጣሚውን በመጠቀም ነው የሱን ጋውን ለብሼ ፎቶግራፍ የተነሳሁት"

ምላሽ ሳልሰጥ አልበሙን ገለጥነው።

ሄለን አጭር ቀሚስ ለብሳ አዋላ ሃይቅ ዳርቻ የተነሳችው ፎቶ ነበር። አይስክሬም እየላሰች የሚያሳይ ፎቶ ቀጠለ። ባንድ የዘንባባ ዛፍ ስር መነፅር አድርጋ ጥቁር አጭር ቀሚስ ለብሳም ተነስታለች። ቁምጣ ለብሳ ቴኒስ እየተጫወተች የሚያሳይ ፎቶግራፍም ተከተለ፣ ሰውነትዋ በጣም ያምራል፣

"ቴኒስ ትጫወቺ ነበር" ስል ጠየቅሁዋት።

"ስፖርት አልወድም። ለፎቶው ስል ብቻ ነው"

ከሴትና ከወንድ ጓደኞቿ ጋር ልብሳቸውን እየተለዋወጡ ከሆራ ሃይቅ ዳርቻ የተነሷቸውን ብዙ ፎቶግራፎች እያየን አለፍን። በመቀጠል ሄለን በአበቦች መሃል ቁጭ ብላ የተነሳችው ፎቶግራፍ ላይ ደረስን!

"አበቦችን በጣም እወዳለሁ"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“እውነት?”

“እንደኔ አበባ የሚወድ የለም!”

በመቀጠል ሄለን አንዲት በእድሜ የገፉ ሴት አቅፋ የተነሳችው ፎቶ መጣ።

“ማን ናቸው እኚህ?”

“እናቴ ናት። በጣም ነው የምወዳት! ለዚህ ቁም ነገር የበቃሁት በእናቴ እርዳታ ነው። እናቴ ባትኖር ኖሮ ‘ዛሬ ሄለን የት ትሆን ነበር?’ ብዬ ሳስብ እደነግጣለሁ። በተለይ ጓደኞቼ ያሉበትን ቦታ ሳይ....”

“ጓደኞችሽ የት ናቸው ዛሬ?”

“ምን ያደርግልሃል?” አለች ፈገግ ብላ።

አልበሟን ገለጠችው።

የአየር ሃይል የፓይለት ልብስ ከለበሱ ወጣቶች መሃል የተነሳችው ፎቶ ነበር። ከፓይለቶቹ አንዱ ዘመዷ መሆኑን ነግራኝ ገለጠችው። በአንድ ግብዣ ላይ ምግብ እያነሱ ይታያል። በመቀጠል ሞላላ አፍንጫ ያለው አንድ ነጭ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ የተነሳችው ፎቶግራፍ ነበር።

“ይወደኝ ነበር” አለች “...ሆላንድ ልውሰድሽ ብሎኝ እንቢ አልኩት። እናቴን ጥዬ መሄድ አልፈልግም”

አልበሙ ሲገለጥ አንድ ጢማም ወጣት ወንድ ብቅ አለ። ሄለን ባልተጠበቀ ሁኔታ አልበሙን እኔ ላይ ጥላ ፊቷን በሁለት እጆቿ ሸፍና እየተንሰቀሰቀች ማልቀስ ጀመረች። በመከራ አባበልኳት። ማልቀሷን ካቆመች በሁዋላ፣

“አጎቴ ነው” አለች።

“በጣም ትቀራረቡ ነበር?”

ራሷን ላይ ታች ከነቀነቀች በሁዋላ፣

“የኔን ሰርግ ለማየት ይመኝ ነበር። ሁልጊዜ ‘ባንቺ ሰርግ ላይ መኪናውን የምነዳው እኔ ነኝ’ ይለኝ ነበር። ድንገት ሞት ቀደመው!”

ሃዘኗን ለማረሳሳት ብዬ አልበሙን ገለጥሁት።

ሌላ ነጭ አቅፎአት የተነሳችው ፎቶግራፍ ነበር።

“እንዋደድ ነበር። ጀርመናዊ ነው። ሜሪ እያለ ነበር የሚጠራኝ። ሚስት ስለነበረችው ተለያየን። ያላገባ ቢሆን ኖሮ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ግን መጋባታችን አይቀርም ነበር"

አልበሙን ገለጥነው።

Panasonic TV ተደግፋ የተነሳችው ፎቶ ነበር። አብራራችልኝ፣

"ቲቪው የተገዛ ጊዜ ለማስታወሻ የተነሳሁት ነው"

ያን ቀን እንደምንም ከዚያ ቤት ወጣሁ። በፍፁም አልተመለስኩም። አግኝቼያትም አላውቅም። ሰብለን ግን አልፎ አልፎ በዚያ መንገድ ሳልፍ ሻይና ቡና ስትሸጥ አያት ነበር...

* * *

ተርኬ ስጨርስ ፅጌረዳ በሳቅ ትንከተከት ነበር።

"አላምንህም" አለች።"...አውቅሃለሁ። በጣም ታጋንናለህ"

በቃጅማው ጊዮርጊስ ስምልላት አለማጋነኔን አመነች። እናቴ የተቀበረችው ቃጂማ ጊዮርጊስ ስለሆነ "በቃጅማው" ከማልኩ እውነት መሆኑ ይታወቃል።

* * *

ለደቂቃ ያህል ፅጌረዳ ተክዛ ከቆየች በሁዋላ፣

"ያኔ ቀውሰህ የነበረ ጊዜ ትዝ ይልሃል?" ስትል ጠየቀችኝ።

"ሁዋላ ሲወራ ሰማሁ እንጂ ትዝ አይለኝም"

"በአሉ ግርማ...ምናምን እያልክ ትለፈልፍ ነበር..."

"ከልጅነቴ የስነ ፅሁፍ ፍቅር ስለነበረኝ ነዋ" አልኳት።

"ስነፅሁፍ...አይደለም ባክህ! ኑሮ ነበር ያቀወሰህ!"

እንዲህ እያለች ከትከት ብላ ስትስቅ ልስማት ፈልጌ ነበር። ባለትዳር ስለሆነች ራሴን ገታሁ። ፅጌረዳ ስትዘረጥጠኝ ደስ ይለኝ ነበር። እንዳለችውም በአንድ ወቅት የአእምሮ መቃወስ የደረሰብኝ በዚህ መፅሃፍ ለመግለፅ በሚከብደኝ የቤተሰብ መጎሳቀል ሳቢያ መሆኑ የማይካድ እውነት ነበር። ከጓደኞቼና ከቤተሰብ እንደሰማሁትም በደብረዘይት ንግድ ባንክ አጠገብ ከሚገኘው ተድላ ሙዚቃ ቤት ደጃፍ ላይ በቦብማርሌይ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሙዚቃ ደንሻለሁ። አቶ እውነቱ ሞላ የተባሉ የከተማዋ ሃብታም ነጋዴ ባደረጉልኝ ርዳታም አእምሮዬ ወደ ነበረበት ለመመለስ ችሎአል። ፅጌረዳ ባታስታውሰኝ ግን ይህን ከባድ የህይወቴን ገጠመኝ ፈፅሞ ረስቼው ነበር።

ለሰከንዶች ያህል በዝምታ አትላንቲክ ሲደነፋ ስትመለከተው ቆየች። የተሰየቱ ንፋስ ውቅያኖሱን ያናውጠው ይዟል። Water Front ደጁ ላይ ተቀምጠናል። ነጭ ቱሪስቶችን ጭና ወደ ሮቢን አይላንድ የምትጓዝ ትልቅ ሰማያዊ ጀልባ በርቀት ትታየናለች። ነጫጭ የባህር ወፎች በአናታችን እየዘመሩ በሙዚቃቸው ያዝናኑናል። ደስ ብሎናል። ፅጌረዳ የበለጠ ደስ እንዳላት ተረድቼያለሁ።

"ሳትነግሪኝ ቶሎ ብለሽ ያገባሽው ለምንድነው?"

"ባሌ ልትሆን እንደማትችል አውቅ ነበር። እኔ ልጅ ለመውለድ ጓጉቼ ነበር። አንተ መፅሃፍ አርግዘህ ነበር። ልረብሽህ አልፈለግሁም። ደሞም አላምንህም ነበር፤ ልብህ ተከፋፍሎ ነበር፤ በዚህ ላይ ትእግስት ያንስሃል። በህይወቴ ሙሉ እንዳንተ ትእግስት ያጠረው ሰው አይቼ አላውቅም። በጣም ያሳስበኛል ያንተ ነገር"

"ለኔ ምንም ስሜት አልነበረሽም?"

"መንገድ እያስቆምክ ወተቴን መድፋት ስትጀምር እወድሃለሁ ብዬሃለሁ"

"አንቺ ጉረኛ!" አልኩ በጣም ገርሞኝ።

"የሆነው ሆኖ አሁን ወንድሜ ነህ! ደ'ሞም ጓደኛዬ ነህ። ባሌ መሆን አትችልም አልኩኝ እንጂ ካንተ ጋር የምግባባውን ያህልማ ከማንም ጋር አልግባባም..."

"ካልሽ ይሁንልሽ፤ አሁን ግን ለማግባት ወስኛለሁ" አልኳት።

"ከሃያ አመት በፊትም እንዲሁ ብለሽኝ ነበር። አሁን አርባ ሊሞላህ ምን ቀረው? ሽበት ጀምሮሃል። ለማግባት ትፎክራለህ እንጂ መቼም አታገባም። የአንተን ስም ከነአባትህ እንጂ ከነሚስትህ ልንጠራ አልቻልንም"

"የአሁኑ ግን የምር ነው" ስል ፎከርኩ።

ፅጌረዳ ዘግየት ብላ ፈፅሞ ያልጠበቅሁትን ርእሰ ጉዳይ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አነሳች፣

"ወያኔዎች ጋር ጫካ ሆናችሁ ከአንዲት ታጋይ ጋዜጠኛ ጋር ፍቅር ጀምረህ ነበር አይደል?"

"ማን ነገረሽ ይህን ታሪክ?" ስል በመደነቅ ጠየቅሁዋት።

"የሆነ ሰው አጫወተኝ"

"ሚልኪያስ ነው?"

"አይደለም!"

"ማነው ታዲያ?"

"አልነግርህም! የሆነው ሆኖ ... ሌላ ጋዜጠኛ ደግሞ እሷን ይወዳት ነበር አሉ"

"አምን!" አልኩ በትካዜ።

"እና እውነት ነው?"

"ምኑ?"

"አዲሳባ ከገባችሁ በሁዋላ ጋዜጠኛው እሷን ገድሎ ራሱንም እንዳጠፋ ነው የሰማሁት"

የማልፈልገው ርእሰ ጉዳይ ቢሆንም ሳልወድ ምላሽ ሰጠሁዋት፤

"እውነት ነው" አልኩ ተክዤ።

"ማን ነበር ስሟ?"

"ዙፋን ፍሰሃ" አልኩ ያቺ ጠይም ውብ ድንቅ ፍጥረት ፊቴ ላይ መጥታ ድቅን እያለች።

* * *

ዙፋንን ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅሁዋት ሃገረሰላም በተባለ የትግራይ ትንሽ መንደር በተዘረጉ ድንኳኖች ውስጥ ተቀምጬ ሳለ ነው። በዚያን ወቅት ከአማረ አረጋዊ ጋር ጋዜጠኞችን ለማሰልጠን በነታምራት ላይኔ ታዝዘን፤ የማስተማሪያ ማኑዋል በማዘጋጀት ስራ ተጠምጄ ነበር።

ሴኮ እና ብርሃኑ አባዲ የተባሉ የኢህአዴግ ሬድዮ ጋዜጠኞች ከሬድዮ ጣቢያው ወደ መቀሌ በእግር በመጓዝ ላይ ሳሉ እኔ ወደ ነበርኩበት ድንኳን ብቅ ብለው ተዋወቁኝ። ከእነዚህ ጋዜጠኞች ጋር በስም እንጂ ከዚያ ቀደም በአካል አንተዋወቅም ነበር። አንዲት ጠይም ሙሉ ሰውነት ያላት እጅግ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ውብ ልጅ አብራቸው ነበረች። የትግርኛው ፕሮግራም ጋዜጠኛ መሆኗን በመግለፅ አስተዋወቁኝ።

"ዙፋን" ስትል ተዋወቀችኝ።

ወደ ሬድዮ ጣቢያው ከተዘዋወርኩ በሁዋላ ከዙፋን ጋር ፍቅር ጀመርን። ከጋብቻ በፊት ግንኙነት መፍጠር በትግሉ ህግ የሚያስቀጣ ወንጀል ስለነበር ግንኙነታችን ጥንቃቄ የታከለበት ነበር። ሌሊት ዙፋን ባትሪ ይዛ ጨለማውን እየሰነጠቀች ወደኔ ዋሻ ትመጣለች። በዚያች ጨለማማ ጎጆ ውስጥ በየእለቱ በሚስጥር መገናኘታችን ቀጠለ።

አንድ ቀን ሌሊት ዙፋን ለቀጣዩ ማለዳ የሚሆነውን ዜና ቀረፃ ጨርሳ ስታበቃ፤ እንደተለመደው ጨለማውን ተገን አድርጋ በላምባዲናዋ እየተመራች ወደኔ ዋሻ ትመጣለች። ዙፋን እኔ ዘንድ ጋደም ብላ እንደተለመደው ደርግ ከወደቀ በሁዋላ ስለምንመሰርተው ትዳር እያወራን ያን የበረሃ ውብ ፍቅር እያጣጣምን ሳለ የዋሻዬ በር ተደበደበ፤

ማመን አቃተኝ! እኩለ ሌሊት አልፎአል!

"ማነው?"

"ዙፋንን ፈልገን ነበር"

"ዙፋን እዚህ የለችም! ምን ልታደርግ እዚህ ትመጣለች?" አልኩ ቆጣ ብዬ።

"ከሌለች ደህና" ሲል ሰማሁ።

"ችግር አለ እንዴ?" ስል ጠየቅሁት።

"ችግር የለም! አምቦ ከተማ ተይዛለች። የነገ ማለዳው ዝግጅት እንዲለወጥ ስለታዘዘ ዙፋንን እየፈለግናት ነው..."

"ማርታ ዘንድ እያት!" አልኩት።

"እዚያ የለችም" ካለ በሁዋላ ሄደ።

ዙፋን ቀስ ብላ ከመደብ አልጋችን ብርድ ልብስ ውስጥ ተመዝዛ ከወጣች በሁዋላ፤ ድምፅዋን አጥፍታ ከኔ ዋሻ ጎጆ ሾልካ ወደ ጫካው የቀረፃ ስቲዲዮ በረረች። በማለዳው የሬድዮ ፕሮግራም ዙፋንን ሰማሁዋት። በዚያ ልብን በሚነድፍ ድምፅዋ የአምቦ ከተማን መያዝ በድጋሚ አበሰረችኝ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አዲሳባ ከተያዘች በሁዋላም ከዙፋን ጋር ፍቅራችን በጥሩ ሁኔታ ቀጥሎ ነበር። ይሁን እንጂ በመካከሉ ያልተጠበቀ አደጋ ተከሰተ። ለረጅም ጊዜ ይከታተላት የነበረ አንድ የትግርኛ ቋንቋ ጋዜጠኛ የኔንና የዙፋንን የጋብቻ ስምምነት ሰማ። ስሜቱን ሊሸከመው ስላልቻለ በተኛችበት ሄዶ ዙፋንን ገደላት። ራሱንም አጠፋ።

የዙፋን አስከሬን የኢህአዴግ ሬዲዮ ከነበረበት አስራተ ካሳ ግቢ ተወስዶ እንዳረፈ ማምሻውን ወደዚያው ሄጄ ነበር። የኔና የዙፋንን ጥብቅ ፍቅር የሬድዮ ጣቢያው ባልደረቦች ያውቁ ነበር። እንደደረስኩ ፍፁም ልቆጣጠረው በማልችለው ሁኔታ እሪታዬን አቀለጥኩት። ከዚያ ቀደም እንደዚያ አምርሬ ያዘንሁት ወላጅ እናቴ የሞተች ጊዜ ብቻ ነበር...

* * *

ፅጌረዳ የኔን ገፅታ አይታ ትክዝ አለች።

"ይቅርታ! የማትፈልገውን ርእስ አነሳሁብህ" አለች።
"መቼ ነው ስለ ዙፋን የሰማሽው?"
"የተገደለች ሰሞን..."
"በዚያን ሰሞን ታዲያ እኔና አንቺ እንገናኝ ነበር'ኮ። እንዴት ሳታነሽልኝ ቀረሽ?"
"ልብህ መሰበሩን ተረድቼ ነበር። ጉዳዩን ባነሳልህ ይበልጥ እንደምጎዳህ አወቅሁ..."
"ለዚህ ነው ተቻኩለሽ ያገባሽው?"
"አይደለም!" አለችኝ ቅጭም ብላ "...እንዳልኩህ ነው። አንተ መንታ መንገድ ላይ መሆንህን አወቅሁና የራሴን መንገድ መረጥሁ፤ እስዋ ስትገደል ከእስዋም ከእኔም ሳትሆን መሃል ላይ ቀረህ። የሆነው ሆኖ ማናችንም ብንሆን የፈለግነውን አላገኘንም.... ህይወት ይህን የመሰለ ቀልድ ትወዳለች..."

ቀዝቃዛ ድባብ ተፈጠረ።

ማልቀስ አማረኝ። እየጮህኩ አልቅሼ ቢወጣልኝ ቀለል

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ይለኝ ነበር። የለም! አላደርገውም! በፍፁም ባላደርገው ይሻላል! እንደምንም ዋጥሁት።

“ወደኔ መምጣትሽን ባልሽ ያውቃል?”

“ያውቃል!” አለች። አያያዘችናም፣ “...ጓደኛዬ እንደሆንክ ያውቃል። በጣም ጥሩ ሰው ነው። ያምነኛል። ለነገሩ ለመቅናት ጊዜ የለውም። ከምትገምተው በላይ ጎበዝ ሰው ነው”

ያለምንም መደባበቅ ልንገራችሁ!? ፀፀት የሚባል እንደ ምላጭ የሰላ ስለት ልቤን ሲሰነጣጥቀው ይሰማኛል። የመጀመሪያ ፍቅረኛዬን ያጣሁት መወሰን ባለመቻሌ ነበር። የአራት ልጆች እናት የሆነችውና ሽበት በለስላሳ ጣቶቹ የደባበሳት ፅጌረዳ፣ ከነግርማዋ፣ ከነውበትዋ፣ ከነለዛዋ፣ ይኸው አጠገቤ ተቀምጣለች።

"አንድ ነገር ልንገርህ?"

"ምን?"

“ለመጀመሪያ ጊዜ ችግኝ ጣቢያ የጉልበት የቀን ስራ ሰርተህ የጥፍር ቀለም የገዛህልኝን ታስታውሳለህ? እኔ በፍፁም አልረሳውም...” ብላ የተለመደ ሳቋን ቀጠለች።

ሳልወድ አሳቀችኝ።

እኔ በበኩሌ ችግኝ ጣቢያ የቀን ስራ መስራቴ እንጂ ለሷ የጥፍር ቀለም መግዛቴ በፍፁም ትዝ አይለኝም።

“ለራሴ ሽራ ጫማ እንኳ በሌለኝ በዚያን ጊዜ እንዴት ነው ላንቺ የጥፍር ቀለም የምገዛው?”

“ማርያምን!” ብላ ማለች “...ገዝተህልኛል! ለመጀመሪያ ጊዜ ስጦታ የተቀበልኩት ካንተ ነው!"

እየቀለደች መሳቋን ቀጥላለች፣

"ጃን ትዝ ትልሃለች? የኛ ውሻ?"

"ጠጉራምዋ?"

"አምስት ወልዳለች። የልጆችዋን ስም ልንገረህ? ጃንጥላ - ጃርት - ጃንቦ - ጃካራንዳ - ጃላላባድ...”

ፅጌረዳ እንደሰከረች ገባኝ። ስለበረዳት ጃኬትዋን ደረበች። ቻፒስቲክ አውጥታም ከንፈሮቿን ቀባባች። እድሜ ውበቷን በፍፁም አልነካውም። የጎንዮሽ ተመለከተችኝ፣

“ሳታገባ ለመቀጠል ነው የምትፈልገው?”

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

"ካገኘሁማ ዛሬውኑ አገባለሁ"
"ለምን ከዚህ አገር አትወጣም?"
"የት ልሂድ ፅጌረዳ?'
"አሜሪካ ግባ"
"እዚያ የወከባ አገር እኔ መኖር እችላለሁ ብለሽ ነው?"
"ወይም እኛ ዘንድ ስዊድን ለምን አትመጣም?"
"አይሆንም! ካንቺ መራቅ ነው የሚሻለኝ!"
ጥቂት በትካዜ ቆየች፣
"ደቡብ አፍሪቃ ለስደተኞች እየከፋ ነው ይባላል። እስከ መቼ ታዲያ እዚህ ትቆያለህ?"
"ሌሊቱ እስኪነጋ"
"መቼ ነው ያንተ ሌሊት የሚነጋው?"
"ሊነጋ ሲል ሁሉም ያውቃል!"

ሌላ ጀልባ ከሮቢን አይላንድ እየተመለሰች ነበር። ነጭ ቱሪስቶች በጀልባዋ ላይ ተጠቅጥቀዋል።
"ተራችን ደርሶአል ፅጌረዳ! እስከ ህይወትሽ ፍፃሜ ልትረሽው የማትችይውን ቦታ አስጎበኝሻለሁ። ኔልሰን ማንዴላ የታሰረበትን ክፍል መጎብኘትና በሮቢን አይላንድ ለማሽ ሰአት መቆየት በመንፈስ ውስጥ የማይረሳ አንዳች ልዩ ስሜት ያሳድራል! ይህ ጉብኝት ላንቺ የማበረከትልሽ የገና ስጦታ ነው" ብዬ እጅዋን ይዤያት ተነሳሁ።
መዳፎችዋ ያቃጥላሉ....
አጥብቃ ተጠግታኝ ወደ ባህሩ ዳርቻ አዘገምን.....

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 29 -
...ሃገር ግን ትኖራለች!

ሁሉም ያልፋል...
ካርፍም እንኩዋ - ዶፍ ዝናሙ ያጎረፈው፣
ሄደ ሄደ - ሄደ ያልቃል፣
ፈሶ ፈሶ - ፈሶ ይደርቃል፣
ፀሃይቱም...
ፀሃይቱም እንኩዋ፣
ቀኑን ሞቃ - ሞቃ - ሞቃ ትበርዳለች፣
መሬት ፊትዋን ስትነሳት ስትርቃት..ትሸሻለች፤

(ግጥም - ታምራት ላይኔ)

* * *

አታስብ ይለኛል - አንዳንዱ ከርፋፋ፣
ጥቂሩ ኮጮ ሆኖ - እውነት እየጠፋ፣
ለምን አላስብም - አስብ አሳምሬ፣
የደላኝ መስሎታል - ከሱ ጋር መኖሬ፣
አታስብ አትበለኝ - ንዝንዝህ ይብቃ፣
አንተው ማሰብ አቁም - ተጎለት እንደ እቃ!

(ግጥም - ሞገስ ሃብቱ)

ቄስ ካለ እሳት አለ ይባላል።

በርግጥ አባባሎችን በመያዝ ብቻ የጨሰውን ሁሉ እሳት ነው ማለት ስህተት ይሆናል። የኢህአዴግ የፖሊት ቢሮ አባላት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በሚሊዮናት የሚገመት ገንዘብ በሩቅ ምስራቅና በአውሮፓ ባንኮች ማከማቸታቸው በተለያዩ መንገዶች ሲገለፅ ቆይቶአል።

"ትንሳኤ" የተባለው ሬድዮ ይህን የሚገልፅ ዝርዝር መረጃዎችን በማቅረቡ እነ መለስ፣ እንደ እሳት እየነደዱ፣ እንደ ጭስ እየጨሱ የሬድዮ ጣቢያውን ሰዎች እስከ መክሰስ ደርሰው ነበር። በተመሳሳይ ethiopianreview.com የተባለው ታዋቂ ድረገፅም የወያኔን ቁስል በሚያሳምም መልኩ እየነካ በማስቸገሩ የኢህአዴግ መሪዎች የድረገፁን ባለቤቶች በአንደኛ ደረጃ ጠላትነት መዝግበው ይዘዋቸዋል። "ጭስ ካለ እሳት አለ" የሚለው አባባል ሳይዘነጋ የማውቀውን ልናገር።

በመሰረቱ የኢህአዴግ ፖሊት ቢሮ አባላት በውጭ ሃገራት ባንክ በውጭ ምንዛሪ ያስቀመጡትን የገንዘብ መጠን ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። የኢህአዴግ ፖሊት ቢሮ አባላት የሚታሙባቸው የኤዢያና የአውሮፓ ባንኮች የደምበኞቻቸውን መረጃዎች በቀላሉ የሚሰጡ አይሆኑም። ትንሳኤ ሬድዮ የነገረንን የገንዘብ መጠን ማረጋገጥ ባልችልም፣ ሬድዮው ትክክል የመሆን እድል እንዳለው የሚጠቁሙ ፍንጮችን ማንሳት ግን የሚገድ አይሆንም።

ምርጫ 97 ወደ ተቃዋሚዎች ባዘነበለ ጊዜ አብዛኞቹ የፖለቲካ ቢሮው አንጋፎች ሻንጣ ማሰር ጀምረው እንደነበር በቂ መረጃዎች አሉ። በስደት ሆኜ እንደሰማሁት ሹማምንቱ የግል ቤቶቻቸውን ከማከራየት አንስተው፣ ሚስትና ልጅን እስከ ማሸሽ ደርሰዋል።

በወቅቱ የመለስ ዜናዊ ባለቤት ልጆችዋን ይዛ ወደ ለንደን አቅንታ ነበር። የተሰጠው ምክንያት "ልጆቹ ከጫጫታው ገለል ብለው እንዲቆዩ" የሚል ሆነ። "ዘመኑ ምናለኝ - ዘመኑ ወርቅ ነው" ብላለች አስቴር አወቀ። በጥይት የሚገደሉ ህፃናትንና ጫጫታ የከበዳቸው ህፃናትን ጎን ለጎን አስቀምጣችሁ ይህቺን አለም ታዘቧት። የስዬ አብርሃ ልጆች ደግሞ፣ "የአስር አመት የኤሌክትሪክ ሂሳብ አልከፈላችሁም" በሚል መብራት ተቋርጦባቸው የትምህርት ቤታቸውን የቤት ስራ ለመስራት ሻማ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ፍሊጋ ላይ ነበሩ።

(ሰዬና መለሰ ሁለቱም የህክምና ተማሪዎች ነበሩ። አብረው ወደ ትግል ወጡ። መለሰ ፖለቲካውን፣ ሰዬ ውትድርናውን ተከፋፍለው በመምራት ደርግን ገለበጡ። ከድል በሁዋላ የካስትሮና የቼጉቬራ ችግር ጊዜውን ጠብቆ መጣባቸው። ሰዬ ግን እንደ ቼ መሄጃ አልነበረውምና በአንድ አገር ውስጥ የሁለት አለም ሰዎች ለመሆን በቁ!)

በምርጫ 97 ታሪካዊ እለት ዋዜማ የዶላር ምንዛሪ ዋጋ አሻቅቦ ነበር። ባለስልጣናቱ የሸሸጉትን ብር ሁሉ በዶንያ እየያዙ ዶላር ፍለጋ ተቅበዝብዘዋል። ጥቂት የማይባሉ ባለስልጣኖች ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን የምእራብ ሃገራትን ዜግነት ያስያዙ ሲሆን፣ የማይሰንፉባት ተግባራቸው ደግሞ ምንጊዜም ቪዛ ማደስን ነው።

የኢትዮጵያ ህግ ድርብ ዜግነትን አይፈቅድም። ይህ ህግ ግን ለባለስልጣናቱ አይሰራም። ብዙዎች ባለስልጣናት የሚስቶቻቸው መውለጃ ሲቃረብ አሜሪካ ሄደው እንዲወልዱ ያደርጓቸዋል። ህፃኑ ማሙዬ ከእናቱ ጋር አሜሪካዊ ይሆናል። አባት ደግሞ የኢትዮጵያ ባለስልጣን። የከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ሁሉም ልጆች አሜሪካ ነው የተወለዱት። ባጫ ደበሌ ደግሞ ሚስቱ አሜሪካዊ ትሆንለት ዘንድ በምክክር አስኮብልሎአታል። ከአዲሳባ በሚላክ ዶላር እየኖረች፣ ኢህአዴግን አውግዛ የፖለቲካ ጥገኛነት ትጠይቃለች። "ንዶች" እና "ብየት" እግራቸው እስኪቀጥን የሚያገለግሉት "አብዮት" ኮፍያው ሲወልቅ ቃቄቻው እንዲህ ርቃኑን ይቀራል።

እነዚህ የጠቀስኳቸው ሹማምንት ዝርክርኮች ስለሆኑ ምስጢራቸው በየሜዳው ወድቆ ተገኘ እንጂ፣ የህወሃትና የብአዴን አመራር አባላትም በተመሳሳይ በአብዮታዊ ቅሌት የተጀቦኑ ናቸው።

በስደት ሆኜ እንደተከታተልኩት፣ የዋናው ሰውዬ ባለቤት ራስዋ ከጫት ንግድ እስከ ባጃጅ የሀንድ ባለሶስት እግር መኪኖች ንግድ ድረስ ታጣድፈዋለች። መነገድ መብቷ ነው። በመንግስት ስልጣን ከለላ አትራፊ መሆን ግን ወንጀል ነው። ያለቀረጥ ማስገባት፣ በተፅእኖ መሸጥ፣ የመከላከያን ሰውና

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ንብረት ለግል ቢዝነስ ማዋል ሁሉ ወንጀሎች ናቸው። የሃረር አካባቢ ገበሬዎች ለመለስ ሚስት ጫት ላለመሸጥ ባመፁ ጊዜ፣ ጀኔራል ባጫ ደበሌ ሰራዊት ልኮ ገበሬው ላይ ዘምቶአል። የኢትዮጵያ ሰራዊት ሁሉ እንደሚያቀው ጀኔራል ባጫ ደበሌ በውትድርና ታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የራሱን የካርታ ንድፍ ስሎ ውጊያ የመራውም ያልታጠቁ የምስራቅ ገበሬዎች ላይ ነው።

በኒውዮርክ የሱዳን የተባበሩት መንግስታት አምባሳደር ከትግሉ ጊዜ ጀምሮ የመለስ የቅርብ ወዳጅ የነበረ ሲሆን፣ ለመለስ ዜናዊ ቤተሰብ የሚያገለግሉ ቪላዎችን በመግዛትና በማዘጋጀት ተልእኮውን በታማኝነት የፈፀመ ጓድ ነው።

"ዲንሾ" ተብሎ ስለሚታወቅ የንግድ ኩባንያ ታውቃላችሁ? የኦህዴድ ንብረት ነበር። ዛሬ ህይወት የለውም። ባይቀበርም ሞቶአል። ታሞ አይደለም የሞተው። ባልታሰበ አደጋ ነው ህይወቱ ከዚህ አለም የተለየችው። የዲንሾ ገዳይ ስዬ አብርሃ ይባላል። ህወሃት "ጉና" የተባለ የንግድ ድርጅት ሲያቋቁም፣ ብአዴን "አምባሰልን" ኦህዴድ "ዲንሾ" ን በመመስረት ነበር ንግድ የጀመሩት።

ደርግ የወደቀ ሰሞን ከኢሊባቡርና ከወለጋ የተገኘ ሶስት ዶንያ ገንዘብ ኩማ ደመቅሳ ቢሮ ይደርሳል። ያ ገንዘብ አድራሻውን ሳይናገር የመሰወሩ ነገር በዚያን ሰሞን ሲከካ ሰንብቶአል። ወሬው ሲቦካ ታዲያ እነ ኩማ ይደናገጡና በገንዘቡ "ዲንሾ"ን እንዳቋቋሙበት ግምገማ ላይ ይገልፃሉ። እኔ በወቅቱ እንዲህ ያሉ ወሬዎችን ችላ ብዬ ማለፍ የማልወድ ችኮና ነገረኛ ነበርኩና ዲንሾ የተቋቋመበት ካፒታል ከየት እንደተገኘ ስፈለፍል፣ ዲንሾ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 600 ሚልዮን መበደሩን ደረስኩበት።

ጭስ ካለ እሳት አለ።

ኩማ ይህን መሰል ወሬዎች እንዳይወጡበት ስለሰጋ የዲንሾን ስራ አስኪያጅ ወንድሙን ሾመው። ወንድምየው ደግሞ ጊዜውን ተጠቀመበት። "ሲሾም ያልበላ" የሚለውን በስራ ላይ አዋለ። ዲንሾ ከእዳ ወደ ኪሳራ መንፋዋቀቅ ሲጀምር ለራሳቸው ሲሉ ባለሙያ ፈለጉና ሾሙበት።

ዱባለ የተባለ የባንክ ገዢ የነበረ ሰው ዲንሾን ተረከበ። ዱባለ በጣም ጎበዝ ባለሙያ ነበር። ዲንሾን አነቃነቀው። 200 አውቶብሶች እንዲገዙ ትእዛዝ ሰጠ። ይህ ወሬ ስዬ ጆሮ ደረሰ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ስዬ "ሰላም የአውቶብሶች ማህበር" የተባለውን መስርቶ ነበርና ተቀናቃኝ ሲመጣበት "የኢህአዴግ የልማት ድርጅቶች ቦርድ ሰብሳቢ" የሚል ስልጣን ለራሱ ይሰጥና የአምባሰልና የዲንሾን ስራአስኪያጆች ስብሰባ ይጠራል። ስዬ ከሚታወቅበት ጠባዩ ዋናው ለጣፊነቱ ነው። ቃል በቃል ዱባለን እንዲህ አለው፣

"እኛ (ህወሃት) የሰላም አውቶብስ ማህበርን ስላቋቋምን እኛስ ከማን እናንሳለን በሚል ነው አውቶብሶቹ እንዲገዙ ያዘዝከው?"

ዱባለ ትንፋሹ ቢቋረጥበትም ጆሮው መስማቱን ግን አላቆመም፣ አያይዞ ስዬ እንዲህ አለው፣

"ባስቸኳይ የታዘዘው የአውቶብስ ስራ ይቋረጥ!"

ዱባለ ትእዛዙን ለማቋረጥ ወደ ካምፓኒው ደወለ። 50 አውቶብሶች ተሰርተዋል። እነሱን መረከብ ግዴታ ሆነ። የቀሪው 150 አውቶብስ ስራ ኪሳራው ተከፍሎ ውሉ ተሰረዘ። የተመረቱት አውቶብሶችም ለሰላም ማህበር እንዲሰጡ ስዬ ቀጭን ትእዛዝ ሰጠ። ዲንሾ በዚያኑ ሰሞን መሞት ጀመረ። ዱባለ የሞቀ የስራ ወኔው ከተኮማተረ በሁዋላ፣ ሞጆ ላይ ስጋ ቤት ከፍቶ ዲንሾን ሊያጠናክር ሞክሮ ነበር። ግን ቢሮ መግባቱን ትቶ እዚያው ስጋ ቤት ቁጭ ብሎ ጥብስና ጥሬ እያስቆረጠ መብላት በመጀመሩ ዱባለ አእምሮውን እንደሳተ ታወቀ። ኩማ ከስራው አንስቶ ወረወረው። የባንክ ገዢ የነበረው ድንቅ ባለሙያ በየጠንቋዩ ቤት እየዞረ ጫት እየተቃመ ይፀለይለት ገባ።

"ምን ሆኖ ታመመ?" ብዬ ጠይቄ ነበር በወቅቱ።

"ሌሊት የስዬን ስም እየጠራ ይቃዣል" ብለው አሳቁኝ። በርግጥ ነገሩ ያሳዝናል እንጂ አያስቅም። እኔ ግን በሳቅ ነው የፈነዳሁት። ስዬ ከተወገደ በሁዋላ ጤንነቱ ይመለስለት አይመለስለት ግን አላውቅም። ዲንሾ ዛሬ ከሞቱት በላይ፣ ካልሞቱት በታች ሆኖ ወደ ጫት ሱቅነት ተለውጦአል።

(በነገራችን ላይ በሺህዎች የሚገመቱ የቅንጅት ደጋፊዎች እየታፈሱ ወደ ዴዴሳ ሲላኩ፣ የማንገዙን ስራ የተረከበው "ሰላም የአውቶብስ ማህበር" ሲሆን፣ ለአገልግሎቱም በሚሊዮናት ከመንግስት ተከፍሎታል።)

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ይህን የሚያነብ አንድ ሰው እንዲህ ይለኝ ይሆናል።

"መሪዎች ሁሉ ዘራፊዎች ናቸው! ምን አዲስ ነገር ነገርከን? እናስ ምን ይጠበስ?"

ወዳጆቼ ሆይ!

ምንም የሚጠበስ ነገር አንጠብቅም። እኛው ራሳችን እየተጠበስን ነው። ከትውልድ ትውልድ፣ እስከመቼ ልጆቻችንን እንደምናስጠብስ ግን የማሰብ ግዴታና መብት አለን። ጃንሆይ በሚሊዮናት ዘረፉ ተባለ። ያም ከጊዜ ጋር ተረሳ።

መንግስቱ ሃይለምማርያም የበቆሎ እርሻ ገዛ፣ ጋዳፊና የኩዌት መንግስታት ለሃገሪቱ የሰጡትን ወደ ኪሱ ጨመረ፣ አዲሳባ ላይ ከውጭ ዜጎች በዶላር የሚገባውን የቤት ኪራይ ወደ ግል ካዝናው ከተተ፣ ፈላሻዎችን ሸጠ፣ ከዚምባብዌ የተበላሸ ትንባሆ እንዲገዛ በመፈረም ሰባት ሚሊዮን ዶላር አተረፈ ተባለ። ያን ሁሉ አወገዝንና እሱም ተረስቶ እዚህ ደረስን።

አሁንም መሪዎች በነባሩ ሃዲድ ላይ ጉዞ ቀጥለዋል።

እኔ በጃንሆይ ዘመን ነው የተወለድኩት። መንጌ ቴክሱ ጃንሆይን በትራስ አፍኖ ገድሎ፣ ቢሮው ወንበሩ ስር ሲቀብራቸው ያኔ እኔ የስድስት አመት ልጅ ነበርኩ። በደርግ ዘመን ደግሞ ወጣት ነበርኩ። በወያኔ ዘመን ጋዜጠኛና ባለስልጣን ሆንኩ። ይህን ስፅፍ የ40 አመት ሰው ስሆን፣ ተራ ስደተኛ ነኝ። እንደ ግለሰብ ተጠቃሚ የሆንኩት በወያኔ ዘመን፣ የተጎዳሁት ደግሞ በደርግ ስርአት ቢሆንም፣ ሚዛናዊ ሆኜ ማሰብ ግን እችላለሁ። በቅርቡ ሶስቱ ተከታታይ መንግስታት በምን እንደሚለያዩና በምን እንደሚመሳሰሉ ለመፃፍ ሞካክሬ ሳልገፋበት ቀረሁ።

ዘውዳዊው የጃንሆይ አገዛዝ ፊውዳላዊ ባህሉን ጠብቆ ሃገሪቱ አንድ ደረጃ ላይ እንድትደርስ ይመኝና ከልቡ ይሰራ ነበር። ደርግ ተፈጥሮውና አቅሙ አይፈቅድለትም ነበርና እንደ ዘመን "የጨለማው ዘመን" ተብሎ ቢዘለል ይሻላል። ወደ ኢህአዴግ ፈጣሪዎች ስንመጣ አገሪቱን የትም ለማድረስ ምንም ህልም እንደሌላቸው እንረዳለን። ህልም አልባ የሆኑት ባለማወቅ አለመሆኑ ሲታሰብ ደግሞ ስጋት ይለኮስብናል። ቢያንስ የተሻለች አገር ፈጥረው "ለልጆቻችንና ለስማችን" የሚሉ አይነት ሰዎች እንኳ ሊሆኑ አልቻሉም። አፄ ዮሃንስ፣ "አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ሃገር" የሚል ህልም ነበራቸው። ለዚህም ሲሉ ህይወታቸውን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ሰጥተዋል። ቴዎድሮስና ሚኒሊክም የተሳሳተ አያያዝ ተጠቀሙ ቢባልም እንኳ፣ "የተማከለ አንድ አስተዳደር ያለው ሃገር፣ እውቀትና ቴክኖሎጂ ማስፋፋት" የመሳሰለ ራእይ ነበራቸው።

"የኢህአዴግ ራእይ ምንድነው?" ብዬ ራሴን ስጠይቅ ግን መልስ አላገኝለትም። ብዙዎች ልክ እንደኔ በኢህአዴግ ተፈጥሮ ላይ ግራ ሲጋቡ ታዝቤያለሁ። የኢህአዴግ የፖለቲካ ባህል በፍፁም የማይገባቸው ጥቂት አይደሉም። በርካታ የኢህአዴግ ታጋዮችና አባላት የተደራጁበትን ድርጅት ምንነት ሳያውቁ፣ የራሳቸውን ጥቅም ሲጎዱ ይታያሉ። ኢህአዴግ ዘላቂ አላማ ያልነበረው፣ እደርስበታለሁ ብሎ ያስቀመጠው ግብ የሌለው ቡድን መሆኑን ብዙ የፖለቲካ ሰዎች የሚፅፉትን ስጠራጥር ቆይቼ ነበር። ለአሰርት አመታት ያገለገልኩት ግንባር ባንድ ቃል የብልጣብልጦች ማህበር የመሆኑ ጉዳይ ግን አሳዛኝ እውነት ነው። በስልጣን እስካለን ድረስ ገዝተንና በልተን፣ ከኛ በሁዋላ ሃገሪቱ ብትበታተንም ትበተን፣ የሚሉ ሃላፊነት የማይሰማቸው፣ የጮሌዎች እድር መሆኑን ዘግይቼ በመገንዘቤ ለራሴ አዝናለሁ። የኢህአዴግ ሰዎች ቅንጣት ታህል የሃገር ፍቅር ስሜት የሌላቸው መሆናቸውንም በድርጊታቸው ማረጋገጡን ተያይዘውታል። "ልጆቻችን!" ብለው ሲናገሩ ከሚስታቸው የወለዷቸውን ልጆች እንጂ፣ የሃገሪቱን ልጆች አይደለም። ይህም ራእይ አልባ ያደርጋቸዋል። ባህርያቸው የተወለዱበትን ብሄር ቀርቶ ልጆቻቸውን እንኳ መወከል አያስችላቸውም። ልጅ በአባቱ ከሚያፍር ባይወለድ ይሻለዋል። "የእገሌ ልጅ ነኝ!" ብሎ ባደባባይ መናገር ያልቻለ ልጅ በስሙ የተቀመጠ ሚሊዮን ዶላር ቢታቀፍ፣ የስጋ እንጂ የመንፈስ ምግብ ሊሆነው አይችልም።

"ትንሳኤ" ሬድዮ ባቀረበልን መረጃ መለስ ዜናዊ ጭስ በጭስ እስኪሆን የተቆጣው፣ በውጭ ሃገር የተቀመጠ ገንዘብ ጉዳይ በዙሪያው ያሉትን ሹማምንት ሁሉ ቀልብ የሚስብ በመሆኑ ነበር።

የህወሃት አባላት ሁሉ የሚያውቁት አንድ እውነት አለ። በትግሉ ወቅት ከአባላትና ከደጋፊዎች የተሰበሰበ፣ ወያኔን ሲያስታጥቁ ከነበሩ የውጭ መንግስታት የተቸረ፣ ለመሳሪያ መግዣ ተብሎ የተሰጠ ገንዘብ ሁሉ ውጭ ሃገር በሚገኙ አካውንቶች እንደተቀመጠ ቆይቶአል። በውጭ ሃገር

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከሚንቀሳቀሱ የወያኔ የንግድ ድርጅቶች የተገኙ በቢሊዮን የሚገመቱ ገቢዎችም ወደ ሃገር ውስጥ አልገቡም። "በትግሉ ዘመን ባፈራነው ገንዘብ ኤፈርትን አቋቁመናል" እያሉ ቢናገሩም ይህ እውነት አይደለም። ኤፈርት የተቋቋመበት ካፒታል ወያኔ አባይን ከተሻገረ በሁዋላ ምእራብ ኢትዮጵያ ከነበሩ ባንኮች፣ ከመከላከያና ከደህንነት መስሪያ ቤቶች በተገኘ ገንዘብ መሆኑን በቅርብ የማውቀው ነው። በትግሉ ወቅት በደርግ ግፈኛ ስርአት ላይ የዘመተው ታጋይ በደሙ ካመጣው ገንዘብ መቋቋሚያ እንኳ አላገኘም። የምስክር ወረቀት እየተሰጠው ተሸኝቶአል። "ትንሳኤ ሬድዮ" የጠቀሳቸው በውጭ ሃገራት የተከፈቱት የባንክ አካውንቶች እየሞሉ በመሄድ ላይ ሲሆኑ፣ በአምባሳደር ብርሃኔ ገብረክርስቶስ አስፈፃሚነት በስብሃትና በመለስ ፊርማ ይንቀሳቀሳሉ። ይህ ገንዘብ በግልፅ አሰራር አይተዳደርም።

የህወሃት የውጭ ሃገራት አካውንት በግልፅ አሰራር እንደማይንቀሳቀስ አንዳንድ አስረጅ ማቅረብ ይቻላል። ህወሃት በአየርላንድ፣ በለንደንና በኒውዮርክ አካውንት እንዳለው ይታወቃል። በትግሉ ወቅት ከሊባኖስ፣ ከሶሪያ፣ ከሱዳንና ከመሳሰሉት መንግስታት ለመሳሪያ ግዢ የተቸሩ ገንዘቦች ወደ ለንደንና ኒውዮርክ ገቢ ሆነዋል።

ብርሃነ ገብረክርስቶስ የህወሃት ማእከላዊ ኮሚቴ አባል ነው። በአሜሪካና በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆኖ አገልግሎአል። ወይም እያገለገለ ነው። በአንድ ወቅት በአምባሳደሩ ስም በኒውዮርክ አካውንት 250 ሚሊዮን ዶላር ተቀምጦ ነበር። ሰይጣን መቼም አሻዋረኛና ሸረኛ እንደመሆኑ፣ አንድ ተንኮል ያቅድና ጉድ ሰራቸው። ሶሎሜ ታደሰ የተባለች ሴት በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተቀጥራ በመስራት ላይ ሳለች፣ ከአምባሳደሩ ጋር በጥሩ ሁኔታ ተቀራርባ ኖራለች። በመቀጠል ሶሎሜ በአምባሳደሩ መልማይነት ማስታወቂያ ሚንስቴር ላይ ተሾመች። ከቀዳሚ እመቤት ጋር የጎሪጥ እስኪተያዩ ድረስም አዲሳባን ነገሰችበት። ቅፅል ስሟ እቴጌ ጣይቱ ሆነ። "ሁሉም ቦታ ሶሎሜ አለች" እያለ ጋዜጠኛው ተሳለቀ። ሶሎሜን በግል አውቃታለሁ። የሰለጠነች ጎበዝ ባለሙያ ናት። የተሾመችው ከችሎታዋ በላይ አይደለም። ይገባታል! ዋናው ችግር ሰይጣን የተባለው ሰይጣን፣ በሶሎሜና በአምባሳደሩ ግንኙነት ላይ ብዙ ያልተረጋገጡ ወሬዎችን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ማስወራት መጀመሩ ነበር። ወሬው ቪዛ አስመትቶ፣ ትኬት ቆርጦ አሜሪካ፣ ከአምባሳደሩ ሚስት ጆሮ ደረሰ። ትዳር መበተን የሰይጣን ዋና ስራ ነውና ባልና ሚስት ተጋጩ። ሚስት ፍቺ ጠየቀች። ተያይዞ ያልተጠበቀ ችግር ተከተለ። ሚስት በአምባሳደሩ ስም ስለተቀመጠው ገንዘብ ታውቅ ነበር። "ከባሌ ጋር ያፈራሁትን ገንዘብ መካፈል እፈልጋለሁ" ስትል አሜሪካ ላይ ፍርድ ቤት አመለከተች። አምባሳደሩ ደንግጠ ወደ መለስ ዜናዊ ይደውላል። ሚስትየዋ ለቅርብ ሰዎች እንዳጫወተችው፣ መለስ ደውሎ ቢያነጋግራትም ሳይግባቡ ይቀራሉ። እልህም ነበርና "ወይ ፍንክች" ትላለች። እነመለስ ወሬው ወደ ህወሃት አባላት ጆሮ እንዳይደርስ ስለሰጉ ወደ መስማማቱ አዘነበሉ። ጀግናይቱ በአሜሪካ ህግ መሰረት በባሏ ስም ከተቀመጠው ገንዘብ ግማሹ ተሰጣት። በአናቱ ካሳ ተመረቀላት። አንድ የኢህአዴግ አባል ይህን ሲያነብ፣ "በርግጥ ይህን ሁሉ የሚፈፅሙት የኔ መሪዎች ናቸውን?" ብሎ ማመን በመቸገር እንደሚንቀጠቀጥ አውቃለሁ። ይህን እውነት ለህዝብ አለማድረስ ራሱ በወንጀል መተባበር ስለሚሆን ሁሉን ፅፌላችሁዋለሁ...

ደቡብ አፍሪቃ በስደት ከከተምኩ በሁዋላ፣ ለጥቂት ሳምንታት እረፍት ሃራሬ ዚምባብዌ ሄጄ ነበር። ኮሎኔል ግርማ በተባለ ሰው በኩል በአጋጣሚ የመንግስቱን ወንድም፣ ጥላሁን ሃይለማርያምን ተዋወቅሁትና ቁጭ ብለን ብዙ አወራን። በወሬ ወሬ የተረዳሁት አንድ እውነት ነበር። ይህም ከመንግስቱ ልጆች አንዷ ዶክተር ትእግስት ሃበሾችን ያለማየት ፍላጎት ማዳበርዋን ነበር። ይህቺ ልጅ አበሻ ለማየት ለምን ጠላች? ወገኖቿ ነን። ምን አደረግናት? አባቷ ገደለን፣ ዘረፈን እንጂ እኛ አልበደልነውም? ምን ሆና ነው አምርራ አበሻን የምትጠላውና ከአበሻ የምትሸሸው? ብዙ ምርምር አያስፈልገውም። በአባቷ ታሪክ አፍራለች። የተረጋገጠ መረጃ ባይኖረንም መንግስቱ ሃይለማርያም ለልጆቹ የሚያወርሳቸው በሚሊዮናት የሚገመት ዶላር ሊኖር ይችላል። ልጆቹ ያሻውን ያህል የዶላር ክምር ቢሸከሙም የመንፈስ ምግብ ሊሆናቸው ከቶ አይችልም። ገንዘብ ብቻውን ርካታን ሊሰጥ አይችልም። በመሆኑም ከወገኖቻቸው የሚሸሹ ልጆችን መውለድ ያሳፍራል እንጂ አያኮራም።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የጠቅላይ ሚንስትራችን ልጅ ሰምሃል ትባላለች። የበረከት ወንድ ልጅ ደግሞ ኮበሌ ይባላል። መለስና በረከት፣ የኮሎኔል መንግስቱ ሴት ልጅ ከገባችበት የጭንቀት ማጥ ልጆቻቸውን ማዳን ለምን እንዳልቻሉ አስቤው መልስ አላገኘሁለትም። መንግስቱ ተከታዮቹን ቆልፎባቸው እንደሄደው ሁሉ፣ የመለስ ተከታዮች ያን ከመሰለ ውርደት ለመዳን መፍትሄው በእጃቸው ነበር። ለልጆቻቸው ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችን የሚሆን ታሪካዊ ተግባር መፈፀም ብቸኛው መፍትሄ ነበር። በሃገራችን ብሄራዊ የፖለቲካ እርቅ ማካሄድ ዘመን የማይሽረው መፍትሄ ነው። "ሙሽራው መቼ እንደሚመጣ አይታወቅምና ተግታችሁ ጠብቁ" ይለናል መፅሃፉ።

በመጨረሻ፣ አንድ የአርመኖች አባባል ትዝ አለኝ። ግመሎች ያልፋሉ፣ ተራሮች ግን ይኖራሉ። ታምራት ላይኔ በብእሩ እንደቋጠረው በርግጥም፣ ሁሉም ያልፋል። ...ሃገር ግን ትኖራለች!

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 30 -
መንገዱ ወዴት ያደርሳል?

ነገ የተባለው - ጥቅጥቁ ጨለማ፣
ቅርፅ የለው አይታይ - በድምፅ አይሰማ፣
ስንዶቹ ተጨንቀው - በስቃይ አለቁ፣
የነገን ብልጭታ - ብርሃን ሲጠብቁ፣
ታውቁ እንደሁ አሰረዱን - ሳትግደረደሩ፣
ነገ እሚገኝበት - የት ይሆን መንደሩ?

(ግጥም – ሻምበል አፈወርቅ ዮሃንስ)

ሌሊት እንቅልፍ እንቢ ካለኝ ማንበብ ወይም Paltalk ላይ መደበሩን ተላምጄዋለሁ። 1999 አጋማሽ ግድም Paltalk ውስጥ arm yourself የሚል የኮድ ስም ከሚጠቀም ሰው ጋር እያወጋሁ ነበር። እኔ ደግሞ Aoromara (አኦሮማራ) በሚል ስም ነበር የገባሁት።

በግል የምንነጋገርበትን መስኮት ከፈተና፣
"የት ሃገር ትገኛለህ?" ሲል ወግ ጀመረ።
"ደቡብ አፍሪቃ"
"የስምህ ትርጉም ምንድነው?" ጥያቄውን አራዘመ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“የአማራና የኦሮሞ ቅልቅል ማለት ነው”

“የሁለቱ ቅልቅል ነህ ማለት ነው?”

“አይደለሁም። በኦሮሞ ምድር የተወለደሁ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ነኝ”

“አኦሮማራ የሚለውን ቃል እንዴት ፈጠርከው?”

“እኔ አልፈጠርኩትም”

“ከየት አገኘኸው ታዲያ?”

“ጌታቸው ጀቤሳ ወይም ያሬድ ጥበቡ የተባለ ሰው ቃለመጠይቅ ሲሰጥ ቃሉን ጠቀሰው። ያሬድ ከአማራና ከኦሮሞ ስለተወለደ ለቀልድ ያህል ለራሱ የብሄር መጠሪያ የፈጠረው ይመስለኛል። ያሬድ ጥበቡን ታውቀዋለህ?”

“አውቀዋለሁ”

“ግን ለምንድነው ይህ የኮድ ቃል ትኩረትህን የሳበው?”

“አኦሮማራ በሚለው ቃል አንድ የልማት ድርጅት ለማቋቋም እያሰብኩ ነበር”

“አንተስ ቃሉን ከየት አገኘኸው?” ስል ጠየቅሁት። ሆኖም የኔን ጥያቄ ዘለለው፣

“ሁለቱ ህዝቦች መተባበርና መነጋገር ከቻሉ ምን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ታውቃለህ?” ሲል ጠየቀኝ።

“AFD” ስል መለስኩ።

“kkkkkkkkkkkkk” የሚል ፃፈልኝ።

ፊደሉ የሳቅ ምልክት ነው።

“ምን አሳቀህ?” አልኩ።

“ተግባብተናል። የAFD ጅማሮ መፍትሄ ይሆናል ብዬ አምናለሁ”

“እኔ ግን ስጋትና ጥርጣሬ አለኝ”

“ለምን?”

“ኢትዮጵያውያን አብረው መብላት እንጂ አብረው መስራት አይችሉም የሚለውን አባባል እያመንኩበት መጥቻለሁ”

“ተሳስተሃል”

“ብሳሳት እመርጣለሁ”

“ተስፋ አድርግ። የራስህን አስተዋፅኦ ደግሞ ጨምርበት። ይሳካል!”

“አንተ ያሬድ ጥበቡ መሆን አለብህ” አልኩ።

“አይደለሁም”

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

“ርግጠኛ ነኝ። ያሬድ ነህ!”

“እኔ ያሬድ ነኝ አላልኩህም። ስለዚህ ርግጠኛ መሆን አትችልም”

“ልክ ነህ! ይቅርታ!”

Arm yourself ብዙ የፖለቲካ ጉዳዮችን አንስቶ አወጋን። ራእይ ያለው ሰው ነበር። ቅንጅት በጀመረው መንገድ በመጓዝ የተሳካ ውጤት ማስገኘት ይቻላል ብሎ በጥብቅ ያምናል። የግለሰቦች አስተዋፆ ሲጠራቀም ሊፈጥረው የሚችለውን ሃይል ያሰምርበታል። በማይረቡ ምክንያቶች ርስበራስ የሚደረጉ ሽኩቻዎችና መጠላለፎች ትግሉን ወደ ሁዋላ ጎትቶታል ብሎ በጣም ይቆጫል።

በዚያኑ እለት ምሽት ከArm yourself ጋር ከተሰነባበትን በሁዋላ፣ *“ተገላቢጦሽ”* የተባለ ሰው ደግሞ በግል መጥቶ ያዋራኝ ጀመር። ይህ ግን ወጣትና ስሜታዊ መሆኑን መገመት ይቻል ነበር።

“ስለመጪው ዘመን ልተንብይልህ?” ሲል ጠየቀኝ።

“ነቢዩ ተገላቢጦሽ፣ እስቲ ተንብይ ልስማህ?”

“2002 ላይ መለስ ዜናዊ ወደ ጌቶቹ አገር ይኮበልላል” ሲል ጀመረ።

“የት ማለት?”

“አሜሪካ ነዋ! ገብሩ አስራት ደግሞ ትግራይን ዳግም ይመራል”

“ቀጥል”

“ኖሮዌይ ላይ ስለተደረገው አንድ ምስጢራዊ ስብሰባ ሰምተሃል? ሌንጮ ለታ ነው ያዘጋጀው”

“ሰምቻለሁ”

“በስብሰባው ላይ እነማን እንደተገኙ አስተውለሃል? ሌንጮ ለታ - ገብሩ አስራት - ያሬድ ጥበቡ - አን ዳርጋቸው ፅጌ - ጀማይካ..... እና ይሄ ምን ማለት እንደሆነ ይገባሃል? አንዳርጋቸውና ያሬድ ጥበቡ ሃይሉ ሻውልን ካስወገዱ በሁዋላ በብርሃኑ ነጋ መሪነት ሌላ ቅንጅት ይፈጥራሉ። ሌንጮ ለታ ደግሞ የዳውድ ኢብሳን ኦነግ ገለል ያደርግና እነ ዲማ ነገዎን ይዞ የኦሮሞን ህዝብ ይወክላሉ። እነ ተወልደ ደግሞ ትግራይን ወክለው ፓርላማ ላይ ይሰየማሉ።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በዚህ እቅድ መለስ ዜናዊ ስለ መስማማቱ ማረጋገጫው ደግሞ በስብሰባው ላይ ጀማይካ መገኘቱ ነው። ጀማይካ ምን ጊዜም የመለስ ወኪል ነው። ከዚያስ? አክራሪዎቹ ሃይሉ ሻውልና ዳውድ ኢብሳ የሌሉባት፤ መለስ ዜናዊም የማይሳተፍባት አዲሲትዋ ኢትዮጵያ ትወለዳለች። ይህ ካልተሳካ እነ መለስ ትግራይን ሊገነጥሉ ወስነዋል። የድንበር ማካለሉን ቶሎ መጨረስ የማይፈልጉትም ታንኩና አይሮፕላኑን ትግራይ ለማሰንበት ነው ይባላል። አንገብጋቢው ዋና ስራቸው ግን በቀረው ጊዜ የተቻለውን ያህል መዝረፍና የተከዜን ግድብ በፍጥነት ማጠናቀቅ ነው ብለው እያጣደፉት ይገኛሉ። ...እንዴት ታየዋለህ?" ሲል ጠየቀኝ።

"ልቦለድ ድርሰት ይመስላል" ስል መለስኩ።

* * *

በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ የሚከፋፈልና የሚዋሃድ ከመብዛቱ የተነሳ ደጋፊዎች ግራ ፈትል ሆኖብናል። በዚህች አጭር እድሜያችን ያልተጠበቁ ክስተቶችን በመታዘብ መቼም ያይን ምስክሮች ነን።

...መንግስቱ ሃይለማርያም እንደ አጤ ቴዎድሮስ ሽጉጡን ሳይጠጣ ቀረ። ታምራት ላይኔ 17 አመታት ታግሎ ሲያበቃ፣ 18 አመታት እስር ተበየነበት። ሻእቢያና ወያኔ ተጣሉ። መለስ ዜናዊ ስዬ አብርሃን አሰረው። ብርቱካን ሚደቅሳ ስዬ አብርሃን በዋስ ለቀቀችው። ሃየሎምና ክንፈ በማይረባ ምክንያት ተገደሉ። ብርሃኑ ነጋ እስር ቤት ውስጥ ሆኖ 600 ገፅ መፅሃፍ ፃፈ። ከእስር የተፈታው የቅንጅት አመራር ተከፋፈለ....

ያልተጠበቀው እየተፈፀመ እዚህ ደርሰናል። ነገም ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ እንደሆነ አለ። ነገን ማየት በቻሉት እየቀናን የተደናበረ ጉዞአችንን ቀጥለናል።

ሌንጮ ለታ በኖርዌይ ስብሰባ ያቀረባቸውን አንዳንድ ጠቃሚ አሳቦች ከያሬድ ጥበቡ መጣጥፍ ላይ አገኘቼ አይቻቸው ነበር። ለመቻቻል የሚያግዙ መነሻ አሳቦችን አቅርቦአል።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለመተማመን የሚያበቁ ዘዴዎችንም ጠቁሞናል። ከዚያም ባሻገር አብሮ መስራት፣ ዴሞክራሲ፣ እርቅ፣ እኩልነት፣ ልማት፣ የሰብአዊ መብቶች መከበር፣ የህግ የበላይነት... እነዚህ ሁሉ መልካም ነገሮች ናቸው። መልካም መሆናቸውን ያልተማረው ገበሬም አሳምሮ ያውቃቸዋል። ያልተመለሰው ዋና ጥያቄ "እነዚህን በጎ አሳቦች እንዴት ተግባራዊ እናድርግ?" የሚለው ነበር። በሃይል ወይስ በሰላማዊ መንገድ?

ይህ እንዳከራከረ ይገኛል...

ሌንጮ ለታ በ1984 ግድም ለኒውስዊክ መፅሄት ሲገልፅ "ከሰሜኑ ጋር ለመግባባት ያደረግነው ጥረት ከንቱ ድካም እንደሆነ ተረጋገጠ" ማለቱ አይዘነጋም።

ዛሬስ ምን ለውጥ አለ?

ጥቅምት 2000 የታተመ "አዲስ ራእይ" የተባለ የኢህአዴግ ልሳን መፅሄት አጊንቼ አንብቤው ነበር። መፅሄቱ ታደሰ ገብረወልድ የተባለ ሰው የፃፈውን መጣጥፍ ይዞ ነበር። ይህ ስም የመለስ ዜናዊ የብእር ስም መሆኑ ግልፅ ነው። ወደ መጣጥፉ ማብቂያ ግድም እንዲህ የሚል አንቀፅ አገኘሁበት፣

"....በምርጫ 97 ህዝቡ ከነቅሬታውና ብሶቱ ኢህአዴግን መምረጥ የወደፊት እድሉን ብሩህ እንደሚያደርግለት ተገንዝቦ ከውሳኖና ከውጭ የተደረገውን ሰፊ ዘመቻ ተቋቁሞ ኢህአዴግን መምረጥ ቻለ!"

ኢህአዴግ በዚህ መንገድ እየቀለደ ለመቀጠል መወሰኑን ግልፅ አድርጎአል። ስርአቱ በዚህ መንገድ እያላገጠ እንዲገዝ የፈቀደለት ህዝቡ ጭምር መሆኑን ማመንም የመጀመሪያው እርምጃ ይመስለኛል....

በ1983 ሃምሌ ወር ታይም መፅሄት ላይ ዩቭጊነይ አሌክሳንደር የተባለ ገጣሚ ያሰፈረው አሳብ በእጅጉ ማርኮኝ ስለነበር እስከዛሬም በማስታወሻ ደብተሬ ይገኛው ቆይቻለሁ። የሩሲያን የአገዛዝ ስርአትና የህዝብ አመለካከት መርምሮ የሰነዘራቸው አስተያየቶች ለኛ ወቅታዊ ሁኔታም የሚያገለግሉ ይመስላሉ።

"ህበረተሰቡ ዛሬ የሚፈልገው የወደፊቱን አርቀው

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የሚያስቡ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን፣ ነገሮችን አስቀድመው መተንበይ የሚችሉትን ጭምር ነው!" ይለናል።

እኛ ለዚህ አልታደልንም።

ገጣሚው ዩቭጊኒይ ለህገወጥ ስርአት መስፋፋትና ለፍትህ መጓደል ተጠያቂዎቹ የአገዛዙ ስርአት አቀንቃኞች ብቻ ሳይሆኑ፣ እነርሱ የፈለጉትን እንዲያደርጉ የፈቀደላቸው ህዝብ ጭምር መሆኑን አበክሮ ይገልፃል። ይህን በሃቀኛነት ማመን ከተቻለ ለችግሮች መፍትሄ ሊገኝ እንደሚችል ይጠቁማል። "በሃቀኛነት ማመን" የሚለው ቃል ሰፊ ሃሳብ ያዘለ ነው። ሉሳካ ሳለሁ አንድ ጥቁር ዛምቢያዊ፣ "ታሪካችሁ ለአፍሪካ ኩራት ነው" አለኝ። ሲያትል ላይ ደግሞ ሌላ ነጭ አሜሪካዊ፣ "ዘመዶችህ በረሃብ እየሞቱ አንተ እንዴት ወፈርክ?" ብሎ ጠየቀኝ። በጎ ገፅታህ ያብረቀርቅ ዘንድ የአስቀያሚ ገፅታህን የችግር ምንጭ ማወቅ ብቸኛው መፍትሄ ነው።

በሃቀኛነትና በበሰለ መንገድ መጪውን ዘመናችንን የጠቆመን ገና የለም። በመሆኑም በህዝቡ ላይ ወንጀል የመፈፀሙ ሂደት በከፋ ሁኔታ ቀጥሎአል። በተከታታይ ሃገሪቱን የመሩ የአገዛዝ ስርአታት ሁሉ የህዝቡ የሞቀ ተስፋ ላይ እሳት እየለኮሱ ስላከማተሩት ግንባር ቀደም ለውጥ ፈላጊዎች ታፍነው ሲጠፉ ህዝቡ በዝምታ የማየትን ልምድ አዳብሮአል። "ታግሰን ነው" እያልን ከሆነም ትእግስታችን ፍርሃት የወለደው ትእግስት ነው። በፍርሃት የውርደት ኩሬ ውስጥ እስከ አንገታችን በመስጠማችን የሚቀመስ እህል ሲያጥረን እንኳ መቆጣት አልቻልንም።

"እኔ አንድ ግለሰብ ነኝ! ምን ማድረግ እችላለሁ?" የሚል ንግግር መስማት የተለመደ ሆኖአል። ይህን ለመሰለው ፍርሃት የሚገኘው ምላሽ አጭርና ግልፅ ነው።

"ከፈራህ ፀጥ ብለህ ተገዛ!"

ከአመታት በፊት ባህሬን የተባለ ሃገር ላይ አንዲት ኢትዮጵያዊት ላይ የሞት ፍርድ ሲፈረድ አዲሳባ ላይ የህዝብ ቁጣ ተቀስቅሶ እንደነበር አስታውሳለሁ። ያቺ ሴት ሞት የተፈረደባት አሳዳሪዋን ገድላ ስታበቃ፣ ሬሳዋን በቢላ ቆራርጣ ፍሪጅ ውስጥ በመክተቷ ነበር። ያቺ ወገናችን ያን ድርጊት ለመፈፀም የበቃችው ከአሳዳሪዋ በደረሰባት በደል አእምሮዋን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በመሳትዋ ሊሆን እንደሚችል ማንም ይገምታልና "ቁጣችን" ተገቢ ነበር። የአገዛዝ ስርአታት በየእለቱ አፍንጫችን ስር በግንባር ቀደም ለውጥ ፈላጊ ግለሰቦች ላይ ግፍ ሲፈፅሙ በህብረት መቆጣት ያልቻልንበት ምክንያትስ ምን ይሆን?

በቅርቡ ደቡብ አፍሪቃ ላይ የህዝብ መጓጓጥ ባቡር እየዘገየ ስላስቸገራቸው የባቡሩ ደምበኞች በቁጣ ባቡሩን ሙሉ በሙሉ በማጋየት በሚሊዮናት የሚገመት ንብረት ሲያወድሙ በቦታው በመገኘት ወደር የሌለውን የህዝብ ቁጣ ለማየት በቅቻለሁ። በዚያ ቦታ ሆኜ የተረዳሁት አቢይ ቁምነገር ቢኖር እኛ ለመብታችን የዚያን እሩብ ያህል እንኳ እንደማንቆጣ ነበር።

የባእድ ወረራ ሲመጣ እንደ እሳተጎመራ የሚፈነዳ ቁጣችንን ለመብታችን ጭምር ልንጠቀምበት ያልቻልንበት ምስጢር ከቶ ምን ይሆን? የአገዛዝ ስርአታት እንደ ጋሪ ፈረስ ጀርባችንን እያሻሹ እንደልባቸው ሊጋልቡን ለምን ቻሉ? ይህ አባባሌ መቸም አልተጋነነም። ግልቢያው በተለያዩ መንገዶች እየተፈፀመ ይገኛል። ተቀናቃኝህ በቀደደልህ ጎዳና እስከጋለብክ ድረስ የጋሪ ፈረስ ሆነሃል። ወያኔ ተቃዋሚዎች ይከፋፈሉ ዘንድ የተሳካ ስራዎች ሲሰራ እያየን ነው።

ገጣሚው ዩቭጊነይ የወቅቱን ሩስያውያን እንደገለፃቸው ሁሉ እኛም በታሪካችን ወንጀሎችን የመፍቀድ ልማድ አዳብረናል። ፍርሃት የወለደው ታጋሽነታችንም ለብዙ ህገወጥ ድርጊቶች በር ከፍቶአል።

በሰላማዊው ትግል ተስፋ ያልቆረጡ ወገኖች ትግላቸውን ቀጥለዋል። የሰላማዊው ትግል ውጤት በተደጋጋሚ የህዝቡን የነፃነት ጥያቄ አኮላሽቶታል። የዚያኑ ያህል ነፋስና ፖለቲከኛ መድረሻው አይታወቅም እያለ "ምናገባኝ" ወደ ተባለው መንደር የሚኮበልለው ዜጋ ቁጥር ሲያሻቅብ ይታያል። አንድ የፖለቲካ ሰው እንደገለፀው፣ "ዜጋ በሃገሩ ጉዳይ 'ምናገባኝ' ማለት ሲጀምር ያቺ ሃገር አበቃላት ማለት ይሆናል"

ለማጠቃለል የኢትዮጵያ ህዝብ የማይቀርለትን ትግል ጫንቃው ላይ ተሸክሞአል። "ኢትዮጵያውያን አብረው መብላት እንጂ አብረው መስራት አይችሉም" የሚለው አባባል እውነት አይሆን ዘንድ እመኛለሁ.....

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

- 31 -
ጉዞ ወደ እውቀት

ደካማ መሆንን አትፍራ፣
ጠንካራ በመሆን አትኩራ፣
ማንም - ምንም - አለም ያሻውን ይበል፣
ራስህን ሁን መንገድህን ተከተል፤
እድልህን ተጠቀምበት - እንጂ አትልቀቀው፣
ወደ ገርነት መመለስን አትተው፤

(ግጥም – ENIGMA – 2 "Return to innocence")
- ከበደ ደበሌ ሮቢ እንደተረጎመው

ከዝቋላ ተራራ አናት ላይ የተገኘ ሰው አሻግሮ ወዲያ ማዶ ካማተረ ቢሾፍቱ ሃይቅን ቁልቁል ማየት ይቻለው ይሆናል። እነሆ እኔ የቢሾፍቱ ልጅ ስሆን፣ ግዙፉ ዝቋላ ተራራ ደግሞ አጎቴ ነው። እናቴ እንደነገረችኝ ከሆነ እኔ የተወለድኩት ቢሾፍቱ ሃይቅ አፋፉ ላይ ነው። ነሃሴ 28፤ 1960 ነበር እለቱ። በዚሁ ሰሞን ደግሞ ነቢዩ አበበና ዳንኤል ተሾመም ከቢሾፍቱ ሃይቅ ዳርቻ ተወልደዋል።

* * *

የአስራ ሶስት አመት ልጅ ሳለሁ አንድ ማለዳ ዳንኤል ተሾመ ከቤት ካስጠራኝ በሁዋላ ለጥብቅ ጉዳይ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

እንደሚፈልገኝ ነገረኝ። በጎርፍ መሄጃ ጉድጓድ ውስጥ ይዞኝ ከገባ በሁዋላም እንዲህ አለኝ፣

"አንድ ጥብቅ ምስጢር አማክርሃለሁ! ሆኖም ለማንም ላለመንገር ማልልኝ?"

"ኅርጊስን!"

"በገብርኤል ማል?"

"አላወራም! ወንፌት አይደለሁም" አልኩ በቅሬታ።

"ወንፌት ነህ ያለህ የለም! በገብርኤል ማልልኝ!"

"ገብርኤልን!"

ዳንኤል ታላቁን ምስጢር ነገረኝ። ከሰፈራችን ልጆች አንዱ የሆነው ነቢዩ አበበ ምንጊዜም ከክፍል አንደኛ የሚወጣበትን ምስጢር እንደደረሰበት ሲነግረኝ ሰውነቴ ሁሉ እንደ እሳት ጋለ።

"ግንኮ እነሱ ከቤተሰባቸው ነው። ወንድሞቹም አንደኛ ነው የሚወጡት" አልኩ በጥርጣሬ።

"ምስጢሩ ያለው እዚያ ላይ ነው" ሲል ዳንኤል ያብራራልኝ ጀመር "...አባታቸው ጋሽ አበበ ዝቋላ ላይ ነጋዴ ናቸው አይደለም? ቃሊቲ ገጠር አካባቢ የኛ ዘመድ የሆነ አንድ ገበሬ አለ። ምስጢሩን ከሱ ነው ያገኘነው። የጋሽ አበበ ዘመዶች በሙሉ ዋና የትውልድ ርስት ቃሊቲ አካባቢ ነው። እና ገበሬው እንደነገረን ዝቋላ ጫካ ውስጥ አንጎልን የሚከፍት አንድ ቀይ ዛፍ አለ ነው የሚባለው። የቀዩን ዛፍ ግንድ በሰንጢ ስትወጋው ወተት ይወጣዋል። ያንን ወተት በቻይና ስኒ ግጥም አድርገህ ከጠጣህ፣ በቃ! ማጥናት የለ...ምን የለ... አንደኛ ትወጣለህ!"

በደስታ ብዛት አንጎሌ ዞረ። ነቢዩ በሰፈራችን ውስጥ ይበልጥ የኔ ጓደኛ ሆኖ ሳለ ይህን ምስጢር ስለደበቀኝ ወዲያውኑ ታዘብኩት።

ዳንኤል ማብራራቱን በመቀጠል የቀዩ ዛፍ ፍሬ ከእየሩሳሌም የመጣ መሆኑን ነገረኝ። አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ እየሩሳሌም ተሳልመው በነፋስ ሰረገላ ወደ ዝቋላ ሲመለሱ በሺህዎች የሚቆጠሩ አእዋፍ ፃድቁ አቡዬን ተከትለው መጥተው ነበር። አንድዋ ወፍ ታዲያ ፍሬውን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

በመንቆሯ ይዛ መጥታ ኖሮ ዝቋላ ጫካ መሃል ወደቀባት። አያያዘና ዳንኤል እንዲህ አለኝ፣

"እና ቀዩን ዛፍ ፍለጋ ከኛ ጋር ትሄዳለህ?"

"ምን ጥያቄ አለው? እሄዳለሁ!"

"ከዚያ በፊት ግን ለምን ነቢዩን አትጠይቀውም? ላንተ የበለጠ ጓደኛህ ስለሆነ ምስጢሩን ማወቅህን ካወቀ ቀዩ ዛፍ ያለበትን ትክክለኛ ቦታ ሊነግርህ ይችላል"

* * *

በዚያው ሰሞን ኪስ ሜዳ ላይ ነቢዩን አገኘሁትና ይህንኑ ጉዳይ አነሳሁለት። ነቢዩ በጣም ስቆ ሲያበቃ፣ "ውሸት ነው" አለኝ። አያያዘናም ብዙ ስዎች ይህን የመሰለ ጥያቄ ጠይቀውት እንደሚያውቁ አጫወተኝ። የአባቱ የንግድ ስራ ወደሚገኝበት ዝቋላ በሚመላለስበት ጊዜ የበላውንና የጠጣውን ጭምር ዘርዝሮ ነገረኝ። እነሱም፣ እንጆራ በክክ ወጥ፣ በሽሮ ወጥ፣ አመት ባል ከሆነ ደግሞ በስጋ ወጥ፣ እርጎ፣ የገብስ ዳቦ፣ ጭኮ፣ ማር፣ መሆናቸውን ነገረኝ። የጠጣውንም ሲነግረኝ ውሃ፣ ወተት፣ ጠላ፣ አንድ ጊዜ ደግሞ ቢራ መቅመሱን ነገረኝ። ከዚህ ሌላ የቀመሰው አለመኖሩንም በቃጅማው ጊዮርጊስ ማለልኝ። ርግጠኛ ለመሆን በቁልቢው ገብርኤል አስማልኩት።

ከዚያም ይህንኑ ተመልሼ ለዳንኤል ነገርኩት።

"ደብቆሃል" አለኝ ዳንኤል በፍጥነት "...ምስጢሩን ከተናገራችሁ እውቀታችሁ ይከሽፋል ብለው ስለነገሯቸው ነው የደበቀህ። ለማንኛውም እኛ በሚቀጥለው ቅዳሜ ዝቋላ እንሄዳለን። ከኔ ጋር የሚሄዱ ስምንት የጨለቅላቃ ሰፈር ልጆች አሉ። አንተ አብረኸን የምትሄድ ከሆነ አስር እን ሆናለን!"

በተስፋና በደስታ ለጉዞ ዝግጁ መሆኔን አረጋገጥኩለት።

* * *

እለቱ ቅዳሜ ነበር፤ ወርሃ - ነሃሴ...በማለዳው ቢሾፍቱን ለቀን ወደ ዝቋላ አቅጣጫ ጉዞ ጀመርን። በመንገዳችን ላይ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ታዲያ ጌቱ አብዲሳና ደረጀ ሞላ ከቤቶቻቸው ፊት ለፊት ብይ ሲጫወቱ አገኘናቸው። ሁለቱም ጓደኞቼም ጎረቤቶቼም ነበሩ። ከደረጀ ጋር ግን ተኮራርፈን ነበር። ጌቱ ጠርቶ ካስቆመኝ በሁዋላ ብይ መጫወቱን በመተው ወደኔ እየሮጠ መጣ፣

"ወዴት እየሄዳችሁ ነው?"

"ምስጢር ነው" አልኩት በዝቅተኛ ድምፅ።

"ከኔ ትደብቃለህ እንዴ?"

ጌቱ ጓደኛዬ ስለሆነ ልነግረው ፈለግሁ። ግን ደግሞ አመነታሁ። ጌቱ ከክፍላችን አራተኛ በመውጣቱ አንደኛ ለመውጣት ብሎ ዝቋላ ድረስ መጓዝ ላይፈልግ ይችላል ብዬ አመነታሁ። እንድነግረው ሲወተውተኝ ግን አላስችል ብሎኝ ነገርኩት።

"ነቢዩ አንደኛ የሚወጣበት ምስጢር ተደርሶበታል! ዝቋላ ላይ ወተት የሚወጣው አንድ ቀይ ዛፍ አለ። እኛ እሱን ልንጠጣ እየሄድን ነው። ጠጥተን ከተመለስን በሁዋላ ግን ሌላ ቀን ላንተ..."

"አልፈልግም" ሲል አቋረጠኝ "...ነቢዩ አበበ ዝቋላ ላይ የቅጠል ጭማቂ ጠጥቶአል የሚባለውን አባቴን ጠይቄው ውሸት ነው ብሎኛል"

በጣም ተናደድኩ!

ሚስጥሩን በመናገሬም ተፀፀትኩ። ወዲያውኑም በገብርኤል መማሌን በማስታወስ ፍርሃት አደረብኝ።

"ካልፈለግህ ተወው! ብይህን ተጫወት!" ብዬው እነ ዳንኤል ላይ ለመድረስ ሩጫዬን ቀጠልኩ።

ጉዞአችንን በተስፋ ቀጠልን።

ጌቱ የነገረኝ ግን ከነከነኝ። አባቱ አስተማሪ ስለሆኑ ጌቱ የነገረኝ እውነት ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ። እናም ይህንኑ አሳቤን ለቡድኑ አባላት አቀረብኩ።

"ይህ የተባለው ግን ውሸት ሊሆን ይችላል!"

ዳንኤል ፈጣን ርምጃውን አቋረጠና ቆመ። በቁመት ከሁላችንም የሚገዝፍ ሲሆን፤ በድብድብም ቢሆን ማንም የሚችለው አልነበረም። የሰፈራችን ጉልቤ ነው። የቀዩ ዛፍ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ታሪክ ውሸት ሊሆን እንደሚችል መናገሬ ታዲያ ክፉኛ አስ ቆጣው።

"ከኛ ጋር መሄድ አትፈልግም?" ሲል አፈጠጠብኝ።

"እፈልጋለሁ"

"መሄድ ከፈለግህ ወሬ አታብዛ"

ስምንቱ የጨለቅላቃ ልጆች ዳንኤል ሲስቅ የሚስቁ፣ ሲቆጣ የሚቆጡ ነበሩና ተንጫጨብኝ። ሊደበድቡኝ የፈለጉም ነበሩ። ዳንኤል ግን ይቅርታ ስላደረገልኝ፣ እኔም ወሬ ላለማብዛት ተስማምቼ እንደገና ጉዞአችን ቀጠለ።

ከአራት ሰአት ፈጣን የሩጫና የርምጃ ጉዞ በሁዋላ ዝቋላ ተራራ አናት ላይ ለመገኘት በቃን። በእድሜ ከገፉ መነኮሳት በቀር የአቦ ቤተክርስትያን ፀጥ ብሎ ጠበቀን። ዝቋላ ተራራ ጫፍ ላይ ለመገኘት ለሁላችንም የመጀመሪያችን ስለነበር ግራ ተጋብተናል። "የአቦ ጢም" የሚል ቅፅል ስም ያላቸው የሸበቱ ዛፎች ደጀ ሰላሙን ከበውታል። ዝቋላ ተራራ ላይ ሃይቅ አለ። ቆሪጥ ተብሎ የሚጠራው ሰይጣን ጥንት በሃይቁ ውስጥ ይኖር እንደነበር የሚነገረውን አፈታሪክ ከልጅነታችን የምናውቀው ነው። ፃድቁ አቦ ዝቋላ ቤተክርስትያንን ያቆሙ ዘንድ በህልም ተገልጠላቸው በመጡ ጊዜ ሰይጣኑን እግሩን ቆርጠው ከዝቋላ አባረው ቢሾፍቱ ሃይቅ እንደከተቱት እየሰማን አድገናል። ዙሪያው በገደላማ ደኖች የተሞላውን ቤተመቅደስ ለመጎብኘት በየአመቱ ቱሪስቶች ወደ ዝቃላ ይጎርፋሉ።

ግብፃዊ መሆናቸው የሚነገርላቸው ፃድቁ አቡዬ የተወለዱት መጋቢት አምስት መሆኑ ይነገራል። እለቱም አርብ ነበር ይባላል። አመተምህረቱ ግን አይታወቅም። ስብሃት ገብረእግዜብሄር እንደሚተርከው ደግሞ የአቦ እናት የጡቷን ጫፍ ወደ ህፃኑ አፍ ባስጠጋች ጊዜ አቡዬ በዚያችው ደቂቃ አንደበታቸው ተከፍቶ፣ "ዛሬ አርብ ነው። በያም ወተት አልጠጣም" ብለዋል። አቡዬ ከተወለዱባት እለት ጀምሮም እህል አልቀመሱም። በፀሎት ላይ ሳሉ ቁራ አይኖቻቸውን ሲጠቀጥቃቸው፣ "ፀሎቴን ከማቋርጥ አይኔ ይፍሰስ" ብለው አይናቸው እንደታወረ፣ እግዚአብሄር ግን ባስቸኳይ ገብርኤልን ልኮ አይኖቻቸውን እንዳበሰላቸውና አይኖቻቸው ተመልሰው ሊበሩ እንደቻሉም እናቴ ደጋግማ ነግራኛለች።

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የአቡዬ አሟሟትም እንዲሁ የተለየና አስገራሚ ነበር። እርጅና ተጫጭኖአቸው ቡታጅራ ከሚገኘው ማረፊያቸው አልጋቸው ላይ ጋደም ባሉበት መልአከ ሞት ይመጣና፣

"አምጣቸው ተብዬ ነውና እንሂድ" ይላቸዋል።

አቡዬ ተቆጡ!

"ተሳስተህ ይሆናል! እኔ ሃጢአት ስላልሰራሁ አልሞትም" ይሉታል።

መልአከ ሞት አለመሳሳቱን ለማሳመን መዝገቡን ገልጦ ቢያሳያቸውም፤ ሊቀበሉ ስላልቻሉ መልአከ ሞት "ከአቅሜ በላይ ነው፤ እምቢ አሉኝ!" ሲል ተመልሶ ለበላይ አምላክ ያመለክታል። እግዚአብሄርም ምንም እንኳ አቡዬ ገና ሲወለዱ ጀምሮ ፃድቅ መሆናቸውን ቢያውቅም፤ እነ ማቱሳላና አብርሃም እነ ኤልያስና ኢሳይያስ እንኳ ሞተው አቡዬ ሊቀሩ ስለማይችሉ እየሱስን ይጠራውና ያዘዋል፣

"አቡዬ አልሞትም እያሉ ስለሆነ፣ ቢቻል በማግባባት፣ ባይቻል ዘዴ ፍጠርና አምጣቸው!"

እየሱስም የአባቱን ትእዛዝ ተቀብሎ ብቻውን እንዳይሆን ገብርኤልን አስከትሎ ቡታጅራ ይመጣል። እናም ሊያግባባቸው ሞከረ።

አቡዬ ግን ወይ ፍንክች!

"ሃጢያት ሰርቼ ስለማላውቅ 'ሞቼ እገኛለሁ እንጂ አልሞትም" ብለው አስቸገሩ።

እየሱስ በማግባባት እንዳልሆነለት ሲያውቅ ዘዴ ፈጠረ። ሰይጣንን በጎን ጠራውና፣

"አቡዬ ላይ የሆነ ሃጢአት ፈልግልኝ" ይለዋል።

ሰይጣን ለዚህ ማን ብሎት? እንኳን ታዝዞ ሳይታዘዝም ሲሰራው የሚውለው ነውና በነፋስ ፍጥነት ከሲኦል አንዲት ዝንብ በወርቅ ሳህን ላይ አስቀምጦ ከተፍ አለ።

"ምስክር! ተናገሪ" ተባለች ዝንቧ።

"አቦ ዝቋላ ሳሉ አንድ ቀን ጭራቸውን ሲያወዛውዙ እኔ በአካባቢው በመዝናናት ላይ ሳለሁ መትተው ገደሉኝ!"

አቦ ደነገጡ!!

ሃጢያት መስራታቸውንም ተቀበሉ። እያዘኑም

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

መሞትን ፈቀዱ። ሆኖም በመልአከ ሞት እጅ አልሄድም ብለው ከእየሱስ ጋር በነፋስ ሰረገላ ላይ ተቀምጠው መንግስተ ሰማያት ገቡ። እንደሚነገረው ከሆነ በዝንቧ አነጋገር ገብርኤል ከት ብሎ ስቆአል። በጣም ያሳቀውም ራሷን ከፍ ለማድረግ "በመዝናናት ላይ ሳለሁ" የሚል ውሸት በመጨመሯ ነበር። ዝንብ በአደጋ ካልሞተች ሰባቱንም የህይወት ዘመን ቀኖችዋን የምታሳልፈው ምግብ ፍለጋ በየቆሻው በመልከስከስ መሆኑን አለም ያውቅላታል።

ይህ ሁሉ ቅዱስ የዝቋላና የቢሾፍቱ ወግ ነው። እኛ ግን እዚህ የተገኘነው ይህን ትረካ ለመስማት ሳይሆን ቀዩን ዛፍ ፍለጋ ነው።

የእውቀት ዛፍ!

ጥቂት እረፍት ካደረግን በሁዋላ ለረጅም ጊዜ በዝቋላ መመንኮሳቸው ወደሚነገርላቸው ቁስ ሄደን የመጣንበትን ምክንያት ገለፅን። ዳንኤል ነበር ተናጋሪው፣

"አባታችን! ወተት የሚያመነጭ ቀይ ዛፍ እዚህ ዝቋላ ጫካ ውስጥ መኖሩን ሰምተን ነው የመጣነውና እባክዎ በየት በኩል እንደሚገኝ ይግለፁልን?"

መነኩሴው በመደነቅ ያጤኑን ጀመር። የሸበቱ ቅንድቦቻቸውንም ከፍ ዝቅ አደረጓቸው። አንድባንድም ባይኖቻቸው መረመሩን።

"ከቀዩ ዛፍ ምን ፈልጋችሁ መጣችሁ?"

"እውቀት!" ስንል መለስን "አንጎላችን እንዲከፈት!"

መነኩሴው በትካዜና በፀጥታ ጥቂት ከቆዩ በሁዋላ፣

"ከእናንተ በፊትም ብዙ ሰዎች ቀዩን ዛፍ ፍለጋ ወደዚህ መጥተዋል! ቀዩን ዛፍ ባይናችሁ ለማየት ችግር የለውም ልጆቹ! በርቀት ልታዩት ትችላላችሁ፤ ወደ ዛፉ መጠጋት ግን ችግር አለው! በጫካው ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸው መርዛማ እባቦችና ዘንዶዎች አሉ። ጫካው ደግሞ እንደምታዩት ጥቅጥቅ ያለና ገደላማ ነው። ሰው ቀርቶ ድመት አያሳልፍም። ዘንዶዎቹ አቦ እዚህ በነበሩ ጊዜ የርሳቸው ጠባቂዎች የነበሩ ናቸው። አሁን በቀዩ ዛፍ አካባቢ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የሰፈሩ በመሆናቸው ወደዚያ መጠጋት አስቸጋሪ ነው"

ፊጠን አልኩና ጠየቅሁ፣
"አባታችን! ከቀዩ ዛፍ ግንድ የሚወጣው ውተት አንጎል ይከፍታል የሚባለው እውነት ነው?"

መነኩሴው ፈገግ አሉ፣
ዘግየት ብለውም ምላሽ ሰጡ።
"ሲባል እንሰማለን! እዚህ ገዳም አርባ አመት ሆነኝ፤ ብዙዎችም ስለዚሁ ጉዳይ ይጠይቁኛል። እስካሁን ግን ወደ ቀዩ ዛፍ መጠጋት የቻለ ሰው ስለመኖሩ አልሰማሁም"
"እዚህ ዝቋላ ነጋዴ የሆኑት የጋሽ አበበ ልጆች ግን የቀዩን ዛፍ ወተት ጠጥተዋል ነው የሚባለው"
"ይህንን ወሬ አልሰማሁም ልጆቼ"
"ቀዩ ዛፍ የት እንዳለ ለማየት እንችላለን?"

መነኩሴው አቅጣጫውን አመላከቱን።
መነኩሴውን ተሰናብተን ወደ ተጠቆምነው አቅጣጫ ተጣደፍን። ከሃይቁ ባሻገር ጉብታው ላይ ደርሰን ወደ ቀኝ ስንመለከት በገደላማና ጥቅጥቅ ባለ ጫካ መሃል በቀይ ቅጠሎች ያሸበረቀ አፍሮ ቀይ ግዙፍ ዛፍ ለማየት ቻልን። ሁላችንም በጩኸት አበድን! ዳንኤል ራሱን መቆጣጠር አልቻለም!
"...ቀዩ ዛፍ! ቀዩ ዛፍ! ቀዩ ዛፍ!..."
መጨጨህ ብቻ ሆንን!
"አላልኳችሁም! ቀዩ ዛፍ ማለት ያውላችሁ!!!"

ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ግን ወደ ቀዩ ዛፍ መጠጋት አደገኛ መሆኑን አስታወስን! ገደል ነው! ጥቅጥቅ ያለ በቆንጥርና በልዩልዩ ዛፎች የተሞላ ደን። መርዛማ እባቦች! ዘንዶዎች! እባቦችና ዘንዶዎች!!

ዳንኤል ትረካውን አራዘመ፣
"አንድ ያልነገርኳችሁ ነገር አለ። እዚህ ከመምጣታችን በፊት ስለ እባቦቹና ዘንዶዎቹ ሰምቼ ነበር። የቃሊቲው ገበሬ ነግሮናል። ጋሽ አበበ ግን ወደ ቀዩ ዛፍ የሚጠጉበት የራሳቸው ዘዴ አላቸው። መጀመሪያ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ከአይኖቻቸው በቀር ሙሉ ሰውነታቸውን በጨርቅ ይጠቀልላሉ። ከዚያም ትልቅ መቀስ በግራ እጃቸው፣ ሰንጢ በቀኝ እጃቸው ይዘው በጫካው ውስጥ በደረታቸው እየተሳቡ ወደ ቀዩ ዛፍ ይጠጋሉ። ዘንዶ ሲመጣባቸው ታዲያ አይንቀሳቀሱም፤ ዝም ይሉታል። ዘንዶው አፉን ከፍቶ ሊውጣቸው ሰጀምር እሳቸው ቀስ ብለው መቀሳቸውን አስቀድመው ወደ አፉ ያስገባሉ። ዘንዶው እየዋጣቸው ሲሄድ እሳቸው በመቀሳቸው እየተረተሩት እንደ አንሶላ ይዘረጉታል። እንዲህ እያሉ ቀዩ ዛፍ ጋር ይደርሳሉ። ጋሽ አበበ አንድ ስኒ ወተት ይዘው ለመመለስ በትንሹ ሶስት ዘንዶ ይገድላሉ። ገበሬው እንደነገረን ከሆነ ይህን ጀብድ አምስት ጊዜ ያህል ፈፅመውታል!"

ፈዝዘን ቀዩን ዛፍ በርቀት ማየት ብቻ ሆነን ቀረን። እኛ በቆምንበት ኮረብታና በቀዩ ዛፍ መካከል በአየር ላይ ግምት አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት አለ። በዚህ መሃል ያለው ጫካና ገደል ተስፋ ያስቆርጣል። የዘንዶና የመርዘኛ እባቡን ትረካ ከሰማን በሁዋላም ተስፋችንና ወኔያችን ሞቶ ነበር።

ዳንኤል ግን ያፅናናን ያዘ፣

"ዛሬ ቀዩ ዛፍ ላይ መድረስ ባንችል ቢያንስ በአይናችን አይተነዋል! ይህንን ምስጢር ለማንም እን ዳትናገሩ! ወሬው ከተሰማ በሳን ሊቀድሙን ይችላሉ! ሌላ ቀን እንደ ጋሽ አበበ ሰውነታችንን በጨርቅ ጠቅልለን፤ በቀኝ እጃችን መቀስ፣ በግራ እጃችን ሰንጢ ይዘን እንመለሳለን! እመኑኝ!"

የመልስ ጉዞ ጀመርን።

መነኩሴውን ስንሰናበታቸው ታዲያ፣ እንዲህ ሲሉ ጠየቁን፣

"ቀዩን ዛፍ አያችሁት?"

"አይተነዋል አባታችን!"

"የሆነው ሆኖ የሚባለው እውነት ከሆነ የቀዩ ዛፍ ወተት አንጎልን የሚከፍተው ከክርስትና በፊት ለሚጠጡት ህፃናት እንጂ ለሌላው አይሰራም"

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የራሱን ተስፋና ሞራል ጠብቆ እኛንም ሲያፅናና የነበረው ዳንኤል ባለበት ደንዝዞ ቀረ። በቆንጨራ እንደተመታ አገዳ መቆም እንኳ ሲያቅተው አስተዋልኩ። መነኩሴው የተሸፋፈኑበትን ቡልኮ እየጎተቱ እንዲህ ሲሉ የማፅናኛ ቃል አከሉልን፣

"ለናንተ ጊዜው ያለፈበት ቢሆንም፤ ትዳር ይዛችሁ ልጆች ስትወልዱ ግን ተመልሳችሁ ልትመጡ ትችላላችሁ። እንዳልኳችሁ ግን የተረጋገጠ ነገር አይደለም"

አንዳችም ቃላት ሳንለዋወጥ ማምሻው ላይ ቢሾፍቱ ደረስን። ከዚያ ወዲህም ስለዚሁ ጉዳይ አንስተን የማናውቅ ሲሆን፤ የቀረን ብቸኛ ተስፋ መፅሃፍ ገልጦ ማንበብ ብቻ ሆኖ ቀረ....

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ድህረ ታሪክ (Epilogue)

በዚህ ባዲሱ ዘመን - የኛ ጌታ አላህ፣
ቁሩ እንዳይናከስ - ያዝልን እባክህ፣
ከበረዶው በታች - ተደብቆ ያለው ሳር፣
ዝናቡ እስኪዋል - እንዳይነካው አሳር፣
ታቀፊና አሙቂው - ደጊቱ እናት ምድር፣
ተገን ሁነሽ አድኝው - ከቁር ከውሽንፍር፣
ሸፍነሽ አቆይው - እንደ ጨቅላ ህፃን፣
ሆነሽ መሸሸጊያው - እንደ እናት ማህፀን፣

(ግጥም - ፋዙ አሊየቫ)
ታየ አባይሬ እንደተረጎመው

እነሆ! ዛሬ ስደት ላይ ነኝ!

እንደ አብዛኛው አበሻ ስደተኛ የማልፈልገውን ስራ እየሰራሁ ለኑሮ እየዳከርኩ ነው። ተስፋ ማጣትና ተስፋ ማግኘትም ተፈራርቀውብኛል። በዚህች አለም ላይ ፍፁም የሆነ ማጣት አሊያ ፍፁም የሆነ ማግኘት ከቶ አለመኖሩንም ከስደት ልምድ አረጋግጬያለሁ። የዛሬው ማጣት ለነገው ማግኘት በር ከፋች የመሆኑን ያህል፣ አገኘሁ ያልከው ማግኘት፣ ወደ ማጣት

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

አዘቅት ይዞህ ሊነጉድም ይችላል። ማጣትና ማግኘት እንደ ህይወትና ሞት አብረው ይጓዛሉ...

ሁሉን ማየት መልካም ነው።

ከፍና ዝቅ ማለትም በጎ ነው። ከፍና ዝቅ ከማለት ህይወት አያሌ ልምድ ትቀስማለች። ሰለሞን እንደፃፈው በርግጥም ፍፁም አዲስ ነገር የለም ከፀሃይ በታች።

ለመሆኑ እኔ ማነኝ!?
ወዴት እየተጓዝኩ ነው?
ዛሬ ለነዚህ ጥያቄዎች በቂና ግልፅ ምላሽ አለኝ።

'ሞት ሃገር የለውም' ይባላል። ሞት አስፈሪ የሚሆነውም አሳፋሪ ሲሆን ብቻ ነው። ቀደም ሲል ሞት ደጋግሞ ስቶኛል። እንኳን የሳተኝ። ያኔ ባላመንኩበት አጀንዳ ሞቼ ቢሆን ኖሮ ይቆጨኝ ነበር። ዛሬ ግን በርግጥ ምን እንደምፈልግ ማወቅ ችያለሁ። ይህን መፅሃፍ ለመውለድ የበቃሁትም ትክክለኛውና የማምንበት የጉዞ ሃዲድ ላይ መሳፈር በመቻሌ ነው። ይህ የጉዞ መስመር ወደ ማንነት መመለስ ይባላል።

እኔ የአድአ ጥቁር አፈር ነኝ። ነፋሻማውና አረንጓዴው ባቦጋያ ሃይቅ፣ ከአመት አመት በኦሮሚኛ የሚዘምረው በልበላ ወንዝ፣ በልጅነት የዘለልንባቸው ተራሮች እነ ጥቁር ተራራ፣ የነጋበትን ጅብ ያሳደድንበት አሞራ ገደል እነዚህ የኔው ናቸው። ሆራ አርሰዲ ላይ የእሬቻው በአል፣ አይኖቼ ሲከፈቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከትኩት የቢሾፍቱ ሃይቅ፣ ደምና አጥንት ሆነው እኔን ገንብተውኛል። ቢሾፍቱ ከተወለዱት የልጅነት ጓደኞቼ ጋር ፖለቲካ አለያይቶን አያውቅም። ምንጊዜም ስንገናኝ እንደ ልጅነታችን እናወጋለን። መለያየትም አይቻልም። ሰው በምግብ ብቻ አይገነባም። አካባቢው ደምና አጥንት ሆኖ ይገነባዋል። ይህን ሁሉ ገፆች የፃፍኩበት ቋንቋ የኔ አይደለምን? ይህን ቋንቋ ከኔ በላይ ማን ይራቀቅበታል? ያለ አማርኛ ቋንቋ እኔ ህይወት የለኝም። ስፈጠር ጀምሮ እኔ እነዚህን ነኝ። እነዚህን ሁሉ እንዳልሆን እኔን የማገድ ስልጣን ያለው ከቶ ማነው?

ማንነትን መከልከል አመፅን ይወልዳል። የሃያ አመት ልጅ ሳለሁ ሙሉጌታ ሉሌ የተባለ የዘመነ ደርግ ባለስልጣን

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ጋዜጠኛ እንዳልሆን ሲከለክለኝ ትልቅ ነገር ያጣሁ መስሎኝ ለአመፅ ተነሳሳሁ። በአርባ አመቴ ወያኔ ማንነቴን ሊነጥቀኝ ፈለገ። ወዴት እንደምጓዝ አሁን በትክክል አውቃለሁ። እንዴት እንደምታገልም እገነዘባለሁ። መብትን ለማስከበር በግልና በድርጅት መልክ የሚደረጉ ትግሎች ሳይሳኩ ሊቀሩ አይችሉም። ያሬድ ጥበቡ፣ "መወድሰ አነግ" በሚል መጣጥፉ እንዳሰፈረው...

...ፈረንጆች የዛሬው ፍፁም ፀጥታ ከማእበሉ መነሳት በፊት ያለውን ሰላም ይመስላል እንደሚሉት፣ እኛም በተቃራኒው የዛሬው ፍጅትና ዋይታ የነገውን ጥልቅ ሰላም የሚያዋልድ የሞት ጩኸት አድርገን እንውሰደው። በኦነግ መገለልና የዳር ታዛቢነት የተከፋነው፣ ለምን የተለየ ሃሳብ ኖረው ብለን አይደለም። ለብዙዎቻችን ጉራጌነት ወይም አማራነታችን፣ የትጋ አቁሞ፣ ኦሮሞነታችን የትጋ እንደሚጀምር ለመለየት እንኳ የማንችልበት ውስብስብ ውስጥ ነው የኖርነው። ባለቅኔው ሰለሞን ዴሬሳ እንደጠየቀን፣ 'በኢያቶቻችን በር ስንት ሰራዊት ማለፉን እናውቃለን?' ነው ነገሩ? የኦሮሞው መለከት ድምፅ እየቀረበ ሲመጣ፣ በአማራ ዋሽንት፣ በትግሬ ክበሮ፣ በጉራጌ ዳንኪራ፣ በደቡብ እምቢልታ ታጅቦ የሚወጣው ህብረ ድምፅ፣ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አእምሮ ሳይሆን ከውስጠ ህሊናው የሚንቆረቆር፣ ታላቅ ሲምፎኒ እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም...

በቀጣዩ ዘመን ለራሴው ህልውና ስል እታገላለሁ። የተነጠቅሁዋቸውን መብቶቼን ለማስመለስ ከመፍጨርጨር ባሻገር ከቶ ምንስ አማራጭ አለኝ? አንድ ግለሰብ ተደራጅቶ ብቻ ሳይሆን በግሉም ለሚጠበቀውና ለምንመኘው ዘመን አስተዋፆ ሊያደርግ ይችላል። በመሆኑም ይህ ጥራዝ ትግል ነው። በመጨረሻ እንደ ግለሰብ ለግሌ የምመኛቸው ጥቂት ነገሮች አይጠፉም።

...አምን!

ከእለታት አንድ ቀን ባህላቸውንና ወተታቸውን እየመገቡ ወዳሳደጉኝ ወደ የረርና ከረዩ ገበሬዎች እንደምመለስ መንፈሴ ዘወትር ሹክ ይለኛል። ወደ ሃገሬ ተመልሼ፣ በቢሾፍቱ ሃይቅ ዳርቻ ወይም በዝቋላ ተራራማዎቹ ቀበሌዎች አካባቢ

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የራሴን ጎጆ እቀልሳለሁ። በጎችና ዶሮዎችን አረባለሁ። የምወዳቸውን ዛፎችም በግቢዬ ውስጥ እተክላለሁ። መፃህፍትንም በብዛት እፅፋለሁ...

ምን ጥያቄ አለው!?

እኔ'ንደሁ ትናንት ቢሾፍቱ ነበርኩ። ነገም ቢሆን ቢሾፍቱ ነኝ! ከነገ ወዲያ ማናችንም ብንሆን በህይወት አንኖርም። በታሪክ በበጎ የመታወስ መብት ያለውም ከቶ የለም.....

pdfMachine
Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!